የእውቀት መንገድ

“More read More see!” (Readers)

“
የእውቀት መንገድ ልታገኙት የምትችሉት በማዳመጥና በማንበብ ብቻ ነው!”

አንተነህ ጌታቸው ወልዴ (ሳይንስኛ & electrospaceX)

2017/2025

ምዕራፍ አንድ

የስኬት መርሆዎች

1. **ፍላጎት (Desire)**

የመጀመሪያው ደረጃ ፍላጎት ነው። ከልብ የመነጨ ፍላጎት፤ ፍላጎታችንን እንደ ዘር ልናየው እንችላለን። ፍሬ እንደሚያፈራ አምነን የምንዘራው ዘር። ዛሬ ዘርተነው ዛሬውኑ ፍሬ የሚሰጠን ተክል የለም። ፍላጎታችንም ልክ እንደ በቆሎ ወይም ማንኛውም ዘር ዛሬ ተዘርቶ በቂ ውሃ፤ በቂ ጸሃይ፤ በቂ እንክብካቤ፤ ካገኘ በኋላ በግዜው የሚያሸት ነው። የምንፈልገውን ነገር ጥርት ባለ መልኩ ማወቁ ይጠቅመናል። ለመረጥነው ነገር ምን ያህል ፍላጎት እንዳለን ለማወቅ የምናደርጋቸውን ነገሮች መቃኘት ያስፈልገናል። ከምንም በላይ በውስጣችን ያለው የትዕግስት መጠን ፍላጎታችን ምን ያህል እንደሆነ ያስረዳናል።

ለምሳሌ፣ ሰዓሊነት ፍላጎቱ የሆነ ሰው ባይከፈለው እንኳን ስዕል መሳሉን አያቆምም። አላማ ብለን ለመረጥነው ነገር በቀላሉ ሊገደብ የማይችል ፍላጎት ሊኖረን ይገባል። ጥልቅ ፍላጎት ማለት ወደ ኋላ እንዳናፈገፍግ የመመለሻውን ድልድይ እንደማቃጠል ያህል ነው።

2. **እምነት (Faith)**

እምነት አላማችን የሚገነባበት መሰረት ነው። የምንፈልገው ነገር ምንም ይሁን ምን እምነት ከሌለን ነዳጅ የሌለው መኪናን ለመንዳት እንደመሞከር ይሆንብናል። የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት እምነት እጅግ ወሳኝ ነገር መሆኑን መዘንጋት የለብንም።

ማርቲን ሉተር ኪንግ ስለ እምነት ደስ የሚል አባባል አለው" እምነት ማለት ሙሉውን ደረጃ እስከየት እንደሚደርሰን ባናውቅም እንኳን የመጀመሪያውን ደረጃ መውጣት ነው" ይላል።

3. **እራስን ማሳመን (Auto Suggestion)**

አይምሮዋችን እውነት ብሎ የሚቀበለው ነገር ደግመን ደጋግመን የምንመግበውን ነው። እዚህ ላይ ይህንን በደንብ የሚያስረዳ አንድ ታሪክ ትዝ አለኝ። ታሪኩ እንዲህ ነው:- "ሁለት ውሾች የነበሩት አንድ ሰው ነበር። አዘውትሮ እኒህን ውሾች አደባባይ እየወሰደ እንዲደባደቡ ያደርግ ነበር። ታዲያ ተመልካቾቹ የትኛው ውሻ በእለቱ እንደሚያሸንፍ ሲጠይቁት "በደንብ የምመግበው ውሻ ነው" ሲል መለሰላቸው።" ሁላችንም ውስጥ ሁለት ዉሾች አሉ:-

- የመልካም እና የክፋት፤
- የልማት እና የጥፋት፤
- የእውቀት እና የድንቁርና፤
- የውድቀት እና የድል ውሾች።

➢ የበላይ ሆኖ የሚመራን ውሻ ዘወትር የምንመግበው ነው። ለራስ መልካም ነገሮችን ደጋግሞ በመንገር አይምሮዋችንን ወደፈለግነው መንገድ መምራት የምንችለው።

4. **በአንድ ነገር ላይ እራስን የተካኑ ማድረግ (Specialize Knowledge)**

ልንሰማራበት በመረጥነው ወይም ፍላጎት ባለን ሙያ ላይ የተሰማሩ ሰዎችን መተዋወቁ እና ቅርርብ መፍጠሩ ወሳኝ ነገር ነው።

1. ጊዜያችንን የምናሳልፈው ከነማን ጋር ነው?
2. የምናውቃቸው ሰዎች ወይም ጓደኞቻችን ለምንፈልገው ሙያ የሚያግዙን ናቸው?

ለምሳሌ፣ ፕሮፌሰር ለመሆን ፍላጎት ያለው ሰው በተቻለው መጠን ዩንቨርሲቲ አካባቢ ካሉ ሰዎች ጋር ግንኙነቱን ቢያዳብር ይጠቅመዋል። ተዋናይ መሆን የሚመኝ ሰው እራሱን ከቲያትር መድረክ አካባቢ ማራቅ የለበትም። ሁላችንም የምንማረው ቀድመውን ካወቁት ነውና፤ የምንፈልገውን ነገር በቅጡ የሚያውቁ ሰዎችን ማወቁ ይጠቅመናል።

5. ነገሮችን በህሊናችን መሳል (Imagination)

ሁሉም ነገር ሃሳብ ነበር። ምንም ነገር እውን ሆኖ ከማየታችን በፊት በአንድ ሰው አይምሮ ውስጥ የተጠነሰሰ ሃሳብ ነበር። የምንፈልገውን ነገር እውን ሆኖ ከማየታችን በፊት በህሊናችን መሳል ትልቁ የስኬት ሚስጥር እንደሆነ ብዙዎች የተስማሙበት ነው። አላማችን ቁልጭ ብሉ በህሊናችን ከታይን ለጉዞዋችን ትልቅ ጉልበት አገኘን ማለት ነው። ምክንያቱም የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ እንደሚሳካ አይምሮዋችን እየነገረን ነው።

6. እቅድ ማውጣት (Organized planning)

እቅድ ማውጣት ጊዜን በአግባቡ እንድንጠቀም ከማድረጉም በላይ፤ በአንድ ጊዜ አንድ ደረጃ እየወጣን ጉዞዋችን አድካሚ እንዳይሆን ያደርግልናል። እቅድ ስናውጣ ነገሮች ሳይደራረቡብን ቀስ በቀስ ወደ ግባችን እንደርሳለን። እቅድ ስናወጣ ግን እራሳችንን በሚያጨናንቅ እና ካልፈጸምነው የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማን በሚያደርግ ሁኔታ ሳይሆን፤ ከጊዜያችን፤ ከባህሪያችን እንዲሁም ከማንነታችን ጋር የሚስማማ እቅድ ነው ማውጣት አለብን። ምክንያቱም ሌላው ያቀደበት መንገድ ለኛ ላይስማማ እና ከግባችን ላያደርሰን ስለሚችል።

7. ውሳኔ (Decision)

“Lack of decision is the top reason for failing.” የሰው ልጅ ውድቀት አንደኛው መንስዔ የውሳኔ ማጣት ነው። አንድ ሰው ምንም ያህል እምቅ እውቀት ቢኖረው፤ ምንም ይህል የሚያስደንቅ ሃሳቦችን ማመንጨት ቢችልም ውሳኔ መወሰን ካልቻለ ግን አቅሙ ሁሉ ከውስጡ አይወጣም። ውሳኔ በማጣት የተነሳ ብዙ ሙዚቃዎች ሳይሰሙ፤ ብዙ መጽሐፎች ሳይጻፉ፤ ብዙ ግኝቶች ሳይገኙ፤ ወደ መቃብር ይወርዳሉ። በሁላችንም ውስጥ ለኛ ብቻ የተሰጠ ስጦታ አለ፤ ይህን ስጦታ ግን አውጠን ሌሎች እንዲያዩት ማድረግ የምንችለው ውሳኔ መወሰን ስንችል ብቻ ነው። የምንወስነው ምንድን ነው ካላችሁ፤ መልሱ የምንወስነው መሆን የምንፈልገውን ነው።

8. ጽናት (Persistence)

ውሳኔ ብቻውን አቅም የለውም። ውሳኔያችን ባህሩን አቋርጦ ከአላማችን ዳርቻ እንዲደርስ የሚያደርገው ሃይል ጽናት ነው። ብዙዎቹ ችን የተለያዩ ውሳኔዎችን እዚህና እዚህ እንወስናለን ነገር ግን ጽናት ኖሮን አንገፋበትም። የወድቀት እና የስኬት ዋናው መለያ ጽናት ነው።

ለምሳሌ ከመጠጥ ሱስ መላቀቅ የሚፈልግ ሰው መቶ ጊዜ ለማቆም ቢወስንም ከውሳኔው ጋር ጽናት ካልተደመረበት በቀር ውሳኔው ብቻውን ምንምዋጋ የለውም። ስለዚህ በውስጣችን ያለውን የጽናት መጠን መፈተሹ እጅግ ወሳኝ ነገር ነው።

9. "ጥምር ሃይል (Power of the master mind)!"

"ሁለት ጭንቅላቶች አንድ ላይ ሲሆኑ ሶስተኛ ጭንቅላት ይወለዳል"። አንድ ሰው የራሱ የሆነ ሃሳብ ወይም ግኝት ሊኖረው ይችላል፤ ከሌሎች ሰዎች ሃሳብ ሲደመር ይበልጥ ይሰምራል። "ከአንድ ብርቱ ሁለት መድሐኒቱ" እንዲል የሃገራችን ሰው። በጋራ የመስራትን ልምድ ማዳበር መቻል አለብን። አብሮ መስራት መቻል ትልቅ ክህሎትም ጭምር ነው።

10. "የምታደርገው ነገር ደስታን ሊስጠህ ይገባል (Enthusiasm)!"

ስቲቭ ጆብስ በህይወት በነበረበት ወቅት እንዲህ ብሎ ነበር "የምንሰራውን ነገር የማንወደው ከሆነ እስከመጨረሻው ለመሄድ አንችልም፤ የሚሰራውን የማይወድ ማንኛውም ሰው ተስፋ ቢቆርጥ አይፈረድበትም።" እውነት ነው! የምንወደውን ነገር ስናደርግ በቀላሉ ተስፋ አንቆርጥም። ሙያችን እንዲሆን የምንመርጠው ነገር የምንወደው ነገር ከሆነ በዛ ነገር ላይ እውቀታችንን ለማዳበርም ሆነ ልምድ ለማግኘት ፍላጎት ይኖረናል። አስቡት ሰውን መርዳት የማይወድ ወይም ለሰ ሰው ምንም ግድ የለለው ሰው የህክምና ባለሙያ ቢሆን፤ በሽተኞቹን እንደ ገንዘብ ማግኛ ከመቁጠር በቀር ለጤንነታቸውም ሆነ ለደስታቸው ዴንታ አይሰጠውም። ስለዚህ የምንሰራው ነገር ምን ያህል ደስታ ወይም እርካት ይሰጠናል የሚለው ጥያቄ በተሰማራንበት መስክ ሁሉ እራሳችንን ልንጠይቀው የሚገባን ጥያቄ ነው።

ምዕራፍ ሁለት

የታዋቂ ሰዎች አባባሎች

“ማንበብ ትልቅ ሀብትን ያጎናፅፋል። እስከዛሬ በአለማችን ላይ ስለተከሠቱ እና በሌሎች ሰዎች ስለተሰሩ ነገሮች በሙሉ ማወቅ የምንችለው ማንበብ ስንጀምር ነው።” **(አብርሃም ሊንከን)**
“በህይወቴ ማወቅ የምፈልጋቸው ነገሮች በሙሉ መፀሀፍቶች ውስጥ አሉ። የኔ ምርጥ ጓደኛ ብዬ የምቀርበው ሰው ያላነበብኩትን መፀሀፍ “እንካ አንብብ” ብሎ የሚሰጠኝ ነው።” **(አብርሃም ሊንከን)**
“እዚህ ምድር ላይ ግዜ የማይሽረው ደስታን የሚሰጠን ብቸኛው ነገር መፀሀፍ የማንበብ ልምድ ነው። ሁሉም ደስታዎቻችን በወረት ከእኛ ሲለዩን መፀሀፍ የማንበብ ልምዳችን ግን ዘወትር ደስተኞች ያደርገናል።” **(አንቶኒ ትሮሎፔ)**

- “ዘወትር ባነበብኩኝ ቁጥር ውስጤ የነበረውና ያለው ትልቁ የመቻል አቅም ይቀሰቀሳል።” **(ማልኮምኤክሥ)**
- “የኔን የግል ህይወት ብቻ ሳይሆን በዙሪያዬ ያሉ ሰዎችን ህይወት መለወጥ የቻሉ ሀሳቦችን መተግበር የቻልኩት መፀሀፍ በማንበቤ ነው።” **(ቤል ሑክሥ)**
- “መፀሀፍን የሚያነብ ሰው በህይወት ውጣ ውረዱ አያማርርም። ሠዎች ለምን ጎዱኝ፣ ለምንስ አያስቡልኝም ብሎም ሌሎችን አይወቅስም። ከሌሎች ጋርም አይቀያየምም ምክንያቱም መፀሀፍ የሚያነብ ሰው ለራሱ ስኬትና ደስተኛነት ራሱ ብቁ ነውና ከሌሎች ምንም ስለማይጠብቅ።” **(ባሮው)**
- “ዛሬ ላይ ያለህ ማንነት የዛሬ አምስት አመት ከሚኖርህ ማንነት ጋር ፍፁም ለውጥ ሳይኖረው ተመሳሳይ ነው። ግን በነዚህ አመታቶች ውስጥ መፀሀፎችን ካነበብክ **አዎ!** ከአሁኑ ይልቅ የዛሬ አምስት አመት የተሻለ ማንነት ይኖርሃል።” **(ቻርሊጃንሥ)**
- “ለአንድ ሠው መፀሀፍ ስትሸጥ የሸጥከው ብዙ ወረቀቶችን፣ የተፃፈበትን ቀለምና ጥራዙን አይደለም። ለርሱ የሸጥክለት ዋናው ነገር ሙሉ የሆነ አዲስ ህይወትን ነው።” **(ክርስቶፈር ሞርሌይ)**
- “በዚህ ዘመን በየትኛውም ሁኔታ በጣም ግዜ የለኝም፣ እረፍት የለኝም ብለህ የምታስብ ቢሆን እንኳን ለማንበብ የግድ ግዜ መስጠት አለብህ። ይህን አላደረክም ማለት ግን በገዛ ፍላጎትህ ራስህን አላዋቂ እያደረከው ነው ማለት ነው።” **(ኮንፊሽየሥ)**
- “ድሮ ልጅ ሣለሁ ወደ ትምህርት ቤት ስሔድ ዘወትር አፍንጫዬን በመፀሀፍ ደብቄ ነበር። ይኸው ዛሬ ላይ ታዲያ እዚህ ለመድረሴ ዋና ምክንያት ሆኖኛል።” **(የሙዚቃ አቀንቃኙ ሱሊዮ)**
- “መፀሀፍትን በሚገባ ማንበብ ማለት በድሮ ዘመን ይኖር ከነበረ በጣም አስተዋይ ሰው ጋር መወያየት ማለት ነው።” **(ሬኔ ዴካርቴሥ)**
- “አዎ! የሚታኘክ ማስቲካ ለማምረት ከምናወጣው ወጪ በላይ ለመፀሀፍቶች ብዙ ወጪን ባናወጣ ኖሮ ይህች ሀገራችን እንዲህ የሠለጠነችና የዘመነች አትሆንም ነበር።” **(አልበርት ሀባርድ)**
- “ከየትኛውም ነገር በላይ ትልቁንና ከፍተኛውን ደስታ የማገኘው ሳነብ ነው።” **(የፋሽን ዲዛይነሯ ቢልብላሥ)**
- “ማንበብ ከቻልክና አንዴ ማንበብ ከጀመርክ በቃ አንተ ነፃነት ያለህ ሠው ነህ።” **(ፍሪድሪክ ዳግላሥ)**
- “ለመኖር ከፈለክ መፀሀፍ አንብብ።” **(ጉስታሽ ፍላውበርት)**
- “መፀሀፍን ከማቃጠል የባሰ በርካታ ወንጀሎች አሉ።ከነዚህ መሃል መፀሀፍትን አለማንበብ አንዱ ትልቁ ወንጀል ነው።”**(ጆሴፍ ብሮድስኪ)**

- ✧ "አላዋቂነትንና ችኩልነትን የምንዋጋበት ብቸኛው ወሳኝ መሣሪያ ማንበብ ነው።" **(ሌኖርድ ቤይንሥ ጆንሰን)**
- ✧ "ዛሬ ያነበበ ነገ መሪ ይሆናል።" **(ማርጋሪት ፉለር)**
- ✧ "መፀሀፍን የማያነብ ሠው ማንበብን ከነጭርሱ ከማይችል ሠው በምንም አይሻልም።" **(ማርክትዌይን)**
- ✧ "በርካቶቻችን መፀሀፍ አንባቢ መሆን እንፈልጋለን። የምናነበው ግን ጥቂቶች ብቻ ነን።" **(ማርክ ትዌይን)**
- ✧ "እኔ የተወለድኩት ማንበብ ከሚገቡኝ ግና አንብቤ ከማልጨርሣቸው የመፀሀፍት ዝርዝሮች ጋር ነው።" **(ማውዲ ኬሲ)**
- ✧ "ለአንድ ጨቅላ ልጅ መፅሐፍ እንዲያነብ ከማድረግ በላይ ልንሠጠው የምንችለው ትልቅ ሥጦታ የለም።" **(ሜይ ኤለን ቼሥ)**
- ✧ "አንድ መፀሀፍ ባነበብን ቁጥር እዚህ ምድር ላይ በሆነ ቦታ ለኛ አንድ በር እየተከፈተልን ነው።" **(ቬራናዛሪያን)**
- ✧ "ለኔ ህይወት ማለት ጥሩ መፀሀፍ ማለት ነው። የበለጠ ወደ ውስጡ በገባን ቁጥር የበለጠ ትርጉም እየሰጠን ይመጣል።" **(ሀሮልድ ሱሽነር)**
- ✧ "እስከዛሬ በህይወቴ ካገኘኋቸው ምክሮች ትልቁ እውቀት ሀይል ነው። ማንበብ ደግሞ አማራጭ የሌለው ተግባር ነው የሚለው ነው።" **(ተዋናይ ዳቪድ ቤይሊ)**
- ✧ "የህይወታችን ትልቁ ደስታ መፀሀፍ ከማንበብ የሚገኝ ነው ብዬ በድፍረት ላውጅ እችላለሁ። ወደፊት እኔ የራሴ መኖሪያ ቤት ሲኖረኝ አንድ ጥሩ ላይብረሪ በውስጡ ካላካተትኩኝ ምን እንደሚውጠኝ አላውቅም።" **(ደራሲ ጆን ኦውስተን)**
- ✧ "መፀሀፎች ወረት የማያውቁ ምርጥ ወዳጆች ናቸው። እጅግ መልካም አማካሪዎችና የችግር ግዜ ደራሾችም ናቸው። እንዲሁም ከምንም በላይ ታላቅ መምህር ናቸው።" **(ቻርሊ ኢሊዬት)**
- ✧ "ማንበብ ከምንገምተው በላይ ዘላቂ የሆነ ደስታን ነው የሚከፍለን" **(ላውራቡሽ)**
- ✧ "መልካም ህይወት መኖር ከፈለግን ዛሬ ነገ ሳንል ማንበብ መጀመር አለብን።" **(ሞርታይመር አለዴር)**
- ✧ "አንድ ሠው ምን አይነት ማንነት እንዳለው ያነበባቸውን መፀሀፎች አይቶ መናገር ይቻላል።" **(ራልፍ ዋልዶ ኤመርሠን)**
- ✧ "አንድ ባህል ወደ ቀጣይ ትውልድ እንዳይተላለፍ ከተፈለገ መፀሀፎችን ማቃጠል አያስፈልግም። ይልቅ ሠዎቹ መፀሀፍ ማንበብን እንዲያቆሙ ማድረግ በቂ ነው።" **(ራይ ብራድበሪ)**
- ✧ "የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለአካላችን የሚጠቅመውን ያህል ንባብም ለአእምሯችን ይጠቅማል።" **(ሪቻርድ ስቲላ)**
- ✧ "ሽረሪቶች እንደተወለዱ በተፈጥሮ ድርን የመስራት ክህሎትን እንደሚያገኙ ሁሉ ህፃናትም ሲወለዱ የመናገር ጥበብና ችሎታ አብሯቸው ይወለዳል። ግና ማንበብ መቻልን እኛ ነን ልናለማምዳቸውና ልናስተምራቸው የሚገባን።" **(ስቴቨን ፒንከር)**
- ✧ "መርከበኞች በአንጸባራቂ ደሴት ላይ ከሚያገኙት ሀብት በላይ ብዙ ሀብት የሚገኘው መፅሀፍቶች ውስጥ ነው።" **(ዋልት ዲስኒ)**
- ✧ "አንተ ጋር ሲመጡ መፀሀፍ በእጃቸው ያልያዙ ሠዎችን በፍፁም አትመን።" **(ሊሞኒ ስኒኬት)**
- ✧ "ለማንበብ ግዜ የለኝም ካልን ለማውራትና ለመፃፍ እንዴት ግዜ እናገኛለን?" **(ስቴቨን ኪንግ)**
- ✧ "ህፃናት እንደሚያደርጉት ለመገረም ብለው መፀሀፍን አያንብቡ። ለመማርም ሆነ ሀልመኛ ለመሆንም ፈልገው አያንብቡ። ይልቅ አዎ! ለመኖር ሲሉ ነው ማንበብ ያለብዎት።" **(ጉስታቮ ፍላውበርት)**
- ✧ "እኔና ጥቂት ሰዎች ስለራሳችን መልካም ነገር የምናስበውና ጥሩ ስሜት የሚሠማን መፀሀፍ ስናነብ ነው።" **(ጄን ስሜይሊ)**

- ✧ "የልጆቻችንን ቀጣይ ህይወት ብሩህ ልናደርግላቸው የምንችልባቸው ጥቂት መንገዶች አሉ። ከነዚህ መንገዶች መሃል ሠፊውና አስተማማኙ በውስጣቸው የንባብ ፍቅርን መዝራት ነው።" **(ማያ አንጀሎ)**
- ✧ "መፀሀፍ ማንበብ ነገሮችን እንድንረዳ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እኛን በቀላሉ እንዲረዱን ይጠቅመናል።" **(ጆን ግሬን)**
- ✧ "አንተ ያላነበብከውን መፀሀፍ አንብብ ብለህ ለልጅህ አትስጠው።" **(ጆርጅ በርናንድ ሾው)**
- ✧ "አንተ ወይም እኛ የማናውቃቸው ነገሮች በሙሉ መፀሀፍት ውስጥ እንዳሉ እናውቃለን?" **(ሲድኒ ስሚዝ)**
- ✧ "እኔ አንብቤ ባስቀመጥኳቸውና በማነባቸው መፀሀፎች ካልተከበብኩ እንቅልፍ በፍፁም አይወስደኝም።" **(ጆርጅ ሉዊሥ በርጌሥ)**
- ✧ "አንዳንድ መፀሀፎች የፈለግነውን እንድናስብ ነፃ ያደርጉናል። አንዳንድ መፀሀፍት ደግሞ ከጭንቀታችን ነፃ ያደርጉናል።" **(ራልፍ ዋልዶ ኤመርሠን)**
- ✧ "ምናባችንን ከተኛበት የሚቀሠቅስልን ሞተር መፀሀፍ ማንበብ ነው።" **(አለን ቤኔት)**
- ✧ "በአሁኑ ሰአት እየተቃጠሉ ካሉ መፀሀፍት በላይ የሚያሳስበኝ በአሁኑ ሰዓት እያልተነበቡ ያሉ መፀሀፎች ናቸው።" **(ጁዲ ብሉሜ)**
- ✧ "ልጆቼ ወደፊት ሲያድጉ ማንበብ የሚወዱና ለእናታችን ትልቅ መፀሀፍ መደርደሪ እንስራላት ብለው የሚጨነቁ ቢሆኑ ደስታዬ ወደር አይኖረውም።" **(አና ክዊድሰን የኒዮርክ ታይምስ ፀሃፊ)**
- ✧ "መፀሀፍት ማለት መቼም ቢሆን የማይርቁን፣ የማያስቀይሙን፣ የማይከዱንና መቼም ቢሆን ተስፋችንን የማያጨልሙብን ወዳጆቻችን ናቸው።" **(ቻርልሥ ኤሊዮት)**
- ✧ "ከውሻ ውጪ የሠው ልጅ ታማኝ ወዳጅ መፀሀፍት ናቸው። ከውሻ ጋር ወዳጅ ስንሆን ግን የማንበብ እድላችን በጣም ያነሠ ነው።" **(ጉርኞ ማርክሥ)**
- ✧ "በመመገቢያ ጠረጴዛህ ላይ መፀሀፎች ይሙሉ። ከዛም በጣም ደስተኛ ትሆናለህ። ትራስህም መፀሀፍቶችን ይሁኑ ከዛም ፍፁም የሠላም እንቅልፍ ትተኛለህ።" **(ፊይዶር ዶስቶኽስኪ)**
- ✧ "መፀሀፍ ማለት በኪሳችን ይዘነው የምንዞረው በመልካም ፍሬዎች የተሞላ እርሻ ነው።" **(ቻይናውያን)**
- ✧ "መፀሀፍ ስናነብ ወደ ውስጣችን በጣም ጠልቀን በመግባት ስለራሳችን የበለጠ ብዙ ነገሮችን ማወቅ እንጀምራለን።"**(ዊልያም ሀዝሊት)**
- ✧ "ትንሽዋ የመፀሀፍ መደርደሪያ እስከዛሬ በአለማችን ላይ ከቀረቡ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በላይ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሃሣቦችን ይዛለች። **(አንድሪው ሮስ)**
- ✧ "ለአንድ ሰአት ብቻ ካነበብክ ወይም የማንበብ ልምድ ካለህ መጨነቅህ አይቀርም። ከሁለት ሰአታት በላይ የማንበብ ልምድ ካለህ ግን በምድር ላይ እንዳንተ ደስተኛ ሰው አይኖርም።" **(ቻርለስ ዴ ሴኮንዳት)**
- ✧ "ከአጠገብህ ፋኖስ ለኩሰህ ወይም ሻማ አብርተህ ቁጭ ብለህ መፀሀፍ ማንበብን የመሰለ ምን ነገር አለ? አስበው በዚያ በምታነብበት ሰዓት ሌላው ቀርቶ እዚህ ምድር ላይ አብረውህ ያልነበሩትን የቀድሞ ትውልድ ሰዎችና አብረውህ የማይኖሩትን የመጪው ትውልድ ሰዎችን ማውራት ትችላለህ።ይህ ደግሞ ከምንም በላይ ትልቅ ዋጋና ትርጉም ያለው አስደሳች እሴት ነው።" **(ኬንኮ ዮሺዳ)**
- ✧ "ሠዎች ህይወትን አንድ የሆነ ነገር ነው ብለው ይገልፃሉ። ለእኔ ግን ህይወት ማለት ማንበብ ማለት ነው።" **(ሎጋ ስሚዝ)**
- ✧ "ማንበባቸውን ተከትሎ በየዘመናቸው ታላቅ ስራን የሰሩ ጀግኖች ቁጥራቸው ስንት ይሆን?" **(ሔነሪ ዳቪድ)**
- ✧ "መፀሀፍትን ስናነብ አእምሯችን ራሱን የቻለ አንድ አስደሳች ኮንሰርት ተዘጋጀለት ማለት ነው። ታዲያ አእምሯችን ደስተኛ በሆነበት ሰዓት ደግሞ የሚያስባቸው ሃሣቦች ምን ያህል ጠቃሚና

የጠለቁ እንደሆኑ ሁላችንም እናውቃለን።" **(ስቴፋኒ ማላርሜ)**

- "መፅሀፍ የሚያነቡ ሠዎች ብቸኝነት አያጠቃቸውም።" **(አጋታ ክርማለት)**
- "መፅሀፍ ማንበብ ነፍስን ያክማል።" **(በቴክሳስ ላይብረሪ መግቢያ ላይ የተፃፈ)**
- "መፅሀፍ የሌለበት መምሪያ ቤት ማለት መስኮት የሌለበት ቤት ማለት ነው።" **(ሎነሬች ማን)**
- "ሠው መንፈሱን መመገብ የሚችለው መፀሀፍትን በማንበብ ብቻ ነው።" **(ኤድዊን ማርክሃም)**
- "የተራበ ከብት ሳር ሲግጥ የሚሰማውን ደስታ ይህል ነው የሠው ልጅም መፅሀፍትን ሲያነብ ከፍተኛ ደስታን የሚያገኘው።" **(ሎርድ ቸስተርፊልድ)**
- "አንድ ሠው ለልጁም ሆነ ለመላው ማህበረሰብ ከሚሰጠው ስጦታዎች ሁሉ ትልቁ አንብቦ ሰዎችን እንዲያነቡ ማስቻሉ ነው።" **(ካርል ካጋን)**
- "ልጆቻችንን ዝም ብለን አይደለም አንብቡ ብለን እንዲያነቡ ማድረግ ያለብን። ይልቁንም በማንበባቸው በጣም ደስተኞች እንዲሆኑና ደጋግሞ የማንበብ ፍቅር እንዲያድርባቸው የሚያደርጉማድረግ ነገሮችንም አብረን ይጠበቅብናል።" **(ካትሪና ፒተርሠን)**
- "ከየትኛውም መዝናኛ በላይ እንደማንበብ ዋጋው ርካሽ ሆኖ በቀላሉ የሚያዝናና ነገር የለም። ደግሞም በማንበብ እንደሚገኘው ዘለቄታዊ ደስታ ሌሎች መዝናኛዎች ዘላቂ ደስታን አይሠጡም።" **(ሌዲ ሞንታኑ)**
- "እኔ ዘወትር የማስበው በቀጣይ ስለማነበው መፀሀፍ ብቻ ነው።" **(ሮኦልድ ዳህል)**
- "መፅሀፍትን ማንበብ መታደል ነው። ምክንያቱም ባነበብን ቁጥር አለማችንን በሚገባ እናውቃታለንና።" **(ኒል ጌይንማን)**
- "የሰው ልጅ ታላቅነት የሚገለፀው በሚያገኘው ነገር ሳይሆን ለማግኘት በሚያሳየው ፅናት ነው።" **ካህሊል ጂብራን**
- "የጅረቶች ብዛትና የዝናብ መዓት የውቅያኖስ ጣዕም እንደማይበርዙት ሁሉ የመከራ ውርጅብኝም የቆራጥ ሰው ህሊናን በድን አያደርገውም እንዲህ ያለ ሰው የህያውነት ሚዛኑን ይጠብቃልና።" (**ሴኒካ)**
- "የደስታ ምንጭ የምትሞላውና ሳታቋርጥ የምትፈሰው ከውስጣችን በሚፈልቁ ብሩህ አስተሳሰቦችና ስሜቶች ነው።"
  (ዊሊያም ላዩምፊሊፕስ)
- "እራስን ሁን፣ የሚሰማህንም ተናገር፣ ምክንያቱም እራስህን በመሆንህ ቅር ለሚላቸዉ ሰዎች ቦታ/ደንታ መሰጠት የለብህም፤ የሚበጁህ ስዎች ደግሞ እራስህን በመሆንህ ቅር አይሰኙምና።" **(ዶ/ር ሱስ)**
- "እንቅፋቶች እንደ ቢላዋ ናቸው። በስለቱ ከያዝናቸው ይቆርጡናል። በእጀታቸው ከያዝናቸው ደግሞ ይጠቅሙናል።" (**ጂምስ ራስል ሐዌል)**
- "እስካመንክበት ድረስ አንድ ትልቅ እርምጃ ለመውሰድ አትፍራ። አንድ ሸለቆ ለመዝለል ሁለት አነስተኛ እርምጃዎችን ለመጠቀም አትችልምና።" **(ዴቪድ ሎይድ ጆርጅ)**
- "በመጣላት የምንፈልገውን ያህል አናገኝም። አውቀን በመተው ግን ያልጠበቅነውን ያህል እናገኛለን። ስለዚህ ከሰዎች ጋር ተስማምተህ ለመኖር መሳሳትህን ካወቅህ ሳታወላውልና ቅር ሳትሰኝ ስህተትህን አርም።" **(ዴል ካርኒኔ)**
- "ቅንዓት ሲመገብ ያደገ ፍቅር አሟሟቱ ከባድ ነው።" **(ላቭስ ኩዩር)**
- "የራስህ ቤተ መንግሥት ሁን አለበለዚያ ዓለም እስር ቤት ትሆንብሀለች።" **(ጆን ዶ)**
- "መታጠፊያ መንገድ ሲያገኝ የሚታጠፍ ፍቅር ፍቅር አይደለም።" **(ሼክስፒር)**
- "መናጢ ደሀና የናጠጠ ቱጃር ምክንያት የሚሰሙበት ትዕግሥት የላቸውም።" **(በፈረዲን)**
- "የህይወት ትግሎችና ሩጫዎች ደስታዬን እንዳይነጥቀኝ በእጅጉ እጠነቀቃለሁ።" **(ኤልሲን)**
- "ዕውቀትህን እንደኪስ ሰዓትህ ሲያስፈልግህ አውጥተህ ተጠቀምበት እንጂ በማያስፈልግህ ጊዜ ሁሉ ለታይታ አታውለው።" **(ፊሊፕ ዳርመር ስታንሆፕ)**

- ✧ ″ሌሎችን የሚያሸብር ሁሉ እርሱ ራሱ በማያቋርጥ ፍርሃት የተዋጠ ነው።″ **(ክላውሲያ)**
- ✧ ″ወገንን ረስቶ ለግል ጥቅም ብቻ መጣር /መስገብገብ በተፈጥሮ ህግ ላይ የሌብነት ተግባር መፈጸም ነው።″ **(ጅካሳ ፔሬቤሪስት)**
- ✧ ″ለወንድ ልጅ ከመንግሥት ይልቅ ሚስት የበለጠ ጉልበተኛ ናት።″ **(ራልፍ ኢመርሰን)**
- ✧ ″ነጻ ሰዎች ነጻ ሆነው ነው የሚኖሩት በቀላሉ የሚገዛቸው ገንዘብና ሀይል ስለሌ ነው።″ **(ሼክስፒር)**
- ✧ ″የወደፊቱን የእርካታ ጊዜ የምታገኝበት የተሻለ መንገድ ያለህበትን ዕለት በሳቅና በፈገግታ ስታሳልፈው ነው።″ **(ቻርለስ ደብሊው)**
- ✧ ″የሰው ልጅ ዲሞክራሲን አይጠግብም መጀመሪያ በትንሽ ሳህን ቀጥሉ በጆንያ ይፈልጋል።″ **(ኢድ አሚን ዳዳ)**
- ✧ ″እያንዳንዱ ሰው ልክ እንደ ጨረቃ ነው። ለማንም የማያሳየው ግማሽ ጎን አለው።″ **(ማርክ ትዌይን)**
- ✧ ""ገንዘብ የማይገዛው ነገር እስከሌለህ ድረስ ባለፀጋ አይደለህም።" **(Unknown)**
- ✧ "የሰው ልጅ ነፃ ነኝ ብሎ የሚያምን የልማድ ባሪያ ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "ጉድለትህን ወደ ፍፁምነት የሚቀይረው፤ ፈጣሪህን እንጂ ሀይማኖትህን አይደለም።" **(Unknown)**
- ✧ "የመገለጥን ብርሃን ትጨብጥ ዘንድ የሥጋን ጨለማ አሸንፍ።" **(Unknown)**
- ✧ "በፍቅር ስትሆን መንገድህን ልትዘነጋ ትችላለህ፤ ነገር ግን አትጠፋም!" **(Unknown)**
- ✧ "በፍቅር የተሰራ ታጢያት፤ ፍቅር ከሌለበት አምልኮ ይበልጣል።" **(Unknown)**
- ✧ "ፈላስፋ በሕይወት ጨዋታ ላይ የተገኘ ተመልካች ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "የእኔ ፍላጎት የፈጣሪን ሀሳብ ማወቅ ነው ፤ ሌላው ሁሉ ዝርዝር ጉዳይ ነወ።" **(Unknown)**
- ✧ "የምትኖረባትን ሕይወት በቅጡ ሳታውቅ ስትሞት ሌላ ዓለም መኖሩን እንዴት ታውቃለህ።" **(Unknown)**
- ✧ "ታላላቅ እምነቶች ሁሉ መነሻቸው መናፍቅነት ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "ያልተመረመረ ህይወት ሊኖሩት የማይገባ ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "የእግዚአብሔር ፍቃድና እውቀት በእኛ አላዋቂነት ሊፈተን አይችልም።" **(Unknown)**
- ✧ "ለማመን እንጂ ላለማመን ምክንያት አያስፈልግም።" **(Unknown)**
- ✧ "የሞት ፍርሃት የሕይወት ማጣፈጫ ቅመም ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "መልካምነት የተደረገልህን ሳይሆን ያልተደረገልህን የመክፈል ብቃት ነው።" **(Unknown)**
- ✧ ″ሠላምን በጉልበት ማስጠበቅ አይቻልም። ሠላምን ማስጠበቅ የሚቻለው በመግባባት ብቻ ነው።″ **(Unknown)**
- ✧ ″ስህተት ሠርቶ የማያውቅ ሠው ምንም ነገር ሞክሮ አያውቅም ማለት ነው።″ **(Unknown)**
- ✧ ″ሁሉም ሠው ብሩህ ጭንቅላት አለው። ነገር ግን አሣን ዛፍ መዝለል አይችልም ብለህ ችሎታውን ካጣጣልከው በህይወትህ ሙሉ አሣ ደደብ እንደሆነ ታስባለህ።″ **(Unknown)**
- ✧ ″ዓይነ ሕሊና ከዕውቀት የላቀ አስፈላጊ ነው።″ (**Unknown)**
- ✧ ″ትምህርት አዕምሯችን የበለጠ እንዲያስብ እንጂ ጥሬ ሃቆችን ለመለማመድ አይደለም።″ (**Unknown)**
- ✧ ″ሙከራህን እስከምታቆም ድረስ በህይወት አትሸነፍም።″ (**Unknown)**
- ✧ ″አንድን ነገር በቀላል ቋንቋ መግለፅ ካልቻልክ ነገሩን አልተረዳኸውም ማለት ነው።″ (**Unknown)**
- ✧ ″እብደት ማለት አንድን ነገር በተመሳሳይ ዘዴ ደግሞ ደጋግሞ በመስራት የተለየ ውጤት መጠበቅ ነው።″ (**Unknown)**
- ✧ ″ደስተኛ ሕይወት ለመኖር ከፈለግክ አንተነትህን ከሠዎች ወይም ከነገሮች ጋር ከማወዳደር ይልቅ ከግብህ ወይም ከዓላማህ ጋር ራስህን እሠር።″ (**Unknown)**

- ✧ ”ስኬታማ ለመሆን ከፈለግክ የስኬት ፍላጎትህ እወድቃለሁ ብለህ ከምትፈራው ፍርሃትህ በእጅጉ የበለጠ መሆን አለበት።” (**Unknown)**
- ✧ ”መቀራረብ በፍቅር ለመውደቅ ዋስትና አይሆንም።” (**Unknown)**
- ✧ ”ዋጋ ያለህ ሠው ለመሆን ሞክር እንጂ ስኬታማ ብቻ ለመሆን አትሞክር።” (**Unknown)**
- ✧ ”ምክንያታዊነት ከአንድ ቦታ አንስቶ ወደሌላ ቦታ ሊወስድህ ይችላል። ዓይነ ሕሊና ግን የትም ይወስድሃል።” (**Unknown)**
- ✧ ”ጎበዝ ሠው ችግሮችን ይፈታል። ብልህ ሠው ግን ችግሮቹ መልሠው እንዳይፈጠሩ ያስወግዳቸዋል።” (**Unknown)**
- ✧ ”ተፈጥሮን በጥልቀት ተመልከት። ያን ጊዜ ሁሉንም ነገሮች በተሻለ ትረዳለህ።” (**Unknown)**
- ✧ ”ሴቶች ብዙ ጊዜ የሚጨነቁበት ወንዶች ጨርሠው በረሷቸው ነገሮች ላይ ነው። ወንዶችም ብዙ ጊዜ የሚጨነቁበት ጉዳይ ሴቶቹ በማያስታውሷቸው ነገሮች ላይ ነው።” (**Unknown)**
- ✧ ”ቅዱሱን ጉጉትህን አትጣለው።” (**Unknown)**
- ✧ ”የአመለካከት ድክመት እየቆየ ሲሄድ የባህሪ ድክመት ይሆናል።” (**Unknown)**
- ✧ ”ሞትን መፍራት ማለት ተገቢ ባልሆኑ ፍርሃቶች መንቦቅቦቅ ነው። ምንም ስጋት የሌለበት ሠው ቢኖር የሞተ ሠው ብቻ ነው።” (**Unknown)**
- ✧ ”ፍፁም የማይመስለውን የሚሞክሩ የማይቻለውን የሚችሉ ናቸው።” (**Unknown)**
- ✧ "ፍቅር ዕርቃኑን ያለ ህፃን ማለት ነው። ታዲያ ለገንዘብ ማስቀመጫ ኪስ ያለው ይመስላችኋል?" **ኦሼድ**
- ✧ "ነፃ የምንሆነው ስለነፃነት ባለን የግንዛቤ ልክ ነው።" **ሉተር ኪንግ**
- ✧ "ልብህ ይናገር ዘንድ ምላስህ ዝም ይበል። እግዚአበሔር ይናገር ዘንድ ደግሞ ልብህ ዝም ይበል።" **አባራሀኒ**
- ✧ "ፖለቲከኛ እራሱ የሚናገረውን ራሱ አያምንም ሌሎች ሲያምኑት ግርም የሚለው ለዚህ ነው።" **ቻርል ደጎል**
- ✧ "ፖለቲከኛ የሰውን ልጅ በሁለት መደብ ይከፍለዋል። ጠላት መምቻ መሣሪያና ጠላት" **ፍሬድሪክ ኒቼ**
- ✧ "የምታልፈው ደቂቃ የእያንዳንዱ ሰው እኩል ሀብት ናት፤ አንዴ ካለፈች ግን የማንም ሀብት አይደለችም።" **ማርክስ አውሬሊየስ**
- ✧ "የማያፈቅር ልብ ከሚኖረኝ የማያዩ አይኖች፣ የማይሰሙ ጆሮዎችና የማይናገር አንደበት ቢኖረኝ ይሻላል።" **ሮበርት ቲዞን**
- ✧ "ያንተ ሀሳብ ሳይጨመርበት ማንም የበታችነት እንዲሰማህ አያደርግህም።" **ኤለኖር ሩዝቬልት**
- ✧ "የደስታ ምንጭ የምትሞላውና ሳታቋርጥ የምትፈሰው ከውስጣችን በሚፈልቁ ብሩህ አስተሳሰቦችና ስሜቶች ነው" **ዊሊያም ላዩምፊሊፕስ**
- ✧ "በውስጥህ ብዙ ዓይነት ባህሪያትና ስብዕናዎች እንዳሉ አትዘንጋ፤ ለራስህ እንግዳ አትሁን። የአዕምሮ ግዛቶችን ዘልቆ ገብቶ ማንነትንና ችሎታን እንደማወቅ ታላቅ ጀብዱ ከቶ የለም።" **ሩሶ**

- ✧ "ጊዜ ማንኛውንም ሀዘን የሚያስወግድ ጥሩ መድሀኒት ነው።" **ሲፈለክስ**
- ✧ "ጥበበኞች ከሺ ዓመታት በፊት የመለሱትን መሐይሞች ዛሬም ይጠይቃሉ።” **ጎቴ**
- ✧ "ፍቅር ከጥልቁ ውስጣችን የሚመጣ ነው። በጥያቄ ልናመጣው አንችልም፤ ሲመጣም ዝም ማሰኘት አይቻልም። ፍቅር እኛ የምናደርገው ምርጫ አይደለም።" **ኦሾ**
- ✧ "ፍቅር ራሱን እንጂ ሌላ ምንም አይሰጥም፤ ከራሱ እንጂ ከሌላ ከማንም ምንም አይቀበልም፤ ፍቅር ለፍቅር በቂ ነውና። ፍቅር ምንም ንብረት የለውም፣ የማንም ንብረት ሊሆንም አይችልም።" **ካህሊል ጂብራን**

- "እንቅፋቶች እንደ ቢላዋ ናቸው። በስለቱ ከያዝናቸው ይቆርጡናል። በእጀታቸው ከያዝናቸው ደግሞ ይጠቅሙናል።"

  ጂምስ ራስል ሐዌል
- "ብቸኛው ታሪክ የሚያስተምረን ትምህርት ቢኖር ሰው ከታሪክ አለመማሩን ነው።" **ኤመርሰን**
- "አለማችን በጣም እየተጎዳች ያለችው ከመጥፎ ሰዎች ክፋት ሳይሆን በጥሩ ሰዎች ዝምታ ነው።" **ናፖሊዮን**
- "ጠቅላላው የአለም ታሪክ በድምሩ ሲታይ ሀገሮች ጠንካራ ሲሆኑ ሁልጊዜ ፍትሀዊ ሆነው አይገኙም። ፍትሀዊ እንሁን ባሉ ጊዜ ደግሞ ጠንካራ ሆነው አይገኙም" **ዊንሰተን ቸርችል**
- "የሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ዋናው ነገር በሌሎች የመሞገስ ጉጉት ነው። ስለዚህ ከሰዎች የምትፈልገውን ለማግኘት የተፈላጊነት ስሜት እንዲሰማቸው አድረግ።" **ዊሊያም ጀምስ**
- "የሰዎችን መልካም ገፅታ ብቻ ነዉ የምመለከተዉ። እኔ ራሴ እንከን የለሽ ሰላልኾንኩ የሌሎችን እንከን የምቆፍርበት ምክንያት የለኝም።" **መሀተመ ጋንዲ**
- "ዝቅተኛ እውቀት ባለህ ቁጥር የምትተኛው እንቅልፍ ከፍተኛ ይሆናል።" (**Unknown)**
- "የሰው ልጅ ከደስታው ይልቅ የሀዘኑን ጊዜያት መቁጠር ይወዳል።" (**Unknown)**
- "በአብዛኛው ጊዜ ሴቶች የፍቅርን ትርጉም የሚጠፋባቸው በውበታቸው ማምለክ ሲጀምሩ ሲሆን ወንዶች ደግሞ በገንዘባቸው ማምለክ ሲጀምሩ ነው።" (**Unknown)**
- "መጀመሪያ ለራስህ ራስህ መሆን ስትጀምር ለማን ምን መሆን እንዳለብህ ትገነዘባለህ።" (**Unknown)**
- "የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታው ሲጨምር የጓደኞቹን ብዛት ይቀንሳል።" (**Unknown)**
- "ከሰዎች ጋር ሮጠህ ያልደረስክበት ነገር ካለ ወደ ተነሳህበት ተመልሰህ ከፈጣሪህ ጋር መሮጥ ጀምር፣ ያኔ ካሰብክበት ሳይሆን ካሰበልህ ቦታ ትደርሳለህ።" (**Unknown)**
- "ጓደኛን አለማመን ከመካድ የከፋ ነው።" (**Unknown)**
- "የራስህን ትኩስ እንጀራ ለመጋገር ስትል የሌላውን ቂጣ አትርገጥ።" (**Unknown)**
- "አንዳንድ ሰዎች የሚወድቁት ሌሎችን በሁለት እግሮቻቸው ለመርገጥ ሲጣጣሩ ነው።" (**Unknown)**
- "ሰው ከጊዜ እና ከማጣት ብዙ ይማራል።" (**Unknown)**
- "አንዳንዴ ሽንፈትም ከድል የበለጠ ዋጋ አለው/ ከማሸነፍ ይልቅ በመሸነፍ ውስጥ ብዙ እውቀት አለ።" (**Unknown)**
- "ሠው የበለጠ እያገኘ በሄደ ቁጥር የበለጠ ስግብግብ እየሆነ ይሄዳል።" (**Unknown)**
- "ሠዎች ትርጉም ያለው ሥራ መስራት ካልቻሉ የመኖር ትርጉምም ይጠፋባቸዋል።" (**Unknown)**
- "ባንኮች ዝናብ ሳይኖር ዣንጥላ ያበድሩህና መዝነብ ሲጀምር ግን ዣንጥላውን ይነጥቁሃል።" **(Unknown)**
- "አዋቂ ሆኖ ለመታየት የምናደርገው ጥረትና ከንቱ ድካም አላዋቂ አድርጎ ያስቀረናል።" (**Unknown)**
- "የምታልፈው ደቂቃ የእያንዳንዱ ሰው እኩል ሀብት ናት፤ አንዴ ካለፈች ግን የማንም ሀብት አይደለችም።" **ማርክስ አውሬሊየስ**
- "የደስታ ምንጭ የምትሞላውና ሳታቋርጥ የምትፈሰው ከውስጣችን በሚፈልቁ ብሩህ አስተሳሰቦችና ስሜቶች ነው።" **ዊሊያም ላዩምፊሊፕስ**
- "በውስጥህ ብዙ ዓይነት ባህሪያትን፣ ስብዕናዎች እንዳሉ አትዘንጋ ለራስህ እንግዳ አትሁን። የአዕምሮ ግዛቶችን ዘልቆ ገብቶ ማንነትንና ችሎታን እንደማወቅ ታላቅ ጀብዱ ከቶ የለም።" **ሩሶ**
- "ተሳስተህ አታውቅም ማለት አዋቂ ነህ ማለት አይደለም ምንም የማይሞክር ሰውም ከስህተት ነፃ ነውና ።" **እንግሊዛውያን**

- ✧ ”ቅሬታንም ሆነ ሙገሳን ሁለቱንም ተቀበል::ፀሀይም ሆነ ዝናብ አበባን ለማሳደግ ይጠቅማል።" **እንግሊዛውያን**
- ✧ "ጊዜ ይከንፋል ነው ያላችሁት በፍጹም ጊዜ አይከንፍም እኛ ነን የምንከንፈው!!" **ሄንሪ ኣውስቲን**
- ✧ "የሰዎችን መልካም ገፅታ ብቻ ነዉ የምመለከተዉ። እኔ ራሴ እንከን የለሽ ሰላልኾንኩ የሌሎችን እንከን የምቆፍርበት ምክንያት የለኝም።" **መሀተመ ጋንዲ**
- ✧ "እንደ ወንድማማቾች መኖር ካለመድን እንደ ሞኞች አብረን እንጠፋለን።" **ማርቲን ሉተር ኪንግ**
- ✧ "ውለታ እንዲዋልላቸው ውለታ የሚውሉ ነጋዴዎች እንጂ የልብ ወዳጆች አይደሉም።" **ሀዲስ አለማየሁ**
- ✧ ”ተፈጥሮ በአዕምሮአችን ውስጥ በቀላሉ የማይረካ እውነትን የሚናፍቅ ተክል ተክላለች።” **ማርክ ቱለስ**
- ✧ "ኪሱ ውስጥ ያለውን አውጥቶ እየሰጠህ ልብህ ውስጥ ያለውን አውጥቶ የሚወስድብህ ሰው እሱ ልቦናው የታወረ ነው፡" **ካህሊል ጂብራን**
- ✧ ”ሰው የሚማር አንድም በፈደል፣ አንድም በሞከራ ነው፣ አንድም በሳር ”ሀ” ብሎ፣ አንድም በኣሳር ”ዋ” ብሎ።” **ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን**
- ✧ ”ቀን ጎድሎብህ ሁሉንም ብታጣ፣ ሁሉም ቢከዳህ፣ ሁሉን ነገር እንደ ነበረ መመለስ የሚያስችልህ አንድ ነገር ብቻ አለ፣ በራስ ልቦና ዉስጥ የምትፈጥረዉ የእይበገሬነት እልህ። አስፋ በቀለ ገ\የሱስ ነበር ያለዉ።” **ያልታበሱ እንባዎች**
- ✧ **“**ጥሩ ነው ወጣት መሆን። ገንዘብ ባይኖርህ ጤና ይኖርሀል፣ መልክ ባይርህ አንጎል ይኖርሀል፣ እዉቀት ባይኖርህ ጉራ ይኖርሀል፣ ፍቅር ባይኖርህ ተስፋ ይኖርሃል፣ ደስታ ባይኖርህ ንዴት ይኖርሀል፣ ምክንያቱም ወጣት ነህና።” **ስብሃት ነበር ያለዉ**
- ✧ "ችግርህን ለመናገር ሀይማኖት ቦታ ትሄዳለህ፤ ደስታህን ለመግለጽ ጭፈራ ቤት ትገባለህ። ለዚህ እኮ ነው ገነት
  የመግባት እድልህ የጠበበው።" **ሮበርት ሙጋቤ**
- ✧ ”ሁሉም ለውጥ እድገት አይደለም ሁሉም እውቀት ጥበብ አይደለም።” **አብርሀም ሊንከን**
- ✧ ”ምንም እንኳን የምትጓዘው በትክክለኛው መንገድ ቢሆንም ቁጭ ብለህ ከቀረህ ልትደፈጥ ትችላለህ።” **ቾል ሮጀርስ**
- ✧ ”መርሳት ሰብአዊነት ሲሆን ስህተትን ማመን ቅዱሳን ነው።” **ዳፉ በወርሰን**
- ✧ ”ሙከራ ከተሳካ ውጤት መንገድ ከፋች ነው።” **ዊልያም ጀምስ**
- ✧ ”አንድ ነገር በማወቅና እሱን በመረዳት መካከል ትልቅ ልዩነት አለ።” **ቾርልስ በኬታር**
- ✧ ”ዛሬ ከባድ ነው። ነገ እንዲሁም ይከፋል። ተነገ ወዲያ ግን ፀሐይ ትወጣለች። መቼም ተስፋ አትቁረጥ።”
- ✧ ”ፍላጎቴ መወደድ ሳይሆን መከበር ነው።” (**Unknown)**
- ✧ ”ሊኖሩን ከሚገቡ እጅግ ጠቃሚ ነገሮች መካከል ትዕግስት ዋነኛው ነው።” (**Unknown)**
- ✧ ”ከተፎካካሪህ መማር እንጂ መኮረጅ የለብህም። ኮርጅ....ፎ በኋላ ግን ትሞታለህ።” (**Unknown)**
- ✧ ”ገንዘብ አላጣንም። ያጣነው ህልመኛ ሰዎችን ነው። ብርቅ የሆኑት ለህልማቸው የሚሞቱ ሰዎች ናቸው።” (**Unknown)**
- ✧ ”በህይወት የሆነ ነገር ስትሞክር፣ የሆነ ነገር ላይ ጠንክረህ ስትሰራና የሆነ ነገር ስትለወጥ መጥፎ ነገር መከሰት ያቆማል።” (**Unknown)**
- ✧ ”መሬቱ ላይ ዘጠኝ ጥንቸሎች ካሉ፤ ያንተ ፍላጎት አንዷን ጥንቸል መያዝ ከሆነ እሷ ላይ ብቻ አተኩር።” (**Unknown)**
- ✧ ”መሪ ባለራዕይ መሆን አለበት። ተከታዮቹ ከሚያዩት በላይ አሻግሮ ማየት አለበት።”

(**Unknown)**

- ✧ “ተፎካካሪዎችን እርሳ። ዝም ብለህ ደንበኞችህ ላይ አተኩር።” (**Unknown)**
- ✧ “ተስፋ ካልቆረጥክ አሁንም እድል አለህ።” (**Unknown)**
- ✧ “ካልደረከው ምንም ነገር አይቻልም።” (**Unknown)**
- ✧ “ሰዎች ስለአንተ በጣም አካብደው ሲያስቡ የመረጋጋት እና ራስህን የመሆን ሀላፊነት ሊኖርህ ይገባል።” (**Unknown)**
- ✧ “ጥሩ ቡድን ሆነን ምን ማድረግ እንደምንፈልግ በትክክል ካወቅን አንዳችን አስራቸውን ማሸነፍ እንችላለን።” (**Unknown)**
- ✧ “ምርጥ ሰዎችን ሳይሆን ትክክለኛ ሰዎችን ፈልግ።” (**Unknown)**
- ✧ “በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለማሸነፍ ከፈለክ ሰዎች ከአንተ የተሻሉ እንደሆኑ በመንገር ልታበረታቸው ያስፍለጋል። ይህን ካደረክ ስኬታማ መሆንህ አይቀርም።” (**Unknown)**
- ✧ “እውነተኛ የቢዝነስ ሰው እና የስራ ፈጣሪ ጠላት የለውም። ይሄን ከተረዳ ምንም ነገር አይገድበውም።” (**Unknown)**
- ✧ “ሁሉም ሰው ጠላቴ ነው ብለህ ስታስብ በዙርያ ያለው ሰው ሁሉ ጠላትህ ሆኖ ታገኘዋለህ።” (**Unknown)**
- ✧ “የተለየ ‘mindset’ ካለህ የተለየ ውጤት ታመጣለህ።” (**Unknown)**
- ✧ “መስፈርቱን የሚያሟሉትን አትቅጠር። እብድ ሀሳብ ያላቸውን ሰዎች ቅጠር።” (**Unknown)**
- ✧ “ሰው ምንም ያድርግ ምንም፣ ተሳካለት አልተሳካለት ከስራው የሚያገኘው ልምድ በራሱ ትልቅ ስኬት ነው።” (**Unknown)**
- ✧ "ብቸኛው ታሪክ የሚያስተምረን ትምህርት ቢኖር ሰው ከታሪክ አለመማሩን ነው።" **ኤመርሰን**
- ✧ "ሰው ከሰውነት ደረጃ ሊያልፍ ፣ ከመልአክትም ከፍ ሊል እንደሚችል ሁሉ ከእንስሳትም ያነሰ ይሆናል።" **ኦሾ**
- ✧ "ጥበበኛ ሰው ማለት የተወረወረውን ድንጋይ መልሶ የሚወረውር ሳይሆን በተወረወረበት ድንጋይ ቤት የሚሰራ ነው።" (**Unknown)**
- ✧ "በሚገባ የተተጠቀሙበት ሕይወት ረዥም ነው።" **ዳቪንቺ**
- ✧ "የአሁን አስተሳሰቦችህ የወደፊት ሕይወትህን ይፈጥራሉ። እጅግ አዘውትረህ የምታስበው ወይም የምታተኩርበት በአብዛኛው ሕይወትህ ሆኖ ይከሰታል።" **ሮሃንዳ ባይረን**
- ✧ "ፍቅር ደንቆሮ ሰው ሊያዳምጠውና አይነስውር ሊያነበው የሚችል ቋንቋ ነው።" **ኮልሬጅ**
- ✧ "አዋቂ ሆኖ ለመታየት የምናደርገው ጥረትና ከንቱ ድካም አላዋቂ አድርጎ ያስቀረናል።" **ሶቅራጥስ**
- ✧ "አእምሮ እንደ ሆድ ነው። ያስገባው በሙሉ ሳይሆን ያዋሃደው ነው ዋጋ ያለው።" **ላፎንቴን**
- ✧ "ሁላችንም እስረኞች ብንሆንም ልዩነታችን አንዳንዶቻችን የታሰርንባቸው ክፍሎች፣ መስኮቶች ሲኖራቸው የአንዳንዶቻችን ግን የላቸውም።" **ካህሊል ጂብራን**
- ✧ "ቅሬታንም ሆነ ሙገሳን ሁለቱንም ተቀበል። ፀሀይም ሆነ ዝናብ አበባን ለማሳደግ ይጠቅማል።" (**Unknown)**
- ✧ "ተሳስተህ አታውቅም ማለት አዋቂ ነህ ማለት አይደለም ምንም የማይሞክር ሰውም ከስህተት ነፃ ነውና።” **እንግሊዛውያን**
- ✧ "ይቅርታ አለማድረግ ማለት አንተ በጠጣኸዉ መርዝ ጠላትህ ካሁን ካሁን ይሞት ይሆን እያሉ እንደ መጠበቅ ያለ ከንቱ ምኞት ነዉ።” **ኔልሰን ማንዴላ**
- ✧ "አዋቂዎች ዝም ሲሉ ቂሎች ይበዛሉ።” ኔልሰን ማንዴላ
- ✧ "ያላነበበ ጭንቅላትና ጨጓራ አንድ ናቸው። ሁለቱም ባዶ ሲሆኑ አሲድ ያመነጫሉ።" **መጋቢ ሃዲስ እሸቱ አለማየሁ**
- ✧ "ባለግሮሰሪ ጠጪውን ይወዳል እንጂ አማቹ ሊያደርገው አይፈልግም።” **አይሁዳዊያን**
- ✧ "ጦርነት የሚያስነሱት ሽማግሌዎች ናቸው፤ የሚዋጉት ግን ወጣቶች ናቸው።" **አልበርት**

አንስታይን

- "ከጊንጥ ንክሻ በላይ የአሽሙረኛ ሰው ሳቅ የበለጠ ያማል።"**ዲዮጋን**
- "የሰው ልጅ ነፃ ነኝ ብሎ የሚያምን የልማድ ባርያ ነው።" **ኦሾ**
- ″ተፈጥሮ በአዕምሮአችን ውስጥ በቀላሉ የማይረካ እውነትን የሚናፍቅ ተክል ተክላለች።″ **ማርክ ቱለስ**
- "የምታልፈው ደቂቃ የእያንዳንዱ ሰው እኩል ሀብት ናት፤ አንዴ ካለፈች ግን የማንም ሀብት አይደለችም።" **ማርክስ አውሬሊየስ**
- "ጊዜ ይከንፋል ነው ያላችሁት በፍጹም ጊዜ አይከንፍም እኛ ነን የምንከንፈው!!" **ሄንሪ ኣውስቲን**
- “መንፈሳዊነት ከሃይማኖት አይመጣም። መንፈሳዊነት የሚመጣው ከነፍሳችን ውስጥ ነው።” **H.Selassie**
- “ሃይማኖትንና መንፈሳዊነትን አንቀላቅል። ሃይማኖት መንፈሳዊነትን ለማጠንከር በሠዎች የተሠራ ነው። ሠው ፍፁም ባለመሆኑ ሃይማኖት ለተለያዩ ዓለማዊ መሣሪያዎች ሲያገለግል ቆይቷል። አንዳንዱ ሃይማኖትን ተደግፎ ሙስና ይሠራል፣ አንዳንዱ ሃይማኖቱን ለፖለቲካ ፍላጎቱ ያውለዋል። አንዳንዱ ሃይማኖትን ሐይሉን ማጠንከሪያና ህዝቡን መጨቆኛ አድርጎ ይጠቀምበታል። መንፈሳዊነት የርዕዮት ዓለም አመለካከት አልያም ስለአምላክ የሚያጠና የዕውቀት ዘርፍ አይለም። መንፈሳዊነት ንፁህና ከተፈጥሮ የተለገሠን የሕይወት መንገድ ነው። መንፈሳዊነት ከሠማየ ሠማያቱና ከአጥናፈ ዓለሙ ጋር የተሳሰረና እርስበርሱ የተዋሃደ ነው።” **H.Selassie**
- “በዓለም ታሪክ በሚሠሩ ሠዎች ውስጥ ትልቅ ስንፍና አለ። በማያውቁና የተሻለ አውቀው የፍትህን ጥያቄ በዝምታ በሚያልፉ መካከል ምንም ልዩነት የለም። ይሄም ክፉ ስራን ሁልጊዜ አሸናፊ እንዲሆን ያደርገዋል።” **H.Selassie**
- “ዕውቀት የፍቅርን መንገድ ይጠርጋል። ፍቅር ደግሞ የመረዳትን አቅም ያዳብራል። ይሄም ትልቅ የሆነ የጋራ ስኬትን ለመቀዳጀት ይመራል።” **H.Selassie**
- “በልምድ ያገኘውን ዕውቀት ሌሎችን ለማገልገል ከመጠቀም ይልቅ በተሠጠው ዕውቀት ራሱን ብቻ ለመጥቀም የሚመኝ ሠው የዕውቀትን ትርጉም የካደና አላስፈጊነቱን ያወጀ ነው።” **H.Selassie**
- “የኢትዮጵያን ህዝብ እንደልጆቻችን እንቆጥራለን።” **H.Selassie**
- “አስተውሉ! ለሐገሩ የሚሞት እሱ እድለኛ ነው። ሞት ግን በሠላሙም ሆነ በጦርነቱ ጊዜ ማንንም ሳይለይ ይዞ ይሄዳል። ከሁሉ ከሁሉ ግን ለነፃነት መሞት ከሌሎች ሞቶች ይበልጣል።” **H.Selassie**
- “ለእንስሳት ርህራሄን ማሳየት ቀላል ነው። እነርሱ እንደሠው ጨካኞች አይደሉም።” **H.Selassie**
- “የሠውን ውስጣዊ የተፈጥሮ ስጦታ የሚዘነጋና የምክንያታዊነቱን የብቃት ሃይል ችላ የሚል ትምህርት፤ እውነተኛ ትምህርት አይባልም።” **H.Selassie**
- “እስካሁን ድረስ ዳዊት ጎልያድን እያሸነፈ ነው።” **H.Selassie**
- “ጥቁርና ነጭ የንግግር ቅርጽ እንጂ ሠዎችን ለመፈረጅ እያገለገለ ስለሆነ ሊወገድ የሚገባ ጉዳይ ነው እላለሁ። ሠዎች በዜግነት፣ በቀለም፣ በዘር፣ በእምነት ቢለያዩ ሠዋዊ ተፈጥሯቸው ግን አንድ ነው።” **H.Selassie**
- “የቁሳዊና የመንፈሳዊ ዕድገቱ እኩል በኩል ለሠው ልጅ አስፈላጊ ነው። በመሆኑም ሁለቱን ጎን ለጎን ያለማቋረጥ አብሮ ይዞ መጓዝ እጅግ ጠቃሚ ነገር ነው።” **H.Selassie**
- “የአዕምሮ ስርዓተ ትምህርት ለእውነተኛው ቅንነት ቅመም ነው። ይሄም ለመንፈሳዊ ጥንካሬ በር ይከፍታል። መንፈሳዊ ሃይል ለዚህኛው ሕይወትም ይሁን ለወዲያኛው ሕይወት ቋሚ መመሪያ ነው።” **H.Selassie**

- “ፍልስፍና አንዱን የዘር የበላይ ሌላውን ዘር የበታች አድርጎ ማየቱን ላንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እስካላቆመ ድረስ ፍልስፍና ኋላቀርና የተተወ ይሆናል። በየትም የዓለማችን ጫፍ ጦርነት አለ። በትኛውም ሐገርና መንግስት የመጀመሪያና ሁለተኛ ዜግነትን የሚባለውን ጉዳይ ማቆም ካልቻለ ሁልጊዜም ቢሆን ጦርነት ይኖራል።” **H.Selassie**
- “ሠው በእንጀራ ብቻ አይኖርም። በአጠቃላይ ሠው ማለት የነፍስና የሃሳብ ውሁድ ነው። አጠቃላዩ ትምህርትና የከፍተኛ ትምህርት ከውጫዊው ምግብ ባሻገር የውስጣዊውን የነፍስና የሃሳብ ምግብን ለመስጠት ማለም ይጠበቅበታል።” **H.Selassie**
- “እንደ አፍሪካዊ ያለፈውን ታሪካችንን መገንዘብ አዲስ ማንነትን ለመመስረት አስፈላጊ ነው።” **H.Selassie**
- “የተማርኩት ይበቃኛል። ከዚህ በላይ ማወቅ አይጠበቅብኝም የሚል ሠው ምንም እንደማያውቅ ይቆጠራል።” **H.Selassie**
- “ለእኔ አትስገዱ! እኔ እግዚአብሔር አይደለሁም! እኔ ሠው ብቻ ነኝ። እኔ ራሴ ለኢየሱስ ክርስቶስ እሠግዳለሁ።” **H.Selassie**
- “ከትንሽ ወይም ከትልቅ መወለድ ሙያ አይደለም። ራስን ከትልቅ ሙያ መውለድ ግን እውነተኛ ሙያ ነው።” **H.Selassie**
- “የሆነ ሠው በሙስሊምና በክርስቲያን መካከል ልዩነት አለ ካለ፤ ይሄ ሠው የኢትዮጵያ ጠላት ነው።” **H.Selassie**
- “አሸናፊ ለመሆን አንድም ሰዉ እንኳ በማይተማመንብህ ወቅት በራስህ ማመን አለብህ።” **ሹገር ሬይ ሮቢንሰን**
- “የራስህን የህይወት እቅድ ዲዛይን ካላደረግክ ዕጣ ፈንታህ የሚሆነው በሌሎች እቅድ ውስጥ መኖር/መውደቅ ይሆናል።” **ጂም ሮን**
- “ጨለማን ጨለማ አይገልጠውም፣ ብርሃን እንጂ፤ ጥላቻንም ጥላቻ አይፍቀውም፣ ጥላቻን ማጥፋት የሚችለው ፍቅር ብቻ ነው።” **ማርቲን ሉተር ኪንግ**
- “የስኬትን ቀመር (ፎርሙላ) ልሰጥህ አልችልም፤ ነገር ግን የዉድቀት ቀመር ልሰጥህ እችላለሁ፤ ያም ሁሉንም ሰዉ ለማስደሰት መሞከር ነዉ።” **ሀርበርት ስዎፕ**
- “የማይገለን የህይወት ፈተና፣ ጠንካራ ያደርገናል።” **ፍሬደሪክ ኒቼ**
- “በዓለም ላይ ራስህን ከማንም ጋር አታወዳድር፤ ያን ካደረክ ራስህን እየሰደብክ ነው።” **አለን ስትራክ**
- “ስለ አንድ ሰው ባህሪ ማወቅ ከፈለግክ ስልጣን ስጠው።” **አብርሃም ሊንከን**
- “ሌሎች ሰዎች ምን ያህል በጣም ጥቂት ጊዜ (ከስንት አንዴ) ስለአንተ እንደሚያስቡ ብታውቅ ኖሮ፤ ሌሎች ስለ እኔ ምን ያስባሉ ብለህ አትጨነቅም ነበር።” **ኤልኖር ሮዝቬልት**
- “እራስን ሁን፣ የሚሰማህንም ተናገር፣ ምክንያቱም እራስህን በመሆንህ ቅር ለሚላቸው ሰዎች ቦታ/ደንታ መስጠት የለብህም፤ የሚበጁህ ሰዎች ደግሞ እራስህን በመሆንህ ቅር አይሰኙምና።” **ዶ/ር ሱስ**
- “ቅን አሳቢ ሰው ጽጌረዳ አበባው ላይ ሲያተኩር ጨለምተኛ ሰው ግን ጽጌረዳውን በመዘንጋት እሾሁ ላይ ያተኩራል።” **ካህሊል ጂብራን**
- ሳንቲም ብዙ ድምፅ ያሰማል፤ ገንዘብ ግን ምንም አያሰማም፤ ስለዚህ ዋጋህ ሲጨምር ወሬህን እየቀነስክ ና!” **ሼክስፒር**
- “ለቀላል ህይወት አትፀልይ፤ ሆኖም አስቸጋሪውን ለመቋቋም ጥንካሬ እንዲኖርህ ፀልይ።” **ብሩስ ሊ**
- ”ሌላን ሰው ለመሆን መፈለግ የራስን ማንነትን ማባከን ነው።” **ኩርት ኮቤይን**
- “የዚህች አለም ታሪክ ማለት በራሳቸዉ የሚያምኑ የጥቂት ግለሰቦች ታሪክ ማለት ነዉ።” **ስዋሚ ቪቬካናንዳ**
- ”የወደፊቱን ለመተንበይ የተሻለው ዘዴ፤ ወደፊትን መፍጠር ነው።” **አለን**

- “ፈጣሪ ካልፈታው ገንዘብ ችግርህን አይፈታውም ፈጣሪ ካልሞላው ሰው ጎንህን አይሞላውም ፈጣሪ ካልገለጸ እውቀት ጥበብ አይሆንም” (**Unknown)**
- “ይቺ ዓለም ለሁሉም እኩል ናት። ዛሬ ብታገኝ ነገ ታጣለህ ዛሬ ብታሸንፍ ነገ ትሸነፋለህ። ለሁሉም ጊዜ አለው የሚባል መዶሻ አለ። መልካምነት ዋጋ ያስከፍልሃልና ሁሌም ፍጹም መልካም ሰው ሁን።” (**Unknown)**
- “ህይወትህ ትርጉም እንዲኖራት ዓላማ ይኑርህ።” (**Unknown)**
- “የአንተነትህ ትልቁ ምዕራፍ ከእውቀትህ በላይ ስራህ መሆኑን አትርሳ።” (**Unknown)**
- “ንጹህ ልብ ልክ እንደ አበባ ናት! ፍሬ ባናገኝባትም ውበቷ ግን እጅግ ማራኪ ነው።” (**Unknown)**
- “የውድቀት መጀመሪያ ራስህን አዋቂና ብቸኛ አድርጎ ማሰብ ነው።” (**Unknown)**
- “ፍጻሜህ እንዲያምር ራስህን አታመጻድቅ ሁሌም ከስህተትህ ለመታረም ፈቃደኛ ሁን ጥፈፋትህን አሜን ብለህ መቀበልህ ክብርህን የሚጎዳብህ አይምሰልህ።” (**Unknown)**
- “ጠቢብ ሰው እንኳን ከራሱ ከሰው ስህተት ተምሮ ራሱን ይጠብቃል ይመለሳልና።” (**Unknown)**
- “በህይወት ውስጥ አንዱ ሲታወር አንዱ መሪ መሆን አለበት።” (**Unknown)**
- “እውነትነ የሚናገር ሰው አፉ ክፉ ይመስላል ልቡ ግን ንጹህ ነው።” (**Unknown)**
- “ህይወት በመደጋገፍ የተሞላች ናትና ወንድምህን ለመርዳት ወደኋላ አትበል!” (**Unknown)**
- "ሕይወት ልክ እንደ ክራር ጨዋታ ነው። አጨዋወቱን ያወቀ ጥሩ ሙዚቃ ይሰማል። ያላወቀ ደግሞ ዝብርቅርቅ ጩኸቷን ለመስማት ይገደዳል።" **ካህሊል ጂብራን**
- "ማሰብ ካልጀመርክ የትኛውም ሽቶ የሕይወትህን መጥፎ ሽታ ሊደብቅ አይቻለውም።" **ዲዮጋን**
- "ፈገግታዋን ይቀጥሉ እና አንድ ቀን ህይወት እርሶን ማበሳጨት ይደክማታል።” (**Unknown)**
- "ውሀ ቅርፁን ከመያዣው ጋር እንደሚያስማማ ሁሉ ብልህም ራሱን ከሁኔታው ጋር ያስማማል።" **(Unknown)**
- "ህይወት ጨካኝ መምህር ነው! ምክንያቱም መምህር አስተምሮ ነው የሚፈትነው ህይወት ግን ፈትኖ ነው የሚያስተምረው።" **ስብሃት ገ/እግዚአብሔር**
- "አንድ ሰው ስትተዋወቀው በልብሱ ልትመዝነው ትችላለህ፣ ስትለየው ግን በአስተሳሰቡ ትመዝነዋለህ።” **Unknown**
- “የአንድን ወንዝ ጥልቀት በሁለት እግሩ የሚለካ ሞኝ ብቻ ነው።” **አፍሪካ**
- “የተሰበረ እጅ ሊሠራ ይችላል፤ የተሰበረ ልብ ግን ከቶውንም ሊሰራ አይችልም።” **ፔርሺያ**
- "ህይወትህን ለመኖር የምትችልባቸው ሁለት መንገዶች ብቻ አሉ። አንዱ ምንም ነገር ተአምር እንዳልሆነ በማሰብ ሲሆን ሌላኛው ደግሞ ሁሉም ነገር ተአምር ነው ብሎ በማሰብ ነው።" **አልበርት አነስታይን**
- "ራሱን የሚያፈቅር ሠው ወደ እውነተኛው ፍቅር ለመድረስ የመጀመሪያውን እርምጃ ተራምዷል።" **ኦሾ**
- "ገንዘብ የማይገዛው ነገር እስከሌለህ ድረስ ባለፀጋ አይደለህም።" **ሱፊስቶች**
- “ፍቅር ሰው የአምላኩን ሀይል እንዲያይ የሚያስችለው መንፈሳዊ ዕውቀት ነው።” **ካህሊል ጂብራን**
- "በወጣትነትህ ያላወቅኸውን በሽምግልናህ አታስተምረውም።" **ቡድሃ**
- "አንተ ከምታውቀውና ከምታምነው በላይ ሌላ ማንነት አለህና እሱን ፈልገህ አግኝ።" **ጲላጦስ**
- "የሴቶች ዋነኛ ችግር ወንዶች ስለሴቶች የሚኖራቸውን ፅንሰ ሃሳብ አሟልተው ለመገኘት ሁልጊዜም መጣራቸው ነው።" **ላውረንስ**
- “ፍ/ቤት በተወሰኑ ዳኞች የተገነባ ሲሆን የዳኝነቱን ሥራ የተሻለ ጠበቃ ላለው ሰው መፍረድ ብቻ ነው።” **ሮበርት ፍሮስት**

- "የራስን ስሜት መቆጣጠር አለመቻል አቅጣጫ ጠቋሚ በሌለው መርከብ እንደመጓዝ ነው።" **ማህተመ ጋንዲ**
- "ተኩላዎች ዳኞች ሆነው በተሰየሙበት ችሎት የበጎች ቀጣይ እጣፋንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም።" **ይዲሽ**
- "ሐብታሞችን ድሃ በማድረግ ድሆችን ሃብታም ማድረግ አይቻልም።" **ዊንስተን ቸርችል**
- "ሃሳባቸውን መለወጥ የማይችሉ ሰዎች፣ ምንም ነገር ሊለውጡ አይችሉም።" **ጆርጅ በርናርድ ሾው**
- "ብልህ ሰው አንድ ቃል ሰምቶ ሁለት ይረዳል።" **አይሁዶች**
- "ብዙ ጊዜ ብቻህን መሆን ካልቻልክ ከሌሎች ጋር ያለህ ግንኙነት ሁሉ የውሸት ነው። ይሄ ብቸኝነትህን ለመሸወድ የምታደርገው እንጂ ሌላ ነገር አይደለም።" **ኦሾ**
- "መሻሻል ማለት መለወጥ ማለት ነው። ፍፁም መሆን ማለት ደግሞ ሁልጊዜ መለወጥ ማለት ነው።" **ዊንስተን ቸርችል**
- "በዕውቀት ላይ የሚደረግ ኢንቨስትመንት የላቀ ትርፍ ያስገኛል።" **ቤንጃሚን ፍራንክሊን**
- "በአቋሙ የፀና ሰው ከሆንክ አቋምህን ሊያስቀይሱ ከሚጥሩ ሰዎች ጋር ኣንገት ለኣንገት ተናንቀህ የክብር ሞት ትሞታለህ። በተቃራኒው አቋም የሌለው ወለዋይ ከሆንክ ደግሞ በጌቶችህ መዳፍ ሥር ወድቀህ በየቀኑ የቁም ሞት ትሞታለህ።" **ባልዛክ**
- "ጨለምተኛ ሠው በየትኛውም አጋጣሚዎቹ ችግሮች ይታዩታል፤ መልካም አሳቢ ግን በችግሮች ውስጥ መልካም አጋጣሚን ያማትራል።" **ዊንሰተን ቸርችል**
- "አሁን ያለህበትን ሁኔታ እያየህ ለምን ትንሽ ሆንኩኝ? ብለህ የምትቆጭ ከሆነ መቼም ቢሆን ትልቅ ሰው ልትሆን አትችልም። ሁሉም በዓለም ላይ ያሉ ትልቅ ሰዎች መጀመሪያ ትንሽ ነበሩ። ማንም የማያውቃቸው ተራ ሰው ነበሩ።" (**Unknown)**
- "በጊዜ ሂደት ግን እውቀታቸውን እያዳበሩ አስተሳሰባቸውን እያሰፉ እምነታቸውን እያጠነከሩ ፍልስፍናቸውን እያጎለበቱ አመለካከታቸውን እያቀኑ ራእያቸውን እያገዘፉ ውሳኔያቸውን እያጠነከሩ አሁን ያላቸውን ትልቅ ማንነት ፈጠሩ ። አሁን ያላቸውንም የማይደረስበት የመሰለ እጅግ ትልቅ ማንነትንም ፈጠሩ።" (**Unknown)**
- **ሊዮ ቶልስቶይ** እንዳለው "ትልቅ ሰው ትልቅ ሆኖ አይወለድም፤ ትልቅ ለመሆን ራሱን ያሳድጋል እንጂ።" **አዎ!** ማንም ትልቅ ሆኖ አልተወለደም። ባራክ ኦባማ ፕሬዘዳንት ሆኖ አልተወለደም። ራሱን ግን የአሜሪካ መሪነት አዘጋጀ። የመጀመሪያ የአሜሪካ ጥቁር ፕሬዘዳንትም ሆነ ። ሀይሌ ገ/ስላሴ ሯጭ ሆኖ አልተ ወለደም። ግን ራሱን ለረጅም ርቀት ሯጭ ንጉስነት አዘጋጀው። የ27 የዓለም ሪከርዶችንም ሰባበረ። ሁለቱን **ለምሳሌ፣** አየን እንጂ ሁሉም ጀግኖች በአንድ ወቅት ራሳቸውን እንኳን መቆጣጠር የማይችሉ ህጻን ነበሩ። የሽንታቸውን ጨርቅ እንኳን እናታቸው ወይ አባታቸው የሚቀይርላቸው የወላጆቻቸው ጥገኛ ነበሩ። ግን እነዚ ሰዎች ራሳቸውን ከጥገኝነት ሂወት አውጥተው አሁን ያሉበት ትልቅ ቦታ ደርሰዋል።
- "አያችሁ ህይወት ሁላችንንም በልጅነታችን እንዴት ከጥገኝነት እንደምንላቀቅ አስተምራናለች። አሁን ያለን ሂወት ላይ ያንን በልጅነታችን እንዴት ራሳችንን ከጥገኝነት እንዳወጣን በማስተማር ለድል እራሳችንን እናዘጋጅ።" (**Unknown)**
- "በልጅነታችን እየዳህን መሄድ ስንጀምር ምንም ያህል ጊዜ ብንወድቅ ተስፋ አንቆርጥም፤ እንደገና እንሞክራለን እንጂ ። ትልቅ ሰው ለመሆንም ያለው ትግል ይህ ነው። በነገሮች ተስፋ አለመቁረጥ።" (**Unknown)**
- "ምንም ያህል ጊዜ ብትወድቁ ለመነሳት የምታደርጉትን ጥረት አለማቋረጥ። ግን የሆነ ጊዜ ላይ ተስፋ ቆርጣችሁ ከወደቃችሁበት ለመነሳት ጥረት ማድረግ ስታቆሙ ያኔ ትልቅነታችሁን ትገሉታላችሁ።" (**Unknown)**
- የምታውቋቸው ትላልቅ ሰዎች ሁሉ ይህንን ተስፋ የሚያስቆርጥ ክልል በድልማለፍ የቻሉ ናቸው። እስቲ አንተም ይህንን ህይወትህ እጅግ የምትፈተንበትንዘመንህን እለፈውና "ትልቁን

አንተነትህን ፍጠረው!" ውስህ ትልቅነትህ አለ። ግን ትልቅነትህ በምኞት ብቻ አይገለጥም። ትልቅነትህ ትግልህን ይፈልጋል። ትልቅነትህ ጥረትህን ይፈልጋል። ትልቅነትህ ብርታትህን ይፈልጋል። ትልቅነትህ ታጋሽነትህን ይፈልጋል። ትልቅነትህ ድፍረትህን ይፈልጋል። ትልቅነትህ ቆራጥነትህን ይፈልጋል። እነዚህን ሁሉ በአንድ ላይ ስታቀናጃቸው ትልቁ ተአምር ይፈጠራል። ትልቁ አንተነትህም እውን ይሆናል።

- ሌሎች ምሳሌ የሚያደርጉትም ትልቁ ማንነትህ ለዓለም ይበረከታል። አንተ ትልቅ የምትሆነው በውስጥህ ያለውን ትልቅነት ማየት ስትችል ነውና ውስጥህን ተመልከት። ፈጣሪንም ይህንን ሁሉ ትልቅነት ስለሰጠህ ከልብህ አመስግን! አመስግኚ!
- "ድልድዩን ከመስበርህ በፊት ዋና እንደምትችል እርግጠኛ ሁን።" **ኬንያ**
- "አዲሱ ባልዲህ ውሃ የሚይዝ መሆኑን ሳታረጋግጥ አሮጌውን አትጣል።" **ስዊድን**
- "አንድን ሰው ልብስ ከመጠየቅህ በፊት መጀመሪያ ለራሱ ምን ዓይነት ልብስ እንደለበሰ ልብ ብለህ ተመልከተው።" **ቤኒን**
- "ውሸት መላውን ዓለም ትዞራለች ፤ እውነት ደግሞ እቤቷ ቁጭ ብላ የሚሆነውን ትጠባበቃለች።" **ፈረንሳይ**
- "ጠማማ ዕድል ያለው ሰው ወደ ወንዝ አትላከው።" **ይዲሽ**
- "በጓደኛህ ግንባር ላይ ያረፈውን ዝምብ ለማባረር ብለህ መጥረቢያ አትጠቀም።" **ቻይና**
- "አይጥ በድመት ላይ ከሳቀች አቅራቢያዋ ጉድጓድ አለ ማለት ነው።" **ናይጄሪያ**
- "ውሃ ውስጥ ሰምጠህ የመሞት ፍላጎት ካለህ በጎደለው ኩሬ ውስጥ እየተንቦራጨክ ራስህን አታሳቃይ።" **ቡልጋሪያ**
- "ተኩላዎች ዳኞች ሆነው በተሰየሙበት ችሎት ላይ የበጎች ቀጣይ ዕጣ ፈንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ለመገመት አያዳግትም።" **ይዲሽ**
- "እንቁላል የሞላ ቅርጫት ተሸክመህ አትጨፍር።" **ጊኒ**
- "አንተ ጠንክረህ በዝምታ ስትሰራ ፣ ስኬትህ ጮኾ ይናገራል።" **ፍራንክ ኦሽን**
- "በሕይወትህ ከዚህ በፊት ያልነበረህ አዲስ ነገር ለማግኘት ከፈለክ፣ አዲስ ሰርተኸው የማታውቀው ስራ ለመስራት መፍቀድ ይኖርብሀል፡" **ቶማስ ጄፈርሰን**
- "ትክክለኛ ሕይወት የሚጀምረው የምኞት ቀጠና ሲያልቅ ነው።" **ዶናልድ**
- "አንተን ሁለት ነገሮች ይገልፁሀል። የመጀመሪያው ምንም የሌለህ ጊዜ የምታሳየው ትዕግስት ሲሆን ሁለተኛው ሁሉም ሲሟላልህ የምታሳየው ጠባይ ነው።" **ኢማም አሊ**
- "በምድር ላይ ትልቁ አስደሳች ነገር ሰዎች አትችልም ያሉህን ሰርተህ ማሳየትህ ነው።" **ዋልተር ባግሆት**
- "ወንዝ ድንጋይ ቦርቡሮ የሚገባው ሀይለኛ ስለሆነ ሳይሆን ያለማቋረጥ ስለሚፈስ ነው። "**ጂም ዋትኪንስ**
- "ህልምህን ለመፈፀም ብዙ ጊዜ በመውሰዱ ተስፋ አትቁረጥ ምክንያቱም ጊዜ ስለሚበር አርቀህ ያየኸው ህልም በፍጥነት መፈፀሙ አይቀርም።" **አርል ኒተንገል**
- "ሰዎች በምታቅደው እቅድ ካልሳቁ ወይም ካልተገረሙ እቅድህ ትንሽ ነው ማለት ነው።" **አዚም ፕሪሚጂ**
- "ለመጀመር ትልቅ መሆን አይጠበቅብህም ነገር ግን ትልቅ ለመሆን መጀመር አለብህ።" **ዚግ ዚግላር**
- "ደስተኛ የሆነ ሕይወት ለመኖር ከፈለክ ከሁኔታና ከሰዎች ጋር ሳይሆን ከአላማና እቅድህ ጋር ተጣበቅ።" **አልበርት አንስታይን**
- "አንተ የምርጫህ ውጤት እንጂ በአንተ ላይ የሚደርሱት ነገሮች ውጤት አይደለህም።" **ካርል ጉስታ**
- **"**ባለትላልቅ አእምሮ ሰዎች በሃሳብ ላይ ይወያያሉ፣ መካከለኞች በ ድርጊት / ሁኔታዎች ላይ ይወያያሉ ባለትናንሾች ቁጭ ብለው ሰው ያማሉ።"**ሪያኖር ሮዝቪልት**

- ″እስካልቆምክ ድረስ በምንም ዝግታ ብትጓዝ መድረስህ አይቀርም።″ **ኮንፊሺየስ**
- “ችሎታ ያለው ሰው ምንም ስራ እስካልሰራ ድረስ ችሎታ በሌለው ጠንካራ ሰራተኛ ይበለጣል።” **ቲም ኖትኪ**
- ″ከውድቀት ይልቅ ጥርጣሬ የነገ ህልምን ይገላል።″ **ሱዚ ካስም**
- “እውቀት ብቻ አይበቃም ተግባራዊ ካልተደረገ በስተቀር ፣ ፍቃደኛነት ብቻ አይበቃም ካልተሰራ በስተቀር።” **ብሩስ ሊ**
- “የዛሬ አመት በዚህ ሰአት ምናለ ምናለ ከአመት በፊት በጀመርኩ የምትላቸው ብዙ ነገሮች ይኖራሉ።” **ካረን ላንብ**
- “ጀማሪዎቹ ለመስራት ከሞከሩት ጊዜ በላይ አለቃቸው ብዙ ጊዜ ወድቋል።” **ስቴፈን ማክክሬን**
- “ብዙ ጊዜ ላለመስራት የምትተዋቸው ስራዎች በውስጣቸው ብዙ እድልን የያዙ ናቸው።” **ሮቢን ሻርማ**
- “አለም የምትቀየረው በአንተ አስተያየት ሳይሆን በአንተ ተግባራዊ ስራ ነው።” **ፖል ኮኢልሆ**
- “መተንፈስ እንደምትፈልግ ያህል ለስኬታማ ሕይወት ጥልቅ ፍላጎት ካለህ ይሳካልሀል።” **ኤሪክ ቶማስ**
- “ፊትህን ወደ ፀሀይ ስታዞር ጥላህ ከኃላህ ይወድቃል።” **የማዎሪ አባባል**
- “99% የሚሆኑ ሰዎች ሀሳብህን ከተጠራጠሩህ ፣ እጅጉን ስተሀል አልያም ታሪክ ልትሰራ ነው።” **ስኮት ቤልስካይ**
- “ፈፅሞ አትድከም ምክንያቱም አሁን እጅግ ከባድ የሆነብህ ስራ ከጥቂት ጊዜያት በኃላ ለሌላ ስራ መሟሟቂያ ይሆናል።” **ያልታወቀ ሰው**
- “ሕይወት ልክ እንደ ካሜራ ነች። የምትፈልገውና ጠቃሚ ነገር ላይ ስታተኩር ሌሎቹ የማያስፈልጉት እየደበዘዙ ይሄዳሉ።”
- “መኖር ካለመኖር ሳይሻል አይቀርም ከመኖር ተስፋ አለ፤ ካለመኖር ምንም።” **ሼክስፒር**
- “ገንዘብ ካጣህ ምንም አላጣህ ጊዜ ካጣህ አንዳች ነገር አጣህ፤ ተስፋ ካጣህ ግን ሁሉን ነገር አጣህ።” **ሼክስፒር**
- “ሰይጣን ለዘዴው ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል።” **ሼክስፒር**
- “ሕይወት ራሷን ላለመጣል በምትቀይሳቸው አቅጣጫዎች ውስጥ ማለፍ የግድ ነው።” **ሼክስፒር**
- “ምን እንደሚሆን እናውቃለን ምን እንደምንሆን ግን አናውቅም።” **ሼክስፒር**
- “የቀንን ውበት አይቶ ለማድነቅ ጨለማን መጠበቅ ያስፈልጋል።” **ሼክስፒር**
- “ነፃ ሰዎች ነፃ ሆነው ነው የሚኖሩት የሚገዛቸው ገንዘብና ሃይል የለም።” **ሼክስፒር**
- “አዋቂዎች ልበ ቀናዎችና ሰብአዊነት የተዋሃዳቸው ሰዎች ሁሉ ምህረት አድራጊዎች ናቸው።” **ሼክስፒር**
- “ፍጥነት የሌለው ሩጫ እንቅልፍ የሌለው መኝታ ትርፉ ድካም ነው።” **ሼክስፒር**
- ″ማፍቀር ሀጢአት አይደልም ነገር ግን በፍቅር ስም በሰው ስሜት ላይ መጫወት ትልቅ ሀጢአት ነው።″ **ሼክስፒር**
- “ከተብቃቃህ ትንሹ ብዙ ነው ⇨ ከተስገበገብክ ብዙው ትንሽ ነው ⇨ ከወደድክ ሩቁ ቅርብ ነው ⇨ ከጠላህ ቅርቡ ሩቅ ነው።” **ሼክስፒር**
- ″ካንቺ የበለጡ ቆንጆዎች እንዳሉ አውቃለሁ ⇨ ነገር ግን የወደድኩሽ በአይኔ ሳይሆን በልቤ ነው።″ (**Uknown)**
- “የሚወድህ ሰው ለራሱ ማድረግ የማይችለውን ነገር አንተን ስለሚወድህና ስለምያፈቅርህ ብቻ ለአንተ ግን ያደርገዋል።” (**Uknown)**
- “ሁለት ከባባድ ጀግኖች ትግስትና ጊዜ ናችዉ።” (**Uknown)**
- “የመፈጠራችን ዋና ዓላማ ሌሎችን ለመርዳት ነው፤ መርዳት ካልቻልን ግን ቢያንስ አንጉዳቸው።” **Uknown**

- ✧ ”ጨለማን ጨለማ አይገልጠውም፣ ብርሃን እንጂ፤ ጥላቻንም ጥላቻ አይፍቀውም፣ ጥላቻን ማጥፋት የሚችለው ፍቅር ብቻ ነው።” (**Uknown)**
- ✧ "ስራ የፈታ አዕምሮ የሰይጣን ፋብሪካ ነው።" **ረቂቅ አሻራ**
- ✧ "ፍቅር ከስራ ጋር እንጂ ብቻውን አያምርም።" **ኢቫንጋዲ**
- ✧ "አስቀድሞ የበሰለ ፍሬ አስቀድሞ ይጠፋል።" **ጣምራ ጦር**
- ✧ "በቅናት የማትቃጠል ሴት የለችም።" **አምሳል**
- ✧ "ወንዶች ሁሉ ባሎች አይደሉም።" **ትንሳኤ**
- ✧ "ሴት ልጅ ጨክና የቆመችበት ቁስል አያማትም።" **አቻሜ**
- ✧ "ዝምታ በራሱ ቋንቋ ነው።" **የዘርሲዎች ፍቅር**
- ✧ ''ቅናት ከፍቅር ጋር አብሮ ይወለዳል። ነገር ግን አብሮ አይሞትም።" **የቅናት ዛር**
- ✧ "ሴቶች ትሁቶች ናቸው። ከወደዱ ሁለመናቸውን አሳልፈው ይሰጣሉ።" **ሰንሰለት**
- ✧ "ለመኖር መድፈር ያስፈልጋል።" **ላምሮት**
- ✧ "ለዚህች አለም ክብደት ተገቢ በሽታዋ ነው።"
- ✧ **“**የጥንቃቄዎች ሁሉ ንጉስ ዝምታ ነው!! የቃየል መስዋት።” (**Uknown)**
- ✧ **“**አንዱ ወንድ ገልቱ ያላትን ሴት ለሌላኛው ወንድ ዘውድ ትሆናለች” (**Uknown)**
- ✧ ”አትቸኩል። በዚህ ዓለም ምን የሚያስቸኩል ነገር አለ? ባይቸኩሉም ህይወት ራሷ አጭር ናት።” (**Uknown)**
- ✧ ”በመወሰንና በማድረግ መካከል ድልድይ የሌለው ገደል አለ።” (**Uknown)**
- ✧ "ጥሩ ምላስ ስዉር ማህተም ያላት የዘመኑ ሰርተፍኬት ናት።" (**Uknown)**
- ✧ "ፍቅር ባይኖር ምድራችን ከመቃብር የማትሻል ትሆን ነበር።" **ሮበርት ብሮዊንግ**
- ✧ "እምነት ባለዩት ነገር ማመን ሲሆን ሽልማቱም ያመንቱን ነገር ማየት ነው።" **ጳጳስ ኦገስቲን**
- ✧ "ፍቅር የተሟላ ህግ ነው።" **ጳውሎስ**
- ✧ "የፍቅር መስፈሪያው ስፍር አልባ ፍቅር ነው።" **በርናንድ ሾው**
- ✧ "ወሳኙ ነገር የገጠመህ ጉዳይ ሳይሆን ምላሽ የሰጠህበት መንገድ ነው" **ኢፒክፌተስ**
- ✧ "ማለም የፈጠራ መነሻ ነው፤ የምትፈልገውን ታልማለህ፣ ያለምከውን ትመኛለህ፤ በመጨረሻም የተመኘኸውን ትፈጥራለህ።" **ጆርጅ በርናንድ ሾው**
- ✧ "በቀላሉ ልናገኛቸው የምንችለውን መልካም ነገሮች የሚያሳጡን ጥርጣሬያችን ነው።" **ዊልያም ሼክሲፒር**
- ✧ "በሚታይ ና በሚነካ ነገር ማመን በፍፁም እምነት አይደለም። ባልታየው ማመን ግን አሸናፊነትና መታደል ነው።" **አብራሀም ሊንከን**
- ✧ "ወሳኙ የምትሰጠው መጠን ትንሽነትና ትልቅነት ሳይሆን በምትሰጠው ነገር ላይ የምትጨምረው ፍቅር ነው።" **ማዘር ቴሬዛ**
- ✧ "አለማችን በጣም እየተጎዳች ያለችው ከመጥፎ ሰዎች ክፋት ሳይሆን በጥሩ ሰዎች ዝምታ ነው።" **ናፖሊዮን**
- ✧ "ከክፋት ስትርቅ ሰላምህን ታበዛለህ፤ ቅንና መልካም ስትሆን ደግሞ ከጭንቀትና ከጸጸት ትድናለህ።" **ዊሊያም ሼክስፒር**
- ✧ "የውሸት ጓደኛና ጥላ ሁለቱም አንድ ናቸዉ። ሁለቱም የሚቆዩት ፀሐይ እስካለች ድረስ ነው።" **ዊሊያም ሼክስፒር**
- ✧ "በብርሃን ስትሆን ሁሉ ነገር ይከተልሃል። ጨለማ ውስጥ ከሆንክ ግን ጥላህ እንኳን አይከተልህም።" **ሂትለር**
- ✧ "ሳንቲም ብዙ ድምፅ ያሰማል። ገንዘብ ግን ምንም አያሰማም። ስለዚህ ዋጋህ ሲጨምር ወሬህን እየቀነስክ ና!" **ዊሊያም ሼክስፒር**
- ✧ "ደሀ ሆነህ ብትወለድ ጥፋቱ ያንተ አይደለም ደሀ ሆነህ ብትሞት ግን ጥፋቱ ያንተ ነው።" **ቢል ጌትስ**

- ✧ "ከሰዎች ጋር ሮጠህ ያልደረስክበት ነገር ካለ ወደ ተነሳህበት ተመልሰህ ከፈጣሪህ ጋር መሮጥ ጀምር፣ ያኔ ካሰብክበት ሳይሆን ካሰበልህ ቦታ ትደርሳለህ።" (**Unknown)**
- ✧ **"**በአብዛኛው ጊዜ ሴቶች የፍቅርን ትርጉም የሚጠፋባቸው በውበታቸው ማምለክ ሲጀምሩ ሲሆን ወንዶች ደግሞ በገንዘባቸው ማምለክ ሲጀምሩ ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "መጀመሪያ ለራስህ ራስህ መሆን ስትጀምር ለማን ምን መሆን እንዳለብህ ትገነዘባለህ።" (**Unknown)**
- ✧ **"**የሰው ልጅ የማሰብ ችሎታው ሲጨምር የጓደኞቹን ብዛት ይቀንሳል።" (**Unknown)**
- ✧ **"**ዝቅተኛ እውቀት ባለህ ቁጥር የምትተኛው እንቅልፍ ከፍተኛ ይሆናል።" (**Unknown)**
- ✧ **"**ጓደኛን አለማመን ከመካድ የከፋ ነው።" (**Unknown)**
- ✧ "የራስህን ትኩስ እንጀራ ለመጋገር ስትል የሌላውን ቂጣ አትርገጥ።" (**Unknown)**
- ✧ "አንዳንድ ሰዎች የሚወድቁት ሌሎችን በሁለት እግሮቻቸው ለመርገጥ ሲጣጣሩ ነው።" (**Unknown)**
- ✧ **"**ሰው ከጊዜ እና ከማጣት ብዙ ይማራል።" (**Unknown)**
- ✧ "አንዳንዴ ሽንፈትም ከድል የበለጠ ዋጋ አለው/ ከማሸነፍ ይልቅ በመሸነፍ ውስጥ ብዙ እውቀት አለ።" (**Unknown)**
- ✧ "ሠው የበለጠ እያገኘ በሄደ ቁጥር የበለጠ ስግብግብ እየሆነ ይሄዳል።" (**Unknown)**
- ✧ "ሠዎች ትርጉም ያለው ሥራ መስራት ካልቻሉ የሞኖር ትርጉምም ይጠፋባቸዋል።" (**Unknown)**
- ✧ "የሰው ልጅ ከደስታው ይልቅ የሀዘኑን ጊዜያት መቁጠር ይወዳል።" (**Unknown)**
- ✧ ባንኮች ዝናብ ሳይኖር ዣንጥላ ያበድሩህና መዝነብ ሲጀምር ግን ዣንጥላውን ይነጥቁሃል።" (**Unknown)**
- ✧ "አዋቂ ሆኖ ለመታየት የምናደርገው ጥረትና ከንቱ ድካም አላዋቂ አድርጎ ያስቀረናል።" (**Unknown)**
- ✧ "አንዳንድ ሰዎች የሌሎችን ድክመት በመናገር ራሳቸውን ጠንካራ ያስመስላሉ!!" (**Unknown)**
- ✧ "ሰው ጉብዝናህን በሹክሹክታ ድከመትህን በኡኡታ ያውራልና አትጨነቅ !!" **(Unknown)**
- ✧ "አላስተዋይ ሰው ብትችል ዝም በል ያለዚያ ግን ያንተን ማንነት ከጀርባህ ሸሽገህ ስለ ሰው አታውራ!!" (**Unknown)**
- ✧ "በስንዴው ማሳ ላይ እራሳቸውን ከፍ ከፍ ያደረጉ ሁሉ እንክርዳዶች ናቸውና ራስክን አቀርቅር !!" (**Unknown)**
- ✧ "ምንም ቢሉህ ደካማ አስተሳሰብ ያለው ሰው እዘንለት እንጂ አትዘንበት ምክንያቱም የሚያስበው የሚያቀውን ያህል ነው! እሱን በመጥላት የምታባክነው ጊዜ ራስህን ውደድበት !!" (**Unknown)**
- ✧ "በራስ መተማመን ማለት ሌሎች ሲቀልዱብህ እና ሲያሾፉብህ በዝምታ ማለፍ ነው ! ለምን ብትል አንተ ማን እንደሆንክ እና እነሱ ማን እንደሆኑ ጠንቅቀህ ስለምታውቅ ነው።" **(Unknown)**
- ✧ "ከአንተ ጀርባ ሆነው ስለሚያወሩ ሰዎች አትጨነቅ እነሱ የራሳቸውን የህይወት መንገድ መስመር ተስኗቸው የአንተን ስህተት በመፈለግ የተጠመዱ ናቸው። ስለ እነሱ አትጨነቅ ምክንያቱም አንተ ሰዎች ምን ይሉኛል ብለህ የምትጨነቅ ከሆነ የሰዎች እስረኛ ነህ!" **(Unknown)**
- ✧ "ስራህ ከበረዶ 10ሺ የነጣ ቢሆንም ከሰው ትችት አታመልጥምና ለሰው ወሬ ጆሮ አትስጥ! አንተ እንደገባህ እንጅ ሰዎች እንደ ተረዱህ አትኑር? ከአንተ በላይ ስለ አንተ የሚያውቅ ማንም የለምና !" **(Unknown)**
- ✧ "በህይወታችን ደግ..... ይቀጥላል አንባቢ ካለ ይቀጥላል።" **(Unknown)**
- ✧ "ሰው ከትልቅ ደግነት ይልቅ ትንሿን ስህተትህ የያል የሰው ፍፁም ስለሌለ አትጨነቅ! ለህሊናህ

ስትል ታመን መልካም አድርግ ጥሩ ስራ? ከህሊናህ በላይ አለቃ የለምና!" **(Unknown)**

- "ትክክለኛ ሰው ከሆኑ ማንንም አይተቹ ትችት የሰዎችን ሞሯል ዝቅ ያደርጋል: የበረታን ሰው ማበርታታት የነፍስ አክስጅን መስጠት ነው! ሞሯል ሰውን ከፍና ጠንካራ የሚያደርግ መሰላል ነው!" **(Unknown)**
- "ስህተት ፈላጊ አይሁኑ ከነገሮች ሁሉ ርካሽ ና ቀላል ስራ የሰውን ስህተት ብቻ እየተከታተሉ ማውጣት ነው! በዚህ ምድር ላይ የሌላውን ድክመት ለማውቅ ከመፈጠር ና ከመጣር የበለጠ ትልቅ ድክመት የለም!" (**Unknown)**
- "ሳይታክቱ ፍቅርን ይስጡ ⇄ ለጠላትዎ ይቅርታን ያስበልጡ ⇄ ለተቃዋሚዎ ፅናትን ያበርክቱ ⇄ ለጓደኛዎ ሐሳብዎን ያወያዩ ⇄ ለሚቀርብዎ ደግነትን ያሳዩ።" (**Unknown)**
- "ለሰው ሁሉ ጥሩነትን ይለግሱ ሳይተቹ ይበርቱ ሰዎችን ያሞግሱ መልካምነትን ይላበሱ!" (**Unknown)**
- "ብቸኛው ታሪክ የሚያስተምረን ትምህርት ቢኖር ሰው ከታሪክ አለመማሩን ነው።" **ኤሞርሰን**
- "ሰው ከሰውነት ደረጃ ሊያልፍ ፣ ከመልአክትም ከፍ ሊል እንደሚችል ሁሉ ከእንስሳትም ያነሰ ይሆናል።" **ኦሾ**
- "የአሁን አስተሳሰቦችህ የወደፊት ሕይወትህን ይፈጥራሉ። እጅግ አዘውትረህ የምታስበው ወይም የምታተኩርበት በአብዛኛው ሕይወትህ ሆኖ ይከሰታል።" **ሮሃንዳ ባይረን**
- "ፍቅር ደንቆሮ ሰው ሊያዳምጠውና አይነስውር ሊያነበው የሚችል ቋንቋ ነው።" **ኮልሬጅ**
- "አእምሮ እንደ ሆድ ነው።ያስገባው በሙሉ ሳይሆን ያዋሃደው ነው ዋጋ ያለው።" **ላፎንቴን**
- "ሁላችንም እስረኞች ብንሆንም ልዩነታችን አንዳንዶቻችን የታሰርንባቸው ክፍሎች፣ መስኮቶች ሲኖራቸው የአንዳንዶቻችን ግን የላቸውም።" **ካህሊል ጂብራን**
- "ቅሬታንም ሆነ ሙገሳን ሁለቱንም ተቀበል። ፀሀይም ሆነ ዝናብ አበባን ለማሳደግ ይጠቅማል።" (**Unknown)**
- "ተሳስተህ አታውቅም ማለት አዋቂ ነህ ማለት አይደለም ምንም የማይሞክር ሰውም ከስህተት ነፃ ነውና።" **እንግሊዛውያን**
- "ምርጡን ጠብቅ፤ ለከፋው ተዘጋጅ፤ በመጣው ተጠቀም!" **Zig Ziglar**
- "እያንዳንዱ ቃል ውጤት አለው፤ እያንዳንዱ ዝምታም እንደዛው!" **Sartre**
- "ተሰብሮ ራሱን ከጠገነ ሰው በላይ ምንም ጠንካራ ነገር የለም!" (**Unknown)**
- "ለውጥ ለህይወት ግብዣ እንጂ ስጋት አይደለም!" **Angel Wisdom**
- "ምርጥ አስተማሪዎች ወዴት መመልከት እንዳለብ ያሳዩሃል ምን ማየት እንዳለብ ግን አይነግሩህም!" **Alexandra K. Trenfor**
- "ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ በመንቀሳቀስ ከራሳችን መራቅ አንችልም!" **Ernest Hemingway**
- "አንድ ሰው 'እምቢ' የማይል ከሆነ 'እሺ' ማለቱ ብዙም ትርጉም የለውም!" **Rollo May**
- "በጥንቃቄ ከማድመጥ ትልቅ ነገር ተምሬያለሁ፤ አብዛኛው ሰው በጭራሽ አያዳምጥም!" **Ernest Hemingway**
- "በአሁኑ ጊዜ የህይወት አስከፊው ገፅታ ከማህበረሰቡ ጥበብን የመሰብሰብ ፍጥነት ይልቅ ሳይንስ ዕውቀት እየሰበሰበ መሆኑ ነው!" **Isaac Asimov**
- "ቁስሎችህ ወደአልሆንከው ማንነት እንዲቀይሩህ ዕድል አትስጣቸው!" **Paulo Coelho**
- "ደስታን ማግኘት ቀላል የሚሆነው ላሉብን ችግሮች ማማረር አቁመን ለሌሉብን ችግሮች በሙሉ ማመስገን ስንጀምር ነው!" (**Unknown)**
- "አንዳንዴ ነገሮች በልታሰበ እና ባልታቀደ መልኩ ሲሄዱ፤ ህይወት ተብሎ ይጠራል!" (**Unknown)**
- "ከቤቱ ሲነፃፀር በር ትንሽ ነው፤ ከበር ሲነፃፀር የቁልፍ ጋን ትንሽ ነው፤ ከቁልፉ ጋን ሲነፃፀር መክፈቻ ቁልፏ ከሁሉም ትንሽ ናት ግን ትልቁን ቤት ትከፍታለች በመሆኑም ትንሽ እና ማስተዋል የታከለበት መፍተሄ ትልቁን ችግር ሊፈታ ይችላል!" (**Unknown)**

- ✧ "ሁልጊዜም ውስጣችን ሆኖ በለውጣችን ከሚገረመው የሆነ ክፍል በስተቀር ጊዜ ሁሉንም ነገር ይቀይራል!" **Thomas Hardy**
- ✧ "ጠቢብ የችግሮቹ መንስዔ ውስጣዊ ግጭቶቹ እንደሆኑ ሲያቅ ሞኝ ሁልጊዜም በሌሎች ያላክካል!" **Michael Meade**
- ✧ "ለመፈፀም ያሰብነው ዕቅድ ምንም ይሁን ምን ከአንበሳ የምንማረው ነገር በአቅማችን ሙሉ በሙሉ መተማመን እና ጉዳያችን እስኪጠናቀቅ በጭራሽ መዘናጋት እንደሌለብን ነው!" **Chanakya**
- ✧ "ብሩህ አዕምሮና መልካም ልብ ማራኪው ጥምረት ነው!" **Nelson Mandala**
- ✧ "በአብዛኛው እኛ ሰዎች ሀይላችንን የምናጣበት የጋራ መንገድ ምንም ሀይል እንደሌለን ዘወትር በማሰብ ነው!" **Alice Walker**
- ✧ "መከራው አስገዳጅ ከመሆኑ በፊት የተንከራተተው ሰው መንከራተቱ ይበልጥ ጠቃሚ ነው!" **Seneca**
- ✧ "እውነት ባላንጣ የምትሆነው እንደጓደኛ የመያዝ ጥበብ ለሌላቸው ብቻ ነው!" **Rabindranath Tagore**
- ✧ "ማን ነበርክ ከሚለው በላይ ማን ትሆናለህ የሚለው ጠቃሚ ነው!" (**Unknown)**
- ✧ "ቆም ማለት፣ ማሰብ፣ መናገር። የመጀመሪያ ሁለቱን በርካታ ሰው ይዘላቸዋል!" (**Unknown)**
- ✧ "በእያንዳንዱ ቀን የአቅምህን እያደረግክ ከሆነ ስለወደፊቱ መጨነቅ አይገባም፤ ስለወደፊቱ መጨነቅ የሚመጣው ዛሬን ስታባክን ነው!" (**Unknown)**
- ✧ "ስኬት የደስታ ቁልፍ አይደለም። ደስታ ነው የስኬት ቁልፍ ፣ የምንሰራውን ከወደድነው ስኬታማ እንሆናለን!" **Albert Schweitzer**
- ✧ "የተሳሳተ ዕውቀት ከድንቁርና የበለጠ አደገኛ ነው!" **George Bernard Shaw**
- ✧ "በህይወት ውስጥ የጀመርከውን በመጨረስ ላይ ከሆንክ በጣም ዕድለኛ ነህ!" (**Unknown)**
- ✧ "ማንኛውም ነገር እስካልተቀበልነው ድረስ መቀየር አንችልም፤ ማውገዝ ያፍነው ይሆናል እንጂ ነፃ አያወጣም!" **Carl Jung**
- ✧ "ያለፈው ማጣቀሻ እንጂ የመኖሪያ ቦታ አይደለም!" (**Unknown)**
- ✧ "ሞኝነቱን የተረዳ እውነተኛ ሞኝ አይደለም!" **Zhuang Zhi**
- ✧ "አክብሮት ለማይገባው ከመስጠት ይልቅ ለሚገባው መከልከል ይሻላል!" **Mark Twain**
- ✧ "ሁለቱም እኩል አስካላዋጡ ድረስ ግንኙነትን ማቆየት አይቻልም፤ የአንድ ወገን ጥረት ብቻውን በቂ አይደለም፤ የጋራ ጥረት ይጠይቃል!" **Tony Gaskins**
- ✧ "ሞኝ ሁልጊዜም በህይወቱ ስለሚያደረገው ነገር ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ሲሆን፤ ብልህ ግን ምንጊዜም መፈተሽን ይመርጣል!" (**Unknown)**
- ✧ "ሰበብ በመደርደር ጎበዝ የሆነ ሰው በሌላ በማንኛውም ነገር ጎበዝ ሊሆን አይችልም!" **Benjamin Franklin**
- ✧ "አንዳንድ መልካም ዜናዎችህን ራስህ ጋር አስቀራቸው፤ ሁሉም ሰው ባንተ ልክ ሊደሰት አይችልም!" (**Unknown)**
- ✧ "እያንዳንዱ ቀን መልካም ላይሆን ይችላል ነገር ግን በእያንዳንዱ ቀን ውስጥ የሆነ መልካም ነገር አይጠፋም!!" (**Unknown)**
- ✧ የህይወት ዓላማ ከተፈጥሮ ጋር ተስማምቶ መኖር ነው!" **Zeno of Citium**
- ✧ "ህይወት የሚዛናዊነት ጉዳይ ነው፤ ያለፈውን የመተው እና አዲሱን የመቀበል!" **Helena Kalivoda**
- ✧ "በማንኛውም ሁኔታ ድንቁርና እና ሀይል ከተዛመዱ ለፍትህ እጅግ አስፈሪ ጠላት እንደሚሆኑ የተረጋገጠ ነው!" **James Baldwin**
- ✧ ባለፈው ውስጥ በመኖር መዳን አይቻልም፤ ካለፈው የምንወጣው ሙሉ በሙሉ አሁንን በመኖር ነው!" **Marianne Williamson**

- ✧ "ከፊታችን ያለውን በመመልከት ተጠመደን አሁን ባለንበት ለመደሰት ጊዜ አጣን!" **Calvin & Hobbs**
- ✧ "ወደኋላ ለመመልከት ያለህ ፍላጎት አነስተኛ ሲሆን በትክክለኛው ጎዳና ለመሆንህ ምልክት ነው።" (**Unknown)**
- ✧ "ዳርቻው ከዓይኑ ሲሰወር የማየት ድፍረቱ የሌለው ሰው አዲስ ውቅያኖስ ሊያገኝ አይችልም!" **Christopher Columbus**
- ✧ "ሳይንስ ተጨማሪ አስር ችግር ሳይፈጥር አንድን ችግር አይፈታም!" **George Bernard Shaw**
- ✧ "ለብቻ መቆም ሁልጊዜ የሚያሳየው ብቸኝነትን ሳይሆን የራስህን ነገሮች በራስህ ለመቆጣጠር ብቁ መሆንህን ነው!" **unknown**
- ✧ "አንድ የተማርኩት ነገር ሰዎች የተናገርከውን ይረሳሉ፤ ያደረግከውንም እንደዛው ነገር ግን እንዲሰማቸው ያደረግከውን መቼም አይረሱም!" **Maya Angelo**
- ✧ "አስተማሪ ራሱን ማስተማር እስካልቀጠለ ድረስ እውነተኛ ትምህርት አይሰጥም፤ ሻማ ማብራቱን እስካልቀጠለ ድረስ ለሌሎች ብርሃን እንደማይሰጠው፤ አስተማሪም ዕውቀቱ ላይ አዲስ ነገር ካልጨመረ የተለመደውን ምዕራፍ እየደገመ የተማሪዎቹ አዕምሮ ላይ ከመጫን ውጭ ሊያፈጥናቸው አይችልም!" **Rabindranath Tagore**
- ✧ "እውነተኛ የለውጥ ሂደት ላይ ስንሆን ከዚህ ቀደም የምናውቀው መስሎን አንማርም ያልነውን እንደ አዲስ መማር እንጀምራለን!" **Henry David Thoreau**
- ✧ "አንድ ሰው ትክክለኛውን ጎዳና ካገኘ ለብቻው መሆኑ በጣም ቀላል ነው!" **Arthur Phillips Prague**
- ✧ "የአንድን ሰው ሚስጥር አትንገር ብሎ ከመናገር ይልቅ ዝም ማለት አስተማማኝ ነው!" **Saddi**
- ✧ "በህይወትህ የተፈጠረው ምንም ይሁን ምን ከመጀመሪያም ለመፈጠር ጊዜ እየጠበቀ ነበር!" **Marcus Aurelius**
- ✧ "አንድ ሰው አውቀዋለሁ ብሎ ያሰበውን ነገር ለመማር አዳጋች ይሆንበታል!" **Epictetus**
- ✧ "አንዱ እና ዋነኛው ከልብ የመነጨ ክብር መገለጫ ሌሎች የሚናገሩት ሲኖራቸው በጥሞና ማዳመጥ ነው!" **Bryant H. McGill**
- ✧ "እውነተኛ ጥበብ ወደ እኛ የሚመጣው ስለህይወት፤ ስለራሳችን እና ስለዓለም ያለን ዕውቀት ምን ያህል ጥቂት እንደሆነ ስንገነዘብ ነው!" **Socrates**
- ✧ "በእድገት ሂደት ውስጥ መውደቅ እና መገፋትን መቀበል የሚያስችል ጥንካሬ ያስፈልገናል!" (**Unknown)**
- ✧ "ፈተናው ሲከብድ እሱን ማለፍ ክብሩም ከፍ ይላል። ብቁ ፓይለት የሚባለው በወጀብ እና አዉሎነፋስ ተፈትኖ ነው!" **Epictetus**
- ✧ "ህቀኛ መሆን ሁልጊዜ ቀላል ላይሆን ይችላል ነገር ግን ያ እስካልሆነ ድረስ እውነተኛ ሰለም ማግኘትም ቀላል አይሆንም!" **unknown**
- ✧ "ብቸኝነት ለኔ የጤናዬ ምንጭ ነው፤ ህይወቴን ትርጉም አዘል የሚያደርግልኝ። ብዙ ጊዜ ማውራት ለኔ ህመም ነው፤ ከቃላት ብክነት ለማገገምም በርካታ የዝምታ ቀናት ያስፈልጉኛል!" **Carl Jung**
- ✧ "ሁሉም ነገር አይነገርም፤ ሁሉም ነገር አይጠገንም አንዳንዴ የሚሻለው መተው ነው!" **(Unknown)**
- ✧ "ከሰው ልጅ ቂልነት አንዱ በደምብ መቀየር ከሚችለው የራሱ ድክመት ይልቅ ለመቀየር አዳጋች በሆነው የሌሎች ድክመት ላይ ትኩረት ማድረጉ ነው!" **Marcus Aurelius**
- ✧ "የየቀኑን ፈተና በድል ከተወጣህ አንድ ቀን ሻምፒዮን መሆንህ አይቀርም!" **(Unknown)**
- ✧ "ነፃ አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች አዕምሮአቸውን በሚዛናዊነት እና ከራሳቸው ልማድ፣ ዕምነት ወይም ክብራቸው ጋር የሚቃረኑ ነገሮችን ለመረዳት ያለፍርሃት ለመጠቀም ፈቃደኛ የሆኑ

ናቸው። ይህ የአይምሮ ደረጃ ሁሉ ጋር አይገኝም ነገር ግን ለትክክለኛ አስተሳሰብ ወሳኝ ነው!" **Leo Tolstoy**

- "በእርግጥ እየፈለግክ ያለህው በትክክል የሚያስፈልግህን ብቻ ከሆነ በህይወትህ ስኬታማ ነህ!" **Vernon Howard**
- "ሀይል ማለት ሌሎችን መቆጣጠር አይደለም። ሀይል ማለት ራስን መቆጣጠር ነው። ሌሎችን ለመቆጣጠር መሞከር ከራሳችን ቁጥጥር ውጭ ለመሆናችን አንዱ ምልክት ነው። ደካማ ሰው ሌሎችን መቆጣጠር ሀይል እንደሆነ ያስባል።" **(Unknown)**
- "ሰላም አዕምሮህን ህይወቴ መሆን አለበት ብለህ ከምታስበው ይልቅ ህይወትን ባለበት ሁኔታ እንዲያስተናብር ደጋግሞ የማሰልጠን ውጤት ነው።" **Wayne W. Dyer**
- "ሁሉም ነገር ባሰብነው መልኩ ሲጓዝ መነቃቃት ቀላል ነው፤ ዋናው ጉዳይ ነገሮች እየከበዱ ሲሄዱ ዲሲፕሊንድ ሆኖ መቆየት ላይ ነው!" (**Unknown)**
- "ሁልጊዜም ድጋሚ እየተከሰተ ዛሬም ደስታ የሚፈጥር ያለፈ አጋጣሚ ያለፈ አይደለም!" **Christina Sharpe**
- "የሚፈርዱ በጭራሽ አይረዱም፤ የሚረዱ በጭራሽ አይፈርዱም!" (**Unknown)**
- "ማንም ቢሆን ሃያም ይሁን አስራስምንት መማር ካቆመ አርጅቷል!" **Henry Ford**
- "አንድ ውድቀት ሺ ጥንካሬን ወይም አንድ ጥንካሬ ሺ ጥፋቶችን ሊሸሽግ ይችላል። ቲኒሹ ብዙ ይጠቁማል!" **Shams Tabrizi**
- "ምርጥ የድሮ መፅሃፎችን ማንበብ ከቀደመው ክፍለዘመን የብሩህ አዕምሮ ባለቤቶች ጋር እንደማውራት ነው!" **Rene Descartes**
- "አድናቆቱን ማንም ቢወስደው ግድ ካልሰጠህ ያለምከውን ታሳካዋለህ!" **Harry S. Truman**
- "አንዳንዶች በተንከል ያድጋሉ አንዳንዶች በደግነት ይወድቃሉ!" **William Shakespeare**
- "ጥቂት ፍልስፍና የሰውን ልጅ አዕምሮ ፈጣሪውን ወደ መካድ ሲያመራው ጠለቅ ያለ ፍልስፍና ግን አዕምሮውን ወደ ሃይማኖት ይመልሰዋል!" **Mandy P. Hall**
- "ታላቁ ድል በጭራሽ አለመውደቅ ላይ ሳይሆን ሁልጊዜም ከወደቅንበት መነሳት ላይ ነው!" **Confucius**
- "የትኛውም ጦር ጊዜው የደረሰን ሃሳብ ማስቆም የሚችል ጥንካሬ የለውም!" **Victor Hugo**
- "ሰላምን ከነፃነት መለየት አይቻልም፤ ምክኒያቱም ማንም ሰው ነፃነት ከሌለው ሰላም ሊሆን አይችልም!" **Malcolm X**
- "ምርጡ በቀል እንደጠላትህ አለመሆን ነው!" **Marcus Aurelius**
- "ተሸናፊዎች ትኩረታቸው አሸናፊዎች ላይ ሲሆን፤ አሸናፊዎች ደግሞ ትኩረታቸው ማሸነፍ ላይ ነው!" (**Unknown)**
- "እያንዳንዱ ትልቅ ነገር ሀልጊዜ ጥሩ አይደለም፤ ጥሩ ነገር ግን ምንጊዜም ትልቅ ነው!" **Demosthenes**
- "መረጋጋት ታላቁ የራስ ስኬት ነው!" **Zen Proverb**
- "ለውጥ የለመድነውን እና ቀላል የሆነውን ህይወት በመተው ሪስክ ወስዶ የተሻለ ነገር የመሞከር ድፍረትን ይጠይቃል!" **T. Arigo**
- "ማድረግ የማትችለው ማድረግ በምትችለው ላይ ጣልቃ እንዲገባ አትፍቀድ!" **John Wooden**
- "በጣም አደገኛው ውሸታም የሚናገረው ውሸት እውነት እንደሆነ የሚየስበው ነው!" (**Unknown)**
- "ሞኝ ራሱን እንደብልጥ ሲያይ ብልጥ ግን የራሱን ሞኝነት ያውቃል!" **William Shakespeare**
- "የሁሉም ትምህርት የመጨረሻ ውጤት ለውጥ ነው፤ እውነተኛ መማር ማስተማር ካለ ለውጥ አለ!" **Leo Buscaglia**

- ✧ "አንዳንዴ ወደፊት መጓዝ ከባድ ይሆናል፤ ነገር ግን አንዴ መጓዝ ስንጀምር፤ ውሳኔያችን ምን ያህል ምርጥ እንደነበር እንረዳለን!" (**Unknown)**
- ✧ "ትክክል የሆነውን ለማድረግ ጊዜው ሁልጊዜም ትክክል ነው!" **Martin Luther King Jr.**
- ✧ "ከሁሉ በላይ; አስቸጋሪ ቅፅበቶችን አትፍራቸው፤ ምርጡ የሚገኘው ከነሱ ነው!" **Rita Levi - Montalcini**
- ✧ "አብዛኛው ሰው ሰላንተ በሚያስበው መጨነቅ ጥቅም የለሽ ነው፤ አብዛኛው ሰው ስለራሱ ምን እንደሚያስብ እንኳን በደምብ አያቅም!" **Mostafa Kamil**
- ✧ "ሀይል ያላቸው ሰዎችን ተመልከት አንድ ነገር ትረዳለህ ህግን መጣስ። ሀይል ሲኖር ራስን መግዛት ትልቅ ጥበብ ነው!" **Noam Chomsky**
- ✧ "የፍቅር የመጀመሪያው ተዓምር መብቂያ ሊኖረው እንደሚችል አላዋቂነት መፍጠር ነው!" **Benjamin Disraeli**
- ✧ "ከባድ ሊሆን ይችላል ግን የማይቻል ነገር የለም፤ የማይቻል የሚመስለው እስክትጀምር ነው!" **(Unknown)**
- ✧ "ብዙውን ጊዜ የሚተቹህ ሰዎች ተመሳሳይ ናቸው፤ ዛሬ ያለህበት ቦታ ለመድረስ ምን ያህል ዋጋ እንደከፈልክ አያውቁም!" (**Unknown)**
- ✧ "ጊዜ ማወቅ የምንፈልገውን በሙሉ ይነግረናል!" (**Unknown)**
- ✧ "ቃላት ከተግባር ጋር ካልተጣጣሙ ዋጋቸውን እያጡ ይሄዳሉ!" **(Unknown)**
- ✧ "ሁሉም አእዋፍት በዝናብ ወቅት መጠለያ ይፈልጋሉ። ንስር ግን ከደመና በላይ በመብረር ዝናቡን ያሳልፋል። ችግር የሁሉም ነው ልዩነቱ የአመለካከት ጉዳይ ነው!" **A.P.J. Abdul Kalam**
- ✧ "ሁልጊዜም ማድረግ ያልቻልኩትን አደርጋለው ምክኒያቱም ምን ባደርግ እንደሚሳካ ልማር እችላለው!" **Pablo Picasso**
- ✧ "ምን ላይ ኮስታራ መሆን አንዳለብህ ተማር እና በተረፈው ሳቅበት!" **Herman Hesse**
- ✧ "ሳያመዛዝኑ ከሚቀበሉኝ ብዙሃን ይልቅ የአንድን ብልህ ሰው የሰላ ትችት እመርጣለሁ!" **Johannes Kepler**
- ✧ "ሁኔታዎች አንተ በምትፈልገው መልኩ እንዲጓዙ አትጠብቅ። ሁኔታውን ባለበት ማስተናገድ ልመድ፤ የሰላም ጎዳና ይህ ነው!" **Epictetus**
- ✧ "ማንበብ ትልቅ ሀብትን ያጎናፅፋል። እስከዛሬ በአለማችን ላይ ስለተከሠቱ እና በሌሎች ሰዎች ስለተሰሩ ነገሮች በሙሉ ማወቅ የምንችለው ማንበብ ስንጀምር ነው።" **አብርሃም ሊንከን**
- ✧ "በህይወቴ ማወቅ የምፈልጋቸው ነገሮች በሙሉ መፀሀፍቶች ውስጥ አሉ። የኔ ምርጥ ጓደኛ ብዬ የምቀርበው ሰው ያላነበብኩትን መፀሀፍ "እንካ አንብብ" ብሎ የሚሰጠኝ ነው።" **አብርሃም ሊንከን**
- ✧ "እዚህ ምድር ላይ ግዜ የማይሽረው ደስታን የሚሰጠን ብቸኛው ነገር መፀሀፍ የማንበብ ልምድ ነው። ሁሉም ደስታዎቻችን በወረት ከእኛ ሲለዩን መፀሀፍ የማንበብ ልምዳችን ግን ዘወትር ደስተኞች ያደርገናል።" **አንቶኒ ትሮሎፔ**
- ✧ "ዘወትር ባነበብኩኝ ቁጥር ውስጤ የነበረውና ያለው ትልቁ የመቻል አቅም ይቀሰቀሳል።" **ማልኮምኤክሥ**
- ✧ "የኔን የግል ህይወት ብቻ ሳይሆን በዙሪያዬ ያሉ ሰዎችን ህይወት መለወጥ የቻሉ ሀሳቦችን መተግበር የቻልኩት መፀሀፍ በማንበቤ ነው።" **ቤል ሑክሥ**
- ✧ "መፀሀፍን የሚያነብ ሰው በህይወት ውጣ ውረዱ አያማርርም። ሠዎች ለምን ጎዱኝ፣ ለምንስ አያስቡልኝም ብሎም ሌሎችን አይወቅስም። ከሌሎች ጋርም አይቀያየምም ምክንያቱም መፀሀፍ የሚያነብ ሰው ለራሱ ስኬትና ደስተኛነት ራሱ ብቁ ነውና ከሌሎች ምንም ስለማይጠብቅ።" **ባሮው**
- ✧ "ዛሬ ላይ ያለህ ማንነት የዛሬ አምስት አመት ከሚኖርህ ማንነት ጋር ፍፁም ለውጥ ሳይኖረው

ተመሳሳይ ነው። ግን በነዚህ አመታቶች ውስጥ መፀሀፎችን ካነበብክ አዎ! ከአሁኑ ይልቅ የዛሬ አምስት አመት የተሻለ ማንነት ይኖርሃል።" **ቻርሊ ጃንሥ**

- "ለአንድ ሠው መፀሀፍ ስትሸጥ የሸጥከው ብዙ ወረቀቶችን፣ የተፃፈበትን ቀለምና ጥራዙን አይደለም። ለርሱ የሸጥክለት ዋናው ነገር ሙሉ የሆነ አዲስ ህይወትን ነው።" **ክርስቶፈር ሞርሌይ**
- "በዚህ ዘመን በየትኛውም ሁኔታ በጣም ግዜ የለኝም፣ እረፍት የለኝም ብለህ የምታስብ ቢሆን እንኳን ለማንበብ የግድ ግዜ መስጠት አለብህ። ይህን አላደረክም ማለት ግን በገዛ ፍላጎትህ ራስህን አላዋቂ እያደረከው ነው ማለት ነው።" **ኮንፊሽየሥ**
- "ድሮ ልጅ ሣለሁ ወደ ትምህርት ቤት ስሔድ ዘወትር አፍንጫዬን በመፀሀፍ ደብቄ ነበር። ይኸው ዛሬ ላይ ታዲያ እዚህ ለመድረሴ ዋና ምክንያት ሆኖኛል።" **የሙዚቃ አቀንቃኙ ሱሊዮ**
- "መፀሀፍትን በሚገባ ማንበብ ማለት በድሮ ዘመን ይኖር ከነበረ በጣም አስተዋይ ሰው ጋር መወያየት ማለት ነው።" **ሬኔ ዴካርቴሥ**
- "**አዎ!** የሚታኝክ ማስቲካ ለማምረት ከምናወጣው ወጪ በላይ ለመፀሀፍቶች ብዙ ወጪን ባናወጣ ኖሮ ይህች ሀገራችን እንዲህ የሠለጠነችና የዘመነች አትሆንም ነበር።" **አልበርት ሀባርድ**
- "ከየትኛውም ነገር በላይ ትልቁንና ከፍተኛውን ደስታ የማገኘው ሳነብ ነው።" **የፋሽን ዲዛይነሯ ቢልብላሥ**
- "ማንበብ ከቻልክና አንዴ ማንበብ ከጀመርክ በቃ አንተ ነፃነት ያለህ ሠው ነህ።" **ፍሪድሪክ ዳግላሥ**
- "ለመኖር ከፈለክ መፀሀፍ አንብብ።" **ጉስታሽ ፍላውበርት**
- "መፀሀፍን ከማቃጠል የባሰ በርካታ ወንጀሎች አሉ። ከነዚህ መሃል መፀሀፍትን አለማንበብ አንዱ ትልቁ ወንጀል ነው።" **ጆሴፍ ብሮድስኪ**
- "አላዋቂነትንና ችኩልነትን የምንዋጋበት ብቸኛው ወሳኝ መሣሪያ ማንበብ ነው።" **ሌኖርድ ቤይንሥ ጆንሰን**
- "ዛሬ ያነበበ ነገ ሞሪ ይሆናል።" **ማርጋሪት ፉለር**
- "መፀሀፍን የማያነብ ሠው ማንበብን ከነጭርሱ ከማይችል ሠው በምንም አይሻልም።" **ማርክትዌይን**
- "በርካቶቻችን መፀሀፍ አንባቢ መሆን እንፈልጋለን። የምናነበው ግን ጥቂቶች ብቻ ነን።" **ማርክ ትዌይን**
- "እኔ የተወለድኩት ማንበብ ከሚገቡኝ ግና አንብቤ ከማልጨርሣቸው የመፀሀፍት ዝርዝሮች ጋር ነው።" **ማውዲ ኬሲ**
- "ለአንድ ጨቅላ ልጅ መፅሐፍ እንዲያነብ ከማድረግ በላይ ልንሠጠው የምንችለው ትልቅ ሥጦታ የለም።" **ሜይ ኤለን ቼሥ**
- "አንድ መፀሀፍ ባነበብን ቁጥር እዚህ ምድር ላይ በሆነ ቦታ ለኛ አንድ በር እየተከፈተልን ነው።" **ቬራናዛሪያን**
- "ለኔ ህይወት ማለት ጥሩ መፀሀፍ ማለት ነው። የበለጠ ወደ ውስጡ በገባን ቁጥር የበለጠ ትርጉም እየሰጠን ይመጣል።" **ሀሮልድ ሱሽነር**
- "እስከዛሬ በህይወቴ ካገኘኋቸው ምክሮች ትልቁ እውቀት ሀይል ነው። ማንበብ ደግሞ አማራጭ የሌለው ተግባር ነው የሚለው ነው።" **ተዋናይ ዳቪድ ቤይሊ**
- "የህይወታችን ትልቁ ደስታ መፀሀፍ ከማንበብ የሚገኝ ነው ብዬ በድፍረት ላውጅ እችላለሁ። ወደፊት እኔ የራሴ መኖሪያ ቤት ሲኖረኝ አንድ ጥሩ ላይብረሪ በውስጡ ካላካተትኩኝ ምን እንደሚውጠኝ አላውቅም።" **ደራሲ ጆን ኦውስተን**
- "መፀሀፎች ወረት የማያውቁ ምርጥ ወዳጆች ናቸው። እጅግ መልካም አማካሪዎችና የችግር ግዜ ደራሾችም ናቸው። እንዲሁም ከምንም በላይ ታላቅ መምህር ናቸው።" **ቻርሊ ኢሊዬት**

- ✧ "አንድ ሠው ምን አይነት ማንነት እንዳለው ያነበባቸውን መፀሀፎች አይቶ መናገር ይቻላል።" **ራልፍ ዋልዶ ኤመርሠን**
- ✧ "አንድ ባህል ወደ ቀጣይ ትውልድ እንዳይተላለፍ ከተፈለገ መፀሀፎችን ማቃጠል አያስፈልግም። ይልቅ ሠዎቹ መፀሀፍ ማንበብን እንዲያቆሙ ማድረግ በቂ ነው።" **ራይ ብራድበሪ**
- ✧ "የአካል ብቃት እንቅስቃሴ ለአካላችን የሚጠቅመውን ያህል ንባብም ለአእምሯችን ይጠቅማል።" **ሪቻርድ ስቲላ**
- ✧ "ሽረሪቶች እንደተወለዱ በተፈጥሮ ድርን የመስራት ክህሎትን እንደሚያገኙ ሁሉ ህፃናትም ሲወለዱ የመናገር ጥበብና ችሎታ አብሯቸው ይወለዳል። ግና ማንበብ መቻልን እኛ ነን ልናለማምዳቸውና ልናስተምራቸው የሚገባን።" **ስቴቨን ፒንከር**
- ✧ "መርከበኞች በአንጸባራቂ ደሴት ላይ ከሚያገኙት ሀብት በላይ ብዙ ሀብት የሚገኘው መፀሀፍቶች ውስጥ ነው።" **ዋልት ዲስኒ**
- ✧ "አንተ ጋር ሲመጡ መፀሀፍ በእጃቸው ያልያዙ ሠዎችን በፍፁም አትመን።" **ሊሞኒ ስኒኬት**
- ✧ "ለማንበብ ግዜ የለኝም ካልን ለማውራትና ለመፃፍ እንዴት ግዜ እናገኛለን?" **ስቴቨን ኪንግ**
- ✧ "ህፃናት እንደሚያደርጉት ለመገረም ብለው መፀሀፍን አያንብቡ። ለመማርም ሆነ ሀልመኛ ለመሆንም ፈልገው አያንብቡ። ይልቅ አዎ! ለመኖር ሲሉ ነው ማንበብ ያለብዎት።" **ጉስታቮ ፍላውበርት**
- ✧ "እኔና ጥቂት ሰዎች ስለራሳችን መልካም ነገር የምናስበውና ጥሩ ስሜት የሚሠማን መፀሀፍ ስናነብ ነው።" **ጂን ስሜይሊ**
- ✧ "የልጆቻችንን ቀጣይ ህይወት ብሩህ ልናደርግላቸው የምንችልባቸው ጥቂት መንገዶች አሉ። ከነዚህ መንገዶች መሃል ሠፈውና አስተማማኙ በውስጣቸው የንባብ ፍቅርን መዝራት ነው።" **ማያ አንጄሉ**
- ✧ "መፀሀፍ ማንበብ ነገሮችን እንድንረዳ ብቻ ሳይሆን ሌሎች እኛን በቀላሉ እንዲረዱን ይጠቅመናል።" **ጆን ግሪን**
- ✧ "አንተ ያላነበብከውን መፀሀፍ አንብብ ብለህ ለልጅህ አትስጠው።" **ጆርጅ በርናንድ ሾው**
- ✧ "አንተ ወይም እኛ የማናውቃቸው ነገሮች በሙሉ መፀሀፍት ውስጥ እንዳሉ እናውቃለን?" **ሲድኒ ስሚዝ**
- ✧ "እኔ አንብቤ ባስቀመጥኳቸውና በማነባቸው መፀሀፎች ካልተከበብኩ እንቅልፍ በፍፁም አይወስደኝም።" **ጆርጅ ሉዊሠ በርጌሠ**
- ✧ "አንዳንድ መፀሀፎች የፈለግነውን እንድናስብ ነፃ ያደርጉናል። አንዳንድ መፀሀፍት ደግሞ ከጭንቀታችን ነፃ ያደርጉናል።" **ራልፍ ዋልዶ ኤመርሠን**
- ✧ "ምናባችንን ከተኛበት የሚቀሠቅስልን ሞተር መፀሀፍ ማንበብ ነው።" **አለን ቤኔት**
- ✧ "በአሁኑ ሰአት እየተቃጠሉ ካሉ መፀሀፍት በላይ የሚያሳስበኝ በአሁኑ ሰዓት እያልተነበቡ ያሉ መፀሀፎች ናቸው።" **ጁዲ ብሉሜ**
- ✧ "ልጆቼ ወደፊት ሲያድጉ ማንበብ የሚወዱና ለእናታችን ትልቅ መፀሀፍ መደርደሪ እንስራላት ብለው የሚጨነቁ ቢሆኑ ደስታዬ ወደር አይኖረውም።" **አና ክዊድሰን የኒዮርክ ታይምስ ፀሃፊ**
- ✧ "መፀሀፍት ማለት መቼም ቢሆን የማይርቁን፣ የማያስቀይሙን፣ የማይከዱንና መቼም ቢሆን ተስፋችንን የማያጨልሙብን ወዳጆቻችን ናቸው።" **ቻርለሠ ኤሊዮት**
- ✧ "ከውሻ ውጪ የሠው ልጅ ታማኝ ወዳጅ መፀሀፍት ናቸው። ከውሻ ጋር ወዳጅ ስንሆን ግን የማንበብ እድላችን በጣም ያነሠ ነው።" **ጉርኞ ማርክሠ**
- ✧ "በመመገቢያ ጠረጴዛህ ላይ መፀሀፎች ይሙሉ።ከዛም በጣም ደስተኛ ትሆናለህ። ትራስህም መፀሀፍቶችን ይሁኑ ከዛም ፍፁም የሠላም እንቅልፍ ትተኛለህ።" **ፊይዶር ዶስቶኽስኪ**
- ✧ "መፀሀፍ ማለት በኪሳችን ይዘነው የምንዞረው በመልካም ፍሬዎች የተሞላ እርሻ ነው።"

ቻይናውያን

- ✧ "መፅሀፍ ስናነብ ወደ ውስጣችን በጣም ጠልቀን በመግባት ስለራሳችን የበለጠ ብዙ ነገሮችን ማወቅ እንጀምራለን።" **ዊልያም ሀዝሊት**
- ✧ "ትንሽዋ የመፅሀፍ መደርደሪያ እስከዛሬ በአለማችን ላይ ከቀረቡ የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በላይ እጅግ ጠቃሚ የሆኑ ሃሣቦችን ይዛለች።" **አንድሪው ሮስ**
- ✧ "ለአንድ ሰአት ብቻ ካነበብክ ወይም የማንበብ ልምድ ካለህ መጨነቅህ አይቀርም። ከሁለት ሰአታት በላይ የማንበብ ልምድ ካለህ ግን በምድር ላይ እንዳንተ ደስተኛ ሰው አይኖርም።" **ቻርለስ ዴ ሴኮንዳት**
- ✧ "ከአጠገብህ ፋኖስ ለኩሰህ ወይም ሻማ አብርተህ ቁጭ ብለህ መፀሀፍ ማንበብን የመሰለ ምን ነገር አለ? አስበው በዚያ በምታነብበት ሰዓት ሌላው ቀርቶ እዚህ ምድር ላይ አብረውህ ያልነበሩትን የቀድሞ ትውልድ ሰዎችና አብረውህ የማይኖሩትን የመጪው ትውልድ ሰዎችን ማውራት ትችላለህ። ይህ ደግሞ ከምንም በላይ ትልቅ ዋጋና ትርጉም ያለው አስደሳች እሴት ነው።" **ኬንኮ ዮሺዳ**
- ✧ "ሠዎች ህይወትን አንድ የሆነ ነገር ነው ብለው ይገልፃሉ። ለእኔ ግን ህይወት ማለት ማንበብ ማለት ነው።" **ሎጋ ስሚዝ**
- ✧ "ማንበባቸውን ተከትሎ በየዘመናቸው ታላቅ ስራን የሰሩ ጀግኖች ቁጥራቸው ስንት ይሆን?" **ሔነሪ ዳቪድ**
- ✧ "መፅሀፍትን ስናነብ አእምሯችን ራሱን የቻለ አንድ አስደሳች ኮንሰርት ተዘጋጀለት ማለት ነው። ታዲያ አእምሯችን ደስተኛ በሆነበት ሰዓት ደግሞ የሚያስባቸው ሃሣቦች ምን ያህል ጠቃሚና የጠለቁ እንደሆኑ ሁላችንም እናውቃለን።" **ስቴፋኒ ማላርሜ**
- ✧ "መፅሀፍ የሚያነቡ ሠዎች ብቸኝነት አያጠቃቸውም።" **አጋታ ክርማለት**
- ✧ "መፅሀፍ ማንበብ ነፍስን ያክማል።" **በቴክሳስ ላይብረሪ መግቢያ ላይ የተፃፈ**
- ✧ "መፅሀፍ የሌለበት መምሪያ ቤት ማለት መስኮት የሌለበት ቤት ማለት ነው።" **ሎነሬች ማን**
- ✧ "ሠው መንፈሱን መመገብ የሚችለው መፀሀፍትን በማንበብ ብቻ ነው።" **ኤድዊን ማርክሃም**
- ✧ "የተራበ ከብት ሳር ሲግጥ የሚሰማውን ደስታ ይህል ነው የሠው ልጅም መፅሀፍትን ሲያነብ ከፍተኛ ደስታን የሚያገኘው።" **ሎርድ ቸስተርፌልድ**
- ✧ "አንድ ሠው ለልጁም ሆነ ለመላው ማህበረሰብ ከሚሰጠው ስጦታዎች ሁሉ ትልቁ አንብቦ ሰዎችን እንዲያነቡ ማስቻሉ ነው።" **ካርል ካጋን**
- ✧ "ልጆቻችንን ዝም ብለን አይደለም አንብቡ ብለን እንዲያነቡ ማድረግ ያለብን። ይልቁንም በማንበባቸው በጣም ደስተኞች እንዲሆኑና ደጋግሞ የማንበብ ፍቅር እንዲያድርባቸው የሚያደርጉማድረግ ነገሮችንም አብረን ይጠበቅብናል።" **ካትሪና ፒተርሠን**
- ✧ "ከየትኛውም መዝናኛ በላይ እንደማንበብ ዋጋው ርካሽ ሆኖ በቀላሉ የሚያዝናና ነገር የለም። ደግሞም በማንበብ እንደሚገኘው ዘለቄታዊ ደስታ ሌሎች መዝናኛዎች ዘላቂ ደስታን አይሠጡም።" **ሌዲ ሞንታኑ**
- ✧ "እኔ ዘወትር የማስበው በቀጣይ ስለማነበው መፀሀፍ ብቻ ነው።" **ሮኦልድ ዳህል**
- ✧ "መፅሀፍትን ማንበብ መታደል ነው። ምክንያቱም ባነበብን ቁጥር አለማችንን በሚገባ እናውቃታለንና።" **ኒል ጌይንማን**
- ✧ "ማንበብ ሙሉ ሰው ያደርጋልና ሁላችንም በማንበብ ራሳችንን በእውቀት ልንገነባ ይገባል የዘወትር ምክሬ ነው።" (**Unknown)**

ምዕራፍ ሶስት

አነቃቂ ምክሮች

1. “ህይወት ደስ ትላለች!”

አዎ! መኖር መታደል ነው፤ ከዛሬው የፈጣሪ እቅዶች፣ የፈጣሪ ሃሳቦች፣ የአምላክ ጥበቃዎች መካተት እጅግ ደስ ያሰኛል። በመኖር ውስጥ የእራስ ስሜት ፍሰት ይታያል፤ የአለም ተፈጠሮ ፍሰት ይጎበኛል። እያንዳንዱ እስትንፋስ ያለውም የሌለውም ድንቅ ተፈጥሮ ሲንቀሳቀስ፣ ሲዘዋወር መመልከት መንፈስን ያድሳል። የህይወት ጣዓም ግሩም ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! አባትነትን አባት ካልሆንክ ስሜቱን አታውቀውም፤ **አዎ!** ጀግኒት...! እናትነትን እናት ካልሆንሽ ስሜቱን አታውቂውም፤ ህይወትም ይቺው ነች፤ ካልኖርሻት፣ ካላጣጣምሺያት ጠዓሟ አይገለጥልሽም፣ አይታውቅሽም።

ምንም ነገር ጠዓም እንዲኖረው ጣፋጭ መሆን የለበትም፤ እየጎመዘዘ የሚወደድ አለ፤ እየመረረ ደስ የሚል አለ። ህይወት ይህች ናት። ጎምዘዝ ያሉ መራራ ክስተቷ ውበቷን አያጠፋውም፤ ምክንያቱም እነዚህ የሚታወቁት በመኖር ውብ ስጦታ ውስጥ ነውና። ውጣ ውረድ የሌለው፣ በፈተና ያልታጀበ የእራስ አለም ከአሰልቺነትም ደካማ ልፍስፍስ ያደርጋል፤ ደስታን ያርቃል ምሬትን ያመጣል፤ ህይወትን ጥላሸት ይቀባታል።

አዎ! ሃዘን ባይኖር ደስታ አይኖርም፤ ለቅሶ ባይኖር ሳቅ አይኖርም፤ ጥላቻ ባይኖር ፍቅርን አናውቀውም፤ ችግር ባይኖር መፍትሔ የለም፤ ክፋት ባይኖር ደግነት ባልኖረ፣ መውደቅ ባይኖር መነሳት፣ ከፍ ማለት አይኖርም። እያንዳንዱ የህይወት ክስተት እራሱን የቻለ በጥበብ የተሞላ እጅግ ማራኪ ስብጥር አለው። አንዱ ለሌላኛው ውበቱን ማሳያ፣ ማድነቂያ፣ ማድመቂያው ነው። አስደሳቹን መምረጥ የህይወትን መልካም ስጦታ፣ ውብ ገፅታ ለመመልከት ለማጣጣም ያስችለናል። **አዎ!** ህይወት ደስ ትላለች! ስትኖራት፣ ስታጣጥማት፣ ከምክንያት ስተፀዳ፣ ችግርህን ስትቀበል፣ መፍትሔም ስትሆነው፤ በአምላክ ስታምን ስትተማመን፣ በእራስህ ስታምን ስትተማመን፣ **አዎ!** እውነትም ህይወት ደስ ትላለች።

2. “ዋጋ ለሰጠህ ዋጋ ስጠው!”

አለም ሰቶ በመቀበል ታምናለች። እኛ ሰዎችም ለምንፈልገው ነገር የሚገባውን ባደረግን ልክ የፈለግነው ነገር በእጃችን ይገባል። ነገሮች ሰው ለሰው በሚሰጠው ሲለካ ግን የተገላቢጦሽ ይሆናል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ልትረዳው ስትፈልገው የሚሸሽህ ስንት ሰው አለ። ስንት ነገር እየሆንክለት ስንቱ አይንህን ለአፈር የሚል አለ። ብዙ ዋጋ ብትከፍልለትም ቅንጣት የማይረዳህም ብዙ አለ። **አዎ!** ያንተ ጥረት፣ ያንተ ልፋት ብቻ ምንም አይቀይርም፤ የምትለፋው ለውጥ ከማይፈልግ፣ ዋጋህን ከሚሰጎስ፣ ትኩረት ከማይሰጥህ ሰው ጋር ከሆነ አርፈህ የእራስህን ህይወት ብትኖር ይሻልሃል።

አዎ! በኑሮህ ሙሃል በሰው እንዲደረግብህ የማትፈልገውን ነገር አንተስ እንዴት ተመልሰዋለህ? ግዜ ለሰጠህ ምን ያክል ጊዜህን ታውሰዋለህ? ትኩረት ለሰጠህ ምን ያክል ትኩረት ትሰጠዋለህ? አንቺስ ጀግኒት..! የሚፈልግሽን ምን ያክል ትፈልጊዋለሽ? የሚቀርብሽን ምን ያክል ትቀርቢዋለሽ? የሚወድሽን ምንያክል ትወጂዋለሽ? **አዎ!** ጀግናዬ..! ዋጋ ለሰጠህ ዋጋ ስጠው። ማንኛውም ሰው ጊዜ ተርፎት አይደለም ላንተ ጊዜ መስጠቱ፤ ሌላ የሚያተኩርበት አቶ አይደለም ወዳንተ መምጣቱ፤ ለእራሱ ችግር

አጥቶ አይደለም ባንተ ችግር መጨነቁ፤ እንቅልፍ ማጣቱ፤ ምናልባት ሰውነቱ አስገድዶት፣ ጓደኝነቱ፣ ወንድምነቱ፣ ወዳጅነቱ ገፋፍቶት ይሆናል። **አዎ!** በምንም ምክንያት አንተን ብሎ ለመጣ ሰው ፊት አትንሳው፣ ትኩረት አትንፈገው፣ ጊዜ አታሳጣው።

አዎ! ጀግኒት..! ፈላጊሽ፣ ወዳጅሽ ብዙ ሊሆን ይችላል፤ የተማረከብሽም እንዲሁ ይበዛ ይሆናል፤ አንቺ ግን አንድ ነሽና ለአንዱ ብቻ ትሆኚያለሽ። **አዎ!** እውነተኛ ወዳጅሽንም በሴትነት ጥበብሽ በቶሎ ለዪ፤ በፍፁም እንዳትታለዪ ዛሬ የበዙት ወዳጆችሽ ነገ አይኖሩም፤ ብልጥ ሁኚ። ለዛሬ ወዳጅሽ ፍቅርን ለግሺ፣ ለሚያስብልሽ፣ ለሚንከባከብሽ እንክብካቤን አትንፈጊው፣ ጠበቅ የሚያደርግሽን እርሱን ያዢ። አዎ! ከወረት ተላቀቂ የሚቀልደውን ህይወት ስትቀልድበት ብዙ ጊዜ አይተናል። በዛሬ ውበትሽ አትታበይ፤ ይልቅ ውስጣዊውን ውበትሽን በሚገባ መሰረት አስይዢው፣ አርሱን ብሎ ለመጣ ቁብ ነገረኛም ትኩረት ስጪው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ሰው አበረሀው ሆነህ፣ አብረሀው እየለፋህ፣ እየተሰቃየህ፣ እያገዝከው ዋጋህን ላይረዳ ይችላል፤ ምንም መስሎ ሊታየው ይችላል። **አዎ!** አንተ ግን አንዳንዴም ቢሆን ለክብርህ ስትል ዞር በል። ይህን ስታደርግም አንተን ብሎ ለመጣ የሚገባውን ክብር መስጠት እንዳትረሳ። **አዎ!** የሚሰጥህን መልሰህ ስጥ፣ የሚደረግልህን መልሰህ አድርግ። ወዳጆችህንም በተለየ ሁኔታ ክብርና እንክብካቤ ለግሳቸው።

3. “ከሁሉም በፊት እራስህን እወቅ!”

ምን ሰራህ? ምን አገኘህ? ምን አጋጠመህ? በምን ውስጥ አለፍክ? ትረኩም እንዲሰጡህ በቅድሚያ ማንነትህን እወቅ።
አዎ! ጀግናዬ..! እውነተኛው ማንነትህን! በዚህ ምደር ማንም አንተን አያውቅህም፤ አንተም ስለራስህ ማንነት እውቀቱ ካለህ በጣም ጎበዝ ሰው ነህ ማለት ነው። **አዎ!** ጀግኒት..! **“Who are you?** “ አንቺ ማነሽ? ከአመታት በፊት በእራሷ ስታፍር፣ ስትሸማቀቅ የነበረችው ሴት ነሽን? ከአመታት በፊት ልቧ የተሰበረ፣ የሚጠግንላት አታ ስትንከራተት የነበረች ያቺ ምስኪን ሴት ነሽን? ከጊዜያት በፊት ኑሮን ለማሸነፍ ስትባዝን፣ ስትለፋ የነበረች ብርቱ ሴት ነሽን?

አዎ! አንቺ ማነሽ? ወደኋላ ስትመለሺ ጊዜያት አልፈዋል፤ ታሪክሽን ስትቃኚ በጣም ትገረሚያለሽ፤ ብርታትሽን ታደንቂያለሽ፤ በአምላክ ድንቅ ስራ ትደመሚያለሽ። የመጣሽበት መንገድ የዛሬዋን አንቺ አስገኝቶልሻል። ከአመታት በፊት የህይወትሽ ዘዋሪ የነበረ፣ ከንፍስሽ ጋር የተሳሰረ፣ ልብሽን በተስፋ የሞላው፣ ትልቅ ስፍራ የሰጠሽው የእኔ የምትይው ሰው ዛሬ የለም፣ አንቺም ረስተሽዋል፤ እርሱም እንደዛው። ህይወት ግን አልቆመም ይቀጥላል። **አዎ!** ማንነትሽን ካወቅሽ፤ ምን ማድረግ እንዳለብሽ፣ እስከ ምን መጓዝ እንዳለብሽ፣ ምን ማድረግ እንደምትችይ ካወቅሽ ሌላው ቀላል ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! አንተ ማነህ? አንተን ማን ያውቅሃል? ወደ ምድር ለምን መጣህ? ካንተ ምን ይጠበቃል? አሁን የት ነህ? ምን እያደረክ ነው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሱን ካዘጋጀህ እራስህን በሚገባ አውቀሃል ማለት ነው። አንድ እውነት አለ የትም ብትሔድ፣ ምንም ያክል ብትወድ ብትወደድ፣ ምንም ያክል ብትቀራረብ፣ ብትዛመድ አንተን ካንተ በላይ የሚያውቅ የለም። የእራስ እውቀትም የመንገድህ መሪ ነው፤ አላማህን ያሳይሃል፤ ህልምህን ይጠቁምሃል፤ የኑሮህን ትርጉም ያስረዳሃል። **አዎ!** አንተ ማነህ? ሰዎች የሚያውቁት፣ የሚያወሩት አይነት ሰው? ወይስ ሌላ ሰው? ገፅታህ፣ መገለጫህ ምንድነው? በሰዎች አዕምሮ ውስጥ የተሰል አይነት ገፅ ወይስ ሌላ? **አዎ!** ከሁሉም በፊት፣ የትም ሳትሔድ ስለ እራስህ ጥልቅ እውቀት ይኑርህ፤ እራስህን እወቅ። በቀጣይም ለችግሮችህ ሁሉ ሌላ የማይችሉት ግዙፍ ችግር ሁንባቸው። ጉዞህን ወደፊት ገስግስ፣ መንገድህን አቅና፣ ትናንት ከምታውቀው አንተ የተሻልክ ሆነህ ተገኝ።

4. “እያለህ እንደሌለህ አትሁን!”

ዙሪያህን ተመልክተሃል? "ምን አነሰህ? ምን ጎደለህ? ምን ይጨመር?" እስክትባል እየጠበክ ነው። የጎደለ ሳይኖር የሚጨመር ነገር የለም፤ ባለህ፣ በተሰጠህ ነገር ተጠቀም። የሌሉህን መቁጠር ከጀመርክ ላያልቅልህ ይችላል፤ ያነሰህን ማሰብ ከጀመርክ ላታቆም ትችላለህ። **አዎ!** ጀግናዬ..! እያለህ እንደሌለህ አትሁን፤ የተበዳሪ አበዳሪ አትሁን፤ አለው ለመባል ለታይታ፣ ለእይታ ብቻ የምትበደር፣ የምታበድር አትሁን። **አዎ!** ሁሉም ዝግጁ ነው፤ የጎደለው ያንተ ንቃት ነው፤ ያነሰው ያንተ ወኔ፣ ያንተ ጥንካሬ፣ ያንተ ብርታት ነው።

አዎ! አትራፊ ሰው ሁሌም ትኩረቱ ወዳለው፣ ወደተሰጠው ነገር ነው። የጎደለውን አስቦት አያውቅም፤ እንዲያቆመውም አይፈቅድለትም፤ ምንም ለማድረግ፣ ምንም ለመጀመር ያለኝ ይበቃኛል ብሎ ያምናል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ዋናው ያለህ ነገር ጊዜ ነው፤ አታባክነው። ዋናው ያለህ ነገር አሁን አለም የደረሰችበት ቴክኖሎጂ ነው፤ እንዳያመልጥህ፤ ዋናው የተሰጠህ ነገር የፈለከውን የማድረግ፣ የፈለክበት የመድረስ ሃይል ነው። ዋናው ያለህ ነገር ጤና፣ ሰላም፣ ፍቅር፣ ብርታት ነው፤ አታሳንሰው።

አዎ! ሁሉም ነገር ተሟልቶለት እራሱን የቀየረ፣ ኑሮውን ያሻሻለ፣ ስኬታማ የሆነ ሰው የለም። ሁሉም የሌለው እንዲኖረው ያለውን ተጠቅሟል፤ የጎደለውን ለማማሟላት የተሰጠውን ሰርቶበታል። ኖሮህ ያልተጠቀምከው ነገር፣ ካለም አይቆጠርም፤ አለህ መባሉ የሚያተርፍልህ ነገር የለም። ተጠቅመህ ውጤቱንና እንዳለህ አሳይ፣ ለሌሎች ምሳሌ፣ ማስተማሪያ ሁን። **አዎ!** ሁሉም ተዘጋጅቶ ተጠቃሚ አታሳጣው፤ ውጤት ማምጣት እየቻለ በስንፍናህ ምክንያት ውጤት አታሳጣው፤ ያለህን ተጠቀም፤ በተሰጠህ አጊጥበት፣ ኩራበት፣ ስራበት፣ አትርፍበት። የጎደለህን ስታስብ ያለህንም እንዳታጣ ተጠንቀቅ።

5. “ልክ እንደ ውጤቱ!”

አዎ! ውጤቱን እንደምትወደው ሂደቱንም ውደደው፤ ልክ ስኬቱን እንደምትናፍቀው መንገዱም ይናፍቅህ፤ የተሻለ ህይወት እንደምትመኝው መስራት፣ መልፋት፣ መትጋትም የእለት ጥማትህ ይሁን። **አዎ!** ጀግናዬ..! ውጤቱ እያማረህ ሂደቱን አትራቅ፤ የሚከፈለውን ዋጋ አትጥላው፤ አትጠየፈው። ያለክፍያ የሚመጣ ውጤት የለም፤ ሳታጠና የምታገኘው **“Grade”** የለም፤ ምርጫው ያንተ ነው። እድሜ ልክህን ጥሩ ውጤት በመመኘት ታሳልፋለህ ወይስ ተነስተህ የሚያከፍልህን ትከፍላለህ? መንገዱን በመፍራት፣ በመሸሽ ብቻ ለስኬት ባዳ ተሆናለህ ወይስ በባዶ እግርህም ቢሆን ጉዞ ትጀምራለህ? ተስፋ እያለህ ተስፋ ትቆርጣለህ ውይስ ተስፋ በሌለበት ተስፈኛ ትሆናለህ? ስትገፋ፣ ስትወድቅ እዛው ትቀራለህ ወይምስ እንደገና ጠንክረህ ትነሳለህ? ችግሮች ሲገጥሙህ ዘለህ ትገባለህ ወይስ ቆም ብለህ ታስባለህ?

አዎ! የመንገዱ፣ የሂደቱ ፍቅር ወሳኝ ነው። ምንም እንኳን ስኬታማ ብትሆን የሔድክበት መንገድ ጤናማና አስደሳች ካልሆነ ስኬትህም ሊያስደስትህ አይችልም። ከውጣ ውረዱ፣ ከችግሩ፣ ከመከራው፣ ከስቃዩ፣ ከድካሙ፣ ከረሃቡ፣ ከጥማቱ ፍቅር ሊይዝህ ይገባል። ስኬቱን እንደምትፈልገው መንገዱም እጅጉን ያስፈልግሃል፣ ይገነባሃል፣ ያንፅሃል፣ ያጠነክርሃል። ስኬትህ ከፍ ያለ ቢሆንም እንኳን በሂደቱ ያፈራሀው ጥንካሬ፣ ያሳደከው ክህሎት፣ ያገኘሀው ጥበብ ስኬትህን እንድትቋቀም፣ እንድትሸከም ያስችልሃል። በነፃነት እድትጠቀመው፣ ተጨማሪ ሰኬትም እንድታገኝበት ያደርግሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! ሳትለፋ፣ ሳትደክም አጭበርብረህ፣ ሰረቀህ፣ ሰው በድለህ፣ አስከፍተህ በአቋራጭ የምታመጣው ስኬት ስሜት አይሰጥህም። እጅህ ላይ ሲገባ ተራ ይሆንብሃል፤ ዋጋ ያጣል፤ አንተንም ዋጋ ያሳጣሃል፤ ስኬታማነት ሳይሆን ወንጀለኛነት እንዲሰማህ ያደርግሃል። **አዎ!** ለስኬትህ ጠዓም፣ ለደስታህ፣

ለእርካታህ ለሂደቱ ያለህ ፍቅር ወሳኝ ነው። ሂደቱን ስትወድ ማቆምን፣ ማቋረጥን፣ ወደኋላ መመለስን ትረሳዋለህ። ሃሳብህ፣ ተግባርህ፣ ምኞትህ ሁሉ ወደፊት ወደ ተሻለው መዳረሻህ ይሆናል። በርታ! ጠንክር! መንገድህን ውደድ፣ ወደፊት ተጓዝ!

"ከእራስህ በላይ ወሳኝ ነገር የለህም!"

የአቀበቶች ብዛት፣ የ **"Social interaction"** ክፍተት፣ የፍራቻ ስር መስደድ፣ የይሉኝታ ተገዢነት የበታችነትና የስሜት መዋዠቅን የሚያስከትሉ አያሌ ችግሮች ናቸው። ስሜቱ የተዛባ፣ የወረደ ሰው እንኪን ወደፊቱን ዛሬ ምን ላይ እንዳለም ማወቅ አይችልም። እራሱን ለመግዛት በጣም ይቸገራል፣ በአሉታዊ ሃሳቦች ይሞላል፣ ስንፍናን መርጦ ሳይሆን በጫና ይቀበለዋል፤ በእራሱ ላይ ያነግሳል። ወደፊት መራመድ ቢፈልግም አይቻለውም። እራስን ችካል ላይ አስሮ ምንም ቢፈራገጡ ችካሉ እስካልተነቀለ ወይም የታሰረው እስካልተፋታ አንድ እርምጃ መራመድ አይቻለውም። በተለይ አዕምሮው የታሰረ ሰው የትም ልሂድ ቢል በውሰጡ የሚፈጠረው ሙግት ይበልጥ እንደሚጎዳው ስለሚያውቅ አርፎ መቀመጥን ይመርጣል።

አዎ! ጀግናዬ..! ነገር ግን እስከመቼ ነው እንደዚህ የምትቀጥለው? በበታችነት ስሜት እየተሰቃየህ፣ ፍራቻህ ተቆጣጥሮህ፣ ከሰው ርቀህ፣ ቀላሉ እየከበደብህ እስከመቼ ትቀጥላለህ? **አዎ!** ንቃ! መክፈል ያለብህን ነገር ክፈል፤ እንደቀላል የምታባክነውን ጊዜ በቃ ማለት ይኖርብሃል። ስሜቱ ከታወቀህ፣ እርዳታ ካስፈለገህ ለመጠየቅ አትሳቀቅ ጠይቅ፤ ምልከታህን አስፋ፤ ከሚረብሹህ ሰዎች መሸሸን ምረጥ፤ በውስጥህ ያለውን የታመቀ ድፍረት እንዲወጣ ፍቀድለት፤ **አዎ!** ያሳርፍህ! ዛሬህን ያስተካክልልህ፣ ወደፊትህን ያስውብልህ፤ እስከዛሬ ያሰብከው፣ የተጨነከው፣ የተጎዳሀው ይበቃሃል። ቀጣዩ የተግባር ጊዜ ነው። የለውጥ ጊዜ ነው። የጥንካሬ፣ የብርታት ጊዜ ነው።

በርታ! ያን ሁሉ ስሜት እንደታሪክ የምታወራበት፣ ሰው ፊት ቆመህ የምታስተምርበት፣ ምሳሌ የምትሆንበት ጊዜ ቀርቧል፤ ጊዜው አንዳያመልጥህ፣ ጉልበትህ እንዳይከዳህ፣ በቶሎ መፍትሔ አበጅለት። ችላ ብለህ የተውከው እንደሆነ፣ ለመቆጣጠር የሚከብድ ደረጃ ላይ ሊደርስብህ ይችላል። **አዎ!** ተረጋጋ፣ እርምጃ ውሰድ፣ ሂደቱን አጣጥም፣ ውጤቱን በጉጉት ጠብቅ፣ ጊዜህን በሚገባ ተጠቀም። ትርፍ ጊዜ አይደለም ዋናውን ጊዜ እራስህ ላይ "invest" አድርገው፤ ዋናውን ጊዜ እራስህን ፈልግበት፣ እራስህንም አግኝበት። ተራዎቹን ፍለጋ ዋናውን ጊዜህን አትሰዋ። በአንተ ህይወት ከእራስህ በላይ ጊዜህን፣ ስሜትህን፣ ንብረትህን ሊሻማ፣ ሊጠቀም የሚችል፣ የሚገባው ዋና ጉዳይ፣ ወሳኝ ነገር የለህም።

6. "ትግል እስከ ጥግ!"

ጀምሮ መተው የለም! ደርሶ ማፈግፈግ አይሆንም! ወስኖ ማቆም አይቻልም! አውርቶ መተው አይደረግም! አቅዶ አለመፈፀም ሊሆን አይችለም! አልሞ መሳት አይቻልም! ህልም ላይ ማንቀላፋት፣ መተኛት አይታሰብም! **አዎ!** ጀግናዬ...! ትግል እስከ ጥግ! እስከ መጨረሻዋ ጥይት! እስከ እስትንፋስህ ፍፃሜ! ለህልምህ የምትኖር ነህ፤ ኑሮህን መርጠሃል፣ ስንክሳሮችህን፣ ፈተናዎችህን ተቀብለሃል፤ ከመሸሽ ፊትለፊት ለመጋፈጥ፣ ለማስተካከል ወስነሃል። የምታደርገውን ታውቃለህ፣ የሚያሻግርህን ህልምህ ለይተሃል፤ የሚያቀናህ፣ ከፍ የሚያደርግህ አንተነትህ፣ ምሉዕነትህ፣ አድራጊነትህ እንደሆነ ገብቶሃል። ሰበብ አስባብ መተረክ፣ ምክንያት መደርደር እንደማያዋጣህ ጠንቅቀህ ታውቃለህ። ሳትፈልግ የምታደርገው ነገር የለም፣ ስሜትህ አይገፋህም፤ እራስህን ገርተሃል፤ ስክነትን፣ እርጋታን ተላብሰሃል። ከብርቱዎች፣ ከጠንካሮች ተርታ ተመድበሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! ለመቀበል፣ ለማመን የሚከብድህን ህይወት ይኖርህ ዘንድ እርምጃዎችህን አስተካክል፤

ትግልህን እስከ ጥግ አድርገው፤ ወደኋላ የሚያስመለክትህ፣ የሚገፋህ አንዳች ልዩ ሃይል ቢኖርም እርሱን አትመን ነገ ይከዳሃል፤ ባዶ ያስቀርሃል፤ ከጨለማው ይከትሃል። **አዎ!** ትኩረትህን፣ አቅምህን ትግልህ ላይ፣ አሸናፊነትህ ላይ፣ ድል አድርጊነትህ ላይ ብቻ አድርግ። በእራስህ ስትሸለም፣ ስትሞገስ፤ በስዎች ስትደቅ አራስህን ተመልከት። የድል ችቦህ በጉልህ ብርሃንን ለሰዎች ሲለግስ ተመልከት። ለአፍታም ቢሆን ትግልህን እንዳታቆም እራስህን፣ ሰዎችን ማስደመምህን ቀጥል።

7. “ጥያቄህ ምንድነው?”

ጥያቄህ ምንድነው? ማንን ትጠይቃለህ? ከመላሽህ ምን ትጠብቃለህ? በእርግጥም የተሻለ መልስ፣ የተሻለ መብራሪያ፣ ትንተና ትጠብቃለህ? **አዎ!** ጀግናዬ...! የምትጠይቀውን ሰው እወቅ። ካንተ የባሰ፣ ጥያቄ ላይ ጥያቄ የሚጨምርለህ፣ ጥያቄህን የሚያሳንስብህ፣ በመጠየቅህ የሚወቅስህ፣ የሚያስጨንቅህ፣ ላንተ ክብር የሌለው ሰው ጋር በፍፁም እንዳትሔድ። ገደል አፋፍ ቆሞ ይዞት የሚገባውን እየጠበቀ ነውና ተጠንቀቅ። አላዋቂ አጋዥ ይፈልጋል፤ አላዋቂነቱን የሚደግፍለት፣ ብቸኝነቱን የሚያስረሳው ሌላ የማያውቅ ሰው እንዲኖረው ይመኛል። **አዎ!** መቼም "አላውቅም ሌላ ሰው ጠይቅ" አይልህም፤ አለማወቁ እንዳይታወቅበት ስለሚፈራ ለጠየከው ሁሉ መልስ ይሰጥሃል፣ የአዋቂነት ልኩን አያውቀውም። አላዋቂነቱ አለማወቁንም አምኖ እንዳይቀበል ያደርገዋል።

አዎ! ጀግናዬ..! የሚያጠፋህን፣ በስንት ትግል ከወጣህው ደረጃ በአንዴ አሽቀንጥሮ የሚጥልህን ሰው ተጠንቀቅ፤ የገነባሀው ማንነት በሰው ፊት፣ በእራስህ ፊት ዋጋ እንዳያጣብህ። የጥያቄዎችህ ሁሉ መልስ ፈጣሪህ ጋር አለ ጠይቅ፤ ከዛም ስትወርድ ከእኔ ይሻለሉ፣ ጥሩ ነገር ሊሰጡኝ ይችላሉ፣ በመንገዴ ይመሩኛል፣ ይደግፉኛል የምትላቸውን ሰዎች ብቻ ጠይቅ፣ ከአዋቂዎችን፣ ከጥበበኞች ተቆራኝ፣ ተጠጋ።

አዎ! ጥያቄህ ምንድነው? ጥያቄህ ምንም ይሁን ነገር ግን መላሽህን በሚገባ እወቀው፤ የጥያቄህን ዋጋ፣ ጥቅም፣ ክብደት ግዝፈት የሚላካለህ መላሽህ ነውና። እንቆቅልህ ብለሀው መልሶ እንቆቅልህ የሚልህን በፍፁም አንዳትጠይቅ። እንቆልህ ብትል ምናውቅለህ የሚለህን፤ በትክክለኛው መንገድ፣ አንተን በሚመጥን ደረጃ የሚመልስልህ፣ ግፋ ቢልም የሚደቁስህ ሳይሆን የሚደግፍህ፣ ቀና የሚያደርግህ “Matured” የሆነ ሰው አለልህ። **አዎ!** ጥበብን ከጠቢባን፣ እውቀትንም ከአዋቂዎች ተማር፣ ውሰድ።

8. “በልብህ ተከተለው!”

ሰው ነህ የምትመኘው፣ የምታስበው ነገር አለህ፤ የምታልመው ነገር አለህ፤ ነገ እንዲሳካልህ የምትፈልገው ነገር አለህ። **አዎ!** ነገር ግን ዛሬ አንተ የምታልመውን ነገር፣ ለመድረስ የምታስበው ደረጃ ሌሎች ሰዎች ቀድመውህ አሳክተውት፣ ደርሰውበት ልታይ ትችላለህ፤ ቅናት ወይም እብሪት ቢጤም ሊፈታተንህ ይችላል። በዚህ መሃል ሁለት ምርጫ አለህ እነርሱ ቀድመውህ በማሳካታቸውና ደረጃውን በመያዛቸውን ተስፋ በመቁረጥ ማቆም ወይም እያንዳንዱን የመጡበትን መንገድ ማጥናት፣ መተግበር፣ ከእነርሱ በእጥፍ ጥረትን መጨመር ከእነርሱም ተሽሎ ከፍ ያለ ደረጃ ላይ መድረስ።

አዎ! ጀግናዬ..! መቼም አለም ዛሬ በዋለችበት ውሎ ነገም አትውልም፤ በሌላ አዲስ ክስተት ትሞላለች። የዛሬና ነገ ለውጥ ይህን ያክል ከሰፋ የአመታት ለውጥስ ምን ሊሆን ይችላል? ያለጥርጥር አስደናቂ ይሆናል። ትናንት እነርሱ የጣሩት ጥረትም ከዛሬ ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር አንድም በዝቶ ውይም አንሶ ሊታይ ይችላል። ስለዚህ እቅድህን ሁሉ ከአለም ለውጥና ሂደት ጋር አቆራኘው። ዛሬ አለም ለወደቁት ቦታ የላትም ነገ ደግሞ ምናልባት ለማንሳት ማስታወሱንም ትረሳው ይሆናል። ውድቀትን ተቀበል ድጋሜ መነሳትን ግን ሌላ ምርጫ አትስጠው፤ ውደቅ ሁሌም ግን ተነስ።

አዎ! ነገሮች በፍጥነት እየተቀየሩ ነው፤ እየከበዱ ነው፤ ትናንት በነበረህ አቋም የዛሬን ኑሮ መቋቋም አትችልም፤ ነገ ደግሞ ይበልጥ ሊከብድህ ይችላል። መበርታት፣ መጠንከር፣ አማራጮችን መመልከት፣ ህልምህን ቶሎ መለየት፣ በእርሱም እራስህን ማብቃት፣ ማስደሰት፣ ከፍ ማድረግ ይኖርብሃል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ነገ መሆን የምትፈልገውን ሰው፣ ዛሬ ሆኖ ያገኘህውን ሰው በልብህ ተከተለው፣ ሂደቶቹን አጥና፣ እርምጃዎቹን ተራመድ፤ ድርጊቶቹን በተሻለ መንገድ ድገም፤ ጥሩ ከራጅ ሁን በስተመጨረሻም የተሻለ ውጤት አስመዝግብ።

9. “ምክንያቶችህን ምክንያት አሳጣቸው!”

ደግሞ ሌላ ቀን አዲስ ጀምበር፤ ውብ ስኬታማ ቀን ልናሳልፍ ነው። እራስህን አዘጋጅ አምላክህን ለስጦታው በማመስገን ቀንህን ጀምረው። ለዚህች ውብ አዲስ ቀን አምላክ ይመስገን! ሳንጠይቅ ይሰጠናል የሚያስፈልገንን እርሱ ያውቃል! **አዎ!** ጀግናዬ..! አምላክ ለአዲስ ቀን አብቅቶሃል፤ አንተ ግን ውሎህን ማስተካከል፣ ማቀድ ይኖርብሃል። የተዝረከረከ ውሎ ቀንህን ያበላሻል፣ እረፍት ያሳጣሃል፤ ህይወትህን ያውካል። ዋና ዋናዎቹን የዛሬ ስራዎች በቅደመተከተል አስቀምጥ፤ አስቸኳና ትኩረትህን የሚፈልጉትን ለይ፤ በተቻለህ መጠን እራስህን በሚጠቅምህ ስራ ለመወጠር ሞክር፣ የሚያሰናክሉህን ጥቃቅን ተግባራት ከእራስህ አርቅ። ዛሬህን ዋጋ ያለው፣ በህይወትህ ላይ የሆነ ነገር የሚጨምር፣ የሚቆጠር ስኬታማ ቀን አድርገው።

አዎ! ቀንህን ሳትጀምር ምክንያቶች ኬትም አይመጡም፣ ቀንህን እስክት ጀምር፣ ወደስራ እስክትገባ ይጠብቃሉ፤ በጀመርክ ቅፅበት እነርሱም በተራቸው ስራቸውን ይጀምራሉ፤ እቅድህን ሊያፈርሱ ይሯሯጣሉ። አትስማቸው! "ሳትጀምር ደክሞሃል ትንሽ እረፍ ይሉሃል" እንዳትሰማ! "አዲስ ዜና አለ አጣራ፣ ተመልከት" ይሉሃል ጆሮ አትስጣቸው! "አሁን ጥሩ ጊዜ አይደለም ቦሃላ ትሰራለህ" ይሉሃል አትስማቸው "ነገም ሌላ ቀን አለህ ዛሬ ትንሽ ከሰራህ ይበቃሃል" ይሉሃል አይበቃኝም ማለት አለብህ። ምክንያቶችህን ምክንያት አሳጣቸው። በተቃራኒያቸው ቁም።

ሰበቦችህን ሰበብ ንሳቸው። መንገዳቸውን አስት፣ አልፈሃቸው ሂድ፤ ቀንህን ለማሳመር፣ ያሰብከውን ለማድረግ፣ ህይወትህን ለመቀየር ማድረግ ያለብህን አስገራሚ ነገር በእየቀኑ አደርግ፤ መጋፈጥ ያሉብህን ነገሮችን የማስተላለፍ ችግር (Procrastination) ፊት ለፊት ተጋፈጥ፤ የዛሬውን ተግባር ዛሬ ጨርስ፤ ነገን ለሌላ የተለየ ውይም ቀጣይ ስራ አዘጋጀው፤ ለተሰጠህ የአድራጊት፣ የቆራጥነት፣ የድንቅነት ስጦታም ዘወትር አምላክህን አመስገን!

10. “ታማኝ፣ እውነተኛ ሁን!”

የምትቆይ ከሆነ በታማኝነት ቆይ፤ የምትሔድ ከሆነም በጊዜ ሂድ፤ ያንተንም አብሮህ ያለውንም ሰው ጊዜና ስሜት አታባክን፣ አመኔታውን አትፈታተን፤ ለትልቅ ሲጠብቅህ ወድቀህ ታች አትገኝ። **አዎ!** ስሜት ሳይኖርህ ስሜት እንዳለህ፣ ጥሩ ወዳጅ እንደሆንክ አታስመስል፤ አፍቃሪ መስለህ የሰው ልብ ሰርስረህ አትግባ፤ እራስህን አድን፣ ወዳጅህንም ነፃ አውጣው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ታማኝ፣ እውነተኛ ሁን። ከጥቅምህ ለስሜትህ ተገዛ፣ ሰብዓዊነትህ ከፍ ይበል፣ ሰውንተህ ይብለጥ። በምንም ሁኔታ ጥቅመኛ ሰው አትሁን፣ እንዳንዴም ቢሆን በተጎጂው፣ በታለለው ሰው ቦታ ሆነህ ነገሮችን ተመልከት፤ **አዎ!** ለመጠቃቀም፣ ለመረዳዳት ሞክር፣ አብሮ ለመስራት አብሮ ለማደግ መንገድህን ክፈት። የምታጣው ነገር ከሌለ የሰውን የምትጠነጥክበት፣ ሌላውን የምታስከፋበት፣ የምታሳዝንበት ምክንያት የለህም።

አዎ! ጀግኒት..! ግንኙነትሽን የቀልድ አታድርጊው፤ ታመኚለት፣ እውነተኛ ስሜትሽን አንፀባርቂ፤ ኑሪው፤ ዋጋ ሰጪው። ከማንም ጋር ይሁን ልባዊ፣ ቅንና መልካም ተግባቦት ፍሬው ያምራል፤ ውጤቱም አመርቂ

ይሆናል። ከሰው ለመኖር ማመን፣ መታመን፣ እውነተኛ መሆን የግድ ነው። ለእራሱ የሚታመን፣ ትክክለኛውን ስሜቱን በተገቢ ሁኔታ ተቀብሎ የሚያስተናግድ፣ ለችግሮቹ በተረጋጋ መንፈስ መፍትሔ የሚፈልግ ሰው ለእራሱ የሚሰጠው ክብርና ቦታ ከፍ ይላል፤ ለሰውችም በሚያሳየው እውነተኝነት፣ ተቀባይነትና ተዓማኒነትን በቀላሉ ያገኛል። **አዎ!** እራስህን አትዋሽ፣ ስሜትህን ግለፅ፤ አታስመስል፤ ታማኝ እውነተኛ ሁን።

11. “አለመፈለግ ስህተት አይደለም!”

በስሜታችን አዛኝነት ከቀረበልን አማራጭ፣ ከመጣልን በረከትም ሆነ ጥፋት መምረጥ የኛ ድርሻ ነው። በምጫችን መሃል የምንፈልገውን ስንመርጥ የማንፈልገውን እንተወዋለን፤ ይህም ጌዴታ ነው። ምክንያቱም ሁሉን መውደድ ስለማይቻል፣ ከተሰጠን ነገርም አንዱን ማስበለጥ ግድ ስለሆነ። **አዎ!** ጀግኒት..! አለመፈለግ ስህተት አይደለም! ያለመፈለግም ጥፋት አይደለም። ህይወት ምርጫ አላት የምንፈልገውን እንመርጣለን፤ ካልተፈለግን እንተዋለን ወደሚፈልገን ፊታችንን እናዞራለን። የሚፈልግሽን አለመፈለግ ስህተት አይደለም፣ ግዴታም ልትፈልጊው አይገባም፤ ካልፈለግሽው ሁለታቹም እውነታውን መቀበል ይኖርባችኋል። ህይወትም የሚፈልጉትን በመፈለግ፣ በመፈላለግ ሲገናኙም ብረከቷን በመቋደስ ትቀጥላለች። ከማትፈልጊው ጋር ጊዜሽን እንድታባክኚ፤ የማትፈልጊውን ህይወት እንድትኖሪ፤ በማይመችሽ አኳሃን እንድትሆኚ፤ ከእራስሽ ውጪ የሚያስገድድሽ አንዳች ሃይል የለም። ሳትፈልጊ፣ ከምርጫሽ ውጪ በጫና የምትጀምሪው ህይወት ደስታን፣ እርካታን ከመጨመር ይልቅ ያለሽንም ሊያሳጣሽ ይችላል።

አዎ! አለመፈለግሽ ስህተት አለመሆኑን እወቂ፣ እንደማንኛውም ትክክለኛ ስሜት ተቀበይው፣ እንደ አመጣጡም አስተናግጂው። አለመፈለግ መጥላት አይደለም፤ አትፈልጊም ማለት ምርጫሽ አይደለም ማለት እንጂ ትጠይዋለሽ ማለት አይደለም፤ ይህም ነፃና ትክክለኛ ስሜት ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! የህይወትን ጠዓም የምታውቀው ለምትፈልገው፣ ለምትወደው ነገር ስትታገል ነው። በማትፈልገው ሰው፣ በማትፈልገው ልማድ፣ በማትፈልገው ሁነት ተከበህ ህይወት ትርጉም አልባ ልትሆንብህ ትችላለች። በቻልከው መጠን መቀየር የማትችለውን ነገር መቀበል፣ መውደድ ሊኖርብህ ይችላል ነገር ግን አለመፈለጉም ጥፋት አይደለም። የሚጠቅምህን ታውቃለህ ስለዚህ እርሱን በምጫህ ታደርጋለህ።

አዎ! ህይወትህን ባትወደው የምትጎዳው አንተ ነህ፤ ብትወደውም የምታተርፈው አንተ ነህ። ሰው ለሚወደው ነገር ዋጋ ይከፍላል፣ ይጥራል፣ ለማሻሻል ይለፋል። **አዎ!** አሁን ያለህበት ሁኔታ ምንም ይሁን እርሱን ተቀበል፣ መኖርን ከልብህ ተጠማ፣ ጓጓለት፣ ፈልገው፤ ለእርሱም አስደሳች ህይወት መሱዓትነት ክፈል፣ የሚገባህን ህይወትም ወደ እራስህ አምጣ።

12. “ስታምን ታየዋለህ!”

ማመን ካለብህ ከልብህ እመን፤ መቀበል ካለብህ በሙሉ ልብህ አድርገው፤ ጥርጣሬህ በፍራቻና ስጋት አጅቦ በሃሳብ፣ በጭንቀት ከመጉዳት በቀር የሚያተርፍልህ ሌላ ነገር አይኖርም። **አዎ!** ስታምን ታየዋለህ! ስታስብ ታደርገዋለህ! ስታቅድ ታሳካዋለህ! ስታልም ትኖረዋለህ! ስትጀምር ትጨርሰዋለህ! **አዎ!** ጀግናዬ..! ሁሉም ነገር ቅድመተከተል አለው። አንዱን ለማስከተል አንዱ መቅደም ይኖርበታል። ከማድረግ ማሰብ ይቀድማል፤ አድርጎ ማሰብ መዘዙ፣ ጣጣው ብዙ ነው። ተዘጋጅተህ፣ አቅደህ የምታደርገው ነገር ቢበላሽም አማራጭ መንገድ አታጣለትም። ዘው ብለህ መግባትህ ግን ዘለህ እንድትወጣ ላይፈቅድልህ ይችላል። ብዛት ያላቸው እሾሆች መንገድህን ሊዘጉብህ ይችላሉ። የገባህበት ፍጥነት ስትወጣ ይከዳሃል። ባትፈልግም ስለፍጥነትህ ሃላፊነቱን ትወስዳለህ። በስሜት፣ በሰው ግፊት፣ ባልተለመደ ጫና የምታደርጋቸው እያንዳንዶቹ ነገሮች የእራሳቸው ዋጋ አላቸው። ያደረከው አንተ

እስከሆንክ ድረስ ያስገደደህ ወይም የመከረህ ሰው ሃላፊነቱን አይወስድም። እርሱን አንተ ዞር ስትል ልታጣው ትችላለህ።

አዎ! ጀግናናዬ..! ምንም ከመጀመርህ፣ ከማድረግህ በፊት አዋጭነቱን፣ ኪሳራውን፣ ጥቅሙን፣ ጉዳቱን በጥንቃቄ አጥና፤ ደጋግመህ አስብ። ስታደርግም ከልብህ አምነህ አድርግ፤ ለማሳካትም እቅድን አስቀድም። ምንም ነገር ለማስተካከል ስታስብ በቅድሚያ ሁሉን ነገር ከእራስህ ጠብቅ፣ እራስህም አድርገው። ያንተን ፍላጎት የሚያሟላለህ ካንተ ውጪ ሌላ አታኝም፤ ህልምህን የሚያውቅ፣ የሚረዳ ካንተ በቀር ማንም አይኖርም፤ ክፍተቶችህን በተሻለ የሚያውቅ፣ የሚረዳ ሌላ ሰው የለም፤ ስለዚህ መሰተካከል ያለባቸውን፣ መደረግ ያለባቸውን፣ መሳካት ያለባቸውን ነገሮች በቅድሚያ እራስህ አስባቸው፣ አንተው አድርጋቸው፤ አንተው ፈፅማቸው፤ ቀሪው ያንተ ሃላፊነት ሲጠናቀቅ የሚከተል ነው።

13. “ማድረግ ጀምረናል!”

ማሰብ ጀምረናል! ማለም ጀምረናል! ማቀድ ጀምረናል! ማድረግ ጀምረናል! ማደግ ጀምረናል! **“No One has a power of stopping us. NO ONE!”** ህልማችን ትልቅ ነው፤ ጥረታችን ከእርሱ ይልቃል፤ ሃሳባችን ልዩ ነው፤ ትግላችን ከእርሱ ይበልጣል፤ እቅዳችን የተጠና ነው፤ አፈፃፀሚችን ግሩም ነው። ግባችን ከፍ ይላል፤ ህይወታችንን ይቀይራል። ራዕያችን ድንቅ ነው፤ ለሃገር፣ ለወገን ይተርፋል። ጉደለትን የሚሞላ፣ ያልነበረውን የሚያመጣ፣ እውብ ደንቅ ክስተት፣ አስገራሚ ግኚትን ያሳየናል። እርምጃችን ወደፊት ነው፣ ትቺቶቻችንን ወደ ሃይል እንቀይራለን፤ ጥላቻን በፍቅር እንተካለን፤ ባለን ተደስተናል፤ ሌላም እንደሚጨመርልን እናምናለን፤ የአምላክ በረከት ከቦናል፤ በግሩም መንፈሱ ተቃኝተናል።

አዎ! ጀግናዬ..! ወደን የምኖረው ህይወት ጀምረናል። ጫና የለበትም፣ ተገደን አይደለም፣ የራዕይን ሃይል ስለምናውቅ፣ የህልም ዋጋ ስለገባን ወደ ትራኩ ገብተናል። **አዎ!** ጠዓም ያለው ህይወት በህልም ውስጥ ይገኛል፤ ትርጉም ያለው ህይወት በራዕይ ውስጥ ይታያል፤ ሰው ስትሆን ፍላጎትህ ምንም ይሁን እንደምታሳካው ታምናለህ፣ እምነትህንም ዛሬ ጀምር፤ ወደ ድርጊት ግባ፤ በሃሳብ ብቻ ከመዋኘት የተግባር ሰው ሁን፤ ብዙ አማራጭ እያለህ እንደሌለህ አትኑር፤ አውንታዊ ሃሳቦች እያሉልህ በአሉታዊው አትሞላ፤ ቀና ማለት እየቻልክ በዝቅታ አትመላለስ፤ ለሰው መትረፍ እየቻልክ ሰው አትጠብቅ። ያሰብከውን ማድረግ፣ ማሳካት ትችላለህ፣ እያደረክም፣ እያሳካህም ነው፣ ሌላም የተሻለ ነገር ማድረግ ትችላለህ።

እመን! ማድረግህን፣ ትግለህን ቀጥል! የማይገባው ቦታ እንዲገኝ እራስህን አታስገድደው፣ አትግፋው። የሚመጥንህ ቦታ እያለ ለማይገባህ ስፍራ አትታገል። የምትጓዝበት፣ የምታርፍበት፣ የምትቆይበት ቦታ ሁሉ ክብርህን እንደሚመጥን እወቅ። የምታገኛቸው፣ የምታወራቸው፣ ጉዳይህን የምታወያያቸው ሰዎች ሁሉ ከአንተ የእሳቤ ደረጃ ጋር መመጣጠናቸውን አረጋግጥ። **አዎ!** ጀግናዬ..! ሃሳብህ እንኳን ምንያህል ያንተን ማንነት ይመጥናል? ንግግርህ፣ ተግባርህ አንተን ይገልፃልን? ያንተ ማንነት መገለጫ ሊሆን ይችላልን? ጥልቅ ምርመራ ያስፈልግሃል። ልኬትህን፣ ክብርህን፣ መጠንህን ሳታውቅ አትተኛ። ምን እንደሚገባህ፣ ምን እንደሚመጥንህ፣ ምን እንደሚያሳድግህ፣ ምን እንደሚያስፈልግህ፣ ምን እንደምትፈልግ በጥልቀት መርምር፣ እራስህንም አግኝ።

14. “ፍቅርህን አታጉድለው!”

አዎ! ፍቅርህን አታጉድለው፤ በሰማይ አታንሳፈው፤ ማረፊያ አበጅለት፤ ደረጃውን ከፍ፣ ስሜቱን ጉላ አድርገው፤ ትርጉም ስጠው፤ ሙሉ አድርገው። **አዎ!** ጀግናዬ..! የፍቅር ህይወትን ሙሉ ከሚያደርጉት

ዋነኛው ነገር ቃልን መኖር፤ ፍቅርን መኖር፤ የሚነገረውን እርሱን ፍቅር መሬት ላይ መተግር ነው። ምናልባት በቃላት ማሸሞንሞን ግማሽ መንገድ ሊያስኬደው ይችላል፣ ተግባር ከሌለው ግን ግቡን መምታት ይሳነዋል። በአንድ አካል ግፊት ብቻም የትም አይደርስም፣ ጫናው ሲበዛ የስሜት ዝለት፣ የአቅም ማነስ ሊያስከትል ይችላል። የፍቅርን ሃያልነት፣ የፍቅርን አስደሳችነት ዘወትር እያወራህ አንተ ካልኖርከው ባዶ ታሪክ እንደመተረክ ይሆናል። ዋና ዋናዎቹ የህይወት ክስተቶች ከቃል ይልቅ ተግባርን ይፈልጋሉ።

አዎ! ፍቅር ቃል ብቻ ሳይሆን ተግባር ነው። የሚተረክ ብቻ ሳይሆን የሚኖር ነው፤ የሚነገር ብቻ ሳይሆን የሚታይ፣ የሚገለፅ ነው።
አዎ! ጀግኒት..! የፍቅርን ሃያልነት በተግባር አሳዪ፣ ከውስጥሽ ኑሪ፤ ምላሽ ይፈልጋልና ተገቢውን ምላሽ በጊዜ ስጪው፤ ዋጋ ያስከፍላልና ዋጋ ክፈይለት። በደናው ጊዜ አብሮ መሆን፣ በደጉ ጊዜ ደግ ደጉን ማሰብ ግዴታ መዋደድ፣ መፋቀር ላያስፈልግ ይችላል። አዎ! የፍቅር መኖር የሚታወቀው በክፉው ጊዜ፣ በአስቸጋሪ ሰዓት፣ ፈተናዎች ሲበዙ፣ ነገሮች ሲከፉ፣ ሲያስቸግሩ ነው። **አዎ!** ፍቅርህን አታጉድለው! ሙሉ ሊያደርጉት ከመጡት ፈተናዎች ከመሸሽ ይልቅ ፊት ለፊት ተጋፈጣቸው፣ ዋጋ ከፍለህ ዋጋ አስከፍላቸው፤ ግንኙነትህንም አጠንክር፤ ፍቅርህንም ሙሉ አድርገው።

15. “እየመጣህ ነው!”

ፈተናዎችህን እያለፍክ ነው፤ ችግሮችህን እያስተካከልክ ነው፤ በእራስ መተማመንህ ጨምሯል፤ እራስህን እያገኘሀው ነው፤ ማንነትህን፣ ልኬትህን፣ የሚገባህን እያወክ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ወደእራስህ አየተመለስክ ነው፤ ወደ እራስህ እየመጣህ ነው። የመጣህበት መንገድ አለመመቻቸት እራስህን ለማግኘት ጠቅሞሃል፤ ምርጡን አንተ አስገኝቶልሃል። "ለምን ይሔ ተፈጠረብኝ አትልም፤ "ለምን በእኔ ላይ" አትልም፤ "እንኳንም መጣብኝ፣ እንኳንም እኔን ጎበኘኝ" ትላለህ። ስጦታህ መሆኑ ይገባሃል፤ አንተ እንድትቀየር፣ በሳል ጥበበኛ እንድትሆን ካለፍክበት ችግር በተሻለ ብቁ የሚያደርግህ ነገር የለም።

አዎ! ጀግኒት..! ምኞትን አለማወቅሽ በእራስሽ እንድትመቻቺ ያደርግሻል፤ በቀላሉ ከመሰበር ይታደግሻል፤ ያድንሻል። በምኞት ያደገ ልጅ ትንሽ ችግር ተራራ ይሆንበታል፤ ተፈትኖ፣ ተጀግሮ ያደገ ልጅስ? ምንም ችግር ለእርሱ አዲስ አይደለም። ተፈትኖ፣ ተቸግሮ፣ ተሰቃይቶ ሁሉን አልፎ ስለመጣ የተገነባ ማንነት አለው፣ በትንሹም በትልቁም የሚሰበር አይደለም። **“chasing a challenge is normal for him.”** ምናልባት ብዞዎች የሚመኙትን ምኞት ላይወደው ይችላል፤ ምክንያቱም መንገዱ ሁሉ ባለመመቸት ታጥሮ ነበር፤ የምኞትን ጠዓም አያውቀውም! አላጋጠመውም። በስተመጨረሻ ግን ትልቁን የስኬት ጠዓም የሚያጣጥመው፣ ዋጋው የሚከፈለው፣ ትልቅ ቦታ የሚደርሰው እርሱ ምኞትን የማያውቀው ልጅ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! ህይወት የማይመጥንህን ችግር አትሰጥህም፣ ማለፍ ለማትችለው ፈተና አታጋፍጥህም። እነርሱ ከአምላክ ቀጥሎ በአምላክህ የተላኩለህ ፈጣሪዎችህ ናቸው፤ ምርጡን አንተን ለመፍጠር የመጡ ናቸው። ይህን ተቀበል፤ ተመርጦልህ እንደሚመጣ የተሻለ ነገር ተመልከተው፣ በተሻለ መንገድም አሸንፈህ እራስህን ማኩራት እንዳለብህ እመን። የህይወት ጦርነት ሁል ጊዜ ወደ ጠንካራ ወይም ፈጣን ሰው አይሄድም፤ ግን ይዋል ይደር እንጂ የሚያሸንፈው አሸንፋለው ብሎ የሚያስብ ሰው ነው። **/ከናፖሊዮን ሂል አንደበት/**

አሸናፊ ለመሆን ቅድሚያ የአሸናፊነት ሃሳብ ያስፈልግሃል። በተሸነፈ ሃሳብ የምታሸንፈው አካል አይኖርም። ሆኖ ለመገኘት የመሆን ሃሳብ፣ በቦታው የመገኘት ሃሳብ፣ የማድረግ ሃሳብ ግድ ያስፈልግሃል። **አዎ!** ጀግናዬ..! እንደምታሸንፍ ማሰብህን ቀጥል፤ አፍታም ስለመሸነፍ፣ ስለማቆም፣

ወደኋላ ስለመመለስ እንዳታስብ። መጀመር ምንያህል እንደ ፈተነህ አስታውስ፤ መቀጠል፣ እዚህ መድረስ ምንያህል እንዳደከመህ፣ ምን እንዳስከፈለህ አስታውስ። መጨረስህን፣ ማሸነፍህን በልብህ ሰንቅ በእርግጥም እውን ታደርገዋለህ፤ ታሸንፋለህ፤ ድል ታደርጋለህ።

16. "ለእራስህ አንተው ድረስለት!"

አንዳንዴ የስብርሃትህን ጥግ አታውቀውም፤ የህመምህ ልኬት አይገባህም፤ የስቃይህ ጫፍ ይርቅሃል፤ የጉዳትህን ክብደት ማሰብ ይሳንሃል፣ በህይወት እያለህ እንደሌለህ ሊሰማህ ይችላል፤ ስብራትህ አጥንትህን ይነካል፣ ውስጥህን ሰርስሮ ይገባል። አስበው ለእዚህ ሁሉ ላበቃህ በደል አንድን ሰው ወይም ብዙ ሰው ተጠያቂ ታደርጋለህ። በውስጥህ የሚመላለሰው መጎዳትህ አይደለም፣ ስብራትህም አይደለም የሰውዬው ማንነት ነው። በብዙ አምነህው በእርሱ መከዳትህ እንቅልፍ ይነሳሃል፣ ሰላምህን ያሳጣሃል። ቦታ ሰተህው ቦታውን ያለ አግባብ መጠቀሙ ይሰብርሃል። ለዚ ማነው ተጠያቂ? ይሔ እንዲሆን ማን ፈቀደ? በሩን ማን ከፈተ? መንገዱን ማን አቀና? የትም አትሂድ፤ የፈቀድከው፣ መንገዱን የከፈትከው አንተ፣ ስልጣን የሰጠሀው አንተ፣ ተጠያቂውም አንተ፣ መፍትሔውም አንተ። **"Nobody else"** አንዳንዴም የህመምህ ጥለቀት ለሰውዬው መልካሙን በመመኘት ዝምታን እንድትመርጥ ሊያደርግህ ይችላል። ይህን ማድረግህ የተወሰነ ሸክምህን ሊያቀልልህ ይችላል ሙሉ ሰላም ግን ሊሰጥህ አይችልም፣ አያሳርፍህም።

አዎ! ጀግናዬ..! ከድካምህ እረፍ፤ ከስቃይህ ተገላገል፤ ውስጥህን አሳርፍ፤ ሰላምን አትርፍ። ቂምን ተው፤ ነገር አትያዝ፤ አዕምሮህን በተበዳይ አስተሳሰብ አታስጨንቀው፤ ዘወትር የሚመኘውን እርጋታ አትንፈገው፤ ሰላሙን አታሳጣው። **አዎ!** እንዲጎዳ እንደፈቀድክ ነፃ እንዲወጣ፣ እንዲማር፣ እራሱን እንዲጠግን ፍቀድ፤ እራሱን እንዲቀይር፣ እንዲያበረታ አድርገው። የከበበውን ጨለማ ግፈፍለት፣ አስወግደው፤ በተስፋ ሙላው፤ **አዎ!** ለእራስህ አንተው ድረስለት፤ አንተው አድነው።

17. "አብዮቱን ማን ይምራው?"

በቀኝ በግራ ከፊት ከኋላ በአብዮተኞት ተከበሃል፣ በለውጥ አራማጅ ባለራዕይዎች፣ በባለ ትልቅ ህልም ባለቤቶች ተውጠሃል። ውስጥህ ስጋት አለ፣ ፍርሃት አለ፣ ወኔ አለ፣ ያልጠራ ትልቅ ህልም አለ፣ ከባድ የሆነ ለብዙዎች የሚተርፍ ራዕይ አለ። ስጋትህ የአብዮቱ ሃይል ነው፤ ፍረሃትህ በአብዮተኞቹ ውስጥ የምታየው ብሩህ ተስፋ፤ እምቅ ሃይል ነው፣ የስኬት ጥማታቸው ነው። "በእውኑ በእኔም ውስጥ አለ?" ትላለህ። መኖሩን ትጠራጠራለህ። በሚገባ አለ፤ ስጋትህን አጥፋ፣ ፍረሃትህን አርቅ፣ ፍጠን አብዮቱን ተቀላቀል።

አዎ! ጀግናዬ..! ይህ ሁሉ ውስጥህ የሚመላለሰው ምናባዊ አለም፣ የሚያስነሳው፣ የሚያነቃው አብዮት ይፈልጋል፤ በሩጫ፣ በትግል፣ በጥረት የታገዘ አብዮት። እንግዲህ አብዮቱን ማን ይምራው? **"Who is gonna lead the revolution?"** ማን ከፊት ይቁም? ማን ያጣጥመው? ማን ወደፊት ይግፋው? ማን ጉልበት ይሁነው? ማንስ ስጋቶቹን ያስወግድ? **አዎ!** እርሱን የምታደርገው ብርቱው፣ ጠንካራው አንተ ነህ። ወደፊትህን የምትወስነው፣ ህልምህን የምታጠራው፣ ጉዞህን የምታፈጥነው፣ ራዕይህን የምታሳካው፤ ሃሳብህን የምትሞላ የአብዮቱ መሪ፣ አብዮቱን የምታፋፍመው አንተ የገዛ ህይወትህ አብዮተኛ ነህ። የምታያቸው ባለራዕይዎች ብርታትህ ናቸው፤ የምታገኛቸው የትልቅ ህልም ባለቤቶች ረዳቶችህ፣ አጋዦችህ ናቸው፤ የቀረብካቸው ብርቱ ሰዎች ጥንካሬህ፣ ብርታትህ ናቸው። አካባቢህ በህይወት ለውጥ አራማጆች እስከተከበበ ከአብዮትህ የሚገታህ፣ እንቅፋት የሚሆንህ ምንም አይኖርም።

አብዮትህ ግብ አለው። ግብህ እራስህን ማነቃነቅ፣ ከፍ ማድረግ፣ መቀየር፣ እምቅ ሃይልህን ማውጣት፣

ተፅኖ ፈጣሪ መሆን፣ ለሌሎች መትረፍ፣ የእርካታን ጥግ መመልከት፣ በሃገርህ፣ በአህጉርህ፣ በአለም ማበብ፣ መፍካት፣ መድመቅ ነው። **አዎ!** አብዮተኛ አይተኛም። እራሱን ያነቃል፣ ሌሎችን ይደግፋል፣ ያበረታል። አሰልቺውን፣ በማይረቡ ልማዶች የመጠመድ ሂደት ገነጣጥሎ አርቆ ይጥላል፣ የእራሱ ጠባቂ፣ የእራሱ እረኛ፣ የትውልድ አርበኛ፣ ለሃገሩ ዘበኛ፣ የአለም ብርቅዬ ሰው ነው። **አዎ!** ህይወትህ ላይ የለውጥ፣ የእድገት፣ የጥንካሬ፣ የአድራጊነት አብዮት አስነሳ። አብዮቱን ከፊት ሆነህ ምራው፣ ግቡንም በጊዜ ምታ፤ ድሉንም ቀድመህ አክብር።

18. “እኔ ታላቅ ነኝ!”

ታላቅ መሆኔን ከማወቄ በፊት እንኪን ተናግሬ ነበር። **/ከመሃመድ አሊ አንደበት/** የሰው ልጅ ተፈጥሮው ታላቅ፤ የፈጠረው የታላቆች ታላቅ ነው። ታላቅ ነገርም ትንሽ ተራ ነገር አይፈጥርም፤ የወረደ ነገር አያስገኝም፤ ክብሩን የሚያሳይ፣ ጥበቡን የሚገልፅ ድንቅ ስራ ይሰራል፤ ግሩም ፍጥረት ይፈጥራል። **አዎ!** ጀግናዬ..! አንተ በታላቁ ፈጣሪ የተፈጠርክ ታላቅ፣ ግሩም ድንቅ ፍጥረት ነህ። ታላቅነትህ ሁሌም አብሮህ ይኖራል፤ ታላቅነትህ በሰውነትህ ውስጥ ይገለፃል፤ በተግባርህ፣ በችሎታህ፣ በምታሳየው ክህሎት፣ በምታመጣው ውጤት፣ በምታስገኘው ድል ድንቅነትህን ዳግም ታስመሰክራለህ። **አዎ!** ታላቅ ነህና ታላቅ ስራ ይጠበቅብሃል፤ ድንቅ ነህና ድንቅ ተግባር ይጠበቅብሃል፤ ንቃ! ተነስ! ለድንቅና ታላቅ ነገር እራስህን አዘጋጅ።

19. “ትኩረትህን... ለሚገባቸው!”

No need of wasting expensive internal energy "FOCUS". አዎ! ትኩረት ውድ ነው። ይህን ውድ ውስጣዊ ሃይልም ማባከን አያስፈልግም። በተገቢው ቦታ፣ ለሚገባቸው ማድረግ፣ መስጠት ያስፈልጋል። ለሚገባው ካልተሰጠ ጉዳቱ ከፍ ይላል፣ ትርፉ ብክነት፣ ስብራት፣ እዞት፣ ቁጪት ይሆናል። የትኩረት አቅጣጫችንን ባስተካከልን ቁጥር በዙሪያችን ያሉ ነገሮችም በቀላሉ ይስተካከላሉ፣ በፈለግነው መንገድና ፍጥነት ይጓዛሉ። **አዎ!** ጀግናዬ..! አሁን ትኩረትህ ምን ላይ ነው። የምትወደው ውይስ የሚወድህ ላይ? ህልምህ ላይ ወይስ ተራ ወሬ ላይ? ዛሬ ላይ ወይስ ትናንትህ፣ ታሪክህ ላይ? እራስህ ላይ ወይስ ሰዎች ላይ?

አዎ! ትኩረትህ ወይ ያጠፋሃል ውይ ያለማሃል። የሚሰጥህ ምርጫ ይሔው ነው። አስፈላጊ ነገር ላይ ካተኮርክ ትለማለህ፤ ወደ አላስፈላጊው ከዞርክ ትጠፋለህ፣ ትበክናለህ። የትኩረት አሻጋሪነቱ በአመርቂ ውጤቱ የሚታይ ነው። አንድን ነገር ከልብህ መፈለግህ በሰጠህው ጊዜ፣ ቦታና ትኩረት ይወሰናል። አንዳንዴ እንደማያስፈልገን እያወቅን ትኩረታችን ግን ወደዛ ሔዷል፣ በእርሱ እንሳባለን፤ ወደዛ ወደማንፈልገው፣ ወደማይጠቅመን፣ ወደማያሻግረን፣ ምንም ወደማይጨምርልን ሃሳባችን ይሳባል። ትርፍ የሌለው ትኩረት እራስን ከመጉዳት አይተናነስም።

አዎ! በሙሉ ትኩረት የተሰራ ስራ አንድም ውጤቱ ያምራል ሁለት ቶሎ ፍሬ ያፈራል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ትኩረትህን... ለሚገባቸው፣ ለሚመጥናቸው ስጥ! ለሚወዱህ፣ ጊዜ፣ ትኩረት ለሰጡህ፣ ለለህልምህ፣ ለራዕይህ፣ ለግብህ፣ ለአላማህ፣ ለዛሬ፣ ለአሁን፣ ለስራህ፣ ለእራስህ፣ ለቤተሰብህ፣ ለሃገርህ። **አዎ!** የምታባክነው የትኩረት ሃይል አይኖርም፤ ትኩረትህን ለሚገባው፣ ለሚያስፈልገው፣ ለሚመጥነው ስትሰጥ የምትፈልገውን፣ የሚገባህን ታገኛለህ፣ እርሱም ወዳንተ ይመጣል፣ እጅጉን ታተርፋለህ፣ ወደ ተሻለው ከፍታም ትሸጋገራለህ።

20. “ህልምህ ነፃነትህ ነው!”

ህልምህ ላንተ ምንድነው? የድካምህ፣ የጮንቀትህ ምክንያት ነውን? እስር ቤት ነውን? የደስታህ ቀበኛ፣ የእረፍትህ ጠላት ነውን? የህይወትህ ፈተና፣ የመንገድህ መሰናክል ነውን? **አዎ!** ጀግናዬ...! ለህልምህ ያለህ ትርጉም እውንነቱን ይወስናል። እንደሚጎዳህ እየተሰማህ መቼም እንዲሰካ ልትጥር አትችልም። እንደ እስር ቤት እያሰብከው ነፃነት ሊሰማህ አይችልም። ስለእርሱ ባሰብክ ቁጥር እየተጨነክ ማረፍ አትችልም። ደስታ እንደነሳህ እያሰብክ የእርካታህ ምክንያት ሊሆን አይችልም።

እዎ! ለህልምህ ያለህን እይታ አስተካክል። ከብዙ ሃሳቦች እርሱን መርጠሀዋል፣ ሳትወደው አትመርጠውም፣ ሳይመችህ የህይወት ዘመን ህልምህ አላደረከውም። የመረጥክበት ምክንያት ያሳምንህ። ህልምህ እሰር ቤት ሳይሆን ከእስር ነፃ የሚያወጣህ፣ ነፃነትን የሚያድልህ ነው። ህልምህ የሚያደክምህ ሳይሆን የህሊና ሰላም፣ የህሊና እረፍት የሚሰጥህ ነው። ህልምህ የህይወት ፈተና ሳይሆን የህይወትህ ስጦታ፣ የመኖርህ ትርጉም ነው።

አዎ! ህልምህ ነፃነትህ ነው፤ ህልምህ ከፍታህ ነው፤ ህልምህ ስኬትህ ነው፤ ህልምህ ደስታህ ነው፤ ህልምህ ስሜትህ ቢበላሽም ያስተካክላል እንጂ መንስኤ አይሆንም። እያደረከው ሰላም ካልሰጠህ፣ ካስጨነቀህ፣ ነፃ ካላደረገህ፣ ሃሳቡ ካደከመህ እርሱ ህልምህ አይደለምና ዳግም እራስህን ተመልከት የህይወት ግብህን፣ አላማህን፣ ህልምህን ዳግም መርምረህ አግኝው፣ እርሱንም መርጠህ ኑረው።

21. “ብርቱ ነህና ሁሌም ትበረታለህ!”

አንዳንዴ አንዳንድ ሰዎች የወዳጅ ጠላት ሆነው ይቀርቡሃል፤ ሁሉ ነገርህን ወስደው ምንም ነገር እንደሌለህ ሲያስቡ ይተውሃል፤
ማንነትህን ካስቀየሩህ ቦሃላ አላዋቂ ይሆኑብሃል፤ ቅዝቃዜ ውስጥ ትተውህ ይሔዳሉ፣ እራስህን በእራስህ እንዴት እንደምታሞቅ ስትማር ግን ይናደዱብሃል፤ በጨለማ ውስጥ ብቻህን ጥለውህ ይሔዳሉ፣ ለእራስህ ብረሃን ሆነህ ስትታይም ይቀኑብሃል፤ ተቸግረህ እያዩህ ዝም ይሉሃል፣ በእራስህ ተቋቁመህ ስታልፈው አይናቸው ይቀላል፤ **አዎ!** እራሳቸውን ብርቱ ለማድረግ ያንተ ውድቀት ግዴታ ይመስላቸዋል፤ እነሱ ለመታወቅ ያንተ ስም መጥፋት አስፈላጊ እንደሆነ ያስባሉ፤ ያንተ ክስረት ለእነርሱ ስኬት አስተዋፅዖ የሚያደርግ ይመስላቸዋል፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! አንዳንዴ አንዳንዶች መንገድ እያላቸው ባንተ ላይ መራመድን ይመርጣሉ፤ የሩጫው መም ትርፍ ቦታ እያለው ባንተ መስመር ይከተሉሃል፣ ያንተን ውድቀት አብዝተው ይፈልጉታል። "ጠላቴን እኔ ጠብቃለሁ ከወዳጄ አንተ ጠብቀኝ" የሚለው ፀሎትም ለዚህ ጊዜ አስፈላጊነቱ ይገባሃል። የቅርበታቸው ልክ እድገትህን፣ ከፍታህን የማይመኙ ላያስመስላቸው ይችላል።

ዋጋቸውን እንድታውቅ ተጣብቀውብህ በሃይል ተገንጥለው ይላቀቁሃል፣ ያኔም ህመምህን ብቻህን ስታስታምም ይመለከቱሃል። በእነርሱ አለመኖር መጎዳትህን ማየት ይፈልጋሉ፤ ያለእነርሱ ባዶ እንደሆንክ ያስባሉ፤ ካልደገፉህ ልፍስፍስ፣ ደካማ፣ በእራስህ የማትቆም ይመስላቸዋል። ለዛም እላፊ ቀርበውህ ከተወዳጁህ ቦሃላ ጥለውህ ሊሔዱ ይሞከራሉ። አንተ ግን ሃሳባቸውን ሁሉ መና ታስቀራለህ፣ ከድርጊታቸው ብዙ ትማራለህ፣ በብዙ እጥፍ ጥለሃቸው ትሔዳለህ፣ የሃሳባቸውን ስሁትነት፣ የድርጊታቸውን ነውርነት ታስተምራቸዋለህ።

አዎ! ጀግናዬ..! አንተ በእራስህ ትቆማለህ፤ ምርኩዝ አያስፈልግህም፤ እራስህን ትችላለህ፤ እራስህን ታበቃለህ። ውድቀትህን ለሚጠባበቁ ቀና ብለህ ታሳያለህ፤ ድክመትህን ለሚመኙ ጥንካሬህን ታስመለክታለህ፤ መጠውለግህን ሲጠብቁ ፈካ ብለህ ትታያቸዋለህ፤ ለሃዘን ሲመኙህ በደስታ

ታበራላቸዋለህ፤ የትም ቢጥሉህ አብዋራህን አራግፈህ ትነሳለህ፣ አፋቸውን ዝም ታሰኛለህ። **አዎ!** አንተ በእራስህ ትቆማለህ፤ እንደገናም ደጋግመህ ትነሳለህ። ብርቱ ነህና ሁሌም ትበረታለህ፤ በርታ!

22. “የተሻለ እያሰቡ፣ በቃኝ የለም!”

ዛሬ እዚህ በእዚህ ሁኔታ እንደምትገኝ ታውቅ ነበርን? እንደዚህ አይነት ሰው እንደምትሆን የነገረህ አለ? አውቀህ ያጠፋሀው፣ አውቀህ የሳትከው መንገድ ነበርን? አውቀህ፣ አስበህ፣ አቅደህ የተለየሀው፣ የራከው ሰው አለን? አውቀህ ያሳለፍከው አጋጣሚ፣ ያልተጠቀምከው እድል ነበረን? **“NO!”** ሳታስበው በአጋጣሚ፣ እንደ እድል እዚህ አልደረስክም፤ ስለፈለከው፣ ስለሰራህበት ዛሬ እዚህ ነህ። **አዎ!** ጀግናዬ..! እውቀትህ ከፍ ሲል የምታያቸው አማራጮች አሉ፤ የተሻለውን ታስባለህ፤ የተሻለውን ትፈልጋለህ፤ በዚህ ፍለጋ ዛሬ ካለህበት ደርሰሃል።

ጉዞህ ሁሉ የተሻለ ነገር ፍለጋ ነው። የተሻለ ደስታ፣ የተሻለ ማንነት፣ የተሻለ ንብረት፣ የተሻለ ሰው። **አዎ!** ከቀድሞው የተሻለ፣ ከፍ የለ፣ አሁን ካለህ የተሻለውን ፍለጋም ፍለጋህን ትቀጥላለህ፣ መንገድህን ትጓዛለህ። "ዛሬ ያለኝ በቂ ነውና ሌላ አልፈልግም" ማለት ትችላለህ፣ አለም ግን እርሱን እንድትል አትፈቅድልህም። በየሰከንዱ አዲስ ነገር ትፈጥራለች፣ አዲስ ነገር ማየትህ አንተም በመንገድህ የተሻለን ፍለጋ እንድተጋ ያደርግልሃል። "የተሻለ ከሆነ የማይገባኝ ነገር የለም" ትላለህ። የምትመኘው ሰው ከዛሬው አንተነትህ የተሻለ ነው። የምታስበው ነገ ከዛሬ በብዙ ከፍ ያለ ነው። የምትናፍቀው ስራ ከዛሬው በእጅጉ የላቀ ነው። ለቤተሰብህ የምትመኘው የፍቅር ህይወት ከዛሬው በጣም የተሻለ ነው። ነገ ሀገርህ ችግሯ ጠፍቶ፣ ዜጎችዋ ተፋቅረው፣ ከድህነት ተላቀው፣ የሚፈልጉትን አግኝተው፣ ክብርን በተሻለ ተጎናፅፈው ማየትን ትመኛለህ።

አዎ! ጀግናዬ..! ፍለጋህ ብቻ እዚህ እንዳላደረሰህም ታውቃለህ፤ መኖትህ ብቻ የተሻለ ነገር እንዳላስገኘልህም ተረድተሃል፤ ትልቁን መመኘት ፈተና አለው። ፈተናው ጥቃቅን ነገሮችን ከመግፋት፣ ከመጠየፍ፣ ከመተው ይጀምራል። አስበው ጥለሃቸው የመጣህውን መንገድህን የሚያስቱ ጥቃቅን አሰናካይ እድሎች፤ ትናንት ትተሃቸው ዛሬ ግን በጊዜያቸው የመጡትን ግሩም በረከቶችም አስባቸው፤ የህይወት አለማህ /Life Purpose/ የተሻለ ነገር መፈለግ፣ የተሻለ ነገር መፍጠር፣ የተሻለ ስራ መስራት፣ የተሻለ ነገን መፍጠር እስከሆነ ድረስ በቃኝ ብለህ የምትተወው ነገር የለም፤ ምክንያቱም ሁሌም ከዛሬ የተሻለ ነገ አለ። ምክንያቱ ዛሬ የምታገኘው ደስታ ላይ መጨመር ትችላለህ፤ ገቢህን ማሳደግ ትችላል፤ ግንኙነተስህን /Social interaction/ በብዙ እጥፍ ማሻሻል ትችላል። የፍቅር፣ የትዳር ህይወትህን በበለጠ **“Romantic”** ማድረግ ትችላለህ፤ ስትፈልገው፣ ስትሰራበት፣ ስትለፋበት ሁሉም ከነበረበት ከፍ ይላል፣ የተሻለ አመርቂ ውጤት ያስገኛል።

አዎ! ጀግናዬ..! የተሻለ እያሰቡ በቃኝ የለም፤ ሁሌም የተሻለ፣ ከፍ ያለ ነገር አለና። በቃኝን ተወው፣ ፍለጋህን ቀጥል፤ አዲስ የተሻለ አንተን፣ የተሻለ ህይወትን፣ የተሻለ ከባቢን መፍጠርህን ግፋበት። የሚወድህ፣ የምትወደው ስላጣህ ሳይሆን፣ ምንም ቢፈጠር እራስህን መውደድ ስላለብህ ብቻ እራስህን ውደድ። ወደሀውም ሳትወደውም ሁሌ አብሮህ የሚሆነው እርሱ ነው፤ አጣህ አገኘህ፣ ተራብክ ጠገብክ፣ ታረዝክ ለበስክ አውጥተህ የማትጥለው፣ የማትቀይረው የገዛ ማንነት አለህ፤ መወደድን አትጠብቅ፣ እራስህን ውደድ፤ ተቀባይነትን አትጠብቅ፣ እራስህን ተቀበል፤ እምነትን አትጠብቅ፣ እራስህን እመን፤ ክብርን አትጠብቅ፣ እራስህን አክብር፤ እርዳታ አትፈልግ፣ እራስህን እርዳ፤ ጊዜ እንዲሰጥህ አትጠብቅ፣ ለእራስህ ጊዜ ስጥ፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! ፍቅርን ከራስ ጀምር፤ በመቀጠል የምታፈቅረውና የሚያፈቅርህን መቼም አታጣም።

23. “የምልከታህ፣ የእሳቤህ ጥራት ውጤቱን ይወስናል!”

የአለም ስጦታዎች፣ የፈጣሪ ግኚቶች ሁሌም በመውስጣቸው መልካም ነገር አለ። በሰው ልጅ ተፈጥሮ ሲሆን ደግሞ አስገራሚው ነገር በጣም ብዙ ነው፤ አስደናቂው መልካሙ ነገር በእየፈርጁ ነው። በወዳጃችን ውስጥ ማየት፣ መመልከት ያልቻልነው ስንት ልዩ፣ አስደሳች ባህሪ ይኖር ይሆን? እንደ ጠላት በፈርጅነው ሰው ውስጥ ስንት እኛንም የሚጠቅም መልካም ገፅ ይኖር ይሆን? **አዎ!** ጀግናዬ..! ሰውን ስትቀርበበው ታውቀዋለህ፣ የሚያበራውን፣ **“Shine”** የሚያደርገውን መልካሙን ማንነቱን መመልከት ትችላለህ። በርቀት ሆነህ ስለነገረህ ብቻ ከምታምን ያለ ንግግር የሚታይህን ብትቀበል፣ ብታምን መልካም ነው።

አዎ! እይታህን ቀይር፣ ምልከታህን አስተካክል። የትም ብትሔድ ማየት ያሰብከውን ታያለህ። ክፋቱን ማየት ከፈለክ እንደውም ሰውዬው ጭራቅ ሊሆንብህ ይችላል። ማየት የፈለከው መልካምነቱን ከሆን መልዓካዊ ባህሪው፣ ቅድስናው፣ ትህትናው፣ መልካምነቱ ጎልቶ ይታይሐል። የጠበከው ክፋት ከሆነ ይገንብሃል፣ ደረጃው ከፍ ይላል፤ እርሱ ክፉ ባይሆንም በውስጥህ የሳልከው ስዕል ክፋቱን ከሆን አንተ ፊት የሚቀርበው ክፋቱ ብቻ ይሆናል። **አዎ!** የምልከታህ፣ የእሳቤህ ጥራት ውጤቱን ይወስነናል። መልካሙን ጠብቅ፣ በጎውን አስብ መልካሙን ታያለህ፣ በጎውን ታገኛለህ፤ ጥሩውን ፈልግ፣ እርሱንም ታገኘዋለህ።

ክፋትን ፍለጋ ወቶ ጥሩ ያገኘ ሰው እጅግ ጥቂት ነው። ጥሩውን አስቦ፣ ተመኝቶ ጥሩ ያገኘ ግን እጅግ ብዙ ነው። ስኬትም ከአያሌዎቹ እጅግ መልካም ሃብቶች አንዱ ነውና ዘወትር ካሰብከው፣ ከተመኘህው፣ ከሰራህበት በብዙ እጥፍ ወደንተ ይመጣል። መልካሙን ማሰብ አያደክምህም፣ አይጎዳህም ስለዚህ፡- መልካሙን አስብ፣ እርሱን ተመኝ፤ አስደሳቹን፣ ጥሩውን እንድታገኝ።

24. “እንዳሰብሽው ባይሆንስ..?”

እንዳሰብሽው ባይሆንስ..? እንደጠበቅሽው ባይወድሽስ? እንደምታፈቅሪው ባያፈቅርሽስ? ምላሾቹ ቢዘገዩ፣ ቢቀዘቅዙስ? እንዳሰብሽው ባይንከባከብሽስ? ባሰብሽው ልክ ባይጠብቅሽስ? ፍቅርን ለማሰሽ ፍቅር ባይቸርሽስ? ያንቺ ቀጣይ እርምጃ ምንድነው? ወዴትስ ነው? **አዎ!** ጀግኒት..! ልብን አሳልፎ ሰጥቶ ማዘዝ ይከብዳል፤ ማንነትን ሰጥቶ እራስን መምራት፣ ማራመድ ከባድ ነው። በሌለ የእራስ ስብዕና ውስኖ ወደፊት መጓዝ አዳጋች ነው። ነገሮችን ከየአቅጣጫው መመልከት ጀምሪ፤ በምንም ሁኔታ፣ ምንም ቢፈጠር፣ ማንንም ብታጪ እራስሽን እስከማጣት ሊያደርስሽ እንደማይገባ እመኚ። ማንም ሰው፣ ሃሳቡና ድርጊቶቹ እራሱን ይወክላሉ። ለሰው ብሎ የሚያደርጋቸውን አንድ ቀን ያቆማል፤ ለእራሱ የሚያደርገውን፣ ይወክለኛል ያለውን በእድሜው ሙሉ ሲተገብረው ይኖራው። ምክንያቱም ሳያደርገው ቢገኝ እራሱን፣ ማንነቱን ሊያጣ ይችላልና።

አዎ! ላንቺ ስሜት ተጨንቆ ሳይሆን የእራሱ ስሜት አስገድዶት፣ ተገዝቶልሽ እንደወደደሽ እወቂ። ሩጫው ወደ ውጭ፣ ወደ ችግር ሳይሆን ወደ ውስጥ፣ ወደ መፍትሔ፣ ወደ ተሻሉ አማራጮች መሆኑን አረጋግጪ። **አዎ!** ጀግናዬ..! ዛሬ እርሷን ማጣትህን ባሰብክ ቅፅበት እራስህንም ማግኘት እንደምትችል አስብ። ዛሬን በህመም ማለፍ ላይገባህ ይችላል ነገ ግን ይህ ህመም ድጋሜ አይሰማህም፣ አንዴም ታልፈዋለህና ወደህ ተቀበለው። አንዳንዴ እንደማይሆን ልብህ እያወቀ ከእራስህ ጋር ትታገላለህ፤ መተው እያለብህ አትተውም፤ ማቆም እያለብህ አታቆምም፤ መራቅ እየቻልክ አትርቅም፤ በአመታት ያልተፈታ ችግር በእንድ ጀምበር እንዲፈታ ትጠብቃለህ፣ በፅኑ ተስፋ ታደርጋለህ። አትፍራ! ማንንም ልታጣ ትችላለህ፣ ማንም ሊለይህ ይችላል በዚህ መሃል እራስህን እንዳታጣ ተጠንቀቅ፣ ማንነትህ እንዳይሸር፣ እንዳይታወክ እራስህን ጠብቅ። ደካማነትህ እንዲጎዳህ አትፍቀድ፤ በቻልከው መጠን የሰውነት ክብርህን

አታሳንስ፤ ክብርን የሚፈልግ እራሱን ያከብራልና። መስጠት ያለብህን ነገር መጥን፣ እርሱን ለየው፣ ሁሉን ሰጥቶ ባዶ መቅረት አለና።

25. “ሃሳብህን መኖር ጀምር!”

ብዙ ማሰብህ አሁንም ሃሳብ ነው፤ ጥቂት መስራትህ መሞከርህ ግን ተግባር ነው። ከበዛው ሃሳብህ በብዙ እጥፍ ይሻላል፤ ሀይል አለው። ከአመታት የተከማቸ ሃሳብ የአንድ ቀን ተግባር፣ የአንድ ቀን እርምጃና ስራ የተሻለ ነገር ያሳያል። ውጤት የሌለው ሃሳብ ከተግባሩ በራቁ እቅዶች የተሞላ ነው። ፋታ የሚሰጥህ ይመስልሃል፣ ነገር ግን ሃሳብነቱ ወደኋላ ከመሳብና ባለማድረግህ ከመታዘብ ውጪ የሚያተርፍልህ ነገር የለም። ሃሳብ ብቻውን የትም አይደርስም፣ የትም አያደርስም ሲቆይ በሃሳብ ይተካል፤ ውጤት እንደናፈቀው ይቀራል፤ ትልቅነቱን ያጣል። ትልቅ ህልም እንዳለህ እያወቅክ ነገር ግን ካልኖርከው ትርጉም የለውም፤ ከማሰብህ ብዛት፣ ሃሳብ ሲታክትህ ከሚተገበር በተጠና፣ በታቀደ መልኩ ቢተገበር፣ ወደስራም ቢገባ ውጤቱ ያማረ ይሆናል።

አዎ! ጀግናዬ..! ሃሳብ አታብዛ! ተግባር ላይ አተኩር፤ መንገድህን በብዙ እቅድ አትሰር፣ በእርምጃህ፣ በፍጥነትህ ልክ አድርገው፤ ባለመቻልህ የምታዝንበት፣ የምትቆጭበት፣ ባለመሳካቱም የምትፀፀትበት ምክንያት የለህም። ብዙ ከማሰብህ ጥቂት መሞከርህ የሚታይ ነገር አምጥቷል፣ ቢሳካም ባይሳካም የሆነ ነገር አሳይቶሃል፣ የት እንዳለህ፣ ምን እንደምትችል፣ ምን እንደሚያዋጣህ አስመልክቶሃል። **አዎ!** ሃሳብህን በትንሹ መተግበርህን ቀጥል፤ መስጠት የምታስበውንም በትንሹ ማካፈል፣ መስጠት፣ መለገስ ሞክር፤ እርምጃህንም ቀስ በቀስ ማድረግህን ቀጥል፤ ሃሳብ አንግበህ ከአመት አመት አትሻገር፤ ዛሬ የተግባር ሰው ሁን፤ ሃሳብህን መኖር ጀምር፤ አንድ እርምጃ ወደፊት ተጓዝ፣ ለሚታይ ውጤት እራስህን አቅርብ።

26. “የጀመርከው ለመጨረስ ነው!”

ስትሸነፍ የሚያበቃ ነገር የለም፤ ስታቆም ግን ያበቃል። ስትሰበር የሚያቆም ነገር የለም፤ ተስፋ ስትቆርጥ ግን ይቆማል። ስትደክም፣ ሰውነትህ ሲዝል የሚበቃ ነገር የለም፤ ትግልህን ስትተወው፣ ስተጠላው ግን ሁሉም ያበቃል። ስትተች፣ ስትገለል የምታጣው ነገር የለም፤ በእርሱ ስታዝን፣ ስትሰበር ግን እራስህንም እስከማጣት ትደርሳለህ። **አዎ!** ጀግናዬ..! ማቆም ትችላለህ ነገር ግን ስትጨርስ፤ መተው ትችላለህ ነገር ግን ፍሬውን ካየህ ቦሃላ ፤መቅረት ትችላለህ ነገር ግን ከደረስክ ቦሃላ።

አዎ! ጀምረህ የምትተወው ነገር የለም፤ ፍሬውን ሳታይ መንከባከብህን የምታቆመው ሰብል የለም። ሃሳብህ፣ አላማህ፣ ግብህ መጨረሻውን ማየት ነው፤ ከፍፃሜው መድረስ ነው። ስኬትህን በማቆም፣ በመተው፣ በማቋረጥ በፍፁም ልታውቀው፣ ልታየው አትችልም። ያቋረጠ መጨረሻው ከመንገድ መቅረት ነው።

አዎ! የጀመርከው ለመጨረስ ነውና ጅማሬህን ከፍፃሜው ለማድረስ ታገል፤ በተስፋህ ውስጥ የሚታይህን የስኬት አለም ዛሬ የጀመርከውን በጅምር ትተህ ልታገኘው፣ ልትጨብጠው አትችልም። የተሻለውን ነገ ማየትህን ቀጥል፤ ማለምህን ቀጥል፣ ለእርሱም መትጋትህን ግፋበት። ሁሌም ነገሮች በነበሩበት አይቀጥሉም መኖር የምትችለው ዛሬ በእጅህ አለ፣ ማስተካከል የምትችለው ነገም በመዳፍህ ነውና ተስፋን ሰንቅ፤ በርታ፤ ጅማሬህንም ከዳር አድርስ።

27. “እውቀትህ ከማንም ይለይሃል!”

ታነባለህ? በጣም አሪፍ! ብዙ አምብበሃል? ብዙ አውቀሃል? በጣም ግሩም ደስ ይላል። በማንበብህ፣ በማወቅህ እርግጠኛ እንደሆንከው፣ እውቀትህን በመኖርህ፣ ንባብህን በመተግበርህ ምንያህል እርግጠኛ ነህ? እውቀት ሲበስል ደስ ይላል፤ ፍሬው ይጣፍጣል። ብዙ ማንበብህ ምናልባት አዕምሮህን ለተግባር ሊያዘጋጀው ይችላል፣ የተሻልክ ሰው ያደርግሃል፣ ልዩነት ፈጣሪ ልዩ ሰው ያደርግሃል። ንባብህን፣ እውቀትህን ስትጠቀመው ግን ሙሉ አዋቂ፣ አድረጊ፣ የተግባር ሰው፣ ግሩም ተምሳሌት ሰው ያደርግሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! እውቀትህ ካማንም ይለይሃል፤ ተግባርህ ግን ከሁሉም ያስበልጥሃል። የጊዜ ችግር እውቀት ብቻ አይደለም፣ ንባብ ብቻ አይደለም ያወቁትን መኖር፣ መተግበር፣ በገሃድ አለም ማሳየት፣ መፈፀም ነው። በማንበብህ የተሻልክ ሰው ነህ፣ በተግባርህ ግን እጅግ አስገራሚ፣ አስደማሚ ተዓምረኛ ሰው መሆን ትችላለህ። አስበው እውቀትህ በተግባር ቢታገዝ፣ በምግባር ቢሞላ የት ትደርሳለህ፣ ምን ስታደርግ ነበር፣ ከማን ጋር ነበርክ። ያወከውን ለማካፈልም ሆነ ለመኖር ድፍረት ያስፈልግሃል፣ ቆራጥነት ወሳኝ ነው። ለእውቀት ባዳ የሆነ ሰው እንደ አዋቂ በሚቆጠርበት፣ በማይመለከተው በሚገባበት፣ አላዋቂነቱን በሃሳቦቹ፣ በተገባሩ በሚያስመሰክርበት በዚህ ጊዜ ያንተ እውቀትህን መሸሸግህ፣ አበርክቶትህን፣ እርዳታህን ማጉደለህ አንተንም ሆነ በዙሪያህ ያሉትን እንዲሁም ሃገርህን ብዙ ያሳጠችኋል። ክብራችሁን፣ የሚገባችሁን ስፍራ፣ የሚገባችህን፣ የሚመጥናችሁን ስጦታ ያሳጣችኋል። **አዎ!** ጀግናዬ..! አዋቂ የተግባር ሰው ሁን፣ የድርሻህን ተወጣ፤ እራስህን አሳርፍ፣ ቤተሰብህን ደግፍ፣ ሃገርህን አበርታ።

28. “ጎዶሎው ነገሬ” (The Missing Piece)

የአንድ ሰው እውነተኛ “ኑዛዜ” መልኬ ላይ፣ ቁመናዬ ላይ፣ ማንነቴ ላይ፣ ዘሬ ላይ፣ ቋንቋዬ ላይ የሆነ የጎደለ ነገር (Missing Piece) እንዳለ ሲሰማኝ ሰነባብቷል። ብቻ ምን አለፋችሁ ከማንነቴ ላይ ተቆርጦ የወጣ የሆነ ነገር እንዳለ እስከሚሰማኝ ድረስ ጎዶሎነትና ባዶነት ይሰማኝ ነበር። ከዚያም ያንን የጎደለ ነገር አግኝቼና አምጥቼ ማንነቴ ላይ ብለጥፈው ሙሉ የምሆን ስለመሰለኝ ያልሄድኩበት ቦታና ያላደረኩት ነገር የለኝም።

በዚህ ጥረቴ ብዙ ነገሮችንም ሞክሬአለሁ። የሚቀባውንም ተቀብቼ፣ የሚለበሰውንም ለብሼ፣ የሚቀየረውንም የራሴን ሁኔታ ለመቀያዬር ሞክሬ፣ ያልሆንኩትን ሆኜና የሆንኩትን ትቼ፣ በዙሪያዬ ያሉትንም እስከመምሰል ራሴን ለውጬ ሞከርኩት። አሁንም ግን ያ ጎዶሎው ነገር አልሞላም ነበር። አሁን አሁን ግን አንድ እውነት እየገባኝ ስለመጣ መረጋጋት ጀምሬአለሁ። ለካስ የጎደለኝ ነገር መነሻው ውጫዊ ሳይሆን ውስጣዊ ነው። ምንም አይነት ውጫዊ ነገሬን በማሟላቴ ደስተኛ ለመሆን ከመሞከሬ በፊት በመጀመሪያ ራሴን ከነማንነቴ (ብርቱውንም ደካማውንም) መቀበልና መረጋጋት እንዳለብኝ ገብቶኛል። የጎደለው ነገሬ “ካለምንም ቅድመ ሁኔታ ራስን መቀበል” የሚባለው ዘመን የማይሽረው እውነታ ነው።

29. “በትናንሽ ጥያቄዎች አምላክህን አታሳንሰው!”

ፈጣሪ አምላክህን በቤቱ ተመላልሰህ፣ ከልብህ ተማፅነህ፣ ለምነህ ያላደረገልህ፣ ያልመለሰልህ ጥያቄ በእውነቱ አለን? የምላሾቹን ሁኔታ ካተረዳህ ምናልባት ዝምታውም ከዋናዎች ምላሾች አንዱ ነው። ያንተ እይታ ስጋዊ ነው። የምትፈልገው ነገር ሁሌ እንደሚጠቅምህ ታስባለህ፤ የጎደለህ፣ የሌለህ ነገር ሲሰጥህ ሙሉ እንደሚያደርግህ ይሰማሃል፤ ብዙ ታግሰህ ባልተፈፀመልህ ጉዳይ አምላክህን ታማርራለህ፣ የእይታህ ውስንነት የአምላክህን ረቂነት ይጋርድብሃል፤ ስጋዊው ፍላጎትህ የአምላክን መለኮታዊ ሃይል

ይሰውርብሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! በትናንሽ ጥያቄዎች አምላክህን አታሳንሰው! ካንተ በላይ አስቦልህ የሰጠህን ትልቅ ነገር ዛሬ ባመጣሀው ትንሽ ፍላጎት አትሰውረው። እርሱኮ ፈጣሪህ ነው፣ የሚገባህን የሚያስፈልግህን የማያውቅ ይመስልሃል? **አዎ!** መቼም አንተ ለእራስህ ከምታስበው ባልተናነሰ ይልቁንም በብዙ እጥፍ በበለጠ የሚሳሳልህ፣ የሚያስብልህ ድንቅ አምላክ አለህ፣ ትልቅነቱን የሚያሳይ፣ የሚመጥነው ጥያቄ ባይኖርም በቻልከው መጠን በትናንሽ ጥያቄዎች ፋታ አትንሳው፣ ትልቅ ሆኖ ሳለ አታሳንሰው፤ ረቂቅ ሆኖ ሳለ አታቅልለው፤ ቸር ሆኖ ሳለ ንፉግ አታድርገው፤ ሁሉን ቻይ ሆኖ ሳለ ቁጡ አታስመስለው፤ **አዎ!** ለረጅም አመታት ጠይቀህ ዛሬም መልስ ያላገኘህለት ጉዳይ ይኖርሃል፣ ዛሬ ቢሆኑልህ ደስ ይሚልህ፣ ምናልባትም ከጭንቀትህ የሚያሳርፉህ አያሌ ጉዳዮች ይኖሩሃል፣ በሰዎች ሳይሆን በአምላክ ብቻ የሚፈቱልህ ብርቱ ችግሮች ይኖሩሃል።

ታገስ! ምድራዊ ፍርድን የሚፈርደውን፣ ትክክል ይሁን አይሁን የማታውቀውን ዳኛ ለአመታት ታግሰህ፣ በስራው ሁሉ እንከን የሌለው፣ በፍርዱ ሁሉ ፍፁም የሆነ አምላክን ለትንሽ ጊዜ መታገስ እንዴት ይከብድሃል? **አዎ!** ጀግናዬ..! የሚገባህን በትዕግስትህ፣ በፅናትህ ልክ እርሱ ይሰጥሃል፣ በእርሱ አፈጣጠር አንተ እንከን የለህም፣ የሚጨምርልህም ሁሉ ስለጎደለህ ሳይሆን ስለሚያስፈልግህና ስለሚገባህ ነው። አምላክህን ታገስ! በእርሱ ታመን! ጥቄህን፣ ተማፅኖህን በታላቅነቱ ለካው፣ ተስፋህንም በእርሱ ላይ አድርግ።

30. “ጽኑ ፍላጎት ይኑርህ!”

ለማደግ ከፈለግህ ራስህን ለማሻሻል ጽኑ ፍላጎት ሊኖርህ ይገባል። ራስን ማሻሻል ማለት ባሉበት ሳይረኩ ከዛሬ ሁኔታ የተሻለ ነገር ውስጥ ለመግባት አስፈላጊውን ነገር ማድረግ ማለት ነው። የተግባር ጥራትና ውጤት ስለተመኘሁት ብቻ አይመጣም። በሌላ አባባል የእኔ መሻሻል በቀጥታ ከተግባሬ፣ ከኑሮዬና ከገቢዬ መሻሻል ጋር ግንኙነት አለው። ብዙ ሰዎች ኑሮአቸው፣ የገቢ ምንጫቸውና የመሳሰሉት ነገሮች እንዲሻሻሉ ይመኛሉ፣ ራሳቸውን ስለማሻሻል ግን አስበውበትም አያውቁም። አእምሮዬ እንዲሻሻል ማንበብ የግድ ነው።

የገቢ ምንጬ እንዲሻሻል እውቀቴንና ብቃቴን ማሻሻል የግድ ነው። የእኔነቴና የብቃቴ መሻሻል ዙሪያዬን ሁሉ የማሻሻልና ነገሮችን ለመልካም የመለወጥ ብርታትና ተጽእኖ አለው። ራስን በማሻሻል የተግባር ስኬት ውስጥ ለመግባት የሚከተሉትን ጥያቄዎች መጠየቅ ትችላለህ። ማድረግ የምፈልገውንና የሚሳካልኝን አውቄ መተግበር ጀምሬአለሁ? ማድረግ የሚሳካልህን ነገር ለይተህ እወቀውና በዚያ ዙሪያ መገንባትን ጀምር። የማይሳካልህ ላይ ከማተኮርና ከመድከም ይልቅ የሚሳካልህ ላይ በማተኮር መገንባት የበለጠ ውጤታማ ያደርግሃል። ብቃትህንና መድረስ የምትችልበትን ደረጃ በሚሳካልህና በቀላሉ በሚፈስስልህ ሁኔታ እንጂ በሚያቅትህና በሚያታግልህ ነገር አትመዝነው። ይህንን ተግባር ማደግ የሚገባው ደረጃ ድረስ አሳድጌዋለሁ?

የሚሳካልህንና የምትፈልገውን ለይተህ መተግበር ከጀመርክ በኋላ ትኩረትህ ያንን ተግባር ወደ ማሳደግ ይሁን። በቅጡ ካላዳበርካቸው የትም ከማያደርሱህ ጥቃቅን ችሎታዎች ጋር ብቻ ከምትታገል በአንድ ነገር በሚገባ መብሰል ውጤቱ የላቀ ነው። ቢያንስ በአንድ ነገር እስከጥጉ የደረሰን እውቀት ለማዳበር ወስን፣ ያንንም ተከታተል። ለእርማት ልቦናዬ ክፍት ነው? “አውቃለሁ፣ ማንም ሊመክረኝና ሊያርመኝ አይችልም” የሚል አመለካከት ያለው ሰው ራሱን ለኋላ ቀርነት ያቀረበ ሰው ነው። እኛ ያላየነውን የሚያዩ፣ የማናውቀውን ደግሞ የሚያውቁ በርካታ ሰዎች በዙሪያችን እንዳሉ በማመን ራሳችንን ለእርማት መክፈት ጠቃሚ ነው። ይህ ከሌላው የመማር “ቀላልነት” የታላላቅ ሰዎች እይታ ነው።

31. “እራስህን አግኝ!”

በህይወት የቀላል ከባድ፣ የትነሽ ትልቅ የምንላቸው የተለያዩ ተግባራት አሉ። እራስን መፈለግ፣ ማግኘት መቻል ከዛም እራስን ማሳደግና ማብቃት የቀላል ከባድ ጉዳይ ነው። ቅለቱ ወጪ የሌለው መሆኑ ነው ክብደቱ ከእራስ ጋር ጠንከር ያለ ትግል መፈለጉ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! እራስህን አግኘው! እኔ ማን ነኝ? ምንድነኝ? ምን እችላለሁ? በምንስ ብቁ ነኝ? ምን ያንሰኛል? ዛሬ እስኬት መራመድ እችላለሁ? ነገስ መዳረሻዬ የት ነው? **አዎ!** በፍላጎትህ መነሻነት እራስህን ትፈልጋለህ፣ በክህሎትህ አጋዥነት ታገኘዋለህ፣ በብቃትህ፣ በብርታትህ ልኬት ታወጣዋለህ፣ ታሳድገዋለህ፣ ታበቃዋለህ። የውጪ ግፊትን /External Pressure/፣ ጫናን እንደ አበርታችና አጋዥ ሃይል መጠቀም የሚኖርብህ ጊዜም ይኖራል። በተለመደው አባባል "ሁሉም ነገር ለበጎ ነው" መሆን ስላለበት ይሆናል፣ ከሆነ አይቀር ስለምን አልጠቀምበትም፣ አላድግበትም፣ ብቁ አለሆንበትም? የሚለው እሳቤም ተከትሎ መምጣት ይኖርበታል።

አዎ! እድገት ሁሌም ስትፈልገው የምትኖረው አይደለም፣ ዘወትር በዙሪያህ ያለ የሚፈልግህ፣ ለመገኘት የቀረበ፣ በሒደት ለመተግበር ይቀለለ፣ ትልቅ ግብዓት፣ የተለየ እርዳታ የማይፈልግ እጅጉን አስፈላጊና ወሳኝ የህይወት መርህና ኩነት ነው። እራሱን የማያውቅ፣ እራሱን ያላገኘ፣ ያላበቃ፣ ያላሳደገ ሰው ፈልጎና መርጦ በፈጠረው ተመሳሳይ የድግግሞሽ አለው ሲኳትን መዋሉ ግልፅ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! በእራስህ ተስፋ አትቁረጥ፣ እለት እለት ፈልገው፣ በፍለጋህ ብዛት የማታውቀውን፣ ያልጠበከውን አንተን ታገኘዋለህ፣ ግኚት፣ እወቀትህ ወደ እድገትህ፣ ወደ ከፍታህ፣ ወደ ብቁነትህ ይመራሃል፣ በአዳዲስ የለውጥ ሂደቶች፣ በተለዩ ግኚቶች የተሞላውን ህይወትም ማጣጣም ትጀምራለህ። ፍለጋህን ቀጥል፣ እራስህን አግኝ፣ እራስህን አብቃ።

32. “ትኩረትህን እራስህ ላይ ብታደርግስ?”

መታደል ይሁን አለመታደል፣ መመረጥ ይሁን አለመመረጥ፣ መመረቅ ይሁን አለመመረቅ እንዲሁ በልማድ በውስጣችን ያለውን እልፍ ጉድፍ ትተን የምናያትን ትንሿን የሰዎች ጥፋት ለማጉላት፣ ለማውራት እንሯሯጣለን። በሰው እንደመፍረድ ቀላል ነገር የለም ለዛም ቀላሉን እንመረጣለን። **አዎ!** ከባዱን የመረጠ ሰውን ለመተቸት፣ ስለሰው ለማውራት ጊዜም አይኖረውም። ስለ ሰዎች ድክመትና ክፍተት ማውራት ህይወቱን እንደማይቀይረው፣ ምንም እንደማጨምርለት ጠንቅቆ ያውቃል። ዋናው ጉዳዩ የእራሱ ነገር እንጂ የሰፈር አሉባልታ አይደለም። ፍላጎቱም ሆነ ምርጫው ሰዎች ሳይሆኑ እራሱ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! አንተስ ትኩረትህን እራስህ ላይ ብታደርግስ? ስለራስህ ማሰብ ብትጀምርስ? የምትወደው ላይ ብታተኩርስ? የማያልቀውን የሰው ህይወት መመርመርህን ብተተወውስ? የምታጣው፣ የሚቀነስብ፣ የሚቀርብህ ነገር አለን? አውቀህ በማትጨርሰው የሰው ልጅ መቋጫ አልባ ጉዳይ እስከ መቼ ትባክናለህ፣ ትጨነቃለህ፣ ትበክናለህ? **አዎ!** ትኩረትህን እራስህ ላይ አድርግ፣ ሃሳብህን ወደራስህ መልስ፣ ተግባሮችህ ሁሉ ከፍታህን የሚያፋጥኑ እንደሚሆኑ ተማመን፤ በድርጊቶችህ እመን! በሃሳብህ ፅና።

33. “ሁሌም በከፍታው ለመቆየት ታገል!”

“There are always ups and downs; But always strive to stay high.” ሁሌም ከፍታና ዝቅታ ይኖራል፤ ነገር ግን ሁሌም በከፍታው ለመቆየት ታገል። **አዎ!** ሁሌም ማግኘት ማጣት አለ፤ መደሰት ማዘን አለ፤ መውጣት መውረድ አለ፤ መብለጥ መበለጥ አለ፤ መጤን መታመሙ አለ፤ ነገር

ግን ከፍታው ላይ ለመቆየት ሞክር። የጊዜና የተፈጥሮ ጉዳይ ይሆንና ዘወትር ባለህበት ከፍታና የደስታ አለም ላትቆይ ትችላለህ። ጥረትህን በጨመርክ ልክ ግን ቆይታህም ይረዝማል። ምኞትን ጥላቻ አለመመቸትን የሚመርጥ፣ ደስታን በመጠየፍ ለሃዘን እጁን የሚሰጥ፣ ከፍታውን ትቶ ወደ ዝቅታ፣ ቁልቁል የሚሮጥ አንዳች ላይገኝ ይችላል። ህይወት ግን ሁሌም አልጋበአልጋ አትሆንልንም፣ በለንበት ከፍታ አታስቀምጠንም አንዳንዴ ዝቅ ማለትን ታሳየናለች፤ ሁሌም በደስታ አትሞላንም አንዳንዴ በሃዘን ትጎሽመናለች፤ ሁሌም ሃሴትን አትለግሰንም አንዳንዴ በአስጨናቂ ክስተቶች ትከበናለች።

አዎ! ጀግናዬ..! ሁሌም በከፍታው ለመቆየት ታገል፤ ከፍታውን መምረጥህን ቀጥል፣ ስፍራህ ከፍታ እንደሆነ እመን፣ መውረድን እምቢ በለ፤ ፍራቻህን ተጋፈጠው፣ ትቺትን ተላመደው፣ ሃዘንን ተቀበለው፣ አስተናግደው እንዳመጣጡም መልሰው፣ ሸኘው። ፈልጎ የሚወድቅ እንዳለመኖሩ አንተም ከከፍታው በቀላሉ አትውረድ፣ የሙጢኝ በል። ፈተና ቢበዛም፣ ሽንፈት ቢቀርብህም በፍፁም እጅህን አትስጥ፤ በከፍታው ለመቆየት ከሚጠበቅብህ በላይ ታገል።

34. “እዚህ ያለሀው ለምንድነው?”

እዚህ ያለሀው ለምንድነው? እዚህ የደረስከው ለምንድነው? ለምን ጀመርክ? ለምን ያንን ተውከው? ለምን ይህን ወደድክ? ለምን ለዚህ ያንን ከፈልክ? ስለምንስ ሌሎች አማራጮችን ትተህ ይህን መረጥክ? **አዎ!** ጀግናዬ..! እዚህ ያለሀው፣ ይህን የመረጥከው፣ በዘህ የመጣህው ልዩነት ለመፍጠር ነው፤ የተሻለ ለማግኘት፣ የተሻልክ ለመሆን ነው፤ ጥረትህን ለማሳደግ፣ ገቢህን ለመጨመር ነው፤ እራስህን ለማብቃት፣ ህልምህን ለመኖር ነው፤ **አዎ!** በምንም ሁኔታ የወረደ፣ የዘቀጠ፣ የማይሆንህ፣ የማይመችህ፣ የማያስኬድህ፣ የማይቀይርህ፣ የማያስደስትህ ነገር ልትመርጥ አትችልም። ትናንትም፣ ዛሬም፣ ነገም ሁሌም ምርጫ አለህ። ነገር ግን የማይገባህን፣ የማይመጥንህን ለመምረጥ የታገልክ እንደሆነ እርሱን የሚመጥንህንና የሚገባህን ታጣለህ።

ከአቅም በላይ መንጠራራት ከአቅም በላይ ጭንቀት ያስከትላል፤ በልክ አለመኖር ድካምን፣ ዝለትን፣ መታከትን ይስባል፤ በመጠን አለመኖር ነገን ያጨልማል፣ እራስን ለፈተና ያጋልጣል፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! የህይወትህ ማብቂያ መቼ ነው? መኖር የምታቆመው መቼ ነው? ምድራዊ ጉዞህ የሚገታው መቼ ነው? አንድም በአምላክ ፍቃድ ነፍስህ ከስጋህ ስትለይ ሌላም ተስፋን ስታጣ፣ ተስፋ ስትቆርጥ፣ የተሻሉ አማራጮችን ማየረት ስታቆም፣ ብርታትህን ስትረሳ፣ ትግልህን ስታቆም ነው። ህይወትህን ትርጉም ስጠው፤ ጠዓም ስጠው፣ በተስፋ ሙላው፣ በሃሴት ደግፈው፣ በአድራጊነትህ አስውበው፣ በደስታ ሙላው።

35. “እቅድህ የህልምህ መንገድ ነው!”

በነበር እንዳይቀር እንዲዘልቅ ውጥኑ መሰረቱን አፅና እንዲሆንልህ ፅኑ ጅማሬህ አምሮ ፍፃሜ ባይሰምር እቅድህ ቢከብድህ ቢርቅ ከተግባር ውጥኑን ማስተቃከል እንደገና መቃኘት ግብህን አስቀምጠህ እቅድህን ማስተካከሉን አንተው እወቅበት **አዎ!** ጀግናዬ..! እቅድህን ማስተካከሉን እወቅበት፣ ያልተሳካው፣ ያልሆነልህ፦ በአላማህ ክብደት፣ በግብህ አይሞከሬነት፣ በህልምህ አይቻሌነት አይደለም። በእቅድህ፣ በውጥንም ትንሽነት፣ በተግባራትህ ፈር አልባነት፣ በድርጊትህ ቀጣይነት ማጣት ይሆናል። የእቅድህ አስፈላጊነት ትልቁን ህሕምህን በተከፋፈለ ትናንሽ፣ አጭጭርና ቀጣይነት ባለው ትግበራ እንድታሳካው ለማድረግ ነው። ይህም እቅዶችህ ሁሉ የተጠኑና ሊተገበሩ የሚችሉ መሆን እንዳለባቸው ማሳያ ነው። እንደየሁኔታው በችግር የለውም አስተሳሰብ፣ በምንም አይሆንም አባዜ አስሬ አትቀያይረው፣ ያሻሻልክ እየመሰለህ ይባስ አታወሳስው።

አዎ! እቅድህ የህልምህ መንገድ ነው፣ አንዱን ሳትጨርስ ሌላ መንገድ፣ ሌላ ጎዳና አትጀምር፣ በቀጣይነት መተግበር ያለበትን እያንደንዱን እቅድ በተመሳሳይ ጊዜ በተመሳሳይ ሁኔታ ለመከወን አትሞክር። መቆጠብ ያለብህን ሃይል ለቀጣይ ጉዞህ አስቀምጠው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ለትግበራ የሚከብድ እቅድ ለምንም አይመችም፤ ማስተካከል፣ ማረም ከለብህ የህሕምህን መንገድ እቅድህን እንጂ ትልቁን ህልምህን አይደለም። ህልምህ ሁሉም ይቻላል፤ እንዴትም ይሆናል፤ ቤትኛውም መንገድ ይሳካል። ግብህ የእውነት ግብ ነው፤ የሚታይ፣ የሚደረግ፣ የሚተገበር፣ የሚጨበጥ፣ የሚፈፀም። ራዕይህም በእውነት የሚታይ ነው፤ እውን የሚሆን፣ የሚዳሰስ፣ በእርቅጥም ባንተ የሚሳካ የሚኖር ነው።

36. “ኩራት ከእራስ ይጀምራል!”

እስካሁን ተስፋ ባለመቁረጥህ ኩራ፤ እራስህን ባለማጣትህ ደስ ይበልህ፤ ወድቀህ ባለመቅረትህ፣ እንቅፋቶችህን በማለፍህ፣ ትቺቶችን ባለመስማትህ፣ ጉዞህን በመቀጠልህ፣ ሁሌም ከትናንት የተሻለ ከባቢ ለመፍጠር በመጣርህ ዘወትር ኩራ። **አዎ!** ጀግናዬ..! የምትሰራው ከልብህ የምትወደውን ስራ ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን እንደምትወደው አድርገህ እየሰራህ ነው። የምትኖረው ህይወት የፈለከውን ያክል ላያስደስትህ ይችላል፣ ነገር ግን ሳታማርር ወደሀው፣ በደስታ እየኖርክ ነው። የከበቡህ ሰዎች በትቺታና በአሉታዊ ሃሳቦች አስጨንቀውህ ይሆናል፣ አንተ ግን ዛሬም ደስታህን እንዲቀሙህ አልፈቀድክም።

አዎ! ጀግኒት..! በእራስሽ የምትኮሪው ሰው ባደረገልሽ እርዳታ ወይም አበርክቶት አይደለም፤ እራስሽን ስለተረዳሽ፣ ስታስፈጊያት ከጎኗ ስለቆምሽ፣ ድክመቷን፣ ክፍተቷን ስለተቀበልሽ፣ እለት እለት እርማት ስለምትሰጪያት፣ ከልብ ስለምትወጂያት በተወዳጇ አንቺ መኩራት ይኖርብሻል። የእራስ ማንነት ልህቀት ለሚደርጉት ነገር ሁሉ ሃላፊነት በመውሰድና የነገሮችን ተፈጥሮ ከአምላክ ቀጥሎ ከእራስ በመጠበቅ የሚመጣ ነው። ሁሌም አንተ የምትሰራውን ስራ "ከእኔ ሌላ በተሻለ ሁኔታ ሊሰራው የሚችል ማንም አይኖርም" የሚል እሳቤ በውስጥህ መፍጠር ይኖርብሃል፣ ሃላፊነትህን እራስህ ተወጣ፣ ግዴታህን ስለገፋህ፣ ስለጠላሀው ብቻ ነገሮች የተሻሉና አንተን ነፃ ሊያደርጉህ አይችሉም፤ ብቁም አትሆንም።

በጥልቅ ሀዘንና ክፋትሽ፣ ያጣሽው አይመለስም ባይሆን በጥንካሬሽና በተማርሽው ልክ የተሻለ፣ ከፍ ያለ፣ የሚመጥንሽ ሌላ እስከ ወዲያኛው የአንቺ የሆነ ነገር ሊቸርሽ ይችላል። ማጣትሽ ለተሻለው እንጂ ለባሰው እንደማያበቃሽ እመኚ፤ ያንቺም እሳቤ ከበፊቱ የተሻለ ነውና የተሻለው እንደሚመጣ አትጠራጠሪ። **አዎ!** ኩራት በነገሮች መምጣትና መቅረት ሳይሆን፣ ሁሌም ባለው ነገር፣ በቋሚው ሁሌም አብሮን በሚኖረው፣ እኛነታችንን በሚገልፀው፣ ባለን ነገር አሃዱ ይባላል። **አዎ!** ኩራት ከእራስ ይጀምራልና ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በእራስህ ኩራ፣ በአንተነትህ ደስ ይበልህ፣ በማንነትህ ሃሴት አድርግ፤ ቀሪዎቹ የሚመጡት፣ የሚጨመሩልህ ሁሉ ባትፈልግም ዋጋህን ከፍ ያደርጋሉ፣ ኩራትህን ይጨምራሉ።

37. “አትስጣቸው፤ ተዋቸው!”

አትጀምርምን ጀምረህ አሳይ፤ አትችልምን ችለህ አሳይ፤ አታደርገውምን አድርገህ አሳይ፤ አይገባህምን አግኝተህ አስመስክር፤ ምንም አታመጣምን አንድ ነገር አምጥተህ አስረሳ፤ ብቃትህን በተግባር ችሎታህን በተጨባጭ ለውጥ አሳይ፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! ትናንት መነቀፍህ፣ ዛሬ መተቸትህ፣ አሁን መገፋትህ የሚያቆምህ አንተ ስትፈቅድለት ብቻ ነው። ያንተ ከፍታ በወረኞችና በሰነፎች የሚመዘን አይደለም። እነርሱ ማውራቱን ይችላሉ አንተ ግን ማድረጉን ትችላለህ፣ እነርሱ ማንቋሸሹን ተክነዋል አንተ ግን መስራቱን አውቀህበታል፤ እነርሱ መተቸቱን ያውቃሉ አንተ ግን ማሳየትህን ታውቃለህ፤ **አዎ!**

ልኬትህ እነርሱ አይደሉም፤ ሚዛንህ የእነርሱ የወረደ እይታ አይደለም፤ ውደድርህ ከጥቃቅን ሃሳብ ባለቤቶች ጋር አይደለም። ልኬትህ ከትናንትናው አንተ ጋር ነው። ሚዛንህ ያለፈው ማንነትህ ነው፤ ውደድርህ ከሚገዳደርህ ውስጣዊ አቅምህ፣ አምላክ ካደለህ ሃይልህ ጋር ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! በየቀኑ ይናገሩህ፣ ይተቹህ፣ ያውርዱህ፣ ያዋርዱህ፣ ይስደቡህ፣ ቡና መጠጫ ያድርጉህ አትስማቸው አዎ! አትስማቸው!

38. “ተዋቸው! ምን ያደርጉልሃል?”

ወይ አይጠቅሙህ ወይ አይጠቀሙብህ፤ ወይ አያነሱህ ወይ አይነሱብህ፤ ወይ አይረዱህ ወይ አይረዱህ፤ ወይ አይደግፉህ ወይ አይደገፉህ፤ ግራ ገብቶአቸው ጋራ ከሚጋቡህ፣ ቀኛቸው ጠፍቶአቸው ፍለጋውን ካቆሙ፣ በደማቅ ቀን ጨለማን ከሚፈልጉ፣ በንጋት ፀሃይን ንቀው ለከዋክብት ከሚዋደቁት ትንሽ አሳቢ፣ ትንሽ አድራጊ ምን ነገር አለህ፣ ምን አገናኘህ? ምንም! አንተ አርፈህ ህልምህን አሳድ እርሱን ኑር፤ የእነርሱ ቃል ደስታ አይሆንህ፣ እረፍት አይሆንህ ወይም ስኬት አይሆህ፣ ከፍ አያደርግህ። ሁሌም ቢሆን ምንም ካለማድረግ ምንም ማድረግ፣ አንድ ነገር መሞከር ይሻሻል። ማድረግህን ቀጥል፣ ህልምህን ኑር፣ እራስህን ቀይር።

39. “ከቃል በላይ ለእራስህ፣ ለህሊናህ ታመን!”

ዋናው ጉዳይ ማን ቃል ገባ የሚለው ሳይሆን ማን አብሮ ቆየ፣ ማን አዛለቀ፣ ማን ታመነ የሚለው ነው። ስንት ቃሉን እንደ እዳና እስር የሚቆጥር ባለበት ዘመን፣ ቃል ሳይገባ፣ መታሰሩን ሳይፈልግ ፍቅሩን ከቃልኪዳን አስበልጦ አራሱን የሰጠ፣ ግፊትን ሳያሻ፣ ጫናን ሳይፈልግ በእራሱ የሚታመን ግሩም ሰው አለ። **አዎ!** ጀግኒት..! ቃልን እንደ እምነት እስር ከቆጠርሽው መቼም ልባዊ እምነትን አታገኚም። ማንም ሰው እስከጥግ የሚታመንልሽ ቃል ስለገባልሽ፣ በቃሉ ተገዶ ሳይሆን ስለሚወድሽ፣ ስለሚያፈቅርሽና ስለሚያከብርሽ ብቻ ነው።

አዎ! ሰውን በቃል ሳይሆን በፍቅር እሰሪው፣ በግድ ሳይሆን በውድ አስገዢው፣ በጫና ሳይሆን በፍላጎቱ ማርኪው፤ ማንኛውም ሰው የሚያመዛዝን ህሊና አለው፣ የትኛው ትክክል የትኛው ስህተት እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል። መታመን እንዳለበት ውስጡ ይነግረዋል፤ መቆጠብ እራሱን መወሰን እንዳለበት ያውቃል፤ አለመታመን ስሜቱን እንደሚጎዳ ያውቃል፤ ከቃል በላይ ህሊናው፣ ፍቅሩ እንደሚያስረው ነጋሪ አያሻውም፤ **አዎ!** ጀገናዬ..! ቃልን ማክበር፣ መታመን ከባድ ሆኖ አይደለም፣ ካልፈለገና ካላመነበት ግን ሳይከብደው በቀላሉ እምነቱን ያጣል፣ ቃሉን ያጥፋል፣ ስህተት መሆኑ እየገባው ስህተት ይሰራል።

አዎ! በመታመንህ ወቅት እምነትህ ለሰው ሳይሆን ለእራስህ፣ ለገዛ ህሊናህ ነው። ላለመታመንህ ግዴታ ሌላ ከሳሽ አያስፈልግህም፣ ለወቀሳና ለትቺት የእራስህ ህሊና አያስቀምጥህም። ምናልባት በብዛቱ ልክ ህሊናህም ሊለምደውና ዝም ሊልህ ይችላል፣ ሲነሳ ግን ሊያጠፋህ እንደሚችል እወቅ። የጥፋተኝነት ስሜትን ማስቀረትም ሆነ ማጥፋት የምትችለው፡- ከቃልህ በላይ ለህሊናህ ስትታመን ነው፤ ከሰዎች ይልቅ ለእራስህ ስትታመን ነው፤ ማንም ዘወትር አንተን የሚጠብቅ፣ እግር በእግር የሚቆጣጠር አካል የለም፤ ገዢህም፣ አዛዥህም የገዛ ህሊናህ ነው። ከእርሱ ያመለጥክ እንደሆነ ማቆሚያህ ከባድ ይሆናል፣ ማመዛዘን ትችላለህ፣ መምረጥ ትችላለህ፣ መወሰን፣ ማድረግ ትችላለህና ሁሌም በታማኝነት ተመላለስ፣ ቃል ካለህ ቃልህን ኑር እርሱን ባይኖርህም ህሊናህን አሳርፍ፣ **አዎ!** ከቃል በላይ ለእራስህ፣ ለህሊናህ ታመን! በጥቂቱ መታመንህ በብዙ ያሾምሃል፣ ትርፍህም ይበዛል፣ ሰላምህም ይፈካል፣ ፍቅርህም ያብባል።

40. “ምክንያት አትሁን!”

በህይወትህ የምታገኘው ሰው ምናልባትም አንድ የሚለይህ፣ የሚርቅህ የመጨረሻ ቀን አለው። ያንን ቀን ግን በውል አታውቀውም። ምንም ያክል ብትቀርበው፣ የልቡን ብታውቅ፣ ብትቆራኘው አንድ ቀን ግን ሁሉን እንደማታውቅ ትሆናለህ፣ ከልብህ አውጥተህ ትጥለዋለህ፣ ከእነጭራሹ ትረሳዋለህ። አንዳንዴ ህይወት እንደዚ ነች። የሆነ ሰሞን አይተህ የማትጠግበውን ሰው ለአይን እንድትርቀው ታደርግሃለች፤ የሆነ ሰሞን ከሃሳብህ አልፎ ህልምህ ውስጥ ያስገባሀውን፣ ህልምህን ያጋራሀውን ሰው ሳታስብ ዞር ታደርግብሃለች፤ የሆነ ሰሞን ስታስብለት፣ ስትጨነቅለት የነበረን ሰው መኖሩንም እንዳታውቅ ታደርግሃለች።

አዎ! ጀግናዬ..! ያንን አንድ ቀን አታውቀውምና መቼም ሰው ጎድተህ፣ ሰው ሰብረህ፣ ሰው አስከፍተህ ያቺን ቀን አታቅርባት። በምንም ሁኔታ የግንኙነትህ ማብቂያ ምክንያት አንተ ላለመሆን ጣር፤ ተገፊ እንጂ ገፊ አትሁን፤ ተጎጂ እንጂ ጎጂ አትሁን፤ ተሰባሪ እንጂ ሰባሪ አትሁን፤ ሰው ላይ ጠባሳን እንደማሳረፍ በፀፀት የሚጎዳ ነገር የለም፤ ሰውን መጉደት ተጎጂው ባይሰማውም ጎጂውን ግን ሁሌም ይከተለዋል።
አዎ! ወዳጅነትህን ከልብህ አድርገው፤ ፍቅርን አትሰስት ለሚገባው ስጠው፤ በክፋትህ የቸግር ምንጭ ከምትሆን፣ ፍቅርን ሰተህ መጎዳትን ምረጥ፤ አምላክም ቢሆን ፍቅርን ሰጥቶ በስቅላት ተጎድቷልና። **አዎ!** የመልካምነትህ ትርፍ ቁስ አይደለም፤ የብድር ፍቅርም አይደለም፤ ትርፍህ ውስጣዊ ሰላም፣ ውስጣዊ እርካታ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ምክንያት አትሁን፤ ለዛች ክፉ የመጨረሻ ቀን ምክንያት አትሁን፤ለዛች አሳዛኝ የመለያየት ቀን ሰበብ አትሁን፤ የቀኗ መቅረብ ሳይሆን ያንተ ምክንያት አለመሆን ያሳስብህ፤ የለብህን ወዳጅ ላለማጣት፣ ያቺን የመጨረሻ ቀንም ለማስቀረት ካንተ የሚቀር ነገር እሰከማይኖር ድረስ የሚጠበቅብህን አድርግ፤ ሃላፊነትህን ፈፅም፤ ግዴታህን ተወጣ።

41. “ልብህ ወርቃማ ነው!”

ዛሬህን በእነዚህ ውብ ቃላት አብራ፤ በእነዚህ ጣፋጭ ንግርቶች አድምቅ፤ "ነፍሴ ውብ ነች፤ አዕምሮዬ ሃይለኛ ነው፤ ወርቃማ ልብ አለኝ፤ እናም ብዙ የማመሰግንበት ምክንያት አለኝ።" **አዎ!** ጀግናዬ..! አንተ ጠንካራ ነህ ከመባል፣ "እኔ ጠንካራ ነኝ" የሚለው ቃል የተሻለ ሃይል አለው። ጥንካሬህን የሚነግርህ አካል ምናልባትም በጊዜው ያስተዋለውን፣ በጥቂት ዘርፍ ያየውን ብርታትህን ይሆናል፣ አንተ ግን በመንገድህ ሁሉ ያለፍከውን፣ የተሻገርከውን፣ የጣስከውን ሁሉ ጠንቅቀህ ታውቀዋለህ፤ ብርቱና ጠንካራ የሆንከው ዛሬ በፈፀምከው ጀብድ ብቻ አይደለም ትናንትም ባሳለፍከው ብርቱ ፈተና እንጂ። በዛሬዎቹ ውስን ተግባራት ብቻም አይደለም፤ በትናንትው አያሌ ተጋድሎዎችም ጭምር አንጂ።

አዎ! የዛሬ ፈተናህ ብርታትህን ማሳያ ነው። ባለፍከው፣ በተጋፈጥከው ልክ፡- ጥንካሬህን ታስተውላለህ፣ ሃይልህን ትረዳለህ፣ አቅምህን ታውቃለህ። ከሌላ አካል ከምታገኘው ብርታት ይልቅ እራስህ የምትፈጥረው ወኔና ሃይል እጅጉን የተሻለ ነው። **“Its not the way someone treat you made an effect, the way you did to yourself do**.” ለውጥ ሊያመጣ የሚችለው የሆነ ሰው የሚሰጥህ ምላሽ ወይም እንክብካቤ ሳይሆን እራስህ ለእራስህ የምትሰጠው እንክብካቤና ምላሽ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! ማንም እንዳይንቅህ ከፈለክ በመጀመሪያ እራስህን አክብር፣ ለእራስህ ቦታ ስጥ፣ ስሜቶችህን ተቆጣጠር፣ ሞተርህን ለማሞቅ፣ ወኔህን ለማምጣት የማንንም ግፊት አትጠብቅ፣ በቅድሚያ አራስህ አድርገው። **አዎ!** ነፍስህ ውብ ነች፤ አዕምሮህ ሃይለኛ ነው፤ ልብህ ወርቃማ ነው፤ ታዲያ ምን አነሰህ? ማመስገኛ ምክንያቶችህስ ብትል እልፍ ናቸው፤ በሰለም፣ በጤና ዛሬን ማየትህ፣ ለዛሬ መብቃትህ ከሁሉም ምክንያቶችህ ይልቃል፣ ትናንት ያልነበረ ዛሬ የተጨመረልህ፣ ትናንት

የተመኘህው ዛሬ የጨበጥከው ነውና። **አዎ!** እያንዳንዱን ስጦታህን ዋጋ ስጠው፣ ብርታትህ አድርገው፣ መነሻህ፣ ቀና የምትልበት፣ እራስህን የምታበቃበት፣ የምታመሰግንበት፣ የምትመሰገንበት አድርገው።

42. “የማትችይውን አትጋፈጪ!”

እንደማይችለው እያወቀ እራሱን ለሽንፈት አሳልፎ የሚሰጥ ሰው ለመሸነፍ የሚታገል፣ ለውድቀት እራሱን የሚያመቻች ሰው ነው። አሸናፊነት ናፍቆቱ፣ ሽንፈት የእለት ተግባሩ ሆኖ ይቀራል። **አዎ!** ጀግኒት...! የማትችይውን አትጋፈጪ! እውነታን አትጋፈጪ አትችይውምና፤ እራስሽን አትዋሺ አያዛልቅሽምና፤ በእርጋታ አስቢ፣ ውስጥሽ ሃሰትነቱን እያወቀ አንቺ ስለፈለግሽ ብቻ እውነት የሚሆን ነገር የለም። የህይወት ገጠመኞችሽ ሊፋቁም ሆነ፣ ሊሻሩ የማይችሉ የአንቺነትሽ እውነታ፣ የህይወትሽ ነፀብራቆችች ናቸው፤ ተጋፍጠሽ፣ ታግለሽ ልትቀይሪያቸው፣ ልትጥያቸው አትችይም።

አዎ! እውነታው አለመፈለግሽ፣ አለመወደድሽ፣ አለመፈቀርሽ ከሆን እላፊ አትጋፈጪው፣ አትድከሚ እውነታውን ሳታቅማሚ ተቀበይ። ችሎታሽን አለመቻልሽን ባወቅሽው ነገር ሳይሆን በምትችይው ላይ አሳዪ። የሆነን ነገር እንዳልሆነ ማድረግ አትችይም ስለዚህ እንዳለሆነ፣ እንዳልተፈጠረ ለማድረግ የምትደክሚበት ምንም ምክንያት አይኖርም። **አዎ!** ጀግናዬ..! የማትችለውን እውነታ አትጋፈጠው፣ አትፋለመው ልታሸንፈው አትችልምና፣ ሃሰት ልታደርገው አትችልምና። እውነታ ውሸት እንዲሆን ከመጣጣር አምኖ መቀበሉ እጅጉን ቀላልና የተሻለ ነው። እውነታው የውጤትህ መበላሸት ከሆነ ምክንያት በመደርደር እራስህን ለማሳመን አትጣር፣ ምድር ላይ ያለውን፣ የሚታየውን እውነታ ባትፈልግም ተቀበለው፤ እውነታው ውድቀትህ ነው፤ ወሳኙ ነገር ግን ዳግም መነሳት መቻልህ ነው። እውነታው የውጤትህ መበላሸት ነው፤ ወሳኙ ነገር ግን ደግም ማስተካከል መቻልህ ነው። እራስህን የዋሸህ እንደሆነ የምትነሳበት፣ የምታስተካክልበት ጊዜም እንዲሁ እንደሚርቅ እወቅ፣ **አዎ!** አማራጮችን የምታየው እውነታን ተቀብለህ ነው፤ በሌላ መንገድ የምትሞክረው ግልፅ የሆነውን አምነህ ነው፤ ወደፊት የምትራመደው ግልፁን፣ የሚታየውን በመቀበል ነው፤ ጉዞህን የምትቀጥለው ድክመትህን በማመን፣ በመቀበል ነው።

አዎ! ብቃትህ፣ እውቀትህ ለስራው የማይመጥን ከሆነ አብቅቷል፤ ሰበብ አታብዛ፤ እራስህን አትዋሸው፣ እወነታውን ተቀበልና እራስህን አሻሽለህ ተመለስ፣ ውድቀትህን በገዛ እጅህ አታፍጥነው፤ ትኩረትህን እውታውን መጋፈጥና እራስህን መዋሸት ላይ ሳይሆን እወነቱን ተቀብሎ ተሻሽሎ በአዲስ ወኔና መንፈስ መቅረቡ ላይ አድርግ፣ እራስህን በምትችለው ነገር አሻሽል፣ በምታሸንፈው መድረክም እራስህን ፈትሽ፣ እራስህን አሳይ።

43. “አምላክህን ፈልግ!”

ምድራዊ ዝለት፣ ምድራዊ ድካም ነፍስህን አስጨንቋታል? መንገድህ ሁሉ በእሾህ ታጥሮብሃል? አለምህ ብረሃን ያጣች ዋሻ ሆናብሃለች? ፈቀቅ የማይል ተራራን የመሰለ ህይወት እየኖርክ፣ እየገፋህ ነው? በሰው መሃል ሰው አተሃል፣ ፍቅር ተነፍጎሃል፣ ብቸኝነት ወሮሃል፣ ብሶት አሰቃይቶሃል? **አዎ!** ጀግናዬ..! አይዞህ! አምላክህን ፈልግ። ሁነኛው ማረፊያህ እርሱን መግኘትህ ነው፤ ሰላምህ በቤቱ አለልህ፣ እረፍትህ በእቅፉ ነው፤ ነገሮች ሲሆኑ ምክንያት አላቸው፤ ያንተም ባዶነት፣ ያንተም እጦት በምክንያት ነው። አምላክ ስለሚፈልግህ ነው፤ አንተም ትፈልገው ዘንድ መንገዱን እያዘጋጀልህ ነው። ከጨለማ የሚያወጣህ የእርሱ ብረሃንነት ነው። ነፍስህን የሚያሰርፈው የእርሱ መግቦት፣ የእርሱ እገዛ ነው።

አዎ! አምላኩን የያዘ አፍሮ፣ ተሰብሮ፣ ተጎድቶ አያውቅም። ከባዱን የሚያቀል፣ ውስብስቡን የሚፈታ፣ ብሶትን የሚሸር ደግ አባት፣ ሩህሩህ አምላክ እያለህ ስለምን ትጨነቃለህ? አኛ ባላውቅነው እርሱ

በሚያውቀው ስንቴ ከአንበሳ መንጋጋ ፈልቀቆ አውጥቶን ይሆን? እኛ ባላስተዋልነው እርሱ በተረዳው ስንቴስ ከጨለማ ህይወት ሰውሮን ይሆን? በእርግጥም ትናንት ማቀድህ፣ ዛሬን ማለምህ፣ ዛሬን ማየትህ፣ ዛሬን መኖርህ በአምላክ ፍቃድ ነው፤ **አዎ!** አምላክህን ፈልግ! አባትህን ፈልግ! በእምነት ፈልገው በእርግጥም ታገኘዋለህ! እምነት ቢጎድልህ እምነትህን እንዲረዳው ተማፀን፣ እርሱን ለምን፤ በተስፋ ፈልገው፣ በተስፋ ጠብቀው በእወነቱ ይመጣል፣ ቢዘገይም የሚቀድመው የለምና! በፍቅር ፈልገው፣ ነፍስህን አፅድተህ፣ አራስህን ሰተህ፣ አንተነትህን ሰውተህ፣ በትህትና ዝቅ ብለህ። "ቸር አምላክ ሆይ ስላሻገርከኝ፣ ስላሳለፍከኝ ስላለፉት ቀናት ተመስገን! ስለዛሬዋ ውብ ስቶታህ፣ ስለምታሳሳው ቀን ተመስገን! ቸር አባት ሆይ ስልምታሳየኝ፣ ስለምታቀናኝ ስለመጪዎቹ የፍቅር ቀናት ተመስገን!" ማለትን በንጋትህ ሁሉ አስታውስ፣ የእለት ተግባርህም አድርገው፣ አምላክህንም ዘወትር ፈልገህ አግኘው፣ ሁሉንም በእርሱ ተሻገር።

የከበቡህ ሊጠብቁህ ነው ወይስ ሊጠበቁብህ? የቀረቡህ ሊረዱህ ወይስ ሊረዱብህ? የሚያስቡልህ ሊያተርፉልህ ወይስ ሊያተርፉብህ? የሚሳሱልህ ሊያራምዱህ ወይስ ሊራመዱብህ? የሚንከባከቡህ ሊያሻግሩህ ወይስ ሊሻገሩብህ? **አዎ!** ጀግናዬ..! በቻልከው መጠን መርምር፤ በቻልከው መጠን ተጠበቅ እራስህን ጠብቅ፤ ቅንነትህን ለሰው ብቻ ሳይሆን ለእራስህም አድርገው፤ እራስህን መግብ፤ እራስህን አፅና፤ እራስህን ተረዳ፤ እራስህን አሳርፍ።

44. “ተስፋህ ምንድነው?”

ተስፋን አጥቶ ህይወት፣ በባዶ ኪስ ሆቴል ገብቶ እንደማዘዘ ነው፤ የማይሆንና እያወክ የማታጠፋው ጥፋት ነው። ነገን ሳታልም፣ ለነገ ሳታቅድ፣ የተሻለን ሳታስብ መኖር እጅጉን አስቸጋሪ ነው። ገንዘብ ሳትይዝ ምንም አታዝም፣ ምንም አይቀርብልህም ተስፋም ካላደረክ የተሻለ ነገር ማግኘት አትችልም። **አዎ!** ጀግናዬ..! የነገ ተስፋህ ምንድነው? ነገ ምን ይታይሃል? ለነገህ ምን ታልማለህ? ህይወት እየከበደ ሲመጣ አንተም ተስፋ ማድረግህን ቀንሰህ ይሆን? ኑሮው ሲያስቸግርህ አንተም እጅ ለመስጠት ተዘጋጅተህ ይሆን? የህይወት ፈተና፣ ውጣውረዱ ተስፋህን ሰርቆህ፣ ቀምቶህ ይሆን?

አዎ! ጀግናዬ..! በእውነቱ በፈተና ወቅት፣ በሰቆቃ ጊዜ ተስፋ ካላደረክ የተስፋህ ጥቅም ምንድነው? በአስቸጋሪ ጊዜ የተሻለው መልካም ሁነት ማየት ካልቻልክ ተስፋህ ለምንስ ይፈይድሃል? ነገሮች ሲመቹህ ብዙ ላትጥር ትችላለህ፤ ዛሬ ሁሉም እንደፈለከው ከሆነ ለነገ ብዙ ላትለፋ ትችላለህ፤ ምቾት ብዙም ተስፋ ከማድረግ ሊያዘናጋህ ይችላል፤ ስቃይ፣ መከራ፣ ችግር ግን ነገ ከዚህ ሁሉ የምታርፍበትን የተሻለ ነገ ተስፋ እንድታደርግ፣ እንድታልም ያደርግሃል። **አዎ!** የነገ ትስፋህ ምንድነው? ተስፋህ ከአምላክህ ቀጥሎ አንተ ነህ፤ ጥረትህ ነው፣ ልፋትህ፣ ትጋትህ፣ ብርታትህ፣ አድራጊነትህ ነው። ዛሬ አታትርፍ፣ ነገም አታትርፍ ከነገ ወዲያ ባሉት ረጅምና መጪ ጊዜያት ግን በእጥፍ ታተርፋለህ፤ በብዙ ይሳካልሃል፤ የዘሬውን ፈተና ትረሳዋለህ።

አዎ! በመንገድህ ሁሉ ብዙ ተስፋ ቢሶች፣ የተስፋህ ፈተናዎች ይገጥሙህ ይሆናል፤ እነርሱ እየተማሩ፣ ስራቸውን እየሰሩ፣ ብዙ ነገር እየሞከሩ አንተ ጋር ሲመጡ ተስፋ እንደሌለህ ቢነግሩህ በፍፁም ጆሮ አትስጣቸው፤ እነርሱ ተስፋ ባይኖራቸው መማር ባልተጠበቀባቸው ነበር፣ ተስፋ ባይኖራቸው መስራት ባልኖረባቸው ነበር። **አዎ!** አንተ ትምህርትህን ወጥረህ ተማር በሚገባ ተስፋ አለህ፤ ስራህን ጠንክረህ ስራ በእርግጥም ተስፋ አለህ፤ ዳገቱን መውጣትህን ቀጥል ጫፉ ላይ የመገኘት ተስፋ አለህ፤ ተቀማጩ፣ ያልሞከረው፣ ሰነፉ ፊትህን ነገህን ተስፋ እንዲያሳጣው፣ እንዲያጨልመው አትፍቀድ። **አዎ!** ሁሌም ተስፋ አለ፣ በእርግጥም ነገ ከዛሬ ይሻላል፣ አምላክ ተስፋን የሰጠን ነገን እንድናልም እንጂ በዛሬው ፈተና ተሰብረን እንድንቀር አይደለም።

45. “ሃይልህ በትኩረትህ አቅጣጫ ይፈሳል!”

ትኩረትህ ወደ ሔደበት ሃይልህ ያመራል። አወከውም አላወከው ትልቅ እምቅ፣ የሃያልነት ሃይል አለ። ያንን ሃይል የሚያዘው የሚመራው ደግሞ ትኩረት የሚባለው ግዙፍ ስሜት ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! አቅምህ፣ ሃይልህ፣ ስሜትህ በትኩረትህ አቅጣጫ ይፈሳል። የምትቆጣጠረው ትኩረትህን ስትገታና ስትቆጣጠር ብቻ ነው። የአለም ስሪቷ ትኩረት መሳብ ላይ ለምን እንዳተኮረ ታውቃለህ? ትኩረትህ የተግባርህ፣ የግኝትህ፣ የውጤትህ ቁልፍ ስለሆነ ነው። አዎ! አለም፣ ቀልብህን ለመሳብ፣ ደጋግመህ እንድታስበው፣ ስሜትህን ለመግዛት በጣም አጭርና ውብ በሆነ ነገር ትደልልሃለች ትኩረትህን ካገኘች ቀጣዩን ስራ በእራስህ ተነሳሽነትና አቅም እንደምትሰራው በሚገባ ታውቃለች። የአዕምሮዓችን ስሪት ይህ ነው።

ትኩረትህ መጥፎ ነገር ላይ ከዋለ፣ የምታፈሰው ግለ ነዋይህም እደዛው መጥፎውን ለመተግበርና ለማስፈፀም ይውላል። አዎ! አንድ የዘወትር ትኩረቱ ዜና መስማት የሆነ ሰው የማውራት ጥማቱንም ሆነ አቅሙን የማይጠቅመውን ያንን ዜና በማስተጋባትና በመተረክ ላይ ያውለዋል። ምናልባትም የማውራት ክህሎቱን ለሚጠቅመው የተሻለ ነገር ቢያውለው ውጤታማነቱ ከፍ ማለቱ አይቀርም።
አዎ! ትኩረትህን ተቆጣጠር ስሜትህን አታባክን፣ ክህሎትህን አታርክስ፣ ብቃትህን አታኮሰስ፣ ሃይልህን አታደንዝዝ። የትኩረትን እምቅ ሃል በጥቃቅን ኢምንተ ነገሮች አታሳንሰው። ስለ ድካምህ እያሰብክ ሁሌም ስንፍናህን አታስታም፤ አንዳንዴ ጥንካሬህንም አስብ፣ ትኩረት ስጠው። ስለ ውድቀትህ እያሰብክ ስብራትን ወደ እራስህ አትጥራው፤ ባይሆን ሃይልና ወኔህን አስታውስ፣ እርሱ ላይ ስራ፣ እርሱን ተጠቀም። **አዎ!** ትኩረትህን ተጠቀም ሃይልህን አሰልጥን! ትኩረትህን አስተካክል አቅምህን አሳይ!

46. “ለማየት ያስጠላህን እያደረክ አትገኝ!”

የማትወደውን ፊልም ደጋግመህ አታይም፤ የማትፈልገው ቦታ ሁሌም አትገኝም፤ ያናደደህን፣ ያበሳጨህን ሰው ማግኘት አትፈልግም፤ የሚጠብህን፣ የማይሆንህን፣ የሚያሳምምህን ጫማ በግድ አታደርግም፤ አትጫማም? **አዎ!** ጀግናዬ..! ታዲያ ለምንድነው የማትወደውን፣ የማይጠቅምህን፣ የማያሳርፍህን ይልቁንም የሚያሳምምህን፣ የሚጎዳህን፣ የሚጥልህን ነገር እየደጋገምክ የምትገኘው? ለምን? ለእንደዚህ አይነት ጥያቄ መልስ ቶሎ አይገኝም ምክንያቱም በልማድ እንጂ ለምን እንደምታደርገው በግልፅ አታውቀውምና። ተገቢ እንዳልሆነ ታውቃለህ ነገር ግን ብዙ ጊዜህን በመዝናናት እሳቤ በመጉላላት ታሳልፋለህ? እንደማይጠቅሙህ ታውቃለህ ነገር ግን ብዙ ጊዜህን ትሰጣቸዋለህ፤ ለአመታት ዜና ስትሰማ ኖረሃል፤ ምንም እንዳላመጣልህም አረጋግጠሃል፤ ነገር ግን ዛሬም ቁጭ ብለህ እርሱን ታያለህ፤ **“Social Media”** መጠቀም ከጀመርክ ጊዜያት ነጎዱ የተወሰነ ነገር አግኝተህ ይሆናል ነገር ግን ከልካይ ስላጣህ ብዙ ነገርህንም አተህበታል፤ እጦትህና ጉዳትህ ግን ዛሬም አብዝቶ ከመጠቀም አላገደህም፤ **አዎ!** በአንድ በኩል ያልተመቹህን፣ የማትወደውን ፊልም ድጋሜ ለማየት ትሳሳለህ በሌላው ጥግ ግን ያንኑ የማትወደውን ፊልም በመሪ ተዋናይነት ደጋግመህ ትሰራለህ፣ ትተውናለህ። ምክንያቱን ሳታውቀው የማይጠቅምህን የድግግሞሽ አጥር ሰርተሃል፣ የትወናህ “**Perfection”** እንጂ የፊልሙ አዋጭነትና ትርፉ አስጨንቆህ አያውቅም፤ የምትሰራው ወደሀው እንዳልሆነ ማሰብ አትፈልግም፤ ሁሉም ጥሩና ጎበዝ ተዋናይ እንደሆንክ እንዲነገርህ ትፈልጋለህ።

አዎ! የማትወደውን፣ የማይጠቅምህን ነገር እያደረክ እስሬ ጎበዝ፣ ጀግና፣ በርታ ብትባል ምን ይረባሃል? የውድቀትህ ብርታት፣ የበታችነትህ ማፍጠኛ፣ ማሞካሻ ከማድረግ በቀር፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! አስተውል! ፊልሙን የማትደግመው ስላልወደድከው፣ ስለማይጠቅምህ፣ ስሜትህን ስላልገዛ ነው፤ ያልወደድከውን ፊልምስ በግፊትና በልማድ ጫና እየደጋገሙ መስራቱን ማቆም አትችልምን? በደምብ ትችላለህ! **አዎ!** ለማየት ያስጠላህን እያደረክ አትገኝ! ውድቀትን አትፈልግም፤ ወድቀህ አትገኝ! ኪሳራን አትፈልግም፤

ከስረህ አትገኝ! ብክነትን አትወድም፤ ብኩን አትሁን! ከሚጥሉህ ልማዶች ተፋታ! ቀና የሚያደርጉህን አዘውትር፤ በእነርሱ ተጠቀም፤ ስኬትህን አፍጥን፤ ውድቀትህን አርቅ።

47. “ፀጋሽ ውበትን ቸሮሻል!”

ብርታቷ ሴትነቷ፣ ወኔዋ እሷነቷ ሃይሏ ልህቀቷ፣ ጥንካሬዋ እሳቤዋ፣ ምልከታዋ፣ እይታዋ። **አዎ!** ጀግኒት..! ብርቱ ሴት ነሽ፤ እሳቤሽ ላቅ ይላል፤ ትግበራሽ ከፍ ይላል፤ ውጤትሽ ያምራል፤ ፀጋሽ ውበትን ቸሮሻል፤ ሴትነትሽ በበረከት ሞልቶሻል፤ "ብርቱዋ እንስት" አስብሎሻል። **አዎ!** ያለፍሽውን ማለፍሽ ዋጋሽን ከፍ አድርጓል፤ ውሎሽን ቀይሯል፣ ሰልፍሽን ከጠንካሮች ተርታ ቀላቅሏል።
የማትኖሪውን አለም አታስቢም፤ በምክንያት ታስቢዋለሽ፣ ጎልተሽ እንድትወጪ የሚያደርግሽም ያ መልካምና ጠንካራው እሳቤሽ ነው። ትንሽነትን ካላነገስሽ፣ ግብዝነት ካልተቆጣጠረሽ በእርግጥም አንቺ ብርቱ ሴት ነሽ። ፊትሽ ማንም ይቁም ግድ የለሽም፤ እራስሽን ለመግለፅ የሚገድብሽ አይኖርም። በፍቃድ ሂደቶች ገነቡሽ፣ በአንቺው ይውንታም እነርሱው ያበቁሻል። የእራስ ፍቅርን ተላበሺ፣ የዋህነትሽ፣ ሴትነትሽ የምትጠቀሚበት እንጂ የሚጎዳሽ አይሁን። ብለሃቷን የምታነግስ፣ እሳቤዋን የምታፀና ብርቱዋን ሴት ሁኚ።

አዎ! ጀግናዬ..! ለጊዜው ማድረጉ ቢከብድህም ማሰብህን፣ ማለምህን እንዳታቆም። እሳቤህ የተግባርህ ምሪት ነውና። ያላሰብከውን ከሰማይ አታወርድም ከምድር አታወጣም ዋናው ምንጩ እሳቤህ ነው። በእራስ መተማመንህ ምንም አይደለም እይታህ ነው። ስኬትህ ከእይታህ፣ ከእሳቤህ፣ ከይቻላል መንፈስህ ይመነጫል። **አዎ!** እራስህን ዝቅ የምታደርገው ከሰዎች ያነስክ ሆነህ ሳይሆን ለትህትናህ ማሳያ ነው። ልነስ ብትልም ተፈጥሮህ፣ ሰውነትህ አይፈቅድልህም፣ አያስችልህም፣ አያሳንስህም። አንተ ትንሽ ሆነህ አታውቅም ምናልባት ለእራስህ ያለህ እሳቤና ምልከታ አሳንሶህ ይሆናል፤ አንተ ዝቅ ያልክ ሆነህ አይደለም፤ ምናልባት ለእራስህ ያለህ ቦታ ዝቅ አድርጎህ ይሆናል። **አዎ!** እሳቤህን አሰትካክል ከፍ በል፤ እሳቤሽን ለውጪ ቀና በይ፤ ፊትህን በእራስህ ወስን፤ መጪዎቹን ጊዜያት አንቺው አስጊጪያቸው፣ አንቺው አስውቢያቸው፣ አንቺው አደላድያቸው።

48. “እራስህ ላይ ‘INVEST’ አድርግ!”

ሰዎች በመጥፎነት ሊፈርጁህ ይቸኩላሉ፤ ያደረሱብህን መጥፎ ነገር ግን አያስታውሱም፤ ሃሳባቸው መበደልና መጎዳት ስለሆነ ችኮላቸውም እርሱን ለማንፀባረቅ ነው። በሰው ፊት ተጎጂ ሆኖ ለመቅረብ መሞከር የእራስ ወዳድነት ስሜትን አጉልተው ከሚያሳዩ ጉዳዮች አንዱ ነው። ህመምህን፣ ጉዳትህን ደጋግመህ ለሰዎች ማውራትህ የሚያድንህ ሊመስልህ ይችላል ነገር ግን ሊያባብስብህም ይችላል ምክንያቱም በባወራህ ቁጥር ህመምህን እያሰብክና እያስታወስክ ነውና። ጤነኛና መልካም በሚባል ግንኙነት ውስጥ መጎዳትን ከመናገር ላለመጉዳት መጠንቀቁ ትኩረትን ያገኛል፤ የተጎጂነት ስሜቱ የሚመጣውም ነገሮች መጥፎ መሆን ሲጀምሩ ነው። ሁለቱም በግንኙነት ውስጥ የነበሩ ሰዎች በሌላኛው እንደተበደሉና እንደተጎዱ ማሰብ ይጀምራሉ፣ እነርሱ ያደረጉት ትዝ አይላቸውም፣ ትኩረታቸው የእራሳቸው ጉዳት እንጂ የሌላው መሰበር አይደለም።

በዚህም ምክንያት ጣታቸውን በሰዎች ላይ ለመቀሰር ይጣደፋሉ። አዎ! ምናልባትም ከአንዴም ሁለቴ ተጎድተን ተበድለን ይሆናል ነገር ግን ሁሌም እኛው ተበዳይ መሆን አንችልም፤ ስለዚህ ስህተትን መርምሮ ለጥፋቱም ይቅርታ መጠየቅ እንጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው።
በእርግጥ በእራስ መፍረድ በሰው እንደመፍረድ ቀላል አይሆንም። **አዎ!** ጀግናዬ..! አንተም ብትሆን ስለራስህ ድክመትና ክፍተት ካወራሀው ሌላውን የተቸህበት ጊዜ በብዙ እጥፍ ይበልጣል። **አዎ!** በሚመለከተን ስንት ጠቃሚ ሃሳብ መስጠት እየቻልን በማይመለከተንና በማይመጥነን የወረደ ነገር

ተጠምደን ጊዜ አተናል። ወቅታዊ ጉዳይ ሁሌም አይጠፋም እርሱ አንደተፋፋመ ነው አንዱ ሲያበቃ አንዱ ይተካል እኛም በየጊዜው በእርሱ የምንጠመድ ከሆነ ትልቅ አደጋ ውስጥ ነን።

አዎ! ጀግናዬ..! ያንተ ጉዳዩን የየለት አጀንዳ ማድረግ 0.5% ተፅኖ መፍጠር ካልቻለ ያንተ ትኩረት መስጠትና አጀንዳ ማድረግ ትርፉ ምንድነው? ማውራት፣ መጫወት፣ ሃሳብ መስጠት ያለ ነው እንደ እራስ ጉዳይ ግን ለእርሱ ተብሎ እንቅልፍ ማጣት፣ መጨነቅ ትርጉም አይሰጥም። **አዎ!** ከሁሉም የሚረዳህ ተጎጂ ሆኖ መታየት፣ ያንተ ያልሆነውን የእራስህ ለማድረግ መጣጣርና በእርሱ ጊዜ ማባከን ሳይሆን የእራስህን ክፍተት መመርመር፣ እርማት መውሰድ፣ እራስህ ላይ ወጪ ማውጣት እራስህን መገንባት ነው። **አዎ!** እራስህ ላይ **"INVEST "**አድርግ፣ ከላቀው ትርፍ ተጠቀም፣ እራስህን አሳድግ፣ የአንድ ሰሞን ብቻ ሳይሆን የሁልጊዜ አጀንዳ ሁን።

49. "በሃሳብህ ቁጪትን አታትርፍ!"

እውቁ ቢልዬነር ስቲቭ ጆብስ ምን ይላል "ተግባር የሌለው ሃሳብ፣ ሃሳብ አይደለም እርሱ ቁጪት ነው።" የዚህን አባባል እውነታነት ለማረጋገጥ የትም አትሒድ፣ ከዚህ በፊት ስታስባቸው፣ ስታሰላስላቸው የነበሩትን አስገራሚ፣ ድንቅና ማራኪ ሃሳቦች አስታውስ። በሃሳብህ፣ የእራሴ የምትለው ጥሩ ስራ ነበረህ፤ በሃሳብህ፣ ይሔ ነው የማይባል ትርፍ የምታገኝበት ንድፍ ነበረህ፤ በምናብህ፣ ከእራስህም አልፎ ሰዎችን ሊጠቅም የሚችል ፈጠራ ነበረህ፤ ፍላጎትህ፣ የሚያሳርፉህና እውቀትህን በብዙ የሚያሳድጉልህ፣ የሚቀይሩህ ሃሳቦችን እንድታመነጭ አድርጎህ ነበር፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! ሃሳቡ ስለነበረህ ባለመተግበርህ ዛሬ ቁጪትን አትርፈሃል፣ ዛሬ ያ ያለፈ ጊዜ እንዲመለስ ትመኛለህ፤ ዛሬ ነገ እያልክ ለዛሬ ደርሰሃል፣ ሲመቸኝ አደርገዋለሁ ስትል ነበር ነገር ግን ሳይሆን ቀረ።

አዎ! በኑሮ ሂደት ነገ የሚባለው ቀን ከዛሬ የተሻለ ፋታ የምናገኝበት ቢመስለንም እርሱ ግን የይባስ የተጨናነቀና ፋታ የማይሰጥ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም ብዙ ጫና አለብን፣ ሃላፊነታችን እየጨመረ ይሔዳል፣ ተራ ነገሮችን እናቆማለን፤ ህይወታችን በሙሉ በቁብ ነገር መሞላት ይጀምራል፤ ማስተዋል እንጀምራለን፤ በአንድም ሆነ በሌላ እውቀታችን ይጨምራል፣ ኑሮን ለማሸነፍም ብዙ ነገር እንሰራለን፤ ያኔ አስገራሚው ሃሳብ ሾልከ ያመልጠናል፤ ሲመቸን ብንልም ሳይመቸን ይቀራል፤ ነገ ነገ ብንልም ያሰብናትን ነገ ሳናገኝ እንቀራለን። "ወይኔ ትናንት ባደርገው ኖሮ" የሚለው ቁጪት እንዲመጣ መንገዱን እንከፍታለን።

አዎ! ጀግናዬ..! በሃሳብህ ቁጪትን አታትርፍ! በምክንያት ተጨንቀህ፣ ተጠበህ ያመጣሀውን ድንቅ ሃሳብ እንደላስፈላጊ ነገር አትጣለው፤ አንተ ብቻ ያለምከውን ትልቅ ህልም እንደ መንደር ወሬ አውርተህ አትለፈው፤ ኑረው! **አዎ!** ብዙ ምክንያት ይኖርሃል፤ ቁጪት ግን ምክንያትን አይሰማም፤ በስተመጨረሻ "የማትኖረው፣ የማትሰራው ከሆነ ይህን ሃሳብ ስለምን አመጣህው?" ሊልህ ይችላል። የዛኔ ምላሽህ ምንድነው? ዝምታና ሌላ ጥያቄ እንዳይጠይቅ እርሱን ማስታመም።

አዎ! ጀግናዬ..! እርሱ አያዋጣህም! አለማሰብ፣ አለማለም፣ አለማቀድ አትችልም ሁሌም በውስጥህ የተሻሉ ሃሳቦች ይመጣሉ፤ ሃሳቦችህ ግን ብቻቸውን አይመጡም ተግባርን ፈልገው፣ ቁጪትንና ወቀሳን በጉያቸው አንግበው ይመጣሉ። ስለዚህ ሁለት አማራጭ አለህ። አንድም ሃሳብህን፣ ህልምህን መተግበር፣ መኖር፤ ሌላም አይንህ እያየ፣ እያወከው ወደ ቁጪት፣ ወደ ጭንቀት፣ ወደ ብስጪት እንዲቀየር መፍቀድና ወደነርሱ ሰተት ብለህ መግባት። **አዎ!** ሃሳብህን የእውነት አስበው፣ የምርህን ኑረው፤ ከልብህ ተግብረው፤ የሚቀይርህ የሰው ህልም ሳይሆን የእራስህ ህልም ነው፤ የሚያቀናህ የሰው ሃሳብ ሳይሆን የእራስህ ሃሳብ ነው።

50. “ህልምሽ ሃያል ነው!”

የጠዋት ፀሃይ፣ የንጋት ጮራ አትሰለችም፤ የወፎች ዜማ አይሰለችም ሁሌ ማለዳ አዲስ ነው። ፍቅራችን ከውስጥ ነው፣ መንፈሳችን ይወደዋል፤ ይናፍቀዋል፣ ይጓጓለታል። **አዎ!** ጀግናዬ...! ህልምህም ይሄው ነው፤ የዘወትር ናፍቆትህ ነው፣ ውስጥህን የሞላው እሳቤው ነው። ህልምህን ከውጥ ወደ ውጭ ትኖረዋለህና መቼም ሊሰለችህ አይችልም፣ እርሱ የህይወትህ ውበት ነው፤ የህይወትህ ደማቅ ቀለም ነው፤ ሁሌም ይነገርሃል፣ ያስታውስሃል "ሙላትህ በእኔ ውስጥ አለ፣ እኔን ምረጥ፣ እኔን ኑረኝ፣ አሳርፈኝ፣ ተንከባከበኝ" ይልሃል!

አዎ! ጀግናዬ..! ህልምህ መቼም አይሰለችህም! ጊዚያዊ አይደለምና፤ ከእራስህ ጋር ከመንፈስህ ጋር ተሳስሯልና፤ በሔድክበት አብሮህ አለ፣ እንደ ቁስ ቦታ በቀየርክ ቁጥር የምትቀይረው አይደለም። ውስጥህ የሚያርፈው፣ ሰላም የሚሰማው፣ መንፈስህ የሚታደሰው፣ ፀጋው የሚበዛለት፣ በሃሴት የሚቃኘው የማይሰለቸውን ሁሌ ማለዳ ማለዳ አዲስ የሆነውን፣ በጊዜ የሚያነቃህን፣ የሰላምህ፣ የደስታህ ምንጭ የሆነውን ህልምህን ስትኖር ነው።

አዎ! ጀግኒት..! ህልምሽን ከሰው እንዲያመሳስልሽ የፈጠርሽው አይደለም፤ በልዩነትሽ ልዩ እንዲያደርግሽ እንጂ። ህልምሽ ከውጪ ወደ ውስጥ የምትኖሪው ሳይሆን፣ ከውስጥ ወደ ውጭ የምትኖሪው ነው። የሚያስተኛሽ፣ የሚያሰንፍሽ አይደለም፤ የሚያነቃሽ፣ ሃይል የሚሆነሽ፣ የሚያበረታሽ፣ ወኔሽ ነው። ለአለም፣ ለህይወት፣ ለከባቢሽ ያለሽን እይታ፣ እሳቤ፣ ምልከታ ሁሉ እርሱ ይቀይረዋል።
በመጥፎ ውስጥ መልካሙን ያሳይሻል፤ በፈታና ውስጥ ድል አድራጊነተን ያስቃኝሻል፤ በድካም እረፍትን፣ በስብራት ውስጥ ቀና ማለትን፣ በመገፋት፣ በመጠላት ወስጥ ጥልቅ ፍቅርን ያጎናፅፍሻል።

አዎ! ህልምሽ ሃያል ነው! ህይወትን የሚተረጉም፣ በየእለቱ፣ በየሰዓቱ፣ በእየደቂቃው፣ በሰከንዱ እንደምትተነፍሽው አየር የህይወት ጠዓም እስትንፋስሽ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ትልቅ ህልም እያለህ ወደኩ፣ ተሰበርኩ፣ ታመምኩ፣ ተጎዳው፣ አቃተኝ፣ አልችልም ብለህ የምትተወው፣ የምትገፋው፣ የምትጥለው አይደለም። ከጊዜያዊ ስሜት ይልቅ ዘላቂ እርካታ ላይ ካተኮርክ፣ እነዚህን ስሜቶች መቼም አታያቸውም፣ እርሱ ያጠፋቸዋል፤ በዛሬ መነፅር ነገን ከተመለከትክ በእርግጥም ምክንያቱ ህልምህ ነው። **አዎ!** የማይሳካ ህልም አታልመም፤ የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ የማይኖር ህልም አይኖርህም፤ ለእራስህ ብቻ አትኖረውም፤ ለብዙዎች ታጋራለህ፣ እነርሱን ትረዳለህ፣ ከአንተም አልፈህ እነርሱን ታሳርፋለህ፣ ታስደስታለህ። **አዎ!** የህልምህን ታልቅነት፣ የህልምህን ሃያልነት፣ የህልምህን ተጨባጭነት፣ የህልምህን ተፈፃሚነት በገሃድ አለም ታሳያለህ።

51. “እየኖርክ ታገል!”

ነገን የምትጠብቀው ለማነው? ነገን የቀጠርከው ለምንድነው? ነገ ይኖሩኛል የምትላቸው እነማናቸው? ከዛሬ ይልቅ ለነገ የምታስበው፣ የምትጨነቀው ምን ሰላለው ነው? **አዎ!** ጀግናዬ..! ለነገ የቀጠርከው ደስታህን ነውን? ቦሃላ የምትለው ለማመስገን ነውን? ሌላ ቀን የምትለው ለመጀመር ነውን? በጫና ውስጥ፣ ከህመም ጋር የምትለፋው ነገ ለማረፍ ነውን? **አዎ!** ነገን ስናስብ ተስፋ ይታየናል፤ ዛሬን ካልኖርነው ግን የነገው ተስፋም ጨለማ ይወረዋል። ሳይኖሩ ነገን ማሰብ አይቻልም። ሁሉም በመጠኑ ሲሆን ጥሩ ነው። ህይወትን አሳዶ መሳደድ አናድርጋት። ገንዘብ ፍለጋ ጤናን መገበር ጤናውን ለማምጣት ገንዘቡን ማጣት፣ ሁለት ያጣ ማሃል ሰፋሪ ያደርጋል። **“Take care of yourself”** እራስህን ጠብቅ! ተራ የሚባል ነገር የለህም እያንዳንዳቸው የተሰጡህ ነገሮች ውድ ናቸው፣ ተመን አየወጣላቸውም።

አዎ! ምናልባት ስለማትከፍልባቸው ዋጋ ቢስ እንዳይመስሉህ፤ እነርሱ ዋጋ የሚባለው ቃል እንኪን አይመጥናቸውም። **አዎ!** በምድራችን በዚህ ሰዓት ምን እየተከናወነ ይሆን? ስንቶች ብረሃን ማየት ናፍቋቸዋል፤ የአይንህን ውድነት ተመልከት። ስንቶች ኮሽታ መስማት ይመኛሉ፤ የጆሮህን ውድነት አስተውል። ስንቶች ሰላምን አተዋል? የሰላምን ጠዓም ታውቀዋለህ፣ ውድነቱን አስታውስ። ስንቶች በእስር ይማቅቃሉ፤ የነፃነትህን ውድነት ተመልከት። ስንቶችስ በአልጋ ላይ ይማቅቃሉ፣ ነፃውን አየር መተንፈስ ይናፍቃሉ፤ የጤናህ ውድነት፣ የእስትንፋስህ ወጋ ይግባህ።

አዎ! ጀግናዬ..! እነዚህን ዛሬ ያሉህን ውድ ስጦታዎች ነገም እንደሚኖርህ ዋስትና የለህም። ስላለህ ለማመስገን አትስሰነፍ፣ አትድከው፤ ስታጣው ብቻ ውድነቱ አይግባህ፤ ሲጎድልህ ብቻ ዋጋውን አታስብ። **አዎ!** እየኖርክ ታገል! እያጣጣምከው ስራ፣ እየተደሰትክ ተፋለም። ትግሉን ስትጨርስ ለመኖር አታስብ፤ ከስራው ቦሃል ኑሮን አጣጥማለው አትበል፤ ደስታህን ከፍልሚያው ቦሃላ አታስቀምጠው፤ ለህይወት ጠዓም ቀጠሮ አትስጠው፤ **“ENJOY THE MOMENT! LIVE AND FIGHT!”**

52. "ዛሬ ቀኑ የእኔ ነው!"

ጥብብን የተሞላች፣ ማስተዋልን የታደለች፣ በአምላክ መንፈስ የተቃኘች ነፍስ እመነቷ ሰላም ይሆናታል፤ ፍቅሯ እረፍት ይሰጣታል፤ ምርጫዋ እርካታ ያጎናፅፋታል። በእምነት፣ ሳትሸማቀቅ፣ በነፃነት፣ በልበ ሙሉነት "ዛሬ ቀኑ የእኔ ነው" ትላለች። **አዎ!** ጀግናዬ..! ያንተን የሆነ ነገር የእኔ ማለት አትፍራ፣ አያሳስብህ። **አዎ!** ዛሬ ቀኑ የእኔ ነው በለ ምክንያቱም ያንተ ሆኖ አይተሀዋልና። ያንተ ሆኖ አግኝተሀዋልና። ያለህን "አለኝ፣ የእኔ ነው" ማለት ጉልበት ነው፤ ሃይል ነው፤ ስልጣን ነው።

አዎ! ባንተ የሆነ ነገር ላይ ስልጣን አለህ፣ ታዝበታለህ፣ ትመራዋለህ፣ ባሻህ መንገድ ታስኬደዋለህ፣ ትጠቀመዋለህ፣ ታጌጥበታለህ። ትልቁ ያለህ ነገር ዛሬ ነው፤ አጊጥበት ተዋብበት፤ ነፍስህን ዋጅበት፤ መንፈስህን ቃኝበት **አዎ!** ዛሬ! **“Today has a profound value!”** ዛሬ ዋጋዋ ጥልቅ ነውና ጥልቅ ቦታ ይገባታል። አሸናፊነትህ በጥረትህ ይወሰናል፤ ባሉህ ነገሮች ይደገፋል፤ በእምነትህ ይጎለብታል፤ በፅናትህ እውን ይሆናል፤ በድንቅነትህ ይበሰራል፤ **አዎ!** ዛሬ ቀኑ ያንተ ነው! **“All 24hrs are YOURS!”** እያንዳንዱ በቃናት ውስጥ የሚኖርህ ነገር ያንተ ንብረት ነው፤ ለመጠቀም አታመንታ፤ ወደኋላ አትበል፣ ያለህን ተጠቀም፣ ፀጋህን ጨምር ስጦታህን አብዛ።

53. “እንዲሰጡህ የምትፈልገውን፣ ለእራስህ ስጥ!”

ለሰው ልጅ ከባድ ከሆኑት ስሜቶች አንደኛውና ዋነኛው ስሜት በሚወዱት ሰው የመገፋት፣ የአለመፈለግና ከእርሱ የመለየት ስሜት ነው። **አዎ!** መለያየት እንደመቀራረቡ፣ እንደመወዳጀቱ፣ እንደመፋቀር ቀላል አይደለም። ለዚህም ነው ለብዙዎቻችን የህመም ምንጭ፣ ለተስፋ ማጣታችን ጠባሳ፣ ለመጪው ግንኙነታችን ጥላሸት የሆነብን። ስንት የታሰበበት፣ ነገ ቤተሰበ እንደሚመሰርት ሲጠበቅ የነበር በጥልቅ ወዳጅነት የተሞላ ግንኙነት ሳይታወቅ ይፈርሳል፤ ያበቃል፤ እንዳልነበር ይሆናል። በዚህ ሂደት አንደኛው ግራ ይገባዋል፤ ሌላኛው መሆን እንዳለበት አምኗል።

አዎ! ጀግኒት...! እርሱ መለየትን፣ ማቆሙን ከፈለገ ምክንያቱን ማወቁ ምንም አያደርግልሽም፣ አይጠቅምሽም። ከአልፈልግም፣ ከበቃኝ በላይ ምክንያት ኬት ሊመጣ ይችላል። **አዎ!** አንቺ መውደድ እንደቻልሽው እርሱም አለመፈለግና ካንቺ ነፃ የመሆን ፍላጎቱን አክብሪለት። የወደዱትን መተው ቀላል ሆኖ አያውቅም፤ ወደፊትም ቀላል አይሆንም፤ አሁንም አይደለም ነገር ግን ብዙ ሰው አድርጎታል ምክንያቱም መሆን ነበረበት፣ መሆንም ስላለበት። አዎ! አንዳንዴ እራስን ከመጣል፣ ከብርን ከማሳነስ፣

ጠቃሚውን የእራስ ጉዳይ፣ የእራስ ስሜት ችላ ከማለት መቆጠብ አስፈላጊ ነው። **አዎ!** ፍቅርሽ ገደብ የለውም፣ ውስጥሽ በእርሱ ተሞልቷል እርሱ ግን ያንን መረዳት አልቻለም፤ ከዚህ በላይ ምን ማድረግ ትችያለሽ? ምንም! ወደ እራስ መመለስ፣ እራስን መጠገን፣ ልብን ማከም፣ በሚገባ መማር፣ ስሜትን መቆጣጠር፣ ለእራስ ክብር መስጠት፣ ሌላ ህይወት እንደሚኖር ማሰብ በቀጣይነት ሊደረጉ የሚገቡ ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው።

አዎ! ጀግናዬ..! ለመሰበር የቀረብ፣ ለመጠገን በእጅጉ የራቀ ልብ ይዘህ እንዴት ከሰው ትቀርባለህ? እንዴት ወዳጅነት ትመሰርታለህ? እንዴትስ እራስህን አሳልፈህ ትሰጣለህ? ስብራትን አትፈልግም፤ ጉዳትን አትሻም፤ **አዎ!** እራስህን ጠብቅ! የሚመችህን፣ የሚግባበህን፣ የተጣጣምከውን ሰው ካገኘህ እሰየው ካልሆነ ግን ብቸኝነትህን አጣጥም፣ ሌሎች እንዲያደርጉልህ የምትፈልገውን ለእራስህ አድርግ፤ እንዲሰጡህ የምትፈልገውን ለእራስህ ስጥ፤ ፍቅርን ከፈለክ፣ እርሱን ለእራስህ ስጠ። ክብርን ከፈለክ፣ ለእራስህ አድርገው። እንክብካቤን ካሻህ፣ እራስህን ተንከባከብ። ነፃ በሆንክበት የብቸኝነት አለም፣ ነፃነትህን እያጣጣምክ፣ ዳግም የማታገኘውን እራስህን ፈልገህ የምታገኝበት ጊዜ በአግባቡ እየተጠቀምክ መጪውን ሁነትና ሰው በአውንታዊነትና በተሻለ ማንነት ለመቀበል እራስህን አዘጋጅ።

54. “እየተለወጥክ ነው!”

በነበሩበት መቆየት /Being stable/ ይህን ያክል ከባድ ላይሆን ይችላል ነገር ግን እርሱም በእራሱ ጥንካሬን ይፈልጋል። ለውጥን፣ መሻሻልን ከሚፈልገው ሰወኛ ባህሪ ማፈንገጥና እርሱን ችሎ፣ ተቋቁሞ፣ የለውጥ ማጣትን አለመመቸት መልመድን ይፈልጋል። ልብህን፣ ውስጥህን አንተ ችላ ብትለው እርሱ ግን ዘወትር የተሻለ ነገር አምጣ ማለቱን አያቆምም፤ በተለይ ነገሮች በፍጥነት የሚለዋወጡበት አካበቢ ከሆነ በሃሳብና በጭንቀት ሰላም ይነሳሃል። በዙሪያህ ያሉ ሰዎች ሩጫ ላይ ከሆኑ "አንተስ ተቀምጠህ ምን ትሰራለህ" ማለቱ አይቀርም። የሚያየው፣ የሚሰማው ነገር እንዲነቃ ያደርገዋል። ስለዚህ በነበሩበት መቆየት ወይም ከለውጥ መራቅ ይህንን የለውጥ መዓበል መቋቋምና መቻልን ይፈልጋል።

አዎ! ጀግናዬ..! ተኝተህ ከህሉናህ ከመጋፈጥና ተነስተህ ከልማዶችህ ከመጋጨት የትኛው ሰላም የሚሰጥህ ይመስልሃል? በእርግጥም ለማዶችህን መጋፈጡ ጥልቅ ሰላም አለው። **አዎ!** ለውጥ የማይፈልገው እሳቤህን ተጋፈጥ፣ ከእርሱ ጋር ተጋጭ፣ የመለወጥ ሃሳብህ ውስጥህን፣ ስሜትህን ፈንቅሎ እንዲወጣ አድርግ፣ ወደ ደርጊት እንዲገፋህ ሃይል ሁነው፣ ምራው፣ የለውጥን ከባድ ግጪት ይፍጠር፣ ከመጥሮው ልማድህ ጋር አላትመው፣ ሰብረህ ጥለሀውም እለፍ።

አዎ! በዚህ ጥሎ የማለፍ፣ የመጋፈጥ፣ የመጋጨት ሂደት መደበኛ፣ ተራ ሰው መሆንህ ያበቃል። ከብዙዎቹ ፍላጎታቸውን ከገደቡት፣ "ያለኝ ይበቃኛል እሷን ይባርክልሽ" በምትለው የዘወትር መፈክራቸው ከታጠሩት መደበኛ ሰዎች ተርታ ትወጣለህ። አንተ ከልብህ ፈልገህ፣ ጥረህ፣ ግረህ ወደ ከፍታው በምታደርገው ጥረት በምንም ሁኔታ ቁጭ ብሎ መናን ከሰማይ ከሚጠብቀው የተሻለና እጅግ ከፍ ያለ በረከት ከችሩ አምላክህ እንደሚሰጥህ ጥርጥር የለውም። የለውጥ ጥማት፣ የከፍታው ረሃብ ከውጥህ መውጣት ይኖርበታል፤ እንቅልፍ ሊነሳህ ይገባል፣ ተራ መደበኛ ሰው መሆንን በቃኝ ማለት መጀመር አለብህ፤ ትናንትም ዛሬም አንድ ነገር ማድረግ ማቆም ይኖርብሃል።

አዎ! የለውጥን መንገድ አጣጥም፣ የከፍታውን ውጣውረድ፣ እሾህ ጋሬጣ ተጋፈጥ፣ ትቺቶችን፣ መገፉትን፣ መጠላትን ተቀበላቸው ያስፈልጉሃል። አዎ! እነርሱ ባይኖሩ እየተለወጥክ መሆኑን በቀላሉ ልታውቅ አትችልም። በነበረበት የመቆየት አባዜ የተጠናወተው መንጋ የተለየና የተሻለ ነገር የሚያደርግን ሰው አለመፈለጉ፣ ማግለሉ፣ መተቸቱና መናቁን ለማወቅ የግድ ምሁርነትን አይጠይቅም። አዎ! ሃሳብህም ሰላም ነስቶሃል፣ በነበርክበት እንድትቆይ ይገፋፋሃል፣ "ምን አስጨነቀህ፣ አርፈህ

ብትቀመጥስ" ማለትን ጀምሯል? እንኳን ደስ አለህ! እየተለወጥክ ነው! **“YOU ARE ON THE WAY!”** ጉዞ ጀምረሃል፣ የሚገባህን መርጠሃል፤ ውሳኔህን መተግበር ጀምረሃል። **አዎ!** ጥማትህ እስኪበርድ፣ ረሃብህ እስኪቀል አታቆምም ትቀጥላለህ፣ ትሮጣለህ፤ በርታ! ቀጥል! ግፋበት!

55. “የአዕምሮህ ጠባቂ ሁን!”

አቅሙ የፈቀደና ያለው ነገር የሚያሳስበው ሰው ለእያንዳንዱ ውድ ንብረቱ ጠባቂ ያዘጋጃል፣ ከቤቱ ጀምሮ ደህንነቱን ያስጠብቃል፣ ጥንቃቄን ቀዳሚ እርምጃው ያደርጋል። ምክንያቱም በፀጥታ ክፍተትም ሆነ በጥበቃ ማነስ ሊያጣው የሚችለውንንና ሊደርስበት የማሚችለውን ጉዳት በሚገባ ያውቃልና። አዎ! ማንኛም ሰው ሰላማዊ ስፍራ /Safe Zone/ ሲሆን ደህንነቱ አያሰጋውም፣ ፀጥታው የተጠበቀ ነው፣ ነፃነቱ የፈለገውን እንዲያደርግ ይፈቅድለታል። በጥበቃው፣ በተረጋገጠው ሰላምና በሚሰማው ነፃነት ምክንያት፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! አንተም የአዕምሮህ ጠባቂ ሁን! ደህንነቱን አስጠብቅ፣ **“Safe Zone”** ፍጠርለት፣ ነፃነትን አጎናፅፈው።

አዎ! ምንም ያክል ገንዘብ ቢኖርህ 24 ሰዓት አዕምሮህን እንዲጠብቅልህ የምጥቀጥረው ሰው አይኖርም። ማድረግ የምትችለው አንድ ነገር የአዕምሮህ ጠባቂ አድርገህ እራስህን መቅጠር ነው። ያሉህ ነገሮች ሁሉ ውድ ናቸው፤ አዕምሮህም የውዶችህ ሁሉ አዛዥ ነውና በዋናነት ጠባቂ የሚያስፈልገው እርሱ ነው። እያንዳንዱ እርምጃዎችህ በአዕምሮህ ውስጥ ይፈበረካሉ፣ በተንቀሳቃሽና ታዛዥ አካላትህ ይተገባሩ፤ ስለዚህ የምንም ነገር መሰረቱና ጠንሳሹ፣ የሚያስበው፣ የሚያሚያመዛዝነው፣ የሚያስተውለው፣ የሚወስነው፣ የሚያጣራው፣ የሚመራው፣ የሚያዘው አዕምሮህ ነውና ጥበቃ የግድ ያስፈልገዋል።

አዎ! ከአሉታዊ ሃሳቦች ጠብቀው! ከሚመርዙ ንግርቶች፣ ከሚያውኩ እሳቤዎች፣ ከጥቃቅንና ከሚያሳንሱ መላምቶች፣ ተስፋን ከሌላቸው፣ ነገን ከሚያጨልሙ፣ ዛሬን ከሚያማርሩ፣ ክፋትን፣ ጥላቻን፣ ተንኮልን ከሚዘሩ የወረዱና የረከሱ ሃሳቦች ጠብቀው፣ ከልለው፣ ሸሽገው። ዘወትር አዎንታዊና መልካም ሃሳቦችን መግበው፤ ተስፋን ስጠው፣ የዛሬን ውበት አሳየው፣ ነገን በተስፋ ብረሃን አስጎብኘው፣ ፍቅርን አሳቢ፣ ፍቅርን ተናፋሪ፣ ፍቅርን ኗሪ አድርገው፤ ሰውነቱን አሳውቀው፣ ሳዋዊ ባህሪውን አጉልተህ አሳየው፣ ሰው እንዲሆን አስችለው፤ ፅናትን፣ ትዕግስትን፣ እርጋታን፣ ቅንነትን መግበው፤ በፀኑ የተጠበቀ አዕምሮ ዘሩ ያማረ፣ ፍሬው ጣፋጭ፣ አበባው የፈካ፣ ሰብሉም የበዛ ብዙዎችን የሚመግብ፣ ለብዙዎች የሚበቃ ነውና የልብ ወዳጁ፣ ታማኝ ጠባቂው ሁንለት።

56. “አምላክ የሾመውን ማንስ ሊሽረው ይችላል?”

የአምላክ ስጦታ፣ የፈጣሪ እገዛ ያደረገው ሰውን ምድርን እንዲገዛ በሰውነቱ ልኬት፣ በማንቱ ጥግ በብርታቱ ብዛት፣ በክሆልቶ፣ በጥበቡ ምክንያት ነው። **አዎ!** አምላክ ያነገሰውን፣ እርሱ የሾመውን ማንስ ሊሽረው ይችላል? **አዎ!** ጀግናዬ..! ሹመትህን አትግፋ፣ ስጦታህን አታርክስ፣ በረከትህን አታሳንስ፣ ሰውነትህን ዋጋ አታሳጣው። የአምላክ እጅ ስራ ነህ፣ አስቦ፣ አመዛዝኖ ወደ ምድር አምጥቶሃል፣ ምድርን ታጣፍጥ ዘንድ የድርሻህን እንድትወጣ ወደዚህ ልኮሃል፣ ሾሞሃል። ሹመትህ ሰውነት ነው፣ **አዎ!** ሰው መሆን። ታላቁ አባት ቅዱስ ዳዊት ውድ ልጁን ጠቢቡ ሶሎሞንን ሲመክር "ልጄ ሆይ ሰው ሁን" ብሎታል።

አዎ! ሰውነት ከሁሉ ይበልጣል፣ ስዋዊ ባህሪ ከሁሉ ይገዝፋል፣ የተገራ አስተሳሰብ፣ በበጎ የተቃኘ፣ ሰውነትን ያነገበ፣ ያገዘፈ ማንነት መተኪያ የለውም። የጊዜያት ለውጥ፣ የነገሮች መቀያየር ለብዙ ዘመናት ሰውነትን ሲፈትን፣ ሰው መሆንን ሲያሳንስ ተመልክተናል። ዋናው ጉዳይ አይቶ መማር፣ አይቶ መለወጥ

መቻል ነው። ወደ ምድር በመምጣትህ ልታማርር ትችላለህ ከመጣህ ቦሃላ ግን ባለመኖርህ የምትወቅሰው ማንም የለም። አለምህን የመፍጠሩ ስልጣን ያንተ ነው። የህይወት አቅጣጫህን የምትመራው፣ ምርጫዎችህን የምታስተካክለው፣ የምትወስነው፣ በተመቸህ የምትጓዘው አንተና አንተ ብቻ ነህ።

ሰውነትን የሚበልጥ ሹመትም ሆነ ነግስና አይኖርም። ንጉስን የሚያስከብረው አንድም ምግባሩ ሌላም ተግባሩ ነው። በጥበብ የተቃኘው ምግበሩ፣ የበሰለው ተግባሩ ብቁ ንጉስ ያደርገዋል። ጥበብን፣ ብስለትን፣ ማስተዋልን ሰው ሲሆን ያገኘው ነው። በምድር ስልጣን ሰው ያነገሰህ እንደሆነ፡- ስላልጠቀምከው ሳይሆን ስላልተመቸሀው፣ ስላልተረዳሀው ሳይሆን በእርሱ ስላልተመራህ፣ ስለደከመህ ሳይሆን ስለሰለቸሀው ብቻ ዙፋንህን ይነቀንቃል፣ ንግስናህን ይፈታተናል፣ ይገዳደራል። አምላክ ግን የማይሻር፣ የማይገፈፍ ዘላለማዊ ንግስናን አምኖ ሰቶሃል። ከክብርህ አትውረድ፣ ስጦታህን አታሳንስ ፣በረከትታህን አትግፋፍ፤ ከዙፋንህ አትነስ። በሰውነት ሹመት፣ በእራስ አለም ንግስና፣ ጥበብን ከምግባር አጣጥመህ ደምቀህ ተገኝ።

57. “ምንያክል ዝግጁ ነሽ?”

ትክክለኛውን ሰው ሲያገኝ የሚያበቃ፣ ብርቱ፣ ፈተና የበዛበት፣ አታካች ፍለጋ አለ። ለሚፈለገው ሰውም ሆነ ሌላ ነገር መስፈርት ይቀመጣል፤ የተገኘ ሲመስለን ግን መስፈርቱ ይዘነጋል። **አዎ!** በዚህ አጋጣሚ በትክክለኛው ሰው የፍለጋ መንገድ የተሳሳቱ ሰዎች በተደጋጋሚ ይገባሉ። የእነርሱ መግባት ብስለታችንን ይጨምራል፣ በጥሩ ያስተምረናል። ሳይሞከር የተሻለ ነገር አይገኝም። ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም እንደሚባለው ሁሉ ገና ለገና ጉዳትን፣ ደግም መሰበርን አስቦ ፍለጋን ማቆም፣ ሰውን መሸሽ እያደር ስሜትን ይጎዳል፤ ለብቸኝነትና ለከፉ ጭንቀት ይዳርጋል። የበዛ ጥንቃቄ ግድ ነው፤ ካለፈው ስህተት መማር ምርጫ ውስጥ የሚገባ አይደለም፤ ነገር ግን እየተማሩ መሞከርና ፍለጋን መቀጠልም የግድ ነው። እኛ ስንቆም ጊዜ አይቆምም፣ እድሜ አይቆምም፣ የምንፈልገው ሰውም በቀደመው መወሰዱ አይቀርም።

አዎ! የተሻለን የሚጠላ የለም፤ አሰፍስፎ የሚጠብቅ ሞልቷል። ስሜትን ማጤን ትክክለኝነቱን ማረጋገጥ፣ የምር ስለመሆኑ መተማመን፣ ለቁብ ነገር መሆን እንዳለበት ማሰብ፣ ዘላቂነቱን ማጣራት በመቀጠልም ሳይረፍድ ስሜትን መግለፅ። ህመሙን የደበቀ መዳኒት አይገኝለትም፣ ስሜቱን የሸሸገም የፈለገውን አያገኝም። እዚም እዛም ስላሉ፣ ስለተቻኮሉ ትክክል ያልሆነውን ነገር ግን ትክክል የሚመስለውን ውሳኔ የወሰንን ሊመስለን ይችላል። ከእያንዳንዱ ውሳኔ በፊት ስክነትና ፅሞና በጣም አስፈላጊ ነው። በጥናት የታገዘ ውሳኔ ውጤቱ ያምራል። ዛሬ ወደን ነገ የምንሸሸው፣ ዛሬ ተመችቶን ነገ የምንርቀው፣ ዛሬ አስቸግረን ነገ የምንቸገርበት ፣ዛሬ አስገድደን ነገ የምንገደድበት አይነት ግንኙነት ውስጥ ለመግባት መጣደፍ አያስፈልግም። ከጥድፊያው ይልቅ በተረጋጋ መንፈስ፣ ከዛሬው የነገውን ረጅምና በፈተና የተሞላ መንገድ በማሰብ የሚደረግ ሙከራ እጅግ አመርቂ ውጤት ያመጣል።

አዎ! ጀግኒት..! ምንያክል ዝግጁ ነሽ? ስህተትሽን ላለመድገም፣ በተለየ መንገድ ለመሞከር፣ ፍለጋሽን ለመቀጠል፣ ብለሃትሽን ለመጠቀም ምንያክል ዝግጁ ነሽ? **አዎ!** እንዳለመታደል ሆኖ በጅምላ መፈረጅ / Generalize / ማድረግ ይቀናናል። አንድ የተሳሳተ ውሳኔ በመወሰኑ የተጎዳ ሰውና በብዙ የተሳሳቱ መንገዶች ተጉዞ የተበደለና የተሰበረ ሰው በእኩል ደረጃ ሴቶች እንዲ ናቸው፣ ወንዶች እንዲ ናቸው በማለት ይፈርጃሉ። **አዎ!** ጀግናዬ..! ምርጫዎችህ፣ ውሳኔዎችህ በድጋሚ ተሳሳቱ ማለት ትክክለኛው ሰው የለም ማለት አይደለም። ምርጫህንጂ ስህተቱ ትክክለኛው ሰው በእርግጥም አለ። የምታገኘው በችኮላ ሳይሆን በእርጋታ ነው፤ በሸሺት ሳይሆን በመቀራረብ ነው፤ በፍራቻ ሳይሆን በድፍረት ነው፤ ከሁሉም በላይ በሌላው ሰው መንፅር አንተም ትክክለኛ ሰው ሆነህ በመገኘት፣ የግንኙነት ሂደቶችና

ጥልቅ ቅርበቶች የሚፈጥሩትን ሁነት በእርጋታ በመመልከት ነው።

58. “ዛሬ የተግባር ቀን ነው!”

ዛሬ ውብ ቀን ነች፤ በተግባርህ፣ በስራህ ደግሞ ይበልጥ ታስውባታለህ፤ **አዎ!** ዛሬ የምታስብበት ቀን አይደለም የምትሰራበት ነው፤ የምትጨነቅበት አይደለም የምታከናውንበት ነው፤ የምታሰላስልበት አይደለም የምትተገብርበት ነው፤ **“Today is an action day!”** ዛሬ የተግባር፣ የስራ ቀን ነው! **The day that level you up. The day that change your life for ever. The day that satisfy your soul. It’s today, not tomorrow or the up coming days, TODAY MAKES ALL THESE.** ሁሉን እውን የሚያደርገው ዛሬ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! የሃሳቦችህ ሁሉ ጅማሬ፣ የህልምህን እውንነት ማየት የምትጀምረው ዛሬ ነው፤ በእራስህ የምትኮራው፣ በአውንታዊ ሃሳቦችህ የምትደሰተው ዛሬ ነው፤ ትግበራህ የሚጀምረው ዛሬ ነው፤ ዛሬ ላይ ሆነህ መጪዎቹን የተሻሉና ውብ ቀናት ማየት ትጀምራለህ፣ የእሳቤህን እውንነት ታረጋግጣለህ፣ የሩጫህን ፍጥነት ትጨምራህ፣ አማራጮችህን ታጤናለህ፣ እነርሱ መተው ሳይሆን አንተ ሄደህ ታገኛቸዋለህ፣ ብታጣቸውም በእራስህ ትፈጥራቸዋለህ፣ የጥበቃህ ጊዜያት ያበቃሉ፤ የዛፉ ቅርጫፍ ፍሬው ከብዶት አብሮት እስኪወድቅ አትጠብቅም እራስህ ወተህ የደረሰውን ፍሬ ብቻ ታወርዳለህ፣ ክህሎትህ፣ አቅምህ ሳታውቀው ተከምሮ ጣራ ከመንካቱና አንተንም ዋጋ ቢስ፣ ባለህ የማትጠቀም ከማድረጉ በፊት አንተ ወደ ተግባር ትገባለህ፣ ጉዞ ትጀምራለህ፣ ህልምህን ተኖራለህ፤ ለአካባቢህ የብረሃን ምንጭ ትሆናለህ።

አዎ! ለረጅም ጊዜያት ይህን ባደርግ፣ ያንን ባደርግ በሚለው የሃሳብ ውጣውረድ፣ የግርታ አለም ተጠምደህ ቆይተሃል፤ ግራ መጋባትህ የገዛ ሃሳብህን ከማምታታት፣ ከማወሳሰብና ስሜትህን ከማውረድ የዘለለ እስከ ዛሬ የጠቀመህ ነገር የለም። ስሜትህን የምትጠግነው ከልብህ ስታዳምጠው ነው፤ ስሜትህን የምትቀይረው ማሰብ አቁመህ ማደርግ ስትጀምር ነው፤ ከባዶነት የምትፀዳው የተግባር ሰው ስትሆን ነው፤ ዋጋህ የሚጨምረው ሃሳብህን ስትኖር ነው። **አዎ!** ስሜትህን የምትጠግነው፣ የምትቀይረው፣ ባዶነትን የምትጥለው፣ ዋጋህን የምትጨምረው ዛሬ ነው፤ ወደ ስራ ግባ፤ **“ACTION”** በርታ! ጠንክር! ቀጥል! የተሻለውን አለም ለእራስህም ለአካባቢህም ፍጠር!

59. “የብቃትህ ጥግ ገና ነው!”

"ብዙ ሰራው፣ ለፋው፣ ተጋው፣ እስከምችለው ታግዬአለው አሁን በቅቶኛል፤ ከዚህ በላይ መሄድ አልችልም፤ ብሔድም ምንም አላመጣም፤" ብለህ ባልህበት ቆመሃል? ጥረትህን ቀንሰሃል? የምትችለው ዛሬ የምትሰራውን ብቻ መስሎ ይሰማሃል? **አዎ!** ከልብህ አስተውል በእርግጥ እስከ ጥግ ታግለሃል? እራስህን ሰውተሃል? ተፈትነሃል፣ ደክመሃል? ተርበሃል፣ ተጠምተሃል፣ ታርዘሃል ምንስ አተሃል? ህይወት በቃኝ እስክትል ደቁሳሃለች? ፈተና አብዝታብሃለች? ሰነፍ፣ ልፍስፍስ፣ በቀላሉ እጅ የምትሰጥ አድርጋሃለች?

አዎ! ጀግናዬ..! ገና ከዚህ በላይ እንደሚጠበቅብህ እመን፤ ፈተናዎች ከዚህ በላይ ቢሆኑ ምን ልትሆን እንደምትችል አስብ፤ ቀላል ነገር ትናንተ ያለፈው ነው። ነገም እንዲሁ ዛሬ ላይ ያለውን በጣም ቀላል ሆኖ ታገኘዋለህ። በነበር የምታወራው የነገ ታሪክህ ዛሬ ከባድ ያልከው ጊዜ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! የዛሬ በቃኝ ከነገው ፈተና አያስጥልህም፤ ለዛሬ እጅህን ሰተህ ለነገስ ምንህን ልትሰጠው ነው? እራስህን? በፍፁም! እጅ መስጠትን እርሳው፣ በቃኝን ጣለው፤ ሁሌም የተሻለውን ማሳደድህን ቀጥል። ህይወት እንድትቀል ከሚማፀኑት ሳይሆን ከእርሷ በላይ ገዝፈው ለመታየት ከሚታገሉት ጋር ተጓዝ። አንተ ጀምረህ ሌላው

እንዲጨርስልህ አትመኝ፤ ትንሽ ሰርተህ ይበቃኛል አትበል፣ የተሻለ ከፍ ያለ ነገር ማግኘት እየቻልክ ስለምን በጥቃቅን ነገሮች እራስህን አጥረህ ታስቀምጣለህ? በቃኝ ካልክ የሚጨምርልህ አታገኝም! ከቆምክ የምታገኘው ነገር አይኖርም! እራስህን ካሳነስክ ማንም ሊያነሳህ አይመጣም፤ ሃሳብህን በበቃኝ፣ በአልችልም ካሰርከው እግርህ የትም አይሔድም፤ እንደሌሎች መሮጥን እየተመኘ ብቻ ባለበት ይቆያል።

አዎ! ጀግናዬ..! የብቃትህ ጥግ ገና ነው። ገና ብዙ ይጠበቅብሃል፣ ብዙ ይቀርሃል፤ ረጅም መንገድ ይጠብቅሃል፤ ጥረትህ ሲጨምር ርዝመቱ በእጥፍ ይቀንሳል። የሚገባህ፣ የሚመጥንህ ዛሬ ያለህ አይደለም ከእርሱ ከፍ ያለ ነው፤ ህልምህ ዛሬ ባለህ ትንሽ ነገር አይደናቀፍም፤ ስንፍና ከብርታትህ በላይ እንዲሆን አትፍቀድ፤ የስኬት ረሃብ፣ የተሻለ ህይወት ጥማት እንዲገፋህ፣ እንዳያስተኛህ አድርግ፣ ከልብህ ተራበው፤ ከአንጀትህ ተጠማው። በጥልቀት ፈልገው። **አዎ!** እየቻልክ ጨለማውን የጭንቀትና የቁጪት ጊዜ ወደራስህ አትጥራው።

መዳረሻህ ሳትደርስ አታቆምም፤ የብቃትህን ጥግ ሳታይ አትመለስም፤ በእራስህ፣ በጥረትህ፣ በድርጊትህ እንድሜ ልክህን መኩራት እስክትችል ትሰራለህ፣ ወደኋላ አትመለከትም፤ ጫፉ ላይ ኩራትህን ታገኘዋለህ፤ ጥጉ ላይ የሚመጥንህ ይጠብቅሃል፤ በሰተመጨረሻ የሚገባህን ትሸለማለህ፤ ዛሬ የራቀህን ነገ የምትደርስበትን፣ የብቃትህን፣ የክህሎትህን ጥግ፣ የኩራትህን ምንጭ ሳትደርስበት አታቆምም። የሚገባህን የሚያጎናፅፍህ ውስጥህ የታመቀው ብርቱ ሃይል ነው። እራስህን አነሳሳ፤ እራስህን አበረታታ፤ እራስህን አብቃ፤ ጥረትህን እስከ ክህሎትህ ጥግ ቀጥል።

60. “ውስጥህ ያለው ተዓምር ይሰራል!”

ብዙ ድምፅ ትሰማለህ የምታዳምጠው ግን ጥቂቱን ነው፤ ብዙ ነገር ታያለህ የምትቀበለው ግን ትንሽ ነው፤ ብዙ ሰው ትተዋወቃለህ የምትቀርበው ግን የተመቹህን ነው፤ ብዙ ሃሳብ አለህ የምታደርገው ግን የምትፈልገውን ነው፤ ብዙ ምርጫ አለህ የመረጥከው ግን ጥቂቱን ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! እመን! በዚው ከቀጠልክ ውስጥህ ያለው ተዓምር ይሰራል፤ ፍላጎትህ ጉልበት ይህንሃል፤ ያንተ “Passion” ብዙዎችን ያስርደምማል፤ ከሁሉ በላይ ፈልገህ አድርገው፤ እራስህን ሰዋለት፤ እራስህን፣ ጊዜህን ስጠው። ስኬትህ በደስታህ ውስጥ ነው። እርካታህ በስኬትህ ውስጥ አለ። በደስታ ወደህ ከውስጥህ፣ ከልብህ የምታደርገው የምትጓዘው እርሱ ስኬትህ ነው፣ ተዓምር የሚሰራው እርሱ ነው፤ የሚያሳርፍህ፣ የሚያረካህ እርሱ ነው።

አዎ! ፍለጋህን ቀጥል! ምን ያስደስተኛል? ምን ያዋጣኛል? ውስጤ ምን አለ? ምን ያረካኛል? ምንስ እችላለው? ብለህ ጠይቅ! እስክትመልሰው እንዳታቆም፤ በድጋሚ ጠይቅ። ህልምህ፣ ራዕይህ፣ ግብህ፣ እርካታህ እዚህ ውስጥ ነውና። **አዎ!** አዳምጥ፤ መጠየቅህንም ቀጥል። ዙሪያህን ተመልከት ምን ችግር አለ? የችግሩ መንስኤ ምንድነው? አንተ መፍትሔው መሆን አትችልምን? በሚገባ ትችላለህ፤ አጥና፤ መርምር፤ ክህሎትህን አውጣ፤ ከውስጥህ ከልብህ ህይወትን አጣጥም፤ ወቀሳ አታብዛ፣ ምክንያት አትደርደር፣ ገደቦችን አታስቀምጥ፤ ነቃ በል፤ ውሎህን አሳምር፤ ዋጋ ባለው በሚቀይርህ ነገር አሳልፍ። በችግሮች ውስጥ እራስህን አውጣ፣ እራስህን አብቃ። ውስጥህ ያለው በችግሮች ላይ እንዲረማመድ፣ ተዓምር እንዲሰራ ፍቀድለት።

61. “እነርሱም ያውሩ፤ አንተም ስራ!”

ለምን ይህን አደረክ፣ ለምን ያንን መረጥክ? እንዴት በዛ ትሔዳለህ፣ ለምን እንደዛ ታደርጋለህ? ይሔኮ አይጠቅምህም፣ ያኮ ያከስርሃል፤ ለምን ትደክማለህ፣ ምን ታመጣለህ? ብቻ የተግባር ሰው ከሆንክ

የማትጠየቀው ነገር የለም፤ ቁጭ ካልክም መጠኑ ቢቀንስም ጥያቄው አይቀርልህም፣ አታመልጠውም፤ በገባህበት ይገባል፤ ይከተልሃል። ለምን? አብዛኛው ሰው ከመስራት ማውራትን ስለሚወድ፣ ከተግበር ትቺት ስለሚቀለው። ቀላሉን ደግሞ የማይፈልገው የለም፤ አንደኛው ሲያቆም ሌላኛው ይቀጥላል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ይሔን ነገር ምንም ብታደርግ ልታቆመው አትችልም። ስትሰራ፡- ለምን ይሔንን፣ እንዴት ይሔንን? ካልሰራህ፡- ለምን አትሰራም፣ እንዴት አትሰራም? የሚሉ ጥያቄዎች ይከተሉሃል።

አዎ! ሳትሰራም፣ ሰርተህም ከተተቸህ፣ ከተወቀስክ አስሬ ሰርተህ፣ አስሬ ተሳስተህ፣ አስሬ መሰደቡን፣ መተቸቱን ምረጥ። የሰው ወሬ ፍራቻ የማትጀምር፣ የማትሰራ፣ የማታደርግ አትሁን። **አዎ!** እነርሱም ያውሩ፤ አንተም ስራ። እነርሱም ይተቹህ፤ አንተም አዲስ ነገር ፍጠር፤ እነርሱም ይንቀፉህ፤ አንተም ጉዞህን ቀጥል፤ እነርሱም ዋጋ ያሳጡት፤ አንተም ዘወትር ከፍ ማለትህን ግፉበት። ሰነፎች፣ ደካሞች፣ ሰበበኞች ትናንት ሲተቹ ነበር፤ ዛሬም እየተቹ ነው፤ ነገም መተቻታቸውን ይቀጥሉሉ። ብርቱዎች፣ ጠንካሮች፣ ታላቆች ትናንትም ሲሰሩ ነበር፤ ዛሬም እየሰሩ ነው፤ ነገም ይሰራሉ። ለማይረቡ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተጨንቀው አያውቁም፤ ይልቅ እንደመማሪያ ይጠቀሙበታል፤ ትክክለኛው መንገድ ላይ እንደሆኑ ያረጋግጡበታል። **አዎ!** ጥያቄ በዛብህ? እንደማይሆንልህ፣ እንደማይሳካልህ ተነገረህ? ፍንጭ ተሰቶሃልና መቼም እንዳታቆም፤ ግብህን ሳትጨብጥ፣ ከመዳረሻህ ሳትደርስ መቆም የለም። አዎ! ድንቅ ሆነህ ተፈጥረሃልና ድንቅ ማድረግህን ትቀጥላለህ።

62. “የፈለከውን ሆኖ ተመልከተው!”

ከማሸነፍህ በፊት አሸንፈህ ተመልከተው፤ ከመድረስህ በፊት ደርሰህ እራስህ እየው፤ ከማሳካትህ በፊት ተሳክቶ ተመልከተው፤ የምትፈልገውን ነገር ቀድመህ በምናብህ እየው፤ ወደርሱ አቅጣጫ ብቻ ተጓዝ፤ እርሱ ላይ ትኩረት አድርግ። ህልምህን ስትኖር የሚሰማህን ስሜት አምጣው፤ በእራስህ ላይ እርሱን አንግሰው፤ ወደፊት እንዲገፋህ ፍቀድለት። **አዎ!** ጀግናዬ..! ለርቀቱ ግድ አትስጠው ያንን የፈለከውን ሆኖ ተመልከተው፤ ተሳክቶ፣ ጨብጠህው፣ ኖሮክ የሚሰማህን ስሜት ማጣጣም ጀምር። በምናብህ የምትፈጥረው፣ በሃሳብህ የሚመላለሰው፣ ቀልብህን፣ ስሜትህን የገዛው ነገር መጥፎም ይሁን ጥሩ መከሰቱ አይቀርም።

አዎ! ስለሃሳብህ አስብ፤ አስጨንቆሃል ወይስ ሰላም ሰቶሃል? አሳምሞሃል ወይስ አሳርፎሃል? አስንፎሃል ወይስ አበርትቶሃል? አነቃቅቶሃል ወይስ ልነፍስፍስ አድርጎሃል? አስሮሃል ወይስ ነፃ አድርጎሃል? **አዎ!** የደከመህ ደክሞህ አይደለም፣ ለአዕምሮህ እንደ ደከመህ ስለነገርከው ነው፤ የደበረህ ደብሮህ አይደለም፣ ህሳብህን ስለድብርት እንዲያስብ ስለገፋሀው ነው፤ የተደሰትከው፣ የቀለለህም ሃሰብህ በደስታና በሃሴት ስለተሞላ ነው፤ ትኩረት የምትሰጠው፣ ደጋግመህ የምታስበው በእውኑ የሚከሰትና የምትኖረው፣ የምትተገብረው ሁነት ነው። አለማሰብ አትችልም፤ ሃሳብህን ማስተካከል፣ መቃኘት ግን ትችላለህ። **አዎ!** ጀግናዬ..! ስለምታስበው አስብ፤ ስለ ምናብህ አስብ፤ ከሃሳብህ ጀርባ ስላሉት ስሜቶች አስተውል። ሀሳቡን ያስተዋለ፣ የገራ፣ ያስተካከለ መንገዱ ሁሉ ቀና ነው፤ ምኞቱ ሁሉ ቅርቡ ነው፤ ህልሙም በእጁ ነው።

63. “ብዙ ስትለቅ፣ ብዙ ታገኛለህ!”

አዎ! ብዙ ስትለቅ፣ ብዙ ታገኛለህ፤ ብዙ ስታገኝ፣ ብዙ ትለቃለህ፤ መልቀቅህ የተሻለውን ለማግኘት መንገዱን ይከፈትልሃል፤ በአንዴ ብዙ አታግበሰብስም፤ ሰው ቢሄድ የተሻለ ሰው ይመጣል፤ ስራ ቢሔድ የተሻለ ስራ ይመጣል፤ ውጤት ቢያንስ የተሻለ እድል ይከፈታል። **አዎ!** ጀግናዬ..! የሆነው ሁሉ ለሚሆነው መንገድ እየከፈተ ነው። የማይሆነውም ላለመሆኑ በቂ ምክንያት አለው። ከአቅምህ በላይ ከሆነ መተውን ልመድ፤ ጊዜ እንዲያደርገው፣ እንዲፈፅመው ፍቀድ።

አዎ! አምባገነን፣ እኔ ያላልኩት አይሁን አትበል። አንተ ስላልከው ሳይሆን መሆን ስላለበት፣ በምክንያት ይሆናል። ውጤትህ እንዳይበላሽ ትፈልግ ነበር ነገር ግን ተበላሸ አንዴ ሆኗል፤ በዚህ ምክንያት የሚያበቃ ነገር የለም፤ ምናልባት በፊት ስታስበው የነበረውን እቅድህን ድጋሜ ከውጤትህ አንፃር መከለስ ሊኖርብህ ይችላል፤ እርሱን አድርግ። **አዎ!** ጀግኒት..! ከተወሰነ ጊዜ ቦሃላ የእራስሽ ቤተሰብ እንዲኖርሽ ታስቢ ነበር ነገር ግን ሳይሆን ቀረ፤ ያልሆነው በምክንያት ነው፤ ለበጎ ነው። ካልሆነ ብለሽ በግድ መስርተሽ ቢሆን ሊገጥምሽ የሚችለው ነገር ምናልባትም ለእድሜ ልክ ጠባሳ ሊያጋልጥሽ ይችል ነበር። የለፋህበት፣ የደከምክበት ስራ ያሰብከውን ውጤት አላመጣለህም ይሆናል፣ በትጋትህ ልክ አላስደሰተህም ይሆናል፤ እርሱም ቢሆን በምክንያት ሆነ። የተወሰነ ጥረትህን ብትጨምር ምናልባት ካሰብከው በላይ በብዙ እጥፍ ታገኝበት ይሆናል። ይህ ያነሰ ውጤትም ለተሻለው ስኬትህ በእልህ ይበለጥ እንደሚያነሳሳህ አስብ።

አዎ! ለስንት አመት ጊዜያችንን ሰተን፣ እራሳችንን ሰውተን፣ ያለንን ሰተን በጉጉት ስንጠብቀው የነበረው ነገር የማይጠቅም፣ ተራና ቀላል ነገር ሆኖ ልናገኘው እንችላለን። ዋናው ጉዳይ ግን ለተራው ነገር ይህን ያክል መሱዓትነት ከከፈልን ትልቅና ዋጋ ላለው ነገር ደግሞ ምንያክል መክፈል እንደምንችል ነው። በመጥፎና እልህ አስጨራሽ ፈተና ውስጥ አስደሳቹንና ተወዳጁን ማንነት እናተርፋለን፣ የላቀውን እናፈራለን። በእኛ እሳቤ ጥሩ የነበረው ነገር ለእኛ ስላማይሆን፣ ሊጎዳንና ሊያጠፋን ስለሚችል መልቀቅ ይኖርብናል። **አዎ!** ጀግናዬ..! በመልቀቅህ፣ በመተውህ፣ በማቆምህ አትፀፀት፤ ባትለቅ የምትቀበለው አይኖርምና፤ ባታቆም ሌሎች አማራጮችን አታይምና፤ የቀረብህ ለበጎ ነው፤ የቀረህበትም ለመልካም ነው፤ መጪውንና የተሻለውን መቀበል ስላለብህ ነው።

64. “አንተ ነህ!”

ወድቆ በበመነሳት፣ አግኝቶ በማጣት፣ ተሰብሮ በመጠገን፣ ወጥቶ በመመለስ ሂደት ውስጥ የብዙ ሰዎች ተሳትፎ ይኖራል ነገር ግን የአንበሳውን ሚና የምትጫወተው አንተ ነህ። **አዎ!** አንተ ነህ! ሰው ታማክራለህ፣ እንዴት ካለህበት ችግር መውጣት እንደምትችል ትጠይቃለህ፣ ምን ማድረግ እንደምትችል ትጠይቃለህ፣ ማን እንደሚረዳህ ታጣራለህ። **አዎ!** ጀግናዬ..! የተም ብትሔድ፣ ማንንም ብትጠይቅ አንድ ሊረዳህና ካለህበት አስከፊ ሁኔታ ሊያላቅቅህ የሚችለው አንድ ሰው እንደሆነ ይነገርሃል፤ እርሱም አንተ ነህ! አማካሪህ አቅጣጫዎችን ሲያስቀምጥልህ "እንደዚህ ብታደርግ፣ እንደዛ ባታደርግ" በማለት የሚጠቁመው ለሌላው ሳይሆን ለእራስህ ነው። እርሱ የሚረዳህ አንተ ስትረዳው፣ ስትረዳው ብቻ ነው።

አዎ! ለየትኛውም ችግርህ መፍትሔው ተቀምጧል፤ ለጊዜው ሊሰወርብህ ይችላል፤ መንገድ እንዲጠቁምህ ካንተ በተሻለ እይታ፣ ማስተዋል የሚችል ሰው ጋር ከሔድክ ግን በቀላሉ ቁልፉን ታገኘዋለህ፣ የምትከፍትበት ግን አንተ ነህ። ሌላኛው ሰው ቁልፉን ከማቀበሉ በቀር ያንተን ጉዳይ ሊከፍተውና ሊዘጋው አይችልም፤ እርሱ ስልጣን ያንተ ነው። **አዎ!** የመፍትሔ ሃሳብ ይሰጥሃል፤ የምትተገብረው ግን አንተ ነህ፤ አቅጣጫዎች ይቀመጡልሃል የምትጠቀመው ግን አንተ ነህ፤ በምንም ሁኔታ ላንተ መፍትሔ መሆን የሚችለው ሰው አንተና አንተ ነህ። አምላክህም የሚረዳህም፣ ከጎንህ የሚቆመው በእራስህ ስታምን፣ በእርሱ ስትተማመን ነው። **አዎ!** ጥበቃውን አቁም፤ የሆነ ሰው መጥቶ ካለህበት አጣብቂኝ እንዲያወዛህ አትጠብቅ፤ እራስህን በብቃት የምትረዳው አንተ ነህ፤ ጠቃሚ ሃሳቦችን ተቀበል፣ እነርሱንም ፈፅም፤ የተግባር ሰው ሁን፤ ችግሮችህን በእራስህ ተጋፈጥ፤ አንተው ፍታቸው።

65. “ውደቅ ግን እንዳትወጣ!”

ውደቅ ግን ከክቡ፣ ከ **“Ring”** አንዳትውጣ፣ ተመታ ግን እንዳትሸነፍ፤ ውረድ ግን በዛው እንዳትቀር፤

ተገፋ ግን እራስህን አትጣ፤ ተላተም ግን ወደኋላ አትመለስ፤ ተጋጭ ግን አታቁም፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! ለመክፈል ተዘጋጅ፤ ሽልማትህንም ትቀበላለህ። የጉዞህ ማብቂያ ስታቆምንጂ ስትወድቅ አይደለም፤ የህልምህ አለመሳካት እምነት ሲጎድልህጂ ስትሰበር አይደለም፤ መዳረሻህ የሚርቅህ ተስፋ ስታጣንጂ መሰናክሎች ስለበዙ አይደለም። **አዎ!** ውደቅ ግን እንዳትወጣ፤ ተሰበር ግን ተስፋ እንዳትቆርጥ፤ ታመም፣ ተሰቃይ፣ ተዋረድ፣ ተተች፣ ተሰደብ ግን መቼም እንዳታቆም። የተፈጠርክለትን ህልም ሳታሳካ አትመለስም፤ ግብህን ሳትመታ መቼም አትቀርም፤ ራዕይህን ሳትጨብጥ ወደኋላ አትልም፤ ያንተ መገለጫ ይህ ነው። ትጋት፣ ልፋት፣ ድካም በስተመጨረሻም ድምቀት፣ ፍካት፤ ውበት።

አዎ! ያንን ስኬቱ በድምቀት የሚታያውን፣ ለሰውች ተምሳሌት የሆነውን፣ በእራሱ የሚተማመነውን፣ በእራሱ የሚኮራውን፣ ራዕይውን በመዳፉ የጨበጠውን፣ ጠንካራውን፣ ብርቱውን ሰው ማንነት ሲያጠኑ፣ ሲያጣሩ በስተመጨረሻ አንተ መሆንህን ያረጋግጣሉ። ውድቀት እንዳላቆመህ ትናገራለህ፣ ትቺት፣ ዘለፋ፣ ጫና፣ ግፊት ካሰብከው እንዳላስቀረህ ትመሰክራለህ። የተመቻቸ መንገድ ገጥሞህ አያውቅም፤ ያንተ ምቾት ህልምህን ስትኖር የምታገኘው ውስጣዊ እርካታ ነው። ከፈተና የፀዳ ጉዞ ተጉዘህ አታውቅም፣ እንቅልፍ እያማረህ አልተኛህም፤ መዝናናት እየፈለክ አላደረከውም፤ ትናንት ፍላጎትህን የገደብከው ዛሬ በነፃነት ልታጣጥመው ነው፤ ትናንት እራስህን ያቀብከው ዛሬን የተሻለ ለማድረግ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! ይህ ያንተ ህይወት ነው። ዛሬ ትተገለህ ነገ ትፈካለህ፤ ዛሬ ትለፋለህ ነገ ትደምቃለህ፤ ዛሬ ትተቻለህ ነገ እርዳታ ትጠየቃለህ፤ **አዎ!** ይህ ነው ያንተ ህይወት፣ ማለምህን ቀጥል፤ እመን፤ የተስፋ ስንቅህ ዘወትር አትለይህ፤ ጥረትህን አድንቅ፣ መንገድህን ውደድ፣ እርሱን አጣጥም፣ በእርሱ ተደሰት።

66. “ትናንት ምን ተከልክ?”

ትናንት ምን ተከልክ? ዛሬስ ምን አሰብክ? አንድ ተክል ካልተተከለ አይበቅልም፤ ሰብልም ካልተዘራ አያፈራም፤ ሁሉም መሰረት አለው፤ ትንሽ መሰረት በሂደት የሚያብብ ፍሬም የሚያፈራ። **አዎ!** ጀግናዬ..! ትናንት ምን ተከልክ? ስለምን ስታወራ ነበር፣ ምንስ አዘወተርክ? ከማን ጋር አሳለፍክ፣ ምንስ ተማርክ? ትናትህን ተከትለው የሚመጡ የዛሬ ውጤቶች ይከቡሃል። እያንዳንዱ ፍሬ የሒደት ውጤት ነው። ዛሬ ተክለው ዛሬ ካለበቀለ የሚሉ ብዙዎች ውጤት አለባ ሆነዋል። በትናንታቸውና በዛሬያቸው መሃል የቀናት ልዩነት ካልሆነ በቀር ምንም አዲስ ነገር የለም። ወደፊት ስላልነበራቸው ባሰቡት መንገድ ሳይሆን ህይወት ባስቀመጠችው ጎዳና ይጓዛሉ። አዎ! የትናንትናህን ውጤት ዛሬ እያየህ ነው። የዘራሀው ዘር ዛሬ ፍሬው በእጅህ ነው። ጥላቻን ከዘራህ ክፋት ውስጥህን ያምሰዋል፤ ፍቅርን ከዘራህ ሰላምን ታተርፋለህ፤ ከዛሬህ ይልቅ ያለፈው ትናንት ካሳሰበህ ዛሬን እያባከንክ ነው።

አዎ! ትናንት ምን አድርገሃል? ዛሬስ ምን አስበሃል? የትናንተ ዋጋ ዛሬ ላይ ሆነህ በሚገባ ይገባሃል፤ ውጤቱን ዛሬ በግልፅ ታያለህ፤ ፍሬው የፈካ ይሆን የተበላሸ፣ እንክብካቤ ያነሰው ይሆን የበዛበት፣ የእድገት ጠላት አረሞች አብረው አድገው ይሆን ተነቅለው። ትናንት ቂም፣ በቀል፣ ጥላቻን ይዘህ ብትታገል፣ ብትለፋ የዛሬው ውጤትህ ከአረም ጋር እንዳደገ ሰብል ነው። ያሰብክበት ሳትደርስ እራስህን ታገኘዋለህ። ይበልጥ ለማደግ በሞከርክ ቁጥር አረሙ አስሮ ይይዝሃል፣ ምግብህን ይሻማሃል፤ በመጨረሻም ማደግ እየቻልክ የእድገትህ ማነቆ ሆኖ ታገኘዋለህ።

አዎ! ጀግናዬ..! ትናንት በሰራሀው ዛሬን እየኖርክ ነው፤ ነገም እጣዋ በዛሬህ ውስጥ ነው። ስለዚህ ዛሬን በማጣጣም ሂደት የምትተክለውን ተክል፣ የምትዘራውን ሰብል ለይ። በምንም ሁኔታ ካደጉ ቦሃላ ያሚስቆጩህ እንዳይሆኑ ተጠንቀቅ። የእድገትህ ማነቆ የሆኑትን አረሞች አስወግድ፤ በምትኩ የእድገት፣ የለውጥህ ግብዓት የሆኑትን መልካም ሃሳቦች ይዘህ ተጓዝ።

67. “በህልሞችህ አመን፤ የተሰጡህ በምክንያት ነውና!”

ምክንያታዊ አመኔታ የስኬት ቁልፍ ነው። አምነህ፣ ተማምነህበት የምታደርገው ነገር የእውንነት መንገዱ ብዙ ነው። ስላመንከው ብቻ ብዙ አማራጮች ታያለህ፣ መሆኑን ስለተቀበልክ ሂደቱ አያሳብህም ዋናው ትኩረትህ ተሳክቶ ማየት ላይ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! የተለየው ትልቁ ህልምህ ወዳንተ ሲመጣ ብዙ ምክንያቶች ይኖሩታል፤ ዋናው ምክንያቱ ግን ህይወትህን ትርጉም ሊሰጣት፣ ሊያሳምርልህና ሊያጣጥምልህ ነው። አንተን ብሎ ሊጠቅምህ የመጣን ሲሳይ መግፋት እንዳማትፈልግ ግልፅ ነው። ህልምህም የመኖርህ ስጦታ፣ የህይወትህ ሲሳይ ነውና ተቀበለው፣ እመነው፣ ተማመንበት። በሁለት መንገድም ታሳካዋለህ አንድም በምትኖረው ሂደት፣ ሌላም ባመንከው፣ በምታሳካው ህልምና በመጨረሻ በምትመታው ግብ።

68. “ግዴለም ደግፈው!”

ስለምን ከማበረታታት ይልቅ ትቺት ይቀናናል? ስለምን ከመደገፍ ይልቅ መግፋት ይቀለናል? ትርፍ ይኖረው ይሆን? ጥቅሙስ ምንድነው? ምንም! በሚለፋ፣ በሚተጋና በሚፋለም ሰው ምክንያት ምናልባት የመበለጥ ስሜት ሊሰማን ይችላል እርሱን ግን ሰርተን፣ ለፍተን እንጂ የሚሰራውን ተችተን፣ ገፍተን፣ አውርደን፣ ወደኋላ ጎትተን ልናስቀረው አንችልም። **አዎ!** ማበረታታትና መደገፍ ባትችል እንኳ ትቺትህን በልክ አድርገው። በአንተ የማይረባና ዋጋ ቢስ እሾህ ቃል ስንት ከእራሱ አለፎ ለሃገር የሚበቃ ሰው ተወግቶ ሊወድቅና ተስፋ ሊቆርጥ እንደሚችል አስታውስ። ማበረታት ካልቻልክ ዝምታን ምረጥ፤ ማንም የፈለገውን እንዲሰራ ፍቀድለት። ደስ ብሎት ድጋፍህን ቢጠይቅ አንተ ባታምንበትም እርሱ ስላመነበት ብቻ ከአሉታዊ ንግግርና ከማሳነስ ተቆጠብ። በእርሱ ውድቀት የምታተርፈው ነገር የለም፤ ምናልባት ብትደግፈው ግን ትልቅ ነው የምትለውን ነገር ባታገኝም የእርሱን ደስታና ምስጋና ታተርፋለህ። ትቺት፣ ዘለፋ፣ ጥላቻ አይልመድብህ ተወው።

አዎ! አንተ ያላደረከውን በማድረጉ ኩራበት፤ አንተ ያላሳካህውን በማሳካቱ አድንቀው፤ አንተ ያልሰራሀውን አስውቦ በመስራቱ አሞካሽው፤ **አዎ!** በአንተ ተስፋ አስቆራጭ ቃላት ካንተ ምድብ እንዲመደብ የምታደርገው ጥረት ያንተንም የእርሱንም ህይወት እንደሚያበላሽ እወቅ። ወዳጅህ ቢሳካለት ከእርሱ በመቀጠል ዋነኛው ተጠቃሚ አንተ ነህ። **አዎ!** ጀግናዬ...! ግዴለም ደግፈው፤ ግዴለም አበርታው፤ አጠንክረው፤ "አለውልህ፣ ከጎንህ ነኝ" በለው፤ ወዳለህበት ዝቅታ ከምትጎትተው ይልቅ ለሚወጣው ከፍታ ድካፍ ሁነው። የእርሱ ስኬት ያንተ ደስታ ይሁን፤ አብረሀው አጣጥም፤ ደስታውን ተካፈል፤ ተጠጋው አብረሀው ተሻገር፤ የእርሱ መንገድ ላንተም በር እንደሚከፍት አስብ። **አዎ!** እንዲደረግልህ የምትፈልገውን ድጋፍ ለወዳጅህ አድርግ፤ ህልሙን እንዲኖር አበርታው፣ የእርሱም ስኬት ያንተ ይሁን።

69. “ከሰነፎች ተጠበቅ!”

አዎ! ቅዱስ መፅሐፍ ልብን የሚያንፅ፣ መንገድን የሚያፀና ደንቅ አስተምህሮ አለው። "ከሰነፍ ሰው ጋር ነገርን አታብዛ፤ አዕምሮ ከሌለውም ጋር አትሒድ፤ ወደ መከራ እንዳያገባህ፣ አንተም በእርሱ ስንፍና እንዳትነቀፍ ተጠበቅ።" ይላል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ስንፍናን የምትጠላው፣ ሰነፍን የምትጠየፈው በምክንያት ነው። ስንፍና ትርፍ የለውም ኪሳራውም ያመዝናል፤ ሰነፉም ቢሆን አንዳች የሚረዳህና የሚያስተምርህ ነገር የለው። ስለዚህም ነው ከሰነፎች ተርታ መጠበቅ የሚኖርብህ። ብርቱ እንኳን ብትሆን ሰነፉ ወዳጅህ ብርታትህን ያኮስሰዋል፣ ያጠፉዋል።

አዎ! ሰነፍ ለስንፍናው ምክንያት አያጣም አስቦበት፣ መርጦት እንደሆነ ሊያሳምንህ ይሞክራል።

እንዲተወው ብትነግረው ልብህን ይደክምሃል። ብልህ ከሆነ ያንተ አንድ ቃል ያነቃዋል፤ ሞኝነቱ ግን ቃላት ብትደረድር፣ ልታሳምነው ብትጥር እዳች ፈቀቅ የሚል ነገር አታገኝም። **አዎ!** ከሰነፍ የቀረበ ግንኙነት አይኑርህ፤ ከሰበበኛ ሰው ጉዳይ አታብዛ፤ ጠልፎ ሊጥልህ የተዘጋጀ አደገኛ መሰናክል እንደሆነ አስተውል። የሰውን ልጅ ውሎውና ወዳጁ ከሚያጠፉት በላይ የሚያጠፋው፣ ገደል የሚከተው፣ ከመንገድ የሚስወጣው ነገር የለም።

አዎ! ብልህ ሁን፤ ከሰነፎች ተጠበቅ! እንዳያሰንፉህ፤ እንዳያስቱህ፤ እንዳያስቀሩህ፤ በፍቃድህም ትልቁን በደል እንዳይበድሉህ በብዙ ተጠበቅ። ልቡን የሚከተል ሰነፍ አይሰማም፤ ወደፊቱን የሚያስብ ከሰነፍ ነገር የለውም፤ ህልሙን የሚኖር በህልመኞች፣ በብርቱዎች ተከቧል፤ ስል ስንፍና ለማሰብ ጊዜ የለውም፤ ይሮጣል፤ ይሯሯጣል፤ በየጊዜው ይባንናል፤ ይነቃል፤ ይታገላል፤ ጆሮው ህልሙን፣ ስኬቱን እንጂ ሰነፎችን ሰምቶ አያውቅም። መንገዱ ሁሉ በሰነፎች የተሞላ ቢሆንም እንዴት እንደሚያልፋቸው ብልሁ አዕምሮው ጠንቀቆ ያውቃል። ወሬን ለወረኞች፣ ስራን ለሰሪዎች። ሰነፍ ማውራት ይችላል፤ ብርቱና ጠንካራው ግን አስውቦ መስራቱን ከስር መሰረቱ ጠንቅቆ ያውቅበታል።

አዎ! ክፋትን፣ ጥላቻን፣ ምቀኝነትን እንደምትጠየፈው ሁሉ፣ ድህነትን፣ ተረጂነትን ያስታቀፈንን ስንፍናንም እንዲሁ አብዝተህ ተጠየፍ፣ አግልለው። ከብርቱዎች፣ ከድንቅ አሳቢዎች፣ ከድንቅ አድራጊዎች ተወዳጅ፣ መንገድህን አፅና፤ ጉዞህን አፍጥን። እየኖርክ ባለው ህይወትና እንዲኖርህ በምትፈልገው መሃል ያለው ልዩነት ምርጫ ይባላል። **አዎ!** እያንዳንዱ ዛሬ ያሉህ፣ የሌሉህ ነገሮች ስለመረጥካቸው ውይም ስላልመረጥካቸው አብረውህ አሉ ወይም ካንተ ተለይተዋል። ወደድክም ጠላህም በዚህ ሰዓት የምታደርገውን ነገር መርጠህ እያደረክ ነው። መፅሐፍ አንብብ፣ ፊለም ተመልከት፣ የቤት ስራ ስራ፣ ከወዳጅ ቤተሰብህ ጋር አሳለፍ ካሉህ ሌሎች አማራጮች እነርሱን መርጠሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! ምርጫህ ተፅዕኖው እስከ ሙሉ ህይወት ለውጥ ድረስ ነው። ስለዚህ በእያንዱ ውሳኔህ፣ በእያንዱ ምርጫህ ፍላጎትህን ደጋግመህ ቃኘው፤ ሌላውን የሚያስደስተው አንተን ሊያበሳጭ ይችላል፤ ሌላውን የሚያሳርፈው አንተን ሰላም ሊነሳህ ይችላል፤ ምንም ነገር ለመምረጥ ከመወሰንህ በፊት ደጋግመህ ልብህን አዳምጥ፤ "ምርጫዬ ይጠቅመኛል? የምፈልገውን ህይወት ይሰጠኛል? ቦሃላ አያስቆጨኝም?" ብለህ ጠይቅ፤ በመቀጠል በጥንቃቄ ከውነው። መኖር ለምትፈልገው ህይወት የሚያበቃህን ምርጫም ምረጥ።

70. “ሳይደርስብህ ንቃ!”

እረፍት አልባ ከሚባሉት ሁነቶች ቦሃላ የሚመጡ አሳራፊ ቀናት አሉ፤ ከባድ ከሚባሉት ቀናት ጀርባ የሚመጡ ቀላል፣ አስደሳች ቀናት አሉ፤ ለአንዳንዱ ቀናት፣ ጊዜያት፣ ሰዓታት እንደሮጡ ይሰሙታል ለሌላው አንዷ ደቂቃ እንደ ወንዝ ዥረት አላልቅ ትለዋለች። ያለንበት ሁነት የተሰጠንን ጊዜ መጠን ሲወስን እናያለን። ግማሹ ጊዜ አጥሮት ይሯሯጣል ሌላው ካለው ጊዜ ብዛት የት እንደሚያሳልፈው፣ በምን እንደሚጨርሰው ግራ ይገባዋል።

አዎ! ጀግናዬ..! ሁሉም ነገር ማብቂያ አለው። አለኝ ብለህ የምትመፃደቅበት ጊዜ የሆነ ሰዓት እንደ ጉም ተኖ ይጠፋል ብትፈልገው አታገኘውም፤ ዛሬ "ጊዜ ለማሳለፍ" የምትለውን ቅፅበት ትረሳዋለህ። ትርፍ የምትለው ሰዓት ይናፍቅሃል፤ የምታርፍበት ጊዜ እንኳን ትርፍ እንዳልሆነ ይገባሃል። **አዎ!** በህይወታችን ተራ ናቸው የምንላቸው ነገሮች ሁሌም ቀላልና ተራ ሆነው አይቀጥሉም። የሆነ ሰዓት ዋጋቸው በጣም ከፍ ይላል፤ ይወደዳሉ። እንደ ቀልድ ሲባክኑ ከርመው ኋላ ግን መገኛቸው ይርቃል። ዛሬም፣ ነገም ለነገሮች የምትሰጠው ምልከታ አንድ አይደለም። ብስለት ይኖራል፣ እድገት ይከተላል።

አዎ! ሳይደርስብህ ንቃ! ሳይመጣብህ ተማር፤ ቸግሩ ሳይደርስብህ አንተ ንቃ፤ ስላለህበት አመስግን፤ ህይወት እያሳመመች ሳታስተምርህ አንተ ቀድመህ ተማር፤ ያለህን ስታጣ ውድነቱ አይግባህ፤ እያለህ ዋጋ ስጠው፤ አተሀው ከምትለምን፣ ስላለህ አመስግንበት። ትርፍ ጊዜ የሚባል ነገር የለም። ላንተ የሚተርፍህ፣ ለሌላው የሚጠብበት ምክንያት የለም። ሁሉም እኩል ሰዓት ተሰቶታል ሌላው ከተግባሩ ብዛት አጥሮት ይሆናል፣ አንተ ግን ከተግባርህ ማነስ ተርፎህ ሳይሆን ተጨማሪ ተሰቶህ ነው። ትርፍ ሲሆን በከንቱ ቢያልፍም ጫና የሌለው ይመስላል፣ ተጨማሪ ሲሆን ግን የተለየ ነገር ለመፍጠር እንዲውል ይገፋፋል።

አዎ! የህይወት ጉዞ ቀጥሏል፤ ትናንት፣ ዛሬ፣ ነገ በተለያዩ ሁነቶች ተሞልተው ይቀጥላሉ። የተሻሉና እራስህን የምታውቅበት፣ እራስህን ከፍ የምታደርግበት፣ ጥሩ ቦታ የምትገኝበት መልካም ጊዜያት እየመጡ ነውና ተሰፋ አትጣ፤ ተስፋ አትቁረጥ፤ ካለህበት ለመውጣት ሁሌም ተስፋ አለህ፤ እመን! መውጫህም ቅርብ ነው፤ ዛሬን ቀና በል፤ ነገ ዝቅ ያሉትን ታቀናለህና።

71. “በቅድሚያ ልማዶቻችንን እኛ እንሰራቸዋለን፤ በመቀጠል እነርሱ ይሰሩናል!”

የልማድን ግሩም ሃይል ለማወቅ ዛሬ ያለንበትን ደረጃ መመልከት በቂ ነው። ዛሬያችን የትናንት ልማዶቻችንን ውጤት መሆኑ ግልፅ ነው። ዋናው ጉዳይ ጠቃሚ ተግባሮች ልማድ እስኪሆኑ የሚያስከፍሉት ዋጋ ከባድ መሆኑ ነው። በእርግጥ አንድ ድርጊት ልማድ ከሆነ እርሱን ማቆሙና በሌላ መቀየሩ በጣም ከባድ ነው። ጥልቅ ጥንካሬን ይጠይቃል፤ ቆራጥነትን ይፈልጋል፤ ጉዳቱን ደጋግሞ ማሰብ ያስፈልጋል፤ እስከ ዛሬ ሲደረግ ቢቆይም ምን እንደጨመረልን፣ ምን እንዳሳጣን ማሰቡ ተገቢ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! ምንያህሉ ልምዶችህ ሰርተውሃል? ምንያህሉስ እያጠፉህ ይገኛሉ? እራስህን ለመፈተሽ አትስነፍ። እራስህን ሳታገኝ የምትሻገረው ደልድይ፣ የምትደርስበት መዳረሻም አይኖርም። **አዎ!** የሚገነቡህም ልማዶችህ ስለፈቀድክላቸው እየገነቡህ፣ እየሰሩህ፣ ከፍ እያደረጉህ ይገኛሉ። የሚያጠፉህ፣ የሚያሳፍሩህ፣ የሚያሸማቅቁህ ልማዶችህም እንዲሁ ስለፈቀድክላቸው እርሱን ያደርጋሉ። በእራስህ ጉዳይ ፈቃጁም ከልካዩም አንተ ነህና እንዲወዳጁህ የምትፈቅድላቸውን ልማዶች ለይ፤ የምትከለክላቸውን፣ ማራቅ ያለብህንም በጊዜ አቁም፤ በጊዜ ተዋቸው፤ መንፈስህን አድስ፤ ውስጥህን አሳርፍ።

72. “የእምነትህ ሃይል ያከራሃል!”

በሰወኛው ሂደት የማታጣው ስህተት፣ የማይለይህ ብርታት አለ። የትኩረትህ ምርጫና የእምነትህ ጉዳይም አንደኛውን ያጎላዋል፤ የየእለት ተግባርህ ያደርገዋል። **አዎ!** በብርታህ ስታምን፣ ትኩረትህን ስትጥልበት፣ በእርምጃዎችህ ስትደሰት፣ በእራስህ ስትተማመን፣ የሚያከራህን ውጤት በእራስህ ስታስመዘግብ፣ የማትለይህን ቃል ትጠቀማለህ። እንደዚህም ትላለህ፦ "እነርሱ ባሉኝ መንገድ ባለመሔዴ ለእራሴ ትልቅ ክብር አለኝ፤ በእራሴ ስለተማመንኩ፣ በመረጥኩት ተጉዤያለው፤ የፈለኩትን አድርጌያለሁ፤ ይሀው ዛሬ እዚህ ደርሼያለሁ።"

የልብ የልብ የሰጠህ በእራስህ መንገድ ያመጣሀው ውጤት ነው። የምትጠብቀው ነገር ቢቀርም አንተ መጓዝህን ከቀጠልክ ያለ ድጋፍ ያሰብክበት ትደርሳለህ፤ ወቃሾችህም ይርቁሃል፣ ነቀፋም ይሸሽሃል። በመቆምህ የምትተቸው ሳይሆን፣ በመሔድህ፣ በመጓዝህ የምታመሰግነው አንድ አካል ይኖርሃል። እርሱም ብርቱውን አንተ ነህ። ማቆም ያለብህ፣ ነገር ግን ማቆም ያልቻልከው፤ መተው ያለብህ፣ ነገር ግን ያልተውከው አስከፊ ተግባር ይኖርሃል፤ እርሱን አቁመህ የሚሰማህን ስሜት ማጣጣም በጀመርክ ቅፅበት ግን በእርግጥም ያለጥርጥር ታቆመዋለህ፤ ከእርሱም ታርፋለህ፣ ከህመምህ ትነፃለህ፣ በእራስህ

ትኮራለህ። የእምነትህ ሃይል ሲገለጥልህ ታየዋለህ፤ ከልብህ የተመኘህው፣ የጣርክበት ነገር ይከሰትልሃል። አንተ ስትቀርበው እርሱ ወዳንተ ይመጣል።

አዎ! ጀግናዬ..! የእምነትህ ሃይል ያኮራሃል፤ የፍላጎትህ ጥግ ቀና ያደርግሃል፤ የጥረትህ ብዛት ከጫፍ ያደርስሃል፤ በሰው ፊት ያቆምሃል፤ የተመኘህውን በእጅህ ይሰጥሃል፤ ትልቁን ህልምህን በምታስበው ልክ ወዳንተ ያቀርበዋል። **አዎ!** ፊትህን እያየህ፣ ዙሪያህን እያማተርክ ጉዞህን በማስተዋል ቀጥል፤ በእምት ደግፈው፤ መዳረሻህን አቅርበው፤ ትኩረትህን ሰብስብ፤ ያጣህውን ተውው፤ ያለህ ላይ ስራ፤ አጥጋቢ፣ የተለየ፣ አኩሪ ውጤትም አግኝ።

73. “የአንድ ቀን ዋጋዋ ስንት ነው?”

በ24 ሰዓታት የተሞላች፣ እንደ አምላክ ፍቃድ ስትደጋገም የምናያት፣ ስያሜዋ ልዩ፣ አመጣጧም የተለየው የአንዷ ቀን ዋጋዋ ስንት ነው? ትናንት፣ ዛሬ፣ ነገ ባለፉት፣ በአሉትና በሚመጡት ቀናት ክፍፍሎች የተፈጠሩ ናቸው። ትናንት ተጠቀምንበት፣ አመለጠን አንዴ ታሪክ ሆኖ አልቋል፤ ቦታውን ለዛሬ ሰቷል፤ ዛሬንም እንዲሁ በእኛው ስልጣን ፍሬያማ ወይም አክሳሪ እንድትሆን አናደርጋታለን፤ ትልቁን ጫናም ከነገችን ላይ እናወርዳለን ወይም እንጨምርበታለን። **አዎ!** ጀግናዬ..! ስራህ በአንድ ቀን ሲበደል ምን እንደምታጣ ታውቃለህ፤ አንድ ቀን ግዴታህን ሳትወጣ ስትቀር ምን እንደሚገጥምህ ታውቃለህ፤ የቀን ጎዶሎ የለም፤ በአምለክ እጅ የተበጀ ሁሉ ሙሉ፣ ሁሉ ፀዱ እንከን አልባ ተደርጎ ተፈጥሯል። የእኛ ለእንከን ፈላጊነት የቀረበ አባዜ ከሰው ግኚቶች አልፎ ከፍፁሙ የአምላክ ስራም ህፀፅ ማውጣት ይዳዳናል።

አዎ! ጀግናዬ..! ፈለክም አልፈለክም በየትኛውም ሂደት ህፀፅን የምትፈጥር፣ የምታጎላ ለእራስህ መሰናክል የምትሆነው አንተው ነህ። "ይሄ ነገር ቢመቻችልኝ እኔም እንደዚ አደርጋለሁ" በሚል መርህ ህይወትህን ትመራለህ፣ ካልተመቻቸስ? መልሱ ያንተ ነው። አስታውስ፡- ማንም ሰው የተመቻቸ ሁኔታ ቢያገኝ ካንተ ባልተናነሰ ሁኔታ ስራውን መስራት ይችላል፤ ዋናው ጉዳይ በተመቻቸ ከባቢ መስራት ሳይሆን ያልተመቸውን ከባቢ እንዲመች ማድረግ ነው። **“That's the weight full”** ዛሬ ስትባክን የስኬት መዳረሻህ ቀን ከነገ ያልፋል ከነገም ቀጥሎ ወዳሉት ቀናት ይሻገራል፤ ህልምህን አንድ ቀን ወይም ከዛም በላይ ትገፉዋለህ፣ ፀፀትን ወደራስህ ትመራዋለህ፣ ወቀሳን ታስከትላለህ፣ ሃላፊነቱ ባንተ ላይ ይወድቃል፤ ዛሬ የገፋሀው፣ ያባከንከው ቀን ነገ ያለ እረፍት ያሰራሃል።

አዎ! ዛሬ፣ አንዷ፣ ለሰነፎች፣ ለብኩኖች እንደ መጫኛ የረዘመች፣ ለብርቱዎች፣ ለትጉዎች፣ ለቆራጦች፣ ለአድራጊዎች ግን በስስት የምትታይ አንድ የተለየ ነገር ታመጣ ዘንድ በጉጉት የምትጠበቅ ውድ ቀን ነች። ዋጋዋ የገባው ይሳሳላታል፣ ይተጋባታል፣ ይወጣባታል፣ ይወርድባታል፣ ይተጋባታል። እርሱ ዋጋዋ ያልገባው፣ ያልተገለጠለት ሲያባክናት፣ ሲባክንባት፣ ርዝመቷን ሲለካ፣ ሰዓቷን ሲያማትር ይውላል። **አዎ!** ጀግናዬ..! የአንዷን ቀን ዋጋ ተረዳ፤ ውድነቷ ይግባህ፤ ያሰብከውን ዛሬ ጀምር፤ ወደ መዳረሻህም ፈጥነህ ቅረብ።

74. “በንግዱ ዓለም፣ በጣም የተሳካላቸው ሰዎች የሚወዱትን የሚሰሩት ናቸው!”

/ከዋረን ቡፌት አንደበት/

በዚህ ውብ አባባል የስኬት ቁልፍ ሩቅ ሆኖ አይታይም። ፍላጎት የስኬት መሰረት ነው። ደስ እያለህ፣ እራስህን ሰተህ፣ ከስራም በላይ እየተዝናናህበት የምትሰራው ስራ፣ ተገደህና በሰዎች ግፊት ከምትሰራው ጋር ሲነፃፀር ልዩነቱ ሰፊ ነው። ምናልባት የምትወደውን ስትሰራ ብዙ መዝናናትና ማረፍ ላያስፈልግህ ይችላል፤ ምክንያቱም ስራህ ያዝናናሃል፤ እርሱን መስራትህም ውስጣዊ እረፍትን ይሰጥሃል። ይህም

አንደኛው የምትወደውን በመስራት የምታተርፈው ገፀበረከትና ስኬታማ የሚያደርግህ ምስጢር ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! የሆነን ሰው ስላዋጣው፣ የምታቀው ሰው ጀምር ስላለህ፣ ሌሎች ሲያተርፉበት ስላየህ ብቻ ፈጥነህ አንድ ስራ ለመጀመር አትጣደፍ። ስራ ካልከው ሁሉም ስራ ነው፤ ውጤት ካልከው ሁሉም ውጤታማ ነው፤ ትርፍ ከፈለክ ሁሉም ትርፋማ ነው። ነገር ግን ይህ ሁሉ እንዲመጣ በቅድሚያ አንተ ውስጥህ ያለውን፣ የምትወደውን፣ የሚያሳርፍህን፣ ሰላም የሚሰጥህን፣ ከስራነቱ በተጨማሪ የሚያዝናናህን ስራ መስራት ይኖርብሃል። የምትወደውን ስራ፤ ካልሆነም የምትሰራውን ውደድ ስኬትንም በደስታህ ውስጥ አግኘው።

75. “የማታውቀውን አንተ ተዋወቀው!”

ወስን! ቆራጥ ሁን! ከዚህ በፊት ሆነህ የማታውቀውን ሰው ትሆናለህ፤ አስበህ የማታውቀውን ታስባለህ፤ አድርገህ የማታውቀውን ነገር ታደርጋለህ፤ ተገኝተህ በማታውቅበት ቦታ ትገኛለህ፤ ደርሰህ የማታውቅበት ስፍራ ትደርሳለህ፤ አይተህ የማታውቀውን ታያለህ፤ ከዚህ በፊት ያላሳካህውን ታሳካለህ፤ ኖሮህ የማያውቀው ይኖርሃል፤ ያልጨበጥከውን ትጨብጣለህ፤ ያላገኘህውን ታገኛለህ፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! ይህን ሁሉ በውሳኔህ ውስጥ፣ በቆራጥነትህ መንገድ ታገኘዋለህ፣ ትጨብጠዋለህ።

አዎ! አንድ በቅጡ የማታውቀው ሰው ውስጥህ እንዳለ እመን፤ የሆነ ጊዜ በፍቃድህ እንደሚገለፅም አትጠራጠር። በአንዴ ላታየው ትችላለህ በሂደት ግን በግልፅ ተከስቶ ታገኘዋለህ። አንተ ብቻ አታሸማቀው፤ አንገቱን አታስደፋው፣ "አትችልም አርፈህ ተቀመጥ" አትበለው፤ በፍፁም መሰናክል አትሁነው። **አዎ!** ተቸግረህ፣ ተበድረህ፣ ለምነህም ቢሆን ያንን ልዩ ሰው አውጣው፤ እድሉንም ስጠው፤ ኩራትህ በእርሱ ውስጥ ነውና፤ ግርማ ሞገስህ በእርሱ ይገለጣልና፤ ስኬትን እርሱ ያጎናፅፍሃልና፤ ከከፍታው እርሱ ያደርስሃልና፤ **አዎ!** በቻልከው መጠን ነፃ አድርገው፤ በፍረሃት አታሸማቀው፤ በበታችነት አትበድለው፤ በጭንቀት እረፍት አትንሳው፤ በተጎጂነት ስሜት አታጎሳቁለው።

ካንተ በላይ የሚረዳው ኬትም እንደማይመጣ ታውቃለህ፣ ካንተ በተሻለም ሊያግዘው የሚችል እንደሌለ ይገባሃል፤ እናም አንተው አነቃቃው፤ አንተው አንቃው፤ አበርታው፤ ደግፈው፤ አግዘው እራሱን አንዲያሳይ፣ እንዲያበረታ አስችለው። በስተመጨረሻም ከድጋፍህ ኋላ፤ ከእገዛህ ጀርባ የሚመጣውን የማታውቀውን አንተ ተዋወቀው፤ ተደመምበት፣ ተደነቅበት፣ አስደንቅበት፤ የት ድረስ መሔድ እንደምትችል፣ ምን ማድረግ እንደምትችል አሳይበት፤ ለደገፉህ ኩራት፣ ለገፉህም ሃፍረት ሁንባቸው። ስትወስን ምን እንደምታመጣ፣ ቆራጥ ስትሆን የት እንደምትገኝ በመዳረሻህ ሁሉ በምታስቀምጠው አሻራ ማስደመምህን ቀጥል።

76. “ለዛሬህ ያለህ ነገር ይበቃሃል!”

ዛሬ ካለህበት ጀምር፤ ዛሬ ያለህን ተጠቀም፤ ዛሬ የምትችለውን አድርግ፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! የተለየና በጣም ትልቅ ነገር አይጠበቅብህም፤ ያንተ ድርሻ ዛሬን መጠቀም ነው፤ ነገንም እንዲሁ መጠቀም፤ መጪዎቹን ጊዜያትም በዘለቄታው መጠቀም፤ ውጤታማ ማድረግ፤ ከአትራፊዎቹ ተርታ መመደብ። **አዎ!** ገዝፎ የታየህ ሃሳብህ ስላገዘፈው ነው። ምንም የተለየና የተወሳሰበ ነገር የለም፤ ምድርን ቆፍረህ የምታወጣው፣ ሰማይን ቧጠህ የምታገኘው እልህ አስጨራሽ ነገር የለም። ህይወትን በእራስህ መንገድ አታወሳስበት፤ ቀለል አርገህ መኖርን ተለማመድ፤ እርሱንም ከዛሬ ጀምር። ዘለህ "ከባዱን ነገር ካላደረኩ" አተበል ከቀላሏ፣ ከትንሿ ጀምር፤ ቶሎ ለመለወጥ ሳይሆን መቼም ቢሆን ተጨባጭ ለውጥ ለማምጣት ስራ።

አዎ! ጀግናዬ..! የዛሬዋ ንጋት የዛሬ ተረኛ ነች። ድርሻዋ በዛሬ ተገድቧል፤ ትናንት አልነበረችም ነገም አትኖርም። አንተም ዛሬ፣ ትናንት ያልነበረህን ለነገም የማታሳድረውን አንድ አዲስ ነገር ጨምር። "በዚህ ቀን ይህን አደረኩ" የሚያስብልህም ይሁን።
ነገን አትጠብቅ፤ ዛሬም ትናንት ነገ ነበር እንግዲህ ሌላ ነገ አትጨምርበት። በጅማሬህ ሂደት ዛሬ ነገን፣ ነገም ሌላ ነገን እንዲወልድ አታድርገው። ሌላ ስትጠባበቅ ያለህንም እንዳታጣ ተጠንቀቅ።

አዎ! ዛሬ ያለህን ተጠቀም፤ አስታውስ ዛሬ ያለህ ነገር ምንም ነገር ለማድረግ በቂ ሆኖ ተሰቶሃል፤ ቢያስፈልግህ ይጨመርልህ ነበር ነገር ግን ዛሬ እንዲኖርህ የተፈለገው፣ አምላክ የፈቀደለህ ዛሬ በእጅህ ያለውን ነው። ምናልባት ነገ ቢጨመርልህ እንኳን በድጋሚ ሌላ ጭማሪ መፈለግህ አይቀርምና በዚህ ዛሬ ባለህ፣ ለዛሬ በተሰጠህ ጀምርበት። ካልሰራህበት ነገ ታጣዋለህ፤ ከሰራህበት ሌላ አዲስ ነገር ይዞልህ ይመጣል። የማትችለውን እስክትችልም ለዛሬ ከምትችለው ጀምር፤ የምትችለውን አድርግ። በቀላሉ ተራመድ ከባዱ ላይ ድረስ። **አዎ!** ለዛሬህ ያለህ ነገር ይበቃሃል! ዛሬ ለመጀመር የሚያስፈልግህ ሁሉ ተሟልቶልሃል፤ ሳይሰራ ትርፍ የሚጠብቅ ነጋዴ፣ ሳይዘራም ፍሬ የሚመኝ ገበሬ የለምና አንተም በቻልከው መጠን ሰርተህ፣ ለፍተህ ውጤቱን ጠብቅ፣ ፍሬውን ተመኝ፤ ያለህ ላይ ሌላ አስጨምር።

77. “እያንዳንዱ አዕምሮ በተለየ መንገድ ያይሃልና እራስህን ሁን!”

/ከሳንጌታ ራና አንደበት/

መሆን የምትችለው መሆን ያሰብከውን ነው። እሳቤህ ሰዎች እንዳሰቡህ መሆን ከሆነ በእርግጥም መሆን ትችላለህ። ነገር ግን ሁሉም ሰው አንተን የሚያይበት የተለየ መነፅር አለው። ለአንዱ መልካም፣ ለአንዱም ክፉ፣ ለአንዱ ሞኝ ለአንዱ ብልጥ ልትሆን ትችላለህ። የእውነት የሚያስቡትን መሆንህን ግን አንተ ታውቃለህ። አንተን የሚያስቡበት እሳቤ የሚሰጡህን ምላሽም መቀየሩ አይቀርም። ይህንን ማስቀረትና በእነተኛው ማኛነት እንዲቀበሉህ ማድረግ የምትችለው ሁሉም እራስህን ሆነህ መቅረብ ስትችል ብቻ ነው። በፍፁም የሰዎችን ፍረጃ ፍራቻ እራስህን አትጣ። **አዎ!** ጀግናዬ..! እራስህን ሁን! እንዲቀበሉህ አይደለም፤ እንዲወዱህም አይደለም፤ እንዲረዱህ አይደለም፣ እንዲያዝኑልህም አይደለም፤ ያንተ ብቻ የሆነ የተለየ ውብ ማንነት ስላለህ ብቻ እራስህን ሁን።

78. “አገልግሎትን አስቀድም!”

አዎ! የህይወት ግብ ይኖርሃል፤ ህልም አለህ ዛሬ በመኖር የምታሳካው ወደፊት በገሃድ እውን የምታደርገው፤ ዘወትር አንተ የምታየው፣ ነግ ለሌሎች ይምታሳየው ትልቅና ድንቅ ህልም አለህ። **አዎ!** ጀግናዬ..! የህልምህ እወንነት፣ የአላማህ መሳካት ከልብ ካሳሰበህ ከሁሉ በፊት አገልግሎትን አስቀድም /Prioritize service/ ፤ ሰው ማትረፍ ላይ አተኩር፣ የሰውን ፍላጎት ለመሙላት ታገል፤ ከልብህ ወርደህ ሌላውን አሳርፍ፤ ቀሪው ተከትሎት ይመጣል።

አዎ! ህልምህ ትልቅ የሚሆነው በሚያመጣልህ ትልቅ ገንዘብ፣ ትልቅ ዝና ወይም ትልቅ ንብረት ሳይሆን በምታተርፈው፣ በምትረዳው የሰው ብዛት፣ በምታገኘው ጥልቅ እርካታ፣ በሚሰጥህ ውስጣዊ ደስታና ሰላም ነው። ገንዘብ እንዴትም ይመጣል፣ ዝና በአልባሌ ነገር ይገኛል፣ ንብረት ከሰው ባነሰ የወረደ ተግባር ይመሰረታል፤ የሰው ፍቅር፣ ፅኑ ሰላምና የመንፈስ እርካታ ግን ለሰው ከመኖርና ሰውን ከማገልገል፣ ከማሳረፍ ውጪ እንዴትም ሊገኝ አይችልም። **አዎ!** ለአገልግሎት ለምታወጣው ወጪ ብዙ አትጨነቅ፣ ሰውን ለመርዳት፣ ፍላጎቱን ለማሟላት፣ ውስጡን ለማሳረፍ ለምትከፍለው ነገር ብዙ አታስብ፤ በትንሽ ነገር መቼም የማይተውህን ትልቅ ቤተሰብ እየገነባህ እንደሆነ ይሰማህ።

አዎ! ትልቁን ስፍራ ከፈለክ አገልግል፤ ከፍ ለማለት ዝቅ በል፤ እግር ስር ውደቅ፤ በቻልከው ለወገንህ ድረስ፤ ስምህን በበጎነት ትከል፤ አገልግሎትህን አስፋ፤ ሰውን በቅንነት ያዝ። መቼም ገንዘብን አታሳድ በአገልግሎትህ በኩል እርሱ እንዲያሳድድህ አድርግ። ሰውን ስታተርፍ፣ ወዳጅን ስታፈራ ገንዘቡ፣ ነብረቱ፣ ዝናው ሁሉ በእጥፍ እንደሚትረፈረፍልህ አትጠራጠር። **"Always prioritize service and get other extra next."** ከምታገኘው ገንዘብ በላይ የአንዱ ደንበኛህ ደስታና እርካታ ይበልጥ ያሳስብህ። ትንሽ ለሚመስሉ ነገር ግን ትልቁን ነገር የሚያጎናፅፉህን ነገሮች በፍፁም ችላ አትበላቸው። ከሁሉም በላይ በምትኖርለት ህልም ወገንህን፣ ህዝብህን፣ አምሳያህን እንዴት እንደምታገለግል ደጋግመህ አስብ።

አዎ! ጀግናዬ..! የሚያነሳህ የገንዘብ ጥማትህ ሳይሆን፣ የሰው ጥማትህ ነው፤ ከፍ የሚያደርግህ ፍቅረ ነዋይ ሳይሆን፣ የሰው ፍቅር ነው፤ የሚያቀናህ የዝና ረሃብህ ሳይሆን የወገንህ ህመም፣ ሰቆቃ እስከ አጥንትህ ሲገባ የሚሰማህ ጥልቅ ስሜት ነው። በእርግጥም ያሰብከውን ታገኛለህ፣ ያለምከውም ይሳካል፤ ነገር ግን ለገንዘብ ተገዝተህ ሳይሆን ገንዘብን በአገልግሎት ገዝተህ ህልምህን አሳካ፤ ያሰብከውን ሙላ፤ ለወገንህም ድረስለት፣ እርሱንም አሳርፍ።

79. "ምን እየጠበክ ነው?"

ምንም ይሁን ምን በጠባቂነት ልማድ የተጠመደ ሰው የሚፈልገውን ሊያውቅ አይችልም፣ መሔጃው አልተገለጠለትም፣ ማረፊያው ተሰውሮበታል፤ የቤቱን ቁልፍ ለሰው ሰጥቶ በሩን ለመክፈት እንደሚታገል አይነት ሰው ነው። መቼ ጥበቃው እንደሚያበቃ አያውቅም፤ በቀረበ መዓድ ፊት ቀርቦ አጉራሹን ጥበቃ ፆሙን ያድራል፤ በእራሱ መብላት እየቻለ ይራባል፤ በእራሱ መስራት እየቻለ ኪሳራውን ያወራርዳል፤ በእጁ የተነካ ነገር የሚያምር አይመስለውም፤ እራሱ ከሚያደርገው ሰዎች የሚሰሩት ይበልጥ አጥጋቢ ይመስለዋል፤ ቀልቡን ይስበዋል።

አዎ! ጀግናዬ..! ምን እየጠበክ ነው? ማንን ጠብቀህ፣ ማንን አገኘህ? ማንን አምነህ፣ ሃሳብህ ሞላልህ? በምንስ መንገድ የጠበከው ተሳካ? በሔድክበት ሁሉ ያንተ ስራ ተሰርቶ እንዲጠብቅህ ትመኛለህን? ያንተ ድርሻ በሌሎች እንዲከወንልህ ትጠብቃለህን? ሌሎች ባመጡት ስኬት ስምህን ከፊት ለማስፈር የምትሯሯጥ ነህን? ባንተ የማድረግ ህፀፅ ምክንያት ሁሉንም ነገር እንዲደረግልህ የመጠበቁ ስሜት እንዴት ነው? **አዎ!** ጀግናዬ..! አትድከም! የጠበከው አያሳርፍህም፤ ጥምህን አይቆርጥልህም፤ አንጀትህን አያርስልህም፤ ረሃብህን አያስታግስልህም፤ ጉጉትህን አይሞላልህም፤ የተመኘህውን አይሰጥህም፤ **አዎ!** የጠበከው ሳይሆን ሲቀር በአንዴ ቅስምህ አይሰበር፤ አንገትህን አትድፋ፤ የበታችነት አይጫንህ፤ በአልችልም ስሜት አትዋጥ። አንዱ ባይሳካ ሌሎች ገና የምታሳካቸው ብዙ ዘርፎች አሉህ።

አዎ! ጀግኒት..! አንቺ በሰራሽው ስራ እነማን እንዲደሰቱ ትጠብቂያለሽ? ባንቺ ደስታ እነማንስ ደስ እንዲሰኙ ትመኚያለሽ? ልፋትሽን አይተው እነማን እንዲያዝኑልሽ ትፈልጊያለሽ? ምንም ያክል ብትጠብቂ፣ ብትመኚ፣ ብትፈልጊ ከፈጣሪና ከእራስሽ ሌላ የፈለግሽውን የሚያሳካልሽ፣ የፈለግሽውን የሚሰጥሽ፣ የሚገባሽን የሚቸርሽ፣ ያለምሽበት የሚያደርስሽ ማንም የለምና በልፋትሽ ኩሪ፣ በትጋትሽ ቀጥዪ።

አዎ! ሳትሰለች፣ ሳትታክት ስራህን ስራ፤ የጠበከውን የምታገኘው፣ የፈለክበት የምትደርሰው፣ የተመኘህው የሚኖርህ ባንተ ጥረትና ልፋት ብቻ ነው። ያ የምትጠብቀው፣ ተስፋ ያደረከው፣ የምትጠባበቀው ሰው የልብህን አያውቅምና፣ ውስጥህንም አይረዳምና በጥበቃ አትድከም፤ አትታወክ፤ እራስህ ሰርተህ እረፍ፣ እራስህ ጥረህ ሰላም አግኝ።

80. “አዕምሮህን ጥበብ መግበው!”

የሚታየውን ማየት፣ መመልከት፣ የሚሰማውን መስማት፣ ማዳመጥ መቻል የአስተውሎት መጠንን ከፍ ያደርጋል፤ በቃትን ያሳድጋል፤ ችሎታን ያዳብራል፤ ፈጣሪነት እንዲንሰራራ ያደርጋል። **አዎ!** መስማት፣ ማዳመጥ፣ ማጤን፣ ማስተዋል፣ ማመዛዘን በስተመጨረሻም ማድረግ። ማየት፣ መመልከት፣ ማረጋገጥ፣ ማመን በስተመጨረሻም መከወን የሚባሉትን ለአድራጊነት የሚያበቁ መመዘኛ ደረጃዎች ማለፍ ተገቢ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! የምታጣው ከመሰለህ ታጣዋለህ፤ እንደምትሸነፍ ከተሰማህ ትሸነፋለህ፤ ውድቀትን ካሰብክ ትወድቃለህ፤ መቅረት ካስጨነቀህ በእርግጥም ትቀራለህ፤ በእያንዳንዱ የአስተሳሰብ ሂደት ውስጥ አዕምሮህ ደጋግመህ የምታስበውንና የምትነግረውን ነገር ያለ ቅድመ ሁኔታ፣ ያለ አመክንዮ አምኖ ይቀበልሃል። ከሰጠሀው ቦላ ለመፋቅና ለመቀየር ብትሞክርም ሁኔታዎችን ያከብድብሃል። እንደምትሸነፍ ነግረሀው አምኖ ከተቀበለ ቦሃላ ካላሸነፍክ ብለህ ብታስጨንቀው፣ የሚጎዳህን ጭንቀት ታተርፋለህ። ፍረሃት መግበሀው፣ ደፋር ካልሆንክ ብለህ ብትታገለው የበለጠ ፍረሃትን የመፍራቱን ስሜት ወደ ውስጥህ ታሰርፃለህ። ቀድሞውኑ መግቦትህን አስተካክል።

አዎ! ጀግናዬ..! አዕምሮህን ማስተዋልን አስተምረው፣ ጥበብን መግበው፤ የአድራጊነትን ጥበብ፣ የአሸናፊነትን ተሞክሮ፣ የማስተዋልን፣ የድፍረትን፣ የእምነትን ጥበብ መግበው፤ በጥቅሉ የመኖረን፣ ህይወትን የማጣጣምን ውድ ጥበብ አስተምረው።
አዎ! ያስተማርከውን፣ ያሳመንከውን፣ የመገብከውን በገሃድ እንድትኖረው ያደርግሃልና። ህይወትህ የአስተሳሰብህ ውጤት ነው። ያላሰብከውን አትኖርም፤ አታደርግም፤ አትፈፅምም፣ አታከናውንም። ካንተ ቁጥጥር ውጪ በሆነ ሁኔታ የሚመጡትን ክስተቶች እንኳን የምትቀበለውና ምላሽ የምችሰጠው በአስተሳሰብህ ልክ ነው።

አዎ! የአዕምሮህን ምግብ ለይ፣ ንጥረ ነገሩን አፅዳ፣ ህይወትህን በደስታ፣ በድል፣ በአድራጊነት፣ በከፍታ፣ በስኬት አጅባት። ውስጥህ ሲቀየር፣ አካባቢህ መቀየር ይጀምራል። ውሎህ ከቢፊቱ የተለየ ይሆናል፤ የምታገኘው ሰው ይቀየራል፤ ወሬዎችህ፣ ትኩረትህ፣ አሳቤህ በሙሉ ከመሰረቱ መቀየር ይጀምራል። ከውስጥ ወደ ውጭ የምታወጣው የለውጥ ሃይል ካንተ አልፎ ለብዙዎች ይተርፋል።

አዎ! ጀግናዬ..! ትናንት ያላየሀውን ለውጥ ታያለህ፤ የሚከቡህ እንዳንተ አይነት ሰዎች ይሆናሉ። ለለውጥ ያለህ ምልከታ በዚህ ደረጃ ክፍ ስላደረገህ፣ ጥረትህን ስለጨመረ፣ አቅምህን ስላወጣ መገረምህ አይቀርም። **አዎ!** ለውጥን ከውስጥ ስትጀምር በእርግጥም አንተነትህን በሙሉ ሲቀይር በእውን ታየዋለህ፤ በገሃድ በምታየው ነገር ማመን ትጀምራለህ። ለውጥን እንድትፈራ የሚደርግህ እሳቤ የህይወት ዘመን ጠላትህ ነው። በነገሮች ተገደህ ከምትቀየር እራስህ ፈልገህ ተለወጥ፤ እድሜ ከሚያስተምርህ እራስህ ተማር፤ ተገደህ ሳይሆን ፈልገህ ወደ ለውጥ ጎዳና ግባ።

81. “በእራስህ ተስፋ ይኑርህ!”

ንግግር ከእራስ ጋር ሲጀመር አንደተለመደው ቀላል ሊሆን አይችልም፤ ትዝብትን ማስከተሉም አይቀርም፤ ግና እራስን ሸሽቶ የትም አይደረስምና ከእራስ ማውራቱ፣ ከእራስ መምከሩ የማይቀርና እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! ለወደድከው ጥሩ ለመሆን እንደምትሞክረው፣ ምን ያክል ለእራስህ ጥሩ ለመሆን ትጥራለህ? በሰዎች ለመወደድ እንደምትለፋው በእራስህ ለመወደድ ምን አድርገሃል? ሰዎችን ላለመበደል እንደምትጠነቀቀው እራስህን ላለመጉዳት ምንያክል ትጠነቀቃለህ? የሰው ስሜት እንደሚያሳስብህ ያንተ ስሜት ምን ያክል ያሳስብሃል? ለሰው ደስታ ብዙ

እንደምታደርገው ለእራስህ ደስታና እርካታ ምን አድርገሃል?

አዎ! ጀግናዬ..! ለእራስ ትኩረት መስጠት ወዳጆቻችንን እንድንዘነጋ ሊያደርገን አይችልም። ብዙዎች ተስፋ ቢጥሉብህም አንተ ግን ከማንም በላይ በእራስህ ላይ ተስፋ ሊኖርህ ይገባል። እራስህን ዘንግተህ ለሰዎች መትረፍ አትችልም፤ እራስህን ጥለህ በሰዎች ፊት ክብር አታገኝም፤ እራስህን ችላ ብለህ የሰዎችን ትኩረት አትስብም፤ አንተ ተጨንቀህ ሰዎችን ማሳረፍ አትችልም፤ በእራስህ እያዘንክ ሌላውን ማስደሰት አይሆንልህም። **አዎ!** ጀግናዬ..! በእራስህ ተስፋ ይኑርህ።

ብዙዎች ተስፋ የሚያደርጉብህ፣ እንደምትችል ስለሚያውቁ ነው። ቤተሰቦችህ የሚተማመኑብህ፣ ካንተ አንድ ነገር ስለሚጠብቁ ነው። ወዳጆችህ የሚያበረቱህ፣ እንደምታከራቸው ስለገባቸው ነው። **አዎ!** እነርሱ በጥቂቱ ቢያውቁህም ባንተ ከመተማመን አልሰነፉም። እነርሱ በትንሹ ቢረዱህም ባንተ ተስፋ አልቆረጡም። አንተስ? በእራስህ ታምናለህን? በችሎታህ ትተማመናለህን? በጥረቱህ፣ በትጋትህ ውጤት ተስፋ አለህን? **አዎ!** ጀግኒት..! ለሰዎች ብቻ መጨነቅሽ ጥሩ ሰው አያስብልሽም፤ ለእራስሽም አሳቢ፣ መልካም ሴት ሁኚላት። ለሌሎች ደስታ ብቻ መልፋትሽ ደግና ሩህሩህ ሊያደርግሽ አይችልም፤ ደስታን ለእራስሽም ፍጠሪ። ፍቅርን ከሌላው ለመስጠት መትጋትሽ ብቻ ተወዳጅ ሊያደርግሽ አይችልም፤ ለእራስሽም ፍቅርን መስጠት ጀምሪ።

አዎ! አንዳንዴ ቤታችን ባዶ ሆኖ በሰው ለመወደድ ብቻ በሞላው ቤት አላስፈላጊና ትርፍ ነገር ለመጨመር እንታገላለን፤ ውስጣችን በድካም ዝሎ ለሌላው ማረፊያ ለመሆን እንጥራለን፤ ትኩረታችን ወደ ውጭ ይሆናል፤ በትርፍና አላስፈለጊ ጉዳዮች ይዋጣል፤ ጓዳችን ባዶ ሆኖ ሳለ የሌላውን በረንዳ ለማሞቅ እንሰየማለን።

አዎ! ጀግናዬ..! የሌላውን ስታሯሩጥ ያንተን እንዳትዘነጋ፤ ከሌላው ስትጠብቅ ለእራስህ ማድረግ የምትችለው እንዳያመልጥህ፤ **አዎ!** ልባችንን እናሳርፍ፣ ለእራሳችን እንድረስ፣ ክፍተታችንን እንሙላ፣ ማንነታችንን እንገንባ በቀጣይ የምናደርገውን ለሰዎች የመድረሱን ጉዳይ በልበ ሙሉነትና በእራስ መተማመን ስሜት ከውስጣችን እንከውነው።

82. “በቀናት ውስጥ መታደስህን ትቀጥላለህ!”

ዛሬ የተሻለ ቀን ነው፤ ዛሬ ውብ፣ አስደሳች፣ ማራኪ ቀን ነው፤ ዛሬ ብሩክ፣ ስኬታማ ቀን ነው። ለዚህም መስጠት የማይሰለቸው፣ እለት እለት ጠብቆቱ ያልተለየን ቸር አምላክ ይመስገን። **አዎ!** ዛሬ አስገራሚ ቀን ነው፤ ደስ ይላል፤ የትናንትናው ድካም የለም በተፈጥሯዊ እረፍት፣ ሰዓቱን ጠብቆ በሚመጣ የዝለታችን ማሳረፊያ ጊዜ ተፈወሷል፤ የዛሬዋን ውብ ቀንም ለማየት በቅቷል።

አዎ! ጀግናዬ..! በአንተ ምርጫ ሳይሆን በተፈጥሮ መልካም ፍቃደ ዛሬን ታድሰሃል፣ ነቅተሃል፣ ፈክተሃል፤ መልከመልካም ሆነሃል፤ ቀንህን በድምቀት ታሳልፋለህ፣ እንደ ጠዋቷ ፀሃይ የፈካ ቀን ይኖርሃል። **አዎ!** በቀናት ውስጥ መታደስህን ትቀጥላለህ፤ አዲሱን አንተ ትፈጥራለህ፤ የተሻለውን፣ ተስፈኛውን፣ ታታሪውን፣ እሩቅ አላሚውን አንተ ታስባለህ፤ ለዛሬ መብቃትህ የነገ ዋስትና አይደለምና ዛሬን በምትፈልገው ልክ ኑራት፣ ለነገህ ጥሪትን አስቀምጥ፣ የሆነ ነገር ትከል ነገር ግን ጠዓሟን በሚገባ አጣጥም።

አዎ! ጀግኒት..! ዋናው ነገር ትናንትን ማለፍሽ አይደለም ዛሬን መየትሽ ነው። አንቺ እስካለሽ ድረስ ትናንት ማለፉ አይቀርም፣ የትንት ዋጋም ከዛሬ ጋር አይነፃፀርም፤ የመጪዎቹ ቀናት ተስፋ ዛሬ ነው። ሴትነትሽ እንደ ፅጌሬዳ አበባ ያስውብሻል፤ ንቃትሽ እንደ ንስር ብልህ ያደርግሻል፤ ጥንካሬሽ እንደ አንበሳ

አይበገሬ ያደርግሻል። አንድ ነገር አስታውሺ ዛሬሽን የሚያበላሽ ነገር ሲገጥምሽ "በእውነቱ እንደኔ ያለች ብርቱ፣ ጠንካራና ትልቅ ህልም ያላት ሴት ቀኗ በትንሽ ነገር እንዲበላሽ ትፈቅዳለችን?" በማለት ጠይቂ፤ በፍፁም አትፈቅድም፤ ፈቅዳም አታውቅም። ስለዚህ ምንም ቢገጥምሽ ጫና ውስጥ የሚከትሽ አይነት ከሆነ አይመጥንሽምና ከአጠገብሽ አርቂው፤ ዞር አድርጊው። ካጋጠመሽ ነገር እራስሽን ከፍ አድርገሽ ተመልከቺ።

አዎ! ጀግናዬ..! አንተ ጠንካራ ሰው ነህ፤ በቀን ውሎህ የሚያስጨንቅህ ነገር ሊመጣብህ ይችላል፣ እናም እራስህን ጠይቅ፤ "እንደኔ ያለ ብርቱ፣ ጠንካራና ባለ ትልቅ ህልም ባለቤት የሆነ ሰው በእንደዚህ አይነት ትንሽ ነገር ይጨነቃልን?" በፍፁም፤ አድርጎት አያውቅም፤ ዛሬም አያደርገውም፤ ስለዚህ እርሱን ረስተህ ትኩረትህን ብርቱና ጠንካሮች ወደሚያደርጉት ስራህ፣ ህሕምህና ራዕይህ ላይ ታደርጋለህ። በእየቀኑ የሚገጥሙህ ስንክሳሮች "በእርግጥም ለእኔ ይመጥናሉ?" ብለህ ጠይቅ። ያንተ ግዝፈት ችግሮችህን፣ ፈተናዎችህን ያሳንሳቸዋል። የማይመጥንህ ነገር አብሮህ እንዲቆይ አትፍቀድ። ዛሬን ከኖርክ ነገህ በእርገጥም የተሻለ፣ ውብና ያማረ እንደሚሆን አትጠራጠር።

83. “የተወለድከው፣ የተፈጠርከው ለማሸነፍ ነው። ነገር ግን አሸናፊ ለመሆን ለማሸነፍ ማቀድ፣ መዘጋጀትና አሸናፊነትን መጠበቅ ይኖርብሃል!”

/ከዚግ ዚግለር አንደበት/

አሸናፊ የምትሆነው የአሸናፊነት ስነ-ልቦና ስታዳብር ነው። ምናልባት የትግሎችህ ብዛት ሊያደክምህ ይችላል ነገር ግን ለማሸነፍ ካቀድክ፣ ከተዘጋጀህና ማሸነፍህን ካመንክ ድሉ ያንተ ነው። ትንሽ ማሰብ ሲደጋገም ያደክማል፣ ሰውነትን ያዝላል። የተደራጀ፣ የተቀናጀ የአሸናፊነት እቅድ ግን ለድል ያበቃልሀ፤ ከጫፍ ያደርሰል።

አዎ! ጀግናዬ..! አሸናፊነትን ምንያክል ትፈልጋለህ? እርሱን ለመቀበልስ ምንያክል ዝግጁ ነህ? የምታሸንፈው በፍላጎትህ መጠን ነው፤
የምትቀበለው ዝግጁ ስትሆን ነው።ጥልቅ ፍላጎትህ፣ የአሸናፊነት ጉጉትህ ሁሌም አሸናፊ ሆነህ እንድትኖር ያደርግሃል፤ እራስህን በአሸናፊዎች ደረጃ እንድታይ ያደርግሃል፤ ትግሉን ስትጀምር ሳታሸንፍ እንደማታቆም ታውቃለህ፤ የጉዞህ ፊፃሜ ድል አድራጊነት ነው፤ መዳረሻህ አሸናፊነት ነው።

84. “በከፍታህ ልዩነትን ፍጠር!”

የሚያወራ ሁሌም አለ፤ አለማችንም የወረኞችና የቃላባዮች እጥረት ገጥሟት አያውቅም፤ የጠፋው የሚያወራውን የሚኖር ሰው ነው። የሚፎክርማ ሞልቷል፤ የጠፋው የፎከረውን የሚያደርግ ነው። ማውራት ቀላል ነው፤ መፎከሩን፣ ማወጁን፤ እወቁልኝ ማብዛትን ማንም ያደርገዋል። "ይህን ላደርግ ነው፤ ያንን ላደርግ ነው" ማለት፣ ቀጠሮ ማብዛት ማንንም አይከብድም፤ የቀላል ቀላል ነው። ከባዱ ነገር መጀመር፣ የከባድ ከባዱም የጀመሩትን መጨረስ ነው።

አዎ! ትልቁን ክፍተት የፈጠሩት ጨራሾች ናቸው። የሰው ልጅ ከባዶ ተነስቶ የአለም ቁንጮ ሲሆን ማየት ያስገርማል። ግማሹ የማንም የትም መድረስ፣ የእራሱም ካለበት መቅረት ግድ አይሰጠውም፤ ምኑም አይደለም። ከባዱን ሲፈራ ቀላሉን ሲደጋግም፣ በመንጋው ተውጦ፣ በመንጋው ሲመላለስ፣ ሲዳክር፣ የዘወትር ወቃሹን ሀሊናውን ሲሸሽ፣ ብሩሁን አዕመሮ አገልግሎት አልባ ሲያደርገው ይታያል፤ በዚህም መሃል ልዩነቱ ይሰፋል። ታታሪዎች ሌትተቀን ይለፋሉ፣ አፈትረልከውም ይጠፋሉ፣ ርቀው ይሔዳሉ፤ ሰነፉም ስንፍናውን እያስታመመ ለልዩነቱ ስፋት የእራሱን አስተዋፅዖ ይወጣል።

አዎ! ጀግናዬ..! በከፍታህ ልዩነትን ፍጠር! ከመንጋው ተለይተህ በእራስህ ተራመድ፤ አስተሳሰብህን፣ ምልከታህን፣ ተግባርህን ለይ፤ ሳትናገር ጀምር፤ ሳትፎክር አድርግ፤ ሳታውጅ ፈፅም፤ በአንደበትህ አትሸወድ፤ ማውራትህ አያስንፍህ፤ በምላስህ አትደለል፣ አትጀነን።
አዎ! ወሬ አንድ ሰሞን ነው፤ ተግባር ግን የሁለ ጊዜ ስራ ነው። ፉከራ ወቅታዊ ነው፤ ትግል ግን ቀጣይነት አለው። እስከ ዛሬው ሂደት ተግባርን የተካ ወሬም ሆነ ፉከራ የለም። በማውራቱና የሚሰራውን በመተንተኑ የተቀየረ የለም፤ ዋናው ጉዳይ፣ ሆኖ መገኘትና የተነተኑትን አድርጎ መገኘት ነው። አዎ! ጀግናዬ..! ከቻልክ ሳታወራ አድርግ፤ አድርገህም እንደ ፈለክ አውራ፤ ካወራህ ግን ቃልህን ኑር፣ ለእርሱ ታመን፤ በተግባር አሳየው።

85. “ለህልምህ ተገዛ!”

ታማኙ ባሪያ የህልሙ አርበኛ፤ ላይ ታች የሚላ ለህልሙ የማይተኛ፤ በጥቂቱ ታምኖ ብዙ የሚያተርፍ፤ ትርፉ በእጁ የሚያብብ፤ ዛሬን በነፃነት ይጠቀማል። የህልሙ፣ የፍላጉቱ፣ የራዕይው ተጠሪነት ለእራሱ ነው። ግዴታውንም በሚገባ ይወጣል፤ ለራዕይው ይቆማል፤ ህልሙን ይንከባከባል፤ የልቡን ከልቡ ይፈፅማል። **አዎ!** የአሉታዊ ልማድ ባርነት ሰውን እንደሚጥልና ገደል እንደሚከተው ሁሉ፣ የአውንታዊና የጠቃሚ እሳቤና ልማድ ተገዢና ባሪያ መሆን የበታችነትን ቀንበር አሽቀንጥሮ ይጥላል፤ የስኬትን ፅዋም ያስጎነጫል።

አዎ! ጀግናዬ..! ለህልምህ ተገዛ፤ ለእርሱ ታመን፤ እንደ ባሪያ አገልግለው፤ ህይወትህን ሰዋለት። የነገሮች ክብደት የሚጀምረው ያልወደዱትን በሌላው ተፅዕኖ መስራት ሲጀምሩ ነው። በዚህ መሃል ነፃነትን ቢፈልጓትም አያገኙዋትም። ሰጪውም ነሺውም ሌላ ሰው ነው። ባለቤቱ፣ ተጠቃሚው ሌላ አዛዡም ሌላ ነው። **አዎ!** አንዴ በምናብህ የእራስህን አለም ፍጠር፣ ባንተ ግዛት የሚመላለሱ እጅግ ብዙ ፍጥረታትን ተመልከት፣ የትም ሲሔዱ፣ ምንም ሲያደርጉ፣ ምንም ሲበሉ አንተ ማወቅ አለብህ፣ ከማድረጋቸው በፊት ሃሳባቸውን ላንተ ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፤ ህይወታቸው በሙሉ ባንተ ፍላጎት ታጥሯል። ያንን አጥር የጣሰ ለሞቱ እንቀረበ አሳስበሃል። ስለዚህ ግዛትህ ያንተ ብቻ ነው፤ የሚኖሩበት ፍጥረታት እንደ ባሪያ ባንተ ትዕዛዝ ብቻ እንዲገዙ አድርገሃል ማለት ነው፤ የእነዛን መስኪን ታዛዦች ሰቆቃ ብትረዳ ምን ያክል አስከፊ እስር ውስጥ አንዳሉ ይገባሃል።

አዎ! ነፃነት የህይወት ጠዓም ነው። ድንቁ አምላክ፣ ጥበብ የማያልቅበቱ፣ የጥበቡ ባለቤት ወደ ምድር ካመጣን ጀምሮ ነፃነትን አድሎናል፤ ሌላው ይቅርና በእርሱ ለማመንና ላለማመን ነፃ ፍቃድና ነፃነት ሰቶናል። ለወደድነው እንድንገዛ፣ የወደድነውን እንድናነግስ። የምድር ነገስታት አቅማቸውን በገደብና ነፃነት በመንሳት ያሳያሉ ቸሩ አምላክ ግን የማይገደብ ነፃነት፣ በሚፈስ ጥልቅ ፍላጎት የአቅሙን ጥግ ያሳያል። አዎ! ጀግናዬ..! ነፃነትህን ተጠቀም፤ ህልምህን ኑርበት፤ ገደቦችህን አርቃቸው፤ ከእነርሱ ሽሽ፤ ለመልካም ልማዶችህ ተገዛ፤ ለህልምህ ታዘዝ፤ አምላክ ለፈጠረህ አላማ ታመን፤ በእርሱ መንገድ ተመላለስ፤ በህይወትህ አንድ አሻራ አሳርፍ፤ ለፍጥረቱና ልጆቹ ረዳት፣ ደጋፊያቸው ሁን።

86. “አንተ የእጣ ፈንታህ ጌታ ነህ። በአካባቢህ ላይ የእራስህን ተጽእኖ ማሳደር፣ እርሱንም መምራትና መቆጣጠር ትችላለህ። ሕይወትህ የምትፈልገውን አይነት እንዲሆን ማድረግ ትችላለህ!”

/ከአስብና ሃብታም ሁን ገፆች/

የችሎታህ ከፍታ፣ የመቻልህ ጥልቅ እሳቤ፣ እንዲኖርህ የምትፈልገውን ነገር እጅህ ያስገባዋል። በአንተነትህ፣ በልዩነትህ አንተ ብቻ የምትችለው፣ የተሰጠህለት ተግባር ይኖራል፤ መቻልህን ተቀብለህ ችለህ ካልተገኘህ ግን አንዳች ዋጋ አይኖረውም። የአቅምህ ሃይል አካባቢህን እሰከ መቆጣጠር ካደረሰህ፣

በእርግጥም ተዓምራትን ማድረግ ይቻልሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! ትችላለህን ተቀበል! **አዎ!** መቀበሉንም ትችላለህ፣ መኖሩን፣ መተግበሩንም ትችላለህ። የገዛ ሃሳብህ ካልሆነ በቀር ሌላ ከልካይ የለህም፤ የእራስህ ስሜት ካልሆነ፣ ከፊትህ የሚቆም አይኖርም፤ የወረዱ፣ ያረጁ፣ ያፈጁና የወደቁ፣ የአትችልም ሃሳቦችን አስወግድና የምትፈልገውን ህይወት በይቻላል መንፈስ መገንባት ጀምር። ማቆም እንደሚቻል ብዙዎች አሳይተውሃል፤ መውደቅ እንደሚቻልም ብዙ ጊዜ አይተሃል፤ አንተ ግን ጥቂቶች ባሳዩህ የመነሳትና የመቀጠለ፣ የይቻላል መንፈስ፣ መዳረሻህን አሳምር፤ ውብ ህይወትን ፍጠር።

87. “እምነትህ አይስ፣ ምስጋና አይለይህ!”

የምታጣው ከሌለህ የምታገኘው ላይ አተኩር፤ የሚቀርብህ ከሌለ የሚጨመርልህን ተመልከት፤ ሳትጠቀም ከምታጣው ተጠቅመህ የሚቀርብህ ይሻላል፤ **አዎ!** የማያልቅ የሚመስል ንብረት ይኖርህ ይሆናል፣ የማይሸረፍ ባለበት የሚቀጥል ጊዜ ያለህ ይመስልህ ይሆናል፣ አብረውህ ያሉ ሰዎች እስከ መጨረሻው አብረውህ የሚቆዩ ሊመስልህ ይችላል፤ ጤናና ጥንካሬህም ባለበት የሚቀጥል ሊመስልህ ይችላል ነገር ግን እንዳሉህ ማመንህ አንድ ነገር ሆኖ ኋላ ስታጣቸው እንዳይቆጭህ ዛሬ ላይ ሆነህ አመስግንባቸው፣ ተጠቀምባቸው፣ ያንተ መሆናቸውን አሳይ፣ በእነርሱ በኩል ብዙ እንዳገኘህ መስክር።

አዎ! ከሌሉ የሉም! ዛሬ የተጨመረልህ ውብና ሙሉ ቀን ሁሌም ላይኖር ይችላል፣ የምታጣበት ጊዜ መኖሩ ግድ ነው። ዛሬን ባየህ ቁጥር የሚቀሩህ ነገዎች እያነሱ ይሔዳሉ፣ ያንተም አቅም ይቀንሳል፣ ተፈጥሮ ስራዋን ትሰራለች፣ ለምንም ነገር እንደዛ ያባከንከውን ጊዜ ስትፈልግ ታጣዋለህ፣ አመስግነህለት የማታውቀው ውዱ ጤናህ ሌት ከቀን አምላክህን እንድትማፀን ሊያደርግህ ይችላል።
አዎ! ጀግናዬ..! ሁሉም ሲኖር ያምራል፤ ምስጋናውም ከልብ ሲሆን ደስ ይላል፤ ልመናው ከአንጀት ሲሆን ምላሽ ያገኛል፤ ዛሬ የተቸገርክ ሊመስልህ ይችላል፣ ዛሬ አስከፊ ቀን ሊመስልህ ይችላል፣ ዛሬ ሰቆቃ እንደበዛ፣ ረሃብ እንደበረታ፣ ምድር እንደተጎዳች ሊሰማህ ይችላል፣ ነገር ግን በዚህ እንዲበቃ አምላክን ካልተማፀንክ፣ ባለው ነገር ካላመሰገንክ ከዚህም የከፋ ጊዜ ሊመጣ እንደሚችል አስታውስ።

አዎ! ፈጣሪ መቼም ፍጥረቱን ጥሎ አያውቅም፤ ለከፋው አውሬም አሳልፎ አይሰጥም ነገር ግን በግማሽ ልብ እያማረርክ በሌላው የአምላክህን ማዳን ብትጠባበቅ አውሬዎች መሃል እራስህን ታገኘዋለህ። ያኔ ትልቁ እምነትህ ይፈተናል እንደሚያድንህ ካላመንክ የአውሬዎች መዓድ ትሆናለህ፣ ቀረጣጥፈው ከመንገድ ያስቀሩሃል፣ ክብርህን ሳታይ ከአለም ይለዩሃል። በድንቅ አድራጊው አምላክ ካመንክ፣ ስላለህበትም ምስጋና ካልተለየህ ግን ከአውሬው መንጋጋ ፈልቅቆ ያወጣሃል፣ ጉዳትህን፣ ስብራትህን ሽሮ ከሰው ፊት ያቆምሃል፣ ባለህ ስለተደሰትክ ሌላ ይጨምርልሃል፣ በእርሱም ስላመንክ የእምነትህን ፍሬ ይመግብሃል።

አዎ! የሚያሳጣህ ነገር ከሌለ ስላለህ ከልብህ አመስግን፤ የሚቀንስብህ ከሌለ በተደረገልህ ዘሬን የማየት፣ በህይወት የመኖር ተዓምር ደስ ይበልህ፤ ብታጣ እንኳን ማጣትህን በበጎ ቁጠረው፤ ቢጎድልብህ እንኳን መጉደሉን በመልካም ተመልከተው። ዋናው ነገር ትናንት ኖሮህ ዛሬ ማጣትህ ሳይሆን፣ ዛሬን ብታጣ ነገም ማግኘት መቻልህ ነው። እምነት ነገሮችን ይቀይራል፣ መንገዱን ያሳምራል፤ ምስጋናም ያለውን ይባርከል ሌላም ይጨምራልና ሁሌም እምነትህ አይነስ፣ ምስጋና አይለይህ። ሰዎች እንደ ጎዳሃቸው በነገሩህ ጊዜ በፍፁም እንዳላደረከው አትወስን፤ እንደዛም አይሰማህ።

አስበህ ላትጎዳቸው ትችላለህ፤ አስበህበት ላታሳምማቸው ትችላለህ፤ ነገር ግን በእነርሱ ውስጥ ጉዳትን ፈጥረሃል አንተም ብትሆን ጎጂ ሆነህ ተስለሃል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ላንተ በጎ ተግባር የሆነው ለሌላው ክፉ

ሊሆን ይችላል፤ አንተ በቀናነት ያደረከው ሁሌም ቀና መልስ ላያገኝ ይችላል፤ ጥሩ ነው ብለህ ያደረከውም በእርግጥም ጥሩ ላይሆን ይችላልና እንዳጠፋህ ሲነገርህ ለክርክር አትፋጠን ይልቅ በእሺታ ተቀበል በቀጣይ ለማረም ተዘጋጅ። ማንም ሰው ጎደተህኛል ሲልህም በእርግጠኝነት እንዳላደረከው አይሰማህ ሳያውቁ መጉዳትም አለና ይልቅ እርማትን ውሰድ፤ ማፅናናቱን አስቀድም፤ በይቅርታ ሻረው።

88. “ለማነው የምትታገለው?”

ትናንት ከሰው ጋር ኖረሃል፣ ዛሬም እየኖርክ ነው፣ ነገም እንዲሁ ትኖራለህ። በዚህም ሂደት ላንተ ካላቸው ስሜት አንፃር ለእያንዳንዱ ሰው የምትሰጠው ስፍራ ይለያያል። አንዳንዴ ከሁሉም በተለየ የምትፈልገው፣ የምትቀርበው፣ የእራስህ ለማድረግ የምትታገለለት፣ መሱዓትነት ለመክፈል የተዘጋጀህለት ሰው ይኖራል። ትግልህ ከልባዊ ፍላጎትና ፍቅር የመነጨ ነው። ነገር ግን በዚህ የአብሮነት ሂደት የቀረብካቸው ሰዎች አንተን በማጣታቸው ምንም ካልተሰማቸው፣ ያንተ አለመኖር ለእነርሱ ለውጥ ከሌለው፣ እነርሱን ለማግኘት መታገል ላይኖርብህ ይችላል። ምክንያቱም በፊትም አብረውህ የነበሩት፣ በእነርሱ ፍላጎት ሳይሆን ባንተ የበዛ ፍላጎትና ትግል ነውና። ማንም ላንተ ስሜት ያለው ሰው አንተን ባጣህ፣ በተለየህ ጊዜ ሰላም ሊሰማው አይችልም፤ ከተሰማውም ላንተ ስሜት አልነበረውም ወይም አንተ ለእርሱ ምንም ቦታ አልነበረህም ማለት ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! ለማነው የምትታገለው? **“Who do you fight for?”** ለማንነው ዋጋ የምትከፍለው? ለማንነው ወዳጆችህን የምትሰዋው? ለማንነው ከቤተሰብህ የምትቆራረጠው? በእርግጥ ላንተ ግድ ላለው፣ ላንተ ለሚጨነቅ ሰው ነውን? በእውነቱ ባንተው ልክ ለሚያስብልህ፣ ለሚሳሳልህ ሰው ነውን? **አዎ!** ጀግኒት..! ስቃይሽ ለማነው? ህመምሽ ለማነው? በእውነቱ ለሚታመምልሽ ሰው ነውን? እራሱን ለሰጠሽ ሰው ነውን? ላንቺ ሲል ለመሱዓት ለተዘጋጀ ሰው ነውን?

አዎ! አስተውዪ! ውጤት የሌለው ትግል አትታገይ፤ ፍሬ የሌለው መሱዓትነት አትክፈይ፤ ትርጉም የሌለው ጭንቀት አትጨነቂ፤ ስሜት አልባ ህመም አትታመሚ፤ **አዎ!** ጀግናዬ..! የሚፈልግህ ሰው የሚበልጠውን ወይም እኩሌታውን መንገድ ባይመጣ እንኳን ቢያንስ ሩቡን መንገድ መጥቶ ይቀበልሃል፤ ባለበት ቆሞ ያንተን መምጣት አይጠባበቅም፤ ትንሽም ቢሆን መንቀሳቀሱ፣ ፍላጎትም ሆነ ምልክት ማሳየቱ አይቀርም። ስትጠጋው የሚሸሽ፣ ስታቀርበው የሚርቅ፣ ስትወደው የሚያገል፣ የሚጠየፍ ሰው እንዴትም ላንተ ስሜት ሊኖረው አይችልም። ለዚህም የምትታገልበት ምክንያት የለህም።

አዎ! ከሰው ጋር መሆንህን እያወክ ብቻህን ቤት እንደማታቆም አስታውስ፤ ትግልህ ትንሽም ቢሆን ላንተ ስሜት ላለው ሰው መሆን እንዳለበት እወቅ። ለማይሆን፣ ቁብ ነገር ለሌለው፣ ለትርጉም አልባ ነገር የምትሰዋው፣ የምትከፍለው ስሜትም ሆነ ጊዜ እንደሌለህ በሚገባ ተረዳ፤ እያንዳንዱ ወጪዎችህ በቂ ምክንያት ያስፈልጋቸዋል፤ እያንዳንዱ ትግሎችህ ለሚባቸው መሆን ይኖርባቸዋል፤ ውጤት ለሌለው፣ ትርፍ አልባ፣ አድካሚ ነገር መልፋትህን አቁም፤ ውድን መሱዓት ውድነትህን ለሚያረጋግጥልህ አውለው።

89. “ሌላ አስደሳች ቀን!”

ደግሞ ሌላ አስደሳች፣ ግሩም ቀን፣ ተወዳጅ፣ ተሸላሚ፣ ተስፋን ፈንጣቂ ውብ ቀን፣ ዛሬ፤ ለዛሬ ቸር አምላክ ይመስገን! ቀናችንን በፍካት እንጀምራለን፤ በደስታ እንቀበላለን፤ እኛን መርጣ መጥታችና፤ አዲስ ሌላ ነገር ልትጨምርልን፣ አዲስ እስትንፋስ ልታስጎነጨን ተከስታለችና። **አዎ!** ጀግናዬ..! ሌላ አስደሳች፣ በተስፋ የተሞላች፣ የአበበች፣ የፈካች ቀን። ተመስገን!

ምን ልዩ ያደርጋታል? ምንስ የተሻለች ያደርጋታል? ቀድሞ ታይታ አታውቅም፤ ድጋሜም አትከሰትም፤ ዛሬ ዛሬ ብቻ ነች፤ ለእርሷ የሚሰማን ስሜትም ተሰምቶን አያውቅም ዛሬ ብቻ ተሰማን፣ ድጋሜም አይሰማንም። በዚህ ሒደት ስንት ቀናት አለፉ? እጅግ ብዙ፣ አያሌ ቀናት አለፉ፣ ትዝታቸውን ይዘው፣ ስሜታቸውን ሸሽገው።

አዎ! ዛሬ ታልፋለች፤ ባዶዋን፣ ያለ ትርፍ እንድታልፍ ግን አታድርጋት ከልብህ አጣጥማት፤ ወደ ውስጥህ አስገባት፤ ዛሬ እንደኖርክ፣ ዛሬ እንደተደሰትክ Feel አድርገው፤ ከልብህ ይሰማህ። ዛሬ የድንቆች ሁሉ ድንቅ ስጦታ ነች፤ ይህቺን ድንቅ ስጦታ ከድንቅ አመምላክ በቀር ሌላ ማንም ሊሰጠን አይችልም። እኛን መርጦ ሰጠን፤ ለዛሬ አበቃን። በመስጠቱ አይዘንብን፣ አይከፋብን፣ አይፀፀትብን በምትኩ በደስታችን ይደሰት፣ በስራችን ይኩራ፣ በስኬታችን ሌላ ብዙ አስደሳች ቀናት ያክልልን፣ ይጨምርልን።

አዎ! ዛሬን ከተደሰትክ፣ ዛሬን ካጣጣምክ ነገን ታያታለህ፣ በተስፋ ጠዓሚ ይሰማሃል። ዛሬን ካረከስክ፣ የአምላክህን ስጦታ ካሳነስክ ለነገህ ምንም ዋስትና የለህም። ስንተ በተሰጠው፣ በሚጨመርለት ሌላ አዲስ ቀን በምስጋና የሚሰክር ሰው እያለ ላንተ ለአማራሪው፣ ለነቃፊው፣ ለተቺው ማን ሌላ ቀን የሚጨምርልህ ይመስልሃል? ማንም! መቼም ዛሬን ሳትኖር፣ ዛሬን እያማረርክ ለነገ ተስፋ አይኖርህም፣ ምናልባትም ከፊትህ ያለው ነግ በይበልጥ የምታማርርበት፣ የምትበሳጭበት የተሻለ ምክንያት ይዞልህ ይመጣ ይሆናል። ያኔም ምሬትህን ትቀጥላለህን?

አዎ! ጀግናዬ..! ዛሬ፣ ከትናንትም ከነገም የተሻለች እንደሆነች አስበህ ተደሰት፣ ደስ ይበልህ። ሌላ ምክንያት አትፈልግ የዛሬን እስትንፋ ስለተነፈስክ፣ ንጋቷን ስላየህ፣ የጠራውን ሰማይ መመልከት ስለቻልክ፣ በጤና ስለ ነቃህ ብቻ ደስ ሊልህ ይገባል። በደስታህ ምክንያት ካንተ በላይ ስኬታማ ሰው ኬትም አይገኝም። አስደሳች ውብ ቀን ማሳለፍ ጀምረሃል፤ ቀንህን በምስጋና አሃዱ ብለሃል፤ ንፁውን አየር ማጣጠሙን ተክነህበታል፤ እንግዲህ ከዚህ በላይ ደስታ፣ ከዚህ በላይ እርካታ ከወዴትስ ይመጣል።

90. <u>“እውነተኛ ውሳኔ የሚለካው አዲስ እርምጃ በወሰድክ ልክ ነው። ምንም እርምጃ ከሌለ፣ በትክክል አልወሰንክም!”</u>

/ከቶኒ ሮቢንስ አንደበት/

የውሳኔህ ብዛት ብዙ ሊሆን ይችላል፣ ድርጊትህ ግን ከውሳኔ አንሶ ከተገኘ፣ አብዛኛዎቹ ውሳኔዎችህ ማደነጋገሪያ፣ ማወነባበጃና እራስን ማታለያ ውሳኔ ነበሩ ማለት ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! እራስህን አትሸውድ! የወሰንከውን ነገር ካላደረክ፣ ገና አልወሰንክም ማለት ነው። ውሳኔዎችህ ወደ ተግባር ሊመሩህ ይችላሉ ካልፈፀምካቸው ግን እንደ ማንኛውም ተራ ንግርት ጊዜያዊና ስሜትን ማብረጃ ብቻ መሆናቸው አይቀርም።

አዎ! ሳታመዛዝን፣ ሳታስተውል፣ በስሜታዊነት የምትወስነው ውሳኔህ ዋጋ እንደሚያስከፍልህ ስለምታውቅ ላትተገብረው ትችላለህ። ነገር ግን እውነታኛው ውሳኔ ከእራስ ጋር ከሚደረግ ጥልቅ ንግግር ቦሃላ የሚመጣው ውሳኔ ነውና እርሱን ፈፅም። የውሳኔህን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ ደጋግመህ መወሰን አይጠበቅብህም፤ ትክክልኛ የሚሆነው አድርገሀው ስትገኝ ብቻ ነው። "ያለ ቆራጥነት አትጀምርም፤ ያለ ፅናት አትጨርስም፤" እውቁና ተወዳጁ የሆሊዩድ አንጋፋ ተዋናይ ዴንዝል ዋሺንግተን አንድ በብዙዎች የሚወደድ ግሩም አባባል አለው። "ያለ ቆራጥነት አትጀምርም፤ ያለ ፅናት አትጨርስም" **አዎ!** ጀግናዬ..! ቆራጥ ካልሆንክ ቆመህ ትቀራለህ፤ ፅናት ከሌለህ መሃል በመድረስ የሚወዳደርህ አይገኝም፤ የነካሀው ሁሉ በጅምር ይቀራል፤ መጨረስ፤ ማከናወን፣ ማገባደድ እንደ ናፈቀህ ይቀራል። ምናልባት ያንተ ችግር መጀመር ላይሆን ይችላል እስካልጨረስክ ግን የጅማሬህ ዋጋ አናሳ መሆኑ አይቀርም።

አዎ! በቆራጥነት ካልጀመርክ ቆጥረህ የማትጨርሰው የጅማሬህ ጠላት ከፊትህ ተሰልፎ ልታገኘው ትችላለህ። ማንም አዲስ ነገር የጀመረ ሰው ሁሉን ፈተናና መሰናክል በቆራጥነት ተጋፍጦ ያለፈ ነው። **አዎ!** ጀግናዬ..! የፅናት ደረጃ ለመድረስ በቆራጥነት መጀመርህ የግድ ነው። ጊዜያዊ ቆራጥነት ሳይሆን ዘላቂ፤ ጊዜያዊ ስሜትን ያማከለ ሳይሆን ልባዊውን፣ ውስጣዊውን ያነገበ።

አዎ! እስከ ዛሬ ጀምረህ ያቆምካቸውን መልካም የህይወት ልማዶች አስታውስ። ፀሎት ማድረስ ጀምረህ አቁመህ ይሆናል፤ **"Exercise"** ጀምረህ አቋርጠህ ይሆናል፤ የቀን፣ የሳምንት፣ የወር እቅድ ማውጣትህን በመሃል ትተሀው ይሆናል፤ ማንበብ ጀምረህ አቁመህ ይሆናል፤ ጥሩ የሚባል ስራ ጀምረህ ምናልባትም ሰልችቶህ አቁመሀው ይሆናል። ነገር ግን ሁሉንም ጠቃሚ ተሞክሮዎች ስታቆም እንደምትጎዳ ታውቃለህ፤ ጉዳትህ ግን ፅናት አንዲኖርህ ሊያደርግ አልቻለም።
ዞር ብለህ ስታስታውስ ያቋረጥክበትን ምክንያት ብትጠየቅ ብዙ ምክንያቶች ታቀርብ ይሆናል፤ አንዳቸውም ግን በቂ አይሆኑም። ያቆምከው ውጤቱን ለማየት ፅናት ስላጣህ ነው፤ ስለቹነትህ ስለበዛ ነው፤ ፍላጎትህ ዘሬ ጀምረህ ነገ መሸለም ስለሆነ ነው።

በዚህ አለም ግን እንደዚህ የሚሰራ ቀላል ቀመር የለም፤ እያንዳንዱ ነገር በሂደት ይጓዛል፤ ዛሬ የተተከለ ተክል ነገ ፍሬ አያፈራም፤ ዛሬ የተሰራ **"Exercise"** ነገ የተስተካከለ ቁመና አያመጣም፤ ዛሬ የተጀመረ ንባብ ነገ ምሁር አያደርግም፤ ዛሬ የተጀመረ **"Business"** ነገ ትርፍ በትርፍ አይሆንም፤ ዛሬ የተዋወካትን ሴት ነገ የጋብቻ ጥያቄ አታቀርብላትም፤ **አዎ!** ድፍረትህ፣ ቆራጥነትህ ካስጀመረህ አይቀር፣ ፅናትና ተግስትም ፍሬውን እንዲያሳዩህ ፍቀድ። የጀመርከውን ሳይሆን የጨረስከውን፣ የነካሀውን ሳይሆን የፈፀምከውን እንዲያበዙልህ አድርግ።

91. "ዛሬ፣ ዋጋዋ ጥልቅ ነው!"

ልዩ ጀምበር ዘወትር አዲስ ነገር ይታይባታል፤ የሚያምር የአምላክ በረከት አብሯት ይመጣል፤ በአዲስነቷ ለአዲስ ክስተት ትጋብዘናለች። በልዩነቷ ልዩነት ፈጣሪ ታደርገናለች። ቀናት ሲቀያየሩ፣ ትናንት በዛሬ ሲተካ፣ ዛሬም በነገ ሲለወጥ እንደማየት ትልቅ የፈጣሪ ስጦታ ምን አለ? **አዎ!** ጀግናዬ..! ዛሬን ስላለህ ነገን ታልማለህ፤ የዛሬን እስትንፋስ በማግኘትህ ስለቀሪዎቹ ብዙ ቀናት ታስባለህ፤ አዲሷ የዛሬ ጀምበር ለብዙዎቹ ነገዎች ብሩህ ተስፋ እንድትሰንቅ ታደርግሃለች። ነገም ሆነ ዛሬ፣ በዛሬ መዳፍ ውስጥ ናቸው። ዛሬን መኖር ስትጀምር ቀሪዎቹ ነገዎችህ የተሻሉ ይሆናሉ፤ ዛሬ የምታንፀው ህንፃ የነገ መኖሪያህ ነው፤ ዛሬ የምትገነባው ማንነት የነገ መገለጫህ፣ መታወቂህ፣ ማረፊያህ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! ዛሬ፣ ዋጋዋ ጥልቅ ነው፤ ትልቅ ነው። መኖርህን እርግጠኛ የምትሆነው በዛሬ ውስጥ ነው፤ ሙሉ ህይወትህን ለማስተካከል፣ ለማበጀት ዛሬ መነሻ፣ መሰረት ነው፤ ሃሳቦችህን በተግባር ለመቀየር እርግጠኛ የምትሆነው ዛሬ ላይ ሆነህ ነው፤ ነገህን የምታበራው ዛሬ በገጠምከው ብረሃናማ አምፑሎች ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! አንድ ሰው እንድተጠቀምበት በማሰብ በስጦታ መልክ የሰጠህን እቃ ሳትጠቀመው ብትቀርና እንዲሁ ባክኖ ቢቀር ቅር እንደሚሰኝ ሁሉ አምላክህም በሰጠህ ልዩ ዛሬ ባለመጠቀምህ ቅር እንዳይሰኝብህ ተጠንቀቅ። አዎ! ትርፍ የምታባክነው ጊዜና ቀን የለህም፤ እያንዳንዱ ቀንና ሰዓት የእራሱ ዋጋ አለው፤ የተሰጠህ እንድታባክነው ሳይሆን እንድትጠቀመው ነው። ሁሉም በምክንያት ተሰቶሃል፤ የቀናት ጭማሬው በምክንያት ነው፤ የሰዎች መምጣት መሔድ በምክንያት ነው፤ ያንተ ዛሬን ማየት፣ ለዛሬ መድረስ በምክንያት ነው። አዎ! ምክንያቱን አለማወቅና በእርሱ አለመጠቀም ግን ዋጋ ያስከፍለናል። በምንም ሁኔታ፣ ከአምላክ በታደልከው ልዩ ስጦታ ውብ በረከት፣ ከሰው ባገኘሀው መልካም አበርክቶት የሆነ ነገር አትርፍ፤ የስጦታዎቸህን ዋጋ ከፍ አድርግ፤ ጥቅማቸውን አጉልተህ አሳይ፤

የሚጠበቅብህንም ድርሻ በሚገባ ተወጣ።

92. “ገንዘብ ምን ሲያደርግ አይተሃል?”

በእውነቱ ገንዘብ ትልቅ ሃይል አለው። ቤት ሲገነባ አይተሃል፤ እቃ ሲገዛ አይተሃል፤ ሀገር ሲገነባ አይተሃል፤ ደስታን ሲገዛስ አይተሃል? ገዝቶ አያውቅም። **አዎ!** ገንዘብ ደስታን አይሰጥህም፤ ገንዘብ ሳገኝ እደሰታለው፣ ንብረት ሳፈራ እደሰታለው የምትል ከሆነ እንዳትሳሳት። እውነት ላይመስልህ ይችላል ለደስታህ ዋናው እምነትህ ነው። ባለኝ ደስተኛ ነኝ ማለት ነው። ለደስታህ መስፈርት አታብጅለት፤ ቀጠሮ አትስጠው። ባሰብከው፣ በቀጠርከው ቀን ያላገኘህው እንደሆነ ልብህ ይሰበራል፣ ህይወት ትርጉም ታጣብሃለች፣ ልፋትህ፣ ድካምህ ውጤት እንደሌለው ይሰማሃል።

አዎ! ጀግናዬ...! የህይወት ሙሉነት ወደፊት በምታገኘው ሳይሆን ዛሬ ባለህ፣ በተሰጠህ ነገር ይወሰናል። ዛሬ ባለህ ካልተደሰትክ ነገም በሚኖርህ ደስተኛ መሆንህ አጠያያቂ ነው። የመስፈርት ብዛት እጅህ ላይ ያለውን ዋጋ ያሳጣዋል፤ ጤናህን፣ ሰላምህን፣ ስራህን፣ ብርታትህን፣ ወኔህን፣ መልካምነትህን አያሉ አለመኖራቸውን ያጎላብሃል። አንተ ስላላየሀው የለህም ማለት አይደለም፤ እራስህን ፈትሽ።

አዎ! ደስታህ ገና ለገና በምታገኘው ገንዘብ ውስጥ ከሆነ፣ በሚኖርህ ስኬት ውስጥ ከሆነ፣ በምታገኛቸው ሰዎች ውስጥ ከሆነ በትልቁ የህይወት ስንቅህ ሌላ አዛዥ ሾምክለት ማለት ነው። እርሱ ሲፈልግ ብቻ ያስደስትሃል፣ ሲፈልግ ብቻ ፈገግታህን ይሰጥሃል ይቀማሃል፤ እርሱ ሲፈልግ ብቻ ስሜትህን ይቆጣጠራል። **አዎ!** ጀግናዬ..! በዚህ ምድር ገንዘብ ትልቅ ሃይል አለው በደስታህ ግን እንዲያዝበት አትፍቀድ፤ ሰላምህን ለማግኘት ዋስትና አታደርገው፤ ጤናህን አትገብርለት፤ ገንዘብ መቼም የማይገዛቸውን ውድ የአምላክ ስጦታዎች ተመልከት፣ በእነርሱም እመን፤ ማንንም ሳትጠብቅ በአንተነትህ፣ በተሰጠህ ውብ የአምላክ በረከት ብቻ ደስተኛ ሁን።

93. “እያንዳንዱ ቀን የተለየ አንተን ይፈልጋል!”

ውስጣዊ ጥማት፣ የልብ ምኞት፣ ጥልቅ የስኬት ረሃብ በፍፁም አያስተኛህም። በየእለቱ መጠጥ አምጣ ይልሃል፤ በእየቀኑ ወደ ምኞትህ ቅረብ ይልሃል፤ እለት እለት ህልምህን እንድትኖር ይታገልሃል፤ ጥምሙ እንድትቆርጥለት በየአቅጣጫው የሚጠጣ ፍለጋ ያማትራል። **አዎ!** ጀግናዬ..! አንድን ነገር መፈለግህ ካልቀረ ከልብህ፣ ከውስጥህ ፈልገው፤ በእርግጥም እንደሚገባህ እመን፤ ስለሚገባህም የማገባህን፣ የሚጠበቅብህን ታደርጋለህ። በግዴለሽነት የምትተወው፣ ከሆነ ይሁን ካልሆን ችግር የለውም የምትለው አይደለም፤ አዎ! በደምብ ችግር አለው ለዛው ዘላቂና መሰረታዊ ችግር፤ ህይወትህን የሚቀይር ነገር፣ ፍላጎትህን የሚያሟላ ነገር ትተህ እንዴት ችግር ላይኖረው ይችላል። ችግርማ አለው፤ ህልምህን ሳይኖሩ ማለፍን የሚበልጥ ችግር የለም፤ የእራስን ደስታ ሳያጠጥሙ መሔድን የመሰለ ችግር ኬት ይመጣል።

አዎ! ጀግናዬ..! ፍላጎትህን ችላ አትበለው፤ ህልምህን አትናቀው፤ ዋጋ ስጠው፤ ስሜትህን አትግደል፤ አዳምጠው፤ አምሮትህን አትግፋው፤ ለማሳካት ታገል፤ ከልብ ካለቀሱ እንባ አይገድም ነውና የምትፈልገውን ነገር ከልብህ ፈልገው። የትም እየው የት ቀልብህን ከገዛ፣ እንደሚቀይርህ ካመንክ በፍፁም ጭራውን አትልቀቅ፣ ወደኋላ አትበል ተከተለው ለእርሱም ብለህ በእየቀኑ እራስህ ላይ ዋጋ እየጨመርክ ተጓዝ፤ አለምን ወደራስህ አቅርብ።

አዎ! በተለየ ፍላጎት ስትሞላ እያንዳንዱ ቀን የተለየ አንተን ይፈልጋል፤ ከትናንት የተሻለ፣ መንፈሱ የጠነከረ፣ ስሜቱ የማይረበሽ፣ ስኬትን በይበልጥ የተራበ፣ ለፍላጎቱ ሲል የሚታገል፣ እንቅልፍ የማይተኛ፣ አርቆ የሚያስብ፣ ዛሬን የሚኖር ነገን የሚያልም። ስለዚህ የቀናቶችህን ፍላጎት አማላ፤ እለት እለት

የተሻልክ ሆነህ ቅረብ።

94. “ወድቆ የቀረ ቀላሉን ይመርጣል!”

አዎ! ለመውደቅ ምንም ማድረግ አይጠበቅብህም፤ መቀመጥህ፣ ተስፋ መቁረጥህ በቂ ነው። ጀምረህ ከተውክ በቃ ትወድቃለህ፣ ምንም የሚያደክምህ ነገር የለም። ሳትጀምር ብትቀር ሃሳብህን ትጥለዋለህ፣ ያንን ግዙፉን ትልቁን ህልምህን መና ታስቀረዋለህ፣ ካሰብከው ልኬት ታወርደዋለህ፣ ዋጋውን ታሳንሰዋለህ፣ እርሱ ቀና ሊያደርግህ ቢዘጋጅም አንተ ግን ውድቀትን ትመርጥለታለህ፣ ከወደቁ፣ ካረጁ፣ ካፈጁ ትናንሽ ሃሳቦች ጋር ትመድበዋለህ። አዎ! ውድቀት ይህን ያህል ቀላል ነው፣ ተራ መሆን ምንም ቅንጣት ክህሎት አይፈልግም፣ ህይወት የሰጠችህን ሁሉ መቀበል **“Maturity”** አይጠይቅም፣ ጥቃቅን ነገሮች ጥቃቅን ነገር ያስደርጉሃል፣ የሃሳብህ፣ የድርጊትህ መሰናክል ናቸው፤ የውድቀትህ መንስዔ ናቸው።

አዎ! ጀግናዬ..! መውደቅ ቀላል ነው፤ ነገር ግን ለመውደቅም ጉዞ መጀመር አለብህ፤ የሃሳብ ጉዞ፣ የድርጊት ጉዞ። ከዛም ውደቅ፣ ተነስ ደጋሜም ውደቅ፤ እንደገና ተነስ እንደገና ውደቅ፣ መጨረሻህን ግን በመነሳት፣ ቀና በማለት ደምድም። **አዎ!** በአዚህ ወድቆ የመነሳት ሂደት ሁለት ነገር ትማራለህ አንድም ለመውደቅ ምንም ማድረግ እደሌለብህ፣ የውድቀትን ቅለት፣ የመጓዝን፣ የማድረግን ክብደት። ሁለት የውድቀትን አስከፊነት፣ አንገት ሰባሪነት ትረዳለህ።

አዎ! ውድቀት ጥላህ ነው፣ ሁሌም ይከተልሃል እርሱን ከፈራህ ግን ምንም ማድረግ አይጠበቅብህም፤ አርፈህ ከተቀመጥክ፣ ካቆምክ የሚከተልህ ጥላም ይጠፉል። **አዎ!** ወድቆ የቀረ ቀላሉን ይመርጣል፤ ውድቀቱን ደጋግሞ የጣለ ከባዱን ፈተና ያልፋል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ለመውደቅ ብለህ የምታወጣው ወጪ፣ የምታጣው እንቅልፍ፣ የምታጣው ጓደኛ፣ ወዳጅ፣ ቤተሰብ፣ የምታነበው ወፅሃፍ፣ የምትኖረው ህልም በፍፁም አይኖርም። የውድቀትን ቀላልነት ካወክ በማንኛውም ሁኔታ ለመውደቅ ቅርብ እንደሆንክ ይሰማህ፣ ነገር ግን ውድቀትን በፍፁም ምርጫህ አታድርገው። **አዎ!** ቀላል ነገር ሊያነሳህ አይችልም፤ ተራ መሆንም የተለየህ አያደርግህም።

95. “አዕምሮህን አሰልጥን!”

አዕምሮ እንደማንኛውም የሰውነት አካል ሰራውን በአግባቡ እንዲሰራ፣ ንቃቱ ከፍ እንዲል፣ ሁሌ የተሻለ አስተሳሰብ እንዲያዳብር ስልጠና ይፈልጋል። ምናልባት ስልጠናው በቋሚነት የሚሰጠው ላይሆን ይችላል፣ ሁን ብሎ ወደ ችግር ፈተና በመግባትም ላይሆን ይችላል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ስልጠናው ከፍ የሚያደርግህ፣ በአዳዲስ ተግባሮች የተሞላ፣ ከባዱን ነገር በመሞከር፣ ቀላልና አሰልቺ ተግባራትን በማስወገድ የሚከወን ታስቦበት ከሚሰጠው ስልጠና በተጨማሪ በተግባር የሚወሰድ የንቃተ ህሊና ስልጠና ነው። ንቁ አይምሮ ፈጣን ነው፤ የሰለጠነ አዕምሮ የሚያቆመው ነገር የለም፤ መጪውን ችግር ቀድሞ ያውቃል ምላሹኝም በጥንቃቄ ይሰጣል፤ በመደናገጥ የሚያበላሸው መልካም አጋጣሚ የለም።

አዎ! ጀግናዬ..! አዕምሮህን አሰልጥን፤ እለት እለት አስተምረው፤ በተሻለ አስተሳሰብ አንፀው፤ አዲስ ነገር አሳየው፤ አውቆ እንዲጠቀም፣ ተጠቅሞ እንዲያተርፍ አስችለው፤ መግቦትህ አይለየው ንባብን መግበው፤ ከሚጠቅመው እውቀት አጋራው፤ መንፈስን የሚያድሱ፣ አዕምሮን በሚያነቁ ውብ ንግግሮች ንቃቱን ጨምር፤ እሳቤውን አስፋ።

አዎ! የሰለጠነ አዕምሮ በቀላሉ ልዩነትን ይፈጥራል፤ ከእራሱ አልፎ ሀገሩን አህጉሩን፣ አለምን በተሻለ ደረጃ ከፍ ያደርጋል፤ ይለውጣል፤ ያንፃል። ለትውልድ የሚሻገር ድንቅ ሃሳብ ይኖረዋል፣ በእርሱም ስሙን ይፅፉል፣ የተሻለ ነገር ይፈጥራል። **አዎ!** ጀግናዬ..! ሁሌም አዕምሮህን ማሰልጠንህን፣ በተሻሉ ሃሳቦች

መሙላትህን፣ የሃሳብህን ልኬት መተግበርህን በፍፁም እንዳትረሳ፤ ለህልምህ እውንነት መሰረቱ የሰለጠ አዕምሮ ነውና።

96. "ህይወትህ ቢፃፍ ምን አይነት ድርሰት ይወጣዋል?"

እውቁ ደራሲ ማሞ ውድነህ ምን ይላል"የማይሰለቸው ድርሰት ሰው ስለእራሱ የሚፅፈው ድርሰት ነው። "በዓሉ ግርማም አክሎ አያንዳንዱ ሰው ውስጥ አንዳንድ አስገራሚ ድርሰት አለ፤ ልዩነቱ መፃፍ መቻልና አለመቻላችን ነው" ይለናል። **አዎ!** ህይወታችን ግሩም ድርሰት ነው በአምላክ የተሰጠን፣ በእኛ የሚመራ። ነገር ግን አንድ ወሳኝ ጥያቄ አለ ምናልባት ብንፅፈው፣ ብንከትበው፣ ብንደርሰው ምንያክል ያኮራናል፣ ያስደስተናል፣ ቀና ያደርገናል ብሎም ምንያክል አስተማሪ ነው? አንድ የመጣበትንና ዛሬ ያለበትን የህይወት ጉዞ በሚገባ የቃኘ ሰው አነሰም በዛም በጉዞው ሁሉ እየተማረ እንደመጣ ያውቀዋል። ህይወቱ ሳይፈልግም አስተምራዋለች። ደስታን በሃዘን፣ ሳቅን በለቅሶ፣ ማግኘትን በማጣት እያፈራረቀች አሳይታዋለች። ሁሉም ሰው የህይወት ድርሰቱን ቢፅፈው በአስደሳች ሁኔታ አንድም ተመሳሳይ ድርሰት ሊገኝ አይችልም።

አዎ! ጀግናዬ...! በእራስህ ድርሰት መሪው ተዋናይ አንተ ነህ። በዙሪያህ ያሉ ሰዎች ረዳት ተዋናዮች ናቸው። በደርሰቱ መሃል ከማንም ጎልተህ የምትታየው አንተ መሪው ተዋናይ ነህ። የሁለት ድርሻ ባለቤት ነህ አንድም ደረሲው ነህ ሌላም መሪ ተዋናይ ነህ። በደራሲነትህ የረዳት ተዋናዮችንና በዙሪያ ያሉትን ሰዎች ማንነት መቀየር ትችላለህ። እንደ ዋና ተዋናይነትህ ተፅኖህን አይተህ ጎልተህ መታየት ትችላለህ። በተፅኖህ ተጠቅመህ የሌላችን ድርሻ ማሳነስ ትችላለህ። **አዎ!** በእራስህ ድርሰት የመቼቱ ወሳኝ አንተ ነህ፤ ነገሮችን በፈለከው መንገድ ማስኬድ ያንተ ድርሻ ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! አንዴ ቆም ብለህ አስብ ህይወትህ ቢፃፍ ምን አይነት ድርሰት ይወጣዋል? የጀብደኛ፣ ድንቅ አድራጊ ድርሰት ወይስ ለንግርት የማይበቃ የተራ ሰው ታሪክ? ከአሸናፊዎች ተርታ የሚመድብህ አኩሪ ድርሰት ወይስ ከተረሱት ተሸናፊዎች የሚጨምርህ የወደቀ ታሪክ? ድንቅ መማሪያ ከሆኑት አስተማሪ ድርሰቶች ወይስ ከማይረቡት የጥፋት ትርክቶች? **አዎ!** የእራስህን አስገራሚ ድንቅ ድርሰት በእራስህ ፃፍ፤ የምትኮራበትን ታሪክ አስቀምጥ፤ ባንተ ብቻ የማያበቃ ለወዳጆችህ የሚተርፍ ዘመን ተሻጋሪ ግሩም ድርሰት፣ ስምህን ከፍ የሚያደርግ፣ ከትላልቆች ጎራ ትልቅ የሚያደርግህን እርሱን የተለየ አስደማሚ ደርሰት ፃፍ።

97. "አንድ እርምጃ ወደፊት!"

ቀድሞ የተገኘ እጅጉን ያተርፋል፤ አዲሱን ያገኛል፤ የተሰራውን የሰራ፣ ተከትሎ የመጣ የተረፈውን ያገኛል። **አዎ!** ጀግናዬ..! አንድ እርምጃ ወደፊት ቀድሞ መገኘት፤ አዲስ ነገር መሞከር፣ ያልተጀመረ መጀመር፣ ያልተደረገ ማድረግ፣ **አዎ!** አንድ እርምጃ ወደፊት ቀድሞ መገኘት ድፍረትን ይፈልጋል፣ ከሌላው መልየትን ይፈልጋል። አንድ እርምጃ መቅደም የተለመደ አይደለም እጅጉን ያስፈራል፤ ምናልባትም ወደ ጨለማ ቤት ከማንም ቀድሞ እንደመግባት ሊያስፈራ ይችላል ነገር ግን ጨለማውን ለመጋፈጥ ቀዳሚ እንደሆንከው ብርሃኑንም ለማምጣት፣ ጨለማውን ለመግፈፍም የቀደምክ መሆን ይኖርብሃል። አዎ! ህይወት ሩጫ ነች ሁሉም በየፊናው ይሮጣል፤ እራሱን ይፈልጋል፤ ፍላጎቱን ይፈልጋል፣ የተመኘው እንዲኖረው ደፋ ቀና ይላል፣ ያልነበረ ይፈጥራል፣ ለመታወቅ ይታገላል፣ ለትርፍ ይሯሯጣል፤ ቀዳሚ ለመሆን እንቅልፉን ያጣል።

አዎ! ጀግናዬ..! በመንገዱ፣ በትግሉ፣ በውደድሩ፣ በስራው ሁሉ አንድ እርጃ ቀደሞ የተገኘ ሰው፣ ፍጥነቱ፣ ድርጊቱ፣ ስራው ሁሉ የቀደመ ነው ከተለመደው ከፍ ያለ፣ አዲስ ነገር በውስጡ የያዘ፤ ጥረቱ እጥፍ ነው፣

ከቀድሞው የተሻለ ነው፤ ድርጊቱ ያይላል፣ ይለያል። **አዎ!** ጀግናዬ..! በመንገድህ ሁሉ አንድ እርምጃ ቀድመህ ተገኝ፣ በአዲስ ግኝት ቀድመህ ተገኝ፣ የእራስህ ነገር በመፍጠር ቀዳሚ ሁን፣ **"Copy"** ማድረጉን ለሌሎች ተውላላቸው፣ አንተ ግን በእራስህ መንገድ ተጓዝ፣ በጉዞህ ሁሉ ቅደማቸው፣ **"Shine by your creativity, be one step ahead on everybody."** የቀደመ ይሸለማል፤ የተቀደመ ይማራል፤ ሽንፈት እስኪያስተምርህ አትጠብቅ ሁሌም ማሸነፍን፣ ቀድሞ መገኘትን ምረጥ።

98. "አዋቂ ያልፋል፤ እውቀት አያልፍም!"

አውቀህ ባላካፈልከው እውቀት አውቃለሁ አትበል። አላዋቂ በሚመስሉህ ላይ መመፃደቅህ፣ እራስህን አዋቂ ማስመሰልህ አዋቂ ሳይሆን አላዋቂ ያደርግሃል። ያወከውን፣ የምታውቀውን፣ የተረዳህውን፣ የተገነዘብከውን ማካፈል ከብዶህ አይደለም፣ ዋጋ የሌለው ስለሚመስልህ አይደለም፣ ለማካፈል በቂ እንደሆነም ስላላመንክ አይደለም።

አዎ! ዋንኛው መሰረታዊ ምክንያትህ የምታውቀውን ስታካፍል፣ የተካፈለህ ሰው እንደሚበልጥህ ስለሚሰማህ ነው። አስበው አንተ በነገርከው ነገር ካንተ ተሸሎ አንድ ነገር ፈጥሮ ሲያሳይህ፣ አስበው አንተ ከስንት አመት በፊት በምታውቀው ነገር እርሱ ዛሬ ካንተ ሰምቶ በልጦህ ሲሔድ፣ አስበው ከኔ በላይ በሚገባ የተረዳው፣ ያወቀው የለም ባልከው ነገር በጥቂቱ ተረድቶህ ሌላ አስደናቂ ነገር ሲሰራ፣ ይህ ሁሉ ያስፈራሃል፤ ስጋት ይጭርብሃል፤ በእራስህ ምንጭነት ሌሎች ካንተ በላይ እንዲፈሱ አትፈልጉም፤ ባንተ ለምነት የአበቦች መፍካት፣ ማማር ደምቆ መታየት ያንተን ለምነትና ውበት የሚያጠፋ ይመስልሃል፣ ካንተ በወጣ እውቀት ከተቀባይህ መነፃፀር የሚያሳንስህ መስሎ ይሰማሃል።

አዎ! ጀግናዬ..! የሚናቅ፣ የሚተወ እውቀት በሌለበት በዚህ አለም መጠቀም በምትችለው ተጠቀም፤ ባልቻልከው ሌሎች ተጠቅመው እንዲጠቅሙህ አድርግ። **አዎ!** የማታስተላልፈው እውቀት እውቀት አይደለም። እውቀትህ ግብዝ ካደረገህ ለአዋቂነት ሩብ ጉዳይ ነህ ማለት ነው። ብታውቅም የአዋቂነት መስፈርት ይጎድልሃል።

አዎ! ጀግናዬ...! አዋቂ ያልፋል፤ እውቀት አያልፍም፤ ሲሸጋገር፣ ሲካፈል፣ ሲታወቅ ይኖራል። አንተ ብታልፍም እውቀትህ አይለፍ፤ አንተ ባትጠቀመው ሌላው ይጠቀመው፤ አንተ ባታተርፍበት ሌላው ያትርፍበት። የአዋቂነት ሌኬትህን ባካፈልከው እውቀት ልኬት መመዘን ጀምር፤ ምን አወኩ? ምን አካፈልኩ? ምን ተጠቀምኩ? ማለት ጀምር። የሚያካፍል አዋቂ ሁሌም አዋቂ ነው። አንድም ለእራሱ፣ ሌላም ለአካፈለው ሰው። ዛሬ ባለንበት ደረጃ ሌላ የሻለ ነገር ማድረግ ባንችል እንኳ ያለንን እውቀት ለሌለው፣ ለሚያስፈልገው እናካፍል፤ እናስተላልፍ፣ ሲጠቀምበት፣ ሲያተርፍበት ስናይ እንደሰት፤ ሌላም እንጨምርለት። አዎ! ማካፈል ያለን ላይ የተሻለ ነገር የጨመርልናልና።

99. "ዋናውን ጠበቅ፣ ቀሪውን ለቀቅ!"

ትርፍ ሆኖ፣ ቀሪ ሆኖ፣ ጎጂ ሆኖ ስሜትሽን የገዛ ቀልብሽን የያዘ፣ ሰላም የነሳሽ፣ እንቅልፍ ያሳጣሽ ነገር ለድርድር ሳይቀርብ መወገድ ይኖርበታል። ለእርሱ የምታውይው ትርፍ ስሜት፣ የምትሰጪው ትርፍ ጊዜ የለሽም። **አዎ!** ጀግኒት..! ዋናዎቹ የህይወት ቅመሞች አንቺን ይሻሉ፤ ትኩረትሽን፣ ጊዜሽን፤ ስሜትሽን፣ ንብረትሽን፣ ጉልበትሽን። አዎ! ዋናውን ጠበቅ፣ ቀሪውን ለቀቅ። ዋናው ጤናሽ፣ ሰላምሽ ነው፤ ዋናው ደስታሽ፣ ሃሴትሽ ነው፤ ዋናው ቤተሰብሽ፣ ወዳጅሽ ነው፤ ዋናው ህልምሽ፣ ስኬትሽ ነው፤ ጠበቅ፣ ሙጭጭ በይባቸው፣ በፍፁም እንዳትፋቺያቸው።

አዎ! ጀግናዬ..! ዋናዎቹን ስትይዝ ተራዎቹ፣ ቀሪዎቹ ቦታቸውን ይለቃሉ። ህይወትህን በአበይት ዋና

ጉዳዮች ስታንፅ፤ ተራዎቹ ቀልድ፣ ቧልት፣ ጫወታ፣ ፌዝ፣ ረብ አልባ ድግግሞሽ፣ ረፍትን የሚነሱ አልባሌ ተግባሮች ገሸሽ ይላሉ። ህይወትህ የተሻለች እንድትሆን ቁብ-ነገር አድርጋት። ህይወት አጭር ነች ሲባል ሰምተሃል ከኖርካት ግን አጭር አይደለችልም፤ ዋናዎቹ የህይወት ቅመሞች ላይ ካተኮርክ ቀላል፣ ጣፋጭ፣ እንዲሁም ረጅም ትሆንለሃለች። ቀሪዎቹ፣ ትርፍና፣ ጥቅም አልባ፣ የማይረቡ ነገሮች ላይ ካሰለፍክ ግን ይባስ እያጠረች ወደማትቀጠል፣ ወደማትዘረጋ፣ ወደማትስተካከል ተሰባሪ፣ አሳዛኝ ቁስ ትቀየራለች፣ ካለፈች የማታገኛት ታሪክ ትሆንብሃለች።

አዎ! እየኖርክ ነዋ? በደስታ፣ በፍቅር፣ በሃሴት ኑር፤ ህይወትን አጣጥም፣ **"Enjoy"** አድርግ፣ ተደሰትባት፣ ቀለል አድርጋት፣ ማማረርህን አቁም፣ ሃዘንህን ተው፣ ቁጪት ይቅርብህ፣ ዘና በል፤ የምትወደውን፣ የሚቀይርህን፣ የሚያስደስትህን፣ የሚያሻግርህን ህልምህን በእቅድ፣ በአላማ ኑር። ህይወትህን ለማቅለል ሁሌም ቀላል ነገር እያደረክ አትገኝ፤ ከባዱን ተጋፈጥ፤ ፈታኙን ተፋለም፤ አስፈሪውን ድፈር፣ ጠንካራውን ተጋጭ። **አዎ!** እስከመቼ ፈርተህ፣ አንድ ወደፊት ሁለት ወደኋላ ትጓዛለህ? እስከመቼ ቀላሉን እያከበድክ፣ እያወሳሰብክ እራስህን ታስጨንቃለህ? እስከመቼ "ይሔም ኑሮ ከተባለ..." እያልክ በምሬት ትኖራለህ? **አዎ!** ዋናዎቹን የህይወት ቅመሞች ጠበቅ አድርግ፤ ቀሪዎቹን ልቀቅ፤ የህይወት አላማህን አግኝ፤ እርሱንም በነፃነት ኑር።

100. "በሁለቱም ጫፍ እንደ ተሳለ ጦር!"

አንድ ሰው በምድራዊ ህይወቱ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች አሉበት። መሱዓትነት የሚያስከፍሉት፣ ዋጋ የሚጠይቁት፣ እይታውን የሚፈትኑ፣ ተግባሩን የሚፈታተኑ። **አዎ!** አለማዊ ወይም ስጋዊ ህይወትና ሰማያዊ ወይም መንፈሳዊ ህይወት። ሁለቱም በየፊናቸው የእራሳቸው መስፈርት አላቸው፤ አንዳቸውም ለአንዳቸው ተደጋጋፊ ናቸው። መንፈሳዊውን ህይወት ትቶ አለማዊው ላይ ማተኮር ከባድ ላይሆን ይችላል፣ አለምን ትቶ ንቆ ዘወትር በመንፈሳዊነት መመላለስ ግን ለአብዛኛው ሰው ከባድ ሆኖ ይታያል። ስጋን ለነፍስ ማስገዛት እንደ ምድራዊ ህይወት ፈተና ይወሰዳል፤ እንደማይቻልም ይነገራል። ነገር ግን ጥቂቶች እርሱን አድርገውታል፤ አለምን ትተዋል፤ ምድርን ንቀዋል፤ አምላካቸውንም በሙሉ ልባቸው አግኝተውታል።

አዎ! ጀግናዬ..! የሚያምን ግን ሁሉ ይቻለዋል። እምነቱ አንድም በፈጣሪ በአምላኩ ነው፤ ሌላም በእራሱ ነው። ሳታምን በግማሽ ልብ እያወላወልክ የምታደርገው ነገር የመሰካት እድሉ በጣም አናሳ ነው። ለዚህ እምነትህ በሁለቱም ጫፍ እንደ ተሳለ ጦር ሊያስመስለህ ይገባል፤ በተግባርም መታገዝ ይኖርበታል። እምነት ያለ ምግባር ሳይዘሩ እንደማጨድ ነውና።
በሁለቱም ጫፍ የተሳለው ጦር ሁለት አንድምታ አለው። አንድም መንፈሳዊና አለማዊ ህይወት ሲሆን፣ ሌላም ሁለቱም ዋና ጉዳዮች የሚያስፈልጉት እምነትና ምግር ነው።

አዎ! ጀግናዬ..! መንፈሳዊ ህይወትህን አጠንክር፣ ከአምላክህ ዘወትር ተነጋገር፣ ሁሌም እንደሚያግዝህ ተማመንበት፣ በመንገድህ አስቀድወም፣ በምድራዊ ህይወት እንዳትታለል፣ ከእርሱም እንዳትርቅ እለት እለት ተማፀነው። በአለማዊ ህይወትህም ጠንካራ፣ ንቁና ድንቅ አድራጊ ሁን፤ የህይወትህን መሪ እራስህ ጨብጥ፤ የምትሔድበትን አቅጣጫ በጥንቃቄ ምረጥ፤ ከአደጋ የፀዳ Safe Zone መሆኑን አረጋግጥ፤ ለማንኛውም የህይወት ክስተትም ወቃሽ ሳትሆን ሃላፊነት የሚሰማህ ሁን። **አዎ!** በሁለቱም ጫፍ እንደተሳለ ጦር በሁለቱም የህይወት አቅጣጫ እራስህን አጠንክር፤ እራስህን አበርታ፣ ሁሌም የተሻልክ ሆነህ ተገኝ።

ምዕራፍ አራት

ጠቅላላ እውቀት

1. “በኢትዮጵያ መንጃ ፈቃድ ማሽከርከር የሚቻልባቸው ሀገራት”

ጣልያን፣ ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ ቤልጂየም፣ ቱርክ፣ ግብፅ፣ ግሪክ፣ ሩስያ፣ ስዊድን፣ ህንድ፣ ዩጎዝላቪያ፣ ጀርመን፣ ኔዘርላንድ፣ የመን፣ ሜክሲኮ፣ ሳዉዲአረቢያ፣ ስዊዘርላንድ፣ ሱዳን፣ ቫቲካን፣ ቡልጋርያ፣ ጃፓን፣ ጋና፣ ስፔን፣ ፖላንድ፣ ሶማሊያ፣ ኢራን፣ ናይጄሪያ፣ ማላዊ፣ ሴኔጋል፣ ዛየር፣ ታንዛኒያ፣ ኢንዶኔዥያ፣ ደ.ኮርያ፣ ማሌዥያ፣ ብሩንዲ፣ ዛምቢያ፣ ሞሮኮ፣ ፊንላንድ፣ ታይላንድ፣ ሃንጋሪ፣ ኮትዲቯር፣ ካሜሩን፣ ኬንያ፣ ኢኳቶሪያልጊኒ፣ ቬንዝዌላ፣ ሴራሊዬን፣ ሩዋንዳ፣ ጀማይካ፣ ቻይና፣ ኡጋንዳ፣ አርጀንቲና፣ ጋቦን፣ ሊቢያ፣ ሩማኒያ፣ አልጄሪያ፣ ሼትናም፣ ጅቡቲ፣ ኮንጎ፣ ቻድ፣ ሞዛምቢክ፣ አዉስትራሊያ፣ አፍጋኒስታን፣ አረብ ሪፐብሊክ፣ እስራኤል፣ ኖርዌይ፣ ናሚብያ፣ ቡርኪና ፋሶ እና ሞሪታንያ

2. “ዛሬ በአለማችን በቀዳሚነት ማእድናት የሚያመርቱ ሀገራትን”

1. በአለም በአልማዝ ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ደቡብ አፍሪካ እና ቦትስዋና**
2. በአለም በኦፒየም ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **አፍጋኒስታን**
3. በአለም በጎማ ዛፍ ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ማሌዢያ**
4. በአለም በቴምር ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ኢራቅ**
5. በአለም በለውዝ ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ቤልጅየም**
6. በአለም በሬድዮ ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ቻይና፣ ጃፓን እና ሲንጋፖር**
7. በአለም በብረት ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ሩስያ፣ አውስትራሊያ እና ብራዚል**
8. በአለም በነዳጅ ዘይት ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **መካከለኛ ምስራቅ፣ ሩሲያ እና አሜሪካ**
9. በአለም በወርቅ ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **ደቡብ አፍሪካ፣ ሩሲያ እና ካናዳ**
10. በአለም በድንጋይ ከሰል ምርት ቀዳሚ ሀገር? ⇨ **አሜሪካ፣ ቻይና እና ሩሲያ**

3. “መኪኖች የተሰሩበት ሀገር:”

1. Lamborghini___Italy
2. Volvo ___ Sweden
3. Renault ___ France
4. Kia__S.korea
5. BMW ___ Germany
6. Ford_____USA
7. Honda___Japan
8. SAIC_____china
9. Nissan _Japan
10. Toyota Japan
11. Volkswagen _Germany
12. Mercedes___Germany
13. Peugeot____ France
14. GAC Group___china

15. Porsche_____Germany
16. Mazda _Japan
17. Mitsubishi _Japan
18. Dodge_____USA
19. Subaru _Japan
20. Landwind___China
21. Daewoo_____S.korea
22. Ferrari_____Italy
23. Opel_____Germany
24. Jeep_____America
25. Hyundai __S.Korea
26. Tata___India
27. Tesla____USA

4. በሞኪና አምራች ድርጅቶች ድጋፍ (sponsor) የሚደረጉ የእግር ኳስ ቡድኖች

1. Hyundai___Lyon
2. Jeep___Juventus
3. Mercedes__Stuttgart
4. Citroen__Arsenal
5. Opel___Mainz
6. Volkswagen___Wolfsburg
7. BMW__Eintracht Frankfurt
8. Audi___Bayern Munich
9. Dacia__Udinese
10. Chevrolet___Manchester united

5. "የኢትዮጵያን መንጃ ፈቃድ የማይቀበሉ ሀገራት ዝርዝር"

ላይቤርያ፣ ካናዳ፣ ጊኒ፣ ማሊ፣ ፓኪስታን፣ ኩባ፣ ኒጀር፣ ሰሜን-ኮርያ፣ ዙምባቡዌ፣ ቱኒዝያ፣ ኒካራጓ፣ ፉልስጤም፣ አንጎላ፣ ኢራቅ፣ ማዳጋስካር፣ ማሊ፣ አየርላንድ፣ ደቡብ-አፍሪካ፣ ሌሴቶ፣ ሞሪሺየስ፣ ኩዌት፣ ቦትስዋና፣ ቶጎ፣ ፖርቹጋል፣ ጋምቢያ፣ ቤኒን እና ዩክሬን

6. "በዞዳይካችሁ መሰረት የሚስማማችሁ ቀለሞች"

- ታውረስ፣ ካፕሪኮርን፣ ጀሚና እና ፒሰስ ---------- የሚወዱት ቀለም **ሰማያዊ** እና **አረንጋዴ**
- ሳጁታሪየስ፣ ኤሪስ፣ ሊብራ እና ሊዮ **----------** የሚመቻቸው ቀለም **ቀይ** እና **ብርቱካናማ**
- አኳርየስ፣ ቪርጎ፣ ካንሰር እና ስኮርፒዮን ----------የሚመቻቸው ቀለም **ነጭ**፣ **ጥቁር** እና **ግራጫ**

7. “የኮከቦች የእድል ቁጥር በግርድፉ”

- **ኤሪስ ---** 1 እና 9
- **ቶረስ ---** 2፣4፣6፣11፣20፣29፣37፣47፣56
- **ጀሚና ---** 3፣8፣12፣23
- **ካንሰር ---** 2፣ 7 ፣11፣ 16፣ 20 ፣25
- **ሊዮ ---** 1፣4 ፣10፣ 13፣ 19 ፣22
- **ቪርጎ ----** 5፣ 14፣ 23፣ 32፣ 41፣ 50
- **ሊብራ ---** 6 ፣15፣ 24፣ 33፣ 42፣ 51፣ 60
- **ስኮርፒዮ ---** 8 ፣9፣ 11፣ 18፣ 22፣ 27፣ 36፣ 45፣ 54፣ 63
- **ሳጁታሪየስ ----** 3 ፣12፣ 21፣ 30
- **ካፕሪኮርን ----** 1፣ 4፣ 8፣ 10 ፣13 ፣17 ፣22
- **አኳሪየስ ----** 4 ፣8 ፣13 ፣17 ፣22፣ 26
- **ፓይሰስ ----** 3፣ 7 ፣9፣ 12፣ 15፣ 16፣ 18 ፣21፣ 25፣ 30 34፣ 43፣ 52

8. “የኮከቦች ቁጥርና የባሕርይ ምሳሌ”

1. ኮከብ ስሙ ሐመል እሳት/**Aries** (ከመጋቢት 12 - ሚያዝያ 12) ፤ ምሳሌው **ድብ** ነው።
2. ኮከብ ስሙ ሠውር መሬት/**Taurus** (ከሚያዝያ 13 - ግንቦት 13) ፤ ምሳሌው **ዝንጀሮ** ነው።
3. ኮከብ ስሙ ገውዝ ነፋስ/**Gemini** (ከግንቦት 14 - ሰኔ 14) ፤ ምሳሌው **ዓጋዘን** ነው።
4. ኮከብ ስሙ ሸርጣን ውኃ/**Cancer** (ከሰኔ 15 - ሐምሌ 16) ፤ ምሳሌው **ቀበሮና** ነው።
5. ኮከብ ስሙ አሰድ እሳት/**Leo** (ከሐምሌ 17 - ነሐሴ 17) ፤ ምሳሌው **አንበሳ** ነው።
6. ኮከብ ስሙ ሰንቡላ መሬት/**Virgo** (ከነሐሴ 18 - መስከረም 13) ፤ ምሳሌው **ጉጉት** ነው።
7. ኮከብ ስሙ ሚዛን ነፋስ/**Libra** (ከመስከረም 14 - ጥቅምት 13) ፤ ምሳሌው **ተኩላ** ነው።
8. ኮከብ ስሙ ዓቅራብ ውኃ/**Scorpio** (ከጥቅምት 14 - ሕዳር 13) ፤ ምሳሌው **ነብር** ነው።
9. ኮከብ ስሙ ቀውስ እሳት/**Sagittarius** (ከሕዳር 14 - ታህሳስ 12) ፤ ምሳሌው **ጅብ** ነው።
10. ኮከብ ስሙ ጀዲ መሬት/**Capricorn** (ከታህሳስ 13 - ጥር 12) ፤ ምሳሌው **ንስር** ነው።
11. ኮከብ ስሙ ደለዊ ነፋስ/**Aquarius** (ከጥር 13 - የካቲት 12) ፤ ምሳሌው **በሬ** ነው።
12. ኮከብ ስሙ ሑት ውሃ/**Pisces** (ከየካቲት 13 - መጋቢት 11) ፤ ምሳሌው **ከይሲ** ነው።

9. “የኮከቦች ትንበያ”

1. "ኤሪስ"

ይሄ ሳምንት ለኤሪሶች አሪፍ የስልጠና እና የጉዞ ግዜ ቢሆን ጥሩ ነው፣ ለተሻለ ስራ ያበቃችዋል። ከሌሎች ሰዎች ጋ ያለችውን ግንኙነት ካሳደጉና፣ ፍላጎታቸውን ለሰው ካታሩ ያልተጠበቀ ጥሩ አጋጣሚ ያገኛሉ። "A work friendship may evolve into something more"

2. "ቶረስ"

በአቅራቢያቹ ለሚገኙ ሰዎች እጃቹን ዘርጉ፣ ምክንያቱም የሆነ ድራማ ወይ ደግሞ ፀብ በአቅሪያባቹ ይኖራል ይሄ ደግሞ ሁሉንም ሰው ሊያስቆጣ ይችላልና። ምችሉትን አድርጉ ግን ነገሮችን አታወሳስቡት፣ ቀለል አድርጉት። "The energy is powerful for making decision that creates a better balance between work and family responsibility.”

3. "ጀሚኒ"

በገንዘብ ዙሪያ ትልቅ ተነሳሽነት ሚኖሯቹና ጠንክሮ ለመስራት ምጥሩበት ግዜ ነው። እንዲሁም አሁን ያላቹበት ሁኔታ ለፈጠራና አዲስ ነገር ለመስራት አመቺው ገንዘብ ማግኛ ጊዜ ነው ይጠቀሙበት። "You may be thinking about creating a partnership with some one more compatible."

4. "ካንሰር"

በምናብ ምታስቡትን ነገር ወደ ተግባር ሚለወጥበት ስለሆነ፣ አብዛኛውን ነገር መሞከር ብዙ አያዋጣም። ምታስቡት አሪፍ የቢዝነስ ሀሳብ ካለ ነገሮች እስኪረጋጉ ትንሽ መታገስ አለባቹ። ነገር ግን የአሪፍ ትርፍ መደራደሪያ ወቅት ልታረጉት ትችላላቹ። በአጠቃላይ ግን ከሌሎች ሰዎች ጋ በጋራ ብትሰሩና፣ ሰዎችን በመንከባከብ ብታውሉት ጥሩ ነው። “Work as a team.”

5. "ሊዮ"

የራሳቹን ስራ ምትሰሩ ከሆነ በስራቹ ኮንፊደንስ ሊኖራቹ ይገባል፣ ይሄ ወቅት የራሳቹ እምነት ሚቀንስበት ነው፣ ስላዚ የራሳቹን ጥሩ ግዜ ማመቻቸት አለባቹ የዛን ግዜ ኖርማል ይሆናል። “The cosmos encourage you to compromise in one awkward situation“

6. "ቪርጎ"

ግዚአቹን በዋዛ ፈዛዛ ከማሳለፍ፣ በአዲስ ፈጠራ፣ ግኝትና ፕሮጀክት ላይ ብታተኩሩ ጥሩ ነው፣ በተፈጥሮ ሰውን የመረዳት እና የማስተማር ብቃት ስላላቹ ለየት ያሉ ነገሮች ላይ ትኩረት አድርጉ። “Boost your confidence.”

7. "ሊብራ"

ይሄ ሳምንት ለሊብራ ለመዝናናትም ሆነ በጎ ነገሮችን ለማድረግ በጣም አሪፍ ግዜ ነው። ድካም ድካም ሊሰማቹ ይችላል ቢሆንም ግን ለመስራት ክፍት አዕምሮ አላቹ። “Expanding your horizons may lead to a new or better job offer”

8. "ስኮርፒዮ"

ደስተኛ ምትሆኑበት አሪፍ ምክንያት አላቹ፣ ራሳቹንም ሆና ቤተሰባቹን ለመጠበቅ ጥሩ ተሰሚነት ላይ ስለሆናቹ። አቋማቹን ሊፈታተን ሚችል ነገር ሊያጋጥማቹ ይችላል። ስለዚ ቆም ብላቹ በደንብ አስቡ። “The more specific you are about what you want, the batter your chance of success.”

9. "ሳጂታሪየስ"

አሁን ላይ ብዙ ውዝግብና ሃላፊነት ላይ ትገኛላቹ፣ ከሰዎች ጋ ያላቹ ግንኙነት በተወሰነ መልኩ ኖርማል አይመስልም፣ እና ይሄን ነገር አስተካክሉት። አሁን ላይ ጥሩ ሀይል አላቹ ተጠቀሙበት። “Tough times don't last forever”

10. "ካብሪኮርን"

ማንኛውንም ነገር ለመስራት በቻላቹት መጠን ምርጥ አድርጋቹ ስሩት ፣ ጥቃቅን ምትሉትን ነገሮች ሳይቀር። በተለይ የፋይናንስ ነገሮች ላይ ትኩረት አድርጉ፣ የአሁኑ ስራቹ ለሚቀጥለው ወር ጥሩ እድል ይዞ ይመጣል። “The energy brings a powerful opportunity to brainstorm about your carer prospect.”

11. "አኳሪየስ"

ብስጭት ወይም ደግሞ ያለመመቸት ስሜት ላይ ናቹ፣ በአከባቢያቹ ያሉት ሰዎች ሲሪየስ ወይም ደግሞ ትኩረት እያረጉባቹ ይሆናል፣ በዚም ምክንያት ነፃነታቹን ስለምትፈልጉት ቅራኔ ውስጥ ልትገቡ

ትችላላቹ። አንድአንድ የስራ እድሎችንም ምታገኙበት እና ምትፈልጉበት ጥሩ ግዜ ላይ ናቹ፣ ሁሉም ግን ላይሳካ ስለሚችል፣ በውስጣቹ ያዙት። “Things will improve soon”

12. "ፓይሰስ"

አሁን ላይ ፓይሰሶች ተመሳሳይ ቦታ ላይ ነው ግዚአቹን እያሳለፋቹ ያላቹት። ጥሩ የስራ ግዜ ላይ ስለሆናቹ ብትንቀሳቀሱ አሪፍ ነው፣ ጤንነታቹንም ጠብቁ፣ ከሰው ጋ ያለቹንም ግንኙነት በልኩ አድርጉ፣ ጥሩ እንቅልፍም ያስፈልጋቹዋል፣ ጥሩ እቅድም አቅዱ። “Don't under estimate your talent”

10. ”የኮከቦች ጠንካራና ደካማ ጎን!”

1. “ኤሪስ”

ጠንካራ ጎናቸው = ደፋር፣ በራሳቸው የሚተማመኑ፣ አዎንታዊ አመለካከትያላቸው፣ ኢነርጄቲክ፣ አሳሽ።

ደካማ ጎናቸው = እራስ ወዳድ፣ ጉረኛ፣ የትዕግስት ማነስ፣ ቶሎ መቆጣት፣ ተለዋዋጭ፣ ወላዋይ።

2. “ታውረስ/ቶረስ”

ጠንካራ ጎናቸው = ታጋሽ፣ የተረጋጉ፣ አስተማማኝ፣ ኃላፊነትን የሚወጡ፣ በድርጊት እና በተግባር የሚያምኑ፣ ታማኝ፣ መንፈሰ ጠንካራ፣ ቆራጥ፣ ፅናት፣ ተንከባካቢ፣ የማይበገሩ፣ ጠንካራ ሰራተኞች።

ደካማ ጎናቸው = ፈጣን ለውጥን አለመቀበላቸው፣ ግትር፣ ተከራካሪነት፣ ቶሎ የማይግባቡ።

3. “ጄሚኒ”

ጠንካራ ጎናቸው = አፍቃሪ፣ ገራም፣ ለማወቅ የሚጓጉ፣ በፍጥነት የመማር ችሎታ፣ ተግባቢ፣ ቶሎ የሚላመዱ።

ደካማ ጎናቸው = ወጥነት ማጣት፣ በቀላሉ የሚደነግጡ፣ የሚወላውሉ፣ ስሜታዊነት፣ ወሬ ወዳድነት፣ ጆሮ ጠቢነታቸው።

4. “ካንሰር”

ጠንካራ ጎናቸው = አሳማኝ፣ ታማኝ፣ ከያዙ የማይለቁ፣ ምናባዊ ልህቀት፣ አዛኝና ሩህሩህ፣ ፈጠራ።

ደካማ ጎናቸው = ተጠራጣሪነት፣ የስሜት ወለዋወጥ፣ እራስ ወዳድ፣ ሙጥኝ ማለት።

5. “ሊዮ “

ጠንካራ ጎናቸው = ደስተኛ፣ ተጫዋች፣ ቸር፣ የታለ ስሜት፣ ፈጠራ፣ አፍቃሪ፣ ጓጊ።

ደካማ ጎናቸው = ልታይ ልታይ ባይነታቸው፣ ንቀት፣ ትዕቢት፣ መንካቻ፣ ደረቅ፣ ኢጎ ሴንተርድ፣ ስንፍና።

6. “ቪርጎ”

ጠንካራ ጎናቸው = አሳቢ፣ ሩህሩህ፣ ጠንካራ ሰራተኛ፣ ተግባራዊ፣ ታጋይ፣ ብልጥ፣ ትጉህ።

ደካማ ጎናቸው = አይን አፋር፣ ሁልጊዜ መዝናናት መፈለጋቸው፣ ጣልቃ ገብነት፣ ባህላዊነት፣ ቁጣ፣ ጭንቀት።

7. “ሊብራ”

ጠንካራ ጎናቸው = ተግባቢነት፣ ቀና አስተሳሰብ፣ ዲፕሎማሲያዊነት፣ ትብብር፣ ግርማ ሞገስ

ደካማ ጎን = አለመወሰን፣ ግጭትን አለማስወገድ፣ ቅሬታን መሸከም፣ እራስን መጉዳት

8. **“ስኮርፒዮ”**

ጠንካራ ጎን = የልብ ወዳጅ፣ ሰው ወዳድ፣ ጀግና፣ ጥልቅ ፍቅር ፣ሚስጥር ጠባቂ

ደካማ ጎን = ቅናተኛ፣ ቀናተኛ፣ ፀበኛ፣ ስሜታዊ፣ እምቢተኛ

9. **“ሳጂታሪየስ “**

ጠንካራ ጎን = ለጋስ፣ በጎ አሳቢ፣ ቀልደኛ፣ ራሳቸውን የሚችሉ፣ ጥንቁቅ፣ ሰው ወዳድ፣ ትሁት

ደካማ ጎን = ግትር፣ ቅብጥብጥ፣ ስሜት አልባ፣ ንግግራቸው ውስን አለመሆን፣ ከሚችሉት በላ ቃል መግባት

10. **“ካፕሪኮርን”**

ጠንካራ ጎን = ስርዓት ያላቸው፣ ራሳቸውን የሚቆጣጠሩ፣ ታላፊነትን የሚወስዱ፣ የመሪነት ብቃት

ደካማ ጎን = አውቃለሁ ባይነት፣ ይቅርታ አለማድረግ፣ ትዕቢተኛ፣ አሉታዊ አስተሳሰብ

11. **“አኳርየስ”**

ጠንካራ ጎን = ነፃና እራስን መቻል፣ ጥሩ ጓደኞች፣ ታማኝ፣ ወጥነት፣ የማይገመቱ፣ ፈጠራ

ደካማ ጎን = ስሜት አልባነት፣ ግልፍተኛ፣ ግትርነት፣ ገለልተኛ፣ ፌዘኛ፣ ተፃራሪ

12. **“ፒሰስ/ፓይሰስ”**

ጠንካራ ጎን = ፍቅር፣ አሳቢነት፣ ብልሀታዊነት፣ አዲስ ሁኔታን መልመድ፣ ደግነት

ደካማ ጎን = ፍርሀት፣ ሲበዛ ማመን፣ እውነታን ለመጋፈጥ አለመፈለግ፣ ተጠቂነት፣ ስራ መፍታት

11. **“በአስትሮሎጂ የተቀመጡት ሁሉም ከከቦች የየራሳቸው ምርጥ መለያ አላቸው። ልዩ መለያቸው ባላቸው ባህርይ (የእሳት ፣ የንፋስ ፣ የመሬት ወይም የውሃ ባ isህርይ) ፣ በገዢ ፕላኔታቸው ተፅዕኖ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ይመሰረታል። ሁሉንም ከከቦች ለየት የሚያደርጋቸው ምርጥ ነገር ምንድን ነው?”**

1**. Aries (ኤሪስ)** ከፍተኛ ኃይልና ፍጥነት ያላቸው በመሆኑ የሚያከናውኑትን ድርጊት ቶሎ በመላመድ በቅልጥፍናና በከፍተኛ ተነሳሽነት መፈፀም ይችላሉ።

2. **Taurus (ቶረስ)** እጅግ በጣም እውነተኛ ከሆኑት ቶረሶች በላይ በየትኛው ኮከብ ላይ እውነትን ትፈልጋላችሁ? ለእውነት የሚኖሩ እንዲሁም ታማኝ ናቸው።

3. **Gemini (ጄሚናይ)** እነዚህ ኮከቦች ሁለገብ ናቸው። ማንኛውንም ነገር በማንኛውም ሁናቴ ውስጥ ሆነው ማከናወን ይችላሉ። በቶሎ ተግባቢ፣ ጨዋታ አዋቂ እንዲሁም የአዕምሮ ልህቀታቸውም ከፍተኛ ነው።

4. **Cancer (ካንሰር)** ሰዎችን በከፍተኛ ሁኔታ መረዳት የሚችሉና ሰዎች ምን እንዳሰቡ ጭምር በልባቸው መረዳት የሚያስችል ኃይል አላቸው። በእናትነት የሚመሰለው ይህ ኮከብ ለሰዎች በማሰብና የሚወዳቸውን ሰው በመንከባከብ ይታወቃል።

5. **Leo (ሊዮ)** የተፈጥሮ መሪነት የተሰጣቸው ሊዮዎች ከፍተኛ የሆነ የራስ መተማመን ያላቸው ከመሆናቸው በተጨማሪ የተለያየ ሀሳብ ያላቸውን ነገሮች አንድ የማድረግ ከፍተኛ ብቃት አላቸው። በአጠገባቸው ያሉት ሰዎች በጠቅላላ የአሸናፊነት ስሜት እንዲኖራቸው ያደርጋሉ።

6. **Virgo (ቪርጎ)** በእያንዳንዱ ድርጊት ላይ ጥቃቅን የሚባሉ ነገሮች ላይ እንኳን ትኩረታቸው ከፍተኛ ነው። የማቀናጀት ስራ በሚፈልጉ ነገሮች ላይ በጠቅላላ ከነሱ በላይ የሚመጥን አይኖርም።

7. **Libra (ሊብራ)** እጅግ በጣም ደስተኛና ሚዛናዊ የሆነ ኑሮን ለመምራት የሚያስችል ስጦታ ተሰቷቸዋል። ይህን የተሰጣቸውንም ስጦታ በዙርያቸው ካሉ ሰዎች ጋር ሆነው ማጣጣምን ይፈልጋሉ።

8. **Scorpio (ስኮርፒዮ)** ታማኝነት ከምንም ነገር በላይ የነሱ መሰረት ነው። በታማኝነት ምንም

ድርድር የማያውቁት ስኮርፒዮዎች ለቃላቸው ታምነው በመኖር የታማኝነት ምሳሌነታቸውን ያሳያሉ። በምትኩም ከሰዎች ታማኝነትን ይፈልጋሉ። ታማኝ ለሆነላቸው ሰው ከነሱ በላይ ምርጥ ጓደኛ አይኖርም።

9. **Sagittarius (ሳጂታርየስ)** ዓለምን የሚመለከቱበት የራሳቸው ዕይታ ያላቸው ሲሆኑ በልባቸው ያሰቡትን ነገር ለማሳካት ወደ ኋላ የሚጎትታቸው ምንም ነገር የለም። እስኪያሳኩት ድረስ!

10. **Capricorn (ካፕሪኮርን)** የሥራ ጉዳይ ሲነሳ ቀድሞ የሚነሳው ካፕሪኮርን ሲሆን በስራቸውም ሆነ በዕለት ዕለት ኑሯቸው ግብረገብ ያላቸው ናቸው። ከስህተት ለመማር ምንም የማያመነቱት ካፕሪኮርኖች ሥራና ሥነምግባር ትልቅ ቦታ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያምናሉ።

11. **Aquarius (አኳሪየስ)** ለሰዎች የቆመ ኮከብ ቢባል ማጋነን አይሆንም። ሰዎችን መርዳት በጣም የሚያስደስታቸው አኳሪየሶች ጥሩ ለውጥ የሚያመጡ ሀሳቦችንም በማመንጨት ይታወቃሉ።

12. **Picses (ፓይሰስ)** ከሰዎች ጋር በጥልቀት መግባባት የሚችሉና ሰዎችን መረዳት የሚፈልጉ ናቸው። ችግሮች ከመከሰታቸው አስቀድመው ሊከሰቱ የሚችሉ ነገሮችን የመተንበይ አቅም አላቸው። ፓይሰሶች ምርጥ ጓደኛም ሆነ የፍቅር አጋር መሆን የሚችሉ ናቸው።

12. "ኮከቦች በአንድ ቃል"

1. **ኤሪስ** = እብድ
2. **ቶረስ** = ግትር
3. **ጀሚኒ** = ሀጻን
4. **ካንሰር** = አልጋ
5. **ሊዮ** = እብሪት
6. **ቪርጎ** = ግርማዊነታቸው
7. **ሊብራ** = ለምን
8. **ስኮርፒዎን** = አስፈሪ
9. **ሳጂታሪየስ** = ጉዞ
10. **ካፕሪኮርን** = እንቅልፋም
11. **አኳርየስ** = ልብ የለሽ
12. **ፓይሰስ** = አይሆንም

13. "በእያንዳንዱ ዞዲይክ ውስጥ ጎልቶ የማይታየው ባህሪይ (የማይታወቅላቸው)"

1. **ኤሪስ** = የፍቅር ሰው ናቸው።
2. **ቶረስ** = ለሰው አሳቢ እና ተንከባካቢ ናቸው።
3. **ጀሚኒ** = ይቅር ባዮች ናቸው።
4. **ካንሰር** = ጠንካሮች ናቸው።
5. **ሊዮ** = ተወዛጋቢ።
6. **ቪርጎ** = ለሰዎች ጥቅም ቅድሚያ የሚሰጡ።
7. **ሊብራ** = ግብዞች ናቸው።
8. **ስኮርፒዮን** = ጥሩ ልብ አላቸው።
9. **ሳጂታሪየስ** = በቀላሉ ይጎዳሉ።
10. **ካፕሪኮርን** = ቧልት ይወዳሉ ግድየለሾች ናቸው።
11. **አኳርየስ** = ስሜታዊ ናቸው።
12. **ፓይሰስ** = ስንፍና ያጠቃቸዋል።

14. "1ምርጥ quality እና 1 ሞጥፎ quality"

1. **ኤሪስ** :------ ጥበበኞች ግን ዝንጉዎች
2. **ቶረስ** :------ ለሰው አሳቢ ግን ዝምተኞች
3. **ጀሚኒ** :------ ቀልደኞች ግን ትዕቢተኛ
4. **ካንሰር** :--------- ስማርት ግን አስመሳዮች
5. **ልዮ** :-------- ስሜታዊ ሰራተኞች ግን አናዳጆች
6. **ቪርጎ** :--------- የፈጠራ ሰዎች ግን ጥንቃቄ አልባ
7. **ሊብራ** :--------- አስቂኝ ግን ድንጉጥ
8. **ስኮርፒዮ** :--------- ጀግኖች ፣ ጀብደኞች ግን ራስወዳድ
9. **ሳጁታሪየስ** :--------- አፍቃሪዎች ግን ግዴለሽ
10. **ካፕሪኮርን** :--------- ልዩ ግን በራሳቸው የማይተማመኑ
11. **አኳርየስ** :--------- ስሜታዊ ሰራተኞች ግን ነጭናጫ
12. **ፒሰስ** :---------- ረጋ ያሉ ግን ግራ የሚያጋቡ

15. “ኮከቦች በፍቅር ሚወድቁለት ነገር”

1. **"ኤሪስ"** ------ ራስ ወዳድ ያልሆኑ፣ አብሮ መስራትን ሚወዱ፣ ምስኪን ፀባይ ያላቸውን እንዲሁም ደጋግ ሰዎችን ይወዳሉ።
2. **"ቶረስ"** --------- ቤተሰባዊነት፣ ታማኝነት፣ ጠንካራና እንዲሁም ፈታ ብሎ ያለፈ ሚስጥራቸውን ሚነግራቸውን ሰው።
3. **"ጀሚኒ"** --------- በዝርዝር (የሚያንፀባርቅ አይን፣ እውነተኛ ፈገግታና ትሪት) እንዲሁም ሚስጥሮችን ሚያጋራቸው ሰው።
4. **"ካንሰር"** -------- ምኞት፣ ሰማያዊ መልክ፣ ወርቃ የሆነ ልብ ያላቸው ሰዎች እና ቅኔአዊ ቀልዶችን።
5. **"ሊዮ"** ---------- ፈጣን፣ ማራኪ ፈገግታ፣ ረጋ ያለ ንክኪ፣ ዝርክርክ ያለ ፀጉርና ኮንፊደንስ ያላቸውን።
6. **"ቪርጎ"** -------- ከግዜ፣ ከሱፍና ከረባት፣ በስራኣቱ ከተስተካከለ ፀጉር፣ መግነጢሳዊ ውበት እንዲሁም ፅድት ካለ ነገር ጋ በፍቅር ይወድቃሉ።
7. **"ሊብራ"** -------- ተጫዋች፣ ቃሉን ሚጠብቅ፣ ጥሩ ቀረቤታ፣ ሚስጥርን መጋራትና የአለኝታናት ቃላት ልውውጥ ማድረግ በሊብራ ነጥብ ያስገኛል።
8. **"ስኮርፒዮ"** ------ አስቂኝ ቀልዶች፣ ትርጉም አዘል ንግግሮች፣ እንዲሁም አንፀባራቂ አይታዎች።
9. **"ሳጁታሪየስ"** --------- ነፃነት፣ Late night conversation ፣ ምርጥ ፈገግታ፣ አሪፍ ስታይል እንዲሁም የሚያምር ከንፈር
10. **"ካብሪኮርን"** ------- ጣፋጭ የሆኑ፣ የደስ ደስ ፣ ቆንጆ ፀጉርና ተነሳሽነት ያላቸው እንዲሁም ደግና ለስራ ተነሳሽ የሆኑ ሰዎችን
11. **"አኳሪየስ"** --------- ጥልቅ የሆነ የአምሮ ግንኙነት፣ አሪፍ ጓደኝነትና ግሩም ስሜት ሚሰጡ ቀልዶችን
12. **"ፓይሰስ"** ------- መሳጭ፣ ሞቅ ያለ፣ የጋለ ሽሙጦችና አስቂኝ ታሪኮች ባለቸው ሰዎች ይመሰጣሉ

16. “ኮከቦች ሚጠሉት ነገር በአንድ መስመር”

1. **ኤሪስ**----------ትክክል እንዳልሆኑ ሲነገራቸው
2. **ጀሚኒ**--------- እንዲረጋጉ ሲነገራቸው
3. **ሊዮ**---------- በሌላ ሰው ሲገለሉ

4. **ሊብራ**--------- ቶሎ ውሳኔ መስጠት
5. **ሳጁታሪየስ**---------- በአንድ ሰርክል ውስጥ ብቻ መወሰን
6. **አኳሪየስ**---------- ህግና ደንብ
7. **ቶረስ**---------- ወደ ማይፈልጉት ነገር ሲገፉ
8. **ካንሰር**---------- በስሜት መነዳት
9. **ቪርጎ**----------የነሱን ነገር ሚነካባቸው ሰው
10. **ስኮርፒዮ**---------ስተታቸውን መቀበል
11. **ካብሪኮርን**--------- የትም ማያደርሱ ነገሮች
12. **ፓይሰስ**---------- ክርክር

17. ከኮቦች ታሪካቸውን በአጭር ቃላት ሲገልፁ

1. **ኤሪስ** — እኔም የሆነ ግዜ ላይ አዛዛኝ ድርጊት ገጥሞኝ ነበር።
2. **ቶረስ** — ፍቅረኛዬ ሙሉ ለሙሉ ቃሉን አልጠበቀም ነበር።
3. **ጀሚኒ** — ለመናገር ፈልጌ ፣ ግን ቃላት አጣው።
4. **ካንሰር** — ሳለቅስ ነበር፣ ምክንያቱም ስለአበዛው።
5. **ሊዮ** — የኔ ኮንፊደንስ ጭንብል ብቻ ነበር።
6. **ቪርጎ** — ሞክርያለው ግን በቂ አልነበረም።
7. **ሊብራ** — ጥልቀት የሌለው ነገር አልወድም ነበር።
8. **ስኮርፒዮ** — ስሜትህን ካልተቆጣጠርከው ትርፉ ህመም ነው።
9. **ሳጁታሪየስ** — የኔ ገነት አምሮዬ ብቻ ነበር።
10. **ካብሪኮርን** — ራሴን ጥብቃለው፣ ምንም ዋጋ ቢያስከፍለኝም።
11. **አኳሪየስ** — ሁሌ ፈገግ በል፣ አንድ ቀን ይቆም ይሆናል ፈገግታህ።
12. **ፓይሰስ** — ቦንብ ነኝ አንድ ቀን ፈነዳለው።

18. "የርሶን ባህሪ ለመረዳት ምን ያህል ጊዜ ይፋጃል?"

1. **ኤሪስ** :-------- 15 ደቂቃ
2. **ቶረስ** :-------- 1 ወር
3. **ጌሚኒ**:-------- 6ወር
4. **ካንሰር**:---------- 2 ሳምንት
5. **ሊዮ**:------------ 1 ስዓት
6. **ቪርጎ**:----------- 2 ወር
7. **ሊብራ**:---------- 3 አመት
8. **ስኮርፕዮ**:-------- 1 አመት
9. **ሳጁታርየስ**:--------- 1 ሳምንት
10. **ካፕሪኮርን**:--------- በዛኑ ሰዓት
11. **አኳርየስ**:------------ 3 ወር
12. **ፒሰስ**:------------ 1:30

19. "ብዘዎቻችን የማናቃቸው አማርኛ የሚመስሉ ግን የባዕድ ሐገር ስሞች ትክክለኛ የአማርኛ ትርጓሜያቸው"

1.ኮሌጅ___መካነ ትምህርት

2. ዩኒቨርስቲ------መካነአምሮ
3. ሌክቸር____ትምህርተ ጉባኤ
4. ሌክቸረር_____መምህረ ጉባኤ
5. ዲን_____ሊቀ ጉባኤ
7. ቢሮ_____መስሪያ ቤት
8. ባንክ_____ቤተ ንዋይ
9. ሲቪል ሰርቪስ____ሰላማዊ አገልግሎት
10. ከስተም_____ኬላ
11. ኮምፒተር____መቀመሪያ
12. ድግሪ___ማዕረግ
13. ሚኒስተር____ምሉክ
14. ማስ ሚዲያ____ምህዋረ ዜና
15. ፎቶ ግራፍ____ብራናዊ ስዕል
16. ራዲዮ____ንፈሰ ድምፅ
17. ፖሊስ___የህግ ዘበኛ
18. ኢንተርኔት___የህዋ አውታር
19. ሎሬት___አምበል፣ ተሸላሚ የቅኔ
20. ዶክተር___ሊቀ ሙህር
21. ኢምባሲ____የእንደራሲ ፅ/ቤት
22. ዲፕሎማት___የመንግስት መልክተኞች
23. ኢኮኖሚክስ___ስነ ብዕል
24. ሀዋላ___ምህዋረ ንዋይ
25. ሳሎን___እንግዳ መቀበያ
26. ቱሪዝም___ስነ ህዋፄ
27. ስካን___ምክታብ
28. ፕሬዝዳንት___ሊቀ ሀገር/ ሙሴ
29. ቴሌኮሚኒኬሽን___ምህዋረ ቃል
30. ቪዛ___የይለፍ ፍቃድ
31. ፓስፖርት___የኬላ ማለፊያ

20. “አባት”

1. የፊዚክስ አባት___ጋሊሊዮ ጋሊሊ
2. የባዮሎጅ አባት___አሪስጣጣሊስ
3. የኬሚስትሪ አባት___ዳቢር ኢብን ሀያን
4. የኤሌክትሪሲቲ አባት___ሚካኤል ማራዳይ
5. የአልጀበራ አባት___ዲዮፋንተስ
6. የጂኦሜትሪ አባት___ኢዩክሊስድ
7. የህክምና አባት _ሂፖክራተስ
8. የጀኔቲክስ አባት___ግሪጎር ሜንዴል
9. የቁጥር አባት___ፊጣጎራዝ
10. የፖለቲካ ሳይንስ አባት_ኒኮስ ማኪያቬሊ
11. የኢኮኖሚ አባት___አዳም ስሚዝ
12. የካልኩለስ አባት___አይዛክ ኒውተን

13. ኮሙኒዝም አባት__ካርል ማርክስ
14. የሬዲዮ አባት___ማርኮኒ
15. የኒውክሌር ፊዚክስ አባት___ሩዝፎርድ
16. የአንጻራዊ ቲዎሪ አባት___አንስታይን
17. የኪንተም ቲዎሪ አባት ___ማክስ ፕላንክ
18. የፔሬዲክ ቴብል አባት___ሜንዴሌቭ
19. የአናቶሚ አባት___ቬሳልየስ
20. የማይክሮክሬዲት አባት___ሞሐመድ የኑስ

21. “የሰውነታችን ብዛት”

- የአጥንታችን ብዛት ~ 206
- የጡንቻዎቻችን ብዛት ~ 639
- የኩላሊቶቻችን ብዛት ~ 2
- የወተት ጥርሶቻችን ብዛት ~ 20
- የጄን አጥንቶቻችን ብዛት ~ 24 (12 ጥንዶች)
- የልባችን ውስጥ ክፍሎች ብዛት ~ 4
- ትልቁ ደም ቅዳ ~ አኦርታ
- ጤናማ የደም ግፊት መጠን ~ 120/80
- የደም ፒ ኤች (PH) መጠን ~ 7.4
- አዲስ የተወለደ ህፃን የአጥንት ብዛት ~ 300
- በጀርባ ላይ የሚገኙ አከርካሪ ብዛት ~ 30
- በአንገት ላይ የሚገኙ አከርካሪ ብዛት ~ 7
- በፊት ላይ የሚገኝ የአጥንት ብዛት ~ 14
- በጭንቅላት ላይ የሚገኝ የአጥንት ብዛት ~ 22
- በደረት ላይ የሚገኝ የአጥንት ብዛት ~ 25
- በክንድ ላይ የሚገኙ የአጥንት ብዛት ~ 6
- በእግር ላይ የሚገኙ የአጥንቶች ብዛት ~ 33
- በእያንዳንድ የእጅ አንጓ (wrist) ላይ የሚገኙ የአጥንቶች ብዛት ~ 8
- በእጅ ላይ የሚገኙ የአጥንቶች ብዛት ~ 27
- በእያንዳንድ ጆሮአችን ላይ የሚገኙ የአጥንቶች ብዛት ~ 3
- በክንድ ላይ የሚገኙ የጡንቻዎች ብዛት ~ 72
- ትልቁ ኦርጋን ~ ቆዳ
- ትልቁ ዕጢ ~ ጉበት
- ትንሹ ሴል ~ የደም ሴል
- ትልቁ ሴል ~ የዕንቁላል ሴል
- ትንሹ አጥንት ~ ሰታፕስ (stapes)
- የመጀመሪያው ንቅለ ተከላ የተደረገው የሰውነት ክፍል ~ ልብ
- አማካይ የትንሹ አንጀት ቁመት ~ 7 ሜትር
- አማካት የትልቁ አንጀት ቁመት ~ 1.5 ሜትር
- አዲስ የተወለደ ህፃን አማካይ ክብደት ~ 2.6 ኪሎ ግራም
- የልብ ምት በአንድ ደቂቃ ውስጥ ~ 72 ጊዜ
- የሰውነት ሙቀት ~ 36.9 ዲግሪ ሴንቲግሬድ (98.4 ዲግሪ ፋራናይት)
- አማካይ የደም መጠን ~ ከ 4-5 ሊትር

- ቀይ የደም ሴል በህይወት የሚቆዮበት ጊዜ ~ 120 ቀናቶች
- የእርግዝና የጊዜ ቆይታ ~ 280 ቀናቶች
- ትልቁ የኢንዶክራይን ዕጢ ~ ታይሮይድ
- ትልቁ የሊምፋቲክ (lymphatic) ዕጢ ~ ጣፊያ
- ግዙፉ ሴል ~ ነርቭ ሴል
- ትልቁ የአእምሮ ክፍል ~ ሰርብረም
- ትልቁና ጠንካራው አጥንት ~ ፌሙር (Femur)
- ትንሹ ጡንቻ ~ ስታፒደስ (Stapedius) (የመካከለኛው ጆሮ)
- በሴል ውስጥ ያለ የክሮሞዞም ብዛት ~ 44 (23 ጥንዶች)
- ትልቁ ጡንቻ ~ መቀመጫ (ቂጥ)

22. "አንድ ፕሮጀክት ቀረፃ ሊያካትታቸው የሚገባቸው ዋና ዋና ነጥቦች"

A. ማውጫ (Table of content)

➢ ገፁ ከሦስት ከበለጠ ማውጫ ሊዘጋጅለት ይገበዋል። ማውጫ ሁሉንም ምዕራፎችና ንዑስ ምዕራፎች ያሉበትን ገፅ ባመላከተ መልኩ መዘጋጀት ይኖርበታል።

B. አጭር መግለጫ (Excutive Summary)

➢ ከግማሽ ገፅ ያልበለጠ ሆኖ ለያካትታቸው የሚገቡ ሃሳቦች፡-

- ፕሮጀክቱ እንዲሰራ ያስገደደው ዋና ችግር
- ፕሮጀክቱ የሚያመጣው ተፅዕኖ
- ለችግሩ የተቀመጠ መፍተሄ
- የፕሮጀክት አዋጭነት የሚያመላክት ግምገማ
- ፕሮጀክቱ የሚያስገኘው ጥቅም
- ፕሮጀክቱ የሚያስፈልገው የገንዘብ መጠንና የሚወስደው ጊዜ መካተት አለባቸው።

C. መግቢያ (Back Ground)

➢ ከአንድ ገፅ ባልበለጠ መገለፅ ሲገባው የሚያካትታቸው ነጥቦች፡-

- ፕሮጀክቱ የሚፈታው ችግር ምን እንደሆነ
- ችግሩን ለምን መፍታት እንዳስፈለገው
- ስለፕሮጀክቱ አጠር ያለ ማብራሪያ የሚሉትን ይይዛል።

D. ፕሮጀክቱ የሚመልሳቸው ችግሮች (Rationale)

➢ ፕሮጀክቱ እንዲሰራ ምክንያት የሆኑ ነገሮች ተሰርተው መገለፅ አለባቸው በተጨማሪም የፕሮጀክቱ አጠቃላይ ግብ ለአንባቢው ግልፅ በሆነ መንገድ መስፈር አለበት።

E. የፕሮጀክቱ ዓላማ (project objective)

➢ ፕሮጀክቱ ሊሰራበት የሚችሉ ዋናውንና ዝርዝር ዓላማዎች ለይቶ ማቅረብ አለበት። ይህም ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ ሊያስገኘው ይችላል ተብሎ የታሰበውን ወጤት መግለፅ ያስፈልጋል።

F. የፕሮጀክቱመግለጫ (project Description)

- የፕሮጀክቱ ስያሜና ዓላማ
- ጉዳዮን የሚያስረዳ ገለፃ

- የፕሮጀክቱ ቀጣይነት
- የፕሮጀክተ የሚተገበርበት ስልት
- ለፕሮጀክቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችና የፕሮጀክቱ የግዜ ሰሌዳ
- ከአስር ገፅ ባልበለጠ መገለፅ አለበት።

G. የፕሮጀክቱ አመራርና አደረጃጀት (project management and organization)

- ፕሮጀክቱን የሚመሩቱና የሚሳተፉ
- የባለሙያዎችን ኃላፊነትና ተግባር
- የፕሮጀክቱን ውስጣዊ አሰራር አደረጃጀት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም መግለፅ አለበት።

H. የፕሮጀክቱ ያገባኛል ባዮችና ተጠቃሚዎች (stakeholders and Beneficiaries):-

- ተጠቃሚዎች(Beneficiaries) ማለት በፕሮጀክቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጠቃሚ የሚሆኑትን ይገልፃል።
- ያገባኛል ባዮች(stakeholders):-

1. **የመጀመሪያ ደረጃ ያገባኛል ባዮች** (**Primary stake holders) ፡-** በፕሮጀክቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በአሉታዊም ሆነ በአወንታዊ ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ወይም በፕሮጀክቱ ላይ የሚያደርሱትን ያካትታል።
2. **የሁለተኛ ደረጃ ያገባኛል ባዮች (secondary stake holders) ፡-** ለፕሮጀክቱ መሰራት የራሳቸው ድርሻና ተፅዕኖ ያላቸው ግለሰቦች፤ ቡድኖችና ተቋማት ተለይተው መዘርዘር አለባቸው።

I. የፕሮጀክቱ ትግበራ (project implementation)

➢ የፕሮጀክት ዕቅድ ማለት የሚሰሩት ስራዎች፤ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ የሀብት ድልድል፤ ስራው በማን፤ እንዴት፤ መቸና የት እንደሚፈፀም መገለፅ አለበት።

J. ሊያጋጥሙ የሚችሉ ስጋትና በጎ ጎኖች (Risk and Assumption)

- ፕሮጀክቱ ተግባራዊ ሲሆን ሊያጋጥሙ ይችላሉ ተብሎ የሚታሰቡ ስጋቶች ይገለፁበታል።
- ለፕሮጀክቱን ተፈፃሚነት የሚያፋጥኑ፤ የሚረዱ በጎ ጎን ያላቸው ነገሮች አብራርቶ በሰንጠረዥ መገለፅ አለበት።

K. ክትትልና ግምገማ (Monitoring and Evaluation)

➢ ይህ ርዕስ የሚይዛቸው፡-

- የስብሰባ ቃለ ጉባኤ፤ የስራ ጉብኝት፤ የማማከር ስራ ሞች እንደሚደረግና በስንት ጊዜ ልዩነት እንደሚቀርብ
- የክትትል ስራ የሚሰራበት ስልት
- የግምገማ ዕቅድን
- ፕሮጀክት እንዴት ለሚመለከታቸው ሪፖርት እንደሚደረግ

L. የፕሮጀክቱ ቀጣይነት (sustainability)

➢ ፕሮጀክቱ የሚሰጠውን ጥቅም ዘላቂነት መገለፅ አለበት።።።

23. "በተለያዩ የስራ መስኮች ፈር ቀዳጅ የሆኑ ኢትዮጵያዊያ ሴቶች"

1. ማሲንቆ ተጨዋች:- **ፋንታዬ ተሰማ**

2. ባለ ሙሉ ሚኒስትር:- **ዶ/ር አዳነች ኪዳነማርያም ሲሆኑ የጤና ጥበቃ ሚኒስትር ነበሩ እና ወ/ሮ መንበረ አለማየሁ ሁለቱም ነሐሴ 4 ቀን 1983 ዓ.ም. ነው የተሾሙት**
3. ዲዛይነር:- **ሳባ አለነ**
4. የውጪ ፀጉር አስተካካይ (ፍሪዘር)ተመራቂ:- **ሜሪ አርምዴ**
5. ሴት አስታማሚ ወይም በዘመናዊ አጠራር ነርስ የሚባሉት የቀዳማዊ ሀይለስላሴ ሴት ልጅ:- **ልዕልት ፀሐይ ሀ/ስላሴ ሲሆኑ በአሁኑ ሰአት ጦር ሐይሎች የሚባለውን ሆስፒታል የመሰረቱት እሳቸው ናቸው።።**
6. የሬዲዮ ጋዜጠኛ:- **ሮማንወርቅ ካሳሁን ሲሆኑ እኚህ ሴት በወቅቱ የማስታወቂያ ፕሮፓጋንዳ መ/ቤት ተብሎ በሚጠራው ስር ይታተም የነበረውን ዝነኛው መፅሔት "መነንን " በማዘጋጀት የመጀመሪያዋ ሴት የመፅሔት አዘጋጅ የሚለውን ድርብ ታሪክ ይጋራሉ።።**
7. አውሮኘላን አብራሪ:- **ወ/ሮ ሙሉ እመቤት እምሩ ሲሆኑ**
8. ለብቻቸው አውሮፕላን ያበረሩት:- **ወ/ሮ አሰገደች አሰፋ ናቸው ጊዜውም 1944 ዓ.ም**
9. ብስክሌት የነዱ:- **እቴጌ ጣይቱ ብጡል**
10. ዳኛ:- **ወ/ሮ አጸደወይን ተክሌ**
11. ሙዚቃቸውን በሽክላ ያሳተሙ:- **እሚሀይ ጽጌማሪያም ገብሩ**
12. የትያትር ተዋናይ:- **ሰላማዊት ገብረ ስላሴ**
13. የፖርላማ ተመራጭ፣ የትምህርት ጥናት ዳይሬክተርና የመጀመሪያዋ በውጭ ሃገር የትምህርት እድል ያገኘኙ:- **ስንዱ ገብሩ**
14. ሴት ሐኪም:- **ውዳድ ኪዳነ ማሪያም**
15. አምባሳደር:- **ዮዲት እምሩ**
16. መሃንዲስ:- **ብርነሽ አስፋው**
17. የአጭር ልብ-ወለድ ደራሲ:- **ወ/ሮ የዝና ወርቁ 1954 ዓ.ም በተሸጠው ሰይጣን የአጭር ልበወለድ መድብል (ጎብረ-ኢትዮጲያ)**
18. የረጅም ልብወለድ ደራሲ:- **ወ/ሮ ፀሐይ መላኩ 1944 ዓ.ም "ቋሳ"**
19. የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር:- **አልማዝ እሸቴ**
20. የኦሎምፒክ ባለወርቅ:- **ሻለቃ ደራርቱ ቱሉ**
21. የመጀመሪያዎቹ ሴት የአየር ትራፊክ ተቆጣጣሪዎች:- **ወ/ሮ ባዩሽ ታደሰና ወ/ሮ ብርቱኳን በቀለ**
22. የመጀመሪያዋ የአ.አ ዩንቨርስቲ ሴት ምሩቅ:- **ፊያሜታ ፕሮታ በ1947**
23. በ1951 ዓ.ም. ከአዲስ አበባ የስነ-ጥበብ ት/ቤት የመጀመሪያዎቹ ተመራቂዎች መሀከል ብቸኛዋ ሴት ሰዓሊ:- **ወ/ሮ ቀፀባ ወርቁ**

24. "ምግቦች ለመፈጨት የሚወስዱት ጊዜ"

1) የወተት ውጤቶች _____ 120 ደቂቃ
2) የበሬ ስጋ ___ 180 ደቂቃ
3) የዶሮ ስጋ ____ ከ90-120 ደቂቃ
4) አሳ ___ ከ45-60 ደቂቃ
5) ድንች _____ ከ90-120 ደቂቃ
6) ፍራፍሬ _____ ከ15-20 ደቂቃ
7) አትክልት _____ ከ30-40 ደቂቃ
8) የተቀቀለ አትክልት _____ 45 ደቂቃ
9) ለውዝ/ አቾሎኒ ____ 180 ደቂቃ

25. “ግንቦት በኢትዮጵያ ታሪክ”

- በአጋጣሚም ይሁን ታስቦበት ግንቦት በኢትዮጵያ ታሪክ በርካታ ድርጊቶች የተፈጸሙበት ወር ነው።
- የገናናው የሸዋ ንጉሥ የንጉሥ ሳህለሥላሴ የልጅ ልጅ፣ የታላቁ ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ ምኒልክ የአክስት ልጅ እንዲሁም የግርማዊ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አባት የሆኑት ልዑል ራስ መኮንን ወልደሚካኤል የተወለዱት በግንቦት መጀመሪያ ቀን በ1844 ዓ.ም ነበር።
- በቀዶ ጥገና ህክምና ዘርፍ የመጀመሪያው ኢትየጵያዊ ሐኪም የሆኑት ፕሮፌሰር ዓስራት ወልደዬስ ያረፉት በግንቦት ወር 1991 ዓ.ም ነው።
- ገናናውና መናኙ የታላቁ አክሱም ንጉሥ አፄ ካሌብ ያረፉት በግንቦት ወር በ20ኛው ቀን ነበር።
- በኢትዮጵያ ፖለቲካ ታሪክ ስማቸው በጉልህ ከሚጠቀሱት እንስቶች መካከል አንዷ የሆኑት የአፄ በካፋ ባለቤት እቴጌ ምንትዋብ ያረፉትም በግንቦት ወር ነው።
- በመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ አፄ ሠይፈአርዕድ እና አፄ እስክንድር ከዚህ ዓለም በሞት የተለዩት በግንቦት ወር ነው።
- የንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ባለቤት እቴጌ ጥሩወርቅ ውቤ ያረፉትም በግንቦት ወር 1860 ዓ.ም ነው።
- አንጋፋውና ዝነኛው ጋዜጠኛ ጳውሎስ ኞኞ ይቺን ዓለም በሞት የተለያት ግንቦት 29 ቀን 1984 ዓ.ም ነው።
- ባለውለታችንና ‹‹የፊደል ገበታ አባት›› ቀኛዝማች ተሥፋ ገብረሥላሴ ግንቦት 26 ቀን 1992 ዓ.ም የዚህ ዓለም የመጨረሻ ቀናቸው ነበረች።
- ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ወራሻቸው የልጅ ልጃቸው ልጅ ኢያሱ ሚካኤል መሆኑን በአዋጅ ያሳወቁት ግንቦት በገባ በ10ኛው ቀን በ1901 ዓ.ም ነው።
- የልጅ ኢያሱ አባት ራስ ሚካኤል አሊ ደግሞ ‹‹ንጉሠ ወሎ ወትግራይ›› ተብለው የነገሡት በግንቦት ወር መገባደጃ ነው።
- የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢ.ህ.አ.ዴ.ግ) አዲስ አበባን የተቆጣጠረውና ስልጣን የያዘውም በግንቦት ወር በ20ኛው ቀን በ1983 ዓ.ም ነው።
- ሊቀመንበር መንግሥቱ ኃይለማርያም አገር ጥለው የሄዱትና ደርግ የወደቀውም በግንቦት ነው።
- የአፍሪካ አንድነት ድርጅት (የአሁኑ የአፍሪካ ኅብረት) እና የአንጋፋው ‹‹አዲስ ዘመን›› ጋዜጣ ምስረታ የተከናወነው በግንቦት ወር ነው።
- እሥራኤል ቤተ-እሥራኤላውያንን ከኢትዮጵያ ወደ እሥራኤል ለመውሰድ ‹‹ዘመቻ ሰለሞን (Operation Solomon)››ን ያካሄደችውም በዚሁ በግንቦት ወር ነው።
- ፎቶ ግራፍና ኢትዮጵያ/ኢትዮጵያውያንም የተዋወቁት ንጉሠ ነገሥት ዳግማዊ አጤ ምኒልክ ግንቦት 13 ቀን 1875 ዓ.ም በተነሱት የመጀመሪያ ፎቷቸው ነው።

26. “የራሳቸው ዘመን አቆጣጠር ያላቸው ሀገራት”

- **ኢትዮጵያ** _አዲሱን 2013 ዓ/ም የጀመረችው ሀገራችን በአፍሪቃ አህጉር የራሷ ካሌንደር ያላት ብቸዋ አገር ነች።
- **እስራኤል**___ በእብራውያን አቆጣጠር 5780ኛው ሮሽ ሀሻናህ (አዲስ አመት) በመስከረም መገባደጃ ይከበራል።
- **ኢራን**__በፐርሺያን አቆጣጠር 1398ኛ አመት ላይ ሲሆኑ አፍጋኖችም ይጠቀሙበታል።
- **ህንድ**__በቡዲስት ካሌንደር 1441 አመት ላይ ይገኛሉ።
- **ቻይና**___በጨረቃ አቆጣጠር 4718 አመት ላይ ሲገኙ ካምቦዲያ፣ ሞንጎሊያ፣ ቪየትናም፣

ላኦስና ሌሎች የእስያ ሀገራትም በቻይኖች አቆጣጠር ይጠቀማሉ።

- **ጃፓን**__32ኛ አመት ላይ ሲገኙ አቆጣጠራቸው በየነገሥታቱ ሲመት ላይ የተመረኮዘ ነው። በዚህም ንጉሥ አኪሂቶ ከነገሱበት ጀምረው 32ኛ አመት ብለው ይቆጥራሉ።
- **ሰሜን ኮሪያ**__ቹቼ ካሌንደር ብለው በሰየሙት አቆጣጠር 109ኛ አመት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ የዘመን ቆጠራ መነሻውን ያደረጉት የሀገሪቱ የዘለአለም አባት ከሚባሉት ኪም ኢል ሱንግ ውልደት ነው።

27. "የአመቱ ወራት ስያሜ"

✓ ከመስከረም እስከ ጳጉሜ የተሰየሙት ወሮቻችን ስያሜያቸውን ከየት እንዳገኙ ያውቃሉ? እስኪ የሚከተለውን ይመልከቱ።

1. **መስከረም (September):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ-----መሴ እና ከረም
   - ትርጉም ---- መሴ-አለፈ፣ ክረምቱ መሸ፤ ከረም--- ክረምት፤ ክረምት አለፈ።
2. **ጥቅምት (October):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ---- ጠቀመ
   - ትርጉም ---- ሠራ፤ ጠቃሚ ጊዜ
3. **ኅዳር (November):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ----- ኀደረ
   - ትርጉም ----- አደረ-ሰው በወርኃ አዝመራ ማሳ ውስጥ ለጥበቃ ማደሩን ይገልፃል።
4. **ታኅሳስ (December):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ----- ኀሠሠ
   - ትርጉም ---- መረመረ--በመኸር ወቅት የሰብል ምርመራን ያመለክታል፤ ሰብዐ ሰገል በታኅሳስ ወር የተወለደውን ጌታችንን ማሰሳቸውን፣ መፈለጋቸውንም ያመለክታል።
5. **ጥር (January):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ----- ነጠረ፣ አጥረየ
   - ትርጉም ----- ነጠረ - ጠረረ- ብልጭ አለ፤ ነጻ፤ የፀሐይን ግለት ወቅት ያሳያል ፤ አጥረየ - ገዛ (ከብቱም ምርቱም የሚሸጥበት የሚገዛበት ወቅት)
6. **የካቲት (February):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ------ ከተተ፣ ከቲት
   - ትርጉም ----- መክተቻ (እኅልን ወደ ጎተራ)
7. **መጋቢት (March):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ---- መገበ
   - ትርጉም ---- በቁሙ የሚመግብ (በጎተራ የተከተተው የሚበላበት)
8. **ሚያዝያ (April):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ---- መሐዘ
   - ትርጉም ---- ኅለመሰ ኅበዘ ሚስት ፈለገ (ወርኃ ሠርግ መሆኑን ሲያጠይቅ)
9. **ግንቦት (May):**
   - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ---- ገነበ
   - ትርጉም ---- ገነባ፤ ሠራ፤ ቆፈረ፤ ሰረሰረ (ለእርሻ የመሬቱን መዘጋጀት ያሳያል)

10. **ሰኔ (June):**
    - የግእዝ ሥርወ ቃሉ --- ሰነየ

- ትርጉም ---- አማረ (አዝርዕቱ)

11. **ሐምሌ (Juliy):**

    የግእዝ ሥርወ ቃሉ ---- ሐመለ

    ትርጉም --- ለመለመ፣ ሐመልማል ሆነ ፣ለቀመ(ለጎመን)

12. **ነሐሴ(August):**
    - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ----- አናሕስየ
    - ትርጉም ---- አቀለለ፤ ተወ (የክረምቱን እያደር መቅለልን ያሳያል)
13. **ጳጉሜ (Shorthen month):**
    - የግእዝ ሥርወ ቃሉ ----- ኤጳጉሚኖስ (ግሪክ)
    - ትርጉም ---- ተጨማሪ ማለት ነው።

28. "ጨረቃ"

- ጨረቃ ከመሬት 384,399 ኪሎ ሜትር ትርቃለች።
- ሙሉ ጨረቃ ከግማሽ ጨረቃ በ 9 እጥፍ ትደምቃለች።
- ጨረቃን ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጠው ሰው ኒል አርምስትሮንግ በግራ እግሩ ነበር ጨረቃን ለመጀመሪያ ጊዜ የረገጠው።
- የጨረቃ ክብደት የመሬትን 0.0123 ነው።
- ጨረቃ በመሬት ዙሪያ ለመዞር 27.321 ቀን ይፈጅባታል።

29. "Hydroelectric Power Plant እንዴት ይሰራል?"

የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጫ ሲገነባ ወሳኙና በጣም አስፈላጊው ነገር በመጓዝ ላይ ከነበረው ውሃ ላይ የተወሰነውን ፐርሰንት "Block" በማድረግ "Reservoir" የማዘጋጀት ስራ ነው። ታዲያ ይሄ ሁሉ ሲሆን ውሃው ግድቡን አቋርጦ መጓዙን አያቆምም፣ ነገር ግን ብዙ ሰዎች ግድብ ሲባል በመጓዝ ላይ የነበረውን ውሃ ሙሉ ለሙሉ ማስቆም ይመስላቸዋል ይህ ግን ስህተት ነው። የግድቡ ሙሌት ስራ ሲጀመር ውሃው ወደ ግድቡ ሲገባ ከነበረው "Natural inlet flow rate" ፍጥነቱንና መጠኑን በመቀነስ ግድቡን ለቆ ይወጣል። ልክ ግድቡ መያዝ የሚችለው የውሃ መጠን ላይ ሲደርስ ወይም የሙሌት ስራው ሲጠናቀቅ የውሃውን "Capacity" እና "Volumetric flow rate" ባገናዘበ መልኩ ከበፊቱ "Outlet flow rate" በመጨመር ውሃው ግድቡን ለቆ ይወጣል። የውሃውን "Outlet flow rate" መጨመር ለምን አስፈለገ? ይህን ማድረግ ያስፈለገበት ትልቁ ምክንያት ግድቡ ከመጠን በላይ ሞልቶ የግድቡ "main structure" ላይ "overloading" ተፈጥሮ "structure" ሩን "damage" አርጎ ጎርፍ እንዳያስከትል በማሰብ ነው።

ታዲያ ይሄ ሁሉ ሲሆን ውሃውን መገደብ ለምን አስፈለገ ብሎ ሚጠይቅ አይጠፋም። ውሃውን መገደብ ያስፈለገበት ምክንያት (Potential energy) የክህሎት ጉልበት ለመፍጠር እንዲረዳ ነው። ታዲያ ይህን ውሃ ዲያሜትራቸው ትልልቅ በሆኑ ትቦዎች (tubes) ወደ ታች በስበት ሀይል (gravitational force) በማስተላለፍ ውሃው "maximum" የሆነ (Kinetic energy) የእንቅስቃሴ ጉልበት እንዲኖረው በማድረግ ከግድቡ በታች በኩል ያሉትን ጀኔሬተሮች በ"turbine" አማካኝነት እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ በ"Electromagnetic induction principle" ኤሌክትሪክ ማመንጨት እና ውሃው ጉዞውን እንዲቀጥል ማድረግ ትልቁ እና ወነኛው ስራ ነው። ይህም ሲሆን "the law of conservation of energy" የተሟላ ነው።

ይህም ME = KE + PE + Loss ይሄ ሁሉ ሲሆን "Potential energy" ወደ "Kinetic energy" ሲቀየር

እና “finally” ይህ “Kinetic energy” ወደ “Electrical energy” ሲቀየር መገንዘብ ይቻላል። ለዚህም ነው። **"Energy neither created nor destroyed just transferred from one form to another"** የሚባለው።

Logo or brand meaning

Nike (ናይክ) ___ የሚለውን ስም ያገኘው ከግሪክ የድል አማልክት ስም በተገናኘ ነው ። በአጭሩ ናይክ የግሪክ አማልክት ስም ነው።
Hyundai (ሃዩንዳይ) _____ በኮሪያ ቋንቋ አዲስ ዘመን ማለት ነው።
Lada (ላዳ) _____ማለት ደሞ የስላቪክ አማልክት ስም ነው።
Coca cola (ኮካ-ኮላ) _____ ስያሜውን ያገኘው ከኮካ ቅጠልና ፍሬ በመሰራቱ ነው።

30. “መስራቾች”

i. **Google** — Larry Page and Sergey Brin
ii. **Facebook** — Mark Zuckerberg
iii. **Yahoo** — David Filo and Jerry Yang
iv. **Twitter** — Jack Dorsey and Dick Costolo
v. **Internet** — Tim Berners Lee
vi. **LinkedIn** — Reid Hoffman, Allen Blue and Koonstantin Guericke
vii. **Email** — Shiva Ayyadurai
viii. **Gtalk** — Richard Wah kan
ix. **Whats up** — Laurel Kirtz
x. **Hotmail** — Sabeer Bhatia
xi. **Wikipedia** — Jimmy Wales
xii. **You tube** — Steve Chen, Chad Hurley and JawedKarim
xiii. **Rediff** — Ajit Balakrishnan
xiv. **Nimbuzz** — Martin Smink and Evert Jaap Lugt
xv. **Myspace** — Chris Dewolfe and Tom Anderson
xvi. **Ibibo** — Ashish Kashyap
xvii. **OLX** — Alec Oxenford and Fabrice Grinda
xviii. **Skype** — Niklas Zennstrom, Janus friis and Reid Hoffman
xix. **Opera** — Jon Stephenson von Tetzchner and Geir Ivarsoy
xx. **Mozilla Firefox** — Dave Hyatt and Blake Ross
xxi. **Telegram** — was started in 2013 by the brothers Nikolai and Pavel Durov.

31. “ከቤርሙዳ ትሪያንግል ጀርባ ያለው ሚስጥራዊ ነገር ምን ይሆን?”

ቤርሙዳ ትሪያንግል በአትላንቲክ ውቅያኖሶች ውስጥ የሚገኝ ከፍተኛ ሀይል እና ስበት ያለው ሚስጥሩ ያልተፈታ ድንቅ ቦታ ነው። ከአሜሪካ ፍሎሪዳ ግዛት ዝቅ ብሎ የሚገኝ ሲሆን በስተ-ደቡብ በኩል ካሪቢያን ደሴት ያዋስነዋል። ቤርሙዳ ትርያንግልን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየው ክርስቶፍር ኮሎምቦስ ነው ዘመኑም 1449 ነበር። አለምን በሚያስስበት ወቅት ቤርሙዳን ሲያይ በመገረም እንዲህ አለ ''በአድማስ ላይ የሚደንስ እንግዳ የሆነ የ ብርሐን ጮራ'' ''በሠማይ ላይ የነገሰ የእሳት ነበልባል'' ''የአቅጣጫ መጦቀሚያ ኮምፓስን የሚያመሠቃቅል ሀይል'' ብሎታል። ታድያ ከዚህ ቦታ ጀረባ ምን ቢኖር ነው

እንዲህ ብርቱና ምታታዊ የሚመስል ክስተትን የሚያሳይ? ይህ ቤርሙዳ ባልታወቀ የስበት ሀይል ሚስጥር በርካታ መርከቦችን አውሮፕላኖችን የሠው ልጅ ህይወትና ሃብት እንደያዙ ድብዛቸውን አጥፍቷል። በመርከብ የሚሄደውን በአውሮፕላን የሚበረውን ወደታች ስቦ ይውጠዋል። የሠመጠው ነገር የት እንደገባ አይታወቅም።

32. "የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ"

1. ስለ ዋቅላሚ (algae) የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ፊኮሎጂ (phycology**
2. ስለ አዕዋፋት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ኦርኒቶሎጂ (Ornithology)**
3. የጀርባ አጥንት ሰለሌላቸው እንስሳት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ማላኮሎጂ (malacology)**
4. ስለ ሰው ልጅ ወይም እንስሳት አካለ መዋቅር የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **አናቶሚ (anatomy)**
5. ስለ ጥገኛ እንስሳት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ፓራሣይቶሎጂ (paracytology)**
6. ስለ ውርስ (heredity) የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ጀነቲክ (genetic)**
7. ስለ ትል (worm) የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ሄልሚንቶሎጂ (helmintology)**
8. ስለ ነፍሳት (insect) የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ኢንቶሞሎጂ (entomology)**
9. ስለ አሣዎች የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ኢክቶሎጂ (ichthyology)**
10. ስለ አጥቢ እንስሳት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ማማሎጂ (mammalogy)**
11. ስለ ፈንገስ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ሚኮሎጂ (mycology)**
12. ስለ ቅሪተ አካል (fosil) የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ፓሊኦንቶሎጂ (paleontology)**
13. ስለ ፈርን የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ቴሪዶሎጂ (pteridology)**
14. አንድ ሴል ስላላቸው እንስሳት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ፕሮቶዞሎጂ (protozology)**
15. ስለ ባክቴሪያ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ባክቴሪዮሎጂ (bacteriology)**
16. ስለ ቫይረስ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ቪሮሎጂ (virology)**
17. ስለ ሽል ለውጥ እና እድገት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ኢምብሪዮሎጂ(embryology)**
18. ስለ ዝግመተ ለውጥ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ኢቮሉሺን (evolution)**
19. ስለ እንስሳት እና እፅዋት ህብረ ህዋስ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ሂስቶሎጂ (Histology)**
20. ስለ ሰው ልጅ አመል/ባህሪ የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ? **ኢትኖሎጂ (ethnology)**

33. "የዳግማዊ ዓፄ ሚኒሊክ 175ኛ አመት የልደት በዓል እየተከበረ ይገኛል ለኢትዮጵያ ካበረከቷቸው አበይት ስራዎች መካከል ጥቂቶቹን እነሆ"

- ✓ 1882 ዓ.ም_____ስልክ
- ✓ 1886 ዓ.ም_____ፖስታ
- ✓ 1886 ዓ.ም_____ባህር ዛፍ
- ✓ 1886 ዓ.ም_____ገንዘብ
- ✓ 1886 ዓ.ም_____የውሃ ቧንቧ
- ✓ 1887 ዓ.ም_____ጫማ
- ✓ 1887 ዓ.ም____ድር
- ✓ 1887 ዓ.ም____የሙዚቃ ት/ቤት
- ✓ 1887 ዓ.ም____የፅህፈት መኪና
- ✓ 1889 ዓ.ም____ኤሌክትሪክ
- ✓ 1889 ዓ.ም____ዘመናዊ ህክምና

- ✓ 1889 ዓ.ም___ሲኒማ
- ✓ 1889 ዓ.ም___የሙዚቃ ሽክላ
- ✓ 1889 ዓ.ም___ቀይ መስቀል
- ✓ 1890 ዓ.ም__ሆስፒታል
- ✓ 1893 ዓ.ም___ባቡር
- ✓ 1893 ዓ.ም___ብስክሌት
- ✓ 1896 ዓ.ም___መንገድ
- ✓ 1897 ዓ.ም___ፍል ውሃ
- ✓ 1898 ዓ.ም___ባንክ
- ✓ 1898 ዓ.ም___ሆቴል
- ✓ 1898 ዓ.ም___ማተሚያ
- ✓ 1898 ዓ.ም____ላስቲክ
- ✓ 1899 ዓ.ም___አራዊት ጥበቃ
- ✓ 1899 ዓ.ም__የጥይት ፋብሪካ
- ✓ 1900 ዓ.ም___ጋዜጣ
- ✓ 1900 ዓ.ም___አውቶሞቢል
- ✓ 1900 ዓ.ም___የሚኒስትሮች ሹመት

34. "ከእንስሳት ዓለም"

- ✧ ቀበሮ በሂወት ዘመኑ አንዴ ብቻ ነው ፍቅረኛ ሚኖረው። ምን አልባት ሚስቱ ከሞተች ቀሪ ሂወቱን ብቻውን ነው የሚያሳልፈው! ምስኪን ታማኝ።
- ✧ የጂብ እድሜ ጣራ 80 ዓመት ነው።
- ✧ አይጦች የራሳቸውን ያልሆነ ልጅ አጥብተው ያሳድጋሉ።
- ✧ የወባ ትንኝ 47 ጥርሶች አላት።
- ✧ ፍየሎች ሴቷን ፍየል ለማማለል ሲሉ እርስበእርስ ይዋጋሉ።
- ✧ ድመት በሂወት ዘመኗ እስከ 100 ግልገሎች መውለድ ትችላለች።
- ✧ እንደ ሰው ህልም ማየት ሚችለው አንስሳ ፈረስ ብቻ ነው።
- ✧ ዳክየ እንቁላል የምትጥለው ጧት ጧት ብቻ ነው።
- ✧ የሌሊት ወፍ ጆረዋ ከተደፈነ መብረር አትችልም።
- ✧ ጊንጥ 12 አይኖች አላት።
- ✧ አዞ ምላሱን ወደውጭ ማውጣት አይችልም።
- ✧ ሴት ካንጋሮ ከወንዱ ምትለየው በደረቷ ባለው ከረጢት ነው።
- ✧ አይጥ ያለ ምግብ 14 ቀን መቆየት ትችላለች።
- ✧ አለም ላይ የመጀመሪያው ለማዳ እንስሳ ውሻ ነው።
- ✧ የጊንጥ መርዝ ጊንጥን ሲገድል የእባብ መርዝ ግን እባብን አይገድልም።
- ✧ በአንድ ጉንዳን መንጋ ውስጥ እስከ ግማሽ ሚሊየን ጉንዳኖች ሊኖሩ ይችላሉ።
- ✧ ማንኛውም ስጋ በል እንስሳ በመብረቅ ተመትቶ የሞተን እንሰሳ አይበላም።
- ✧ ቢራቢሮ 12, 000 አይኖች አሏት።
- ✧ የመሬት ትል 5 ልቦች አሏት።

35. "SOME AFRICAN COUNTRIES AND THEIR SLOGANS"

1. **South Africa** ----- Rainbow Nation.

2. **Rwanda** ------ Land of a Thousand Hills.
3. **Madagascar** ----- The Red Island.
4. **Lesotho** ------ The Kingdom in the Sky.
5. **Egypt** ------ The Gift of the Nile.
6. **Burkina Faso** ----- Land of the Upright Men.
7. **Ghana** ----- The gateway to Africa / Stars of Africa.
8. **Nigeria** ------ The Giant of Africa.
9. **Namibia** ------- Land of the Brave.
10. **Uganda** ------ The Pearl of Africa.
11. **Malawi** ------- The Warm heart of Africa.
12. **Zambia** ------- The real Africa.
13. **Kenya** ----- The pride of Africa.
14. **Tanzania** ------- Brain of Africa (Bongo)
15. **Gambia** ------ The smiling coast of Africa.
16. **Ethiopia** ------ The land of origin.
17. **Burkina faso** ------ The land of upright men.
18. **Morroco** ----- The land of colours.
19. **Mauritius** ------ The continental island.
20. **Comoros** ------- The perfum island
21. **Sierra leone** ------ Salon.
22. **Chad** ------- The dead heart of Africa.
23. **Mali** ------- The eyes of Africa.
24. **Djibouti** ------ The pearl of the gulf of tadjiboura.
25. **Cape Verde** ------ Ilha do.
26. **Sao tome and Principe** ------ The chocolate island.
27. **Cameroun** ---------- The hinge of Africa.
28. **Seychelles** ------ The land of perpetual summer.
29. **Gabon** --------- Le bled.
30. **Somali** -------- The horn of Africa.
31. **Botswana** -------- Peaceful nation.

36. "Famous brands' names and their meaning"

- **Coca Cola**----------The two main ingredients were Coca leaves and Cola berries.
- **Pepsi**----------Pay every pence spending on it.
- **Google**---------- Derived from 'googol' which means 1 followed by 100 zeros.
- **Adidas**---------Named after owner Adolf Dassler whose nickname was Adi. Adi Dassler became Adidas.
- **Amazon**---------CEO Jeff Bezos wanted a name starting with 'A'. He chose Amazon because it is the biggest river in the world, just what he wanted his company to be.
- **Sony**----------Derived from the Latin word, 'Sonus' (meaning sound) and an

American slang word, 'Sonny' (meaning bright youngster).

- **Volkswagen**----------Means 'People's car' in German.
- **Fanta**--------The head of the German Coca-Cola team asked them to use their 'Fantasie' (imagination) to come up with the name. That did not take long though.
- **HP (Hewlett Packard)** ----------William Hewlett and David Packard flipped a coin to decide whose name would come first.
- **Microsoft**---------A combination of the words Microcomputer and Software.

37. "List of Inventions and Discoveries"

1. **Blood Group**_____Karl Lansdsteiner
2. **Airplane**_____Wilber and Orville Wright
3. **Gramophone**_____Thomas Edison
4. **Hydrogen**_____Henry Cavendis
5. **Insulin**_____Sir Frederick Banting
6. **Light Bulb**_____Thomas Edison
7. **Motorcycle**_____Gottlieb Daimler
8. **X-ray**_____Wilhelm Conrad Roentgen
9. **Theory of Evolution**_____Charles Darwin
10. **Penicillin**_____Alexander Fleming
11. **Polio Vaccine**_____Jonas Edward Salk
12. **Printing Press**_____Johannes Gutenber
13. **Dynamo**_____ Michael Faraday
14. **Nuclear Reactor**_____Enrico Fermi
15. **Atom Bomb**_____Julius Robert Oppenheimer

38. "SI Units"

- **Force**_____Newton (N)
- **Frequency**_____Hertz (Hz)
- **Inductance**_____Henry (H)
- **Electric charge**_____Coulomb (C)
- **Electric potential (Voltage)**_____Volt (V)
- **Capacitance**_____Farad (F)
- **Magnetic flux**_____Weber (Wb)
- **Resistance**_____Ohm (Ω)
- **Magnetic flux density**_____Tesla (T)
- **Energy, Work and Heat**_____Joule (J)
- **Power**_____Watt (W)
- **Angle**_____Radian (rad)
- **Radioactivity**_____Becquerel (Bq)
- **Luminous flux**_____Lumen (lm)
- **Radiant flux**_____Watt (W)

39. What is the planet of ____?

- Smallest----------**Mercury**
- Biggest----------**Jupiter**
- Coldest----------**Neptune**
- Hottest----------**Venus**
- Closest to Sun----------**Mercury**
- Farthest from Sun----------**Neptune**
- Densest----------**Earth**
- Fast Rotation ----------**Jupiter**
- Slow Rotation----------**Venus**
- Fast Revolution ----------**Mercury**
- Slow Revolution ----------**Neptune**

40. " Nine planet's"

ኣጣርድ ወይም ሜርኩሪ___ መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፈለክ ነው። ይህ ፈለክ ከ ፀሐይ ባለው ርቀት ቅርቡ (1ኛው) ነው። ከበስተኋላው ዘጠኙም ፈለኮች ማለትም ቬነስ ፣ መሬት፣ ማርስ፣ ጁፒተር ፣ ሳተርን፣ኡራኑስ ፣ ነፕቲዩን እና ፕሉቶ ይገኛሉ። ስሙ «ኣጣርድ» የተወረደ ከ አረብኛው «ኡጣሪድ» ነበር። በድሮ ጊዜ ይህ የአረመኔ ጣዖት ስም ነበር። ሙሽሩኮች ይህ የጥበብ ጣኦት እንደ ነበር ስላመኑ፣ የፈለኩ ስም ከዚህ ጣኦት ስም መጥቶ በየቋንቋው ይለያይ ነበር።

ስለዚህ የፈለክም ሆነ የጣኦት ስም በ ፋርስኛ «ቲር»፣ በባቢሎንኛ «ናቡ»፣ በ ጥንታዊ እንግሊዝኛ «ዎደን»፣ በ ግሪክ «ሄርሜስ»፣ በ ሮማይስጥም «ሜርኩሪዩስ» ሆነ። «ሜርኩሪ» የሚለው እንግሊዝኛ ሲሆን ከዚሁ ሮማይስጥ ስም መጣ። በ ዕብራይስጥ ግን ስሙ «ኮካብ ሐማህ» ወይም «የፀሐይ ኮከብ» ይባላል። ይህ ፈለክ በዚህ ረጨት ውስጥ ከሚገኙ ፈለኮች በመጠኑ ትንሹ ነው። ዲያሜትሩ 2439.7 ኪ.ሜ ብቻ ነው። መዋቅሩ ከመሬት ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ቋጥኞች የበዙበት ነው።

ዘሃራ ወይም ቬነስ____መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፈለክ ነው። ይህ ፕላኔት ከ ፀሐይ ባለው ርቀት ሁለተኛ (2ኛው) ቅርቡ ነው። ከበስተኋላው ሰባቱ ፈለኮች ማለትም መሬት፣ ማርስ፣ ጁፒተር፣ ሳተርን ኡራኑስ፣ ነፕቲዩን እና ፕሉቶ ይገኛሉ። ከፊቱ የምትገኘው ብቸኛዋ ፈለክ ኣጣርድ ናት። ዘሃራ የሚለው ስም በዐረብኛ «ዙህራ» ሲሆን ይህ ማለት ቁንጅና ወይም አበባ ነው። በአንድ ጥንታዊ የአረብ ትውፊት ዘንድ ዙህራ የተባለች ሴት በተዓምር ፈለክ ሆነች። አረቦች ይህን ትውፊት ከአይሁዶች፣ አይሁዶችም ከ ባቢሎን ሰዎች እንደ ተበደሩት ይታመናል። በኩፋሮች ዘንድ ፈለኩ የፍቅር ጣዖት ስም ይባል ነበር፤ በ እንግሊዝኛ ቬነስ የሚለው ስም የሮማይስጥ የጣዖት ስም ነው። በ እብራይስጥ ደግሞ ለዚሁ ፈለክ ያለው ስም «ኖጋህ» ሲሆን ይህ በ አማርኛ ማለት «ንጋት» ነው (የንጋት ኮከብ)።

ይህ ፈለክ በመሬት ሰማይ ላይ ከሚታዩ አካላት እንደ ጨረቃ ሁሉ ግዙፉ አካል ነው። ይህን ፈለክ ለማየት ጥሩ ጊዜ የሚሆነው ጠዋት ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት እንዲሁም ማታ ፀሐይ ከጠለቀች በኋላ ነው። ፈለኩ በነዚህ ሁለት ጊዜያት በደማቅ ቀይ ብርሃኑ ተለይቶ ይታወቃል። የተሰራው ከ መሬት ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ ቋጥኝ ከበዛበት አካል ነው። ይህም ባህሪው ከ ሶስቱ ፈለኮች ማለትም ከሜርኩሪ፣

መሬት እና ማርስ ጋር ተመሳሳይ ባህሪ እንዲኖረው ያደርገዋል። እነዚህ በአንድነት በኢንግሊዝኛው ተሬስትሪያል ፈለኮች በመባል ይታወቃሉ።

መሬት (Earth) _____ በ ሥርዓተ ፀሐይ ውስጥ ከ ፀሐይ ባላት ርቀት ሶስተኛ (3ኛ) በግዝፈት ደግሞ ከ ፕላኔቶች ሁሉ አምስተኛ ግዙፍ የሆነች ፈለክ ናት። በግዝፈት እና በይዘት ቋጥኛዊ ይዘት ካላቸው ወይንም በ እንግሊዝኛ ው ተሬስትሪያል ፈለኮች ከሚባሉት የመጀመሪያውን ደረጃ ትይዛለች። በተለምዶ ዓለም ወይም ምድር እየተባለች ትጠራለች። በሳይንሳዊ የተለምዶ ስም ደግሞ «ሰማያዊዋ ፕላኔት» እየተባለች ትጠራለች።

ይህች ፕላኔት የሰው ልጅን ጨምሮ ለብዙ ሚሊዮን ዝርያዎች መኖሪያ ናት። ከምድር ብዛት (ከ ላይ አፈር) አትክልት ሁሉ እየበቀሉ ሲሆን ለሰው ልጅና ለእንስሳ ያስፈለጉት እህል፣ ፍራፍሬ፣ መድኃኒቶችና ሌሎችም ሁሉ ታስገኛለች። ይህም የታወቀች ብቸኛዋ ህይወት ያለው ነገር መኖሪያ ያደርጋታል። ስለዚህ ነው በተለያዩ እምነቶች ዘንድ ምድራዊት እማማችን የተባለችው።

ማርስ ወይም ቀይዋ ፈለክ_____መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፈለክ ነው። ይህ ፈለክ ከ ፀሐይ ባለው ርቀት 4ኛ (አራተኛ) ነው። ከበፊቱ ሜርኩሪ፣ ቬነስ እና መሬት የተባሉ ፈለኮች ይገኛሉ። ከበስተኋላው ደግሞ ጁፒተር፣ ሳተርን፣ ኡራኑስ፣ ነፕቲዩን እና ፕሉቶ የተባሉት ይገኛሉ።

ይህ ፈለክ በዚህ ረጨት ውስጥ ከሚገኙ ፕላኔቶች በግዝፈቱ የስድስተኛ ደረጃን ይይዛል። እስከ ቅርብ ግዜ ድረስ ህይወት ያለው ነገር ይኖርበታል ተብሎ ሲታመን ቆይቷል። ነገር ግን በቅርቡ የወጡ መረጃዎች ህይወት ያለው ነገር እንዳልተገኘ «ኢኮነም ድሉተ» መሆኑን ያመላክታሉ። በአብዛሃኛው በካርቦንዳይኦክሳይድ የተሞላ ቢሆንም በአንጻራዊ ሁኔታ ለ ህይወት ያላቸው ነገሮች ምቹ የሆነ ከባቢ አየር አለው። መጠኑ ከመሬት ያንሳል። በተለምዶ ቀይዋ ፈለክ እየተባለች ትጠራለች።

ጁፒተር (Jupiter)_____ መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፕላኔት ነው። ይህ ፈለክ ከ ፀሐይ ባለው ርቀት 5ኛ (አምስተኛ) ነው። ከበፊቱ ሜርኩሪ፣ ቬነስ ፣ መሬት እና ማርስ የተባሉ ፈለኮች ይገኛሉ። ከበስተኋላው ደግሞ ሳተርን ፣ ኡራኑስ ፣ ነፕቲዩን እና ፕሉቶ የተባሉት ይገኛሉ።

ይህ ፈለክ በዚህ ረጨት ውስጥ ከሚገኙ ፈለኮች በግዝፈቱ የመጀመሪያውን ደረጃ ይይዛል። ግዙፍ የ ጋዝ ክምችት እንደሆነ ይታመናል። ይህም የጸሃይን አንድ አንድ ሺኛ (1/1000ኛ) ብቻ ክብደት እንዲኖረው ያደርገዋል። ነገር ግን የሌሎቹን ፈለኮች ድምር ክብደት በሁለት ከግማሽ እጥፍ (2.5x) ይሆናል። በረጨቱ ውስጥ የጋዝ ክምችት የሆኑት ፈለኮች ሳተርን፣ ኡራኑስ፣ ነፕቲዩን እና ራሱ ጁፒተር ናቸው። በአብዛሃኛው ሃይድሮጅን ከተባለ ጋዝ እና ሩቡን (1/4 ኛውን) ክብደት ከሚይዘው ሂሊየም ከተባለ ንጥረነገር የተሰራ ነው። ጁፒተር ስልሳ ሦስት ጨረቃዎች አሏት። ከእነዚህ ውስጥ አራቱ ማለትም አዮ ፣ዩሮፓ፣ ጋኒሜድ እና ካሊስቶ የጋሊሊዮ ጨረቃዎች በመባል ይታወቃሉ።

ሳተርን (ማህፈድ) _____መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፕላኔት ነው። ይህ ፕላኔት ከ ፀሐይ ባለው ርቀት 6ኛ (ስድስተኛ) ነው። ከበፊቱ ሜርኩሪ፣ ቬነስ ፣ መሬት፣ ማርስ እና ጁፒተር የተባሉ ፕላኔቶች ይገኛሉ። ከበስተኋላው ደግሞ ኡራኑስ ፣ ነፕቲዩን እና ፕሉቶ የተባሉት ይገኛሉ። ይህ ፕላኔት በዚህ ረጨት ውስጥ ከሚገኙ ፕላኔቶች በግዝፈቱ የሁለተኛነትን ደረጃ ይይዛል።

ግዙፍ የ ጋዝ ክምችት እንደሆነ ይታመናል። በረጨቱ ውስጥ የጋዝ ክምችት የሆኑት ፕላኔቶች ጁፒተር ፣ ኡራኑስ ፣ ነፕቲዩን እና ራሱ ሳተርን ናቸው። በዚህም የተነሳ ጆቪያን ወይም ጁፒተርን መሳይ እየተባለ ይጠራል። በአብዛሃኛው ሃይድሮጅን ከተባለ ጋዝ እና በ ጥቂት መጠን ሂሊየም ከተባለ ንጥረነገር የተሰራ ነው። ፕላኔቱ በተለይም ዙሪያውን በሚገኙ በቀለበቶቹ ይታወቃል። እነዚህ ቀለበቶች ከሳተርን ወገብ ከ6630 ኪ.ሜ እስከ 120700 ኪ.ሜ ርቀት ድረስ ይገኛሉ። በአማካይ እያንዳንዳቸው እስከ 20 ሜ ድረስ ወፍረት ያላቸው ቀለበቶች ናቸው። የተሰሩት በአብዛሃኛው ከውሃ፣ ከበረዶ እና ከሌሎች ንጥረ ነገሮች ነው።

ኡራኑስ_____ መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፕላኔት ነው። ይህ ፕላኔት ከ ፀሐይ ባለው ርቀት 7ኛ (ሰባተኛ) ነው። ከበፊቱ ኣጣርድ ፣ ቬነስ ፣ መሬት፣ ማርስ፣ ጁፒተር እና ሳተርን የተባሉ ፕላኔቶች ይገኛሉ። ከበስተኋላው ደግሞ ነፕቲዩን እና ትንሹ ፕሉቶ ይገኛሉ።

ይህ ፕላኔት በዚህ ረጨት ውስጥ ከሚገኙ ፕላኔቶች በግዝፈቱ የሶስተኛነትን ደረጃ ይይዛል። ግዙፍ የጋዝ ክምችት እንደሆነ ይታመናል። በ ረጨቱ ውስጥ የጋዝ ክምችት የሆኑት ፕላኔቶች ጁፒተር፣ ነፕቲዩን፣ ሳተርን እና ራሱ ኡራኑስ ናቸው። በዚህም የተነሳ ጆቪያን ወይም ጁፒተርን መሳይ እየተባለ ይጠራል። በአብዛሃኛው ሃይድሮጅን እና ሂሊየም ከተባሉ ንጥረነገሮች የተሰራ ነው። በአጠቃላይ ክብደቱ ደግሞ የአራተኛነትን ደረጃ የያዘ ነው።

ነፕቲዩን (Neptune)_____ መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፕላኔት ነው። ይህ ፕላኔት ከ ፀሐይ ባለው ርቀት 8ኛ (ስምንተኛ) ነው። ከበፊቱ ኣጣርድ ፣ ቬነስ ፣ መሬት፣ ማርስ፣ ጁፒተር፣ ሳተርን እና ኡራኑስ የተባሉ ፕላኔቶች ይገኛሉ። ከበስተኋላው ደግሞ ትንሹ ፕሉቶ ይገኛል።

ይህ ፕላኔት በዚህ ረጨት ውስጥ ከሚገኙ ፕላኔቶች በግዝፈቱ የአራተኛነትን ደረጃ ይይዛል። ግዙፍ የ ጋዝ ክምችት እንደሆነ ይታመናል። በረጨቱ ውስጥ የጋዝ ክምችት የሆኑት ፕላኔቶች ጁፒተር፣ ኡራኑስ፣ ሳተርን እና ራሱ ነፕቲዩን ናቸው። በዚህም የተነሳ ጆቪያን ወይም ጁፒተርን መሳይ እየተባለ ይጠራል። በአብዛሃኛው ሃይድሮጅን እና ሂሊየም ከተባሉ ንጥረነገሮች የተሰራ ነው።

ፕሉቶ (Pluto)_____መሬት በምትገኝበት ማለትም ሚልክ ዌይ ተብሎ በሚጠራው ረጨት ወይም የከዋክብት ስብስብ ውስጥ የሚገኝ ፕላኔት ነው። ይህ ፕላኔት ከ ፀሐይ ባለው ርቀት 9ኛ (ዘጠኛ) ነው። ከበፊቱ ሁሉም ፕላኔት ማለትም ኣጣርድ፣ ቬነስ፣ መሬት፣ ማርስ፣ ጁፒተር፣ ሳተርን፣ ኡራኑስ እና ነፕቲዩን ይገኛሉ። በዚህም ርቀቱ ትክክለኛ ምስሉ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ሊገኝ አልቻለም። አሁን የሚገኘው ምስል በጊዜው ባለው ከፍተኛ ቴክኖሎጂ የተገኘ ነው። ክዚህ በላይ የጠራ ምስል ሊገኝ አልቻለም። ራሳቸውን ችለው በ ፀሐይ ዙሪያ ሊንቀሳቀሱ የሚያስችላቸው ይዘት ያላቸው ወይንም በእንግሊዝኛው ድዋርፍ ፕላኔትስ ከሚባሉ አካላት አንዱ ነው። ይህ አካል ፕላኔት መሆኑ የተረጋገጠው በቅርብ ግዜ ነው።

41. “በኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ሥርዓት ውስጥ የነበሩ መዓረጋትና የመዓረጋቱ ተዋረድ”

1. ራስ ቢትወደድ _ የንጉሥ አማካሪ
2. ራስ _ የሰፋፊ ግዛት ጠቅላይ ግዛት ተሿሚ
3. ደጃዝማች _ የአራትና የአምስት ሻምበል ኃላፊ
4. ሊጋባ _ የንጉሠ ነገሥቱ ዋና አጋፋሪ የሚጠራበት

5. ፊት አውራሪ _ የጦር ሚኒስተሩ ማዕረግ
6. አጋፉሪ _ የሊጋባው ምክትል
7. ቀኝ አዝማች _ የሻንበል የበላይ
8. ባልደራስ _ የንጉሡን በቅሎና ፈረስ የሚጭን አለቃ
9. ባሻ _ የሻንበሎች ሁሉ ስም
10. በሰላማዊ ክፍል የሚሰጥ የማዕረግ ስምና የደረጃ ተዋረድ
11. ቢትወደድ _ እንደ ጠቅላይ ሚኒስትር ያለ
12. አፈ ንጉሥ _ የፍርድ ሚኒስተር
13. ጸሐፊ ትዕዛዝ _ የጽሕፈት ሚኒስተር
14. አዛዥ _ የግቢ ሚኒስተር
15. በጅሮንድ _ የገንዘብ ሚኒስተር
16. ነጋድራስ _ የንግድ ሚኒስተር
17. ብላቴን ጌታ _ በልዩ ልዩ የሚኒስተር ሥልጣን ላገኙ የሚሰጥ
18. ሊቀ መኪስ _ ንጉሠ ነገሥት በነገሡና ጉባኤ ባደረጉ ጊዜ በግራና በቀኝ የሚቆሙ
19. ባላታ _ በየ ስራ ክፍል ያሉ ጠቅላይ ዳይሬክተሮች የሚሰጥ
20. ልጅ _ የመኳንት ልጅ የሚጠሩበት
21. መርዕድ _ አዝማችና አቤት አልጋ ወራሽ ለሆኑ (ላልሆኑ) ልጆች የሚሰጥ ስም

42. “ስለ ሚልኪዋይ ጋላክሲያችን አንዳንድ እውነታዎች”

1) ሚልኪዌይ ከሌሎች ጋላክሲዎች የተሰራ ነበር።
2) ሚልኪዌይ ዳርክ ማተር አለው ግን በቀጥታ ሊያዩት አይችሉም።
3) ሚልኪዋይ ጋላክሲ የቪርጎ ሱፐርክላስተር ጋላክሲ ቡድን አካል ነው።
4) የእኛን ሚልኪዌይ ጋላክሲን ሙሉ በሙሉ ማየት አንችልም።
5) የእኛ ሚልኪዋይ ጋላክሲ ከ 200 ቢሊዮን በላይ ኮከቦች አሉት።
6) በእኛ ጋላክሲ ማእከል ግዙፍ ብላክ ሆል አለ።
7) ሚልኪዌይ ጋላክሲ በ 4 ቢሊዮን ዓመታት ውስጥ ከአንድሮሜዳ ጋላክሲ ጋር ይጋጫሉ።
8) የሚልኪዌይ ጋላክሲ ዕድሜ ልክ እንደ ዩኒቨርስያችን እድሜ ነው ።
9) የእኛ ሚልኪዌይ ጋላክሲ በሴኮንድ በ 600 ኪ.ሜ አማካይ ፍጥነት በ Space ውስጥ እየተንቀሳቀሰ ነው ።
10) ሚልኪዌይ ጋላክሲ ስሙ የተገኘው ከግሪክ አፈታሪክ ነው ።

43. “በኛ ሶላር ሲስተም ውስጥ የሚገኙ አስደማሚ እውነታዎች”

- ፕላኔት ሳተረን በኛ ሶላር ሲስተም ውስጥ ብዙ ጨረቃዎች ያሉት ፕላኔት ሲሆን በዙሪያው ከ81 በላይ ጨረቃዎቹ ይገኛሉ።
- በኛ ሶላር ሲስተም ውስጥ ከሚገኙ ጨረቃዎች መካከል ጋናሜድ ተብሎ የሚጠራው የጁፒተር ጨረቃ ከፕላኔት ሜርኩሪ በክብደት ይበልጣል። ጨረቃ ላይ የሚገኘው የሰው ልጆች የጫማ አሻራ በጭራሽ አይጠፋም ምክንያቱም ጨረቃ ላይ ምንም አይነት ንፋስ ባለመኖሩ ነው። ታይተን የተሰኘቹ የኔፕቱን ጨረቃ ባልተለመደ መለኩ ፕላኔቱን በግራ በኩል ነው የምትዞረው ነገረ ግን ይሄ ጨረቃ ለምን ከሌሎች ጨረቃዎች አንፃር በተቃራኒ እንደሚዞር የሚታወቀ ነገረ የለም ይሁን እንጂ አንዳድ መላምቶች ይሄ ጨረቃ በአስትሮይድ ድብደባ ምክንያት የእሽክርክሪቱን አቅጣጫ በተቃራኒ በኩል እንዳደረገ ይገምታሉ።
- የፕላኔት ፑሉቶ ጨረቃ በክብደት የፕላኔቱን ግማሽ የሚሆን ሲሆን ይህም ፕላኔቶ በራሱ ዛቢያ

ሲሽከረከር የራሱን አክሰስ እንዳይጠብቅ አድርጎታል።

- ❖ ፕላኔት ጁፒተር የኛን አለም በክብደት 318 ጊዜ የሚያጥፍት ሲሆን አጠቃላይ በኛ ሶላር ሲስተም ውስጥ የሚገኙት ፕላኔቶች ተደምረው የሚሰጡትን፡- ክብደት ደግሞ በ2.5 እጥፍ ጊዜ ይበልጣል።
- ❖ የኛ ፀሐይ ፕላኔቶችን ወደራሷ ትሰባለች በተመሳሳይ ፕላኒቶችም ይሄን የፀሐይ ጉልበት የሚቃረን የስበት ሐይልን ይጠቀማሉ በስተመጨረሻ የጓታች እና የሳቢ ሐይል እኩል ሲሆን ፕላኔቶቹ ጠፈር ላይ ፀሐይን እየዞሩ ይቀራሉ።
- ❖ ጠፈር የሚባለው አከባቢ ከኛ ምደር 62 ማይሎችን ብቻ የሚርቅ ሲሆን መኪናን ወደ ላይ እየነዳን አንድ ሳሀት ባለሞላ ጊዜ ውስጥ እዚህ ቦታ መድረስ እንችላለን።
- ❖ የሰው ልጆች ጠፈር ላይ የምንኖሩ ቢሆን ኑሮ ምድር ላይ ካለን ቁመት በ5cm ከፍ ያለ ቁመት ይኖረን ነበር።
- ❖ ፕላኔት ፕሉቶ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲገኝ ፕላኔት ቢባልም በ2006 ግን ከፕላኔትነት ተሰርዞ ዱዋርፍ ፕላኔት ተብሏል ይሄ ዱዋርፍ ፕላኔት የቆዳ ስፍቱ በጣም ትንሽ ሲሆን ከአሜሪካ አህጉር ወይም "North America " ጋር እኩል ነው።
- ❖ ማታ ላይ የሚታዩት ሁሉም አብረቅራቂ ነገሮች ኮከቦች ላይሆኑ ይችላሉ ምክንያቱም ፕላኔት ሜርኩሪ ቬኑስ ማርስ ጁፒተር ሳተርን እንዲውም የተለያዩ ሰው ሰራሽ ሳተላይቶች ልክ እንደክዋክብት ሊያበሩ ይችላሉ።
- ❖ የውሃ በረዶ በኛ ምድር ላይ ማየት የተለመደ ነገረ ነው ነገረ ግን የውሃ በረዶ በኛ ምድር ብቻ ተወስኖ የቀረ አደለም በኛ ሶላር ሲስተም ውስጥ በሁሉም ቦታዎች ላይ ይገኛል።

44. “አስደናቂ እውነታዎች”

- ከ7.3 ቢልዬን የአለም ህዝብ ውስጥ 6.5 ቢልየን (90%) sየሚሆነው የአለም ህዝብ የሚኖረው በሰሜን ንፍቀ ክበብ (northen hemisphare) ነው።
- ወፎች አይሸኑም።
- ጉንዳኖች ፈፅሞ አይተኙም፤ሳንባ የላቸውም፤ሰራተኛ ጉንዳን እስከ 7 ዓመት ሊኖር ይችላል ንግስቷ ግን እስከ 15 ዓመት ልትኖር ትችላለች።
- ሻርክ ብቸኛው የማይታመም እንሰሳ ነው ምንም አይነት በሽታ አያጠቃውም ካንሰርን ጨምሮ።
- ፈረሶች እና ላሞች ቁመው ነው የሚያንቀላፉት።
- የማር ንብ ሁለት ሆድ ሲኖራቸው አንዱ ለማር ሲሆን ሁለተኛው ለሚመገቡት ምግብ ማስቀመጫ ያገለግላቸዋል።
- ትልቁ ነጭ ሻርክ ከሶስት ወር በላይ ሳይበላ መጓዝ ይችላል።
- አብዘሃኞቹ ዝሆኖች በክብደት ከስማያዊ አሳነባሪ (Blue whale) ምላስ ያንሳሉ።
- በረሮ በረሃብ እስኪሞት ድረስ ለሳምንት ያህል ጭንቅላቱ ተቆርጦ በህይወት መቆየት ይችላል።
- የአህያ አይን አቀማመጥ በአንድ ግዜ አራቱንም እግሮች ማይት ያስችሉታል።
- ዶልፊን ውሀ ውስጥ ከ24ኪ.ሚ ርቀት ያለ ድምፅ በቀላሉ መስማት ይችላል።
- የወባ ትንኝ 47 ጥርስ አላት።
- በጣም ከፍተኛ ድምፅ ያለው ሙዚቃ የምንጠጣውን የአልኮል መጠን ይጨምረዋል።
- ግሪክ በአለማችን በጣም ረጅም ብሔራዊ መዝሙር ያላት ሀገር ስትሆን መዝሙሩም 158 ስንኞችን ይዟል።
- የምንሰማው የሙዚቃ ዓይነት ስለአካባቢያችን የሚኖረንን አመለካከት የመቀየር አቅም አለው።
- በ2015 ዓ.ም ቴይለር ስዊፍት በቀን ከ1 ሚሊየን ዶላር በላይ ገቢ አግኝታለች፤ በየአመቱም

በፈረንጆቹ ታህሳስ 13 የቴይለር ስዊፍት ቀን እየተባለ ይከበርላታል።

- አንድ ጥናት እንደሚያሳየው ከሆነ መኪና በሚያሽከረክሩበት ወቅት ሰምተው የማያቁትን ሙዚቃ ቢሰሙ ተረጋግተው እንዲነዱ ይረዳዎታል።
- ክላሲካል ሙዚቃዎች የአዳማጩን የአእምሮ ልህቀት ደረጃ ለመጨመር ይረዳል።
- ማንኛውም ሁለት የሜዳ አህያ አንድ አይነት መስመር አይኖራቸውም።
- ቢራቢሮ የሚቀምሱት በጎላ እግራቸው ነው።
- ወንድ ሸረሪት የወሲብ አካል በአንድ እግሩ ጫፍ ላይ ይገኛል።
- ንቦች አምስት አይን አላቸው።
- አሳማ በተፈጥሮ ወደ ሰማይ ማየት አያስችለውም።
- አይጥ ከተራበች የራሷን ጅራት ትበላለች።
- ለሚስቱ ታማኝ የሆነ እንስሳ ቀበሮ ብቻ ነው።
- ሰማያዊ አሳነባሪ በመጠን እስካሁን በአለማችን ከነበሩ እና ካሉ እንሰሳዎች ትልቁ ነው።
- የለሌት ወፍ ብቸኛዋ ከአጥቢዎች መብረር የምትችል ሲሆን የእግር አጥንቶቿ ከመቅጠናቸው የተነሳ መብረር እንጂ መራመድ አትችልም።
- የሌሊት ወፍ ምንግዜም ከዋሻ ሲወጡ ወደ ግራ ይበራሉ።
- እባብ አይኖቹ ቢከደኑም በአይኖቹ ቆብ ማየት ይችላል።
- ወንድ የወባ ትንኝ አይናደፍም ሴቷ ብቻ ናት መናደፍ የምትችለው።
- የዱር አይጥ በፍጥነት መራባት የሚችሉ ሲሆን በ18 ወራት ብቻ 2 አይጦች 1 ሚሊዮን ዘመዶችን ማፍራት ይችላሉ።
- አንድ ንብ አንድ የሾርባ ማንኪያ ማር ለማዘጋጀት ከ 4000 በላይ አበቦችን መጎብኘት አለባት።
- ቀንድ አውጣ ለ3 አመት መተኛት ይችላል።
- አንድ ላይ የተያያዘ የሸረሪት ድር ተመሳሳይ ወፍረት ካለው አንድ ላይ ከተያያዘ የብረት ሺቦ ይጠነክራል።
- ዝሆኖች ከ3ማይል ላይ ያለ ውሀ ማሽተት ይችላሉ።
- ኦይስትር (Oyster) የተባለ የአሳ ዝርያ ከአንዱ ፆታ ወደ ሌላኛው እንዲሁም ወደ ነበረበት ለወሲብ በሚመቸው ፆታውን መቀየር ይችላል።
- በየአመቱ 1/3 የሚሆነው የአለማችን ሰብል በተባይ ነብሳት ይወድማል።
- አሜሪካ ሰዎች ላይ የሰራቻቸው የተለያዩ የሳይንስ ምርምሮች።
- አሜሪካ በሳይንስ ስም ሰዎችን እንደ አይጥ በመጠቀም የተለያዩ ሙከራዎችን አርጋለች።
- ከ 30 ሚሊዮን በላይ የፌስቡክ አካውንቶች የሞቱ ሰዎች ናቸው።
- የቤት ፈረሶች አንድ ሰው ሲያዝን ፊቱን በማየት ብቻ ሃዘኔታውን መረዳት ይችላሉ።
- ጃፓን ውስጥ የብዙ ሰዎች መጠሪያ የሆኑት ስሞች ሚናቶ ፣ ሳቶ እና ሱዙኪ ናቸው። በእንግሊዝ እና በአሜሪካ ደግሞ የብዙ ሰዎች መጠሪያ ስሚዝ ነው ። በአለም ላይ የብዙ ሰዎች መጠሪያ ደግሞ ሙሃመድ የሚለው ነው።
- ጥናት እንዳለው ከሆነ ለፍቅር ጓደኛቸው ታማኝ ያልሆኑ ሰዎች የማሰብ ብቃታቸው በጣም ዝቅ ያለ ነው።
- ሰዎች እንስሳቶችን በሚገሉበት ፍጥነት ሰዎች እርስ በራሳቸው ቢገዳደሉ አለም ላይ ያሉ ሰዎች ለመሞት 17 ቀናት ነበር ሚፈጅባቸው!
- ጠፈር ላይ ያሉ የክዋክብት ተመራማሪዎች በ1 ወር 1% የሚሆነው አጥንታቸውን ያጣሉ! ይህም በሚሸኑበት ጊዜ የሰውነታቸው 1% ሚሆነው በየወሩ ከሽንት ጋር ተደባልቆ ስለሚወጣ ነው።
- በአማካኝ የህዝብ መታጠቢያ ገንዳ ውስጥ ካለው ውሀ 72 ሊትሩ ሽንት ነው።
- ግመል የሀሞት ከረጢት የለውም። ከእንስሳት ሁሉ በጣም ቁመኛ እንስሳት ግመል ናት።ግመል አንድ እንስሳ ወይም ሰው ቢተናኮላት ለሰባት አመት ያህል ቂም ትይዛለች። የግመል ግልገል

አናጦሊ ትባላለች።

- በኢንዶኖዢያ ብቻ የሚገኝ ጥቁር ዶሮ አለ! ከላይ ያለው ሰውነቱ ብቻ ሳይሆን አጥንቶቹ እና ወስጣዊ የሰውነት አካላቶቹ በሙሉ ጥቁር ነው።
- አይነ ስውር, መላጣ እና ጀሮው ከርቀት የማይሰማ ሰውዬ በመብረቅ ተመቶ ሶስቱም ችግሮቹ በአንዴ ተፈተውለት ነበር።
- የድመት ሽንት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ አንደ እንቁ ያበረቀርቃል። ድመቶች የሚያሸቱት በአፍንጫና በላንቃቸው ነው።
- ዳክዬ እንቁላል የምትጥለው ጠዋት ጠዋት ነው።
- ጉጉት በድቅድቅ ጨለማ ውስጥ ጥርት አድርጋ ማየት ትችላለች።
- የከተማ አዕዋፍ ና የገጠር አዕዋፍ ዝማሬ ይለያያል።
- ሽንኩርት በምንከትፍበት ወቅት ማስቲካ ማኘክ ከመቃጠል ያድናል።
- አፍንጫ ቢያንስ 50,000 ሽታዎችን ማስታወስ ይችላል።
- ከ1525 እስከ 1866 ድረስ ብቻ ከ12.5 ሚሊየን በላይ አፍሪካውያን ታፍነው በባርነት ተሸጠዋል።
- ሴቶች በቀን 20,000 ቃላት ይናገራሉ። ይህ ማለት ከወንዶች 13,000 ቃላት ይልቃል ማለት ነው።
- በየ 90 ሰከንዱ አንዲት ሴት ልጅ በማጣጥ ብቻ ህይወቷ ያልፋል።
- ቢል ጌትስ በቀን 1 ሚልዮን ዶላር ቢያጠፋ ድሃ ለመሆን 218 አመታት ይፈጅበታል።
- ደስ የሚሉ የእንስሳትን ፎቶ በስራ ቦታ መመልከት በስራ ያለን ተነሳሺነትና ውጤታማነትን እንደሚጨምር ጥናቶች ይናገራሉ።
- አንጎላችን በየቀኑ አዳዲስ ትውስታን በመዘገበ ቁጥር እርስ በእርስ የሚገናኝበት አዳዲስ ሽቦዎችን ይፈጥራል።
- አንጎላችን ሶስት ሚሊየን የቴሌቭዥን ሰአታት ፕሮግራሞችን በአንድ ላይ የመያዝ አቅም አለው።
- በአንድ ቀን ውስጥ በድምር ለ40 ደቂቃ ያክል ማንኛውም ሰው አይነስውር ይሆናል! አይናችን ሲንቀሳቀስ አንጎላችን የማየት ብቃታችንን ያግደዋል ለዛም ነው በመስታወት የአይናችንን እንቅስቃሴ ማየት የማንችለው።
- በአለማችን ላይ ከፍተኛ የሆነ የግድያ ወንጀል የሚፈፀምባት ሀገር ኤል ሳልቫዶር ስትሆን በአማካኝ ከ100,000 ሰዎች ውስጥ 55.5% የሚሆኑት ግድያ ይፈፀምባቸዋል።
- እባብ ለ 3 ዐመት ሣይተኛ ሊቆይ ይችላል።
- የደም ሽታና የሽቶ መአዛ ፈረሶችን እጅግ በጣም ከመረበሽ አልፎ ያስደነብራቸዋል።ለሻርኮች ደግሞ ደም እንደ ሽቶ መአዛ ይማርካቸዋል።
- ሻርክ ደምን የማሽተት ብቃቱ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ አንዲት ጠብታ ደምን ከ15 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ሆኖ ማሽተት ይችላል።
- ህይወት ካላቸው ነገሮች ሁሉ በምንም አይነት ህመም ወይም በበሽታ የማይጠቃ ብቸኛ ፍጥረት ሻርክ ነው።
- ወንዱ ጥንቸል ሚስቱን ለሌሎች የሚያስተዋውቀው ላይዋ ላይ ሽንቱን በመሸናት ነው።
- ዜሮ ቁጥር የተፈለሰፈው በህድን ወስጥ ነው።
- አብዛኛው ራስን የማጥፋት ድርጊት የሚፈፀመው ሰኞ እለት ነው።
- በሀገሯ ፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሴቶች ቁጥር ያላት ሀገር ሩዋንዳ ስትሆን በፓርላማዋ ካሉት ጠቅላላ መቀመጫዎ ውስጥ 56.3% (50/80) የሚሆነው የተያዘው በሴቶች ነው።
- በሽንት ብቻ የሞባይል ቻርጅ የሚያደርግበትን መንገድ ሳይንቲስቶች እየሰሩ ነው።
- ንስር ከሰው አይን 8 እጥፍ የማየት ብቃት አለው። ሚታመም የሚታከመውም በነዚ አይኖቹ አተኩሮ ፀሀይን በማየት ነው።

- “Earth” ላይ 88 ቀን “Mercury” ላይ አንድ አመት ነው።
- የአንበጣ እግር ከክብደቱ አንፃር ሲታይ የኛን የእግር ጡንቻ ጥንካሬ በ1000 እጥፍ ይበልጣል።
- የኮሶ ትል አስከ 23 ሜትር እርዝመት እና 35 አመት እድሜ ቆይታ ሊኖረው ይችላል።
- ከአጥቢ እንስሳዎች መሀል ከሰውነቱ ክብደት አንፃር ትንሽ ልብ ይለው አንበሳ ነው።
- የአሳማ ብልት የለስላሳ መክፈቻ ቅርፅ አለው።
- ሪቦን የተባሉ እንስሳዎች ምግብ ካጡ ራሳቸውን በራሳቸው በልተው ይጨርሳሉ።
- ሮናልዲኒዮ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚዲያዎችን ቀልብ የሳበው 13 አመቱ ላይ ሲሆን የሱ ቡድን ተጋጣሚውን 23-0 ባሸነፈበት ጨዋታላ 23ቱንም እሱ ነበር ያስቆጠራቸው።
- “Black_Death” ስም የተሰየመው ከ1347-1351 የነበረው የወረርሽኝ በሽታ የEurope ህዝብን በአንድ ሶስተኛ ቀንሶ ነበር።
- በአለም ላይ ካሉት አጥቢ እንስሳት መሃል ሰውና ዝንጀሮ ብቻ ቀለማትን መለየት ሲችሉ ፣ የተቀሩት አይችሉም።
- አንድ የክብሪት ሳጥን የሚያህል ንፁህ ወርቅ ሲጠፈጠፍ አንድ የሜዳ ቴኒስ መጫወቻ ያህላል።
- ጉማሬ ከሰው በተሻለ ፍጥነት መሮጥ ይችላል።
- ካንጋሮ ጭራዋ መሬት ሳይነካ መዝለል አትችልም።
- የሰው ልጅ በየቀኑ ከ 40 -100 የሚደርሱ የፀጉር ዘለላዎችን ያጣል።
- በታይዋን የሚገኝ አንድ ካምፓኒ ከስንዴ የመመገቢያ ሳህኖችን በማምረትላይ ይገኛል፤ ሳህኑ ታስቦ የተሠራው ሰዎች ከተመገቡ በኋላ ህኖችን ከማጠብ ይልቅ እንዲበሏቸው ነው።
- በ1845 በወጣው የእንግሊዝ ህግ መሠረት ራስን ለመግደል መሞከር ከባድ ወንጀል እንደሆነ የተደነገገ ሲሆን፤ ራሱን ለመግደል ሙከራ ሲያደርግ የተገኘ ሰው በስቅላት እንዲቀጣ ይደረግ ነበር።
- የእንግሊዝ ጠቅላይ ሚኒስተር የነበሩት ታላቁ ዊኒስተን ቸርችል የተወለዱት በአንድ የዳንስ ውድድር ወቅት በሴቶች መፀዳጃ ቤት ውስጥ ነበር።
- አይዛክ ኒውተን የስበት ህግን ባገኘበት ወቅት የ23ዓመት ወጣት ነበር።
- ሁለት ሚሊዮን የቀይ ደም ሴሎች በየሠከንዱ ይሞታሉ።
- ከሰውነታችን ክብደት ውስጥ ሰባት ከመቶ የሚሆነውን የያዘው ደም ነው።
- የአንድ ቀይ የደም ሴል የህይወት ዘመን ከ120 ቀናት አይበልጥም።
- በፍጥነት የሚበቅለው ጥፍር የመሀል ጣት ሲሆን፣ ዝግ ብሎ የሚበቅለው ደግሞ የአውራ ጣት ነው።
- አንድ ፅንስ ለመጀመሪያ ጊዜ የሚያዛጋው በ11ኛው ሳምንት ላይ ነው።
- እንግሊዝ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ዝይዎች የንግስቲቷ ንብረት ተደርገው ነው የሚቆጠሩት።
- አይጥ ከግመል በተሻለ መልኩ ረጅም ርቀት መሔድ ትችላለች።
- "Underground" የሚለው ቃል በ"und" የሚጀምርና የሚጨርስ ብቸኛው የእንግሊዘኛ ቃል ነው።
- ጥይት የማይበሳው የጥይት መከላከያ ሰደርያ እሳት ማጥፊያ የነፍስ መከላከያ ዋይፐር እና ሌዘር ፕሪንተር ሁሉም የተፈለሰፉት በሴቶች ነው።
- ታላቁ የጦር ጀግና ጄንጊስ ከሀን ሕይወቱ ያለፈችው ወሲብ በመፈፀም ላይ እያለ ነበር።
- ስልክ ፈጣሪው አሌክስአንደር ግርሀም ቤል ለሚስቱም ሆነ ለእናቱ ስልክ ደውሎ አያውቅም። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሁለቱም መስማት የተሳናቸው መሆናቸው ነው።
- ድመቶች ከመቶ በላይ የተለያየ ድምፅ ማውጣት የሚችሉ ሲሆን ; በአንፃሩ ውሻ ማውጣት የሚችለው ድምፅ አስር ብቻ ነው።
- አልበርት አንስታይን እና ቻርልስ ዳርዊን ሁለቱም የአክስታቸውን ልጅ ነው ያገቡት።
- የጣት መገጣጠሚያዎችዎን ሲያጮሁ የሚሰሙት ድምፅ የናይትሮጂን ጋዝ

አረፋ ሲፈነዳ የሚያሰማውን ድምፅ ነው።

- የወንድ የዘር ፍሬ ሆርሞን ሲጨምር ደስታም በዛው ይጨምራል። ያለልክ ከጨመረ ግን የሰው ስቃይም ጭምር ሊያስደስተው ይችላል።
- የሠው አእምሮ ከ18 አመት በኃላ ማደግ ያቆማል።
- የ"facebook" ተጠቃሚዎች የአሜሪካ ቻይና እና ብራዚልን ህዝቦች ቁጥርን ቦንሶ ይገኛል።
- ቻይና ውስጥ Panda መግደል የሞት ቅጣት ያስቀጣል።
- ፀጉራችን ድምፅ ያወጣል።ፀጉራችን ውስጥ በጆሮ የማይሰማ ረቂቅ ድምፅ እንደሚመነጭ በሳይንስ ተረጋግጧል።
- ለህፃናት ጮክ ብሎ ማንበብ የአእምሮ እድገታቸውን ያዳብራል።
- አንድ ሰው በአማካኝ በአመት 2,500 ጊዜ መፀዳጃ ቤት ይጠቀማል።
- በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሆቴል የተገነባው እ.ኤ.አ. በ 1898 ሲሆን አሁንም አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።
- አዲስ አበባ በ8,000 ጫማ በመቀመጥ በዓለም ሦስተኛ ከፍ ያለች ዋና ከተማ ነች።
- ኢትዮጵያ የተመሰረተችው ከክርስቶስ ልደት በፊት 980 አካባቢ ሲሆን በምድር ካሉ ጥንታዊ ሀገሮች አንዷ ነች።
- ወደ 70% የሚሆነው የአፍሪካ ተራሮች በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛሉ።
- ወደ ግማሽ ያህሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ዕድሜው ከ 15 ዓመት በታች ነው ።
- በጃፓን ከህጻን ልጆች ዳይፐር ይልቅ የአዛውንቶች ዳይፐር በብዛት ይሸጣል።በርካታ አዛውንቶች ናቸው የሚገኙት።
- የቀጭኔዎች የፍቅር መግለጫ ጎንበስ ብሎ ሽንት መቅመስ ነው።
- በአለም ላይ ከፍተኛ የወርቅ ጌጣጌጥ ተጠቃሚ አገር ህንድ ናት።
- በአለም ላይ ብዙ ፖስታ ቤት ያላት አገር ሕንድ ናት።
- ህንድ የ10 ሺህዎች ዓመታት የስልጣኔ ታሪክና አላት።
- ሕንድ 700 የተለያዩ ቋንቋዎች አላት።
- "Albatrose" የተባለው ወፍ እየበረረ መተኛት ይችላል።
- በስዊዘርላንድ ግማሽ የሚሆኑት ጋብቻዎች በፍቺ ይጠናቀቃሉ።
- ከኑክሌር ጦርነት ጋር በተያያዘ ስዊዘርላንድ መላ ህዝቧን ለማኖር የሚያስችል በቂ ጋሻ አላት።
- ለስዊዘርላንድ ዜግነት ለማመልከት ቢያንስ ለ 12 ዓመታት በስዊዘርላንድ መኖር አለብዎት።
- ስዊዘርላንድ በዓለም ላይ በጣም ብዙ ቸኮሌት ታመርታለች።
- ስዊዘርላንድ በመጀመሪያ "Helvetia" ተብላ ትጠራ ነበር።
- የስዊዝ ቾኮሌት ሰሪዎች ሄንሪ ‹ናስቴል› እና ‹ዳንኤል ፒተር› ወተት ቸኮሌት ፈለሰፉ።
- በስዊዘርላንድ ውስጥ ማስተማር ከፍተኛ ደመወዝ ከሚከፈላቸው ሙያዎች አንዱ ነው።
- አብዛኛዎቹ የዓለም የቅንጦት ሰዓቶች በስዊዘርላንድ ነው ሚመረቱት እንደ ቲሶት፣ ታግ ሄየር፣ ሮሌክስ እና ፓተክ ፊሊፕ ያሉ ናቸው።
- ስዊዘርላንድ ውስጥ የበረዶ መንሸራተት ፣ የበረዶ መንሸራተቻ እና የተራራ መውጣት ታዋቂ ስፖርቶች ናቸው።
- በስዊዘርላንድ ራስን ማጥፋቱ ህጋዊ ነው።
- በዓለም የመጀመሪያው ፈጣን ቡና የሆነው ኔስካፌ በስዊዘርላንድ ተፈለሰፈ።
- በስዊዘርላንድ የባንክ ሻጮች በጥይት መከላከያ መስታወት ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው።
- በፀሐይ ኃይል የሚንቀሳቀስ አውሮፕላን የገነባች ብቸኛዋ ሀገር ስዊዘርላንድ ናት።
- ብዙ ሰዎች የአፍንጫቸው እርዝመት ከአውራ ጣታቸው ጋር እኩል ነው።
- በእግርኳስ ጨዋታ ከፍተኛ የተቆጠረው ጎል 149 ነው።
- በምዕራብ ቻይና ውስጥ ለሻይ ማጣፈጫ የሚጠቀሙት ከስኳር ይልቅ ጨውን ነው።
- ብዙ ጨረቃ ያላት ፕላኔት ሳተርን ስትሆን 61 የተፈጥሮ ሳተላይቶች አሏት።

- መሬት ከጨረቃ በ400 አጥፍ ትገዝፍለች።
- በአለም ዙሪያ በየደቂቃው 6,000 የመብረቅ ብልጭታዎች ይከሰታሉ።
- የሰውነታችንን ሚዛን የሚጠብቀው የጆሮአችን የውስጠኛው ክፍል ነው።
- 38% አሜሪካውያን ከፍቅረኞቻቸው የበለጠ መኪናቸውን እንደሚወዱ ተናግረዋል።
- ሀርፒ ንስር አስፈሪ ፍጡር ነው። ቁመቱ 91cm ክንፉ ቢዘረጋ 2m ርዝመት አለው። መገኛውም በደቡብና በማእከላዊ አሜሪካ ነው። ድምፅ አያሠማም።
- Karl Marx አራቱንም ሴት ልጆቹን Jenny ብሎ ስም ሰቷቸዋል።
- በጭንቀት ውስጥ ያሉ ሰዎች ከደስተኛ ሰዎች በላይ ብዙ ብር ያወጣሉ።
- ንስር ከሰው አይን 8 እጥፍ የማየት ብቃት አለው።ሚታመም የሚታከመውም በነዚ አይኖቹ አተኩሮ ፀሀይን በማየት ነው።
- ረጅም ቃል የማንበብ ፍርሀት "Hippopotomonstroesquipedaliophobia" ይባላል።
- እየሄድን ስልክ መነካካት ከእየነዳን ስልክ ከመነካካት የበዛ አደጋ አለው።
- ሐዋይ በተባለች የአሜሪካ ግዛት ውስጥ ምሽት ከ4 ሰአት በኋላ መሳቅ ክልክል ነው።
- በሐዋይ ግዛት ውስጥ የመልካም ምኞት ምሳሌ ወይም ገድ ተብሎ የሚከበር እንስሳ ሻርክ ነው።
- ሐዋይ ውስጥ ጀልባ የሌለው ሰው በህግ ይቀጣል።
- ላሞች የላይ ጥርስ የላቸዉም።
- ማቲው ሆግ ይባላል ፤ ይህ ግለሰብ ሁሌም እንደሰከረ ነው። የሚሰክረው ጠጥቶ አይደለም። ሰውነቱ በራሱ ግዜ አልኮል ያመርታል ይህም “Auto Brewery Syndrome” ይባላል። በትንሽ አንጀቱ ውስጥ የሚጠራቀመው የእርሾ መጠን ወደ ንፁህ አልኮልነት ይቀየርና ወደ ደም ዝውውር ይሰራጫል ከዛ በቃ ይሰክራል እንደ ጠጣ ሰው ራሱን መቆጣጠር አይችልም።
- የተወሰኑ የ”Scotland” እና “japan” ቦታዎች ሰማያዊ ብርሀን ነው ያላቸው ይህም ወንጀል ለመቀነስ ይረዳል ብለው አስበው ነው።
- አዲስ ከሚወለዱ 2,000 ህፃናት ውስጥ 1 ህፃን ከነሙሉ ጥርሱ ይወለዳል።
- ሰውን ከምግብ እጦት ይልቅ በእንቅልፍ እጦት በአጭር ቀናት ውስጥ ይሞታል።
- ያለ እንቅልፍ ብዙ ቀናት የመቆየት ሪከርድ የያዘው ራንዲ ጋድኔ የተባለ ሰው ሲሆን ሪከርድ 264 ሰአታት ወይም 11 ቀናት ነው።
- የጣት አሻራ የሚፈጠረው ከ3ኛው የጽንስ ወራት ጀምሮ ነው።
- ፔሩ ከግብፅ የበለጡ ፒራሚዶች አሏት።
- የፅህፈት መሣሪያ የተፈጠረው በ1829 ነበር።
- ሣውዲ አረቢያ ወንዝ የሌላት ሀገር ናት።
- ጨረቃ ክብደቷ 81 ቢሊየን ቶን ይመዝናል።
- ፊሊፒንስ ሀገር ውስጥ በአንድ ሰዓት ውስጥ ብቻ 3.2 million ዛፎችን በመትከል የአለም ሪከርድን መስበር ችለዋል።
- አንድ ሰው በቀን 1.7ለ ሊትር ምራቅ ያመነጫል።
- አንድ ሰው በቀን 0.5 ሊትር ውሀ በትንፋሽ ያወጣል።
- በአንድ ደቂቃ ውስጥ እስከ 40000 የቆዳ ሴሎቻችን ይሞታሉ።
- “Black and White” ቴሌቭዥን እያየ ያደገ ልጅ ብዙ ጊዜ የሚያየው ህልም በ”black and white” ነው።
- ሆሊዉድ በሚል ስያሜ የሚጠሩ አስር ከተሞች አሉ።
- “Set” የሚለው የኢንግሊዘኛ ቃል 463 ትርጉሞች አሉት።
- ሱሚና የተባለው አደገኛ አውሎ ንፍስ ፍጥነቱ ከጄት ፍጥነት ይበልጣል።
- በአለም ላይ 7,000,000 ሚልየነሮች አሉ።
- ታዋቂው የሩሲያ ገዥ ታላቁ ጴጥሮስ ወንዶችን የጺም ቀረጥ ያስከፍል ነበር።

- አይስላንድ ውስጥ የቤት ውሻ ማርባት ክልክል ነው።
- የአይናችን ክብደት 28 ግራም ነው።
- ሠው ከ 600 በላይ ጡንቻ አለው።
- 11% የሚሆኑ ሠዎች ግራኝ ናቸው።
- 1 ሠው ከዕድሜው 25 አመት በእንቅልፍ ያሣልፋል።
- 96% ሻማ የሚገዙ ሴቶች ናቸው።
- ብሉቱዝ እ.ኤ.አ በ 1994 በ ጀርመን ኢንጂነር ጃፕ ሀርትሰን ተፈጠረ።
- ንስርን ሊጠልፍ የሚፈልግ ብቸኛ በራሪ እንስሣ ቁራ ነው።
- አንድ ሰው ለ8 አመታት ከ7ወር ለ6 ቀን ያክል ቢጮህ ለአንድ ሲኒ ቡና የሚበቃ “Sound Energy” ያገኛል።
- ከወተት አይነቶች ሁሉ ውድ የሆነው የአይጥ ወተት ነው።ዋጋውም 22 ሺህ ዶላር ነው።
- በሶሻል ሚዲያ ላይ የሚገናኙ ሰዎች በአካል ከሚገናኙ ሰዎች የበለጠ የመታበት እድላቸው ሰፊ ነው።
- ወንድ ሆነህ የእርግዝና መመርመሪያ መሳሪያ ላይ ሽንተህ ሁለት ቀያይ መስመሮች ከመጡ ምንአልባት በካንሰር ህመም ተጠቅተሀል ማለት ነው።
- በ2001 Russia ለ”International Space Station” ላይ ላሉ ሰዎች ለትራንስፖርት 1ሚሊዮን $ አውጥታ “pizza hut “ ልካላቸው ነበር።
- አንድ እርሳስ 50,000 ቃላትን ይጽፋል።
- ብዙ ሰዎች ሽረሪትን ከሞት በላይ ይፈራሉ።
- ብረት ከዛገ በኋላ ክብደቱ ይጨምራል።
- ውሻን በሰንሰለት ማሰር በሶስት እጥፍ የበለጠ ተናካሽ ያደርገዋል።
- 50% የሚሆኑ ሰዎች በሌላ የፍቅር ግንኙነት ውስጥ ያለ ሰውን ይወዳሉ።
- ትንኞች በይበልጥ የደም አይነታቸው "O" በሆኑ ሰዎች ይሳባሉ። (የደም አይነታቸው ኦ የሆኑ ሰዎች በትንኝ ለመነከስ ቅርብ ናቸው።)
- ሰው በአማካኝ በቀን 6 ጊዜ ይሸናል።
- ማር የድምፅ ውበትን ያስተካክላል።
- ከአንድ ጀምረን እስከ አንድ ትሪሊዮን ያለውን ቁጥር በቃላችን ለመጥራት በቀን 24 ሰአት ብንቆጥር 31,688 ዓመታት ይፈጅብናል።
- እርድ የተጨመረበት ምግብ መመገብ ለካንሰር የመጋለጥ እድልን ይቀንሳል።
- በአንድ የሽቶ ፈሳሽ ውስጥ 250 ዓይነት ቅመሞች ይገኛሉ።
- ቡና የሚመደበው ከፍራፍሬ ዘርፍ ነው።
- “The Matrix” ይህን ፊልም ለመፃፍ 5 አመት ፈጅቷል።
- 3% የሚሆነው የአይናችን ክብደት ጨው ነው።
- ልጅ በአብዛኛው ቁመቱን ከአባቱ፤ ውፍረትን ከእናቱ ይወርሳል።
- የምላሳችን ጣዕም የመለያ እጢ በየ10 ቀኑ በአዲስ ይተካል።
- የአለማችን አራዳው ውሻ (The world's smartest dog) የሚል ስያሜ የተሰጠው ቼዘር የተባለው ውሻ ነው። ይህ ውሻ 1,022 ቃላቶችን ሸምድዶ በመያዘ ለውሾች የሚሰጠውን የመጀመሪያ ዲግሪ ይዟል።
- አንድ የግብፅ ፒራሚድ ያረፈበት ሥፍራ 2 ኢንተርናሽናል የእግርኳስ ሜዳ ያህል ስፋት አለው።
- በኒውዮርክ የሚገኘው ኤምፓየር ስቴት ቢውልዲንግ የተባለው ሕንፃ የተገነባው ከ10,000,000 ብሎኬቶች/ጡብ/ ነው።
- በቼዝ ጨዋታ የመጀመሪያዎቹን አራት ጠጠሮች ለማንቀሳቀስ ብቻ 318,979,564,000 አማራጮች አሉ።
- በአለማችን ላይ ምርጥ ፈረስ ጋላቢዎች በመባል የሚደነቁት ህዝቦች ኢራናውያን ናቸው።

- ወንዱ ፈረስ 40 ጥርሶች ሲኖሩት ሴቷ ማለትም ባዝራ ፈረስ ደግሞ 36 ጥርሶች አሏት።
- በአሜሪካ ውስጥ 5,143 ኤርፖርቶች ወይም የአውሮፕላን ማረፊያዎች ይገኛሉ።
- ፈርዲናንድ ማጄላን ለመጀመሪያ ጊዜ መሬትን የዞረባት መርከብ "ቪክቶሪያ" ትባላለች።
- በአለም ዙሪያ በየአመቱ 50,000,000 መኪናዎች ይፈበረካሉ።
- በአለም ዙርያ በ 10 ሴኮንዶች ውስጥ 13 ሰው የሞታሉ።
- በአለም ዙሪያ በእያንዳንዱ ሴኮንድ 3 ልጆች ይወለዳሉ።
- የአለማችን የተፈጥሮ ንፁህ ውሀ የሚገኘው በግሪክ ሲሆን መገኛውም በ መሊሳኒ ሀይቅ ነው ሀይቁም ንፁህ ከመሆኑ የተነሳ መርከቦች በአየር ላይ የሚሄዱ ነው የሚመስለው።
- ሰማያዊ አሳነባሪ በአለም ላይ እስከዛሬ ከኖሩ እንስሳቶች ሁሉ በመጠን ትልቁ ነው።
- የሰማያዊ አሳነባሪ ምላስ ከዝሆን ክብደት እኩል ሲሆን ልቡ ደሞ ከአንድ መካከለኛ መኪና ጋር የሚስተካከል ክብደት አለው።
- በብዛት ክሪል የተባሉ ትንንሽ የአሳ ዝርያዎችን የሚመገብ ሲሆን በቀን 40 ሚልየን ክሪሎችን ይመገባል።
- በአፉ ውስጥ በአንድ ጊዜ እስከ 5,000 ኪ.ግ ምግብ እና ውሀ የመያዝ አቅም አለው።
- አዲስ የተወለድ ሰማያዊ አሳ ነባሪ በቀን 600 ሊትር ወተት የሚጠጣ ሲሆን አንድ አመት እስኪሞላው ድረስ በየቀኑ 90 ኪሎ ግራም ክብደት ይጨምራል።
- ዝቅተኛ ሞገድ ያለው ድምፅ የሚያወጡ ሲሆን አንድ ሰማያዊ አሳነባሪ የሌላውን ሰማያዊ አሳነባሪ ድምፅ ከ1,600 ኪሎ ሜትር ርቀት ለይቶ መስማት ይችላል።
- ለመጥፋት ከተቃረቡ የእንስሳት ዝርያዎች ውስጥ የተመደቡ ሲሆን በዓለም ላይ የቀሩት ሰማያዊ አሳነባሪዎች ቁጥራቸው ከ10,000-25,000 ይገመታል።
- በጃፓን ባህል የፈረስ ጥሬ ስጋ ተወዳጅ እና ዝነኛ ምግብ ነው።
- ቡና በጃፓን ውስጥ በጣም ተወዳጅ መጠጥ ሲሆን 85 ፐርሰንት የምታስገባው ከጃማይካ ነው።
- በዓለማችን ውስጥ ከፍተኛ ቁጥር ያለው የመኪና አምራች አገር ጃፓን ናት።
- በጃፓን ባህል ሰው ሲሞት ምንጊዜም የሚቀበረው ጫንቅላቱን በስተሰሜን አቅጣጫ ተደርጎ ነው ። ይህ እንዲህ ሲሆን ለእንቅልፍ ጋደም በሚሉበት ወቅት ደግሞ ጭንቅላታቸውን በስተሰሜን አቅጣጫ አድርገው አይተኙም።
- "Friends" የመጨረሻው ምዕራፍ ለዕይታ የበቃው እንደ ኤውሮፖውያን አቆጣጠር በ 2004 ቢሆንም አሁንም ድረስ “warner brose” በየአመቱ አንድ ቢልየን ዶላር ይሰበስብበታል። ስድስቱ አክተሮች ደግሞ በአንድ ወቅት በሰሩት ተወዳጅ ስራ ብቻ ሀያ ሚሊየን ዶላር በአመት ያገኛሉ።
- በጥንት ዘመን የሰው ልጅ የልብ ስራ ለማሰብ ፣ የአንጎል ደግሞ የሰውነትን ሙቀትን ለመቆጣጠር ተደርጎ እንደተሰራ ተደርጎ ይታሰብ ነበር ፤ የአንጎል ስራ ማሰብ እና መረጃን ማጠራቀም እንደሆነ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስረዳው ጥንታዊው የግሪክ ፈላስፋ የሆነው "አሌማኤሩን ዘ ክሮቶን" ይባላል። ዘመኑም ከክ/ል/በፊት 300 አመት ላይ ነበር።
- 30Kg የሚመዝን ሠው ጨረቃ ላይ 10Kg ብቻ ይመዝናል። ግን ፀሀይ ላይ 1680Kg ይመዝናል።
- በአንድ ወቅት በሞናኮ ውስጥ "ቻርለስ ቻፕሊንን" አስመስሎ የማቅረብ ወይም የኢሚቴሽን ውድድር ተካሂዶ ነበር። አስገራሚው ነገር ቻርለስ ቻፕሊን ማንም ባላወቀበት ሁኔታ ውድድሩ ውስጥ በመግባት ሶስተኛ ወጥቶ ሽልማቱን ተቀብሏል። ሽልማቱን በእጁ እስኪያስገባ ድረስ ግን ቻርሊ መሆኑ አልታወቀበትም ነበር።
- የ”Ferrari” መኪና ማምረቻ ድርጅት ለድርጅቱ ተቀጣሪዎች ፌራሪ መኪና እንዲጠቀሙ አይፈቅድም።
- በአለም ላይ ዝቅተኛ የህፃናት ወሊድ ቁጥር ያላት ሀገር ላቲቪያ ስትሆን በአመት በአማካኝ

በላቲቪያ ውስጥ 15,000 ህፃናት ብቻ ይወለዳሉ !ይህ ማለት በዚህች ሀገር በቀን በመላው ሀገሪቷ ላይ የሚወለዱት የህፃናት ቁጥር 41 ብቻ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

- በረሮዎች ፈጣን ከመሆናቸው የተነሳ በሰአት 4 mile መጓዝ ይችላሉ።
- አንገታቸው ተቆርጦ ለሰባት ቀን መኖር የሚችሉ ብቸኛ ነብሳት በረሮዎች ናቸው።
- እየፈጠን በሄድን ቁጥር እያጠርን እንመጣለን።
- የፊዚክስ ሊቁ አይዛክ ኒውተን እስከ እለት ሞቱ ድረስ ድንግል ነበር።
- በውቅያኖስ ውስት ያለው ወርቅ ሙሉ ለሙሉ ቢወጣና እኩል ቢከፋፈል ለእያንዳንዱ የዓለም ዜጋ 20 ኪሎ ግራም ይዳረሳል።
- ጡረታን ለአለም ህዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ያስተዋወቀች ሀገር አውሮፓዊቷ ሀገር "ጀርመን" ናት ።
- በአሜሪካ በየ 39 ደቂቃ አዲስ የወሲብ ፊልም ይፈጠራል።
- አውስትራሊያ ውስጥ በጣም ትልቅ ከመሆናቸው የተነሳ እባብ ገድለው መብላት የሚችሉ ሸረሪቶች አሉ።
- ዩራነስ በተባለችው ፕላኔት ላይ ፀሀይ ለ42 አመታት በተከታታይ ትታያለች (ትወጣለች) ቀጥሎም ለ42 ተከታታይ አመታት ደግሞ ትጠልቃለች።
- ኤለን መስክ የኮሌጅ ተማሪ በነበረበት ወቅት የቤት ኪራይ ለመክፈል ሲል ቤቱን የምሽት ክበብ (Night Club) አርጎት ነበር።
- ኤለን መስክ የዓለማችን 1ኛ ሃብታም ሲሆን፤ የ"Space X" እና "Tesla" መስራች እና ባለቤትም ጭምር ነው።
- የትምባሆ ኩባንያዎች እንደ አዲስ ዓመት ውሳኔ ብዙ ሰዎች ማጨስ ለማቆም በሚሞክሩበት በጥር ወር ለማስታወቂያ ብዙ ገንዘብ ያጠፋሉ።
- በአርጀንቲና ሮዛሪዮ ከተማ ውስጥ የሚወለዱትን ማንኛውም ልጆች ወላጆቻቸው ለልጆቻቸው ስማቸውን ሜሲ ብለው ማውጣት አይችሉም ስሙን ማውጣት በህግ የተከለከለ ነው። ምክንያቱም ስሙ የሊዮኔል አንድሪያስ ሜሲ ብቻ ነው ለሌላ ሰው ይሄ ስም አይገባውም የሚል ምልከታ እና ለሱ ከበሬታ ስላላቸው ነው።
- በተለያዩ ጊዜያት የናዚውን አለቃ አረመኔውን "አዶልፍ ሂትለርን" ለመግደል የአውሮፓ ታላላቅ የሀገራት መሪዎች እቅዶች ያወጡ ቢሆንም አልተተገበሩም ነበር። ምክንያቱም ምናልባት እሱን ከገደልን ቡሀላ ሌላ የባሰ አረመኔ መሪ ቢመጣስ በሚል ፍራቻ ነበር።
- ለመጀመሪያ ጊዜ የሰው ልጅ የደም ልውውጥ ያደረገው ከራሱ መሰል የሰው ልጅ አነበረም ይልቁንም ለመጀመሪያ ጊዜ የደም ልውውጥ ወይም የደም ልገሳን ሊያገኝ የቻለው ከእንስሳቶች ነበር። በ1667 ዓ.ም ጂን ባፕታይዝ የተባለ ተመራማሪ የበግን ደም ለአንድ ህመምተኛ ልጅ በደም ስሩ ውስጥ በመስጠት ህይወቱን ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ሊታደግ ችሏል እናም የደም መስጠት የተጀመረውም ከዚ አመት ጀምሮም ነበር ደም ለጋሿም እንስሳ በግ ነበረች።
- የጃኪ ቻን አባት ሰላይ እና እናቱ የአደንዛዥ ዕፅ ነጋዴ እንደነበሩ ያውቃሉ? እናቱ እና አባቱ የተገናኙትም አባቱ እናቱን ሲሰልል ሳለ ነበር።
- የእጃችንን ጣቶች ስንስባቸው ስናጥፋቸው የምንሰማው ቋቋ የሚሉ ድምፆች የሚመጡት ከአጥንታችን መተሻሸት ሳይሆን ጣታችን መሀል ያሉት ጋዞች ሲፈነዱ ነው።
- ቁጥር አንዱ የአለማችን ሳይንቲስት የነበረው አልበርት አንስታይን ከኮሌጅ እንደተመረቀ በስራ ማጣት በርካታ አመታቶችን ተንከራቶ ነበር።
- አንዳንድ የቀንድ አውጣ ዝርያዎች በአንድ አካል ላይ የወንድም የሴትም ብልት አሏቸው።
- እስከ 1986 ድረስ ዶክተሮች ህፃናት ህመም ሊሰማቸው ይችላል ብለው አላሰቡም ነበር እና ያለ ማደንዘዣ በጨቅላ ህጻናት ላይ ክፍት የልብ ቀዶ ጥገናዎችን አድርገዋል።
- K2-141b፡ የገሃነም ፕላኔት።

- Almost-- የሚለው ቃል የእንግሊዘኛ ፊደል ተራን ተከትሎ የሚጻፍ ረጅሙ ቃል ነው።
- Rhythm- የሚለው ቃል ቫውል ሳይኖረው የሚጻፍ ረጅሙ የእንግሊዘኛ ቃል ነው።
- ሰው አተነፋፈሱን ሆን ብሎ በተፈጥሮ በማቆም እራሱን ሊያጠፋ አይችልም (ሌላ አካል /ሰው ካላፈነው በቀር)
- በረሮ ጭንቅላቱ ተቆርጦ ሳምንታት ሳይሞት መቆየት ይችላል።
- ጭራሽ መዝለል የማይችል እንስሳ ዝሆን ብቻ ነው።
- ዶልፊኖች አንድ አይናቸውን ከፍተው ይተኛሉ።
- እስከአሁን ከተመዘገበው ዶሮ መብረር የምትችለው አስከ 13 ሰከንድ ብቻ ነው።
- ቀጭኔ 21 ኢንች በሚረዝመው ምላሷ ጆሮዋን ማጽዳት ትችላለች።
- ሰው በቀን በአማካይ እስከ አስር ግዜ ይስቃል።
- ሰጎን አይኗ ከአንጎሏ ይተልቃል።
- ሳይንቲስቶች ድንጋያማ ዝናብ የምትጥልበት እና ውቅያኖሶች ከላቫ የተሠሩባትን የገሃነም ፕላኔት አገኙ።
- በአሜሪካዋ ግዛት በኦክላሆማ በዉሻ ላይ መቀለድ በህግ ያስቀጣል። አንድ ሰው ወደ ዉሻ ጠጋ በማለት አስቂኝ ሆነ ፊት ለውሻው ቢያሳይ በእስር ወይም በገንዘብ ሊቀጣ እንደሚችል በህግ ተደንግጓል።
- በጀርመኖች ባህል በሰርግ ወቅት ሙሽራው መልካም ዕድል እንዲገጥመው ተብሎ በኪሱ ውስጥ ዳቦና ጨው ይይዛል።
- ካልጠገቡ አይከፍሉም በዴንማርክ በዴንማርክ ሬስቶራንቶች ገብተው የሚመገቡ ከሆነና ምገቡ ካላጠገበዎ ሂሳብ ለመክፈል አይገደዱም እንዲሁ ሳይከፍሉ ከሬስቶራንቱ ውልቅ ማለት ይችላሉ።
- በማርሻል አርት ጥበቡ አለምን ከማስገረሙ በፊት የአክሽን ፊልም ኮኮብ የሆነው ጃኪ ቻን በ1970ዎቹ የሰራው የወሲብ-ኮሜዲ "All in the Family" ፊልም በሆንግ ኮንግ በጣም ተወዳጅ ለመሆን በቅቶ ነበር። እናም ስለዛ ጊዜም ሲጠየቅ "በሰዓቱ አዋጪው ስራ እሱ ነበር።" ሲል ነበር የመለሰው።
- በምድረ አሜሪካ በእያንዳንዷ ደቂቃ አንድ አዲስ መፅሀፍ ይታተማል።
- በአሥረኛው ክፍለ ዘመን የፋርስ ታላቁ ቪዚየር አብዱል ካሳም እስማኤል ቤተመጻሕፍቱን በሄደበት ሁሉ ተሸክሞ ነበር የሚጓዘው። አራት መቶ ግመሎችን 117,000 ጥራዝ መፅሀፎችን ለመሸከም ይገለገልባቸው ነበር።
- በካናዳ ከሶስት ሚሊዮን የሚልቁ ሀይቆች ይገኛሉ። ሃምሳ በመቶ የሚሆኑት ካናዳውያንም የተማሩና ከከፍተኛ ተቋማት የተመረቁ ናቸው። ካናዳን በተማረ የሰው ኃይል ቁጥር እስራኤልና ጃፓን ይከተሏታል።
- ገና እንደ ተወለደ ልክ እንደ አባቱ አርባ ሜትር አነጣጥሮ መናደፍ የሚችል ብቸኛ ፍጥረት ኮብራ ነው።
- በየአመቱ በህንድ ውስጥ አዲስ የሚወለደው የህፃናት ቁጥር በአውስትራሊያ አህጉር ውስጥ ካለው የህዝብ ብዛት ይበልጣል።
- መብረቅ ምድርን ወደ 8 ሚሊየን ጊዜ በአንድ ቀን ይመታል።
- በአለም ላይ ብዙ ልጆች የሚወለዱት በዕለተ ማክሰኞ ነው።
- የቦሊቪያ ትልቁ እስር ቤት በራሱ ህብረተሰብ ያለው ከመሆኑም በላይ በግድግዳዎቹ ውስጥ ጠባቂዎች የሉትም። እስረኞች የራሳቸውን መሪ ይመርጣሉ፣ የራሳቸውን ህጎች ያወጣሉ፣ ለሴል ኪራይ የሚከፍሉ ስራዎችን ያገኛሉ፣ ከቤተሰቦቻቸው ጋር እንኳን መኖር ይችላሉ።
- ጃፖን ውስጥ ሼፍ ከመሆን ዶክተር መሆን ይቀላል፤ ሼፍ ለመሆን ቢያንስ 15 አመት መማር ያስፈልጋል።
- "The Aline hand syndrome የሚባል እንግዳ አይነት በሽታ አለ ይህ በሽታ እጃችን

ከአእምሯችን ትዕዛዝ መቀበል ትቶ በራሱ መመራት ሲጀምር ነው። ይህ ኬዝ ጉዳይ ያለባቸው ሰዎች ራሳቸውን በራሳቸው እጅ አንቆ የመግደል ዕድላቸው የሰፋ ነው። መፍትሔውም እጅን እስከመጨረሻው መቁረጥ ነው።"

- አለማችን ላይ ካሉ የ እንቁራሪት ዝርያዎች በሙሉ ትልቁ ጎሊያድ እንቁራሪት ነው። ትልቀታቸው ከቤት ውስጥ ድመት እኩል ይሆናል። የሚገኙት በኢኳቶሪያል ጊኒ እና በካሜሮን ብቻ ሲሆን በመጥፋት ላይ ያሉ እንስሳዎች ናቸው። ጎሊያድ እንቁራሪቶች 3ሜትር ያክል መዝለል ይችላሉ። ሌሎች ትናንሽ እንቁራሪቶችን ስልቅጥ አድርገው ይውጣሉ እንዲሁም፣ እባቦችን፣ አይጦችን እና አሳዎችንም ይመገባሉ። ለመዋጥ አመቺ ይሁንላቸው እንጂ ያገኙትን እንስሳ አይምሩም። የጎሊያድ እንቁራሪቶች ዋና ጠላት የሰው ልጅ ነው። የሰው ልጅ እነዚህን እንቁራሪቶች በስፋት ለምግብነት ስለሚጠቀማቸው እና ወደተለያዩ ሀገራቶች ኤክስፖርት ሲለሚደረጉ ቁጥራቸው ተመናምኖ ለመጥፋት ተቃርቧል።
- ህንድ ውስጥ በየ15 ደቂቃ 1 ፆታዊ ጥቃት በ ሴቶች ላይ ይደርሳል።
- በሮም ከተማ ዉስጥ በ312BC የተገነባ "the appian way" ሚባል ጥንታዊ መንገድ ያለ ሲሆን እስካሁንም ድረስ ይጠቀሙበታል።
- ዳይመንድ ከፍተኛ ጥቅሙ (80%) በተላልቅ ፋብሪካዎች ውስጥ ለሚሰሩ ስራዎች እንደ መሳሪያነት ነው። 20% ብቻ ለጌጣጌጥነት ይውላል።
- በቪክቶርያና በአውስትሬልያ ፍቃድ የተሰጠው ኤሌክትሪሽያን ብቻ ነው አምፖል መቀየር የሚችለው።
- 7 ቁጥር በአምላክ ዘንድ የፍጻሜ ቁጥር ነው ይባላል። ፍጥረቱ ጨርሶ ፈጥሮ በ7ኛው ቀን ከሰራው ስራ ሁሉ አረፈ፣ ምድር 7 አህጉራት 7 ውቅያኖስ ተመሰረተች፣ ሳምታት በ7ቀናት ተሰሩ፣ ቀስተ_ደመና በ7 ህብር ቀለማት ተሰሩ፣ ሰው 7 መሰረታዊ ክፍሎች አሉት፣ 7 ዋና ዋና ኦርጋንስ፣ 7 የሰውነት የቆሻሻ ማስወገጃ ቀዳዳ አሉት።
- 666 ወይም 6 ቁጥር ይህን የፍፃሜ ቁጥር ጎዶሎ የማድረግ ሀሳብ ነው ብለው የሚከራከሩ ሰዎች አሉ።
- ደቡብ ኮሪያ በ2017 ባደረገችው የሚሳኤል ሙከራ በድንገት በአንዱ የራሷ ከተማ ላይ ወድቆ ጉዳት አድርሷል።
- ለ20 ደቂቃ ከሃሳብ ተላቆ በደንብ መመሰጥ ለ2 ሰአት ከመተኛት እኩል ነው።
- “VATICAN CITY” 800 ህዝብ ብቻ ያላት ሲሆን ይህም በአለማችን ትንሽ የህዝብ ቁጥር ያላት ከተማ ያረጋታል።
- ጥናቶች እንደሚሉት በአብዛኛው መልከ መልካም ወንዶች በፍቅር ለመረታት እጅጉን ቅርብ ናቸው።ትንሽ ቀረቤታ ፍቅር እንዲይዛቸው ያደርጋል ።አብዛኞቹም ፍቅር የሚይዛቸው ልክ እንደሱ መልከ መልካም ከሆነች ሴት ሳይሆን መካከለኛ ውበት ካላት ሴት ነው። ነገርግን አብዛኞቹ ቆንጆ ወንዶች የሚይዛቸው ፍቅር ጊዚያዊ ነው።
- አፍሪካ ከዓለም በትልቅነቱም ሆነ በሕዝብ ብዛት ሁለተኛዋ ናት። እስልምና በአፍሪካ የበላይ ሃይማኖት ነው። ክርስትና ሁለተኛው ነው። አረብኛም በአፍሪካ ውስጥ በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው። አፍሪካ በአለም ሁለተኛዋ ትልቅ አህጉር ብትሆንም አጭር የባህር ዳርቻ አላት። አፍሪካ በአለም ላይ በማእከላዊ የምትገኝ አህጉር ነች። ሁለቱም ፕራይም ሜሪድያን (0 ዲግሪ ኬንትሮስ) እና ወገብ (0 ዲግሪ ኬክሮስ) በላዩ ላይ ተቆርጠዋል። ናይጄሪያ በአፍሪካ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር (154.7 ሚሊዮን ህዝብ) አላት። ይህም ከአፍሪካ አጠቃላይ ህዝብ 18 በመቶውን ይወክላል። የዓለማችን ረጃጅም ትልቁ የምድር እንስሳት ሁለቱም ከአፍሪካ የመጡ ናቸው። እነሱም በቅደም ተከተል የቀጭኔ እና የአፍሪካ ዝሆን ናቸው። በአፍሪካ ውስጥ ወደ 2,000 የሚጠጉ የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩ ሲሆን እያንዳንዳቸው የተለያዩ ዘዬዎች ሲኖራቸው አረብኛ ደግሞ በአፍሪካ አህጉር በስፋት የሚነገር ቋንቋ ነው። የአለማችን ረጅሙ ወንዝ አባይ እና የአለማችን ትልቁ በረሃ ሰሃራ ሁለቱም በአፍሪካ ውስጥ ይገኛሉ።

- አንዱ የጄሊፊሽ ዝርያ ቱሪቶፕሲስ ዶርኒ " የማይሞት " ነው። ለአካላዊ ጉዳት ወይም ለሌላ ማንኛውም ጉዳት ምላሽ ወደ እድገታቸው ሂደት ወደ ፖሊፕ መመለስ ይችላሉ።
- ቀንድ አውጣዎች የአየሩ ሁኔታ እርጥብ ካልሆነ ፍላጎታቸውን ለማሟላት እስከ ሶስት አመት እንደሚተኛ ይታወቃል።
- የማር ንቦች በየሰከንዱ 230 ጊዜ ክንፋቸውን ያራግባሉ።
- ሲወለድ ፓንዳ ግልገል ከመዳፊት ያነሰ እና ክብደቱ አራት አውንስ ብቻ ነው።
- ፈረሶች እና ላሞች ቆመው መተኛት ይችላሉ ነገር ግን ሲተኙ ብቻ ነው ማለም የሚችሉት።
- የኮዋላ (እንስሳ ነው) የጣት አሻራዎች ከሰዎች አይለዩም በጣም የወንጀል ትዕይንቶችን ሊያበላሹ ይችላሉ።
- ሆድዎ ያበሳጫል ብለው ያስባሉ? የሙት ሸርጣኖች በሆዳቸው ውስጥ ጥርሶችን በመጠቀም በጥሬው ያጉራሉ።
- በቦአንትሮፒ የሚሰቃዩ ሰዎች ላም እንደሆኑ ያምናሉ እናም ህይወታቸውን እንደ ላም ለመኖር ይሞክራሉ።
- በሶስት ሰዎች መካከል የሚደረግ ድብድብ እውነተኛው ይባላል።
- በማርስ ላይ የፀሐይ መጥለቅ ሰማያዊ ነው።
- በአርጀንቲና ከጀመርክ በቲዎሪ ደረጃ "ለቻይና ጉድጓድ መቆፈር" ትችላለህ።
- በጥንት ጊዜ የሸረሪት ድር እንደ ማሰሪያ ያገለግል ነበር።
- ከሁሉም አጥንቶችዎ አንድ አራተኛው በእግርዎ ውስጥ ይገኛሉ።
- ደመና ከአንድ ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ሊመዝን ይችላል።
- በዓለም ላይ ትልቁ መቆለፊያ 916 ፓውንድ ይመዝናል።
- በእስያ የምትገኘው ሲሪላንካ ውስጥ ዝሆን የገደለ የሞት ፍርድ ይፈረድበታል።
- የሰው ልጅ የእጁ 50% ጥንካሬ የሚመጣው ከትንሿ ጣት ነው።
- አይስላንድ በአለማችን አንደኛ ሰላማዊ ሃገር ናት። ለዚህም ማሳያ ይሆን ዘንድ በሃገሩ ውስት አንድም የፀጥታ ሃይል አስከባሪ አለመኖሩ ነው።
- ከማጥናትም ሆነ ፈተና ከመፈተን በፊት ቸኮሎት መብላት የበለጠ እንዲገባ እና የማስታወስ ችሎታም እንዲጨምር ያረጋል።
- ላጲስ ከመፈጠሩ በፊት በእርሳስ የተፃፈን ለማጥፋት ሰዎች የዳቦ ቁራሽ ይጠቀሙ ነበር።
- ማንኛውም በጉርምስና እድሜ ውስጥ የሚገኝ ወጣት በየ20 ሰከንድ ስለ ወሲብ ያስባል።
- ባስ መቆሚያ ቦታ ጋር ጥይት በማይበሳው መስታወት ውስጥ የሚገኘው ንብረትነቱ ጥይት የማይበሳው መስታወት ድርጅት የሆነው $3 Million ይገኛል።ድርጅቱም "ይህንን መስታወት የሰበረ ብሩን መውሰድ ይችላል" ይላል። በዚህም ምክንያት ብዙዎች መስታወቱን ሰብረው ብሩን ሊወስዱ ቢሞክሩም ግን ማረግ አልቻሉም።
- በጃፓን የባቡር ጣብያ ውስጥ ሰዎችን በባቡር ውስጥ ለመጠቅጠቅ ሰራተኞች ተቀጥረው ይገኛሉ። የነሱም ስራ ሰዎችን በአስቸጋሪ ሁኔታ እየገፉ መጠቅጠቅ ነው።
- የኮምፒውተር ኪቦርዶችን በሁለት ጣታቸው ብቻ የሚጠቀሙ ሰዎች "Hunt and peck" ይባላሉ።
- "O" ታይፕ ደም ያላቸው ሰዎች "A" ታይፕ ደም ካላቸው ሰዎች በቢንቢ እና በወባ የመነከስ እድላቸው በእጥፍ ነው።
- ህፃን ልጆች 75% ሰውነታቸው ውሀ ነው።
- አምስተርዳም ውስጥ ከሞትክና ቀባሪ ካጣህ መንግስት እጅግ ያማረና የተከበረ የቀብር ስነስርአት አዘጋጅቶልሀል።
- የቀጭኔ ምላስ በጣም ረጅም ከመሆኑ የተነሳ የጆሮቻቸውን ውስጠኛ ክፍል ማሸት ይችላሉ።
- ሳምሰንግ ከአፕል 38 ዓመት እና 1 ወር ዕድሜ አለው።

45. “ስለ አማርኛ ቋንቋ እውነታዎች”

- ከምዕራብ አፍሪቃው ሀውሳ እና ከምስራቅ አፍሪቃው ስዋህሊ ቀጥሎ የአፍሪቃ ትልቁ ቋንቋ ነ ው።
- ከሰሜቲክ የቋንቋ ቤተሰቦች በስፋት በመነገር ያለም ሁለተኛ ቋንቋ ነው።
- ከ85.6ሚሊየን በላይ ተናጋሪ አለው።
- ከ 1272ዓም ጀምሮ የኢትዮጵያ የመንግሥት ቋንቋ ነው።
- ከአፍሪቃ ብቸኛው ባለፊደል ቋንቋ ሲሆን፣ ፊደላቱን ከወንድሙ ከግዕዝ ተውሷል። የላንቃ ድምፆችንምራሱ ፈጥሯል። (ሸ፣ጨ፣ዠ፣ቸ፣ጀ፣)
- የኢትዮጵያ የስራ ቋንቋ ሲሆን የአሜሪካ መንግስትም አማርኛ በአሜሪካ የስራ ቋንቋ እንዲሆን ፈቅዷል።
- ከ 1981 ጀምሮ አማርኛ በዶክተር አበራ ሞላ አማካኝነትእስከ ሙሉ ፊደላቱ የኮምፒውተር ቋንቋ ሆኗል ።
- ከመጋቢት 10/ 2008 ጀምሮ ደግሞ የጎግል መተርጎሚያ ቋንቋ ሁኗል።
- አሁን ላይ በጎግል አማካኝነት አማርኛን ወደ ማንኛውም ቋንቋ መተርጎም ይቻላል።
- አማርኛ በአለም ላይ ያሉ ነገሮችን ከ 85 ከሞቶው በላይ ማግለፅ ይችላል ።

46. “30 አስደናቂ ጤና ነክ እውነታዎች”

- ✓ አንድ አዲስ ሰው አንድ ቤት ውስጥ ሲገባ 37 ሚሊዮን ባክቴሪያዎች አብረው ይገባሉ።
- ✓ አንጎል 10 ዋት አምፖል በሚሰራበት የኃይል መጠን ነው የሚሰራው።
- ✓ ኒውሮኖች በዕድሜ ዘመናችን በሙሉ ማደጋቸውን አያቋርጡም።
- ✓ የፊት ፀጉር ከየትኛውም አይነት የቆዳ ፀጉር የበለጠ በፍጥነት ያድጋል።
- ✓ የሰው ልጅ ፀጉር አማካይ ዕድሜ ከ3-7 ዓመት ነው።
- ✓ ልብ 9 ሜትር ርቀት ደም ወደፊት ለመርጨት የሚያስችል ግፊት ይፈጥራል።
- ✓ ከመወለዳችሁ በኋላ የመስማት ኃይላችሁ ይቀንሳል።
- ✓ ከሳምንቱ ቀናት ውስጥ ሰኞ ድንገተኛ የልብ ህመም በብዛት የሚከሰትበት ቀን ነው።
- ✓ ጠዋት ጠዋት ቁመታችን ከማታ ቁመታችን በአንድ ሴንቲ ሜትር ይረዝማል።
- ✓ ራሱን የማይጠግን ብቸኛው የሰውነታችን ክፍል ጥርሳችን ነው።
- ✓ በእያንዳንዱ ደቂቃ 300 ሚሊዮን ሴሎች ሰውነታችን ውስጥ ይሞታሉ።
- ✓ በየቀኑ አንድ አዋቂ ሰው 300 ቢሊዮን ሴሎችን ያመርታል።
- ✓ የእያንዳንዱ ሰው የምላስ አሻራ የተለያየ ነው።
- ✓ ዓለማችን ላይ በብዛት የሚገኘው የደም አይነት ኦ ነው።
- ✓ የምትተኙበት ክፍል ቅዝቃዜ በጨመረ መጠን የምትመለከቱት ህልም መጥፎ የሚሆንበት ዕድልን ይጨምራል።
- ✓ ስሜታቸው ሲነካ ማልቀስ የሚችሉ እንስሳት ሰዎች ብቻ ናቸው።
- ✓ ሴቶች ከወንዶች ባነሰ መልኩ ካሎሪ ቀስ ብለው ያቃጥላሉ። በቀን በአማካይ 50 ካሎሪ ብቻ ሴቶች ያቃጥላሉ።
- ✓ ሴቶች ከወንዶች የበለጠ ጠረንን መለየት ይችላሉ።
- ✓ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ስቅ ይላቸዋል።
- ✓ ምራቃችሁ ከምግብ ጋር ካልተቀላቀለ ወይም ምግብ በምራቅ ካልሟሟ የምግቡን ጣዕም መለየት አንችልም።
- ✓ ከሰውነታችን ውስጥ እጅግ በጣም ጠንካራው ጡንቻ ምላስ ነው።

- ✓ እጅግ በጣም ጠጣሩ የሰውነታችን አጥንት የመንጋጋ አጥንት ነው።
- ✓ አንድ ሰው ሳይበላ 20 ቀን መቆየት ይችል ይሆናል ዉሃ ሳይጠጣ ግን ከ2 ቀን በላይ ለመቆየት ይቸገራል።
- ✓ ደም በቀጥታ የማያገኘው ብቸኛው የሰውነታችን ክፍል የዓይናችን ኮርኒያ ነው ኮርኒያ የኦክስጂን አቅርቦት በቀጥታ ከአየር ያገኛል።
- ✓ ሳንባችን በቀን ከሁለት ሚሊየን ሊትር በላይ አየር ይስባል።
- ✓ አፍንጫችን የአየር ማሞቂያ እና ማቀዝቀዣ መሳሪያችን ነው ቀዝቃዛውን አየር ያሞቃል፣ ሞቃቱን አየር ያቀዘቅዛል።
- ✓ የደም ሴሎች በአማካይ 120 ቀናት ይኖራሉ።
- ✓ በእያንዳንዱ ጊዜ ሰውነታችን ውስጥ 25 ትሪሊዮን ቀይ የደም ሴሎች ይኖራሉ።
- ✓ ፈገግታ ቢያንስ ሰላሳ ጡንቻዎችን ያንቀሳቅሳል።
- ✓ ውሃ ለሰዉነታችን ደም ዝዉዉር እጅግ ጠቃሚ ነው።

47. “የታላቁ ሕዳሴ ግድብ እውነታዎች”

- ✧ የግንባታው የመሰረት ድንጋይ የተቀመጠበት እለት - መጋቢት 24 ቀን 2003 ዓ.ም፤
- ✧ የግንባታው ስፍራ፡- በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሄራዊ ክልላዊ መንግሥት ጉባ ወረዳ፤
- ✧ የዋናው ግድብ ከፍታ -145 ሜትር፤
- ✧ የዋናው ግድብ ርዝመት -1 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር፤
- ✧ የዋናው ግድብ ውፍረት - የግድቡ ግርጌ 130 ሜትር ሲሆን የግድቡ ጫፍ ወይም የላይኛው ክፍል 11 ሜትር፤
- ✧ ግድቡ የሚይዘው የውሃ መጠን -74 ቢሊየን ኪዩቢክ ሜትር፤
- ✧ ግድቡ የሚሸፍነው የቦታ ስፋት -1 ሺህ 680 ስኩዌር ኪሎ ሜትር፤
- ✧ ሲጠናቀቅ ውሃ የሚተኛበት መሬት ርዝመት 246 ኪሎ ሜትር፤
- ✧ የኮርቻ ግድብ /Saddle Dam/ ከፍታ- 50 ሜትር፤
- ✧ የኮርቻ ግድብ /Saddle Dam/ ርዝመት 5.2 ኪ.ሜ
- ✧ ግድቡ16 የኃይል ማመንጫ ዩኒቶች አሉት፤
- ✧ እያንዳንዱ ዩኒት የሚያመነጨው የኃይል መጠን ከ375 እስከ 400 ሜጋ ዋት፤
- ✧ ጠቅላላ ግድቡ ሲጠናቀቅ የሚያመነጨው ኃይል መጠን፡ 6 ሽህ 450 ሜጋ ዋት
- ✧ ከ500 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በመስኖ ማልማት ያስችላል፤
- ✧ ከ10 ቶን በላይ ዓሳን ማምረት ያስችላል፤
- ✧ ከ40 በላይ ደሴቶች ይኖሩታል።
- ✧ ከግድቡ የውሃ ላይ የትራንስፖርት፣ የአሳ ልማትና ለቱሪዝም ኢንዱስትሪ አገልግሎት ይውላል።..
- ✧ ታዳሽ ኃይል በመሆን የከባቢ ብክለትን ይከላከላል።
- ✧ የከተሞችን ተሞክሮ በመቀመር በአዲሱ የህዳሴ ሐይቅ ዙሪያ ዘመናዊ ከተማ ለመመስረት ያስችላል።
- ✧ ግድቡ በትልቅነቱ በአፍሪካ አንደኛ ደረጃን ይዟል።

48. “የሰው አንጎል እውነታዎች”

- ➢ 80% አንጎል ውሃ ነው።
- ➢ አንድ መካከለኛ የጎልማሳ ወንድ አንጎል 1375 ግራም ይመዝናል።
- ➢ የተተወ የልጆች አንጎል ከጤናማ ልጅ በጣም ትንሽ ሊሆን ይችላል።
- ➢ ሰመመን (ሕመም) ተብሎ የሚጠራው ሁኔታ የስሜት ሕዋሳትን ወደ መደራረብ ሊያመራ

ይችላል። በሌላ አገላለጽ አንዳንድ ሰዎች ቃላትን መቅመስ ወይም ቀለሞችን መስማት ይችላሉ።

- የሰው አንጎል ቀኝ ጎን ራስን የማወቅ ሃላፊነት አለበት።
- በአንጎል ሴሎች ላይ የሚደርሰው ማንኛውም ጉዳት ሙሉ በሙሉ ሊጠገን አይችልም።
- የአከርካሪ አጥንት መሠረት በጣም ስሜታዊ የሆኑ የነርቭ ክሮች አሉት።
- አንጎል ከሞተ በኋላ እስከ 37 ሰዓታት ያህል ድረስ የኤሌክትሪክ ሞገድ ምልክቶችን መላክ ይቀጥላል።
- አንጎል ቀን ከሌት በበለጠ በጣም ንቁ ነው።
- አንጎል ራሱ ህመም ሊሰማው አይችልም።
- አንጎል በ 10 ዋት አምፖል ኃይል መጠን ይሠራል።
- በምትተኛበት ጊዜ እንኳን - አንጎልህ እንደ አንድ ትንሽ አምፖል ብዙ ኃይል ያመነጫል።
- ዕድሜው እየገፋ ሲሄድ አንጎሉ በዓመት አንድ ግራም ብቻ ያጠፋል። ከአራት አንጎል ብቻ የአንጎል ሴሎች የሚሰሩ እና የተቀሩት ህዋሶችም በቁጠባ ውስጥ ይቀመጣሉ።
- የእኛ አንጎል ከ 100 ቢሊዮን የነርቭ ሴሎች አሉት። የአዋቂ ሰው አንጎል ከጠቅላላ የሰውነት ክብደት 2% ገደማ ነው።
- በአዕምሮ ግራ ግራ በኩል አዳምጡ እና ሴቶች ሁለቱንም የአንጎል ጎኖች ይጠቀማሉ።
- አማካይ የሰው አንጎል 3 ፓውንድ ይመዝናል።
- የሰው አንጎል በደቂቃ እስከ 1,000 የሚደርሱ ቃላትን ማንበብ ይችላል።
- የሰው አንጎል ሕዋስ እንደ ኢንሳይክሎፔዲያ ብሪታኒካ 5 እጥፍ ያህል መረጃ መያዝ ይችላል። ወይም ለዚያ ጉዳይ ማንኛውም ሌላ ኢንሳይክሎፔዲያ።
- የሰው አንጎል 60% የነጭ ጉዳይ እና 40% ግራጫ ንጥረ ነገር ነው ያለው።
- የሰው አንጎል ከአጽናፈ ሰማይ አተሞች ጋር እኩል የሆኑ ሀሳቦችን ለመፍጠር ችሎታ አለው።
- የሰው አንጎል ከ 10 ቢሊዮን በላይ የነርቭ ሴሎች እና ከ 50 ቢሊዮን በላይ ሌሎች ሴሎች የተገነባ እና ከሶስት ፓውንድ በታች ይመዝናል።
- 3000+ Ghz የማሄድ ፍጥነት ያለው የሰው አንጎል በጣም ኃይለኛ ኮምፒተር ነው የሰው አንጎል እንደ ቅቤ በጣም ለስላሳ ነው።
- የሰው አንጎል በ 18 ዓመቱ ማደግ ያቆማል።
- የሰው አንጎል የሰውነታችንን ሀይል 20% የሚጠቀምና 2% የሚሆነው የሰውነታችንን ክብደት የሚጨምር ነው።
- አንድ ነገር በምንነካበት ጊዜ በ 124 ሚ.ግ. ወደ አንጎላችን መልእክት እንልካለን።
- የቀዝቃዛ የአየር ሁኔታ የሰዎችን የማስታወስ እና ትኩረትን ያሻሽላል።
- አማካይ የሰው አንጎል ስፋት 140 ሚሜ ነው።
- የሰው አንጎል አጠቃላይ ስፋት 25,000 ካሬ ሴ.ሜ ነው።
- የአእምሮዎ የረጅም ጊዜ ማህደረ ትውስታ እስከ 1 ኪድሪሊዮን (1 ሚሊዮን ቢሊዮን) የሚደርሱ የተለያዩ መረጃዎችን ይይዛል።
- በሰው አንጎል ውስጥ ከ 1, 000, 000, 000, 000, 000 በላይ ግንኙነቶች እንዳሉት ይገመታል።
- ወደ አንጎል የሚወስዱ እና የሚመጡ ግፊቶች በሰዓት እስከ 170 ማይል ያህል ይጓዛሉ።
- በአማካይ የአዋቂ ሴት አንጎል ክብደት 1275 ግራም ነው።
- በአማካይ ከ 100,000 እስከ 1,000,000 ኬሚካዊ ግብረመልሶች በአንጎላችን ውስጥ ይከናወናሉ።
- አማካይ የሰው ጭንቅላት 10 ፓውንድ ይመዝናል።
- የሰው አንጎል አማካይ ርዝመት 167 ሚ.ሜ ነው እና አማካይ ቁመቱ 93 ሚሜ ነው።
- የሰውን አንጎል ግራ ክፍል የሰውነት ቀኝ ጎን ይቆጣጠራል እንዲሁም የአንጎል የቀኝ ጎን የአካሉን ግራ ክፍል ይቆጣጠራል።

- የነርቭ ስርዓት በሰዓት በ 180 ማይሎች ፍጥነት መልእክቶችን ወደ አንጎል ያስተላልፋል።
- በፍቅር ጊዜ አንጎሉ በአምፌታሚኖች የሚለቀቁትን የነርቭ ሐኪሞች እና ሆርሞኖች ተመሳሳይ ኮክቴል ያስለቅቃል፣ ይህም የልብ ምትን እንዲጨምር፣ የምግብ ፍላጎት እና እንቅልፍ ያስከትላል እንዲሁም ከፍተኛ የመረበሽ ስሜት ያስከትላል።
- የእርስዎ አንጎል 20% የሚሆነው የኦክስጂን እና የካሎሪ መጠንዎን ይጠቀማል።

49. "የማናስተውላቸው ልምዶቻችን አንዳንዶቹ ለከፋ የጤና ችግር እንደሚዳርጉ አስበውት ያውቃሉ?"

- መድኃኒት በቀዝቃዛ ውሃ አይውሰዱ።
- ውሃ ጠዋት አብዝተው ማታ ግን በጥቂቱ ይጠጡ።
- መድኃኒት ከወሰዱ ወይም ከተመገቡ በኋላ ወዲያው አይተኙ።
- ፕላስቲክ 'React' ስለሚያደርግ ሻይ በፕላስቲክ ዕቃ አይጠጡ ምግብንም በPolythene ወረቀት ላይ አይመገቡ።
- የስልክዎ ባትሪ መጠን እጅግ ዝቅተኛ ከሆነ ስልክ አያንሱ። ምክንያቱም በዚህ ሰዓት 'ራዴሽኑ' በ1000 እጥፍ ይጠነክራል።
- የሞባይል ካርድ ሲገዙ በጥፍርዎ አይፋቁት። ምክንያቱም ቁጥሩ የተሸፈነው በሲሊቨር ናይትሮ ኦክሳይድ ስለሆነ ለቆዳ ካንሰር ተጋላጭ ያደርጎታል።
- ሞባይሎትን በፍጹም ቻርጅ ላይ አድርገው አይጠቀሙ።
- በሞባይል ስልክ ሲነጋገሩ በግራያለው ጆሮዎ ብቻ ይነጋገሩ።
- የተሻለ የእንቅልፍ ሰዓት የሚባለው ከምሽቱ 4:00 ሰዓት እስከ 10:00 ነው።
- ከቀኑ 11:00 ሰዓት በኋላ ከበድ ያለ ምግብ አይውሰዱ።
- እንዲሁም አንድ ነገር በፍፁም አይዘንጉ - ይሄንን መረጃ ሼር ማድረግዎ።
- የአለማችን ትልቋ ሀገር ሩስያ ስትሆን 17.09 ሚሊየን km2 የሆነ የቆዳ ስፋት አላት።
- በአለማችን ላይ በርሀማዋ ሀገር ሊቢያ ስትሆን ከአጠቃላይ የቆዳ ስፋቷ 99% የሚሆነው በረሀማነት የሚፈረጅ ነው።
- በአለማችን ላይ ምንም አይነት ወንዝ የሌላት ሀገር ሳውድ አረቢያ ነች።
- ለሴቶች የመምረጥ መብትን ቀድማ የሰጠች ሀገር ኒውዝላድ ነች።
- አሜሪካ በአለማችን ላይ ብዙ ክርሰቲያኖች የሚኖሩባት ሀገር ስትሆን ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛቷ 245.9 ሚሊየን የሚሆኑት ክርሰቲያኖች ናቸው።
- ብዙ የሆነ የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ ህዝብ ያላት ሀገር ኢንዶኔዢያ ስትሆን ከ209 ሚሊየን በላይ የሚሆነው ህዝቧ ሙስሊሞች ናቸው።
- በአለማችን ላይ ከፍተኛ የሆነ የሀይቅ ብዛት ያላት ሀገር ካናዳ ስትሆን ወደ 3 ሚሊየን የሚጠጉ ሀይቆች ሲኖራት ይህም በአለማችን ላይ ካሉት የሀይቆች ብዛት 60% ይሸፍናል።
- በአለማችን ላይ ከፍተኛ የሆነ የግድያ ወንጀል የሚፈፀምባት ሀገር ኤል ሳልቫዶር ስትሆን በአማካኝ ከ100,000 ሰዎች ውስጥ 55.5% የሚሆኑት ግድያ ይፈፀምባቸዋል።
- በሀገሯ ፓርላማ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የሴቶች ቁጥር ያላት ሀገር ሩዋንዳ ስትሆን በፓርላማዋ ካሉት ጠቅላላ መቀመጫዎ ውስጥ 56.3% (50/80) የሚሆነው የተያዘው በሴቶች ነው።
- ዴንማርክ በአለማችን ላይ አነስተኛ የሆነ የሙስና ወንጀል የሚፈፀምባት ሀገር ናት።

50. "ለአንጎል ጎጂ የሆኑ 8 ልማዶች"

1. ቁርስ አለመመገብ:

ቁርስ የማይመገቡ ከሆነ በሰውነትዎ ውስጥ የሚገኘውን የደም ስኳር መጠን ስለሚቀንስ ለአንጎል

የሚደርሰውን የምግብ መጠን በማስተጓጎል ለጉዳት ይዳርገናል።

2. **በህመም ወቅት በቂ እረፍት አለማድረግ:**

ሰውነታችን በህመም ሲጠቃ በቂ እረፍት ማድረግ እና ከህመሙ ማገገም በአንጎል ላይ ተጨማሪ ጫና እንዳይኖር ይረዳል።

3. **ሲጋራ ማጤስ:**

ሲጋራ ማጤስ የሚያስከትለው ጉዳት ከፍተኛ እንደሆነ የሚታወቅ ነው። የልብ ህመም፣ የሳምባ ካንሰር እና ስትሮክን ከማስከተል ባለፈ በአንጎል ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል።

4. **ከፍተኛ የስኳር መጠን ያላቸውን ምግቦች ማዘውተር:**

ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ጣፋጭነት ያላቸው ምግቦችና መጠጦች ማዘውተር ለአንጎል ጉዳት መንስኤ ናቸው።

5. **የአየር ብክለት:**

አንጎል ከየትኛውም የሰውነት ክፍሎቻችን በበለጠ ኦክስጂን ያስፈልገዋል። የምንተነፍሰው አየር የተበከለ ከሆነና ለአንጎል የሚደርሰው የኦክስጅን መጠን ከቀነሰ ጉዳት ያስከትላል።

6. **የእንቅልፍ እጦት:**

እንቅልፍ አንጎልን እረፍት እንዲያገኝ የምናደርግበት ሂደት ስለሆነ በቂ እንቅልፍ አለመውሰድ ለጉዳት ይዳርጋል። ለረጅም ጊዜ እንቅልፍ ማጣት የአንጎል ህዋሳት ሞትን ያፋጥናል።

7. **የአልኮል መጠጥ ማብዛት:**

በቀን የምንወስደው የአልኮል መጠጥ ከፍተኛ ከሆነ የአንጎል ህዋሶቻችንን ቀስ በቀስ ሊገድል ስለሚችል ከፍተኛ ጉዳት ያስከትላል።

8. **የምግብ አይነቶችን አለመምረጥ:**

ለጤና ተስማሚ የሆኑ ምግቦችን መመገብ ለአንጎል ጤናማነት ወሳኝ ነው።

51. "ኢትዮጵያ (Ethiopia)"

1. በአፍሪካ በቀኝ ግዛት ያልተገዛች ብቻኛ ሀገር ናት።
2. ከሌሎች በተለየ አስራ ሶስት ወር ያላት ሀገር ናት።
3. ከ80 በላይ ቋንቋ ይነገርባታል።
4. የቡና ተክል ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው ኢትዮጵያ ውስጥ ነው።
5. 13 ቅርሶችን በ UNESCO በማስመዝገብ ከአፍሪካ ቀዳሚ ናት።
6. ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው መርካቶ የፍሪካ ትልቁ የገበያ ማእከል ነው።
7. በአሁጉራችን በህዝብ ብዛት ናይጄሪያን በመከተል ሁለተኛውን ስፍራ ይዛለች።
8. በዓለማችን የባህር ወደብ ከሌላቸው ሀገራት በህዝብ ብዛት ቀዳሚ ናት።
9. በአፍሪካ የራሷ ፊደልና ቁጥር ያላት ብቸኛዋ ሀገር ናት።
10. በዓለማችን ብዙ ርቀት በመጓዝ ቀዳሚ የሆነው የአባይ ወንዝ መነሻ ናት።
11. የኢትዮጵያ ዋና ከተማ የሆነችው አዲስ አበባ የአፍሪካ ህብረት መቀመጫ ናት።
12. ከ200 በላይ የቋንቋ ዘዬ ይነገርባታል።
13. የሀገሪቷ ሰም በመጽሐፍ ቅዱስ(42+)ና በቁራን በርካታ ጊዜ ተጠቅሷል።

14. በአፍሪካ የመጀመሪያው የኦሎምፒክ ወርቅ ሜዳልያ ያስገኘው ኢትዮጵያዊው አበበ በቂላ ነው።
15. ከሌሎች ሀገራት የተለየ የሰዓት እና የካላንደር አቆጣጠር አላት።
16. ከአርመንያ በመቀጠል ክርስትና ብሔራዊ ሃይማኖቴ ነው ብላ የተቀበለች ሁለተኛዋ ሀገር ናት።
17. በአፍርካ የመጀመሪያው መስጊድ መገኛ ናት።
18. በቀንድ ከብት ብዛት ከአሁጉራችን ቀዳሚናት።
19. ክርስቶስ የተሰቀለበት መስቀል የቀኝ ክፍሉ የሚገኝባት ሀገር ናት።
20. በኢትዮጵያ ውስጥ 924 የአእዋፍ ዝርያ ያሉ ሲሆን 23 ያህሉ በሌላ ዓለማት የማይገኙ ናቸው።

ምዕራፍ አምስት

ቴክኖሎጂ (Technology)

1. “የኮምፒውተር ኪቦርዳችን ላይ ከላይ የሚገኙትን (F1-F12) በተኖች ጥቅማቸውን”

- እነዚህን የኪይቦርድ በተኖች ከዚህ በፊት ድምፅ ለመጨመር እንዲሁም የብርሃን መጠን ለማስተካከል ተጥቀምውባቸው ይሆናል። ነገር ግን ጥቅማቸው ከዚህ ከፍ ያለ ነው ሁሉም ኮምፒውተር በሚያስብል ሁኔታ እነዚህን በተኖች ይዞ ነው የሚመጣው። እና ምንም ማስተካከል ሳያስፈልግ መጠቀም እንችላለን። ይሁን እንጂ አንዳንድ ኮምፒውተሮች ላይ እነዚህን በተኖች ለመጠቀም FN የሚለውን በተን በቅድሚያ መንካት አለብን።

✓ **“ከF1 እስከ F12 ያሉትን በተኖች ጥቅም”**

i. **የ “F1” ጥቅሞች**

- ከ”Windows ቁልፍ (button) ጋር በጋራ ስንነካው help menuን ያመጣልናል።
- Excel እና Word በምንጠቀምበት ወቅት ከ Control ጋር በጋራ ስንነካው Hides or displays ribbon menu ያደርግልናል።

ii. **የ “F2” ጥቅሞች**

- Alt + Ctrl + F2 Windows Document Library in Microsoft Office.
- Allows you to edit the selected folder or file name in Windows Explorer.

iii. **የ “F3” ጥቅሞች**

- Opens search feature in Windows Explorer.
- Shift + F3 - lets you change from lowercase to uppercase to all caps in Word.
- Opens find feature in Firefox and Chrome.

iv. **የ “F4” ጥቅሞች**

- Alt + F4 closes window
- Places the cursor in the address bar in Explorer.

v. **የ “F5” ጥቅሞች**

- Starts slideshow in Power Point
- Refreshes Internet browser pages
- Opens Find and Replace in Microsoft Office

vi. **የ “F6” ጥቅሞች**

- Goes to the next page in a split screen in Microsoft Word
- Ctrl + F6 lets you easily switch between Word documents

vii. **የ “F7” ጥቅሞች**

- Alt + F7 does a spelling and grammar check in Microsoft Word
- Shift + F7 open Thesaurumode Microsoft Word

viii. **የ “F8” ጥቅሞች**

- In Excel, enables extend mode for arrow keys
- Enables safe mode in Windows

ix. **የ “F9” ጥቅሞች**

- Ctrl + F9 inserts empty fields into Word
- Updates fields in Word

x. **የ “F10” ጥቅሞች**

- Opens menu bar
- Ctrl + F10 maximizes window in Word
- Shift + F10 does the same thing as a right click

xi. **የ “F11” ጥቅሞች**

- Exits and enter full screen mode in browsers
- Shift + F11 adds a new spreadsheet in Excel

xii. **የ “F12” ጥቅሞች**

- Opens Save As in Word
- Shift + F12 saves Word document
- Ctrl + F12 opens Word document

2. “ሮቦቶች እና የተሰማሩበት የስራ ዘርፍ”

ሮቦቶች በተለያዩ ሰዎች እይታ የተለያየ መልክ ይዘዉ ኖረዋል። ሮቦት የሚለዉ ስም "robota" ከሚለዉ የቼክ ቋንቋ የመጣ ቃል ሲሆን፣ ትርጉሙም የግዳጅ ሠራተኛ ወይም አገልጋይ ማለት ነዉ። ሮቦቶች ልክ እንደ ሰማቸዉ ትርጉም ሳይታክቱ እና ደከመኝ ሳይሉ ስራቸዉን የሚያከናዉኑ የሰዉ ልጆች አጋዥ ናቸዉ። ለአንዳንድ የሰዉ ልጆች ረዳት እንደሆኑ ተደርገዉ የሚታዩት ሮቦቶች በሌሎች ሠዎች ዓይን ደግሞ ከስማቸዉ አፈንግጠዉ ወደፊት የሰዉ ልጆችን ሊተኩ፣ ሊቆጣጠሩና ሊገዙም የሚችሉ አደገኛ ሰዉ-ሰራሽ ማሽኖች እንደሆኑ ተደርገዉም ይታያሉ። በዓለም ዙርያ በተለያዩ ዘርፎች፣ በተለይም በኢንዱስትሪዉ ሥራ ላይ የተሰማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሮቦቶች በርካታ አገልግሎት እየሠጡ ይገኛሉ። ከእነዚህ ዉስጥ ጥቃቶቹን እንመልከት፡-

1. ወተት አላቢዉ ሮቦት:

እኛ በተለምዶዉ ከምናዉቀዉ በሰዉ እጅ ከሚከናወነዉ የላም ወተት አስተላለብ ሌላ ሮቦቶች ይህንን ተግባር እጅግ በተቀላጠፈ ሁኔታ እንደሚያከናዉኑ ታዉቃላቹህ? "Robotic Milking" ወይንም "Automatic Milking System" -- AMS" በመባል የሚታወቀዉ አሰራር ያለምንም የሰዉ ጣልቃ ገብነት በተቀላጠፈ ሁኔታ በኮምፒዉተር ትዕዛዝ የሚታገዙ ሮቦቶች ከላም ላይ ወተትን የማለቡን ተግባር ይፈጽማሉ። የመሣሪየዉ ዋጋ ከ140 እስከ 200 ሺህ ዶላር ያወጣል።

2. የሮቦት ፖሊስ:

በማሽን የታገዘ ግድያ መፈጸም አዲስ ነገር አደለም። ጠመንጃ፣ ታንክ፣ የጦር አዉሮፕላን እና የመሳሰሉት በሰዉ ቢታገዙም ይህንኑ ሲፈጽሙ የቆዩ ማሽኖች ናቸዉ። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሰዉ አልባ ድሮኖች የሚፈለገዉ ቦታ ድረስ በመሄድ ጥቃት እንዲሰነዝሩ እየተደረገ ይገኛል። ሮቦቶች ቦምብ ለማምከን፣ ወንጀለኛን አድኖ ለመያዝ እና ለመሳሰሉት ከፍተኛ ጥቅም የወንጀል መከላከል ስራዎች የአሜሪካ የፖሊስ ሀይልን ማገዝ ከጀመሩም ሰነባብተዋል። ነገር ግን በ2006 ዓ.ም የሆነዉ ለየት ያለ ነገር ነበር። በአሜሪካ ሀገር በጥቁሮች ላይ በሚፈጸም ተከታታይ የፖሊስ ግድያ ተበሳጭቶ በዳላስ ቴክሳስ ዉስጥ አምስት ፖሊሶችን የገደለዉን ጥቁር አሜሪነበር ስናይፐር (የሮቦቱ ስም) አድኖ በመግደል ሮቦት ለመጀመሪያ ጊዜ በወንጀል መከላከል ግድያ ላይ ቀጥተኛ ተሳታፊ ሆኗል።

ሮቦቱ የሚፈነዳ ገዳይ መሳሪያን በመሸከም ነበር ስናይፐሩ ወደተሸሸገበት ቦታ በመሄድ ግድያዉን የፈጸመዉ። ይህ ስናይፐር ተጨማሪ ሰዎችን ከመግደሉ በፊት ለማስቆም ያለዉ ብቸኛ አማራጭ ይኸዉ እንደነበር የተናገሩት ባለስልጣናት፣ ሰዉን ወደእርሱ ልኮ በቁጥጥር ስር ለማዋል ወይንም በሰዉ እጅ ለመግደል ፍጹም አደገኛ ሁኔታ እንደነበርም ገልጸዋል። ምክንያቱም ደግሞ ስናይፐሩ ከዚህ ቀደም የሚሊቴሪ ስልጠና የወሠደ በመሆኑ እና አንዲሁም ግድያ ይፈጽም የነበረበት ቦታ እርሱን በቁጥጥር ለማዋል ፈጽሞ የማይመች ስለነበረ ነዉ። በሚሊቴሪ ስራ ላይ የዋለ የሮቦት አሰራር በአሜሪካ የፖሊስ ሃይል ዉስጥ ተሰማርቶ ሰዉን በመግደል ተግባር ላይ መዋሉ አከራካሪ ሆኖ ሰንብቷል።

ወደፊት ይህ ቴክኖሎጂ ከመስመር የወጣ አሠራር ዉስጥ ሊገባ እንደሚችልም አመልካች ሁኔታን ፈጥሯል። በአንጻሩ ሮቦቶች ከባድ በሆነ ሁኔታ ዉስጥ አልፈዉ የነፍስ ማዳን ስራ ላይ ተሰማርተዉ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጡም ይገኛሉ። በ2001 ዓ.ም ኒዉ ዮርክ ከተማ ላይ በአሸባሪዎች ጥቄት በተፈጸመበት ከወደሙት የዓለም የንግድ ማዕከል ህንፃዎች ዉስጥ ከፍተኛ ሙቀት ካለዉ ብረታ ብረትና ከሲሚንቶ ፍርስራሽ በታች የተረፉ ሰዎችን ለመፈለግ በርካታ ሮቦቶች ተሠማርተዉ ነበር።

3. ሮቦት ዘበኛ:

"Knightscope" የተባለ ተንቀሳቃሽ ሮቦት በትምህርት ቤቶች፣ በንግድ ስፍራዎች፣ በህዝብ መናፈሻዎች፣ በቢሮ ህንፃዎችና በመሳሰሉ ስፍራዎች ላይ የጥበቃ ስራን ለማከናወን በስራ ላይ ዉሏል። የሮቦቱ አምራቾች እንደገለጹት ለዚህ ፈጠራ የተነሳሱበት በዲሴምበር 14 2012 ዓ.ም በአሜሪካኗ የከነቲከት (Connecticut) ግዛት በሚገኝ ሳንዲ ሁክ የተባለ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ዉስጥ በአንድ ነፍሰ ገዳይ አማካኝነት የተከሰተ አሰቃቂ የሆነ የህጻናት እልቂት ነዉ። የሮቦቱ ፈጣሪዎች እንዲህ ያለዉን አደጋ እንዳይከሰት የቅድመ መከላከል በማድረግ ይህ ጠባቂ ሮቦት ትልቅ አስተዋጽዎ እንደሚኖረዉ ተናግረዋል። 1.5 ሜትር ርዝመትና 136 ኪሎ ግራም ክብደት ያለዉ ይህ ሮቦት በላዉ ላይ በተገጠሙለት የቪድዮ ካሜራ፣ ሙቀትን በመለካት እንቅስቃሴን መለየት በሚችል ቴክኖሎጂ፣ ራዳር፣ ጨረር፣ ማይክሮፎንና የአየር ብክለት መለኪያ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ጥበቃን ማከናወንና የወንጀል እንቅስቃሴዎችን መከታተል ይቻላል። አስጊ ሁኔታን ካስተዋለ ወዲያዉኑ ለፖሊስ መጠቆም የሚችልበት ፈጣን የመገናኛ ቴክኖሎጂም ተካቶለታል።

4. ሮቦት ሼፍ:

"Moley" ይባላል። በዓለም ላይ የመጀመሪያዉ የሮቦት ሼፍ ነዉ። ሁለት እጆች ያሉት ይህ ሮቦት ከሙሉ አዉቶማቲክ የምግብ ማደራጃና ማብሰያ ጋር አብሮ የሚመጣ ሲሆን እጆቹ ከጣሪያ የሚወርዱና የሰዉ ልጅ እጅ የሚሰራዉን ተግባር ማከናወን የሚችሉ ናቸዉ። በሚያስደንቅ ሁኔታ የሰዉ እጅ አይነት

እንቅስቃሴ ያለዉ ይህ ሞሊ የሮቦት ሼፍ የምግብ ግብዓቶችን ከመምረጥ፣ ከመመጠን ወይም ከመለካት፣ ከመክተፍ፣ ከማማሰል፣ ማብሰያ እቃዎችን አንስቶ የሚገባቸዉ ቦታ ከማስቀመጥ አንስቶ አብስሎ እስኪጨርስ ማብሰያዉን እስከ ማጽዳት ድረስ አስገራሚ የማብሰል ክንዉን ያካሂዳል።

ማብሰል በራሱ የሚወደድ ተግባር ቢሆንም፣ በስራና የዕለት ተዕለት ጉዞ ዉስጥ የተጠመዱ ሰዎች ወደፊት በማብሰል ይጠፍ የነበረዉ ሰዓታቸዉን ከሚወዱት ሰዉ ጋር በመጫወት ወይንም ሌሎች ነገሮችን በማከናወን ሊያሳልፉ ይችላሉ። ይህንን ሮቦት በ "touch screen" እንዲሁም በስልክ ላይ በሚጫን "app" መቆጣጠር ይቻላል። የሮቦት እጁን መጠቀም በማያስፈልግ ጊዜ ወደ ጣሪያዉ እንዲሰበሰብ አድርጎ ማብሰያ ቦታዉን ለሰዉ ጥቅም ማዋል ይቻላል። ይህ ቴክኖሎጂ የሙከራ ጊዜዉን አጠናቆ በጥቂት ዓመታት ዉስጥ ለተጠቃሚዎች እንደሚቀርብ ታዉቋል።

5. ሮቦት የፍርማሲ ሰራተኛ:

ከላይ እንደተጠቀሰዉ በካሊፎርኒያ የዩንቨርስቲ ሆስፒቴል ዉስጥ የሚገኝ መድሀኒት ቤት ዉስጥ አገልግሎት መስጠት የጀመረዉ ሮቦት የመጀመሪያዉ በመስኩ በፍርማሲ የተሰማራ ሮቦት ቢሆንም፣ ይህ አሰራር ወደፋት በስፍት ሊቀጥል እንደሚችል አመልካች ሁኔታ እየታየ ነዉ። እንግሊዝ ሀገር በሚገኝ ሆስፒታል ዉስጥ የሚገኝ ልላ መድሀኒት ቤትም ሰዉን ተክቶ የፍርማሲ ስራ የሚሰራ ሮቦት ተግባራዊ ሆኗል። መድሃኒቶች ከመደርደሪያቸዉ ወስዶ ለደንበኞች ማቀበል የሚችል እጆች የተገጠሙለት ሮቦት ይህንን ተግባር በጥቂት ሴኮንዶች ዉስጥ ያከናዉናል።

6. አረጋዉያን አጫዋቹና ረዳቱ ሮቦት:

በጃፓን ዉስጥ የአረጋዉያን ቁጥር ከፍተኛ ነዉ። 20 በመቶዉ የጃፓን ህዝብ እድሜዉ ከ65 ዓመት በላይ ሲሆን፣ ወጣቱ ህብረተሰብ ደግሞ ከማነሱ ባሻገር ህይወቱ እጅጉን የተጨናነቀ ዓይነት ስለሆነ ከአረጋዉያን ጋር የሚያጠፋዉ ጊዜ የለዉም። ይህንን ችግር ለማቃለል የሚችል የሙከራ የሮቦት ቴክኖሎጂ በዚችዉ ሀገር ተፈጥሮ በስራ ላይ ዉሏል። ፈጠራዉን በስራ ላይ ያዋለዉ የአረጋዉያን መጦሪያ ተቋም ቴክኖሎጂዉ ደንበኞቹን ለማገልገል አስችዋጽዎ እያደረገ እንደሚገኝ ገልጿል። ሌላ አይነት የአረጋዉየን አጋዥ ሮቦት ደግሞ ምግብንና ዉሃን በማቀበል በብራትን በማብራትና በማጥፋት እንዲሁም ቤትን በማጽዳት አረጋዉያንን የሚያገለግል ሲሆን፣ ወደፊት ይህ አሰራር በተለያዩ ሀገራት በሰፊዉ ተግባራዊ እንደሚሆን ይጠበቃል።

7. ገዳይ ተዋጊ ሮቦቶች:

ሰዉ ሰራሽ ክህሎት እና የሮቦቲክ አሰራር የተገጠመላቸዉ ቴክኖሎጂዎች በጦርነት ዘርፍ ከገቡ ሰነባበተ። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነዉ የድሮን ቴክኖሎጂ ነዉ። ፓይለቱ በሺህ ኪሎሜትሮች ርቆ ድሮኑን በሪሞት ኮንትሮል በመቆጣጠር የሚፈለገዉን ኢላማ መቶ የጠላትን ግዛት መደምሰስና ሰዉን መግደል ይችላል። የወደፊቱ ስጋት ደግሞ ከዚህ ባለፈ መልኩ የሮቦት ወታደሮች "humanoid robots" ቢፈጥሩስ የሚል ነዉ። እንደዚህ ያለዉ ፈጠራ ሀያዉ ከሆነ የጦርነት መልክ ከዚህ በፊት ሆኖ በማያዉቅ ሁኔታ እስከ ወዲያኛዉ ሊቀየር ይችላል። አቅም የሌላቸዉ ሀገራት የሰዉ ወታደር ሲያሰልፉ ኃያላኑ በሮቦት ወታደሮቻቸዉ የሚዋጓቸዉ ከሆነ ጦርነት አዲስና አስፈሪ መልክ ይይዛል ማለት ነዉ። ጦርነት መቼም ቢሆን በጎገጽታ ኖሮት አያዉቅም፣ ወደፊትም አይኖረዉም! ይሁንና መከሰቱ በማይቀር ወቅት ግን ይብዛም ይነስም ዓለም ዓቀፍ መተዳደሪያና ደንብ አለዉ።

ለዚህ ነዉ እንደ ኒኩሊየር ቦንብ ያለ ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ አልያም ደግሞ የኬሚካልና ባዮሎጂካል

መሳሪያን በጦርነት ላይ መጠቀም አይቻልም የሚል ስምምነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተተግብሮ የሚገኝዉ። ታድያ ወደፊት ሮቦት ወታደሮች ቢሰሩ እገዳ ይጣልባቸዉ ይሆን? ኢላን መስክን ጨምሮ ሌሎች ታዋቂ ግለሰቦች ገዳይ ሮቦቶች ፈጽሞ እንዳይሰሩ ካሁኑ ጠንካራ እገዳ መጣል አለበት ሲሉ የተባበሩት መንግስታት ይህን ጉዳይ በህግ ደረጃ እንዲያስፈጽም ዋና ኃላፊነትን ወስዶ መስራት አለበት ብለዋል።

የስራ አጥነት ስጋት፣ "ከእኛ ብቃት አልፈዉ እና ትዕዛዝ መቀበል አቁመዉ ይቆጣጠሩን ይሆን?" የሚል ፍርሃትና ሌሎች በርካታ የጎንዮሽ ስጋቶች እንዳሉ ሆነዉ የሮቦቶች በጎ ገጽታ ደግሞ የሚካድ አደለም። "እኛዉ የፈጠርናቸዉ ሮቦቶች ይገዙን ይሆን?" ተብሎ በሚሰጋበት ወቅትም የሰዉ ልጅ አዲስ ነገርን የማወቅ ጉጉቱ ከምድር አልፎ ጎዋ ድረስ በመሄድ ጭራሽ አይቶ የማያዉቀዉን የአጽናፈ ዓለም ክፍል የማየት ፍለጎቱን ፈጽሞ አላቋረጠም። ምናልባትም የሰዉ ልጅ ወደፊት ለምርምር ብቻ ሳይሆን ለቱሪዝም እና ለጫጉ ሽርሽር ከዉብ ደሴቶች ባለፈ ጉዞዉን ወደ ጠፈር ያደርግ ይሆን?

3. “IT Acronyms”

- ✓ **GOOGLE**-------Global Organization Of Oriented Group Language Of Earth.
- ✓ **YAHOO**--------Yet Another Hierarchical Officious Oracle.
- ✓ **WINDOW**------Wide Interactive Network Development for Office work Solution.
- ✓ **COMPUTER**--------Common Oriented Machine Particularly United and used under Technical and Educational Research.
- ✓ **VIRUS**----------Vital Information Resources Under Siege.
- ✓ **UMTS**----------Universal Mobile Telecommunicati ons System.
- ✓ **AMOLED**----------Active-matrix organic light-emitting diode.
- ✓ **OLED**----------Organic light-emitting diode.
- ✓ **IMEI**----------International Mobile Equipment Identity.
- ✓ **ESN**----------Electronic Serial Number.
- ✓ **UPS**----------Uninterruptible power supply.
- ✓ **HDMI**----------High-Definition Multimedia Interface.
- ✓ **VPN**----------Virtual private network.
- ✓ **APN**----------Access Point Name.
- ✓ **SIM**----------Subscriber Identity Module.
- ✓ **LED**----------Light emitting diode.
- ✓ **DLNA**---------Digital Living Network Alliance.
- ✓ **RAM**----------Random access memory.
- ✓ **ROM**----------Read only memory.
- ✓ **VGA**---------Video Graphics Array.
- ✓ **QVGA**----------Quarter Video Graphics Array.
- ✓ **WVGA**----------Wide video graphics array.
- ✓ **WXGA**--------Widescreen Extended Graphics Array.
- ✓ **USB**----------Universal serial Bus.
- ✓ **WLAN**----------Wireless Local Area Network.
- ✓ **PPI**---------Pixels Per Inch.
- ✓ **LCD**-------Liquid Crystal Display.

- ✓ **HSDPA**----------High speed down-link packet access.
- ✓ **HSUPA**--------High-Speed Uplink Packet Access.
- ✓ **HSPA**----------High Speed

4. "የኮምፒውተር ክፍሎች"

1) Motherboard:

- ❖ **Motherboard** የኮምፒውተር ክፍል ዋናው የኤሌክትሪክ ሰርኪዩት ሰሉዳ ሲሆን ተለቅ ያለ እና ዋና የኮምፒውተር ክፍል ነው።
- ❖ ሁሉም የኮምፒውተር ክፍሎች ከ**Motherboard** ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተገናኙ ሲሆን ይህም በመሰረታዊነት የኮምፒውተሩ ክፍሎች እርስ በርስ መረጃ እና ትዕዛዞችን እንዲለዋወጡ ያስችላል።
- ❖ ካለ **Motherboard** ኮምፒውተር የማይታሰብ ነው። ለምሳሌ፡- የኮምፒውተሩ ኤሌክትሪክ አቅራቢ(Power Supply) ለሲዲ ማንበቢያው (CD drive) የኤሌክትሪክ ሃይል መስጠት ካልቻለ ሲዲ ማንበቢያው መስራት አይችልም።

2) Central Processing Unit (CPU):

- ❖ **CPU** የኮምፒውተሩ ማዕከላዊ ማቀነባበሪያ ክፍል ሲሆን ማቀናበሪያ(processor) አልያም የኮምፒውተር አዕምሮ ሌላኛው መታወቂያ ስሞቹ ናቸው።
- ❖ **CPU** ከተጠቃሚ ወደ ኮምፒውተሩ የሚገቡትን ትዕዛዞች በሙሉ በመቀበል ኮምፒውተሩ በአግባቡ ትዕዛዙን እንዲከውን የሚያደርገው በ motherboard ላይ የሚገኝ ትንሽ የኤሌክትሮኒክ ቺፕ ነው።
- ❖ የማቀናበር ሃይል(processing power) የኮምፒውተርን ፍጥነት ግልፅ በሆነ መልኩ ይጨምራል። ስለሆነም ፈጣን ማቀነባበሪያ ኮምፒውተሮችን ፈጣን ያደርጋቸዋል።

3) Random Access Memory (RAM):

- ❖ **RAM** ማሕደረ-ትውስታ የኮምፒውተሩ ጊዜያዊ መረጃዎችን አልያም ስሌቶችን የሚያኖርበት እና በሚያስፈልግ ጊዜ(ኮምፒውተሩን ከማጥፋታችን አልያም ዳግም ከማስነሳታችን በፊት) መረጃዎችን ወይንም ስሌቶችን የሚሰጠን ነው።
- ❖ **RAM** ከ CPU ጋር በመተባበር ዳታዎች በተሰካ ሁኔታ የሚያቀነባብር ወሳኝ የኮምፒውተር ክፍል ነው።
- ❖ የ**RAM** መጠን በመጨመር የኮምፒውተሮችን የማህደረ-ትውስታ በማስፋት የማቀነባበር አቅሙን ማሻሻል ይችላል

4) Hard Drive:

- ❖ **Hard drive** ለኮምፒውተሮች እንደ ትልቅ ቤተ-መፀሃፍት ነው። ምክኒያቱም ፋይሎችን፤ሙዚቃዎችን፤ምስሎችን፤ ሰነዶችን፤ ወዘተ ለዘለቄታው የምናኖርበት ሁነኛ ክፍል ነው።
- ❖ **Hard drive** በግል ከምናኖራቸው መረጃዎች ባለፈ የኮምፒውተሩ አሰራር ሂደት(operating system) የሚጫንበት እና በአግባቡ ኮምፒውተሩ ለተጠቃሚዎች አገልግሎት ምቹ የሚያደርጉትን የአሰራር ሂደት ፋይሎች(operating system files) የሚቀመጡበት የኮምፒውተር ክፍል ነው።

5. “5G ቴክኖሎጂ እንዴት ይሰራል?”

የ **5G** ቴክኖሎጂ የ አምስተኛው ትውልድ የሞባይል ቴክኖሎጂ ሲሆን የዲጂታል ዓለሙ የሚፈልገውን ፈጣን ግንኙነት ለመፍጠር ትልቅ እርምጃ ያራመደ ቴክኖሎጂ ተደርጎም ይወሰዳል። የ 5G ቴክኖሎጂ የመረጃ መለዋወጫ ፍጥነትን አሁን ካለው የ **4G** ቴክኖሎጂ ከ10 እስከ 100 የተሻለ እጥፍ እንደሚልቅ ይገምታል። ይህም ማለት የሞባይል ኢንተርኔት ተጠቃሚዎችን እስከዛሬ ከነበረው የ**m/s** ፍጥነት ወደ **g/s** ያሳድገዋል ማለት ነው።

ኒዮርክ በሚገኘው የኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲ የኤሌክትሪካል ኢንጂነሪንግ ተባባሪ ፕሮፌሰር የሆኑት **ሃሪሽ ክሪሺናስዋሚ** እንዳሉት "የ 5G ቴክኖሎጂ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው ምክንያቱም አሁን ባለው የኔትዎርክ ፍጥነት መተግበር ያልቻልናቸውን ከፊተኛ የሆነ የኔትዎርክ አቅምን የሚጠይቁ መተግበሪያዎችን እንድንጠቀም ያስችለናል ለምሳሌ በ ጊጋ ባይት ደረጃ ያሉ ተንቀሳቃሽ መስሎችን በሰከንድ ከኢንተርኔት ማውረድ ያስችለናል እንድሁም እንደ ቨርችዋል ሪያሊቲ መተግበሪያና ሰው አልባ መኪኖችን ላይ ለፈጣን የመረጃ ዝውውር መጠቀም ያስችለናል።" በተጨማሪም ዘመኑ እየፈጠራቸው ያሉ ቴክኖሎጂዎች ማለትም እንደ አጉመንትድ ሪያሊቲ እና ሰው አልባ መኪኖች ከፍተኛ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ፍጥነትን ይሻሉ ስለሆነም የ5G ቴክኖሎጂ የመረጃ የመዘግየት ሂደንት ወደ 1 ሚሊ ሴኮንድ ዝቅ ማድረን አላማ አድርጎ ተነስቷል ይህ ማለት ተንቀሳቃች መሳሪያዎች መረጃን የ1 ሴኮንድ 1/1000 ባነሰ መለዋወጥ ያስችላቸዋል።

ባለፉት ትውልዶች ቴክኖሎጂዎች የሚጠቀሙት የኤሌክትሮማግኔቲክ ጨረርን እንደ ሬድዮ ሞገድ ባሉ ቴክኖሎጂዎች በመሆኑ የእነዚህ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ በከፍተኛ ሁኔታ የኔትዎርክ መጨናነቅን ይፈጠርበታል። ስለሆነም ይህንን ችግር ለመቅረፍ ከፍተኛ የሆነ የራድዮ ሞገድ ከመጠየቁም በላይ በ ሴንቲሜትር የሚለካውን ወደ ሚሊሜትር ሞገድ ዝቅ ማድረግ አስፈልጓል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ቀድመን ከምናውቀው ትልልቅ የሆኑ የኔትዎርክ ምሰሶዎች በላይ በማይፈልጉ የህንጻዎች አናት እና በመብራት አስተላላፊ ምሰሶዎች ላይ ሊገጠሙ የሚችሉ በመሆኑ ቴክኖሎጂዎቹ አዲስ የግንኙነት መንገድ የክፈቱ አስብሏቸዋል። ነገር ግን እነዚህ የሞገድ አይነቶች ሌሎች ተግዳሮቶች አጋጥሟቸዋል ከነዚህም መካከል ሞገዶቹ በዛፎችና በህንጻዎች ከመዋጥ አልዳኑም። ነገር ግን እነዚህ በመጠናቸው አንስተኛ የሆኑ የኔትዎክ አስተላላፊዎች ለአዳዲስ የምርምር ስራዎች መፈጠር ጉልህ አስተዋጾ ነበራቸው።

የአምስተኛው ትውልድ ኔትዎርክ የመፈጠር ምክንያትም ናቸው። የአምስተኛው ትውልድ ኔትዎርክ (5G) ቀድሞ በነበሩት የኔትዎርክ አስተላላፊዎች ላይ ቁጥራቸው በርከት ያሉ በመጠን አነስተኛ የሆኑ አንቴናዎችን በመጨመር እንዲሁም የማስተላለፍ አቅማቸውን በማሳደግ ከፍተኛ የሆነ የመረጃ መላላኪያ ፍጥነትን በመጨመር የተፈጠረ ሲሆን የመረጃ መዘግየትን በእጅጉ ቀንሷል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ከዚህ በተጨማሪም በፊት ከነበሩት የኔትዎርክ አስተላላፊዎች ያነሰ የኤሌክትሪክ ሃይል መጠቀማቸውም ልዩ ያደርጋቸዋል።

6. “Basic Computer Questions and Answers”

I. The length of IP address is? **32 bits**
II. Facebook was launched in? **2004**
III. The docx file contains? **MS Office Word**
IV. The file extension DLL stands for? **Dynamic Link Library**
V. The extension of a MS Access Database is? **Mdb**

VI. The key combination used to permanently delete a file from Windows computer? **Shift + delete**
VII. Shortcut Key to open a new document is? **Ctrl + N**
VIII. Data is permanently stored in? **Hard Disk**
IX. What are the steps to upgrade a 32-bit version to a 64-bit version of Windows? **It cannot be upgraded**
X. To change a lowercase letter to uppercase and uppercase letter to lowercase select? **Sentence Case**
XI. CSS stands for: **Cascading Style Sheets**
XII. The general format of the URL is as follows: **type: // Address /path /**
XIII. The computer abbreviation "OS" stands for: **Operating System**
XIV. The shortcut key to delete a file without sending to recycle Bin is: **Shift + Del**
XV. How many versions of Windows 8 for PC have been released? **3 versions**
XVI. A group of 8 bits is called: **Byte**
XVII. To subscript a text, shortcut key is: **Ctrl + <**
XVIII. The file extension .jsp stands for: **Java Server Page**
XIX. What is the full form of WWW? **World Wide Web**
XX. The microphone converts the sound into: **Electrical Signals**
XXI. A device which connects multiple nodes to the network is: **A hub**
XXII. Windows 7 was released in which year?
XXIII. What is Windows XP? **An operating system**
XXIV. ATM stands for: **Automated Teller Machine**
XXV. Which one of these is used to find information on World Wide Web? **Search Engine**
XXVI. ".gif" is an extension of which type of file? **Image**
XXVII. Who is the founder of IBM Company? **Thomas J. Watson**
XXVIII. Volatile Memory is: **Ram**
XXIX. When you delete an object, Windows XP sends it to: **Recycle Bin**
XXX. A folder in windows c can't be made with the name: **Con/Com1**

7. "SD፣ HD፣ 4K እና 8K ምንድን ናቸው?"

የቴክኖሎጅ ርቀት እና ምጥቀት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣ ሲሆን በተለይ ከእይታ (ምስል) ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች ደግሞ ለማመን የሚከብዱ ተአምራት እየሆኑ መጥተዋል። የምስል ጥራት በፒክስል የሚለካ ሲሆን በ3 ዋና ዋና ደረጃዎች ይከፈላል። እነሱም

1. **SD** [**standard_definition**]--------መደበኛ ጥራት
2. **HD** [**High definition**]----------ከፍተኛ ጥራት
3. **UHD** [**Ultra high definition**]---------ከመጠን ያለፈ ጥራት ናቸው።

ፒክስል [**pixels**] ስንል አንድን ምስል ለመስራት የሚያስችል ትንሿ ነጥብ (ስኩዌር) ማለታችን ነው። **የፒክስሎች** ስብስብ **ሪዞሉሽን** [**Resolution**] ሊሰኝ ይችላል።

ለምሳሌ፦ ከአንድ ምስል ላይ አንድ ስኩየር (ልክ ኬሚስትሪ ላይ atom እንደምንለው) ወስደን ብንመለከት የወርድ ነጥቦች ስብስብ ብዛት × የቁመት ነጥቦች ስብስብ ብዛት ፒክስል ይባላል ማለት

ነው።

- ✓ 720 × 480 pi ሲባል 720 = የወርድ (Word) ነጥቦች ብዛት እና 480 = ቁመት (Height) ነጥቦች ብዛት በአንድ ሊከፈል በማይችል ስኩዌር ውስጥ ማለታችን ነው። ፒክስል በበዛ ቁጥር ጥራት ይጨምራል። በሌላ በኩል የምስሉ MB ም ይጨምራል። በየዘመናቱ የመጡ የምስል ጥራት እድገትን ብንመለከት ከመጀመሪያው እስከ አሁን ድረስ የሚከተሉትን ይመስላል።

1. **SD** = 720 × 480
   PAL = 768 × 576
   NTSC = 720 × 534 (የድሮ ሪሲቨሮች)
2. **HD** = 2K
   HD = 1280 × 720
   Full HD = 1920 x 1080
3. **UHD** = 4K= 3840 × 2160 (16:9 YouTube size)
   5K = 5120 × 2700
   6K = 6144 × 3160
   8K = 7680 × 4320 አሁን የደረስንበት የመጨረሻው ቴክኖሎጅ።

ሀገራችን ላይ በስፋት በአሁኑ ሰዓት በአብዛኛው ሰው ቤት የሚገኘው **Full HD** እና **4K** ሪሲቨር ሲሆን አልፎ አልፎ 8Kም ይኖራል። ነገር ግን እዚ ላይ ልንገነዘበው የሚገባን ነገር ቢኖር ባለ **8K** ቻናልን ለመመልከት ሪሲቨራችን እንዲሁም ቲቪያችን የግዴታ **8K** ሊሆን ይገባል። አለበለዚያ የቻናሉ ጥራት ምን ያህል እንደሆነ ለመለየት እንቸገራለን። ያ ማለት **HD** ቻናሎችን በ**AV** ኬብል እንደመመልከት ይሆናል ማለት ነው።።።።

8. “በይነመረቡ (Internet) ምንድነው?”

በይነመረብ [Internet] በዓለም ዙሪያ በኩባንያዎች፣ በመንግሥታት፣ በዩኒቨርሲቲዎች እና በሌሎች ድርጅቶች የሚተዳደሩ የኮምፒተር ኔትዎርኮች እርስ በእርስ እንዲነጋገሩ የሚያስችል ሰፊ አውታረመረብ ነው። ውጤቱም ብዛት ያላቸው ኬብሎች፣ ኮምፒተሮች፣ የመረጃ ማዕከላት ፣ ራውተሮች፣ አገልጋዮች፣ ተደጋጋሚዎች፣ ሳተላይቶች እና የ”**Wifi**” ማማዎች የዲጂታል መረጃ በዓለም ዙሪያ እንዲጓዝ የሚያስችላቸው ነው።

ሳምንታዊውን ሱቅ ለማዘዝ፣ ሕይወትዎን በፌስቡክ ላይ ለማጋራት፣ በ”Netflix”ላይ”Outcast”ን በሸረት እንዲለቀቁ፣ በወልሎንግንግ ውስጥ ለሚኖሩ እህትዎ በኢሜል እንዲልኩ እና በዓለም ላይ በጣም ትንሽ የሆነውን ድመት ለመፈለግ የሚያስችል መሠረተ ልማት ነው።

9. “በይነመረቡ (Internet) ምን ያህል ትልቅ ነው?”

አንድ ልኬት በውስጡ የሚያጠናው የመረጃ መጠን ነው-በቀን ወደ አምስት ገደማ የሚሆኑ። ያ በሰከንድ 40,000 የሁለት ሰዓት መደበኛ ጥራት ፊልሞች ጋር እኩል ነው። የተወሰነ ሽቦን ይወስዳል። ደብዛዛዎችን እና አህጉሮችን ለማገናኘት በሞቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ማይሎች ኬብሎች በችግር የተሻገሩ አገራት እና ሌሎችም በባህር ወለሎች ይቀመጣሉ። ወደ 300 የሚጠጉ የባህር ሰርጓጅ ኬብሎች፣ ጥልቀት ያለው የባህር ውስጥ ልዩነት እንደ የአትክልት ቧንቧ ብቻ ነው፣ ዘመናዊውን በይነመረብ ያስገኛል። አብዛኛዎቹ በብርሃን ፍጥነት መረጃን የሚያስተላልፉ የፀጉር-ቀጭን ፋይበር ኦፕቲክስ ጥቅሎች ናቸው።

10. “ሰው ሰራሽ ዝናብ (Seeding Technology)”

ደመና ያለበት አካባቢ ላይ በአውሮፕላን የኬሚካል ርጭት ይደረጋል። ንጥረ ነገሩ (ሲልቨር አይወዳይድና ፖታሺየም አይወዳይድ) ተበታትኖ የነበረው ደመና ላይ ሲያርፍ ደመናው እንዲሰበሰብና ወፈር ወዳለ የውሃ እንክብል እንዲቀየር ያደርገዋል። ይህ የውሃ እንክብል በመሬት ስበት አማካኝነት ወደ መሬት እንዲዘነብ ይገደዳል። የንጥረ ነገር ርጭቱ ሀገራት እንዳላቸው አቅም ከመሬት ወደ ደመናው መርጨትም የሚቻልባቸው ሁኔታዎች አሉ። በሮኬት መልክ መተኮስ የሚቻል ሲሆን በሰው አልባ አውሮፕላኖችም ርጭት ማድረግ ይቻላል። የተለመደው ግን በአውሮፕላን ከደመናው በላይ አልያም በታች እየበረሩ መርጨት ነው።

ዝናብ በአርቴፊሻል መንገድ ማዝነብ የተጀመረው ወደ 1950 ዎቹ አካባቢ ወደ ሀገረ ታይላድ ነው። ህዝቤ ሆይ ይሄ ታአምር ሳይሆን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ነው። ዝናብን በ አርቴፊሻል መንገድ ማዝነብ ከተጀመረ ትንሽ ሰንበትበት ብልዋል። ለንደኛ ያሉ ደሃ ሀገራት ግን አዲስ ነገር ነው። በአለም ላይ ካሉ ሀገራት ውስጥ በብዛት አርተፊሻል ዝናብ ምታዘንበው **ቻይና** ናት። ቻይና በአመት እስከ 50 ሚልዮን ሜትር ኪዩብ ታዘንባለች።

- ✓ **<u>ዋና ምታዘንብባቸውም ምክንያቶች</u>**

- የእርሻ መሬትን ድርቅ ለማስወገድ ወይም ለማቃለል፣
- ትላልቅ የመስኖ ውሃ ማጠራቀሚያ ታንኮችን ለመሙላት ወይም የውሃ አቅርቦት አቅም እንዲጨምር፣
- ለኃይል ማመንጫ የውሃ መጠን እንዲጨምር

11. “ኳንተም (Quantum)”

ይህ ቴክኖሎጂ የንዑስ-አቶሚክ ቅንጣቶችን ሚስጥራዊ ዓለም ይጠቀማል። የኳንተም ማስላት የቴክኖሎጂ መሠረታዊ ነገሮች ምናልባት ብዙዎቻችንን ግራ የሚያጋቡ ቢሆኑም በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። እንደ የምስል ማወቂያን፣ ምስጠራ ምስጠራን እና ከፋይናንስ ፖርትፎሊዮ ተመላሽነትን ማመቻቸት ያሉ ተግባራት ከዚህ አዲስ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

12. “1G፣ 2G፣ 3G፣ 4G እና 5G የተንቀሳቃሽ ስልክ አውታረመረቦች (cellular networks)”

“G” ምህጻረ ቃል ሲሆን “GENERATION” ማለት ነው። የኢንተርኔት ፍጥነት የሚወሰነው በምንጠቀመው ወይም በተዘረጋው የኔትወርክ ቴክኖሎጂ ነው። ማለትም 1G, 2G, 3G, 4G, 5G እንዚህም እያንዳንዳቸው ጀነሬሽን እንደ ስታንዳርድ ጠቀምጠዋል እንደ ሞባይል ስልክ ስርዓት ያገለግላሉ።

- **1G (1ጂ)** ----- በ1980ዎቹ ተግባራዊ የተደረገው ሲሆን ይህ ቴክኖሎጂ የመጀመርያ ጀነሪሽን ሲሆን ድምጽ እና አናሎግ አገልግሎት ይስጥ ነበር መረጃዎችን ለመላክ **2.4kbps** ፍጥነት ነበረው።

- **2G (2ጂ)** ----- ኔትወርክ በፊንላንድ በ1991 የተጀመረው ሞባይል ስልኮች ወደ ዲጂታል

ዓለም እንዲዘዋወሩ አስቺሎል። 2G ለመደወል እና ሚስጥራዊ ጽሑፍ(encryption) እንዲሁም ለኤስኤምኤስ(SMS)፣ ለሥዕል መልእክት መላላኪያ እና ለኤምኤምኤስ(MMS) ተፈቅዷል። 2ጂ ከፍተኛው ፍጥነት **50kbps** ያህል ነበር።

- **3G (3ጂ)** ---- ኔትወርክ የበለጠ መረጃን፣ ቪዲዮ ኮል እና ሞባይል ኢንተርኔት የተጀመረበት ሲሆን ግዜው እ.ኤ.አ በ1998 ነበር። የ3ጂ ኔትወርክ ፍጥነት በእንቅስቃሴ ውስጥ እና ከእንቅስቃሴ ውጭ ስንሆን ይለያያል። በእንቅስቃሴ ውስጥ ከሆን **384kbps** የኢንተርኔት ፍጥነት ይኖረዋል እንዲሁም ከእንቅስቃሴ ውጭ ስንሆን 2mbps የኢንተርኔት ፍጥነት ይኖረዋል።

- **4G (4ጂ)** ---- ወይም የወቅቱ የተንቀሳቃሽ ስልክ ኔትወርክ ሲሆን በ2000 እ.ኤ.አ የተለቀቀ እንዲሁም ከ 3G ከ 500 እጥፍ ይበልጣል። ባለከፍተኛ ጥራት የሞባይል ቴሌቪዥን ፣ የቪዲዮ ኮንፈረንስ እና ሌሎችንም መደገፍ ችሏል። ፍጥነት በእንቅስቃሴ ውስጥ እና ከእንቅስቃሴ ውጭ ስንሆን ይለያያል። በእንቅስቃሴ ውስጥ ከሆን **10 mbps** ሊሆን ይችላል፣ እና እንቅስቃሴ ውስጥ ካልሆን **100 mbps** ሊሆን ይችላል። እንደ አለንበት ቦታ እና እንደ እንቀስቃሴቺን የኢንተርኔት ፍጥነታችን 10s -100s of mbps መካከል ይቀያየራል። እንቅስቃሴ ሲባልም እየተራመድን ወይም ተሽከርካ ውስጥ ልንሆን እንቺላለን።

- **5G (5ጂ)** ---- በአሁኑ ጊዜ በልማት ላይ ያለ ሲሆን 4Gን ለማሻሻል ታሰቦ ነው ይህም 5G ከፍተኛው ፍጥነት ሲኖረው **35.46 Gbps** በፍጥነት ለመድረስ ያለመ ሲሆን ይህም ከ 4 ጂ በ 35 እጥፍ ይበልጣል።

13. “Google Founders”

“Larry Pag and Sergay Brin” እ.ኤ.አ በ 1998 ፈረንሳይ አለም ዋንጫን ደቡብ አፍሪካ ደግሞ አፍሪካ ዋንጫን ለማዘጋጀት የበቁበት ጊዜ ሲሆን እነዚህ ሁለት ወጣቶች (ፎቶ) ከምድረ አሜሪካ በወረሀ ሴብቴምበር በካሊፎርኒያ ውስጥ የኢንተርኔት መረጃ መፈለጊያ ገፅ የሆነውን ጎግል (google) ለዓለም ያበረከቱበት ወቅት ነበር። ታዲያ ይህ ግኝት ዛሬ ላይ በመላው ዓለም ለሚገኙ የኢንተርኔት ተጠቃሚዎች መረጃን በቀላሉ እንዲያገኙ ሲያስችል ለግኝቱ ባለቤቶች ላሪ ፔጅ እና ሰርጄይ ብሪን ደግሞ እያንዳንዳቸውን የ15 ቢልየን ዶላር ባለቤት ለማድረግ አስችሎዋቸዋል።

14. “የተለያዩ የቴክኖሎጂ ካምፓኒዎች ሎጎዎች ትርጉም”

- ✓ **Apple** የ"Computer science" አባት ተብሎ የሚጠራው **Alen Turing** በ ሁለተኛው የ አለም ጦርነት ወቅት **enigma code** በመባል የሚታወቀውን የ"German military command" የሚስጥር ኮድ በመስበር ሚሊየኖችን ከሞት ለመታደግ ችሏል ነገር ግን ለደህንነት ስጋት ነው ተብሎ ስለታሰበ በ **"cyanide"** የተለወሰ **"apple"** በመስጠት አንዴ ከመጉመጡ ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል። በዚህም ምክንያት "Apple" ካምፓኒ እሱን ለመዘከር ሎጎው አድርጎታል።

- ✓ **Amazon** የ"online" መገበያያ የሆነው አማዞን ሎጎ አይታቹት ከሆነ ከ **A** ተነስቶ እስከ **Z** ድረስ የሚሄድ ቀስት አለው። ይሄም የሚያሳየው ምንም ነገር አማዞን ላይ ተፈልጎ እንደማይታጣ ሲሆን፤ **Amazon** የሚለው ስም ደሞ ከ አለማችን ትልቁ ደን እና ወንዝ ከሆነው ከብራዚሉ **"Amazon"** የተወሰደ ሲሆን የድርጅቱን ግዝፈት ለመግለጽ

የተጠቀሙበት ነው።

- ✓ **Nike** known as" SWOOSH" የራይት ምልክት በ ግሪክ አፈታሪክ ውስጥ የ እንቅስቃሴ ፣ የመብረር ፣ የ ድል እና የፍጥነት ምልክትን ነው። የተወሰኑት እንደሚያስቡት የ"check mark" ምልክት አይደለም። ናይክም ይሄን ለመግለጽ ነው ምልክቱ ያደረገው።

- ✓ **Facebook** የፌስቡክ ምልክት small capital **"f"** ነው። ይሄም ፌስቡክ የሚለውን የሚገልጽ መሆኑን ብዙዎቹ ያምናሉ ነገር ግን ከዚህ በተጨማሪም ሰው አጎንብሶ ሲጠቀም ያሳያል የሚል መላምንትም አለ። ሰማያዊ የሆነው ደሞ የfb ፈጣሪ የሆነው **zuckerberg color blindness** ስለሆነ ነው።

- ✓ **IBM** የተለያዩ የ electronics ምርቶችን የሚያመርተው **International Business Machine**, IBM ሎጎው ላይ ያለው ነጫጭ ወደ ጎን የተሰመሩ መስመሮች የሚያመለክተው ከምንም በፊት እኩልነት ይቅደም የሚለውን ነው።

15. "ዓለምን የለወጡ ሴት ሳይንቲስቶች"

ዓለማችንን በመለወጥ በኩል እና ሴትነት በራሱ ይዞት የሚመጣውን ጫና ተቋቁመው ልይነት መፍጠር የቻሉ ብዙ ሴቶች ያሉ ሲሆን ከዚህ በታች የምትመለከቷቸውም ይህን ጀበድ የፈፀሙና ለመጪዎቹም መንገድ የጠረጉ ናቸው።

1. ቫለንታይን ት ረሽኮቫ

በህዋ ጥናት እና ምርምር እ.አ.አ በ1963 የሩሲያ "ቮስቶክ" የተባለች መንኮራኩርን ይዛ ወደ ህዋ በመብረር ያረፈች የመጀመሪያዋ ሴት ስነህዋ ተመራማሪ ለመሆን የበቃች ሲሆን ለዚህም ተግባር የወሰደባት ጊዜ ሶስት ቀናቶች ብቻ ነበሩ። የሷን ፈለግ በመከተል ከ20 አመት በሆላ ሴሊ ራይድ ወደ ህዋ በመጎዝ በአለም ሁለተኛዋ እና በአሜሪካ የመጀመሪያዎ ሴት የስነ-ህዋ ሳይንስ ተመራማሪ ለመሆን ችላለች።

2. ሜሪ ኩሪ

እ.አ.አ በ1903 "በራዴሽን" ዙሪያ ባደረገችው ጥናት እና ምርምር የመጀመሪያዋ ሴት የኖቭል ፕራይዝ ተሸላሚ ለመሆን ስትበቃ ፤ እ.አ.አ በ1911 በኬሚስትሪ ዘርፍ ባደረገችው ጥናት እና ምርምር "ራዲየም" እና "ፖሎኒየም" የተባሉ ሁለት ንጥረ-ነገሮችን በማግኘት የመጀመሪያዋ ሴት ባለሁለት ኖቭል ፕራይዝ ተሸላሚ ለመሆን በቅታለች። በሁለት የተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ሁለት የኖቭል ሽልማቶችን በማሸነፍ በአለማችን የመጀመሪያዋ ለመሆን ችላለች።

3. ኢኒጂነር ዳና አሊሪያ

እ.አ.አ 1961 የመጀመሪያዋ ሴት የናሳ ኢኒጂነር ዳና አሊሪያ ትምህርቷን የተከታተለችው በኮምፒውተር ሳይንስ ኢኒጂነሪንግ ነው። ስራዋን የጀመረችው በካርኒፎርኒያ "ጄት ፕሮፑሊሽን ላብራቶሪ" ቢሆንም በሆላላይ ግን የመጀመሪያዋ ሴት የናሳ ኢኒጂነር ለመሆን በቅታለች። ዳና አሊሪያ በናሳ ቆይታዋ የጠፈር ተመራማሪዎች ከጠፈር ወደ ምድር መረጃዎችን እና መልእክቶችን የሚያስተላልፉበት በየነ-መረብ ለመዘርጋት በቅታለች። በዚህም ስራዋ በአሜሪካን የወታደሮች ጥናት እና ምርምር ላብራቶሪ ውስጥ

የመጀመሪያዋ ሴት ስራ አስኪያጅ ሆናለች።

4. **አሚሊያ ኢርሀርት**

እንደ እ.አ.አ ከ1930 በፊት አንድ ሰው ለብቻው የአትላንቲክ ውቅያኖስን በኢሊኮፍተር ለማቋረጥ ብዙ ሙከራዎች ተደርገው ነበር። ነገር ግን ይህን ማሳካት የቻለው አንድ ሰው ብቻ ነው ። እንደ እ.አ.አ በ1932 አሚሊያ ኢርሀርት የአትላንቲክ ውቅያኖስን በማቋረጥ በአለማችን ሁለተኛዋ እና የመጀመሪያዋ ሴት ለመሆን በቅታለች። ይሄንን ጉዞ ለማጠናቀቅ የፈጀባት 15 ሰዓት ብቻ ሲሆን ሰአቱም በወቅቱ ሪከርድ ሆኖ ተይዟል። እ.አ.አ በ1937 አለምን ለመዞር ባደረገችው በረራ ሙከራ እስካሁንም የደረሰችበት ሳይታወቅ ልትጠፋ ችላለች። እንደ እ.አ.አ በ1953 ጃኬሊን ኮችራን የሷን ፈለግ በመከተል የንፋስ እንቅፋችነትን በመቀነስ የጄት ፍጥነትን ከአስራአንድ አመት በታላ በእጥፍ መጨመር ችላለች።

16. “የሰዉ-ሰራሽ ክህሎት አይነቶች ስንት ናቸዉ?”

1. **Artificial Narrow Intelligence (ANI)** ------ ይህ አይነቱ ሰዉ-ሰራሽ ክህሎት "Weak AI" በመባልም የሚታወቅ ሲሆን፣ አንድን ጉዳይ ብቻ በትክክልና በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዲያከናዉን ተደርጎ የሚሠራ ነዉ። ቼዝን በመጫወት ላይ ብቻ የላቀ ብቃት እንዲኖረዉ ተደርጎ የተሠራ ኮምፒዉተር ለዚህ እንደምሳሌ የሚጠቀስ ነዉ። ፕሮግራም ከተደረገበት ተግባር ዉጪ ሌላ ነገርን ማከናወን አይችሉም። በአሁኑ ሰዓት ያሉ የሰዉ-ሰራሽ ክህሎት ብቃት ያላቸዉን ኮምፒዉተሮችና ማሽኖች አብዛኞቹ የዚህ አይነቶቹ ናቸዉ።

2. **Artificial General Intelligence (AGI) ----** ይህ አይነቱ ሰዉ-ሠራሽ ክህሎት "Strong AI" ወይንም "Human-Level AI" በመባልም የሚታወቅ ሲሆን፣ በአንድ ነገር ላይ በተቀላጠፈ ሰዉ-ሠራሽ ክህሎት አማካኝነት ማከናወን እንዲችል ተደርጎ የተሠራ ነዉ። አሁን ባለዉ አሠራር እንዲህ አይነቱን ሰዉ ሰራሽ ክህሎት መፍጠር በጣም ከባድ ነዉ። በሞያ ዘርፉ የተሰማሩ ባለሞያዎች ይህን ዓይነት ማሽን ለመፍጠር በሰዉ አዕምሮ ዉስጥ የሚከናወንን አመንክዮ፣ እቅድ፣ የተወሳሰበ ሃሳብን መረዳት፣ አንድን ነገር ፈጥኖ ለይቶ ማወቅ፣ መፍትሄን መፈለግ፣ ዉሳኔን በፍጥነት መስጠት፣ በተፈጥሮ የሰዉ ቋንቋ መግባባት፣ ካለፈ ልምድ መማርና ሌሎችን ብቃቶችን ለማሽኑ በሰዉ ሰራሽ ፕሮግራም ማድረግ ያስፈልጋል ይላሉ። ይህ አይነቱ የማሽን ብቃት ገና በምርምርና በጥናት ደረጃ ያለ ሲሆን፣ ተግባራዊ ለማድረግ ምናልባትም ረጅም ዓመታት ሊወስድ እንደሚችል ይነገራል።

3. **Artificial Super Intelligence (ASI)** ---- እንግሊዛዊዉ ፈላስፋና በሰዉ ሠራሽ ክህሎት ዘርፍ በርካታ ጥናታዊ ጽሑፍ በማቅረብ የሚታወቀዉ ኒክ ቦስትሮም "በማንኛዉም ዘርፍ አለ የሚባል ጠቢብ ሰዉን በእጅጉ የሚበልጥ የሳይንስና የስነ-ጥበብ ፈጠራ ችሎታ ያለዉ፣ እንዲሁም ጠቅላላ እዉቀትንና ማህበራዊ ክህሎትን ጨምሮ በሁሉም ዘርፍ የጠለቀ ዕዉቀት ያለዉ" ሲል Artificial Super Intelligence (ASI) ቴክኖሎጂ ሊኖረዉ የሚችለዉን ጽንሰ-ሃሳባዊ ብቃት ይገልጸዋል። የሳይንስ ልብ-ወለድ ፊልም ላይ ከሚታይ ምናባዊ የፈጠራ ስራ ባልዘለለ መልኩ ዕዉን ለመሆን ገና እጅጉን ሩቅ የሆነዉን ይህ አይነቱን ሰዉ-ሠራሽ ክህሎት የሰዉ ልጅ ተሳክቶለት ተግባራዊ ማድረግ ቢችል፣ መልሶ ማስቆም እንደማይቻልና ከሰዉ ቁጥጥር ዉጭ እንደሚሆን ይነገራል። አንዳንዶች ምናልባትም ሰዉን ሙሉ በሙሉ የሚገዛበትም ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል ይላሉ። በራሳችን እጅ ሰርተን ሊገዙን?

17. “የዘመናዊ ኮምፒዉተር አፈጣጠርና እድገት አጭር ታሪክ”

- **1950ዎቹ** ---- በ "ቫኪዩም ቲዩብ" ብቻ ይሰሩ የነበሩት ኮምፒዉተሮች መጠናቸዉ የአንድ ቤት መጠን እስኪያክል ድረስ እጅግ ግዙፍ የነበሩ ሲሆን በአንጻሩ ደግሞ እጅግ ቀርፋፍ ነበሩ። በወቅቱ እነዚህን ኮምፒዉተሮች በብቸኝነት ይጠቀምባቸዉ የነበረዉ የአሜሪካ ሚሊቴሪ ተቋም ሲሆን ዋጋቸዉም የትም የሌለ ነበር።

- **1960ዎቹ** ---- በትራንዚስተሮች መፈጠር የተነሳ ቀርፍፍዉን የ"ቫኪዩም ቲዩብን" አሰራርን በመቀየር የኮምፒዉተሮች የአካል መጠን መቀነስ ሲቻል ብቃታቸዉንም ማሻሻል ተቻለ። በዚህ ወቅት ነበር ሜይንፍሬም (mainframe) የተባሉ ፈጣንና ወድ ኮምፒዉተሮች ተፈጥረዉ ከማሊቴሪና የመንግስት ተቋም አልፎ ለግል ድርጅቶች ጥቅም መዋል የጀመሩት።

- **1970ዎቹ** --- በመቶዎች የሚቆጠሩ ትራንዚስተሮችን ያካተተ ኢንቴግሬትድ ሰርኪዩት "Intergrated Circute Board" አንድ ክፍልን ሊሞላ የሚችል መጠን ያለዉን የሜይንፍሬም ኮምፒዉተር አሳንሶ በጠረጴዛ ላይ የሚቀመጥ ኮምፒዉተር "Desktop" እንዲፈጠር አስቻለ።

- **1980ዎቹ** ---- በሚሊዮን የሚቆጠሩ ትራንዚስተሮች እጅግ በጣም ትኝሽ መጠን ባለዉ የኮምፒዉተር ቺፕ ዉስጥ ሀያዉ መሆን የኮምፒዉተር በጣም አንሶ በአንዲት ቦርሳ ዉስጥ የሚገባና ከድርጅት አልፎ ለግል ጥቅም መዋል የሚችልበት "Personal Computer (PC)" ዘመን ተወለደ። ኮምፒዉተሮች ጠረጴዛ ላይ ከመቀመጥ አልፈዉ ጭን ላይ የሚቀመጡበትን መጠን ይዘዉ "laptop" በሚል ስያሜ ብቅ አለ።

- **1990ዎቹ** --- የኢንተርንት መወለድ ኮምፒዉተሮች እርስ በእርሳቸዉ እና በሌላ ቦታ ከሚገኝ ከፍተኛ አቅምና የመረጃ ብዛት ያለዉ የኮምፒዉተር ስብስብ "datacenter" ጋር ተገናኝተዉ ከዚህ ቀደም በራሳቸዉ አቅም ብቻ ከሚሰጡት አገልግሎት እጅግ የላቀ ጥቅምን በፍጥነት መስጠት እንዲችሉ አደረገ።

- **2000ዎቹ** ---- ለእጃችን መዳፍ እንኳን የማይሞሉ፣ ነገር ግን ብቃታቸዉ ከአንድ መጠኑ ከፍ ካለና ምርጥ ከሚባል ኮምፒዉተር ያልተናነሰ ተግባር ማከናወን የሚችሉ እንደ ረቀቀ ስልክ (Smartphone) ያሉ ተንቀሳቃሽ ቁሶች (mobile devices) በስራ ላይ ዋሉ። ከስልኮችም አልፈዉ ታብሌቶቻችን፣ ሰዓቶቻችን፣ የቤት ቁሶቻችን፣ መኪናዎቻችን እና ልብሶቻችን ሳይቀሩ የኮምፒዉቲንግ ብቃት እየተካተተላቸዉ ይገኛል። ከዚህም በተጨማሪ ይህ ዘመን አብሮን ባለ ኮምፒዉተር ላይ ብቻ ከመደገፍ ይልቅ እንደ ክላዉድ ኮምፒዉቲንግ (Cloud computing) እና የመሴሰሉት የተራቀቁ በኢንተርኔት ተገናኝተዉ መሰራት የሚችሉ እና ከእኛ ርቀዉ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች ተበታትነዉ በሚገኙ እጅግ ፈጣን ኮምፒዉተሮች አማካኝነት በርካታ ተግባር ማከናወን ተቻለ። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰዉ ክላዉድ ኮምፒዉቲንግ ማለት የኮምፒዉተር ተጠቃሚዎች ሶፍትዌርን፣ ሃርድዌርን፣ መረጃን እና የተለያዩ ዲጂታል አሠራሮችን በራሳቸዉ ኮምፒዉተር ላይ ከመጫን ይልቅ ካሉበት ሰርቨሮች በኢንተርኔት አማካኝነት በየትኛዉም ጊዜና ቦታ ልክ መቦራትና ዉሃ ቤታችን ድረስ እንደሚመጣዉ ከአገለግሎት ሰጪዎች ላይ በሚፈልጉት መጠን መጠቀም የሚያስችል አሠራር ነዉ።

- ይህ ሁሉ ፈጽሞ የበቃ በማይመስልበት ሁኔታ የኮምፒዉተር እድገትና ፍጥነት ሩጫዉን ቀጥሏል። ከላይ የተጠቀሰዉን አስደናቂ የኮምፒዉተር የለዉጥ እድገት ሀያዉ ያደረገልን የMoore's Law ወደ ፍጻሜ እየመጣ ያለ ይመስላል። ምክንያቱም የትራንዚስተሮች እጅግ አናሳ በሆነ መጠንና በጣም በተጠቀጠቀ ሁኔታ በአነስተኛ ቦታ ላይ እንዲያርፉ የሚደረግበት

የቺፕ አሠራር የመጨረሻ ገደቡና ጥጉ ላይ እየደረሰ ስለመጣ ነዉ። አንድን ትራንዚስተር ምንም ያህል እናሳንሰዉ ብንል ከአቶሚክ መጠን በታች ልናደርገዉ አንችልም። ይህ ሂደት ወደ ፍጻሜዉ እየተቃረበ የመምጫቱን ጉዴይ ባለሞያዎች፣ ምሁራን፣ ተመራማሪዎች እና አምራቾችም ይስማሙበታል። የትንቢቱ ባለቤት ጎርደን ሙር እራሱ በ2015 ዓ.ም በሰጠዉ ቃለ ምልልስ ከ50 ዓመታት በፊት የተነበየዉ Moore's Law ማክተማያዉ እየተቃረበ እንደመጣ ጠቁሟል። ኮምፒዉተር እስከዛሬ በዚህ አይነት የረቀቀ የእድገት ሂደት ዉስጥ ካለፈ፣ "ታድያ ከዚህ በላይ ምን ይመጣል?" የሚል ጥያቄ ወደ አእምሮ ይመጣል።

18. "ታድያ ከዚህ በላይ ምን ይመጣል?"

- በእርግጥ ቀጣዩቹ ኮምፒዉተሮች ምን አይነት ይሆኑ ይሆን? የወደፊቶቹ ኮምፒዉተሮች በጨረር፣ በኳንተም የፊዚክስ ህግ እና በሰዉነታችን ዉስጥ በሚገኙ በዲኤንኤ አማካኝነት የሚሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ። እንዲሁም በማንኛዉም ቁስ ላይ ተለጥፈዉ የሚገኙ፣ ወይም ደግሞ የራሳችን ኮምፒዉተር ሳያስፈልገን በሌላ ቦታ ተቀምጠዉ በኢንተርኔት አማካኝነት ያላቸዉን አቅም ሙሉ በሙሉ ከፈለግነዉ ቦታ ሆነን መጠቀም የምንችልባቸዉ አይነቶችም ሊሆኑ ይችላሉ።

- የፋይበር ኦፕቲክስ "Finer-optic" ወይንም በጨረር አማካኝነት መረጃን ከአንድ ኮምፒዉተር ወደ ሌላዉ በፈጣን ሁኔታ በማስተላለፉ አሰራር ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እያበረከቱ ይገኛሉ። በፋይበር ኦፕታክስ የሚተላለፉ መረጃዎች በኤሌትሪክ ሽቦ ዉስጥ ከሚተላለፉት ፍጥነታቸዉ በእጅጉ የተሻለ ሲሆን፣ በተጨማሪም እንደ ኤሌክትሮማግኔቲክ ያሉ የተለያዩ ጣልቃ ገብ ግብዓቶች አሠራሩን አያደናቅፉትም ። ታድያ ለምን ከኤሌትሪክ ትራንዚስተር ይልቅ በጨረር የሚሰራ ኮምፒዉተር መስራት አይቻልም? ይህን ማድረግ ከተቻለ የኮምፒዉተሮችን የዉስጥ የመረጃ አቀማመር አቅም እጅጉን እንዲጨምር ማድረግ ይቻላል። ምንም እንኳን ተመራማሪዎች በዚህ ዙርያ ተስፋ ሰጪ የሙከራ ስራዎች ቢያከናዉኑም መጠኑ ያነሰና በብዛት ተመርቶ በኮምፒዉተሮች ዉስጥ ሊገጠም የሚችልን በጨረር የሚሠሩ ቺፕ ህያዉ ለማድረግ ሙሉ ስኬትን እስከአሁን አላገኙም።

- በጨረር አማካኝነት የሚሰሩ ኮምፒዉተሮችን ለመፍጠር በሚደረገዉ ምርምር የኢትዮጵያዉ ዶክተር ሰለሞን አስፍ እጅ አለበት። ዶክተር ሰለሞን የበርካታ ፈጠራ ስራዎች ባለቤት ሲሆን በዋናነት የሚታወቅበት የፈጠራ ስራዉ በተለመደዉ አሠራር በኤሌትሪክ ከሚሰሩ ትራንዚስተሮች ይልቅ ኮምፒዉተሮች በብርሃን ጨረር (optical pulse) አማካኝነት መረጃን ለማስላት የሚችሉበትን ሙከራ ያደረገበት የምርምር ስራዉ ነዉ። ይህ ግኝት ለወደፊቶቹ ኮምፒዉተሮች አሁን ካሉት ማሽኖች እስከ አንድ ሺህ እጥፍ ፍጥነት እንደሚሰጣቸዉ ሲጠበቅ፣ የኤሌክትሪክ ፍጆታንም በእጅጉ ይቆጥባል ተብሏል። የዶክተር ሰለሞን ዋና ግኝት ፎቶዲቴክተር (photodetector) የሚባሉትና የብርሃን ጨረር መልዕክትን (optical signals) አጉልተዉ የሚያስተላልፉ ቁሶች (በሞያዊ አጠራራቸዉ "amplifiers") እንዴት አድርገዉ መልዕክትን ለማይክሮፕሮሰሰሮች በሚገባ መንገድ በማስተላለፍ ጨረር መልዕክቶችን ወደ ኤሌክትሪክ መልዕክት (electrical signals) በመቀየር ለኮምፒዉተር አሰራር ጥቅም እንዲዉሉ ማድረግ ነዉ።

ምዕራፍ ስድስት
ስለ ሀገሮች አጫጭር ታሪክ

1. ግብፅ (Egypt):

- በጋዛሰርድ፣ በእስራኤል፣ በሊቢያ፣ በሱዳን፣ በሜዲትራንያን እና በቀይ ባህር የተከበበች አፍሪካዊ ሀገር ነች።
- ከክርስቶስ ልደት በፊት በ3100ዓ.ዓ እንደተመሰረተች ታሪክ ይነግረናል። ይህም በዓለማችን ቀዳሚ ህዝቦች ያደርጋቸዋል።
- የግብፅ ስልጣኔ የጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 1350 ዓ.ዓ ላይ ነው።
- ግብፅ ፓፒረስ የሚባል ለመፃፋ የሚጠቀሙበት ቅጠል ሲሆን ውሑፉ ደግሞ ሄሮግሎፊክስ ይባላል።
- ጥንታዊ ግብፆች በ ሒሳብ እና በ ሳይንስ ይታወቁ ነበር። እንዲሁም በህንፃ ግንባታ፣ በመድሀኒት፣ በቀን አቆጣጠር እና በሌሎች ልዮልዮ ፈጠራዎች ቀዳሚዎቹ ናቸው።
- ለአሁኑ ስልጣኔያችን ጥንታዊ ግብፆች የፈጠሩልን ብዙብዙ ነገሮች አሉ።
  ለምሳሌ፡- መስኖ፣ ወረቀት፣ ብዕር፣ ቁልፍ፣ ቅባቶች እና የጥርስ ሳሙና የሚጠቀሱ ናቸው።
- ንጉስ ፈርኦን ቤተ መቅደስ፣ ፒራሚዶች እና የተለያዮ በወቅቱ አስደናቂ የሆኑ ሀውልቶች ማሰራት ችሏል። በአሁኑ ጊዜ 130 የሚሆኑ ፒራሚዶች በግብፅ ይገኛሉ።
- ዘመናዊ ግብፆች ብቅ ማለት የጀመሩት በ1944 ዓ.ም ላይ ነው።

2. ቻይና (China):

- ከክርስቶስ ልደት በፊት 2070 ቻይና ተመሰረተች።
- ጥንታዊ እና ረዥም የዘመናዊነት ታሪክ ያላት የእስያ አህጉር ቀዳሚ ሀገር ናት።
- በጥንቷ ቻይና ግብር ይከፈል ነበር የህግ የበላይነትም ነበር።
- ለመጀመሪያ ጊዜ ሻይን የጠጡ ሰዎች ቻይናውያን ናቸው። የሻይ ቅጠልን በመጀመሪያ ለመድሀኒትነት ይጠቀሙት ነበር ከጊዜ በኋላ ግን የእለተእለት መጠጥ ተደርጓል።
- በ2002 ዓም 2400 ዓመት እድሜ ያለው የሾርባ ሳህን በቁፋሮ ተገኝቷል።
- በአለማችን ብዙ ህዝብ ያላት ቀዳሚ ሀገር ናት።
- በዓለም በትልቅነቷ 4 ተኛ ደረጃ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት።
- ቻይና 14 ሀገራት ጎረቤቶቿ ናቸው።
- የቻይና ፊደል ከ 8000 በላይ ሲሆኑ እስከ 13 አመት ያሉ ልጆች 3000 የሚሆኑትን ማንበብ እና መፃፍ ይችላሉ።
- የቻይናውያን አዲስ አመት ለ 15 ቀናት በደማቅ ሁኔታ ሲከበር ይታያል።

3. ህንድ (India):

- ህንድ በእስያ የምትገኝ በባህል እና በታሪክ የበለፀገች ሀገር ናት።
- በፓኪስታን በቻይና በኔፓል እና በባንግላዲሽ የተከበበች ስትሆን ዋና ከተማዋ ኒውዴልሂ ትባላለች ።
- ህንድ ውስጥ ሰዎች መኖር ጀምረዋል ተብሎ የሚታሰበው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ 1500

ላይ ነው።

- በህዝብ ብዛቷ ደግሞ 2 ተኛ ደረጃ ላይ ናት።
- ህንድ ለዓለም በሒሳብ በርካታ ነገሮች አበርክታለች እነዚህም:- አልጀብራ (Algebra)፣ ካልኩለስ (Calculus)፣ ትሪጎኖሜትሪ (Trignometry) እና ዜሮ ቁጥር (Zero number) የተፈለሰፈው በህንድ ነው።
- በህንድ ከክርስቶስ ልደት በፊት 700 ላይ የተሰራ ታክሻሺላ ዩኒቨርሲቲይ በአለማችን ጥንታዊ ዩኒቨርሲቲይ ነው።

4. ኢትዮጲያ (Ethiopia):

- ኢትዮጲያ ቀደምት ከሆኑት ሀገራት ውስጥ በቀዳሚነት የተቀመጠች ሀገር ናት።
- ኢትዮጲያ ውስጥ ስልጣኔ የጀመረው ከክ/ልደት በፊት 980 አካባቢ ነው።
- ቀደምት የሰው ቅሪተ አካል የተገኘው በኢትዮጲያ ሲሆን ከብዙ ሚልዮን አመታት በፊት ነው።
- ኢትዮጲያ በእደ-ጥበብ፣ በግብርና፣ በፍልስፍና፣ በክዋክብት እና በህክምና እውቀቶችን ለዓለም ያበረከተች ሀገር ናት።
- የራሷ የሆነ ቋንቋ፣ ፊደል እንዲሁም የቀን አቆጣጠር ያላት ባህሏን እና እምነቷን እስከዛሬ ጠብቃ ያቆየች ጥንታዊ ሀገር ናት።

5. ግሪክ (Greek):

- የግሪክ ታሪክ የሚጀምረው ከክልደት በፊት 800 ላይ ነው።
- ግሪክ ለዓለማችን መለወጥ ከፍተኛ አስተዋፅኦ አበርክታለች።
- ዘመናዊነት እንዲስፋፋ እና አዳዲስ ሀሳቦች እንዲፈጠሩ እንዲሁም የህንፃ አሰራሮች ማስተዋወቅ የቻለች ሀገር ናት።
- የሳይንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የስነ-ውሑፍ፣ የህግ እና የፖለቲካ እድገትም ባለቤት ናት።
- የመጀመሪያ የኦሎምፒክ ጨዋታ የተደረገው ከክ/ልደት በፊት 776 ላይ ግሪክ ውስጥ ነው።
- ከአልባኒያ፣ ከሰሜን መቆዲንያ፣ ከ ቡልጋሪያ፣ ከቱርክ ጋር ትዋሰናች።
- የግሪክ 18 ቅርሶቿን በዩኔስኮ አስመዝግባለች።
- ሀገሪቷ 85/100 የሚሆነው ቦታዎቿ በተራራማ የተሸፈነ ነው።

6. ጃፓን (Japan):

- ጃፓን ከክ/ልደት በፊት 600 ላይ እንደተመሰረተች ይገመታል።
- በእስያ የምትገኝ ሀገር ስትሆን 4 ትላልቅ ደሴቶች እና ከ 6800 በላይ ትናንሽ ደሴቶች ተሰብስበው ጃፓንን ፈጥረዋታል።
- አርኪዮሎጂስቶች በዚያን ጊዜ ሰዎች የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች አግኝተዋል።
- ጃፓን እየዘመነች የመጣችው በ 900 አመታት ውስጥ ነው።
- በአሁኑ ጊዜ ባህሏን ጠብቃ እየኖረች ያለች ዘመናዊ ሀገር ነች።

7. ኢራን (Iran):

- ኢራን ከ/ክልደት በፊት 550 ላይ ተመሰረተች።
- በደቡብ ምዕራብ እስያ ላይ የምትገኝ ሀገር ናት።

- የኢራን ቋንቋ ፐርሺያን ይባላል።
- የኢራን ሌላኛው ስሟ ፐርሺያ ነው ዋና ከተማዋ ደግሞ ትሒራን ትባላለች።
- በጥንት ጊዜ ስልጣኔ የነበራት ሀገር ስትሆን ከክ/ልደት በፊት 4000 ላይ ነው ስልጣኔን የጀመረችው።
- በነዳጅ እና በምንጣፍ ታዋቂ ሀገር ናት።
- በሚያማምሩ የምንጣፍ ስራዎቿ አለምን ለ 2000 አመታት ስታስደምም ኖራለች።
- 1 ጊዜ የእግር ኳስ ሜዳ የሚያክል ምንጣፍ ሰርታ ነበር።
- አንዳንድ ጊዜ ኢራናውያን በሚያስደንቅ ምንጣፋቸው ላይ አውቀው ስህተት ይሰራሉ። ይህም በአለም ከፈጣሪ በቀር ፍፁም ሰው የለም የሚለውን ለማሳየት ነው።

8. <u>ፖርቹጋል (Porchugal):</u>

- የብዙ ሺህ አመታት ባለታሪክ ስትሆን ስልጣኔ ተጀመረ የሚባለው 711 ዓ.ም ላይ ነው።
- ከአውሮፓ ሀገራት ረዥም ታሪክ ያላት ሀገር ስትሆን ዋና ከተማዋ ደግሞ ሊዝበን ትባላለች።
- ምዕራብ አውሮፓ የምትገኝ ሀገር ስትሆን በአትላንቲክ እና በሜዲትራንያን ባህር የተከበበች ናት።
- በአሳ ማስገር፣ በነዳጅ፣ በሲሚንቶ ምርት፣ በፕላስቲክ ምርት፣ በአልባሳት እንዲሁም በኢኮኖሚ ምርት ኢኮኖሚዋን የያዙልት ናቸው።

9. <u>ፈረንሳይ (France)</u>:

- 476 ዓ.ም ላይ ተመሰረተች።
- በምዕራብ አውሮፓ ትልቋ ሀገር ናት።
- ዋና ከተማዋ ፓሪስ ስትሆን በ8 ሀገራት ትዋሰናለች።
- በ4ተኛው ክ/ዘመን ብቅ ማለት እንደጀመሩ ይነገራል። በ17ተኛው ክ/ዘመን ፈረንሳይ ታላቅ ሀገር ነበረች። በእስያ እና በአፍሪካ በርካታ ቀኝ የገዛቻቸው ሀገራት ነበሯት።

ምዕራፍ ሰባት

ኢንተርፕርነር (Entrepreneur) and ቢዝነስ (Business)

1. ኢንተርፕርነር (Entrepreneur)

"የምፈልገውን ነገር መሥራት፤ የምሻውን ነገር ማግኘት እፈልግ ነበር። አሁን ሁሉም ዕውን እየሆኑልኝ ስለሆነ ማድረግ የምፈልገውን እና እንዲኖረኝ የምፈልጋቸውን ነገሮች የእኔ የማድረግ አቅም አለኝ።" የሚለው ጃክ ካንፊልድ የሕይዎት ፍልስፍናው "ራዕይና ህልም ይኑርህ፤ ከዚያም እውን እንዲሆን ጥረት አድርግ" የሚል ነው።
በጃክ አመለካከት ማንኛውም ራዕይ ያለውና ለዚያ ራዕዩ እውን መሆን የሚታትር ሰው ኢንተርፕርነር ነው። ጃክ እንዲህ ይላል "ብዙ ሰዎችን እያቸው።የሆነ አንድ ሰው ጨዋታ እስኪፈጠር ይጠብቃሉ።እነዚህ ሰዎች ያን ጨዋታ ለመጫወት ፍላጎታቸው ይህ ነው አይባልም።

ለምሳሌ ጨዋታው እግር ኳስ ቢሆን እግር ኳስ ለመጫወት እንጅ እግር ኳስ ስለሚጠይቀው የቡድን ስራ ምንም አይጠይቁም። ያለ ቡድኑ አባላት ቅንጅት ደግሞ ውጤታማ ቡድን መገንባት አይቻልም። ጃክ ቀጠል አድርጎም ራዕይና ህልምህ ዕውን የሚሆኑት ግን የራስህ የሆነ አንድ ቢዝነስ በመጀመር ወይም ስለምትሰራው/ስለምታደርገው/ስለምትጫወተው ነገር የጨዋታውን ሕግ ስታውቅ ነው።"

ጃክ ስለ ለውጥና ስኬት ሥራዬ ብሎ ማውጠንጠን የጀመረው በ 1966 ከሃርቫርድ ዩኒቨርስቲ ተመርቆ ኢነር ሲቲ/Inner-City ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚያስተምርበት ጊዜ W.Clement ተቋም በዚያ በሚያዘጋጀው ጤናማና ትክክለኛ የአይምሮ እድገትን በሚመለከት ወርክሾፕ ላይ በሚካፈልበት ወቅት ነበር። ከዚህ በኋላ ጃክ ከራሱ ልምድና እውቀት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን በሥነ ልቡና በራስ መተማመን እና በራስ ተነሳሽነት ላይ የሚያጠነጥን ፕሮግራም **"Seminars"** በመቅረጽ ለተግባራዊነቱ ደፋ ቀና ማለት ጀመረ።

"Insight Training" የተባለው ለትርፍ ያልተቋቋመ ድርጅት በሚያዘጋጀው የግለሰብን እና የባለሙያዎችን ብቃት የሚያዳብር ዝግጅቶች ላይ በማስተማር የቀረጸውን ፕሮጀክት/ፕሮግራም ትክክለኛነት ያረጋገጠው ጃክ፤ በ 1983 የራሱን ድርጅት አቋቋመ።
"ሁሌ ያለፍኩባቸውን የስራ ጊዜያት ዞሬ ስመለከታቸው የሚታየኝ ዋና ነገር ቢኖር የሆነ ነገር በምፈልግበት ወቅት ወደምፈልገው ነገር መሄዴ ነው።" በማለት በከፍተኛ የራስ መተማመን መንፈስ የሚናገረውሁለት ጃክ አርአዬ የሚላቸው ሰዎች ወላጅ አባቱንና የእንጀራ አባቱን ሲሆን "እነዚህ ሰዎች ሁሌ የሚፈልጉትን ለማግኘት ይታትሩ ነበር። ግን ብዙ ጊዜ አይሳካላቸውም ነበር። እንዲያውም አልፎ አልፎ ይወድቁ ነበር። ነገር ግን ሁሌም ይጥራሉ።በእውነት ይሄ ለኔ በውስጤ ትልቅ መነቃቃትን ብርታትን እና መነሳሳትን ነው የፈጠረብኝ።" ይላል። የ **"The Canfield Training Group"** ሊቀመንበር እና ደራሲ **ጃክ ካንፊልድ**

2. “ቢዝነስ የሚመራበት ዋነኛ ነጥቦች”

እስካሁን የነበረው የቢዝነስ አሰራር ባህላዊ በልምድና በግምት የሚመራ ነበር ቢባል ማጋነን አይሆንም። ምክንያቱም ከእጅ ወደ አፍ እንጂ ለእድገት እንዳላበቃን የሚታወቅ ነው። ከአሁን በኋላ ግን በቀድሞው መንገድ መቀጠል አይቻልም። ምክንያቱ ደግሞ ለውጥና እድገት ስለሚያስፈልገን ነው። አሁን ለውጥ (ፓራዳይምሺፍት) ያስፈልገናል። ከቀድሞው ባህላዊና ልማዳዊ የቢዝነስ አሰራር ወጥተን፣ በእቅድና በዘመናዊ የቢዝነስ አሰራር መመራት ያስፈልጋል። ያኔ ነው በአጭር ጊዜ ሀብት ማፍራት፣ መክበርና አገር ማሳደግ የምንችለው።

አንዳንድ የቢዝነስ ሰዎችና ወጣቱ ኃይል፣ ለአገሪቷ አዲስ የሆነው የቢዝነስ አሰራር የገባቸው ይመስላል። ምክንቱም የቢዝነስ ዕቅድ፣ የቢዝነስ ግብ፣ ማለት ጀምረዋላ! የእኔም አነሳስ ይህንኑ ዘመናዊ የቢዝነስ አሰራር ማጠናከር ነው። ምክንያቱም 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ሆነን ቢዝነስም ሆነ ሕይወት ያለ ዕቅድና ግብ መምራት ኋላ ቀርነት ነው የሚል እምነት አለኝ። ወጣቶች፣ በግልም ሆነ ተደራጅተው በዝንባሌና በችሎታቸው የራሳቸውን ቢዝነስ እየጀመሩ ነው። ይኼ ጥሩ የዕድገት መሰረት ነው። ታዲያ ድካማቸው ፍሬ እንዲያፈራ ግልጽና የጠራ ዓላማና ግብ ሊኖራቸው ይገባል። ማንኛውም ዕቅድና ግብ ደግሞ በሳይንስ በተረጋገጠ “ስማርት” በተባለ ዘዴ መፈተን አለበት። በእነዚህ መመዘኛዎች የተቃኘ ቢዝነስ ስኬታማ እንደሚሆን እሙን ነው።

ቢዝነስ የጀመራችሁ፣ ዕቅድና ግባችሁን በ”ስማርት” እንድትፈትሹና እንድታቃኑ፣ ዝግጅት ላይ የሆናችሁ ደግሞ እቅድና ግባችሁን በ”ስማርት” እንድትቀርፁ አራቱን ዘዴዎች አቅርበናል። “ስማርት” የሚለው ቃል ሰፊ ትርጉም ቢኖረውም “SMART” ስፔሲፊክ፣ ሜዠረብል፣ አቴንኤብል፣ ሪያሊስቲክ ታይምቴብል ከሚሉት ቃላት የመጀመሪያ ፊደላት የተወሰደ ምህፃረ ቃል ነው።
ስፔስፊክ (Specific):- የሚለው የቢዝነስ ግባችሁ፣ ከሌላው የቢዝነስ ፕላንና ግብ ጋር የማይመሳሰል፣ በራሱ የጥራት ደረጃና ነባራዊ ሁኔታ የሚተገበር፣ ግልፅና ጥርት ያለ፣ በወረቀት ላይ የሰፈረ መሆነ አለበት።

በደፈናው ግባችን ሀብት ማፍራት፣ ዕድገት ማስመዝገብ፣ ኤክስፖርት ማድረግ፣ የሚል ከሆነ ልክ አይደለም። ነገር ግን በዚህ ጊዜ ውስጥ ዘመናዊ ማምረቻ መሳሪያዎች በመትከል፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል (ባለሙያ) በመጠቀም በአንድ፣ ሁለት፣ አምስት፣ አስር፣ ዓመት እዚህ ደረጃ ላይ (አንድ፣ ሁለት፣ አምስት፣ ሀምሳ፣ ሚሊዮን ብር ገቢ ላይ እንደርሳለን በማለት አሰራሩንና የሚደረስበትን ደረጃ ጥርት ባለ መንገድ በግልጽ ማስቀመጥ አለበት።

ግቡ የሚለካ (Measurable) መሆን አለበት። አንድ ድርጅት በየጊዜው የደረሰበትን ውጤት (ደረጃ) መመዝገብ አለበት። ውጤት ማወቅ እደርስበታለሁ ለተባለ ግብ፣ ትክክለኛ መስመር ላይ መሆን ወይም ወደኋላ መቅረትን ያመለክታል። በዓመቱ መጨረሻ አንድ ሚሊዮን ብር ገቢ ይኖረናል ካላችሁ፣ በዓመቱ አጋማሽ ግማሽ ሚሊዮን ብር ሊኖራችሁ ይገባል። ካልሆነ አተገባበራችሁ ወይም ሌላ ስህተት ተፈጥሯል ማለት ነው። ስለዚህ ግባችሁን ለማሟላት ቆም ብላችሁ ራሳችሁን መፈተሽና ስህተትን አርሞ፣ ግብን ለማሳካት መወሰድ ያለባቸውን እርምጃዎች መቀየስ ያስፈልጋል።

የበጀት መዝጊያው የሚያሳየው ግባችሁ መሳካቱን ወይም ችግር እንደገጠመው ነው። ግባችን ያልተሳካው በጥሬ ዕቃ አቅርቦት ማነስ፣ በገበያ መጥፋት፣ በመብራት መቆራረጥ፣ ምክንያት መደርደር አይገባም። ለምን መሰላችሁ? መጀመሪያውኑ ዕቅዱ ሲወጣ፣ ችግሮች ሊያጋጥሙ እንደሚችሉ ገምቶ ጥሬ ዕቃ ቢያጥረን፣ ገበያ ቢጠፋ መብራት ቢቆራረጥ ብሎ መፍትሔ ማበጀት ያስፈልጋል። ግቡ የሚሳካ (Attainable) መሆን አለበት። ግብ ለይስሙላ ሳይሆን፣ በእርግጠኝነት ማሳካት የሚቻል፣ ወይም

አስቸጋሪ ሁኔታ እንኳ ቢያጋጥም መስዋዕት በመክፈል የሚሰካ እንጂ በተጨባጭ ሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ፣ ሁኔታዎችን ያላገናዘበ ከመጠን በላይ
የተለጠጠና (Ambitious) ስሜታዊ መሆን የለበትም።

ዓመታዊ ግባችሁ አንድ ሚሊዮን ብር ገቢ ማግኘት ነው እንበል። ነገር ግን በዓመቱ መጨረሻ የደረሳችሁበት ገቢ 100ሺ ብር ቢሆን መጀመሪያውኑ ስታቅዱ ምናልባት ገቢያችን በፍፁም ያልጠበቅነው ቢሆን በምን ዓይነት መስዋዕትነት እናሳካዋለን? በማለት ካላሰባችሁ በጣም ከባድ ችግር ነው። ቀደም ሲል የነበረው ዓመታዊ ገቢ የሸያጫችሁን 20 በመቶ ቢሆን ያልተጠበቁ ድንገተኛ ሁኔታዎች ተከስተው ችግር ቢፈጠር፣ ግባችሁን ለማሳካት በሳምንት ከ90 እስከ 100 ሰዓት መስራት እንዳለባችሁ ካልወሰናችሁ፣
ከፍተኛ ውድቀት ያጋጥማችኋል።

ተጨባጭና ትክክለኛ የጊዜ ገደብ (Realistic Timetable) አንድ ፕሮጀክት ወይም ግብ የጊዜ ገደብ ከሌለው፣ የውሸት ይሆናል። ምን ማለት ነው? በዓመቱ መጨረሻ 5 ሚሊዮን ብር ገቢ እናገኛለን፣ ፕሮጀክቱን በ18 ወር ጨርሰን እናስረክባለን፣ ተብሎ መታቀድና ግብ መቆረጥ አለበት። ያለበለዚያ ዋጋ የለውም። ብዙ ጊዜ የጊዜ ገደብ ሲቃረብ መጣደፍ የሰው ልጅ ባህርይ ነው። የጊዜ ገደብ ሳይቃረብ የሚሰሩት ቅድሚያ የሚሰጣቸው አጣዳፊ ነገሮች ናቸው። ይህ ሁኔታ ሕልምና ግብዎን ወደ ኋላ ይገፋል፤ ዕቅድ ያሰናክላል። አንድ ፕሮጀክት ጊዜ በወሰደ ቁጥር የብዙ ነገር ወጪ ይጨምራል፤ ትርፍ ይቀንሳል። ስለዚህ ነው ብዙ የውጭ ተቋራጮች በተዋዋሉበት ወይም ከዚያ በታች በሆነ ጊዜ ጨርሰው ለማስረከብ የሚጣደፉት።

3. "<u>አዲስ ቢዝነስ ከመጀመራችን በፊት ልናጤናቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች</u>"

በርካቶቻችን በግላችን ስራ ፈጥረን ለመንቀሳቀስ ስናስብ ቀድሞ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ስኬት ሳይሆን ኪሳራ ነው። አንዳንድ ሰዎችም ስኬታማ እንሆንበታለን የሚሉትን ቢዝነስ ሳያስቡበት በፍጥነት ይገቡና ማጣፊያው ሲያጥራቸው ይስተዋላል። ለማንኛውም የትኛውም ንግድ ትርፍ እንደሚያስገኘው ሁሉ ኪሳራም አለውና ልናጤናቸው የሚገቡ ነጥቦች አሉ። አዲስ የንግድ ሀሳብ ይዘን ገበያውን ለመቀላቀል ስናስብ ቀለል አርገን አይተነው ልንገባበት አልያም ብዙ ነገሮች ተምታተውብን ጊዜ ልናጠፋ እንችላለን። ታዲያ እኛም ቸኩሎ ወደ ቢዝነስ ውስጥ ከመግባት ወይም ስራ ለመጀመር ከመፍራት የሚታደጉ ናቸው ያልናቸውን **አራት** ነጥቦች ልንነግራችሁ ወደናል።

1. <u>የቢዝነስ ሃሳብዎ በገበያው አዋጭ መሆኑን እርግጠኛ መሆን:</u>

በአዕምሮዎ የሚመላለስ የንግድ ሃሳብ አለ? በሌሊት ከእንቅልፍዎ የሚቀሰቅስዎትስ? አዎ ከሆነ መልስዎ በእነዚህ ሃሳቦች ላይ ማተኮር እና በገበያው አዋጭ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባዎታል።

2. <u>ጠንካራ የቢዝነስ እቅድ ማውጣት:</u>

በአዕምሯችን ላይ የሚመላለሰው የንግድ ሃሳብ በገበያው ትርፋማ መሆኑን ካረጋገጥን በኋላ እንዴት ወደ ስራ ልንገባ እንደምንችል የሚያሳይ ዝርዝር እቅድ ማውጣት ያስፈልጋል። የቢዝነስ እቅዳችን እነዚህን ሊያካትት ይችላል።

- ✓ የቢዝነሳችን ራዕይ - ከምን ተነስቶ የት ይደርሳል?
- ✓ የገበያ ትኩረታችን ማን ነው?
- ✓ ከሌሎች ተመሳሳይ አገልግሎት ሰጪዎች ልዩ የሚያደርገን ነገር ምንድን ነው?

✓ ለቢዝነሱ የሚያስፈልገን አጠቃላይ ወጪ እና የሚሸፈንበት መንገድ (የፋይናንስ ምንጭ) በየቀኑ የምንመለከታቸውን አዳዲስ ነገሮች በወረቀት ላይ ማስፈር እና በተደጋጋሚ መከለስ ጥሩ የቢዝነስ እቅድ ለማውጣት ይረዳል። በፋይናንሱ ረገድ በአቅማችን የምንከውናቸውን ስራዎች አስቀድመን በመለየት በተረጋጋ አኳኋን ወደ ስራ መግባትም ያስፈልጋል።

3. ሰዎችን ማነጋገር:

ልንጀምረው ካሰብነው ቢዝነስ ጋር ግንኙነት ካላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች ጋር ግንኙነት መፍጠርም ያሰብነው ስራ ወደ ተግባር ተቀይሮ ውጤት እንዲያመጣ ከፍተኛ ሚና አለው። በተለይም እንደ ትዊተር ባሉ ማህበራዊ ድረገጾች ሃሳብን እና ምኞትን ማጋራት የተሻለ የቢዝነስ ሃሳብ ለማግኘት ይረዳል።

4. የስራ ፈጠራ ክህሎትን ማሳደግ:

የስራ ፈጠራ ዝንባሌያችንን ለማሳደግ በመደበኛ ትምህርት የምናገኘው እውቀት ብቻውን በቂ አይደለም። ስለሆነም የተለያዩ መፅሃፍትን ማንበብ፣ ጦማሮችንና ድረ ገፆችን መመልከት ልንጀምረው ላሰብነው ቢዝነስ በቂ መረጃ ከማቅረብ ባለፈ ሌሎች የቢዝነስ አማራጮችን ለማስፋት ያግዛል።
በአጠቃላይ ብንጀምረው ስኬታማ እንደምንሆን በምናስበው ስራ በሙሉ ፍላጎት ከተንቀሳቀስን ውጤታማ መሆናችን አይቀሬ ነው። ከላይ የተጠቀስናቸውን የቅድመ ዝግጅት ምዕራፎች በስኬት ከተወጣናቸው የምናልመውን ቢዝነስ እውን ለማድረግ እንደማይከብደን እናምናለን።

ምዕራፍ ስምንት
የታዋቂ ሰዎች የህይወት ታሪክ

1. “ሊዮናርዶ ዳቪን”

ሊዮናርዶ ዳቪን 1452-1519 ዓ.ታላቅ ባለራዕይ ሰዓሊ፣ የፈጠራ ባለምያ፣ መሃንዲስ፣ ፈላስፋ፣ የሂሳቢ ሊቅ፣ ፀሐፊ እና ታዋቂው ሁለገብ ጣልያናው ባለራዕይ ምሁር ልዮናርዶ ዳቪንች ነው ብንል ማጋነን አይሆንም። ከሰራቸው አስደናቂ ስራዎች አንዳንዱን እንሆ። በብዛት ዳቪንች የሚታወቀው የጌታ እራት **“THE LAST SUPPER”** እና ምናሊዛ በተሰኙት አስደናቂ ስዕሎቹ ነው። የሚገርመው የምናልዛን ከንፈር ብቻ ለመሳል 11 ዓመት ከ 11 ወራት ፈጅቶበታል። ይኔ ጥበበኛ ሰው በአንድ ጊዜ ብቻ በአንድ እጁ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን እየፃፈ በሌላው እጁ ደግሞ ድንቅ ስዕል መሳል ይችል ነበር።

ይህ ድንቅ ምሁር በርካታ ዘመን ተሻጋሪ የሆኑ ድንቅ የፈጠራ ዲዛይኖች ለአለም አበርክቷል። ከ1452-1519 ዓ.ም ይኖር የነበረው ይህ ታላቅ ባለራዕይ በጨለማ እየኖረ ብርሃን ያይ ነበር። ገና ሳይንስና ቴክኖሎጂ በቅጡ እንኳን ትርጉም ሳይሰጠው የሰው ልጅ ወደፈት ከብዙ መቶ ዓመታት በኃላ ይፈጥረዋል ብሎ ያሰባቸውን ነገሮች በአስደናቂ በሆነ ምናባዊ የፈጠራ ክህሎቱ በወረቀት ላይ እስፍሮ ነበር።

ከእነዝ መላል አንዳንዱን የበረራ ማሽን ዲዛይን **“FLYING MACHINE” /Ornithopter** ምንም እንኳን የመጀመሪያው የተሳካ የአውሮፕላን ፈጠራ እና በረራ የተከናወነው በአሜሪካውያኑ ወንድማማቾች በኦልቨር እና አልበርት ራይት በ1903 ዓ.ም ቢሆኑም፣ ዳ ቪንች ከእነርሱ 400 ዓመታት በፈት ቀድሞ የባለራዕይ አዕምሮውን በመጠቀምና የተፈጥሮ የበረራ ክህሎት ካላቸው አዕዋፍት ሃሳቡን በመውሰድ 33 ጫማ የክንፍ ስፋት ያለውን የበራሪ ማሽን ዲዛይን አድርጎ ነበር። ከዝያር ብዙ የምባሉ ፈጠራዎችን ድዛይን አድርጎል ለምሳሌ ለመጀመር ጊዜ የፖራሹት ዲዛይን የእልኮፕተር ዲዛይን የታንክ ዲዛይን።

2. “ለመሆኑ የአማዞን መስራች ማን ነዉ። እንዴትስ ተመሰረተ?”

በጃኑዋሪ 12 1964 ዓ.ም ነዉ ሜክሲኮ በተባለች የአሜሪካ ክፍለ ግዛት ዉስጥ የተወለደዉ ጄፍ ቤዞስ ገና በወጣትነቱ ነበር ለኮምፒዉተር ፍቅር ያደረበት። ከዚህም የተነሳ የወላጆቹን የመኪና ማቆሚያ ጋራዥ በመዉሰድ የራሱ የኮምፒዉተር ቤተ-ሙከራ አደረገዉ። የ2ተኛ ደረጃ ትምህርቱን በከፍተኛ ዉጤት ከተመረቀ በኃላ በታዋቂዉ የፕሪንስተን ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ ድግሪዉን በኮምፒዉተር ሳይንስና ኤሬክትሪካል ኢንጅነሪንግ በ1986 ዓ.ም. በከፍተኛ ማዕረግ ተመርቋል። በርካታ የሥራ መቀጠር እድሎችን ያገኘዉ ጄፍ በዞስ በኒዉዮርክ ከተማ በከፍተኛ ደሞዝና ታላፊነት ተቀጥሮ መሥራት ጀመረ።

ምንም እንኳን ተቀጥሮ የሚሰራበት ስራ ከፍተኛ ደመወዝ የሚያስገኝለትና ስልጣንንም ያቀናጀዉ ቢሆንም፣ ሥራዉን ከአራት አመት በኃላ ለቆ በመዉጣት ዛሬ በኢንተርኔት ዘርፍ ታላቅ ስኬት የተቀናጀዉን አማዞንን ለማቋቋም ተነሳ። በወቅቱ ገና አዲስ የነበረዉን ኢ-ኮሜርስን ለማካሄድ ምርጥ ስራዉን የመልቀቅ እርምጃዉ እብድ ቢመስልም የፈጠራ ባለሙያዎች ባህርይ አንድን ነገር ለመሞከር መድፈርና ዉድቀትን አለመፍራት በጄፍ ቤዞስ ዉስጥም ጎልቶ ታይቷል። በ1994 ዓ.ም ኒዉዮርክን ለቆ ኑሮዉን በሲያትል ከተማ በማድረግ የመጀመሪያዉን የመፅሀፍ መገበያያ ድረ-ገፅ ይፍ አደረገ።

የመኖርያ ቤቱን የመኪና ጋራዥ የኮምፒዉተር ተቋሙ፣ መኝታ ቤቶቹንም ቢሮ በማድረግ ከጥቂት ሠራተኞች ጋር ስራዉን ጀመረ። 300 ያክል ዘመድ ወዳጆቹን ለሙከራ ወደ ስራዉ የመገበያያ ድረ-ገፅ በመጋበዝ አነስተኛ ክፍያን እየተቀበለ መፅሃፍትን በኢንተርኔት ላይ መሸጥ የተጀመረዉ ስራ በጁላይ 1995 ዓ.ም **"amazon.com"** በሚል ስም ለተጠቃሚ ክፍት አደረገ። ቤዞስ አማዞን የሚለዉን ስም ያወጣዉ በሁለት ምክንያቶች ነበር። የመጀመሪያዉ የአማዞንን ጫካ በመወከል በርካታ መፅሃፍት የሚገኙበት ግዙፍ የኢንተርኔት መደብር መሆኑን ለማሳየት ሲሆን፣ ሁለተኛዉ ደግሞ በወቅቱ ድረ-ገጾች በፊደል ቅደም ተከተል ይደረደሩ ስለነበር በቀላሉ ለሰዎችበድረ-ገጾች ማሰሻ ላይ እንዲታይ ታስቦ ነበር።

የአማዞን መለያ አርማ በሶስት የመሻሻል ሂደት ዉስጥ ያለፈ ሲሆን፣ በ2000 ዓ.ም የተደረገዉ መሻሻል ዛሬ ድረስ የምናቀዉን መልክ ሰጥቶታል። በዚህ የመለያ አርማ ላይ ያለዉ ከፍ **"A"** ተነስቶ **"Z"** ጋር የሚደርስ ቀስት ሁሉንም ነገር በአማዞን ላይ ማግኘት እንደሚቻል ለማሳየት ነዉ። ድረ-ገጹ ተወዳጅነትን ያተረፈዉ ወድያዉኑ ነበር። በ60 ቀናት ዉስጥ ያለምንም ማስታወቂያ በበርካታ የአሜሪካ ግዛቶች እና ከ45 በላይ አገራት ዉስጥ የሚነኙ ደንበኞች ዋጋዉ ከ$20 ሺህ በላይ የሚያወጣ የመፅሃፍ ግዢን ፈጸሙ። በ1997 ዓ.ም አማዞን አክስዮኑን ለህዝብ መሸጥ ጀመረ። ጄፍ ቤዞስ በድረ-ገጹ ላይ የሚሸጠዉን እቃ ከመፅሃፍት ባለፈ መልኩ በማሳደግ ሲዲዎቹንና ፊልሞችን አካቶ መሸጥ ጀመረ።

ቀጥሎም የህጻናት አሻንጉሊቶችን፣ ልብሶችንና የኤሌክትሮኒክ እቃዎችንና በርካታ ምርቶችን መሸጡን ቀጠለ። በወቅቱ ተከስቶ በነበረዉ የኢንተርኔት ኢኮኖሚ ቀዉስ "dot com crisis" ብዙ ኩባንያዎችን ከገበያ ዉጪ ቢያደርጋቸዉም አማዞን ግን ትርፍማነቱን ቀጥሎ በ1995 ዓ.ም ከአካሄደዉ የ500 ሺህ ዶላር ሽያጭ በጥቂት ዓመት ዉስጥ ቁጥሩ እጅግ ጨምሮ ወደ ሚሊየኖች ገባ። አማዞን በ2007 ዓ.ም የመፅሃፍት ነባራዊ እዉነታ የሚቀይር ፈጠራ አስተዋወቀ። ኪንድል የዲጂታል መፅሃፍ ማንበቢያ "e-reader" በመፍጠር የታተሙ መፅሃፍትን ከመግዛት በተጨማሪ አንባቢዎች ዲጂታል መፅሃፍትን በኪንድል ገዝቶ በማዉረድ እንዲጠቀሙ አስቻለ።

በ2011 ዓ.ም ኪንድል ፍየር የተባለዉን ታብሌትም ይፍ አድርጎ የገበያ ፉክክርን ተቀላቀለ። ኩባንያዉ በመላዉ ዓለም በርካታ ቢሮዎች፣ የመረጃ ተቋማት (datacenters) እና ከ150 ሺህ በላይ ሰራተኞች አሉት። በሰከንድ እስከ 500 የግዢ ትዕዛዞችን ማስተናገድ የሚችለዉ አማዞን በመላዉ አለም ከ244 ሚሊየን በላይ ቋሚ ደንበኞች እንዳሉት ይነገራል። በአሁኑ ሰዓት በአመት በአማካኝ ወደ $130 ቢሊየን በላይ ሽያጭ ያከናዉናል። ጄፍ ቤዞሰ ከ$110 ቢሊየን በላይ በማካበት በአጠቃላይ የሰዉ ልጅ ታሪክ ዉስጥ ትልቁ ባለጸጋ ሊሆን በቅቷል። ከ1990ዎቹ ጀምሮ በዓለም ላይ አንደኛ ባለጸጋ የሆነዉን ቢል ጌትስ ለመጀመሪያ ጊዜ በሃብት በመብለጥ የዓለማችን 1ኛ ባለጸጋ መሆን የቻለዉም በ2017 አጋማሽ ላይ ነበር። የባለጸግነቱ እርከን በየጊዜው ቢቀያየርም በፎርብስ ዘገባ መሠረት ጄፍ ቤዞስ በሰዉ ልጅ ታሪክ ዉስጥ ቁንጮ የዓለማችን ባለጸጋ ሊሆን በቅቷል።

ምዕራፍ ዘጠኝ

ሥነ ልቡና (Psychology)

ሥነልቡና በታሪኩ ውስጥ የተለያየ ትርጓሜ ይዞ የመጣ ሲሆን አሁን በደረሰበት የዕድገት ደረጃ ግን አብዛኞቹ ተመራማሪዎች የሚስማሙበት ትርጉም ይህን ይመስላል። ሳይኮሎጂ ከሁለት የግሪክ ቃላት ሳይኪ እና ሎጎስ (Psyche & logos) የሚሉ ቃላቶች የተወሰደ ነው። (Psych) ሳይኪ | Mind (ነፍስ - አዕምሮ - መንፈስ) ሲሆን (Logos) ሎጎስ | Disclosure (ገለፃ /ጥናት) ማለት ነዉ። በዚህም መሰረት ሥነልቡና ማለት፡- ስለ ባህሪይ እና የአዕምሮ አሰራር ሂደት የሚያጠና ሳይንስ ነው። ባህሪይ ስንል ማናቸውም የምናረጋቸዉና በአይን የሚታዩ ነገሮች ሲሆኑ የአዕምሮ አሰራር ሂደት ደግሞ በአይን የማይታይ ግን በተግባር የሚገለፅ ነዉ።

ሳይንስ ስንል ሳይንስ የሚያልፍባቸውን ሂደቶች ስለሚያልፍ ነዉ እነርሱም (**Emperica**l / በሙከራ የተረጋገጠና መመልከት የምንችለው) (**Objective** / ከግል ስሜት ጋር ያልተያያዘና ከገሀዱ አለም ጋር የተገናኘ) (**Systematic** / በስርአት የተቀረፀና የሚሰራ) (Replicable / ውጤቱ ሆነ ሂደቱ በሌላ ሰው መደገም የሚችል) ናቸው። ሌላው ሥነልቡና ማህበራዊ ወይስ ተፈጥሮአዊ ሳይንስ ነው የሚለው ጥያቄ ነው። ምንም እንኳን ባለንበት ሀገር ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም የትምህርት ተቋም እንደማህበራዊ ሳይንስ የሚታይና የሚሰጥ ሲሆን ባብዛኞቹ ባደጉት ሀገራት ግን ከህክምና ትምህርት ክፍል ስር የሚሰጥ በተፈጥሮአዊ ሳይንስ ስር ያለ ትምህርት ነው። ሥነ ልቡና አዕምሮን አያጠናም ይልቁንስ ስለ አዕምሮ አሰራር ሂደት እንጂ። (ስለአዕምሮ የሚያጠኑት ኒውሮሎጂስት እና ሳይካትሪስቶች ናቸዉ።)

<u>የሥነልቦና ትምህርት ዋና አላማ / ግብ (goal) አራት ናቸው እነርሱም ፡-</u>

1. ባህሪን መግለፅ (Describe)
2. ባህሪን ማብራራት (Explain)
3. ባህሪን መተንበይ (predict)
4. ባህሪን መምራት /መቆጣጠር (control)

ሥነልቡና (Psychology) መገለጫ ምልክት (Symbol) ያለዉ ሲሆን ምልክቱ የግሪኩ 23ኛ ካፒታል ሊተር Ψ ሳይ (Psi) ነዉ። የ ሳይ ምልክት የተገለበጠ "ሐ" ይመስላል። በዚህ ምልክት ' Ψ ' ላይ ያሉት ሶስት አምዶች አንዳንድ የዘርፉ ተመራማሪዎች በነዚህ ሶስት ነገሮች ይመስሏቸዋል

1. ነፍስን (Soul)
2. ሀሳብን (Mind)
3. መንፈስን (Spirit)

1. <u>"የሳይኮሎጂ እውነታዎች"</u>

- ሴቶች አብዛኛውን ግዜ ጥያቄ ሲጠይቁ መልሱን እያወቁ ነው ስለዚህ ባትዋሻቸዉ የተሻለ ነው።
- ሴቶች ችግር ለመፍታት ሁለቱንም የጭንቅላታቸውን ክፍል ሲጠቀሙ ወንዶች ግን አንዱ ብቻ ነው የሚጠቀሙት።
- ሴቶች ካሉበት የድብርት ስሜት የሚያወጣቸውንና የሚያስቃቸው ወንድ ይወዳሉ።

- ድብርት ነገሮችን የማስታወስ ችሎታችን ላይ ተፅእኖ ያሳድራል።
- ሙዚቃ ማዳመጥ ጭንቀትን ይቀንሳል እና በሽታ የመከላከል አቅምን ይጨምራል።
- አብዛኞቹ ወንዶች ከ እናታቸው ባህሪ ጋር ተመሳሳይነት ያላትን ሴት ይፈልጋሉ።
- በጥናት እንደተረጋገጠው ሴቶች ሚስጥር መጠበቅ የሚችሉት ለ 47ሰአት ከ15 ደቂቃ ማለትም ለ 2ቀን ብቻ ነዉ።
- አብዛኞቹ ወንዶች እንደ አባታቸው መሆን ይፈልጋሉ ይለናል።
- ሴቶች አንድ ወንድ ከሌላ ሴት ጋር ሲናነፃፅራቸዉ አይወዱም ከእናትህ ጋር ራሱ።
- በሴቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚናገሩት ከሆነ አለማችን ካሉ ሴቶች 70% የሚሆኑት ህመማቸውን በዝምታ ነው ሚገልፁት።
- አብዛኞቹ ወንዶች ሲያፍሩ ወደቀኝ ወደግራ ያያሉ ቅንድባቸውን ና ግንባራቸውን ሲያኩ ሴቶች ደግሞ ወደታች ያያሉ ከጆሮአቸው በስተጀርባ ያለውን የፀጉር ክፍል ያስተካክላሉ።
- ሳይኮሎጂው እንደሚለን የሰው ልጅ ጆሮና አፍንጫ ማደግ አያቆምም ይለናል።
- ከራስችን ጋር ማውራት Smart ያደርገናል ይላሉ። የሳይኮሎጂስቶች
- የምቶደውን ሰው እጅ ከያዝክ ይህ አካላዊ ህመምን እንዲሁም ማንኛውንም የጭንቀት እና የፍርሃት ስሜትን ለማስታገስ ይረዳል።
- ከ18 እስከ 24 የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ወጣት ሴቶች አብዛኛውን ግዜ ጭንቀት ያጠቃቸዋል።
- ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴቶች በአንዴ ብዙ ነገሮችን በመስራት (multitasking) ላይ ከ ወንዶች የተሻሉ ናቸዉ።
- ሴቶች የሰወችን ፊት በማስታወስ ከወንዶች የተሻሉ ናቸው ይለናል። ሳይኮሎጂው
- ሴቶች ከወንዶች አንፃር ጭንቀታምና ፈሪ ናቸው።
- ለመዋሸት በጣም አስቸጋሪ ስሜቶች ሀዘን እና ቁጣ ናቸው።
- አንድን ነገር ለ21 ቀን በተመሳሳይ ሰአት ካደረግን ያ ያደረገንነዉ ነገር ልማድ ይሆናል ለ91 ቀን ካደረግንነው ደግም ቋሚ ልማድ ይሆናል ይሉናል። ሳይኮሎጂስቶች
- በጥናት እንደተረጋገጠው ግባችንን ለሌሎች መንገር ተነሳሽነትን ያስጣል ያ ደግሞ ግባችንን የማሳካት አቅማችንን ይቀንሳል።
- ወረኛ ሴትና ጭምት ወንድ አንድ ላይ ቢሆኑ ምርጥ ባልና ሚስት ይሆናሉ ይለናል። ሳይኮሎጂው
- ከሴት ይልቅ ብዙ የወንድ ጓደኛ ያላት ሴት ልጅ ደስተኛ የጤነኛና ረጅም እድሜ ትኖራለች ይላሉ። ሳይኮሎጂስቶች
- አንድ ሴት ከአንድ ወንድ ጋር ሆና ከሳቀች እነሱን የምታይ ሌላ ሴት ልጁ ማራኪ እንደሆነ ታስባለች ይለናል። ሳይኮሎጂው
- ሳይኮሎጂስቶች እንደሚሉት የተማርነውን ነገር ደጋግመን ካለየዉ አእምሮአችን በፍጥነት ይረሳል ይላሉ።
- ሴቶች ከወንዶች በተሻለ ስሜትን መረዳት እና ማንበብ ይችላሉ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ እነሱ ራሳቸው ለስሜታዊነት የተጋለጡ ናቸው።
- ሴቶች ለከፍተኛ የስሜት መለዋወጥ በጣም የተጋለጡ ናቸው፣ሴቶች አዘውትረው ከሚያናግሯቸው ሰዎች ይልቅ እነርሱን ችላ ለሚሏቸው የበለጠ ያስባሉ ይሉናል። ሳይኮሎጂስቶች
- ወንዶች ብዙ ጊዜ እርዳታ መጠየቅን ይጠላሉ እና ምንም አይነት እርዳታን በራሳቸው ማድረግ እንደማይችሉ እስኪሰማቸው ድረስ ከመናገር ይቆጠባሉ።
- ወንዶች ውድቅነትን ይፈራሉ ትኩረት ና ፍቅርን ይፈልጋሉ እና ፍጹምነትን ያልማሉ።
- ሴቶች ውሸት በጣም ይጠላሉ ግልፅ የሚሆንላቸውን ወንድ ይወዳሉ።
- የምንሰማው የሙዚቃ አይነት አለምን የምንመለከትበት መንገድ ላይ ተጽእኖ ያሳድራል።

- ሙዚቃ የጠፉ ትውስታዎችን ለመመለስ ይረዳል ይላሉ። ሳይኮሎጂስቶች
- ስፖርት እየሰሩ መዚቃ ማዳመጥ ከፍተኛ ተነሳሽነት ያመጣል፤ እንዲሁም እሩጫ እየሮጡ ከሆነ ደግሞ እንዲፈጥኑ ያደርጋል።
- በጥናት እንደተረጋገጠው በቀን ከ 5 እስከ 10 ዘፈኖችን ማዳመጥ የማስታወስ ችሎታን ያሻሽላል, በሽታ የመከላከል አቅምን ያጠናክራል እና ጭንቀትን በ 80% ይቀንሳል።
- አራት ሰወች ቢኖሩ ና 3ቱ ቢስቁ አራተኛው ግን ሳይገባው ይስቃል።
- አሳ መመገብ የደም መርጋት የደም ግፊት አልዛይመር ወይም የምርሳት በሽታን ሲከላከል የልብ ጤንነት የተጠበቀ ያደርጋል።
- አብዛኞቹ ወንዶች ዶክተር ጋር ሄዶ መታየት ይጠላሉ ብዙግዜም ችላ ይላሉ።
- ስንወለድ በህፃንነታችን ሰውነታችን 300 አጥንት አለዉ ግን ጎረምሳ ልጆች 260 አጥንት ብቻ ነዉ ያላቸው።
- ፍቅር አካላዊ ጤንነትን ያሻሽላል።
- የሚወዱትን ሰው ምስል ማየት የጭንቀትና የህመም ስሜትን ይቀንሳል እና ከተጎዱ ወይም ከታመሙ በፍጥነት እንዲድኑ ይረዳዎታል።
- ብዙውን ጊዜ አንድ የምኖደውን ሰው ማጣት እንቅልፍ ማጣት ሊያስከትል ይችላል።
- የሰው ልጅ እንቅልፍ ለ 11 ቀን ካልተኛ ይሞታል።
- ጥናት ካጠናን ቦኋላ በቂ እንቅልፍ መተኛት ያነበብነው በአእምሮአችን ብዙ ግዜ እንዲቆይ ቶሎ እንዳይረሳ ያደርጋል።
- ወንዶች ከሴቶች ሁለት እጥፍ ይዋሻሉ ይሉናል። በሳይኮሎጂስቶች
- በጥናት ግዜ በቂ ውሀ መጠጣት ያስፈልጋል አለበለዚያ አእምሯችንን እያስጨነቅን ነዉ።
- ብዙ ግዜ የRap ሙዚቃ የሚሰሙ ሰወች ንዴታም ይሆናሉ።
- ጥናት ስናጠና ማሲቲካ ማኘክ “focus” ወይም ጥናታችን ላይ ትኩረት እንድናደርግ ይረዳናል።
- በሳይኮሎጂ "research" እንደተረጋገጠው እሁድ ቀን ከምሽቱ 7:26 ላይ ሰወች ደስተኛ ይሆናሉ ይሉናል። ሳይኮሎጂስቶች (የስነልቦና ባለሙያዎች)
- በአማካኝ ሰው በቀን 4 ውሸት፣ በአመት 1460 እና እስከ 60 አመቱ በአጠቃላይ 87,600 ውሸቶችን ይናገራል።
- ከ10 ሰአታት በላይ አዘውትረው የሚተኙ ሰዎች ለልብ ህመም፣ ለስትሮክ፣ ለአይነት 2 የስኪር ህመም እና ለድብርት የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ ነው።
- ሴቶች ከባሎቻቸው በላይ በጣም ለሚቀርብዋቸው ጓደኛ ሚስጥር ይነግራሉ ይለናል። ሳይኮሎጂው
- ንዴት ለረጅም ጊዜ በልብ ድካም እና በስትሮክ የመያዝ እድልን ይጨምራል እናም በሽታ የመከላከል ስርዓትን ያዳክማል።
- የስሜት መጎዳት ከአካላዊ ህመም ይልቅ በጣም ያማ።
- ለራሳቸው ዝቅተኛ ግምት ያላቸው ሰዎች ሌሎችን የመተቸት ዕድላቸው ከፍተኛ ነው።
- የውፍረት መቀነሻ መድሀኒት ተጠቅመን ውፍረታችን ሲቀንስ መደሀኒቱን የምናቆም ከሆነ ከበፊቱ በላይ እኖፍራለን።
- ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከሰወች ጋር ያለን ጥሩ ግንኙነት ከአካል ብቃት እንቅስቃሴ በላይ ለረጅም ጊዜ ህይወት ይጠቅማል።
- ከሰው ልጅ ዉጪ የሚስቁ እንስሳት ውሻና ድመት ናቸው።
- ንዴትን ለመቆጣጠር ችግር ከተፈጠረበት አከባቢ ወይም ሰዎች ዞር ማለት ለማብረድ ይረዳናል በተጨማሪም ውሃ መጠጣት ና አየር መቀበል ጠቃሚ ነዉ።
- የረሳነውን እቃ ለማስታወስ አይናችንን ጨፍኖ ማሰብ በቶሎ ለማስታወስ ይረዳናል።
- ጉንጅን የሚያጠነንክር Sport መስራት የልብ ና የስትሮክ ህመምን ይከላከላል ለአዛውንቶች ሂወትን ያረዝማል በ46% የልብ በሽታን ይቀንሳል።

- አእምሮአችን አንድ ነገር ላይ “focus” ወይም ማተኮር የሚችለው ለ25 ና ለ 30 ደቂቃ ነው ነገርግን ከትንሽ ግዜ እረፍት ቦኋላ ቶሎ ተመልሶ ይነቃቃል።
- ብዙ ሰአት የሚያነብ ተማሪዎች ያነበብትን ያክል ውጤት የማያገኙት ለዚህ ነው 3 4 5 ሰአት ቁጭ ብሎ ማንበብ አይጠቅምም የአእምሮን አወቃቀር ማወቅ አለብን።
- በጥናት ላይ በተደረገ የሳይኮሎጂ research ማታ ከማጥናት ይልቅ ጠዋት ላይ ማጥናት የተሻለ ነው የይህም የሆነው አእምሮአችን ቀን በስራ ወይም በትምህርት ነክ ነገሮች ስለሚወጠር ማታ ላይ ቀጥታ እረፍት ነዉ ሚፈልገው።
- ጠዋት ደግሞ አእምሮአች ከበቂ የእንቅልፍ እረፍት ቦኋላ ስለሚነሳ ነገሮች ለመያዝ ለመረዳት ለመስራት ፈጣን ይሆናል።
- እንደ ደስተኛ አክት የምታደርግ ከሆነ ሰወች ከ አንተ ጋር መሆን ይፈልጋሉ ሰወች ደስተኛ ሰወችን ይወዳሉ ምክንያቱም እነርሱ እንደአንተ ደስተኛ መሆን ስለሚፈልጉ።

ምዕራፍ አስር

ጥያቄ እና መልስ

1. ስለ ሕዝብ ቆጠራ የሚያጠና ሣይንስ ምን ይባላል? ⇨ **Census**
2. የዝሆን ልጅ ምን ይባላል? ⇨ **አልሞሌ**
3. በ አዲስ አበባ የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ማን ይባላል? ⇨ **ቀራንዮ መድሀኒዓለም**
4. ለጀርመን "nazi" ካልን ለጣልያን ምን? ⇨ **Facist**
5. በአለም ላይ ብዙ ወንዶች የሚጠሩበት ስም ምን ይባላል? ⇨ **መሐሙድ**
6. የአለማችን የመጅመሪያው ህገ መንግሥት ምን ይባላል? ⇨ **Magna Carta (እንግሊዝ)**
7. የአይሮፕላን አደጋ መመዝገቢያ ክፍል ምን ይባላል? ⇨ **Black box**
8. ለሽቶ ለመቀመሚያ የሚያገለግለው ዝባድ የተባለውን ፈሳሽ የምታመነጭ እንስሳ ማናት? ⇨ **ጥርኝ**
9. ዝምብ ምግብ የምትመገብበት ክፍል ምን ይባላል? ⇨ **Probosis**
10. በህይወት እያለን የምንሞትበት ቅፅበት መቼ ነው? ⇨ **በምናስነጥስበት ወቅት ለዛም ነው ይማርህ/ሽ የምንባባለው**
11. ለእግር ኪስ ኮሚሽነር ካልን ለቦክስ ምን እንላለን? ⇨ **ጁሪ**
12. የአለማችን ሐይማኖታዊ ከተማ ማን ነች? ⇨ **እየሩሳሌም (እስራኤል)**
13. ወተት ሲቆመጥጥ የሚወጣ አሲድ ምን ይባላል? ⇨ **Lactic acid**
14. የግሪክ የፍቅር አማልክት ምን ይባላል? ⇨ **Aphrodite**
15. የአፄ ቴዎድሮስ ታማኝ ወታደር ማን ይባላል? ⇨**ገብርዬ**
16. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሆቴል ማን ይባላል? ⇨ **እቴጌ ጣይቱ ሆቴል**
17. አዲስ አበባ መች ተቆረቆረች? ⇨ **በህዳር 1867**
18. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሆስፒታል ማን ይባላል? ⇨ **ዳግማዊ ምኒልክ በ1902**
19. አፄ ዮሐንስ የት ሞተ? ⇨ **መተማ በ1881**
20. የአፄ ሐይለ ሰላሴ የትውልድ ቦታ የት ነው? ⇨ **ሐረርጌ ኤጀርሣ**
21. የአፄ ምኒልክ የመጀመሪያ ሚስት ማብ ይባላሉ? ⇨ **ወ/ሮ ባፈና**
22. የአፄ ሐይለ ሰላሴ ውሻ ማን ትባላለች? ⇨ **ሉሉ**
23. የህንድ የመገበያያ ገንዘብ ምን ይባላል? ⇨ **ሩፒ**
24. የእንቁላል ማስፈልፈያ መሳሪያ ምን ይባላል? ⇨ **ኢንኩቤተር**
25. የአይነስውራን መፃፊያ ምን ይባላል? ⇨ **ብሬል**
26. ለህንድ ቦሊውድ ካልን ለናይጀሪያ ምን እንላለን? ⇨ **ኖሊውድ**
27. ከምግብ አይነቶች የማይበላሸው የቱ ነው? ⇨ **ማር**
28. አሣ ሲተኛ አይኑን አይከድንም ለምን? ⇨ **የአይን ቆብ ስለሌለው**
29. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ማነው? ⇨ **ደብረ ዳሞ**
30. የኮምፒዩተር ሶፍትዌር ፈጣሪ ማን ይባላል? ⇨ **ቢል ጌት**
31. አትላንቲክ እና ህንድ ውቅያኖስ የት ይገናኛሉ? ⇨ **ደቡብ አፍሪካ (cape of good hope)**
32. በአሜሪካ የተገኘች አፍሪካዊ ሀገር ማናት? ⇨ **ላይቤሪያ**
33. ጳጉሜ 6 የምትሆነው በምን ምክንያት ነው? ⇨ **365 1/4*4=1 365+1=366**
34. ከውልደት እስከ ህልፈተ ህይወት እድገቱን የማያቆም የሰውነት ክፍላችን ምንድነው? ⇨ **ፀጉር እና ጥፍር**
35. ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያላት ከተማ ማናት? ⇨ **ሜክሲኮ ሲቲ**

36. በወረቀት ገንዘብ መገበያየት የጀመረች ሐገር ማነች? ⇨ **ቻይና**
37. በሀገራችን በረኪና የሚባለው ወንዝ የት ይገኛል? ⇨ **ወሎ**
38. የአለማችን ትንሿ ሉዐላዊ ሀገር ማናት? ⇨ **ቫቲካን**
39. ሴቶችን በግዳጅ ወደ ውትድርና የምታሰልፍ ሀገር ማናት? ⇨ **እስራኤል**
40. በአለም ላይ አንድ አዋሳኝ ሀገር ያላት ብቸኛ ሀገር ማናት? ⇨ **ሌሴቶ**
41. ፍፁም ዘውዳዊ ወይም ንጉሣዊ አገዛዝ ያለባት አፍሪካዊ ሀገር ማናት? ⇨ **ስዋዚላንድ**
42. ወንዶች "deodorant" በብዛት የሚጠቀሙባት ሀገር ማናት? ⇨ **ጃፓን**
43. "The rainbow nation" ወይም የቀስተ ደመና ሀገር የምትባለው ማናት? ⇨ **ደቡብ አፍሪካ**
44. የአፄ ዮሐንስ የፈረስ ስም ማን ይባላል? ⇨ **በዝብዝ**
45. የአፄ ምኒልክ የፈረስ ስም ማን ይባላል? ⇨ **አባ ዳኛው**
46. ለመጀመርያ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የገባው የጭነት መኪና ምን ይባላል? ⇨ **ትሬንታ ኪትሮ (ጣሊያን)**
47. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባንክ ቤት ምን ይባላል? ⇨ **አቢሲኒያ ባንክ (1905)**
48. የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ ሴት ጋዜጠኛ ማን ትባላለች? ⇨ **ሮማንወርቅ ካሳሁን፣ ሀሊና ፈጠነ፣ አስገደች**
49. ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የቀረቡ ቲያትሮች ምን ምን ናቸው? ⇨ **ፋጉላ እና አፋጀሽኝ**
50. የአፄ ምኒልክ ሚስት ማን ትባላለች? ⇨ **እቴጌ ጣይቱ**
51. ልጅ እያሱ የት ሞተ? ⇨ **ገራ ሙለታ በ1936EC**
52. የኢትዮ ኤርትራ ስምምነት የት ተካሄደ? ⇨ **አልጀሪያ**
53. አፄ ቴዎድሮስ የት ነገሰ? ⇨ **ደራስጌ ማርያም**
54. የአፄ ቴወድሮስ ታማኝ ወታደር? ⇨ **ገብርዬ**
55. አፄ ምኒልክ መች ሞተ? ⇨ **በታህሳስ 1905**
56. አዲስ አበባ መች ተቆረቆረች? ⇨ **1867 በእቴጌ ጣይቱ**
57. የኢትዮ ጅቡቲ የምድር ባቡር መች ተከፈተ? ⇨ **1908 እ.ኤ.አ**
58. የምኒልክ ሚስት ማን ይባላሉ? ⇨ **እቴጌ ጣይቱ**
59. የምኒልክ ልጅ ማን ይባላሉ? ⇨ **ሸዋረገድ እና ዘውዲቱ**
60. የልጅ እያሱ ሞግዚት ማን ይባላል? ⇨ **ራስ ተሰማ ናደው**
61. ልጅ እያሱ የማን ልጅ ነው? ⇨ **የንጉሥ ሚካኤል (መሐመድ አሊ)**
62. የኢትዮጵያን ፊደል እና ቁጥር ንድፍ ማን አወጣው ⇨ **ቁጥሩን ሊቁ ዲሜጥሮስ**
63. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሲኒማ ቤት? ⇨ **ሰይጣን ቤት**
64. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ፋርማሲ ምን? ⇨ **ፋርማሲ ጆርጅያ (1904)**
65. የመጀመሪያዋ ኢትዮጵያዊ ሴት ጋዜጠኛ? ⇨ **ሮማን ወርቅ ካሣሁን**
66. ንጉስ ኢዛና ክርስትናን እንዲቀበል ያጠመቀው? ⇨ **ፍሪምናጦስ (አባሰላማ)**
67. መኪና የነዳ የመጀመሪያው አፍሪካዊ መሪ? ⇨ **አፄ ምኒልክ**
68. የመጀመሪያዋ አፍሪካዊ/ኢትዮጵያዊ ሴት አይሮፕላን አብራሪ? ⇨ **አሰገደች አሰፋ**
69. የመጀመሪያዋ እውቅና ያገኘች ሴት አፍሪካዊ መሪ (head of state)? ⇨ **ንግስት ዘውዲቱ**
70. አባቦራ በመባል የሚታወቀው ኢትዮጵያዊው ተዋጊ? ⇨ **ገረሱ ዱኪ**
71. የመጀመሪያው የኢትዮ ቴሌኮም ስራ አስኪያጅ? ⇨ **በትሩ አድማሱ**
72. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ባንክ ቤት? ⇨ **አቢሲኒያ ባንክ**
73. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሆስፒታል? ⇨ **ምኒልክ ሆስፒታል**
74. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሆቴል? ⇨ **ጣይቱ ሆቴል**
75. በሰውነታችን ውስጥ ስንት የጎድን አጥንቶች አሉ? ⇨ **12 ጥንድ የጎድን አጥንት**
76. ሽበት በምን እጥረት ይከሰታል? ⇨ **በ" melanin" እጥረት**
77. አጥንት ከአጥንት በምን ይያያዛል? ⇨ **"Ligament"**

78. አጥንት ከጡንቻ በምን ይያያዛል? ⇨ **"Tendon"**
79. ለማሽተት የሚጠቅመን ኢንዛይም ምን ይባላል? ⇨ **Olfactory nerve**
80. የአዮዲን እጥረት ምን ያስከትላል? ⇨ **እንቅርት (goiter)**
81. ቀይ ሽንኩርት ስንከትፍ የሚያስለቅሰን ነገር ምን ይባላል? ⇨ **"Sulfuric acid"**
82. ጉንዳን የሰውን ልጅ ሲነክስ የሚወጣው አሲድ ምን ይባላል? ⇨ **"Formic acid"**
83. ጡንቻችን እንዲሸማቀቅ (ስትራፖ እንዲይዘን) የሚያደርገን አሲድ ምን ይባላል? ⇨ **"Lactic acid"**
84. ወንድ ልጅ ምን ያህል "X" chromosome አለው? ⇨ **አንድ X chromosome አለው ወንድ፡ XY chromosome ሴት፡ XX chromosome**
85. እሣት ከምን ይሰራል? ⇨ **oxygen+fuel+heat ከነዚህም ውስጥ አንዱ ከጎደለ እሣት አይፈጠርም።**
86. ቀረቀበ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው? ⇨ **ጠገበ**
87. ልትወልድ የደረሰች ነፍሰጡር ሴት ምን ትባላለች? ⇨ **ድረስ፣ ወረግቡ**
88. ሶስት ጉልቻ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው? ⇨ **ጋብቻ፣ ትዳር**
89. መዳፍ ለሚለው ቃል ተቃራኒ ቃል ምንድነው? ⇨ **አይበሉባ**
90. አንድ ሰው ወጡን ቅቤ ነሰረው ብሎ ቢናገር ምን ለማለት ፈልጎ ነው? ⇨ **ቅቤ በዛበት ማለቱ ነው።**
91. ጥራዝ ነጠቅ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው ? ⇨ **ያልተማረ**
92. ረጋ ሰራሽ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው? ⇨ **የማያምር ስራ**
93. ዋንጫ ልቅለቃ ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው? ⇨ **የአንገት እስክስታ**
94. ኩታ ገጠም ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው ? ⇨ **ድንበርተኛ**
95. ምራቀ ደንዳና ለሚለው ቃል ተመሳሳይ ቃል ምንድነው? ⇨ **ብዙ የማይበላ**
96. VAT ወይም ተጨማሪ እሴት ታክስን ያስተዋወቀች ሃገር ማናት? ⇨ **ፈረንሳይ**
97. ከ 6-12 ወራት ምግብ ሣትመገብ መቆየት የምትችል እንስሳ ምን ትባላለች? ⇨ **ጊንጥ**
98. ቀን እና ለሊት እኩል የሚሆኑት መች ነው? ⇨ **ፀሃይ የምድር ወገብ ወይም "equator" ላይ ስትሆን**
99. ጅብ የሚስቀው ለምንድነው? ⇨ **ለጓደኞቹ ምግብ ማግኘቱን ሲናገር**
100. ጡረታን ያስተዋወቀች ሀገር ማናት? ⇨ **ጀርመን**
101. የጣሊያኖቹ ኢንተር ሚላን እና ኤሲ ሚላን የእግር ኳስ ክለቦች በጋራ የሚጠቀሙበት ሜዳ ምን ይባላል? ⇨ **ጄሴፔ ሣንሲሮ**
102. ታይታኒክ መርከብ ከየት ወደ የት በመጓዝ ላይ እያለች ነው የሰጠመችው? ⇨ **ከእንግሊዝ ሣውዝሃምፕተን ወደ አሜሪካ ኒውዮርክ**
103. በዓለም ላይ ትልቁ ደሴት የት ነው? ⇨ **ግሪንላንድ**
104. ሙት ባህር በየትኞቹ ሁለት አገሮች መካከል ይገኛል? ⇨ **እስራኤል እና ዮርዳኖስ**
105. በረሃ የሌለበት በአለም ላይ ብቸኛዋ አህጉር ማናት? ⇨ **አውሮፓ**
106. በዓለም ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሙስሊም ያለው ሀገር የት ነው? ⇨ **ኢንዶኔዥያ**
107. ዘመናዊ የባንክ ኖት በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በየትኛው ሀገር ነው? ⇨ **ስዊድን**
108. ሴቶች እንዲመርጡ የፈቀደች የመጀመሪያዋ ሀገር? ⇨ **ኒውዚላንድ**
109. በኦሎምፒክ ምልክት ውስጥ ስንት ቀለበቶች አሉ? ⇨ **አምስት**
110. በ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ክርስትናን ለመጀመሪያ ጊዜ የተቀበሉት የኢትዮጵያ ነገሥታት ማንና ማን ናቸው? ⇨ **አብርሃ እና አፅብሐ**
111. ጌታ ሲወለድ የነበሩት የእስራኤልና የኢትዮጵያ ነገሥታት እነማን ነበሩ? ⇨ **ሄሮድስ እና ንጉስ ባዚን**
112. በአፍሪካ ቀዳሚ የሞባይል ስልክ ተጠቃሚ ሃገር ማናት? ⇨ **ኮንጎ**

113. የሰንደቅ አላማ ወይም ባንዲራ መስቀያ ብረት ጫፍ ላይ ያለው 3 ማእዘን ቅርፅ ምን ይባላል? ⇨ **ልሣነ ሰንደቅ**

114. ሁሉም ፕላኔቶች ከምስራቅ ወደ ምእራብ ሲዞሩ ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ ማለትም ከምእራብ ወደ ምስራቅ የምትዞር ፕላኔት ማነች? ⇨ **ፕሉቶ**

115. በአለም ላይ ብዙ ሰዎች የሚጠሩበት የወንድ ስም ማን ይባላል? ⇨ **መሐሙድ**

116. መቀስን የፈለሰፈው ወይም ያገኘው ማነው? ⇨ **ሊዮናርዶ ዳቪንቺ**

117. እርጥብ ልጅ ለሚለው አማርኛ ቃል አቻ ፍቺ ምንድነው? ⇨ **ገና የተወለደ አራስ ልጅ**


118. የእስልምና ሐይማኖትን ወደ ሐገሯ በመቀበል ቀዳሚ የሆናች አፍሪካዊ ሀገር ማናት? ⇨ **ኢትዮጵያ**


119. በእስልምና ትምህርት አስተምሮ ሦስቱ ቅዱሳን ቦታዎች እነማን ናቸው? ⇨ **መካ፣ መዲና እና እየሩሳሌም**



Scan Me Please


ሳይንስኛ
ይህም አለ?
አንተነህ ጌታቸው
2017 ዓ.ም


ሳ
Science Dictionary
Physicist Antenah Getachew
2017 E.C


የእውቀት
መንገድ
አንተነህ ጌታቸው
2014 ዓ.ም